# የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፨

## ከፀሄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ፀሄ ፡ ቴዎድሮስ ።


ተጻፈ ፡

ከተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኩሪያ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ
በ፳ኛ ፡ ዘጠኝኛው ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ መስከረም ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ· ም.

ትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ።



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።



ግርማዊት እቴጌ መነን ።

## መቅድምና ፡ መግቢያ ።

በዚህ ፡ መቅድምና ፡ መግቢያ ፡ ውስጥ ።

፩ኛ ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ካለው ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በኢ
ትዮጵያ ፡ አጻጻፍ ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፡ የቀድሞ ፡ አጻጻፍ ፡ በሚል ፡ አርእስት ።

፪ኛ ፡ በያይነቱ ፡ የተጻፉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡
፡ መውጣታቸው ።

፫ኛ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ጻፉ ።

፬ኛ ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እነዚህን ፡ አራት ፡
፡ የተከፈሉትን ፡ ጠቅላላ ፡ አሳቦች ፡ በየተራ ፡ ለማስረዳት ፡ እፈልጋለሁ ።

## ፩ኛ ፡ የቀድሞ ፡ አጻጻፍ ።

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ የተጻፉት ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ወይም ፡ ነገደ ፡
ዓዝያን ፡ የምንላቸው ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ገብተው ፡
መጡ ፡ ግዕዝ ፡ ቲግረ ፡ ትግርኛ ፡ አማርኛ ፡ በየነገዳቸው ፡ ቋንቋ ፡ ይነጋገሩ ፡
ደ ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ ተቀያይጦ ፡ የተፈጠረ ፡ ፩ ፡ ሳባዊ ፡ ቋንቋ ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡
ሁ ፡ ይናገሩም ፡ ይጽፉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም ። ስለ ፡ ጉዟ
ው ፡ ስላሰፋፈራቸው ፡ ስለ ፡ ነገዳቸው ፡ ቍጥርና ፡ ዐይነት ፡ ብዛትና ማነስ ፡ ምናል
፡ ያለቃ ፡ ታዬ ፡ መጽሐፍ ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ እንደሚያስረዳ ፡ ስለ ፡ ቋንቋቸ
ም ፡ በትክክል ፡ የሚያውቅ ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ።

አሁን ፡ ግን ፡ ለማስረዳት ፡ የምሞክረው ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መንግሥት ፡
ት ፡ በአኵስምና ፡ በላስታ ፡ በሸዋም ፡ መንግሥት ፡ ተያይዞ ፡ በመጣው ፡ ዐይነት ፡ ይል
ም ፡ ያሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ በተጻፈበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥ
፡ አጻጻፍ ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ ለመጻፍ ፡ ስፈልግ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የታወሰኝን ፡ ለኛ ፡
ር ፡ አጻጻፍ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነውን ፡ የሮማውያንን ፡ የላቲን ፡ ቋንቋ ፡ እጠቅሳለሁ ።

ሮማውያን ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ ዠምረው ፡ የደቡብ ፡ ኤው
ፓ ፡ ቋንቋ ፡ እስከ ፡ ተፈጠረ ፡ ድረስ ፡ ሲገዙ ፡ የዚያ ፡ ጊዜ ፡ ቋንቋቸው ፡ ላቲን ፡ እንደ ፡
ረ ፡ ሥልጣኔያቸውም ፡ ከታወቀው ፡ ከግሪክ ፡ ሥልጣኔ ፡ የተወራረሰ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ቶዎቻችን ፡ እናውቃለን ። ስለዚህ ፡ ሮማውያን ፡ ዓለምን ፡ ወደ ፡ መግዛት ፡ ደረጃ ፡ ወጥ
ው ፡ በኋላም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ መገዛት ፡ ደረጃ ፡ እስኪወርዱ ፡ ድረስ ፡ የጦር ፡ አለቆቹ
ቡር ፡ የሚናገሩበት ፡ አስተዳዳሪዎቹ ፡ ትእዛዛቸውን ፡ በዋጅና ፡ በመልክት ፡ የሚያስ
ልፉበት ፡ መምህራኑ ፡ የሚያስተምሩበት ፡ ቋንቋ ፡ ላቲን ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አን
ድ ፡ ጊዜ ፡ ጲላጦስ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ የሚገዙት ፡ አገር ፡ የራሱ ፡ ነው ፡
ሊለው ፡ በብዙ ፡ ቋንቋ ፡ መተርጐሙና ፡ መነገሩ ፡ ባይቀር ፡ ተገዥዎቹ ፡ የአፍሪካና ፡ የም
ራቅ ፡ አንዳንዶቹም ፡ ያውሮፓ ፡ ሕዝቦች ፡ ቀጥተኛውንና ፡ ዋነኛውን ፡ የላቲን ፡ ቋንቋ ፡
ገባቡ ፡ ባለማወቅ ፡ ይቸገሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እዚህም ፡ ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የበላይ ፡
ተዳዳሪዎቹ ፡ ሊቃውንቱ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ ያደባባይ ፡ መነጋገሪያው ፡
ግርኛ ፡ ቢሆን ፡ የመንፈሳዊው ፡ መጻሕፍትና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ መልክቱም ፡ ዐዋ
ጁ ፡ የሚነገረው ፡ ከተነገረም ፡ በኋላ ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ ቀሪ ፡ እንዲሆን ፡ የሚጻ

ፈው ፡ በግዕዝ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ባማርኛ ፡ መጻፍ ፡ ቢጀመርም ፡ ቅሉ ፡ ያማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ የማያውቀው ፡ የጋላ፡የጉራጌ ፡ ያዳል ፡ የሱማሌ ፡ ሕዝብ፡እስከ፡ ዛሬም ፡ እንደሚቸገር ፡ የግዕዙን ፡ ቋንቋና ፡ ሰዋስዉንም ፡ የማያውቀው ፡ ያማራውና ፡ የትግሬው ፡ ሕዝብ፡ሳይቀር ፡ ይበልጥ ፡ ይቸገርበት ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ አሁን ፡ የተነሣንበትን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ታሪክ ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓቶች ፡ አዛዦች ፤ ጸሐፍት ፡ ትእዛዞች ፡ ሲጽፉ፡ የጻድቃንንና ፡ የሰማዕታቱን፡ ገድልና ፡ ድርሳን ፡ ደግሞ ፡ ጳጳሶቹ ፡ እጨጌዎቹ ፡ አበ ፡ ምኔቶቹ ፡ መነኰሳቱ ፡ ራሳቸው ፡ ሲጽፉ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ቋንቋ፡ከዕብራይጥ ፡ ከዐረብ ፡ ከግሪክ፡እየተረጐሙ ፡ ሲገለብጡ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ፡ጽሕፈታቸው ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር። ስለዚህ ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ምሥጢራዊነት ፡ ቅዱስነት ፡ ተከባሪነት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ በተናጋሪውም ፡ በሰሚውም ፡ ዘንድ፡ ያስገምት ፡ ነበር ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ የላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ለኢጣሊያዎች ፡ ለፈረንሳዊና ፡ ለኤስፓኞች ፡ የሚሰጠው ፡ የኵራትና ፡ ያዋቂነት ፡ ስሜት ፡ የግዕዙም ፡ ቋንቋ ፡ እንደዚሁ ፡ ለሚያውቀው ፡ ወገን ፡ የሚሰጠው ፡ የኵራት ፡ ስሜት ፡ በዚያው ፡ ዐይነት ፡ እስከ ፡ ዛሬ፡ እንደ ፡ ቀጠለ ፡ ነው ።

የቀድሞ ፡ መንፈሳውያን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወይም፡ አሁን፡የተነሣንበትን ፡ የነገሥታትን፡ ታሪክ ፡ የሚጽፉት ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዞች ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ ቁም ፡ ጸሐፊዎቻቸው ፡ የበግና ፡ የፍየል ፡ ቈዳ፡ፍቀው ፡ አለስልሰው ፡ ቈርጠው ፡ ከፍፈው ፡ ብራናውን ፡ በሸንበቆ ፡ ብርዕ ፡ ጽሕፈትን ፡ እንዲቀበል ፡ ያዘጋጁታል ፡ አዘጋጅተው ፡ ሲጨርሱም ፡ የንጉሡን፡ ታሪክ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ መጻፍ ፡ ይጀምራሉ ። ሲጀምሩም ፡ በሙብልም ፡ በሌላውም፡ የሥራ ፡ ዥመራ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያደርጉት፡ ‹በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ንዌጥን ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽሒፈ ፡ ዜናሁ ፡ ለእገሌ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ . . . . . . . . . . .› ብለው ፡ ይጀምራሉ ፡ በሚጽፉበትም ፡ ጊዜ፡የንጉሡን ፡ ታሪክ ንጉሡ ፡ ከሚወደው ፡ ሰማዕት ፤ ወይም ፡ መልአክ ፡ ጋራ ፡ እያነጣጠሩ ፡ እያቈላለፉ ፡ ይጽፉታል ። ራሱ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገን ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ አለቃ ፡ ስለ ፡ ሆነ፡ ሰዋስውና ፡ ቅኔ ፡ ከናገባቡ ፡ ያወቀ፤ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ የተማረ ፤ ገድልና ፡ ድርሳን ፡ ያነበበ፡በመሆኑ ፡ የጌታውን ፡ ንጉሥ፡ ታሪክ ፡ ከመንፈሳዊው፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ እያገናኘ ፡ ለመጻፍ፡ችግር ፡ አይሆንበትም ። እንደዚሁም ፡ መንፈሳውያኑ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያነዱን፡መልአክ ፡ ወይም ፡ ሰማዕት ፡ ገድልና ፡ ድርሳን ፡ ሲጽፉ ፡ በየምክንያቱ ፡ ከተጋጠመው ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ እየደረቡ ፡ ይጽፉታል ። ይኸውም ፡ የዐፄ፡ልብነ፡ ድንግል ፡ ታሪክ ፡ ከድርሳነ ፡ ኡራኤል ፡ ወይም ፡ ራጉኤል ፡ ጋራ ፡ በንድነት ፡ እንደሚጻፍ ፤ ከዚያም ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በተድባበ ፡ ማርያም ፤ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ በክብራን ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ገዳም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ የወዳጁ ፡ ታቦት ፡ አብሮ ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ እንደሚገኝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የዘመኑ ፡ ጸሓፊም ፡ በዘመኑ ፡ የነበረውን ፡ የንጉሡን፡ ታሪክ ፡ በሚጽፍበት ፡ ጊዜ፡ በማጋነን ፡ በማወደስ ፡ ልክ ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ ታቦቱ ፡ ገድልና ፡ ታምራት ፡ ያቀራርበዋል ። ስለ ፡ ራሱ ፡ ስለ ፡ ንጉሡ ፡ ሲጽፍ ፡ «አልቦ ፡ ዘይመስሎ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ወእምቅድሜሁ ፤ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የሚመስለው ፡ የለም» ፡ . . . ፡ ይላል ። ስለ ፡ [illegible] ፡ እምርጉቅ ተዘ

ርዉ ፡ ከመ ፡ ጢስ ፡ እምቅድመ፡ ገጸ፡ ነፋስ ፡ . . . ፡ ወጕዩ፡ ውስተ፡ አድባር ፤ ወይቤሎሙ፤ ለአድባር ፡ ደቁ፡ ላዕሌነ፡ ወከድኑነ፡ እምገጸ ፡ ንጉሥ ፡ እገሌ ፡ . . . ፡ ወይፈቅዱ ፡ ተኀጢሙ፡ ምድር ፡ በከመ ፡ ውኅጠቶሙ ፡ ለዳታን ፡ ወለአቤሮን ፤ . . . ፡ ጠላቶቹ ፡ በሩቅ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ጪስ ፡ ከነፋስ ፡ ፊት ፡ ፀኖ ፡ እንደሚጠፋ ፡ እነሱም ፡ በነው ፡ ጠፉ ፤ ወደ ፡ ተራ ራም ፡ ሸሽተው ፡ ለተራራዎቹ ፡ እንደዚህ ፡ አሏቸው ፡ እናንት ፡ ተራሮች ፡ በላያችን ፡ ውደቁና ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ደብቁን ፡ መሬትንም ፡ ተከፍተሽ ፡ እባክሽ ፡ እንደ ፡ ዳታ ንና ፡ እንደ ፡ አቤሮን ፡ ዋጪን ፡ አሏት ፡ ይላል ። . . .

ታሪከ ፡ ነገሥቱን ፡ ስናነብ ፡ እንደምንረዳው ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዙ ፡ እንደዚህ ፡ አድ ርጎ ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ፻፮ ፡ ቍጥር ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ። በራዕየ ፡ ዮሐንስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፤ ላይ ፡ ያነበብነውን ፡ እያስታወሰ ፡ በየጊዜው ፡ ወደሚፈጸመው ፡ ታሪክ ፡ እያመጣ ፡ ንጉሡ ፡ ከጋሎች ፡ ከፈላሾች ፡ ከላስቶች ፡ የተዋጋበትን ፡ ታሪክ ፡ ሲተርክ ፡ በየመካከሉ ፡ የንጉሡን ፡ ጠላቶች ፡ የተባሉት ፡ ያልተናገሩትን ፡ የፍርሃት ፡ ንግግር ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፡ እያስመሰለ ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ በማጋነንና ፡ በማድነቅ ፡ (በቃለ ፡ አጋኖ ፡ ወአንክሮ) ፡ የገዢግንነቱን ፡ የኀይሉን ፡ የሥልጣኑን ፡ በሌላ ፡ ፊት ፡ የደግነቱን ፡ የመ ሓሪነቱን፤ የጸሎቱን፤ የትሩፋቱን ፡ ታሪክ፡ በቤቱ፡ ወይም፡ በቤተ፡ መንግሥቱ ፡ ቀን፡ ቀን፡ ሲጽፍ ፡ ይውልና፡ ማታ ፡ ማታ፡ ከግብር ፡ በኋላ ፡ ወይም፡ ከጕዞ ፡ በደረበት ፡ ከተማ፡ ያነብለ ታል ። ንጉሡም ፡ ሰምቶ፡ እዚህ ፡ ላይ፡ አበጀኸ ፡ እዚህ፡ ላይ፡ አጠፋህ ፡ እዚህ፡ ላይ፡ አሳነ ስኸ፡ ጨምር፡ እዚህ፡ ላይ፡ አበዛኸ፡ ቀንስ፡ሳይለው፡አይቀርም፡ አንዳንድ፡ጊዜም፡ ጸሓፌ፡ ትእዛዙ፡ የጻፈውን፡ ሰምቶ፡ በሙሉ፡ ተቀብሎ፡ ያመሰግነዋል። ጽሑፉም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት፡ የተወደደ ፡ ሲሆን ፡ ሽልማት ፡ ሹመት ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ እልቅና ፡ የጸ ሓፌ ፡ ትእዛዝነት ፡ የጽራግ ፡ ማሰሬነት ፡ የዓቃቤ፡ ሰዓትነት፡ ሹመት ፡ ከንጉሡ፡ ለጸሓፌ፡ ትእዛዙ ፡ እንደሚሰጥ ፡ የታወቀና ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ እያንዳንዱ ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዝ ፡ የየራሱን፡ ንጉሥ፡ «ከርሱ፡በፊት ፡ አልተነሣም፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ እንደነርሱ ፡ ያለ ፡ አይነሣም ፡ ጠላቶቹም ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ በነኑ ፡ . . . እያለ ፡ በመጻፉ ፡ ዛሬ ፡ ያብዛኞቹ ፡ ነገሥታት፡ ታሪክ፡ ነገሥት፡ ይኸንኑ ፡ አንድ ፡ ዐይነት፡ አድናቆት፡ ከምስጋና፡ ጋራ ፡ የያዘ፡ በመሆኑ፡ የዛሬው፡ አንባቢና ፡ ጸሓፊ ፡ የቀደሞዎቹን፡ ነገሥታት ፡ ደረቅ ፡ ታሪካቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ ማስተካከል ፡ ማበላለጥ ፡ ማመዛዘን ፡ በሚፈልግበት ፡ ጊዜ፡ ግር ፡ ይለው፡ ይሆናል። ቢሆንም፡ ከደንብ፡ያለፈውን፡ምስጋና፡እየዘ ለሉ ፡ ሥራቸውን ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ መስፈርና ፡ ወደ ፡ ማመዛዘን ፡ የተሄደ ፡ እንደሆነ ፡ ማን ፡ ከማን ፡ እንደሚበልጥ፡ለመረዳት ፡ ብዙ፡የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ አይገኝም ። ብዙው ፡ ምስ ጋና ፡ በብዙ ፡ ሥራ ፡ በብዙው ፡ ሥራ ፡ በብዙ ፡ ምስጋና ፡ እርስ ፡ በርሱ፡ ተደጋግፎ ፡ ሳይ ገኝ ፡ የቀረውን ፡ ለመለየትና፡ ለመያዝ፡ ወይም፡ ለመጣል፡ ምንም፡ ያኸል ፡ አያስቸግርም ።

ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ቀድሞ ፡ በተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ የሚቸግረው ፡ አብዛኛው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ የተጻፈበት ፡ ጊዜና፡ የጸሓፊው፡ ስም ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ፡ ውስጥ ፡ በደንብ ፡ ሳይጻፍ ፡ በመቅረቱ ፡ ነው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ የሚታየው ፡ አበቅቴና ፡ በዚያ ፡ ዓመት ፡ በተራው ፡ የሚጠራው ፡ የወንጌላዊው ፡ ስም ፡ ንጉሡ ፡ በዘ መኑ ፡ ባደረገው ፡ ጦርነትና፡ ጕዞ፡ ያደባባይ ፡ ፍርድ ፡ ወይም፡ የከተማ፡ ቍርቈራና፡ የቤተ፡

ክርስቲያን ፡ አተካከል፡ ውስጥ ፡ በዘመነ ፡ ማርቆስ፡ በዘመነ፡ ሉቃስ ፡ . . . ፡ እያለፈ፡ተጽፎ፡ ሲገኝ ፡ ለዛሬ፡ ጊዜ ፡ ያበቅቴውና፡ የወንጌላዊው፡ ስም ፡ አገልግሎቱ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ በመሆኑ፡ ወሩና ፡ ቀኑም ፡ በትክክል ፡ ተጽፎ ፡ ቢገኝ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ ሳይጻፍ ፡ በመቅረቱ ፡ የተጠቀሰው ፡ ወርና ፡ ቀን ፡ የማንኛው ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መሆኑን ፡ ለመለየት ፡ ይኸና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ የዚያ ፡ ጊዜ ፡ ያጻጻፍ ፡ ደንብ ፡ ለዛሬ ፡ ጊዜ ፡ አጻጻፍና ፡ አነባበብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኗል ።

ደግሞ ፡ የጥንቱ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ወይም ፡ ክብረ ፡ ነገሥት ፤ በውስጡ ፡ ከታሪክ ፡ ነገሥቱ፡ ይልቅ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ፡ የመንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ የያዘ ፤ ከዚያም ፡ ያንዱን፡ ንጉሥ ፡ የይኩኖ ፡ አምላክን ፤ ወይም ፡ የላሊበላን ፡ ታሪክ ፡ ጠቅሶ ፡ የቀሩትን ፡ ነገሥታት ፤ ዝር ዝራቸውን ፡ ብቻ ፡ እየጻፈ ፡ ማለፍ ፡ እንጂ ፡ በመደዳው ፡ የመንግሥቱንና ፡ የነገ ሥታቱን ፡ ታሪክ ፡ አይገልጽም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ቋንቋ ፡ ግዕዝ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አማርኛ ፡ መጻፊያው ብራና፡ ብርዑ ፡ ሸንበቆ ፡ ቀለሙ፡ ለዚሁ፡ ግቡ፡ የሆነ፡ የቅጠላቅጠልና፡ የእኽል፡ እራፊ፡ ጸሓ ፊዎቹ፡ ታሪክ፡ ነገሥት፡ ክብረ ፡ ነገሥት ፡ ብዕለ፡ነገሥት ፡ የሚባለውን ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓቶች ፡ ይልቁንም ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዞቹ ፡ . . . ፡ የሰማዕታቱን ፡ የመላእክቱን ፡ የቅዱሳኑን፡ገድልና ፡ ድርሳን፡ በጠቅላላው፡ የመንፈሳዊውን ፡ ወገን፡ ደግሞ ፡ ጳጳሳቱ፡ ዕጨጌዎቹ ፡ መነኰሳቱ ፡ ቀሳውስቱ ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ ሥራቸው፡ አንዳንድ፡ ጊዜ ፡ የቤተ፡ክህነቱ፡ ከቤተ፡መንግ ሥቱ፡ የተደባለቀና፡የተያያዘ፡ በመሆኑ፡ጸሓፌ፡ ትእዛዙ፡ የመንፈሳዊውን፡ ዕጨጌውም ፡ ታሪከ፡ነገሥቱን፡ታሪኩን፡ከመንፈሳዊ፤ መንፈሳዊውን፡ ከታሪክ፡ አደባልቀው፡ ሲጽፉ፡ይገ ኛሉ ። እንደዚህም፡ሆኖ፡ በቀን፡ ብዛት፡ በእጅ፡ እየተጻፈ፡ ሲያልቅ፡ በየቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በየገዳሙ፡ በየደብሩ ፡ ባንዳንድ ፡ ታላላቅ፡ ቀሳውስትና ፡ መኳንንት፡ቤት ፡ ይቀመጣል ። ከዚያም፡ አንዱ፡ ከሌላው ፡ እየገለበጠ ፡ ሲወስድ፡ ሌላውም፡ ሊቅ ፡ በቀን ፡ ብዛት፡ ተምሮ ፡ እርሱ፡ ደግሞ፡ በተራው ፡ መምህር ፡ ሆኖ ፡ ሲያስተምርበት ፡ ወይም ፡ በደባባይ ፡ ቆሞ ፡ ሲስብክበት ፡ ሕዝቡና ፡ ተማሪው ፡ እሬቱ ፡ ተሰብስቦ ፡ በዝርሮው ፡ እያዳመጠ ፡ ከመማር ፡ በቀር ፡ ትምህርቱን፡ በጽሑፍ ፡ አስቀርቶ ፡ እንደዛሬ ፡ ጊዜ ፡ ለመማርና ፡ እንደ፡ መምህሩ ፡ በቶሎ ፡ ሊቅ ፡ ለመሆን ፡ የችግሩ፡ ዐይነት፡ ብዙ፡ ነበር ። ማናቸውም፡ ሰው ፡ ከመጽሐፉ ፡ ላይ ፡ ለመገልበጥ ፡ በገንዘብና ፡ በችሎት ፡ ረገድ ፡ ዐቅም ፡ ያንሰዋል ። ቢገለበጥም፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ከሊቃውንትና ፡ ከመጻሕፍተ ፡ መነኰሳት ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ በጥቅስ ፡ እየ ተሰባጠረ ፡ የተጻፈውን ፡ የመጽሐፉን ፡ ትርጉምና ፡ ምሥጢሩን ፡ የሚያውቀው ፡ ያው ፡ የቃደለው ፡ ሊቅ ፡ በልክ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለዕውቀት ፡ የጓጓው ፡ ተማሪ ፡ እነዚሁ ፡ መጻሕፍትና ፡ ሊቃውንት ፡ ወዳሉበት ፡ ገዳምና ፡ ደብር ፡ ሄዶ ፡ ለሊቁ ፡ እንደ ፡ አሽከር፡ ሆኖ ፡ እያገለገለ ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ተማሪው ፡ ብልኅነት ፡ እንዳስተማሪው ፡ ቸርነትና ፡ ገርነት ፡ ሊማር ፡ ይችላል ። በፈረንጆች ፡ አገር ፡ ከሺሕ ፡ ፬፻፵ ፡ ዓመተ ፡ ምሕ ረት ፡ ዝምሮ ፡ የማኅተምና ፡ የወረቀት ፡ የጽሑፍ ፡ ማብዣ ፡ መኪናና ፡ ብልኀት ፡ ተገኝቶ ፡ ከዚሁ ፡ ከኛው ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰለው ፡ የጽሑፍ ፡ ችግር ፡ ከተቃለለ ፡ ወዲህ ፡ በኛ ፡ አገር ፡ ግን ፡ የዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ከበደ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ቈየ ።

## ፪ኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡

እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ባገራችን ፡ ብዙ ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥጋዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጻፈ ፤ በየጊዜው ፡ ከዐረብና ፡ ከሌላም ፡ ቋንቋ ፡ ተተረጐመ ። ይኸውም ፡ በሥጋዊ ፡ ረገድ ፡ እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፤ ክብረ ፡ ነገሥት ፤ ብዕለ ፡ ነገሥት ፤ ሥርዓተ ፡ መንግሥት ። በመንፈሳዊ ፡ በኩል ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ሊቃውንት ፡ መጻሕፍተ ፡ መነኰሳት ፡ ገድልና ፡ ድርሳን ፤ ድጓውና ፡ ጾመ ፡ ድጓው ፤ መዋሥዕትና ፡ ዝማሬው ፡ መልክአ ፡ መልክና ፡ ድርሰት ፤ በሌላው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፤ እንደ ፡ ዐቃቤ ፡ ርእስ ፡ እንደ ፡ መድፍነ ፡ ፀር ፡ ......... የመሳሰለው ፡ የአስማትና ፡ የጥንቈላ ፡ ጽሑፍ ፡ ሳይቀር ፡ አስማቱ ፡ በጠልሰም ፤ የቀረው ፡ በሐረግ ፡ ያለሐረግ ፡ በድጕስ ፡ ያለድጕስ ፡ ጥቂቱ ፡ በማርኛ ፡ አብዛኛው ፡ በግዕዝ ፡ እየሆነ ፡ በሙሉና ፡ በከፊል ፡ እየተጻፈ ፡ ካንዱ ፡ ገዳምና ፡ ደብር ፡ ወደ ፡ ሌላው ፤ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፤ ከንዳንዶቹ ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ ወደ ፡ ሌሎቹ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ተቀምጦ ፡ በየመልኩ ፡ እየተሠራበት ፡ ሲኖር ፡ ከሺሕ ፡ ፭፻፲፭ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ መከከል ፡ በግራኝ ፡ አሕመድ ፡ መነሣት ፡ ምክንያት ፡ እነዚህ ፡ የሥጋዊና ፡ የመንፈሳዊ ፡ መጻሕፍት ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲሰደድ ፡ ባከኑ ። አብያተ ፡ ክርስቲያናቱና ፡ ገዳማቱ ፡ ሲቃጠሉም ፡ አብረው ፡ ተቃጠሉ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዠምሮ ፡ መንግሥት ፡ ተመልሶ ፡ ሲቋቋም ፡ በየደሴቱ ፡ ከግራኝ ፡ አሕመድና ፡ ከጭፍሮቹ ፡ የተረፉት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየተገለበጡ ፡ በየጊዜው ፡ ከሚጻፉት ፡ ጋራ ፡ መበርከት ፡ ዠመሩ ። ታሪከ ፡ ነገሥቱም ፡ የነዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ በወልደ ፡ ሃይማኖት ፤ የነዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ በነአዛዥ ፡ ተክለ ፡ ሥላሴ ፡ (ጢኖ) ፡ በነአዛዥ ፡ ድልበ ፡ የነቀዳማይ ፡ ዮሐንስ ፤ የነኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፤ የነዐፄ ፡ በካፋ ፤ የነዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ በአዛዥ ፡ ሐዋርያ ፡ ክርስቶስ ፡ በአዛዥ ፡ ዘወልድ ፤ በአዛዥ ፡ ሲኖዳ ፤ በልጁ ፡ በክንፈ ፡ ሚካኤል ፤ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ያንዳንድ ፡ ነገሥታት ፡ በነሊቅ ፡ ዐጽቁ ፡ እጅ ፡ በሌሎቹም ፡ አሁን ፡ በማስታውሳቸው ፡ ሊቃውንት ፡ እጅ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ በብራና ፡ እየተጻፈ ፡ በጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ አድባራት ፡ ተቀመጠ ። ሌላውም ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥጋዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ በነእጨጌ ፡ ዕንባቆም ፡ በነአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በነሚካኤል ፡ በነጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ አሚድ ፡ ድካም ፡ ግማሹ ፡ በረብኛ ፡ ተጽፎ ፡ የቀረውም ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተተርጕሞ ፡ የነበረውን ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፤ የተነሡት ፡ እያሻሻሉ ፡ ሠርተው ፡ የመጻሕፍቱ ፡ ቍጥር ፡ ምናልባት ፡ ከግራኝ ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ ወደ ፡ መብለጥ ፡ ደረሰ ።

እንደዚሁ ፡ ሆኖ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ይልቁንም ፡ የመንፈሳዊው ፡ ክፍል ፡ በበረከተበት ፡ በሺሕ ፡ ፬፻ና ፡ በሺሕ ፡ ፰፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መከከል ፡ ከፖርቱጋልና ፡ ከኤስፓኝ ፡ ወዲህ ፡ ከተነሡት ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ከፈረንሳዊ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ከጀርመን ፡ አገር ፡ ብዙዎች ፡ አገር ፡ መርማሪዎችና ፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡ እየመጡ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በያውራጃው ፡ መቀመጥ ፡ ዠመሩ ። እነዚህም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በግዥም ፡ በስጦታም ፡ የኢትዮጵያን ፡ መጻሕፍት ፡ እየሰበሰቡ ፡ ወዳገራቸው ፡ ሲልኩ ፡ ቈይተው ፡

በኋላም ፡ ራሳቸው ፡ ወዳገራቸው፡ በሚመለሱበት ፡ ጊዜ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ይወስዱ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሄዱት ፡ መጻሕፍት ፡ በእንግሊዝና ፡ በፈረንሣይ ፡ በጀርመንና ፡ በኢጣሊያ ፡ ........ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት፡ በደንብ ፡ ቊጥርና ፡ ማውጫ ፡ እየተበጀላቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ዠመር ።

## ሀ-በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ መጻሕፍቶቻችን ።

በዚህ፡መጽሐፍ፡ባፄ፡ኢዮአስ፡ዘመን ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የሚ ባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ በሺሕ ፡ ፲፯፻፷፱ ፡ ዓ፡ ም ፡ በኢትዮጵያ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የብራና ፡ መጽሐፍ ፡ ሰብስቦ ፡ ወሰደ ፤ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ጥበበ ፡ ሰሎሞን ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ የክብረ ፡ ነገሥት ፡ የሄኖክ ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኙበታል ። ክብረ ፡ ነገሥቱን ፡ የሰጡት ፡ እርሱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ የመንግሥቱ ፡ እንደራሴ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ ሥዑል ፡ ሚካኤል ፡ ናቸው ፤ እርሱም ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ ይዞ ፡ ወዳገሩ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ባማረ ፡ ጥራዝና ፡ ብራና ፡ የተጻፈውን ፡ የሄኖክን፡ መጽሐፍ ፡ ለሉዊ ፡ ፲፭ኛ ፡ ለፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ አበረከተለትና ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲቀመጥ ፡ ተደረገ ። የቀሩትንም ፡ ብሩስ ፡ ወደ ፡ ሎን ዶን ፡ ይዟቸው ፡ ገብቶ ፡ ለቦድሌያን ፡ መጻሕፍት፡ ቤት ፡- አክስፎርድ ፡ (BODLEIAN LIBRARY OXFORD) ሰጠውና ፡ በደንብ ፡ ተቀመጠ ።

ከርሱ ፡ ወዲህም ፡ እነሳልት ፡ እነፒርስ ፡ እነሙሕላይዘን ፡ አርኖልድ ፡ እነክራፍ ፡ አያሌ ፡ መጻሕፍት ፡ አጠራቅመው ፡ ወሰዱ ። ቀጥሎ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ማኅበር ፡ መሪዎች ፡ አማካይነት ፡ ፲፱ ፡ የሚሆኑ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መጻሕፍት፡ ወደ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ገቡ ። ከነዚህም ፡ አብዛኞቹ ፡ ለየብቻ፡ የተጻፉ ፡ አርባዕት ፡ ወንጌል፤ ዳዊት ፤ ራእየ ፡ ዮሐንስ ፤ ድጓ ፡ ናቸው ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የኦክስፎርድን ፤ የካምብሪጅን ፡ የኤ ዲምቡርግን ፡ ታላላቅ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ በኩል ፡ እንዲከ ብሩ ፡ ያደረጋቸው ፡ በሺሕ ፡ ፲፰፻፷ ፡ ዓ፡ ም፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ የተደረገው ፡ የመቅደላ ፡ ጦርነት ፡ ነው ።

ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ ከመዋጋታቸው ፡ ቀደም ብሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከትግሬ ፡ ከሸዋ ፡ ከጐጃምና ፡ ከበጌምድር ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሁሉ ፡ እያሰበ ሰቡ ፡ መቅደላ፡ በመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀምጠውት ፡ ነበር። በዠኔራል ናፒዬር ፡ እየተመራ ፡ የመጣው ፡ የእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ በሺህ ፡ ፲፰፻፷ ዓ፡ ም ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ በሸነፈ ፡ ጊዜ ፡ ቊጥሩ ፡ እስከ፩ ፡ ሺህ ፡ የሚደርስ ፡ ጥራዝ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ ያማረ ፡ ውስጡ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐረግ ፡ ያጌጠ ፡ በግዕዝና ፡ ባማርኛ፡ የተጻፈ ፤ መጽሐፍ ፡ በያይነቱ ፡ በዚሁ ፡ በመቅደላ ፡ አገኘ ። ከዚያ ፡ በዠኔራሉና ፡ በዋቢ ዎቹ ፡ እየተመረመረ ፡ ያልጓጉለትን ፡ አምስት ፡ መቶውን ፡ መጻሕፍት ፡ በየመንገዳቸው ፡ ላገኙት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ መኳንንት ፡ እንደዚሁም ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ አደሉት ። ምርጥ ፡ የሆኑትን ፡ አምስት ፡ መቶውን ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ሎንዶን ፡ ይዘዋቸው፡ ሄዱና ፡ በመንግሥት ፡ ፈቃድ፡በዋናው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ተከፋፍለው ፡ ተቀ

መጡ ። እነዚህንም ፡ አቀማመጣቸውን ፡ በደንብ ፡ አዘጋጅተው ፡ ዝርዝራቸውን ፡ (ካታሎ
ጋቸውን) ፡ ባንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ያወጡት ፡ ዊሊያም ፡ ራይት ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝና ፡
ዲልማን ፡ የሚባለው ፡ የጀርመን ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። ከዚሁ ፡ ከየቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ከተ
ቀመጠው ፡ እየቃረሙ ፡ ራሳቸውም ፡ የተመለከቱትን ፡ እየጨመሩ ፡ እነዋሊስ ፡ ባጅ ፡ የኢ
ትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ጽፈው ፡ አወጡ ። እንደዚሁም ፡ በዚያው ፡ ከተቀመጠው ፡ ራሱን ፡
ግዕዙን ፡ በማተሚያ ፡ እያሳተሙ ፡ አወጡት ፤ ከዚሁ ፡ ውስጥ ፡ እኔ ፡ ያየሁት ፡ ባጅ ፡ ያሳ
ተመው ፡ ዜና ፡ እስክንድር ፤ ብሉንዴል ፡ ያሳተመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ዜና ፡
መዋዕል ፡ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ ያላየኋቸው ፡ መጻሕፍት ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ በግዕዙ ፡
ቋንቋ ፡ ጐን ፡ እንግሊዝኛው ፡ እየተጨመረ ፡ ታትመው ፡ ወጥተዋል ።

## ለ–በፈረንሳዊ ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ መጻሕፍቶቻችን ።

እንግሊዝና ፡ ፈረንሳዊ ፡ በግዛት ፡ በጥቅም ፡ እንደሚሽቀዳደሙ ፡ በዚህም ፡
በጽሑፍ ፡ ስብሰባና ፡ በመጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ድርጅት ፡ በኩል ፡ ያላቸው ፡ ትጋ
ትና ፡ ፉክክር ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ። በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡
ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሻርል ፡ ፖንሴ ፡ በኩል ፡ ግንኙነት ፡ ተደርጎ ፡ መተዋወቅ ፡
ከተዠመረ ፡ ወዲህ ፤ ብዙ ፡ ፈረንሳዮች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣታቸውን ፡
ገልጸናል ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ሙሴ ፡ ሮሺ ፡ ዴሪኩር ፡ ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡
ሥላሴ ፡ ከመገናኘቱ ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ማጠራቀም ፡ ዠመረ ።
ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴም ፡ ተገናኝቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ሲመለስ ፡ ንጉሥ ፡ ሣህለ ፡
ሥላሴ ፡ ለፈረንሳዊ ፡ ንጉሥ ፡ ለሉዊ ፡ ፊሊፕ ፡ የሚሰጥ ፡ አንድ ፡ ስንክሳርና ፡ አንድ ፡
ፍትሐ፡ነገሥት፡ሰጥተዉት፡ርሱ፡ራሱ ፡ ካጠራቀማቸው ፡ ጋር ፡ ጨምሮ ፡ ፳፫ ፡ የሚሆኑ ፡ ልዩ
ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ከርሱ ፡ ወዲህ ፡ ጋሊ ፡ ፓሴቦስክና ፡ ሞንዶ ፡ ቪዳዬ ፡
የሚባሉት ፡ በየጊዜው ፡ የተቻላቸውን ፡ ሰብስበው ፡ ወሰዱ ። ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡
የኢትዮጵያን ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ያጋዘ ፡ ሙሴ ፡ ቶማስ ፡ አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ ነው ።
እርሱም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ በትግሬ ፤ በበጌምድር ፡ በጐጃም ፡ በሸዋ ፡ ገዳማ
ትና ፡ አድባራት ፡ እየተዘዋወረ ፡ ቈጥራቸው ፡ እስከ ፡ ፪፻፴፬ ፡ የሚደርስ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡
የብራና ፡ መጻሕፍት ፡ አጠራቅሞ ፡ ወዳገሩ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ አባል ፡ ለሆ
ነበት ፡ የሲያንስ ፡ አካዴሚ ፡ (የዕውቀት ፡ ጉባኤ) ፡ ለሚባለው ፡ ማኅበር ፡ ሰጠ ። በኋ
ላም ፡ በዚሁ ፡ ማኅበር ፡ ፈቃድ ፡ በፓሪስ ፡ በሕዝብ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ተዛውሮ
ተቀመጠ ። ከዚያም ፡ እነማርሴል ፡ ኮሄን ፡ የወሰዱት ፡ በፈረንሳዊ ፡ አውራጃና ፡ ይልቁ
ንም ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ድረስ ፡ በሚደርሱት ፡ ታላላቅ ፡ የመ
ጻሕፍት ፡ ቤቶች ፡ በየጊዜው ፡ የተሰበሰበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጽሐፍ ፡ በደንብ ፡ እየተ
ቀመጠ ፡ ከዚሁ ፡ እነዞቴምቤርግ ፡ እነግሪቦ ፡ እነሼን ፡ ማሪዉስ ፡ እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ እነኮ
ይዲ ፡ ሌሎችም ፡ ጸሐፊዎችና ፡ መርማሪዎች ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ ተደረገ ።

## ሐ–በጀርመን ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ መጻሕፍቶቻችን ።

በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ወደ ፡ ጀርመን ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍቶቻችን ፡ ሄደዋል ። በሂ
አብ ፡ ሉዶልፍ ፡ በምስተር ፡ ፍላድ ፡ በቴዎድሩስ ፡ ፔትራስ ፡ እጅ ፡ አስቀድሞ ፡ ብዙዎች ፡

መጻሕፍት ፡ ሄዱ ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ፔቴርማን ፡ ፵ ፡ ብሩግሽ ፡ ፲፫ ፡ ሌፕሲዩስ ፡ ፱ ፡ ኢዜንቤርግ ፡ ፯ ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲወስዱ ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ በነዚሁ ፡ በሚሲዮኖችና ፡ ባገር ፡ መርማሪዎች ፡ በቆንሲሎች ፡ በኩል ፡ በግዥና ፡ በስጦታ ፡ እየተሰበሰበ ፡ የሄደው ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ኤኖ ፡ ሊትማን ፡ ፳፰ ፡ ፍሌሚንግ ፡ ፹ ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ በተጨማሪነት ፡ አገቡና ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ጌትነት ፡ የጀርመን ፡ ከተሞች ፡ ቤርሊን ፡ "ሌይብጺንግ ፡ ......" መጻሕፍት ፡ ቤቶች ፡ ከጓደኞቻቸው ፡ ከሎንዶን ፡ ከፓሪስ ፡ እንዳያንሱ ፡ አደረጉ ።

## መ-በኢጣልያ ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ መጻሕፍቶቻችን ።

የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ በኢጣልያ ፡ ከተማዎች ፡ በሮማ ፡ በቫቲካን ፡ በጄኖቫ ፡ በሚላኖ ፡ በሌሎችም ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ይገኛሉ ። የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ከሺሕ ፡ ፬፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዠምሮ ፡ በሚሲዮናውያኑ ፡ እጅ ፡ አንዳንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ከሺሕ ፡ ፰፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፰፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፳፱ ፡ ዓመት ፡ የነበሩት ፡ ጆሴፔ ፡ ሳፔቶ ፡ የሚባሉት ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ፳ ፡ የሚሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወሰዱ ። በወሰዷቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የኩፋሌ ፡ የስንክሳር ፡ የሔኖክ ፡ የቅዳሴ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኙባቸዋል ።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ዠምሮ ፡ ይልቁንም ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ለቫቲካን ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ሚኒስትሮቹ ፡ ቆንሲሎቹ ፡ ለውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፤ የቀሩትም ፡ ለቅኝ ፡ አገር ፡ ሚኒስቴራቸው ፤ እንደ ፡ ከንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ እንደ ፡ ቼሩሊ ፡ ያሉትም ፡ ለየግል ፡ መጻሕፍት ፡ ቤታቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ አገር ፡ እየወሰዱ ፡ በነፋማጋሊ ፡ በነዛኑቶ ፡ እጅ ፡ በሥርዓትና ፡ በደንብ ፡ ዝርዝሩ ፡ እየተጻፈ ፡ ማውጫ ፡ እየተበጀለት ፡ ተቀመጠ ። በተረፈ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ በመስኮብ ፡ በአሜሪካ ፡ በቤልጂክ ፡ በነምሳ ፡ .... ይገኛሉ ።

## ፫ኛ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ጻፉ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የተጋዘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጽሐፍ ፡ ዐይነቱ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ሀ—ቁጥሩ ፡ በብሉይ ፡ ውስጥ የሆነ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ የሰሎሞን ፡ ማሕልይና ፡ ምሳሌ ፤ ሲራክ ፤ ሔኖክ ፤ እነሱ ፤ አክታቴዉኩስ ፡ ብለው ፡ የሰየሙት ፡ ፰ቱ ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ። ....

ለ—ከሐዲስ ፡ ውስጥ ፡ ሙሉውን ፡ ወይም ፡ እየተለየ ፡ የተጻፈው ፡ አርባዕቱ ፡ ወንጌል ፤ የሐዋርያት ፡ ሥራና ፡ መልእክት ።

ሐ —ከሊቃውንት ፡ የሚቈጠሩት ፡ ያፊ ፡ ወርቅ ፤ የቄርሎስ ፡ መጻሕፍት ፡ ከዚያም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፤ ስንክሳር ፤ ግንዘት ፤ ሃይማኖተ ፡ አበው ፤ ቅዳሴ ፤ ድጓ ፤ ጾመ ፡ ድጓ ፤ መጽሐፈ ፡ ሐዊ ፤ ፭ቱ ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፤ .....

መ —ያቡሻህር ፡ መጽሐፍ ፤ የዘመንና ፡ የከዋክብትን ፡ መለዋወጥ ፡ የሚያመለክት ።

ሠ—እንደ ፡ አዋልድ ፡ የሚቈጠረው ፡ የጻድቃንና ፡ የሐዋርያት ፡ የሰማዕታትና ፡ የመላእክት ፡ ድርሳንና ፡ ገድል ፤ ለምሳሌ ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፤ ገድለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፤ ገድለ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ድርሳነ ፡ ሚካኤል ።

ረ—ግማሹ ፡ እንደ ፡ ትምህርተ ፡ ኅቡአት ፤ እንደ ፡ ማኅሌተ ፡ ጽጌ ፤ እንደ ፡ መልክአ ፡ ማርያምና ፡ መልክአ ፡ ኢየሱስ ፤ እንደ ፡ ሰይፈ ፡ ሥላሴ ፤ እንደ ፡ ሐጹረ ፡ መስቀል ፤ እንደ ፡ ኪዳን ፤ እንደ ፡ ዕቀበኒ ፡ ያለው ፡ የጸሎትና ፡ የድግምት ፡ መጽሐፍ ።

ሰ—ግማሹ ፡ ዐውደ ፡ ነገሥት ፤ ዐቃቤ ፡ ርእስ ፤ መድፍነ ፡ ፀር ፡ ልሳነ ፡ ሰብእ ፡ የሚባለው ፡ የአስማትና ፡ የጥንቈላ ፡ መጽሐፍ ፤ ለቍርጠት ፤ ለውጋት ፤ ለሰው ፡ ዐይን፤ ለውቃቢ ፤ ለዛር ፡ ውላጅ፡ የሚደገመው ፡ግማሹ ፡ በዝርግ ፡ ግማሹ፡ለክታብ ፡ የተጠቀለለ፡ ሆኖ ፡ የሄደው ፡ጽሑፍ ፡ ሁሉ፡በፈረንጆች፡ተመርምሮ ፡ዋዛና ፡ ቁም፡ነገሩ፡ታውቋል ።

ቀ—የቀረው ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተነሣበትን ፡ ጽሑፍ ፡ በቀጥታ ፡ የሚመለከተው ፡ የታሪክ ነገሥትና ፡ የክብረ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ።

እንግዴህ ፡ ይኸ ሁሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ባማርኛና ፡ በግዕዝ ፡ በጥቍርና፡በቀይ፡ ቀለም በብራናና ፡ በወረቀት ፡ እየተጻፈ ፡ ግማሹ ፡ በሐረግና ፡ በጠልሰም ፡ እያጌጠ ፡ በኢትዮጵያ የተቀመጠውን ፡ ያኽል ፡ በኤውሮፓ ፡ ዕፍረት ፡ አላገኘም ። መርማሪዎቹ ፡ እነዲልማን ፡ እነማርሴል ፡ ኮሄን ፤ እነጕይዲ ፤ እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ፤እነግሪዮል ፤ እነበጂ፡ዕረፍት ፡ ነሥተው ፡ ላዩንም ፡ ውስጡንም ፡ ሐረጉንም ፡ ጽሕፈቱንም ፡ ቃሉንም ፡ አገላብጠው ፡ አጣሩት ፡ የምን ፡ ዘመን ፡ ጽሕፈትና ፡ ሐረግ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፊደሉ ፡ አጣጣልና ፡ የቃሉ ፡ ንግግር ፡ ከየት ፡ እንደ ፡ መነጨ ፡ ከማን ፡ እንደሚመሳሰል ፡ እየለዩ ፡ ከግብጽና ፡ ከአሶር ፡ ከሳባና ከፋርስ ፡ ከዕብራይስጥና ፡ ከጽርእ ፤ ከላቲንም ፡ የሚገናኘውን ፡ ለየብቻ ፡ እየመረመሩ ፡ አበጠሩት ። እነዚህ ፡ የኢጣልያና ፡ የጀርመን ፡ የእንግሊዝና ፡የፈረንሳዊ ፡ ሊቃውንት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ግንኙነት ፡ እያደረጉ ፡ በያገሩ ፡ የተቀመጠውን ፡ መጽሐፍ ፡ እየተላላኩ ፡ እያገኙ ፡ ያልተመለከቱትን ፡ እየተመለከቱ ፡ ላልተመለከተው ፡ እያመለከቱ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ፡ያለው፡የመጽሐፍ፡ዐይነትና፡ዝርዝር፡ "በተቻለ ፡ መንገድ ፡ መጽሐፉም ፡ ራሱ„ ፡ በየከተማቸው ፡ እንዲገኝና ፡ ላመራመር ፡ እንዲመች ፡ አደረጉ ። ለምሳሌ ፡ ጀርመኑ ፡ ዲልማን ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ ከሚገኙቱ ፡ መጻሕፍት ፡ በቀር ፡ የፓሪስንም ፡ የሎንዶንንም ፡ መጻሕፍት ፡ እየተመለከተ ፡ ራሱ ፡ ባዘጋጀው ፡ የዝርዝር ፡«የካታሎግ" ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገኙ ፡ ሲያደርግ ፡ እንደዚሁም ፡ ውሊያም ፡ ራይት፡ እንግሊዙ ፤ኮንቲ፡ ሮስኒ ፡ ኢጣልያኑ ፡ በሌሎች ፡ ከተሞች ፡ የተቀመጡትን ፡ የመጻሕፍት ፡ ስምና ፡ ዝርዝር ፡ በራሳቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ ለፈላጊ ፡ ለተመልካች ፡ ለመርማሪ ፡ ለጸሐፊ ፡ እንዲመች ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ እየጣሩ ፡ አዘጋጅተው፡በክበሬታ ፡ አስቀመጡት።

እንደዚሁም ፡ ከደረጉ ፡ በኋላ ፡ ለዚህ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክና፡ጕዳይ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ከሠዉትና ፡ ዋነኛ ፡ ሆነው ፡ ከሚቈጠሩት ፡ ሊቃውንት ፡ ውስጥ ፡

ሙሴ ፡ አ ፡ ዲልማን ፡ (A.Dillmann)፲፪ ፡መጻሕፍት ፡ አሳትሟል ፤ ከዚሁ ፡ በጣም ፡ የታወቀውና ፡ የተደነቀው ፡ Lexicon Linguæ Æthiopicæ ፡ የሚባለው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፎ ፡ በ1865 ፡ ዓ ፡ ም ፡ በላይጵጺግ ፡ የታተመ ፡ ነው ።

ካሮል ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ (Carlo Conti Rossini) እንዚሁኑ ፡ መጻሕፍት ፡ በደንብ ፡ እየመረመረ ፡ እስከ ፡ ፳፫ ፡ የሚደርሱ ፡ ታላላቅና ፡ ታናናሽ ፡ መጻሕፍት ፡ ባገሩ ፡ በሮማ ፡ አሳትሟል ። በነዚህም ፡ በታተሙት ፡ ውስጥ ።

ሀ) የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ታሪክ ፡

ለ) የዛጔዎች ፡ ታሪክ ፡

ሐ) የኢትዮጵያ ፡ የጽሑፍ ፡ ታሪክ ፡

መ) የደብረ ፡ ቢዘን ፡ ገድለ ፡ ፊልጶስና ፡ ገድለ ፡ ዮሐንስ ፡

ሠ) የያሬድና ፡ የጳንጠሌዎን ፡ ገድል ፡

ረ) የቅዱስ ፡ መርቆሬዎስ ፡ ታሪክ ፡

ሰ) በምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ታሪክ ፤ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡

ቀ) ግብጽና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጥንት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡

በ) ሴማዊ ፡ የሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋና ፡ ጽሑፍ ፡

ተ) ስለ ፡ ዛጔ ፡ መንግሥት ፡ አወዳደቅ ፡

ኀ) የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ . . . . . . . , ይገኝበታል ። ከነዚህም ፡ የመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፉ ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ መሆኑ ፡ በተመልካቾች ፡ ዘንድ ፡ ተገምቷል ።

ኢኛሲዮ ፡ ጒይዲ ፡ (Ignazio Guidi) ደግሞ ፡ የጻፉቸውን ፡ ያሳተሟቸው ፡ እስከ ፡ ፴፪ ይደርሳሉ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡

ሀ) ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ ቋንቋ ፡

ለ) ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ መስኮብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ሐ) የኢትዮጵያ ፡ ተረትና ፡ ዕንቈቅልሽ ፡

መ) የዘሚካኤል ፡ (አቡነ ፡ አረጋዊ) ፡ ሕይወት ፡

ሠ) የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በግዕዝና ፡ በኢጣልያንኛ ፡

ረ) በምዕራፍ ፡ ፴፯ የጠቀስነው ፡ የቀዳማዊ ፡ ዮሐንስ ፤ የኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ የበካፋና ፡ የዳግማዊ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፤ በቀጥታ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ የታተመው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡

ሰ) ስንክሳር ፡ ይገኝበታል ።

ሙሴ ፡ ማርሴል ፡ ኮሄን ፡ (Marcel Cohen) ፲፫ ፡ መጻሕፍት ፡ አሳትሟል ፤ ከነዚሁ ፡

ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖትና ፡ ሥርዓት ።

ለ) የኢትዮጵያ ፡ ያማርኛ ፡ ግሥና ፡ የቅጽል ፡ አገባብ ።

ሐ) የካምና ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ አለበት ። ርሱም ፡ ራሱ ፡ በምሥራቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያማርኛና ፡ የግዕዝ ፡ መምህርነት ፡ አለው ።

ሙሴ ፡ ፔሩሾን ፡ ዡል ፡ (Pérouchon Jules) ፲፯ ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትሟል ። የርሱም ፡ አብዛኞቹ ፡ የዐፄ ፡ ላሊበላ ፤ የዐፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፤ የዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፤ የዐፄ ፡ እስክንድር ፤ የዐፄ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ የዓፄ ፡ ናዖድ ፤ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፤ የዐፄ ፡ ሚናስ ፤ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፤ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ታሪክና ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ናቸው ፤ ከነዚህም ፡ እርሱ ፤ ከጻፉቸው ፡ በቀር ፡ በግዕዝ ፡ ራሱ ፡ ያሳተመው ፡ ይበልጣል ።

ሙሴ ፡ አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ (Antoine d'Abbadie) ፡ ፲፯ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፏል ። እርሱም ፡ በጻፉቸው ፡ ውስጥ ።

ሀ—ስለ ፡ ከም ፡ ቋንቋ ።

ለ—በአኵስም ፡ ሐውልቶች ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙት ፡ ጽሑፎች ።

ሐ—ስለ ፡ ጋሎች ።

መ አበሻና ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሚል ፡ ይገኝበታል ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፤ እነዋሊስ ፡ ባጂ ፤ እነሩፔል ፡ እነሊትማን ፤ እነግሪዎል ፡ እነሸን ፤ እነለፌብር ፤ እነሉዶልፍ ፤ እነካሜረር ፡ እነቼሩሊ ፡ የጻፉትና ፡ ያሳተሙት ፡ ቍጥሩንና ፡ ስሙን ፡ እንኳን ፡ በዚህ ፡ መቅድም ፡ ዘርዝረን ፡ አንጨርሰውም ። እነዚህም ፡ ዐዋቂዎች ፡ መጻሕፍቶቻችንን ፡ ከመረመሯቸው ፡ በኋላ ፡ መቅድምና ፡ ምልክት ፡ (ኖት) ፡ ብቻ ፡ እየጨመሩ ፡ በግዕዝኛው ፡ ቋንቋ ፡ እንዳለ ፡ ያትሙታል ፡ ለምሳሌ ፤ ጕይዲ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥታችንን ፡ ዋሊስ ፡ ባጂ ፡ ዜና ፡ እስክንድራችንን ፡ አትመው ፡ ያወጡት ፡ እንዳለ ፡ በግዕዙ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። የቀረውን ፡ ደግሞ ፡ እየመረመሩ ፡ እነሱ ፡ በቋንቋቸው ፡ በራሳቸው ድካም ፡ ለሚጽፉት ፡ (ለሚደርሱት) ፡ መጽሐፍ ፡ ድጋፍና ፡ መጠቀሚያ ፡ ብቻ ፡ አድርገው ፡ ይጽፉበታል ።

በዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጽሐፍ ፡ ጕዳይ ፤

፩ኛ ፡ የጥንት ፡ ዕጨጌዎችና ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዞች ፡ ታሪኩንም ፡ መንፈሳዊውንም ፡ በብራና ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ጽፈው ፡ ማቈየታቸው ፡ ያስመሰግናቸዋል ።

፪ኛ ፡ የኛዎቹ ፡ በብራና ፡ ጽፈው ፡ አስቀምጠውት ፡ የነበረውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ፈረንጆቹ ፡ ወደየአገራቸው ፡ ወስደው ፡ ለጽሑፉ ፡ ዋጋ ፡ በመስጠት ፡ በደንብ ፡ እያስቀመጡ ፡ ከዚያም ፡ በምርመራ ፡ እየጻፉ ፡ የቀረውንም ፡ ራሱን ፡ በማተሚያ ፡ ቤት ፡ እያተሙ ፡ በያገሩ ፡ ማዳረሳቸው ፤ ከገራችን ፤ ወደነሱ ፡ አገር ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ እነሱ ፡ ያሳተሙት ፡ እየተመለሰ ፡ ወደአገራችን ፡ እንዲገባ ፡ ማድረጋቸው ፡ በጣም ፡ ያስመሰግናቸዋል ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በአኵስም ፤ በላስታ ፤ በሸዋና ፡ በጐንደር ፡ በየገዳሙ ፤ በየደብሩ ፡ በየደሴቱ ፡ አስቀምጠው ፡ መነኰሳቱና ፡ ሊቃውንቱ ፡ የሚሣሡለትን ፡ የታሪክና ፡ የሃይማኖት ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ገና ፡ ዱሮ ፡ እነጕይዲ ፡ እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ እነባጅ ፤ እነዲልማን ፤ እነኮሂን ፡ በማኅተም ፡ አትመው ፡ አራብተውታል ። የምሥራቅን ፡ ቋንቋና ፡ ሃይማኖት ፡ ልማድና ፡ ሥርዓት ፡ ለመመርመር ፡ የተነሣው ፡ ሊቅ ፡ ሁሉ ፡ የታተመውን ፡ ወደ ፡ ቋንቋው ፡ ተርጕሞ ፡ የምሥጢሩን ፡ ቁም ፡ ነገሩኛነት ፡ ተመልክቶ ፡ ጨርሶታል ፡ እንኳን ፡ ቁም ፡ ነገረኛነት ፡ ያለው ፡ የታሪክና ፡ የመንፈሳዊው ፡ መጽሐፍ ፡ በቀይና ፡ በጥቁር ፡ ቀለም ፡ በብራና ፡ እየተጻፈ ፡ ተጠቅሎ ፡ በክታብ ፡ ሆኖ ፡ በንገት ፡ የሚያዘው ፡ ያስማት ፤ የመድፍን ፡ ፀር ፤ የዐቃቤ ፡ ርእስ ፡ ጽሑፎችን ፡ ሁሉ ፡ በነግሪዎል ፤ በነባጅ ፤ በነግሪቦ ፡ እየተተረጐመ ፡ ተመርምሯል ።

እነዚህ ፡ ላይ ፡ ስማቸውን ፡ የጠቀስነው ፡ እነዲልማን ፤ እነጉይዲ ፤ እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ እነኮሂን ፤ እነግሪዎል ፤ እነሊትማን ፤ የብራና ፡ ጽሑፎችን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ቋንቋችን ፡ ስለ ፡ ዘራችን ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታችን ፡ ቍጥሩ ፡ የበረከተና ፡ የተለያየ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲጽፉ ፡ ራሱን ፡ የግዕዙን ፡ ወይም ፡ ያማርኛውን ፡ ያሳተ

ሙት ፡ ወይም ፡ ያንዱን ፡ ክፍል ፡ ጉዳይ ፡ አበጥረው ፡ በጠለቀ ፡ መንገድ ፡ መርም ረው ፡ የጻፉ ፡ ያንድ ፡ ወገን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ።

ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ራሳቸው ፡ መርምረው ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ የጻፈውን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በሙሉና ፡ በከፊል ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ በየቋንቋቸው ፡ እንደ ችሎታቸው ፡ የጻፉት ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ክፍል ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። እነዚያም ፡ በድካም ፡ የሠሩትን ፡ እነዚህ ፡ ብዙ ፡ ሳይደክሙ ፡ በራሳቸው ፡ አነጋገርና ፡ አሰካክ ፡ ብቻ ፡ የደረሱ ፡ አሉ ።

የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከጻፉት ፡ ውስጥ ፡ ዋነኞቹን ፡ ለአንከቢና ፡ ለፈላጊ ፡ እን ዲመቹ ፡ ሙሉ ፡ ስማቸውንና ፡ የመጽሐፉን ፡ አርእስት ፡ ከዚህ ፡ ግርጌ ፡ ጽፌዋለሁ ።

፩ኛ ፡ ካሚሎ ፡ ቤካሪ ፡ (Camillo Beccari) የሚባለው ፡ ቀድሞ ፡ ከ፱፻ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ገምር ፡ በ፱፻ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በ፱፻ ፡ ሥርፀ ፡ ድንግል ፡ በ፱፻ ፡ ሱስንዮስ ፡ በ፱፻ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተቀመጡት ፡ የኢየሱሳውያን ፡ ሚሲዮኖች ፡ እነ ዳልሜይዳ ፡ እነባራዳስ ፡ እነሜንዴዝ ፡ እነፓኤዝ ፡ በዚያው ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ በፓርቱ ጋል ፡ አለዚያም ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ የጻፉትን ፡ በንድነት ፡ አደራጅቶ ፡ «Rerum Æthiopicarum scriptores occidentales inediti a sæculo XVI ád XIX» በሚል ፡ አርእስት ፡ በ1903–በ1917 ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያወጣው ፡ በ፲፭ ፡ ክፍል ፡ የተከፈለ ፡ በኢ ትዮጵያ ፡ የሺህ ፡ ፲፱-፲፱—፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። በነዚህ ፡ ዘመናት ፡ ከነአልቫሬዝ ፡ ከነካስታንሆዘ ፡ ከነሎቦ ፡ ከነፔሬይራ ፡ ከነቴሌዝ ፡ የተጻፈው ፡ ከዚሁ ፡ ጋራ ፡ የሚደረብ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ (James Bruce) ኢትዮጵያን ፡ አይቶ ፡ ከተመለሰ ፡ ወዲህ ፡ "Travels to discover the Source of the Nile, in the Years 1768, 1769, 1770, 1771, 1771 and 1773" በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፰ ፡ ክፍል ፡ የተጻፈና ፡ ከ1805-1879 ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ።

፫ኛ ፡ ዋሊስ ፡ በጅ ፡ (Wallis Budge) A History of Ethiopia (Nubia and Abissinia) በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፪ ፡ ክፍል ፡ 1928 ።

፬ኛ ፡ ዣን ፡ ሞሪዬ ፡ (Jean Morié) A Les civilisaions Africaines. Histoire De l'Ethiopie (Nubie et Abissinie) depuis les temps les plus reculésjusqu' à nos jours በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፪ ፡ ክፍል ፡ መጽሐፍ ፡ በ1904 ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ።

፭ኛ ፡ ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኩልቦ ፡ (jean. B. Coulbeaux) Histoire Politique et Religieuse d. Abissinie Depuis les temps les plus reculés jusqu' à l' avénement du Ménélik II በሚል ፡ አርእስት ፡ በ፪ ፡ ክፍል ፡ መጽሐፍ ፡ በ1929 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ።

፮ኛ ፡ ባሴት ፡ ረኔ ፡ (Basset René) Étude sur l' Histoire d' Ethiopie) (በ1881) -Rapport sur les Études berbers, Ethiopienne et arabes- (ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ስለ ፡ ዐረብና ፡ ስለ ፡ በርበር ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያውያን) ፡ ያጠናው ፡ ጽሑፍና ፡ በ1887-1891 ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተመ ።

፳ኛ ሩፔል ኤድዋርድ (Ruppel Eduard) Reise in Abissnia በሚል አርእ ስት የተጻፈው በ፪ ክፍል ሆኖ ባ1838—1840 ዓ፡ ም የታተመ ።

፳፩ኛ ፤ ሉካ ፡ ዴ ፡ ሳቤሊ ፡ (Luca dei sabelli) Storia di Abissinia የሐበሻ ፡ (የኢትዮጵያ) ፡ ታሪክ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ባ፬ ፡ ክፍል ፡ ጽፎ ፡ ባ1936|37 ፡ (1)ዓ፡ ም፡ ያሳተመው ፡ ነው ።

በተረፈ ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ሰዋስው ፡ ስለ ፡ ሥርዓትና ፡ ልማድ ፤ ስለ ፡ ጉዞ፤ እያ ንዳንዱ ፡ የውጪ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የጻፈውን ፡ ሁሉ፡ ስሙን ፡ ከነመጽሐፉ ፡ በዚህ፡ መቅ ድም ፡ ጽፎ ፡ ለመጨረስ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።

ያገራችንን ፡ ጽሑፍ፡ ዝርዝሩን ፡ ለማወቅ፡ የፈለገ ፡ እንግሊዙ፡ ዊሊያም ፡ ራይት፡ ጀርመኑ ፡ ዲልማን ፡ የጻፉትን፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደግሞ ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ አርእስት ፡ የጻፉ ትን፡ ደራሲዎች ፡ ስማቸውንና ፡ የመጽሐፉን ፡ አርእስት፡ ደግሞ ፡ ከፉማጋሊና ፡ ከዛኑቶ፡ ከዱቼዝን ፡ ፉርኔና ፡ ከማርሴል ፡ ኮሄን ፡ ከጕዩዲና ፡ ከኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ከሞሬሲ ፡ ደኮፔ ፡ የዝርዝር ፡ (የቢብልዮግራፊ) ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ።

፬ኛ ፤ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ።

በለፈው፡ እንደ ፡ ተጻፈው፡ የውጪ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች፡ ለመንግሥታቸው፡ ወይም፡ ራሳቸውን ፡ የጸሐፊነት ፡ ዝንባሌያቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ከያለበት ፡ ጠቃቅሰው ፡ እንዳቅ ማቸው ፡ በየቋንቋቸው ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ መጻፋቸውን ፤ ተረድተ ናል ። በዚህም ፡ ጽሕፈታቸው ፡ በሌላው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚደርስበት ፡ የቦታና ፡ የሰው ፡ ስም ፡ የቀን ፡ አቆጣጠር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከራሱ ፡ ከታሪኩ ፡ ስሕተት ፡ ቢኖርበትም ፡ ጠቃሚነቱ፡ የተረጋገጠ፡ ነው። ዳሩ ፡ ግን፡ የሚጠቅመው፡ ለራሳቸውና፡ ቋንቋውን፡ ለሚ ያውቀው ፡ ወገን ፡ እንጂ ፡ በሙሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አብዛኛ ፡ ሕዝብ ፡ ሊጠቅም፡ አይ ችልም ።

በዚሁ፡ ዐይነት ፡ ያንዱን ፡ ንጉሥ፡ የላሊበላን፤ ወይም፡ የይኩኖ ፡ አምላክን፡ ታሪክ፡ ገምግሮ፡ የቀሩትን፡ ዝርዝራቸውን፡ ብቻ፡ ጽፎ ፡ የሚተወው፡ ከደንበኛው፡ ታሪክ፡ ይልቅ፡ መንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ የሚያበረክተው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቋንቋው ፡ ገንዘባችን ፡ ጸሐፊዎቹም ፡ አባቶቻችን ፡ ቢሆኑ ፡ የጽሑፉ ፡ አገልጋይነት ፡ ለነዚያው ፡ ለግዕዝ፡ ዐዋቂዎች፡ ብቻ፡ እንጂ፡ ለጠቅላላው፡ ሕዝብ፡ በሙሉ፡ እንደማያገለግል ፡ ርግጥ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የዛሬው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወጣቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ ታሪክ፡ ለማን በብ ፡ የጓጓ ፡ ሆኖ ፡ መደዳውን ፡ በማርኛ ፡ የተጻፈ ፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክ ፡ በማጣት፡ መቸ ገሩ ፡ ስለ፡ ተሰማኝ ፡ ዐቅሜ፡ በሚፈቅደው ፡ መጠን፡ ይኸንኑ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ፡ ተስፋ፡ አድርጌ ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥቱም ፡ ከውጪ ፡ አገር ፡ ጽሑፍም ፡ በቃል ፡ ከሚነገረውም ፡ አዋጥቼ ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ በዋናው ፡ ቋንቋችን ፡ በማርኛ ፡ ጽፌ ፡ ለሕዝብ ፡ ለመግ ለጽ ፡ አሰብሁ ።

(1) ሁሉም ፡ መጽሐፍ ፡ የታተመበት ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቍጥር ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ ፡ ብዬ ፡ የሠየም ምሁትን፡ መጽሐፍ፡ ካሳተምሁ፡ ወዲህ፡ ይኸን፡ ያሁኑን፡ መጽሐፍ፡ ለመጻፍ፡ ምኞት፡ ነበ ረኝ ። ስለዚህ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ፡ የሚረዳኝን፡ ደራሲው፡ ያልታወቀ፡ እያለፈ፡ የኢትዮጵያን፡ ታሪክ ፡ በግዕዝ ፡ የሚናገር ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ካነበብሁ ፡ በኋላ ፡ ባለፈው ፡ ስማቸውን ፡ የጠቀስኋቸውን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ የተጻፉትን ፡ የኩልቦንና ፡ የሳቤሊን፡ መጻሕ ፍት ፡ ስመለከት ፡ ቆየሁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሺሕ ፡ ፱፻፴፮ ፡ ዓ፡ ም ፡ ጽሕፈቱን ፡ ዠምሬ ፡ በሺሕ ፡ ፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጨረስሁ ። በዚሁ ፡ ዓመት ፡ አለቃ ፡ ነጋሽ ፡ ኃይሉ ፡ የእጁን ፡ ጽሑፍ ፡ ወስደው ፡ በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ ከተጻፉት ፡ ቅኔዎች ፡ እኔ ፡ ያላገኘኋቸውን፡ ካንዳ ንድ ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ጨምረው ፡ መለሱልኝ ፤ በዚህም ፡ ከልቤ ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

ከዚያም ፡ በመካከሉ ፡ በግዕዙ ፡ ቋንቋ ፡ እነአዛዥ ፡ ሲኖዳ ፡ ቀድሞ ፡ ጽፈውት፡ የቈ የውን ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኢኛሲዮ ፡ ጕዪዲ ፡ ሮማ ፡ ያሳተመውን ፡ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ አእላፍ፡ ሰገድን ፤ የዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድን ፡ የዐፄ ፡ በካፋ ፡ መሲሕ ፡ ሰገድን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፤ ቀጥሎም ፡ ወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚባለው፡ ጽፎ ፡ ያቈየውን ፡ ከንቲ ሮሲኒ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ በቀጥታ ፡ ተርጕሞ ፡ ያሳተመው ፡ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ መለክ፡ ሰገድን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት፡ ስላገኘሁት፡ ቀድሞ፡ የጻፍሑትን ፡ ከነዚሁ ፡ ከዳዲሶቹ፡ ጽሑፎች ፡ ጋር ፡ እያስተያየሁ ፡ የጻፍሑትን ፡ እንደገና ፡ አርሜ ፡ ሠራሁ ። የመዠመሪያው ፡ ጽሑፌ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ከታተመ ፡ በኋላ ፡ በሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ከአልቫሬድና ፡ ከዐረብ ፡ ፋቂህ፡ መጻሕፍት ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ እየተረጐምሁ ፡ ስለጨመርሁበት ፡ በፊተኛው ፡ ከታተመው ፡ ባሁኑ ፡ የታተመው ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ በዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጨመረው ፡ እስከ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ እንደታተመ ፡ በመካከሉ ፡ ወደ ፡ ፳ኤል ፡ አገር ፡ ለሥራ ፡ ታዝዤ ፡ ስለሄድሁ ፡ ባለሁበት ፡ አገር ፡ ያማርኛ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ባለመኖሩ ፡ በመልእክትም ፡ ማሳተሙን ፡ ለመቀጠል ፡ ስለአልተቻለ ፡ ከ ፲፰ ፡ ምዕራፍ ፡ የቀጠለው ፡ ጽሑፍ ፡ ያለው ፡ የፊተኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ላንባቢ ፡ አስገነዝባለሁ ።

ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ የሠራው ፡ ሁሉ ፡ ከመነቀፍ ፡ አለመዝለሉን ፡ ማወቅም ፡ ብቻ ፡ ሳይ ሆን፡ ታሪኩም ፡ እንዲጣራ ፡ የንግግሩ፡ ቅርጽና ፡ የጽሑፉ ፡ አቀማመጥም ፡ እንዲያምር ፡ ስል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ደግሜ ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ብጽፈው ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ሙሉና ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ እምነቴን ፡ አልጥልበትም ። ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ ለመሥ ራት ፡ መቻሉን ፡ ሳውቅ ፡ ለታሪክ ፡ ፍለጋና ፡ ለመጻፊያ ፡ የበቃ ፡ ጊዜ ፡ በማጣት ፡ እያወቅሁ ፡ ያለፍሁት ፡ ሞልቷል ። ቢሆንም ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ የወገኝን ፡ ታሪክ ፡ አስፈላ ጊነት ፡ ከመቼውም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ለሚያውቀው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ ወጣት ፡ ይኸው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚያገለግል ፡ እምነት ፡ አለኝ ።

ይኸንን ፡ መጽሐፍ ፡ ስጽፍ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሰፊው ፡ እጽፈዋለሁ ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ የማደርገውን ፡ ስለ ፡ ዘራችን ፡ አመጣጥና ፡ መንግሥታችን ፡ ከቆመበት ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ መጻፍ ፡ እስከ ፡ ዠመርሁበት ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ጽፌ ፡ የምዕራፍ ፡ መዠመሪያ ፡ አድርጌ ዋለሁ ። ይኸውም ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ላለው ፡ ለዋናው ፡

ጽሑፍ ፡ መያያዣ ፡ እንዲሆን ፡ ስል ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በዋናው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ሸዋ ፡ ሳሉ ፡ መንግሥታቸውን ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ዥመሩና ፡ በኋላም ፡ ከአዳሎችና ፡ ይልቁንም፡ ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ ያደረጉትን ፡ ጦርነት ፡ የመንግሥቱን ፡ መደብ ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ከተዛወረ ፡ ወዲህ ፡ የጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠረፍና ፡ ወደብ ፡ ከሆነው ፡ ከምጥዋ ፡ የቱርክን ፡ ገዥነት ፡ ለማስወገድ ፡ በጦርነትም ፡ በፖለቲክም፡ የጣሩትን ፡ እንደዚሁም ፡ነገሥታቱ፡ ርዳታም ፡ ሥልጣኔም ፡ ወዳጅነትም፡ ለማግኘት ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ፡ ያደረጉት ፡ ግንኙነት ፡ ከውሳጣዊው ፡ ጦርነታችን ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በመጠኑ ፡ ተገልጿል ።

ይህም ፡ ያሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ታትሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ከታተመው ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሚባለው ፡ መጽሐፍ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፤ (ከሺሕ ፡ ፫፻ ፡ ዓ፡ ም፡ ዠምሮ እስከ፡ ሺሕ ፡ ፱፻፴፫ ፡ ዓ፡ ም)፡ ድረስ ፡ ያራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ እንዲያስገኝ ፡ ነው ።

ተ፡ ጻ፡ መ፡

ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

ም ዕ ራ ፍ ፡ ፩ ።

ስለ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ።

ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በፊት ፡ ለነገሡት ፡ ነገሥታት በዘመናቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ ከዔ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል በሚባለው ፡ በ፩ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ። በየጊዜው ፡ በየቋንቋው ፡ የተጻፈው ፡ ያገራችንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚያስረዳን ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ድንግል ፡ ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ልጅ ፡ የዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ። ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ቅድም ፡ አያታቸው ፡ ናቸው ።

ዐፄ ፡ ናዖድ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ገዝተው ፡ ሲሞቱ ፡ በሺ፫፻ ፡ ዓ. ም. ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ገና ፡ በ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ወጣት ሳሉ ፡ ነገሡ ። ስመ መንግሥታቸውም ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ተባለ ። ወናግ ፡ ማለት ፡ በውጋዴን ፡ ቋንቋ ፡ አንበሳ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የግዕዙን ፡ ወይም ፡ የአማርኛውን ፡ ቋንቋ ፡ «አንበሳ ፡ ስገድን» ፡ ትተው ፡ በውጋዴን (በሱማሌ) ቋንቋ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ የተባሉበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በይፋትና ፡ በፈጠጋር ፡ ያለውን ፡ ግዛት ፡ የሚያውኩ ፡ ያዳልና ፡ የሱማሌ ፡ ተወላጆች ፡ ስለሆኑ ፡ እነርሱ ፡ በሚያውቁት ፡ ቋንቋ ፡ ተሰይሞ ፡ ለማስፈራራት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ የነርሱ ፡ ገዥ ፡

ጭምር ፡ መሆናቸውን ፡ ለማስታወቅ ፡ ይሁን ፤ ወይም ፡ ከባታቸው ፡ ከዐፄ ፡ ናዖድ ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ (አንበሳ ፡ ሰገድ) ፡ በትርጉም ፡ ቢቀር ፡ ባጠራር ፡ እንዲለያይ ፡ ይሁን ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም ። ወደፊት ፡ እንደሚገኘው ፡ ዐፄ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ራሳቸው ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥና ፡ ለሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ እኘህ ፡ ንጉሥ በጻፉዋቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ላይ ፡ «ስሜ ፡ ልብነ (ዕጣን) ድንግል ፡ ትርጓሜው ፡ ድንግል ፡ ያበራችለት ፡ ይኸም ፡ ስም ፡ የተሰጠኝ ፡ ቅድስት ፡ ጥምቀትን ፡ በተቀበልሁበት ፡ ቀን ፡ ነው ፤ በነገሥሁ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ዳዊት ፡ ተባልሁ ፡ »ስለሚል ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ሆኖ ፡ በሁለት ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ወጣት ፡ ስለነበሩ ፡ በመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ እናታቸው ፡ እቴጌ ፡ ናዖድ ፡ ሞገሳ ፡ የቅድም ፡ አያታቸው ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ በሞግዚትነት ፡ ያግዟቸው ፡ ነበር ፡ ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፺ ፡ ላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ እነራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እነራስ ፡ ደገልሃን ፡ የቀሩትም ፡ ታላላቅና ፡ ታናናሽ ፡ መኳንንት ፡ የመንግሥቱ ፡ የሥልጣንና ፡ የሥራ ፡ ተካፋይ ፡ እንደሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የመገመሪያ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ የሰላምና ፡ የደስታ ፡ ቢሆንም ፡ የመጨረሻ ፡ ጊዜያቸው ፡ በግራኝ ፡ መነሣት ፡ ምክንያት ፡ የጦርነት ፡ የሁከት ፡ የመከራና ፡ የስደት ፡ ጊዜ ፡ ሆኖባቸዋል ። ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በቀጥታም ፡ በእቴጌ ፡ እሌኒ ፡ በኩልም ፡ ቢወዳጁ ፡ የገመሩት ፡ ወዳጅነት ፡ ለጊዜው ፡ ጠቡን ፡ አጣደፈው ፡ እንጂ ፡ ከወረራ ፡ ሊያድናቸው ፡ አልቻለም ። ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ በሚቀጥሉት ፡ ምዕራፎች ፡ በሰፊው ፡ እናገኛለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ስለ ፡ ፖርቱጋል ፡ መንግሥት ።

የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በምዕራብና ፡ በደቡብ ፡ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ፤ በምሥራቅና ፡ በሰሜን ፡ ከኤስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ ይዋሰናል ። የጥንት ፡ ስሙ ፡ ሉዚታኒ ፡ ነው ፡ በመገመሪያም ፡ ባገሪቱ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝቦች ፡ (ሴልቶ ፡ ኢቤሪክ) ፡ የሚባሉ ፡ የህንዶ-ኤውሮፔዎ ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ በኋላ ፡ ወደ ላቲንነት ፡ በልማድና ፡ በኑሮ ፡ በሃይማኖትም ፡ የተለወጡ ፡ ናቸው ። ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ደረሰው ፡ የፖርቱጋል ፡ ሕዝብ ፡ በጀርመንና ፡ በኖርማንዲ ፡ በሮማውያንና ፡ በዐረቦች ፡ ሞሬ ፡ (ማውሪታኒ) ፡ በሚባሉ ፡ በአፍሪካ ፡ ሰሜን ፡ ሕዝብና ፡ በዕብራውያንም ፡ የተቀያየጠ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ሰፊ ፡ ዘመን ፡ በሮማውያን ፡ ስለ ፡ ተገዙ ፡ በዘርም ፡ በልማድም ፡ አብዛኛውን ፡ ወደ ፡ ላቲንነት ፡ ተለውጠዋል ። የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ ፡ በምስተኛውና ፡ በስምንተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መከከል ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እየተከታተለ ፡ ቢዚጎትና ፡ ስዌብ ፡ የሚባሉ ፡ የጀርመኖች ፡ ቀጥሎም ፡ የዐረቦች ፡

ወረራ ፡ ደርሶባቸዋል ። ባስረኛው ፡ መቶ ፡ ዓ፡ ም፡ ግን ፡ አስቱሪዮ ፡ የሚባሉት ፡ የክር ስቲያን ፡ ወገኖች ፡ እስላሞቹን ፡ አጥፍተው ፡ ሊስቦን ፡ ገብተው ፡ ገዥ ፡ ሆነው ፡ መንግሥታቸውን ፡ አቋቋሙ ። ከዚያ ፡ ከ፲፱ ፡ እስከ ፡ ፲፩ ፡ መቶ ፡ ዓ፡ ም፡ ድረስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ የቡርጎኝ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ ሲገዛው ፡ ቆይቶ ፡ በኋላ፡ ሔቢዝ ፡ ለተባለው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አሳለፈው ። በነዚህ ፡ መሪነት ፡ ጊዜ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ባ፲፭ኛውና ፡ ባ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የፖ ርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በሌላው ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ በባሕርና ፡ በመርከብ ፡ ኃያል ፡ ሆነ ።

በዚህ ፡ ባ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የቱርክ ፡ የመስኮብ ፡ የጀርመን ፡ የእንግሊዝ ፡ የፈረንሳዊ ፡ የኤስፓኝ ፡ መንግሥታት ፡ እንደ ፡ ኃያላን ፡ መንግሥታት ፡ መቆጠራቸው ፡ አልቀረም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የፖርቱ ጋል ፡ መንግሥት ፡ በሌላው ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ በመርከብና ፡ አገር ፡ በመያዝ ፡ ከቀሩት ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ። የቀሩት ፡ የኤውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ እዚያው ፡ እየወ ሰናቸው ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ መሬትና ፡ በሚያዋስኑአቸው ፡ ታናናሽ ፡ መንግሥ ታት ፡ ላይ ፡ ገዥነታቸውን ፡ ለማጽደቅ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ሲጣሉ ፡ ገሚሶችም ፡ ሃይማኖትን ፡ ለማሻሻል ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲጨቃጨቁ ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግ ሥት ፡ ግን ፡ ደኅና ፡ ደኅና ፡ መርከቦች ፡ አዘጋጅቶ ፡ እየላከ ፡ ከመንግሥቱና ፡ ከኤ ውሮፓ ፡ ርቆ ፡ የሚገኘውን ፡ ያሜሪካንን ፡ የእስያን ፡ ያፍሪካን ፡ አገሮች ፡ ያስመረ ምር ፡ ነበር ። መርማሪዎቹም ፡ እነቫስኮ ፡ ደጋማ ፡ እነፔሬዝ ፡ እነአንድራድ ፡ እነካ ብራል ፡ በመርከብ ፡ እየሔዱ ፡ ለመከላከል ፡ ጉልበት ፡ የሌለውንና ፡ በጠባዩ ፡ ሀብት ፡ ያለበትን ፡ አገር ፡ መርምረው ፡ ሲመለሱ ፡ መንግሥቱ ፡ ወታደር ፡ በመር ከብ ፡ እየላከ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ ያዘ ።

እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፭፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕ ረት ፡ ፒየር ፡ አልቫሬዝ ፡ ካብራል ፡ የተባለው ፡ የፖርቱጋል ፡ መኰንን ፡ በትልቅ ፡ መርከብ ፡ ሔዶ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ለቀረው ፡ ዓለም ፡ ያልታወቀውን ፡ የብራዚልን ፡ አገር ፡ አስገበረና ፡ በፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ስም ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ አደረገው ። ከዚያም ፡ አገር ፡ በተገኘው ፡ ወርቅ ፡ መንግሥቱ ፡ ሀብታም ፡ ሆነ።እንደዚሁም፡የመዠመሪያ ፡ የን ጉሥ ፡ እንደራሴ ፡ የተባለው ፡ ፍራንቼስኮ ፡ ዳልሜዳ ፡ ወደህንድ ፡ አገር ፡ ሔዶ ፡ አገሩን ፡ ያዘ ። ከተማውንም ፡ በጐአ ፡ አድርጎ ፡ ህንድንም ፡ የፖርቱጋል ፡ የቅኝ ግዛት ፡ አደረገና ፡ አገረ ፡ ገዥውም ፡ የንጉሥ ፡ እንደራሴ ፡ ይባል ፡ ዠመር ። ከዚ ያም ፡ በትልቁ ፡ ውቅያኖስ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ደሴቶች ፡ ኑቤል ፡ ጉኔንና ፡ ዛሬ ፡ ፊሊፒን ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ በየጊዜው ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ አስገበራቸው ። በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያም ፡ እነኮቪልሐኦ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በአፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመን ፡ መጥተው ፡ እንደመረመሩትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በነሱ ፡ አጠራር ፡ የቄሱ ፡ የዮሐንስ ፡ መንግሥት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ አውርተው ፡ እንደነበረ ፡ ሌላ ፡ የፖርቱጋል ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ በአፍሪካ ፡ ድን

በር ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ላይም ፡ እየተመላለሰ ፡ አስቀድሞ ፡ ከያዙት ፡ ከቱርኮች ፡ ከግብጾች ፡ እየተዋጋ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተሸነፈ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እያሸነፈ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተመላለሰ ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደጠቀስነው ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ታላቅነት ፡ በሌላው ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ታወቀ ፡ እንደዚሁም ፡ ፩ኛ ፡ ትልቅ ፡ መንግሥት ፡ መሆኑ ፡ ፪ኛ ፡ ክርስቲያን ፡ መሆኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባሉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ እየተነገረ ፡ ዝናው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ መሰማት ፡ ቻለ ።

ይልቁንም ፡ እላይ ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ ፔድሮ ፡ ደኮቬልሐኦ ፡ ዐፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ የታወቀና ፡ ተስፋ ፡ የሚደረግበት ፡ ሆነ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ለመንግሥቱ ፡ እንደራሴ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ የነበሩት ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ ንግሥት ፡ እሌኒና ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የዝምድና ፡ ደብዳቤ ፡ ከፖርቱጋሉ ፡ ንጉሥ ፡ ከአማኑኤል ፡ በኋላም ፡ ከተከታዩ ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋር ፡ መጻጻፍ ፡ የጀመሩት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ ከተጻጻፉም ፡ በኋላ ፡ በግራኝ ፡ ወረራ ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የረዱት ፡ ፖርቱጋሎች ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ነው ። እርዳታውም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የክርስቲያንነት ፡ ጉዳይ ፡ ቢኖርበትም ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ የግዛት ፡ መስፋፋትም ፡ አሳብ ፡ እንደነበረበት ፡ ባለፈው ፡ ገልጸናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ የአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ ድጋፍ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሲያገኝ ፡ ተቀናቃኝ ፡ የሆኑት ፡ የሐረርና ፡ የአዳል ፡ እስላሞች ፡ ደግሞ ፡ በበኩላቸው ፡ የእስላም ፡ መንግሥት ፡ የሚሆን ፡ ደጋፊ ፡ ከውጭ ፡ አላጡም ። እነዚህም ፡ መጀመሪያ ፡ የዐረብ ፡ ቀጥሎ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው ።

እንዲያውም ፡ ክርስቲያኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከአውሮፓ ፡ ምሥራቅ ፡ እርዳታ ፡ ሲጠብቅ ፡ የአዳሎቹና ፡ የሱማሌዎቹ ፡ መሪዎች ፡ ግን ፡ ከዋናው ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥትና ፡ ይልቁንም ፡ የርሱ ፡ ጥገኛና ፡ ተገዥ ፡ ከሆኑት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከሚያዋስኑት ፡ ከግብፅ ፡ ከየመንና ፡ ከዘቢድ ፡ ፓሻዎች ፡ በቅርብ ፡ እርዳታ ፡ በማግኘታቸው ፡ እያደር ፡ አይለው ፡ በመጨረሻም ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ መሪነት ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ መቻላቸውን ወደፊት ፡ በዝርዝር ፡ ልንመለከት ፡ ነው ።

ስለዐረቦች ፡ አነሣሥ ፡ ስለቱርኮች ፡ ገናንነት ፡ ከአውሮፓ ፡ መንግሥታት በኢየሩሳሌም ፡ ስለመዋጋታቸውና ፡ ስለማሸነፋቸው ፡ በመጨረሻም ፡ የቈስጥንጥንያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በ፲፬፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ አሸንፈው ፡ ከአውሮፓ ፡ ምሥራቅና ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ በፍጹም ፡ የክርስቲያንን ፡ መንግሥት ፡ አጥፍተው ፡ የራሳቸውን ፡ ግዛት ፡ እንደዘረጉ ፡ በመጀመሪያው ፡ መጽሐፌ ፡ ከምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡ እስከ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፮ ፡ ድረስ ፡ በ፪ኛው ፡ መጽሐፌ ፡ በምዕራፍ ፡ ፵፪ ፡ አመልክቻለሁ ።

በመጨረሻም ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ የአውሮፓን ፡ ምሥራቅ ፡ የአፍሪካን ፡ ሰሜን ፡ ይዞ ፡ ካስገበረ ፡ በኋላ ፡ ወደየመንም ፡ ወደኑብያም ፡ ገብቶ ፡ ሲመሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ወደሆነው ፡ ወደሱዋኪም ፡ ደርሶ ፡ ቀጥሎም ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ምጥዋን ፡ ያዘ ። ፖርቱጋሎችም ፡ ሕንድን ፡ ከያዙ ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙሪያ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ ከቱርክ ፡ ወታደር ፡ እየተሻሙ ፡ አገር ፡ የሚይዙበት ፡ ከኢትዮጵያም ፡ ጋር ፡ እንከቢልሐአን ፡ እየላኩ ፡ የዝምድናና ፡ የፖለቲካ ፡ ወዳጅነት ፡ የወጠኑበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ ቱርክ ፡ ወይም ፡ በቱርክ ፡ ጥገኝነት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ግብፆችና ፡ አረቦች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሉትን ፡ እስላሞች ፡ በመደገፍ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መንግሥት ፡ ለመገልበጥ ፡ ሲመኙ ፡ የፖርቱጋል ፡ ወታደሮች ፡ ደግሞ ፡ በሩቅ ፡ ዝናውን ፡ ሲሰሙት ፡ የኖሩትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ አግኝተው ፡ የዚህን ፡ መንግሥት ፡ መሣሪያነት ፡ ካገኙ ፡ በኋላ ፡ ግዛታቸውን ፡ በአፍሪካ ፡ ዙሪያ ፡ ለማስፋፋት ፡ ምኞት ፡ ነበራቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የነርሱ ፡ አገር ፡ ከመራቁ ፡ ስለአፍሪካም ፡ ግዛት ፡ ያላቸው ፡ ምኞት ፡ ከመቀዝቀዙ ፡ የተነሣ ፡ በተነከሱት ፡ ወዳጅነት ፡ ምክንያት ፡ ክርስቲያናዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ብቻውን ፡ በእስላሞቹ ፡ ሕብረት ፡ ፊት ፡ እንዲሠዋ ፡ አደረጉት ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

የኢትዮጵያና ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ግንኙነት ፡ —እቴጌ ፡ ዕሌኒ ፡ በማቴዎስ እጅ ወደፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አማኑኤል ፡ የላኩት ፡ ደብዳቤ ፡ —የፖርቱጋል ፡ ንጉሥና ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የላኩዋቸው ፡ መልክተኞች—የተደረገላቸው ፡ አቀባበል ፡ መልክተኞቹ ፡ የተሰማቸው ፡ ቅርታና ፡ የመጨረሻው ፡ ስምምነት ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ መደቡ ፡ ከላስታ ፡ ወደሸዋ ፡ ከዞረ ፡ ወዲህ ፡ ነገሥታቱ ፡ እነአምደ ፡ ጽዮን ፡ እነአፄ ፡ ይስሐቅ ፡ እነጺዜ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ በየጊዜው ፡ ከአዳልና ፡ ከይፋት ፡ የእስላም ፡ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያደረጉትን ፡ የማሰመን ፡ ጦርነት ፡ በ፪ኛው ፡ መጽሐፌ ፡ ተመልክተናል ።

ይኸንንም ፡ ጦርነት ፡ ለማስቀረት ፡ ነገሥታቱ ፡ እነበእደ ፡ ማርያም ፡ እነናዖድ ፡ ከደዋሮው ፡ ከአዳሉ ፡ ባላባቶች ፡ ቢጋቡም ፡ የጦርነቱን ፡ ሁካታ ፡ ሊዘጋው ፡ አልቻለም ። ደዋሮው ፡ ሲገዛ ፡ አዳሉ ፡ እምቢ ፡ ባይ ፡ ነው ፡ አዳሉ ፡ ሲሸነፍ ፡ ሱማሌው ፡ ይነሣል ። ስለዚህ ፡ የመንግሥቱ ፡ ዋና ፡ ሞግዚት ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ለአዳሎችና ፡ ለሱማሌዎች ፡ መሣሪያ ፡ እየሰጡ ፡ ጉልበት ፡ የሆኗቸው ፡ የግብጽና ፡ የአረብ ፡ አገሮች ፡ መሆናቸውን ፡ ስለሚያውቁት ፡ ወደነዚሁ ፡ አገሮች ፡ የወዳጅነት ፡ ደብዳቤ ፡ እየተላላኩ ፡ በየ

ጊዜው ፡ የሚሆነውን ፡ ግጭት ፡ አቅልለውት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ አጭር ፡ ታሪኩንና ፡ ፍጻሜውን ፡ ወደፊት ፡ የምንመለከተው ፡ ይማም ፡ ማኅፉዝ ፡ የዘይላ ፡ ሹም ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ፈጠጋር ፡ እስከ ፡ ደዋሮ ፡ እስከ ፡ ይፋት ፡ ድረስ ፡ እየመጣ ፡ አገር ፡ እየዘረፈ ፡ በየጊዜው ፡ ስላስቸገረ ፡ የእርሱ ፡ ደጋፊና ፡ የሃይማኖት ፡ አንድነት ፡ ካላቸው ፡ አገሮች ፡ ከግብጽና ፡ ከዐረብ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ በደብዳቤ ፡ መዛመድ ፡ መሠረት ፡ እንደማይሆን ፡ ተረዳት ።

በዚህ ምክንያት ፡ የነዚያን ፡ ወገን ፡ ትተው ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ መዛመድ ፡ የሚሻል ፡ መሆኑን ፡ ገምተው ፡ አሳባቸውን ፡ ወሰኑ ። የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ባንድ ፡ ወገን ፡ የቱርኮቹና ፡ የዐረቦች ፡ የሃይማኖትም ፡ የግዛትም ፡ ባላንጣ ፡ በመሆኑ ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ካቶሊካዊ ፡ ቢሆን ፡ በጠቅላላው ፡ ክርስቲያን ፡ በመሆኑ ፡ የሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊያዛምደው ፡ ምክንያትና ፡ መንገድ ፡ መስጠቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ደግሞ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ባፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መጥቶ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ በክብር የተቀመጠው ፡ ፔድሮ ፡ ደ ፡ ኮቪልሐኦ ፡ የዚህኑ ፡ የግንኙነቱን ፡ መንገድ ፡ የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡ ታላቅነቱንም ፡ ክርስቲያንነቱንም ፡ ከዐረቦች ፡ ጋር ፡ ያለውንም ፡ ጠብ ፡ እያስረዳ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ሳይደለድለው ፡ አልቀረም ። የርሱንም ፡ አሳብ ፡ የሚደግፉ ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከሶርያ ፡ ከአርመንያ ፡ የመጡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጆች ፡ የሃይማኖትም ፡ የመንግሥትም ፡ ሥራ ፡ ለቤተ መንግሥቱም ፡ ለግላቸውም ፡ የሚሠሩ ፡ ነበሩ ።

ስለዚህ ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ የጀመሩትን ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ሳያቋርጡ ፡ በምሥጢር ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ለመወዳጀት ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ ደብዳቤ ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀመሩ ። ይኸንንም ፡ የሚያስረዳን ፡ መላክተኛው ፡ ወደፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ሄዶ ፡ ሳይመለስ ፡ በመካከሉ ፡ እንደኤሙ ፡ አቆጣጠር ፡ በ፲፭፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እንደእስላሞች ፡ የሂጅራ ፡ ቍጥር ፡ ፱፻፳፫) ፡ ላይ ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ ደብዳቤ ፡ ለማመሉክ ፡ ከንሱል ፡ ጉሬ ፡ መላካቸው ፡ ነው ። የበሴት ፡ ረኔን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵፩-፩፻፵፪ ፡ ተመልከት ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ያዘጋጁትን ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ፔድሮ ፡ ደ ፡ ኮቪልሐኦ ፡ እንዳይወስድ ፡ ባጠገባቸው ፡ እንደማያዝም ፡ ባይሆን ፡ ብዙ ፡ ሐሳብና ፡ ምክር ፡ እየሰጠ ፡ የሚያጽናና ፡ ስለሆነ ፡ እርሱን ፡ ትተው ፡ ለመልእክቱ ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባል ፡ የአርመን ፡ ተወላጅ ፡ መረጡ ። እርሱም ፡ የተመረጠበት ፡ ምክንያት ፡ ክርስቲያንና ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፤ ታማኝ ፡ ከመሆኑ ፡ በላይ ፡ በንግድ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ፡ ወደግብጽ ፡ ወደሕንድ ፡ እየተመላለሰ ፡ አገር ፡ በማወቁ ፡ ነው ። ፪ኛም ፡ ዜግነቱ ፡ የቱርክ ፡ ስለሆነ ? ፡ በየበሩ ፡ በየጠረፉ ፡ የእስላሞቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደውጭ ፡ አገር ፡ የሚመላለሰውን ፡ እየፈቱ ፡ በማሠር ፡ በመፍታት ፡ የሚያጸኑትን ፡ ችግር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አይፈጽሙበትም ፡ ተብሎ ፡ የታሰበ ፡ ይመስላል።

ስለዚህ ፡ ማቴዎስ ፡ እንደኤው ፡ ቁጥር ፡ በ፲፭፻፲ ፡ (እንደ ፡ ኢ.ት ፤ ቁጥር ፡ ፲፭
፻፪) ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከንግሥት ፡ እሌኒ ፡ ደብዳቤውን ፡ ይዞ ፡ ለጉዞ ፡ ተዘጋጀ ። ከርሱም ፡ ጋር፡
አብሮ ፡ የሄደ ፡ ፩ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመንገድ ፡ ሞተ ፡ ይባላል ። ማቴዎስ ፡
ግን ገጹ ፡ በረከቱን ፡ ይዞ ፡ ወደሕንድ ፡ ተጓዘ ። ወደሕንድ ፡ መሄዱ ፡ ወደሊስቦን ፡ የሚ
መላለስ ፡ መርከብ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ግዛታቸው ፡ ከነበረው ፡ ከሕንድ ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡
ዘንድ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ስለማይገኝ ፡ ይመስላል ። ሕንድ ፡ ግዛት ፡ በተለይ ፡ ዳቡል ፡ እሚባ
ለው ፡ ከተማ ፡ ሲደርስ ፡ ቱርኮቹን ፡ በመፍራት ፡ አከሄዱ ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ እንጂ ፡
እንደ ፡ ንጉሥ ፡ መላክተኛ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ፤ የፖርቱጋሉን ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ አግ
ኝቶ ፡ ወደሊስቦን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ተልከ ፡ የሚሔድ ፡ መሆኑን ፡
ገልጾ ፡ ማናቸውንም ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርግለት ፡ ጠየቀው ። አገረ ፡ ገዥው ፡ የተላከ
ህበትን ፡ ጉዳይ ፡ ግለጽልኝ ፡ ቢለው ፡ አልችልም ፡ አለው ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ በዚሁ ፡
ማቴዎስን ፡ ተቀይሞ ፡ የቱርኮች ፡ ሰላይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ አሠረው ።
የዚህን ፡ ወሬ ፡ በሕንድ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ የሚቀመጠው ፡ ዋናው ፡ የንጉሡ ፡ እንደ
ራሴ ፡ አልቡኬርክ ፡ ሰምቶ ፡ አስፈትቶ ፡ ወደጐአ ፡ ወሰደው ። እርሱም ፡ እንደዚ
ያው ፡ እንዳገረ ፡ ገዥው ፡ መላክተኛው ፡ የያዘውን ፡ ጉዳይ ፡ ለማወቅ ፡ ፈልጎ ፡ ማና
ቸውንም ፡ የሚያስፈልግህን ፡ እርዳታ ፡ ጨምሬ ፡ ወደሊስቦን ፡ እልክሃለሁና ፡ ለኔ ፡
ንገረኝ ፡ ቢለው ፡ ማቴዎስ ፡ የተላክሁት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የምሥጢር ፡ ነገር ፡ ስለሆነ፡
ለራሱ ፡ ለንጉሡ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማንም ፡ አልነግርም ፡ ብሎ ፡ እምቢታውን ፡
ስላጸና ፡ የንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ ሰሞኑን ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ነሥቶት ፡ ሰነበተ ፡ ይባላል ።
ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመጨረሻ ፡ እንደራሴውም ፡ በዚያ ፡ ያሉት ፡ የፖርቱጋል ፡ መኳን
ንትና ፡ ቀሳውስት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርስቲያንነት ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡
ጋር ፡ ሊገጥመር ፡ የታሰበውን ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ በመረዳት ፡ በመጨረሻ ፡
መላክተኛውን ፡ በክበሬታ ፡ ይዘው ፡ አስተናግደው ፡ ራሳቸው ፡ በመርከብ ፡ አሳ
ፍረው ፡ ወደፖርቱጋል ፡ ሰደዱት ። ማቴዎስም ፡ ማናቸውንም ፡ የጉዞ ፡ ችግር ፡
ታግሦ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በለቀቀ ፡ በ፫ኛው ፡ ዓመት ፡ እዋናው ፡ ከተማ ፡ ሊስቦን ፡ ደረ
ሰና ፡ ከእቴጌ ፡ እሌኒ ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤና ፡ ገጹ ፡ በረከት ፡ ትልቁና ፡ ዕድ
ላሙ ፡ ለሚባለው ፡ ለንጉሡ ፡ ለአማኑኤል ፡ አስረከበ ።

ትክክለኛውን ፡ የደብዳቤ ፡ ቅጅ ፡ ለማግኘት ፡ ችግር ፡ ነው ። በፖርቱጋል ፡
ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አርሺብ ፡ መኖር ፡ አለመኖሩንም ፡ አላረጋገጥም ። ነገር ፡ ግን ፡
ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ወደፖርቱጋል ፡ ተተርጉሞ ፡ ቀጥሎ ፡ ከፖርቱ
ጋል ፡ ወደላቲን ፡ ከላቲን ፡ ወደቶስካን ፡ ከቶስካን ፡ ወደቀድሞ ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ ተተ
ርጉሞ ፡ ትክክለኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ገርን ፡ ቲምፖራል ፡ የሚባል ፡ ባሳተመው ፡ ላይ ፡
ስለሚገኝ ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ እነሆ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ተርጕሜዋለሁ ።

እሌኒ ፡ ንግሥት ፡ ለአማኑኤል ፡ የጻፉት ፡ እንደዘመኑ ፡ በግዕዝ ፡
መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። አማርኛ ፡ የሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡ መሆኑ ፡ ሳይቀር ፡ በዚ
ያን ፡ ዘመን ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በጐንደር ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታቶቻችን ፡ ደብ
ዳቤ ፡ የሚጽፉት ፡ በግዕዝ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ግዕዝኛ ፡ ደብዳቤ ፡ በስ
ፊው ፡ እንዳመለከትነው ፡ በፈረንጅ ፡ ግዕዝኛ ፡ አውቀት ፡ ከቋንቋ ፡ ወደቋንቋ ፡ ሲተ

ረጎም ፡ ከአሳብ ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ ከንግግር ፡ ቅርጽ ፡ መዝነፉ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። የሆን ፡ ሆኖ ፡ ከቀድሞው ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ እኔ ፡ እንደዚህ ፡ ብዬ ፡ ተርጉሜዋለሁ ።

«በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ። በቤተ ፡ ልሔም ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ የተወለደው ፡ የጌታችን ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደኅንነት ፡ ጸጋና ፡ በረከት ፡ በጣም ፡ ለተወደደው ፡ በጣም ፡ ክርስቲያን ፡ ለሆነው ፡ ወንድማችን ፡ አማኑኤል ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ የባሕር ፡ ገዥ ፡ ያረመኔዎችና ፡ የጨከኞች ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌታችን ፡ መልካም ፡ ሀብትና ፡ አሸናፊነትንም ፡ በጠላቶችህ ፡ ላይ ይስጥህ ። የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አዳኝነት ፡ በበሠሩት ፡ በአራቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ በቅዱስ ፡ ማቴዎስ ፡ በቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ በቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ በቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ጸሎት ፡ መንግሥትህም ፡ በየአለበት ፡ ያለው ፡ ግዛትህም ፡ ይስፋ ፡ ይርዘም ። ከትልቁ ፡ የጦር ፡ አለቃህ ፡ ከትሪስታን ፡ ዳ ፡ ኩኛ ፡ ዘንድ ፡ አንዱ ፡ ዮሐንስ ፡ (GIOVANI) ቄስ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ አንዱም ፡ እንደሱ ፡ የመሰለ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባል ፡ ጎሜዝ ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመ ፡ ሁለት ፡ መላክተኞች ፡ ወደኛ ፡ መጥተው ፡ ስንቅና ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ መጠየቃቸውን ፡ እናስታውቅሃለን ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቄስ ፡ ስንልክ ፡ በሚባርከን ፡ በፓትሪያርክ ፡ ማርቆስ ፡ ፈቃድ ፡ በአገልግሎቱ ፡ ወንድማችን ፡ የሆነውን ፡ መላክተኛችንን ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባለውን ፡ ወዳንተ ፡ ላክሁት ። ፓትሪያርክ ፡ ማርቆስም ፡ የኛና ፡ የአገራችን ፡ ሁሉ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ የቅድስት ፡ ሥላሴና ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሃይማኖት ፡ ዓምድ ፡ ናቸው ። እስከ ፡ ሚያስፈልገው ፡ ድረስ ፡ ስንቅም ፡ ወታደርም ፡ ለመላክ ፡ የተዘጋጀን ፡ መሆናችንን ፡ በሕንድ ፡ ስለ ፡ አዳኛችን ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሚዋጋው ፡ የጦር ፡ አለቃህ ፡ እንዲነግረው ፡ መላክተኛችንን ፡ ማቴዎስን ፡ አዝነዋል ። ምክንያቱም ፡ የካይሮ ፡ መስፍን ፡ ሱልጻ (ጣ) ን ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ሰብስቦ ፡ ወታደሮችህን ፡ ሊወጋ ፡ አስቡዋል ማለትን ፡ ስለሰማን ፡ ነው ። ይኸም ፡ እንደሰማነው ፡ በሕንድ ፡ ያሉት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ያደረጉብትን ፡ ለመበቀል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

በመጨረሻ ፡ በርሱ ፡ (በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡) የማያምኑት ፡ ወደቀንበሩ ፡ እንዲገቡ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድስናው ፡ እነዚህን ፡ የጦር ፡ አለቆችህን ፡ በበለጠና ፡ በተሻለ ፡ እየጠበቀ ፡ ዘወትር ፡ ያበርታቸው ። በእነዚህም ፡ አረመኔዎች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ልከን ፡ በባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ወይም ፡ በመካ ፡ መኼጃ ፡ ላይ ፡ በባብኤል ፡ ሜንደል ፡ (ባብ ፡ ኤል ፡ መንደብ ፡) ላይ ፡ ወይም ፡ ወደዚዳም ፡ ወደብ ፡ ወይም ፡ ወደቶር ፡ እንዲጠባበቁ ፡ ለማድረግ ፡ ችለናል ። ምክንያቱም ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቃብር ፡ (ኢየሩሳሌም ፡) የምንልከው ፡ ስለትና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ በውሾች ፡ እንዳይዋጥ ፡ እነዚህ ፡ አረመኔ ፡ እስላሞች ፡ ከምድር ፡ ገጽ ፡ በፍጹም ፡ እንዲጠፉ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ እናቱ ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ በፈረንጅ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ተወልዶ ፡ እስላሞችንና ፡ አረመኔዎችን ፡ ከዓለም ፡ ፊት ፡ ያጠፋቸዋል ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡ ተናግረው ፡ የነበረው ፡ የተስፋ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ በውነት ፡ እንመለከታለን ።

መላክተኞችን ፡ ማቴዎስ ፡ የሚነግርህን ፡ ሁሉ ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ እንደነገርንህ ፡ ቆጥረህ ፡ እመነው ። በቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ካሉት ፡ ከታላላቆቹ ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ እርሱ ፡ ስለሆነ ፡ ወደአንተ ፡ ለመላክ ፡ መረጥነው ። . . . ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የመጡት ፡ መልክተኞቻችሁ ፡ ጉዳያችንን ፡ የምንፈልገውን ፡ ያህል ፡ አልገለጹልህም ፡ ብለን ፡ ጠርጥረናል ።

በኢየሩሳሌም ፡ አዳኛችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእርግጥ ፡ ከተሰቀለበት ፡ መስቀል ፡ (ግማደ ፡ መስቀል ፡) ላይ ፡ የተሠራውን ፡ አንድ ፡ መስቀል ፡ በመላክተኞችን ፡ እጅ ፡ ልከንልሃል ። ከመጣልን ፡ ግማደ ፡ መስቀል ፡ ሁለት ፡ መስቀል ፡ አሠርተን ፡ አንዱን ፡ ለኛ ፡ አስቀርተን ፡ አንደኛውን ፡ በብር ፡ አንበር ፡ አሥረን ፡ ለአንተ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ለመላክተኞችን ፡ ሰጠነው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝህ ፡ ቢሆን ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁን ፡ ለወንዶች ፡ ልጆቻችን ፤ ወንዶች ፡ ልጆቻችሁን ፡ ለሴት ፡ ልጆቻችን ፡ ሰጥታችሁን ፡ በሕግ ፡ ቢጋቡ ፡ ለኛ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘንና ፡ ለሁላችንም ፡ የወንድማማችነት ፡ ዝምድና ፡ የሚመሠርት ፡ ትልቅ ፡ ጥቅም ፡ ነው ። ለዛሬውም ፡ ለወደፊቱም ፡ በጋብቻ ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ መዛመድን ፡ እንወዳለን ።

በተረፈ ፡ የአዳኛችንና ፡ የቤዛችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ደህንነትና ፡ ጸጋ ፡ ባንተና ፡ በልጆችህ ፡ በቤተ ፡ ሰቦችህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይውረድ ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተነገረው ፡ በቀር ፡ የኛን ፡ የጦር ፡ ወታደሮችንና ፡ ኃይላችንን ፡ ከናንተ ፡ ኃይል ፡ ጋር ፡ ብናደባልቀው ፡ እግዚአብሔር ፡ የተጨመረበት ፡ እንደሆነ ፡ የቅድስት ፡ ሃይማኖታችን ፡ ጠላት ፡ የሆኑትን ፡ አረመኔዎች ፡ ለማጥፋት ፡ በቂ ፡ መሆኑን ፡ እናስታውቅሃለን ። አገራችንና ፡ ግዛታችን ፡ የሚገኘው ፡ ከባሕር ርቆ  በየብስ ፡ (መሬት) ፡ ላይ ፡ ስለሆነና ፡ ምንም ፡ ወደብ ፡ ስለሌለን ፡ የባሕር ፡ ጦር ፡ ለመደራጀት ፡ አልቻልንም ። መርከበኛ ፡ ወታደርም ፡ የለንም ። ስለዚህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሥጋና ፡ ይግባውና ፡ በሌላውና ፡ እንደዚሁም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ካለህ ፡ ከንተ ፡ ጋር ፡ መደባለቅና ፡ ቃል ፡ኪዳን፡ ማድረግ ፡ አስፈለገን ። ባለፈው ፡ እንደነበረ ፡ አሁንም ፡ ለወደፊቱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ረዳትህ ፡ ይሁን ። በሕንድ ፡ የሠራኸው ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ (ጦርነትና ፡ ድል) ፡ ተአምራት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊሠራው ፡ አይችልም ። ለሺ ፡ መርከብ ፡ የሚበቃ ፡ ስንቅና ፡ ማናቸውንም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በብዙ ፡ ልንሰጥ ፡ እንችላለን ። »

እነሆ ፡ የደብዳቤው ፡ ቃል ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ ይህ ፡ ነው ። ጉዳዩ ፡ ወደፍጻሜ ፡
ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ በጐረቤቶች ፡ እስላሞች ፡ ዘንድ ፡ አደጋ ፡ እንዳያመጣ ፡
ይኸን ፡ ቃል ፡ ንግሥት ፡ እሌኒ ፡ ሲልኩ ፡ በጠበቀ ፡ ምሥጢር ፡ ማቴዎስን ፡
አደራ ፡ ብለው ፡ ነው ። መላክተኛውም ፡ ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ በሕንድ ፡
ያሉት ፡ የፖርቱጋል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እንኳን ፡ የተላክህበትን ፡ ጉዳዩን ፡ ግለጽ
ልን ፡ እያሉ ፡ በማሰርም ፡ በማባበልም ፡ ቢጐተጕቱት ፡ ምሥጢሩን ፡ ሳያወጣ ፡
የንግሥቲቱን ፡ አደራና ፡ እምነት ፡ ሳያጐድል ፡ በትክክል ፡ ለንጉሡ ፡ ለአማኑኤል
ብቻ ፡ መስጠቱ ፡ የሚያስመሰግነው ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ።

ገጸ ፡ በረከት ፡ ተብሎ ፡ የተላከው ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ባዜ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡
መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከመጣው ፡ ግማደ ፡ መስ
ቀል ፡ ላይ ፡ ተቆርጦ ፡ እንደመስቀል ፡ ተቀርጾ ፡ የተሠራ ፡ ነው ፡ ማለት ፡
ነው ። ይኸም ፡ ግማደ ፡ መስቀል ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተሰቀለበት ፡
እቴጌ እሌኒ ፡ የትልቁ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ እናት ፡ ከተደበቀበት ፡ አግኝታው ፡ ከነበ
ረው ፡ ከእውነተኛው ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ ተቆርጦ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በኢት
ዮጵያ ፡ ነገሥታትና ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ የከበረና ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ የሚታይ ፡
ነው ። በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አልማዝና ፡ ወርቅ ፡ ከአልማዝና ፡ ከወርቅ ፡ የተሠ
ራም ፡ ሌላ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሳይጠፉ ፡ ይኸንን ፡ የእንጨት ፡ መስቀል ፡ አሠር
ተው ፡ መላካቸው ፡ የፖርቱጋልን ፡ ንጉሥ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የሚያስደስተው
ነገር ፡ እንደሌለ ፡ በሌላው ፡ በወርቅና ፡ በአልማዝ ፡ በብር ፡ ሀብት ፡ ራሱ ፡
በጣም ፡ የከበረ ፡ መሆኑን ፡ ገምተው ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የዝምድናው ፡
ዋና ፡ ምክንያት ፡ የክርስቶስን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመከላከል ፡ እስላሞቹን ፡ ለመቃወም
ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለሚፈልገው ፡ ዝምድና ፡ የጌታችን ፡ መስቀል ፡
መላክ ፡ ለጉዳዩ ፡ ተስማሚና ፡ አግባብ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ማሰባቸውም ፡ የታወቀ ፡ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፕሬትሬስ ፡ ዦን ፡ (ቄሱ ፡ ዮሐንስ) ፡ በሚባል ፡
ፍጹም ፡ ክርስቲያን ፡ በሆነ ፡ ንጉሥ ፡ የሚመራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በአፍሪካ ፡
ምሥራቅ ፡ አለ ፡ ማለትን ፡ ከኢትዮጵያና ፡ ከሕንድ ፡ ግዛቱ ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡
እያመጡ ፡ ወሬውን ፡ ሲሰማ ፡ የነበረውን ፡ አገር ፡ አሁን ፡ መላክተኛው ፡ ምንም ፡
አርመን ፡ ሆኖ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ቢሆን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡
በክብርና ፡ በደስታ ፡ እንደተቀበለው ፡ በየመጽሐፉ ፡ ተገልጿል ። ነገር ፡ ግን ፡
ይህ ፡ ሰው ፡ ዘሩ ፡ አርመን ፡ ቢሆንም ፡ ሃይማኖቱ ፡ ተዋሕዶ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን
ዠምሮ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ያገለገለ ፡ እንደአንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መኰንን ፡
የሚቆጠር ፡ መሆኑንም ፡ ንግሥቲቱ ፡ በደብዳቤያቸው ፡ ላይ ፡ ገልጸውታል ።
በዚህም ፡ ላይ ፡ ይኸን ፡ ለመሰለው ፡ መልእክት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ያላየ ፡ የውጭ
አገር ፡ ቋንቋ ፡ የማያውቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መኰንን ፡ ከመላክ ፡ እርሱን ፡ መላክ
ቸው ፡ ለነገሩ ፡ ተስማሚ ፡ ሰው ፡ መፈለጋቸውን ፡ ያስረዳል ። ይህም ፡ ሰው ፡
ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ ሃይማኖቱ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋይነቱ ፡ የኢትዮ
ጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ለጉዞ ፡ እንዳይቸገር ፡ የቱርክን ፡ ዜግነት ፡ ደርቦ ፡
ይዞ ፡ ይሆናል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ማቴዎስ ፡ ሊስበን ፡ ከገባ ፡ ዠምሮ ፡ ወደሮማ ፡ እስኪሄድ ፡ ድረስ ፡ እንደአንድ ፡ መስፍን ፡ በጌትነትና ፡ በከበሬታ ፡ ተቀምጦ ፡ ያኢትዮጵያን ታላቅነትና ፡ ሀብታምነት ፡ የሕዝቡንም ፡ ዠግንነት ፡ በየጊዜው ፡ ለንጉሡ ፡ ሲተርክ፡ ሰነበተ ። የፖርቱጋል ፡ ንጉሥም ፡ አማኑኤል ፡ ከሰፈው ፡ ግዛቱ ፡ ከሕንድ ፡ ጋር ፡ በመከከለኛ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚገኙትን ፡ አገሮች ፡ ለመደበለቅ ፡ ኢየሩሳሌም ንም ፡ ከቱርክ ፡ ግዛት ፡ ለማውጣት ፡ ከሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳስ ፡ ጋር ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ ነበረውና ፡ አሁን ፡ ከእቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ደብዳቤና ፡ ከማቴዎስ ፡ አንደበት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኝነት ፡ በማግኘቱ ፡ ደስ ፡ አለው ። የኢትዮ ጵያ ፡ ጓደኝነት ፡ ለግዛት ፡ መስፋፊያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንደዚሁም ፡ የኢትዮ ጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ከደከመው ፡ ከእስክ ንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥር ፡ አውጥቶ ፡ በሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ውስጥ ፡ እንዲ ሆን ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ከሊቃነ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሳይጻጻፍበት ፡ አልቀረም ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ማቴዎስን ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምሮ ፡ ወደሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ወደ ፡ ልዮን ፡ ፲ረኛ ፡ ላከው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ በመል እክት ፡ ተስማምተው ፡ ከጳጳሱ ፡ ወገን ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመስበክ ፡ ዶም ፡ ፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝ ፡ (Dom : Francseco : Alvarez) ፡ ጂዮቫኒ ፡ ፌርና ንዴዝ ፡ (Giovani Fernandez) ፡ ፒዬትሮ ፡ አልፎንሱ ፡ ሜንዴዝ ፡ Pietro Alpho Nsu mendez ፡ ከንጉሡ ፡ ወገን ፡ የፖሊቲካውን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመራ ፡ ዶም ፡ ኤድ ዋርዶ ፡ ጋልቫም ፡ (Dom Edouardo galvam) ፡ ከሌሎች ፡ ተከታዮች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመምጣት ፡ ተመረጡ ። እነሱም ፡ ከፖርቱጋል ፡ ንጉሥና ፡ ከሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለእቴጌ ፡ እሌኒና ፡ ለወጣቱ ፡ ላዒ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ (ዳዊት) ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ አቆጣጠር ፡ ጥቅምት ፡ ፩ ሺ፭፻፲፬ ፡ (እንደ ኢ.ት ፡ ሺ፭፻፯) ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ግድም ፡ በመርከብ ፡ ተሣፈሩ ። ተጕዘውም ፡ ከማራን ፡ እሚ ባለው ወደየመን ፡ ግዛት የሚጠጋ ፡ እቀይ ፡ ባሕር ፡ ደሴት ፡ ሲደርሱ ፡ የመላክተኞቹ አለቃ ፡ ከመንገድ ፡ ጉዞ ፡ ከበረሀ ፡ ሙቀት ፡ ጋራ ፡ በዕድሜ ፡ የሸመገለ ፡ የ፹፯ ፡ ዓመት ሰው ፡ ነበርና ፡ ሞተ ። ከመከከላቸው ፡ ፫ቱም ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ በዳሕላቅ ፡ ደሴት ፡ ሞቱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተረፉትም ፡ ተስፋ ፡ ወደመቁረጥ ፡ አዘንብለው ፡ ወደ ኢትዮጵያ ፡ መቀጠላቸውን ፡ ትተው ፡ ግዛታቸው ወደሆነው ፡ ወደሕንድ ፡ ሄዱ ። በዚ ያም ፡ እንደደረሱ ፡ አዲስ ፡ ተሾሞ ፡ የመጣው ፡ ዲዬጎ ፡ ሎፔዝ ፡ (Diego Lopez) ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ መርከብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ መላክተኞቹን ፡ በዚያ ፡ አሳፍሮ ፡ በየ መንገዱ ፡ የሚገጥማቸውን ፡ የቱርክ ፡ ወታደር ፡ እየመቱ ፡ አልፈው ፡ በቶሎ ፡ እምጥዋ ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። የምጥዋ ፡ ሕዝቦች ፡ መርከቡን ፡ ሲያዩ ፡ ቱርኮች ፡ ሊዘርፉ ፡ መጡብን ፡ ብለው ፡ ሲሸሹ ፡ ከመከከላቸው ፡ ፩ዱ ፡ ብቻ ፡ ወደመር ከቡ ፡ ተጠግቶ ፡ አነጋገረና ፡ አሁን ፡ ያሉበት ፡ የምጥዋ ፡ ወደብ ፡ የክርስቲ ያኑ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሆኑን ፡ ገለጸላቸው ፡ የመርከቡም ፡ አለቃ ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ የልብስ ፡ ስጦታ ፡ አደረገለት ።

በማግሥቱ ፡ በባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ውስጥ ፡ የሚታዘዘው ፡ የአርኪቆ ፡ ደሴት ፡ ሹም ፡ (ናይብ) ፡ እጠረፍ ፡ ድረስ ፡ ከነሰዉ ፡ መጥቶ ፡ ከፖርቱጊዞቹና ፡ ከንግቱ ምስ ፡ ተገናኘ ፡ እሱም ፡ ያገሩን ፡ የመንገዱን ፡ ሁኔታ ፡ ገለጸላቸው ። አብረው ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ የአርኪኮው ፡ ሹም ፡ ለፖርቱጊዞቹ ፡ አራት ፡ ሠንጋ ፡ ለእርድ ፡ አቀረበላቸው ፡ እነርሱም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ የሐር ፡ ልብስ ፡ ሰጥተው ፡ ደስ ፡ አሰኙት ። እዚያው ፡ ሳሉ ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ ገዳም ፡ ደብረ ፡ ቢዘንን ፡ በእጁ ፡ እየጠቀሰ ፡ እያሳየ ፡ የገዳሙ ፡ መነኰሳት ፡ የናንተን ፡ መምጣት ፡ ሰምተው ፡ ሊቀበሉዋችሁ ፡ መንገድ ፡ ዠምረዋል ፡ ብሎ ፡ ለመርከቡ ፡ ሹም ፡ ነገረው ። ከጥቂት ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፡ መነኰሳቱ ፡ ደርሰው ፡ ከፖርቱጊዞች ፡ ተገናኙ ፡ ይል ቁንም ፡ የሚያውቁትን ፡ ማቴዎስን ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ በደስታና ፡ በናፍቆት ፡ ተሳስመው ፡ ተገናኝተው ፡ ይጨዋወቱ ፡ ዠመር ። ከዚያ ፡ ፖርቱጊዞቹም ፡ መነኰሳቱም ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ከተማ ፡ ኼደው ፡ የእስላሞቹን ፡ መስጊድ ፡ ውስጡን ፡ ለዋውጠው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አድርገው ፡ ቅዳሴ ፡ ቀደሱበት ። የመርከበኞቹ ፡ ሹም ፡ ይህ ፡ መስጊድ ፡ የነበረውና ፡ ዛሬ ፡ የተቀደሰበት ፡ ጽንሰታ ፡ ለማርያም ፡ ተብሎ ፡ እንዲሠየም ፡ አስቦ ፡ ነበር ፡ ይኸንንም ፡ ማለቱ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የፖርቱጋል ፡ ግንኙነት ፡ ወደፊት ፡ እየሰፋ ፡ የሚኼደው ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ሥፍራ ፡ መጸነሱን ፡ (መዠመሩን) ፡ ለማስረዳት ፡ ይመስላል ። ፖርቱጊዞቹና ፡ መነኰሳቱ ፡ ምጥዋ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ እንደሰነበቱ ፡ በአምስተኛው ፡ ቀን ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ሺ፭፻ ፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግዛቱ ፡ ከወዲህ ፡ ከትግሬ ፡ ዠምሮ ፡ የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዳርና ፡ ዳር ፡ ምጥዋን ፡ ሁሉ ፡ የሚገዛው ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዶሪ ፡ መጣና ፡ ተገናኛቸው ። በሁለቱም ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነ ፤ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዶሬ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እናት ፡ የእቴጌ ፡ ናዖድ ፡ ሞገሳ ፡ ወንድም ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የመርከቡ ፡ አዛዥ ፡ሎፔዝ ፡ ደ ፡ ስኵዌራ ፡ በሟቹ ፡ በኤድዋርዶ ፡ ጋልባም ፡ ፈንታ ፡ ዶም ፡ ሮድሪግ ፡ ደ ፡ ሊማ ፡ ዋና ፡ የመልክተኞች ፡ ሹም ፡ ጂዎርጂዎ ፡ ደ ፡ አብሬን ፡ ምክትል ፡ አድርጎ ፡ በሹመት ፡ ደለደለ ። ፍራንቼስኮ ፡ አልባሬዝ ፡ ያንኑ ፡ የመንፈሳዊውንና ፡ የቤተ ፡ ክህነቱን ፡ ወገን ፡ መሪነቱን ፡ ያዘ ። ሌሎቹም ፡ ፩ዱ ፡ ሰአሊ ፡ ፩ዱ ፡ ሐኪም ፡ ፩ዱ ፡ ጸሐፊ ፡ ሆነው ፡ በደንበኛ ፡ መዝገብ ፡ የታወቁ ፡ ፲፪ ፡ ሰዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ትርፉ ፡ ሠራተኛና ፡ አጃቢው ፡ ከዚህ ፡ ቍጥር ፡ ያልፋል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከምጥዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አለበት ፡ አንጾኪያ ፡ (ይፋት) ፡ ለመድረስ ፡ ገና ፡ ረዥም ፡ጉዞ ፡ አለ ። በዚህ ፡ መካከልም ፡ ብዙ ፡ የተለዋወጠ ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ የጉዳዩ ፡ ወጣኝና ፡ አሳቢ ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ትተው ፡ ጐጃም ፡ እመርጡለ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ኼደው ፡ በዚያው ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ ተጸምደው ፡ ሳሉ ፡ ሞቱ ። እርሳቸውም ፡ ወደዚያ ፡ የኼዱት ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እሙሉ ፡ አቅም ፡ ደርሰው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ በሙሉ ፡ መያዝ ፡ ስለፈለጉ ፡

በዚሁ ፡ ሞግዚታቸውን ፡ ስለአስቀየሟቸው ፡ ይሁን ፤ ወይም ፡ ዕድሜያቸው ፡ ገፍቶ ፡ በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ ለቀው ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከሁለቱ ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ የእርጅናው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ባለፈው ፡ እንዳመለከትነው ። እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ያዩ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ ስለሆኑ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ያዩ ፡ እስክንድርን ፡ ያዩ ፡ ናዖድን ፡ መንግሥት ፡ ያስለፉ ፡ ስለሆኑ ፡ በሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከሰባ ፡ ዓመት ፡ እንደሚያልፍ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ዋናው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መላክተኛ ፡ ማቴዎስም ፡ መልክተኞቹን ፡ ይዤ ፡ ሄጄ ፡ ከንጉሡ ፡ አገናኝቼ ፡ የተላክሁበትን ፡ ጉዳይ ፡ እፍጻሜ ፡ አደርሳለሁ ፡ እያለ ፡ ሲመኝ ፡ ከዚያው ፡ ከጠረፍ ፡ ሳይነሣ ፡ ታሞ ፡ ሞተና ፡ በመልክተኞቹ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ሆነ ። ቢሆንም ፡ የተላኩበትን ፡ መልእክት ፡ ለመፈጸም ፡ ከምጥዋ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ቢዘን ፡ መጥተው ፡ ሰንብተው ፡ ከዚያም ፡ ጉዞአቸውን ፡ ወደፊት ፡ ቀጥለው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ዘመንም ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እጨጌ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞተው ፡ በርሳቸው ፡ እግር ፡ የሚተኩትን ፡ ለመምረጥ ፡ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ እጨጌ ፡ ዕንባቆም ፡ ተመርጠው ፡ ደስታ ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፡ ለዚሁ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሊቃውንትና ፡ መነኮሳት ፡ እንግዶቹን ፡ በመልካም ፡ አስተያየትና ፡ አክብሮት ፡ ተቀብለው ፡ አስተናገዱዋቸው ። ከዚያም ፡ ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ድንግል ፡ ወደሚገኙበት ፡ ወደ ፡ እንጾኪያ ፡ (ይፋት) ፡ ሄደው ፡ እንደኤው ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፭፻፳ ፡ (እንደ ፡ ኢት ፡ ቍ ፡ ሺ፭፻፲፪ ?) ፡ ዓ. ም. በጥቅምት ፡ ወር ፡ ተገናኙ ። ከንጉሣቸውና ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሳቸው ፡ የተላከውንም ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አቀረቡ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ፖርቱጊዞቹ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በብዙ ፡ ይዘው ፡ ይመጣሉ ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ ተደርጎ ፡ ነበርና ፡ ከመጭዎቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፤ የቀሩትም ፡ የፖለቲካ ፡ ሰዎች ፡ ስለነበሩ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ አላመጡም ፡ ነበርና ፡ በንጉሡና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ቅርታ ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ይልቁንም ፡ የእቴጌ ፡ እሌኒና ፡ የመላክተኛው ፡ የማቴዎስ ፡ መሞትና ፡ ከጉዳዩ ፡ መውጣት ፡ ነገሩን ፡ ሊያቀዘቅዘው ፡ እንደሚችል ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ንጉሡና ፡ መኳንንቱ ፡ እነዚያ ፡ እንደተመኙትና ፡ እንደጠበቁት ፡ መልካምና ፡ የደመቀ ፡ አቀባበል ፡ አላደረጉላቸውም ። ከንጉሡም ፡ ከመገናኘታቸው ፡ በፊት ፡ አስተናባሪዎቹ ፡ እዚጅ ፡ አስቀምጠው ፡ ስላቆዩዋቸው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ዓቢያን ፡ ሊቀ ፡ ንዑሳን ፡ የሚባሉት ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ሊጋባና ፡ የልፍኝ ፡ አስከልካዮች ፡ «ተነሡ ፡ ቁጭ ፡ በሉ» ፡ እያሉ ፡ የሚያደርጉት ፡ ያገራችን ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓት ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ይልቁንም ፡ ከታላቁ ፡ ከፖርቱጋል ፡ ንጉሥና ፡ ከሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘንድ ፡ ለመጡ ፡ መልእክተኞች ፡ ቅርታ ፡ መጨመሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ብሩስም ፡ ኩልበም ፡ ሌሎችም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ራሱ ፡ አልቫሬዝ ፡ በፖርቱጋል ፡ ቋንቋ ፡ ከጻፈው ፡ ላይ ፡ እየተረጐሙ ፡ ስለ ፡ አቀባበሉ ፡ የጻፉትን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንመልከት ።

«ንጉሡ ፡ እኛን ፡ ለመቀበል ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ እንዲሆን ፡ አድርጓል ። የንጉሡ ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ያለው ፡ ድንኳን ፡ በመከከል ፡ ሆኖ ፡ ዙሪያውን ፡ ሌሎች ፡ ነጭና ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ ያላቸው ፡ ድንኳኖች ፡ ተተክለዋል ። ንጉሡ ፡ በታላቁ ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ዙሪያውን ፡ በመጋረጃ ፡ ተከልሎ ፡ በውስጠኛው ፡ ተቀምጧል ። በውጭ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥሩ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ሕዝቡም ፡ ወደፊት ፡ እንዳይገፋ ፡ ከልካዮች ፡ ይጠብቁታል ። በመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፡ (ደረጃ) ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሹማምንት ፡ የበዓል ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ይታያሉ . . . . . ፡ በንጉሡ ፡ ድንኳን ፡ በራፍ ፡ አጠገብ ፡ የንጉሡ ፡ አራት ፡ የሚያማምሩ ፡ ፈረሶች ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ዕቃና ፡ ኮርቻ ፡ ተጭነው ፡ ቆመው ፡ ይታያሉ ። ከነርሱ ፡ በታች ፡ አሥር ፡ ሺ የሹማምንት ፡ ፈረሶች ፡ ተሰልፈው ፡ ይታያሉ ። በንጉሡ ፡ ፈረሶች ፡ ፊትና ፡ ኋላ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሹማምንት ፡ ነጫጭ ፡ ልብሳቸውን ፡ አደግድገው ፡ ቆመዋል ። ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ጐፈር ፡ የለበሱ ፡ በእጃቸው ፡ አለንጋ ፡ ይዘው ፡ ንጉሡ ፡ በሚያልፍበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ የመከልከል ፡ (የማጋፈር) ፡ ተግባር ፡ ያላቸው ፡ ይታያሉ ። . . . ከዚያ ፡ መቶ ፡ የሚሆኑ ፡ ከልካዮች ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ እየቀደዱ ፡ አልፈው ፡ ዙፋኑ ፡ ወዳለበት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ . . . ሲደርሱ ፡ ሁሉም ፡ እጁ ፡ መሬት ፡ እስኪነካ ፡ ድረስ ፡ በጥልቅ ፡ እጅ ፡ ሲነሣ ፡ መላክተኞቹም ፡ እንደዚሁ ፡ ባክብሮት ፡ እጅ ፡ ነሡ ። በንጉሡና ፡ በነርሱ ፡ መካከል ፡ የሚያምር ፡ መጋረጃ ፡ ስላለ ፡ ንጉሡ ፡ አይታይም ። በመላክተኞቹ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አውሬ ፡ ቆዳ ፡ በርኖስ ፡ ካባ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ጥልፍና ፡ ክፈፍ ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ቁልፍ ፡ ያለው ፡ የለበሱ ፡ ሠራተኞች ፡ ሁሉም ፡ በያለበት ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ሥራቸውን ፡ ያስተናብራሉ ። እነርሱም ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ሆነው ፡ መላክተኞቹን ፡ ወደመጀመሪያው ፡ አጥር ፡ አገቡዋቸውና ፡ በዚያ ፡ አቆዩዋቸው ። የመግቢያው ፡ በር ፡ በሰንሰለት ፡ በታሠሩ ፡ አራት ፡ አንበሶች ፡ ይጠበቃል ፡ በመላክተኞቹ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወደንጉሡ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚችሉ ፡ ዙፋኑንም ፡ የሚጠብቁ ፡ አራት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይገኛሉ ። መላክተኞቹ ፡ አስገቢዎቹ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡ የሚያደርጉትን ፡ እየተከተሉ ፡ ለጥ እያሉ ፡ ለማይታየው ፡ ለግርማዊነቱ ፡ እጅ ፡ ነሡ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ቲንሽ ፡ ጸጥታ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በዕድሜ ፡ የሸመገለ ፡ መነኵሴ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ የሚባለው ፡ ፪ኛው ፡ ባለሥልጣን ፡ ከድንኳኑ ፡ (ንጉሡ ፡ ካሉበት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ) ብቅ ፡ አለና ፡ „እነማናችሁ ፡ ከወዴትስ ፡ መጥታችኋል„ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ ይኸንንም ፡ የጠየቀው ፡ ሥርዓት ፡ ለመፈጸም ፡ እንጂ ፡ ከወዴት ፡ እንደመጡ ፡ እነማን ፡ መሆናቸውም ፡ ታውቋል ። ይሁን እንጂ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ መልሱን ፡ ከገና ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መጋረጃው ፡ ገብቶ ፡ ለጌታው ፡ ከነገረ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወጥቶ ፡ ይኸንኑ ፡ ጥያቄ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ አቀረበ ። በ፫ኛው ፡ ጥያቄ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ መላክተኛ ፡ (አምባሳደሩ ፡) ገርሞት ፡ ዝም ፡ ሲል ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ የመጣችሁበትን ፡ ጉዳይ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ እንድነግርላችሁ ፡

አስታውቋኝ ፡ አለ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዋናው ፡ መላክተኛ ፡ ዶም ፡ ሮድሪግ ፡ (Dom Rodrigue) የተላከሁበትን ፡ ጉዳይ ፡ ከንጉሡ ፡ በቀር ፡ ለሌላ ፡ አልነግርም ፡ ከዚህም ፡ ጋር ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ተገናኝቼ ፡ ንጉሣዊ ፡ እጃቸውን ፡ ስሜ ፡ ስለክርስቲያኖች ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ አንድነት ፡ ስለሕዝቡም ፡ ብልጽግናና ፡ ስላገሩ ፡ ልማት ፡ ምኞቱን ፡ ማቅረብ ፡ እፈልጋለሁ ። ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጠ ። ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ይኸን ፡ መልስ ፡ ለንጉሡ ፡ ከነገረ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ከሕንድ ፡ ከንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ የመጣውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ እንድታቀርቡ ፡ ንጉሡ ፡ አዝዞዋል ፡ አለና ፡ ገጸ ፡ በረከቱ ፡ እየተቆጠረ ፡ እንደጠረጴዛ ፡ አለው ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ ተደረደረ ። ለገጸ ፡ በረከት ፡ የተደረገውን ፡ የሐር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልብስ ፡ በማየት ፡ ከውጭ ፡ የሚመለከተው ፡ ሕዝብ ፡ አድናቆቱን ፡ በድምፁ ፡ ሲገልጽ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ተመልሶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጣችሁ ፡ አለና ያቀባበሉ ፡ በዓል ፡ በዚሁ ፡ ብቻ ፡ ሌላም ፡ ንግግርና ፡ ጭውውት ፡ ሳይጨመርበት ፡ አለቀና ፡ መላክተኞቹ ፡ ወደሠፈሬቻቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ አጋፋሪዎቹ ፡ አመለከቷቸው ። ወደሠፈር ፡ ሄደው ፡ ትንሽ ፡ እንደቆዩ ፡ ድርጎው ፡ ተቀጣጥሎ ፡ እሠፈር ፡ ድረስ ፡ መጣ ።

እስከሁን ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ስንመለከት ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ከአሥር ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ማቴዎስን ፡ ወደፖርቱጋል ፡ ሲልኩ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ገና ፡ ወጣትና ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ እንዳልጨበጡና ፡ የእቴጌ ፡ እሌኒንና ፤ የማቴዎስን ፡ ድካም ፤ በዚህ ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ የሚገኘውንም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ እንኳን ፡ በወጣትነታቸው ፡ ጊዜ ፡ አሁንም ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ደርሰው ፡ ሥልጣኑን ፡ በያዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ እንዳላመዛዘኑትና ዋጋ ፡ እንዳልሰጡት ፡ ያስረዳል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ በመዠመሪያው ፡ ፲ ፡ ከቨ.ልሐአን ፡ ልክ ፡ ግንኙነቱን ፡ የወጠነው ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ቢሆን ፡ «ልጃችንን ፡ ከልጆቻችሁ ፡ እናጋባ ፡ ኃይልና ፡ ኃይላችንን ፡ አንድነት ፡ አድርገን ፡ የሁላችንንም ፡ ጠላት ፡ እስላምን ፡ እናጥቃ» ፡ የሚል ፡ የጥያቄ ፡ ቃል ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ የተጻፈው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ነው ። የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መላክተኛ ፡ በክብር ፡ ተቀብለው ፡ ራሱ ፡ አነጋግሮ ፡ እንዳንድ ፡ መስፍን ፡ ሲያከባክብ ፡ ሰንብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ የራሱን ፡ መላክተኛ ፡ ሲልክና ፡ መላክተኞቹ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ያልታሰበ ፡ ሁኔታ ፡ ሲደርስባቸው ፡ ከንጉሡ ፡ ተገናኝተው ፡ እጅ ፡ መንሣትና ፡ መነጋገር ፡ ሲከለከሉ ፡ እንዳልታወቀ ፡ ሰው ፡ ከወዴት ፡ መጥታችኋል ፡ እየተባሉ ፡ ሲጠየቁ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚሰማቸውን ፡ ቅርታ ፡ ለመገመት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አያስቸግርም ። ምናልባት ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ጭምር ፡ ያለዚያ ፡ ማቴዎስ ፡ እንኳን ፡ በሕይወት ፡ ኖሮ ፡ መላክተኞቹን ፡ እንደያዘ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ አሉበት ፡ እስከ ፡ አንጻኪያ ፡ ከተማ ፡ ገብቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ነገሩንም ፡ ከሥሩ ፡ እያስረዳ ፡ ጥቅሙንም ፡ እየገለጸ ፤ ንጉሡንም ፡ እየመከረ ፡ ያቀባበሉን ፡ አኳኋን ፡ ለመላክተኞቹ ፡ ሳያሻሽልላቸው ፡ ባልቀረም ፡ ነበር ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ንጉሡ ፡ ከፖርቱጋል ፡ አገር ፡ ይመጣልኛል ፡ ብለው ፡ የጠበ ቁት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሲሆን ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ከሊስቦን ፡ ሕንድ ፡ ከሕንድ ፡ ምጥዋ ፡ ከምጥዋ ፡ ደብረ ፡ ቢዘን ፡ በጉዞና ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ረዥሙን ፡ ጉዞ ፡ ሲያደርጉ ፡ ይልቁንም ፡ የመዠመሪያው ፡ ዋና ፡ መላክተኛ ፡ ዶም ፡ ጋልበም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ ትንሽ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ደህና ፡ ደህናው ፡ ዕቃ ፡ በየመንገዱ ፡ ምናልባት ፡ ለአርኪኮው ፡ ባላባትና ፡ ለባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ለሌላም ፡ እየተሰጠ ፡ ስለባከነ ፡ በዚህም ፡ ንጉሡ ፡ ቅርቃ ፡ ገብቷቸው ፡ እንደነበረ ፡ አልባሬዝ ፡ በጽሑፉ ፡ ገልጿል ።

ምናልባት ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከትልቁ ፡ መንግሥት ፡ ከፖርቱ ጋልና ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ የ፫ትና ፡ የ፬ት ፡ ዓመት ፡ ጉዞ ፡ አድርገው ፡ የመ ጡትን ፡ መላክተኞች ፡ ችላ ፡ ያሉበት ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ። ይኸ ውም ፡ መላክተኞቹ ፡ ይልቁንም ፡ ከሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ከልዮን ፡ ፲ኛ ፡ ተል ከው ፡ የመጡት ፡ በ፪ ፡ ባሕርይ ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያምኑና ፡ ይኸንኑ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ለመስፋፋት ፡ መምጣታቸው ፡ ሲታወቅ ፡ ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከተ ደረገው ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ዠምሮ ፡ የእስክንድርያና ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ጠበኞች ፡ ስለሆኑ ፡ የኛም ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከእስክን ድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እየመነጬ ፡ በተቀበሉትና ፡ ባጠኑት ፡ የእስክንድርያ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዲዮስቆሮስን ፩ ፡ ባሕርይ ፡ እንዳይል ፡ ያወገዘበትን ፡ ጉባዔ ፡ የኛ ፡ ሊቃውንት ፡ ማኅበረ ፡ ከለባት (የውሾች ፡ ጉባዔ ፡) የሚሉ ፡ በዘ መኑ ፡ የነበረውን ፡ ታላቁን ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ልዮን ፩ኛን ፡ ‹ልዮን ፡ ከሐዲ ፡ መጣ ፡ . . . › እያሉ ፡ የሚሰድቡ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የኢት ዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ቄስ ፡ ሐፄው ፡ መነከሳት ፤ ጽራግ ፡ ማሠሬው ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙም ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገኖች ፡ ስለሆኑ ፡ እነዚህ ፡ ከሮማ ፡ የመጡትን ፡ መላክተኞች ፡ በጠብ ፡ ዓይን ፡ ተመል ክተው ፡ ንጉሡም ፡ በአቀባበል ፡ ችላ ፡ እንዲሉ ፡ በግድ ፡ ሳይሆን ፡ በአነጋገርና ፡ በምክር ፡ እነዚሁ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አስገድደዋቸው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ። እንዳጋጣሚ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ልዮን ፡ ፲ረኛ ፡ የሚባል ፡ የሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ስሙም ፡ ከዚያው ፡ በኢትዮጵያና ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተጠላው ፡ ከልዮን ፩ኛ ፡ ጋር ፡ ይገጥማልና ፡ ስሙም ፡ ቢለይ ፡ በታሪክ ፡ እንደሚያውቁት ፡ የስሙ ፡ መግጠም ፡ ከልዮን ፡ ዘንድ ፡ መጣን ፡ ሲሉ ፡ ይበልጥ ፡ ቀፎአቸው ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ በነዚህ ፡ መል ክተኞች ፡ ሳቢያ ፡ ገብቶ ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ አገራችንን ፡ ያቀማናል ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ገብቶ ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ።

በተረፈ ፡ ደግሞ ፡ ማቴዎስ ፡ ሲላክ ፡ የሐረርጌው ፡ ባላባት ፡ የዘይላው ፡ ገዥ ፡ እስከ ፡ ይፋት ፡ እስከ ፡ ደዋሮ ፡ እየዘረፈ ፡ በሠጋበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ ማኅፉዝን ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ካጠፉት ፡ ወዲህ ፡ ለጊዜው ፡ አስጊ ፡ ነገር ፡ ስላልታየ ፡ ማቴዎስም ፡ ከተላከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ሊሞላው ፡ ስለተቃረበ ፡ ጉዳዩም የእስላሞቹም ፡ አስጊነት ፡ ወደ ፡ መዘንጋት ፡ ስለደረሰ ፡ ‹ከየት ፡ መጥታችኋል ፡ ጉዳያችሁስ ፡ ምንድነው › እስከ መባል ፡ ደርሰው ፡ ይሆናል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ አልቫሬዝ ፡ አጻጻፍ ፡ መላክተኞቹ ፡ ከንጉሡ ፡ ሳይገናኙ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዙሪያ ፡ የሚገኙት ፡ ፭ ፡ አንድ ፡ የጣልያን ፡ የጀርመን ፡ የፈረንሳዊ ፡ (ከታላን) ፡ ተወላጆች ፡ እንዳይገናኙዋቸው ፡ ተከልክለው ፡ የያዙትንም ፡ ዕቃ ፡ ምንድነው ፡ አሳዩን ፡ ስጡን ፡ እያሉ ፡ ሲያጉላሉዋቸው ፡ ማን ፡ ጠራችሁና ፡ መጣችሁ ፡ ሲሏቸው ፡ እነርሱም ፡ በመምጣታቸው ፡ ሲመረሩ ፡ ሲያዝኑ ፡ ሰንብተው ፡ በመጨረሻው ፡ በመጡ ፡ በሥረኛው ፡ ቀን ፡ እንደገና ፡ ፩ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከር ፡ በጧት ፡ ተልኮ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወሰዳቸው ፡፡ ሄደውም ፡ በእሾህ ፡ እታጠረው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ አቆዩዋቸው ፡ ከዚያ ፡ ፬ ፡ የሚሆኑ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡ መጥተው ፡ ንጉሡ ፡ ወዳሉበት ፡ አስገቡዋቸው ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንት ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዘው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በረዥሙ ፡ የተሰለፉ ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ሙብራት ፡ ይዘው የቆሙ ፡ ነበሩ ፡ ከዚያ ፡ መላክተኞቹ ፡ እንደተገናኙ ፡ «ማቴዎስን ፡ ወደ ፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ አልላክሁም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ የተላከልኝ ፡ ነገር ፡ ነበር ፡ እንደምን ፡ አልደረሰኝም" ፡ ብለው ፡ ንጉሡ ፡ አምባሳደሩን ፡ ቢጠይቁት ፡፡ አምባሳደሩ ፡ ዶም ፡ ሮድሪግ ፡ «የመዠመሪያው ፡ አምባሳደር ፡ (ዶም ፡ ጋልቫም) ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ለመግባት ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠን ፡ ነበር ፡ ለመንገዳችን ፡ የሚያስፈልገንን ፡ ቲንሽ ፡ ዕቃ ፡ ይዘን ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፡ ሳናስበው ፡ ፩ ፡ መርከብ ፡ ይዘን ፡ ምጥዋ ፡ አደረሰን ፡ የዛሬው ፡ መልእክት ፡ የመዠመሪያ ፡ እርምጃ ፡ ነው ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ሌሎች ፡ ደንበኞች ፡ መልክተኞች ይመጣሉ" ፡ ብሎ ፡ አስረዳና ፡ የተላከበትን ፡ ዋናውን ፡ መልእክት ፡ ለመናገር ፡ እንደሚችል ፡ ቢጠይቅ ፡ ንጉሡ ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ ወደገቡበት ፡ የፖሊቲካ ፡ ጉዳይና ፡ አገር ፡ ቆርጠው ፡ ለመስጠት ፡ ወደታሰበበት ፡ አሳብ ፡ ላለመግባት ፡ ነገሩን ፡ ባጭሩ ፡ አቋረጡና ፡ ተለያዩ ፡፡

ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የፖርቱጋል ፡ መልክተኞችና ፡ ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የመዠመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ቅርታና ፡ ክርክር ፡ እያደረ ፡ ተሠርዞ ፡ ወደመቀራረብና ፡ ወደመወዳጀት ፡ ደረሱ ፡፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የየግል ፡ ጉዳያቸውን ፡ እያደር ፡ ተገላልጠው ፡ ሲነጋገሩ ፡ የሁለቱም ፡ ጉዳይ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ በጥቅም ፡ የተያያዘ ፡ መሆኑን ፡ ወደመረዳትና ፡ በመከከሉ ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ቢገጥምም ፡ ቅርታቸውን ፡ ሁለቱም ፡ እያሳለፉ ፡ የወደፊቱ ፡ ጥቅም ፡ የሚከናወንበትን ፡ አሳብ ፡ ያደራጁ ፡ ዠመር ፡፡ የፖርቱጋሎቹ ፡ ጉዳይ ፡ ክርስቲያኑን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ የዘይላን ፡ የምጥዋን ፡ ወደብ ፡ ከቱርኮቹና ፡ ከዐረቦቹ ፡ እየተሻሙ ፡ ለመያዝ ፡ ነው ፡፡ ከዚህም ጋር ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስና ፡ መላክተኞቹ ፡ በፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ተጠግቶ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ በሰፊው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ለማግባት ፡ ነው ፡፡ የኢትዮጵያ ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ አገር ፡ ቆርጠ ፡ ሳይሰጡ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሳይለውጡ ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ በወዳጅነት ፡ ተሳስሮ ፡ በደቡብና ፡ በምሥራቅ ፡ ያሉትን ፡ በየጊዜው ፡

እየሸፈቱ ፡ አንገዛም ፡ የሚሉትን ፡ ሲመቻቸውም ፡ እስከ ፡ ይፋት ፡ እስከ ፡ ደዋሮ ፡ ድረስ ፡ እየወጡ ፡ አገር ፡ የሚዘርፉትን ፡ የአዳልና ፡ የሱማሌን ፡ ባላባቶች ፡ ለመደምሰስ ፤ ከዚያም ፡ የሚቻል ፡ ሲሆን ፡ የነርሱን ፡ ደጋፊ ፡ የቱርክን ፡ መንግሥት ፡ ማጥፋትና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይኸም ፡ ባይቻል ፡ በር ፡ የሆኑትን ፡ የምጥዋን ፡ የዘይላን ፡ በር ፡ አስለቅቆ ፡ ነጻ ፡ አውጥቶ ፡ ሊሳለሙም ፡ ሊነግዱም ፡ ወደ ፡ ቅድስት ሀገር ፡ የሚሄዱት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከስርያም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚመጡት ፡ መነከሳትና ፡ ሊቃውንት ፡ እንደልባቸው ፡ እንዲመላለሱ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በዘመኑ ፡ ያላቸውን ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ እንደፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ወታደር ፡ ለማሠልጠንና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦርና ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ በገራቸው ፡ ለማስገባት ፡ ምኞት ፡ ስለ ፡ ነበራቸው ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳይ ፡ ባለፈው ፡ ለምን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ አልመጡልኝም ፡ ብለው ፡ በመቀየም ፡ ፈንታ ፡ ለወደፊቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ መልክተኞቹን ፡ ያቀራርቧቸው ፡ ገሥመር ።

ስለዚህ ፡ ዶም ፡ ሮደሪግና ፡ ጓደኞቹ ፡ እነዶም ፡ አልባሬዝ ፡ በሬተኛው ፡ ቀን ፡ ከተገናኙ ፡ ወዲህ ፡ እንደገና ፡ ከአጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ተገናኝተው ፡ የፖርቱጋልንና ፡ የቱርክን ፡ ኀይል ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ አንሥተው ፡ ሲነጋገሩ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ የፖርቱጋል ፡ መርከብ ፡ ሲመጣ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ መላክተኛ ፡ እልካለሁ ፡ አሁን ፡ ደክሟችኋልና ፡ እረፉ ፡ ብለው ፡ አሰናበቷቸው ። መላክተኞቹም ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ "የኛ ፡ ቄሶች ፡ እንዳገራችን ፡ ልማድ ፤ ቅዳሴ ፡ እየቀደሱ ፡ ጸሎት ፡ እንዲያደርጉ ፡ ይፈቀድልን„ ፡ ብሎ ፡ ዋናው ፡ መላክተኛ ፡ ቢለምናቸው ፡ «መልካም ፡ ነው ፡ ይቀድሱ ፡ እንኳን ፡ እናንተ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እስላሞቹ ፡ እንኳን ፡ በግዛቴ ፡ እንደሃይማኖታቸው ፡ ጸሎታቸውን ፡ ሲያደርሱ ፡ አይከለከሉም» ፡ ብለው ፡ ፈቀዱላቸውና ፡ ማናቸውንም ፡ ጉዳያቸውንና ፡ ጥያቄያቸውን ፡ አቃኑላቸው ። እንዲያውም ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክህነቱን ፡ ኀላፊ ፡ ዶም ፡ ፍራንቼስኮ ፡ አልባሬዝን ፡ እየጠሩ ፡ ስለሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ አነጋገሩት ፡ ቅዳሴም የሚቀድስበት ፡ አንድ ፡ ከማኀፉዝ ፡ ጦርነት ፡ የተማረከ ፡ ጥሩ ባለቀለም ፡ ድንኳን ፡ ሰጡት ። እንደዚሁም ፡ ይኸው ፡ አልቫሬዝ ፡ የጻፈው ፡ እንደሚለው ፡ በቅዳሴና ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ እንዳትዘነጉኝ ፡ (ስሜን ፡ እንድታነሡ) ፡ ብለው ፡ እንደለመኑትና ፡ እንደዚሁም ፡ በሚቀደስበት ፡ ጊዜ ፡ ሹማምንቶቻቸው ፡ ተገኝተው ፡ እንዲያዳምጡ ፡ ማዘዛቸውን ፡ ራሳቸውም ፡ የገና ፡ በዓል ፡ ሲደርስ ፡ እንደሚገኙ ፡ ተስፋ ፡ እንደሰጡት ፡ ይገልጻል ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በሕንድ ፡ እንደራሴ ፡ በኩል ፡ በዶም ፡ ሮደሪግ ፡ እጅ ፡ የመጣው ፡ መልእክት ፡ አልተነበበም ፡ ነበር ፡ እንደኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፭፻፳፫ ፡ ዓ፡ ም ፡ ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል፡

የወርቅ ፡ ዘውድ ፡ በራሳቸው ፡ ደፍተው ፡ በእጃቸው ፡ የብር ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ በሚያማምሩ ፡ በሁለት ፡ መከዳዎች ፡ መካከል ፡ እመንበረ ፡ ዳዊታቸው ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ዋናው ፡ መልክተኛ ፡ የመልእክቱን ፡ ደብዳቤ ፡ ለንጉሡ ፡ አቀረበና ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ (ግዕዝ ፡ ወይስ ፡ አማርኛ ?) ፡ እየተ ተረጐመ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሙት ። በመልእክቱም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሥጋና ፡ አቀረቡ ።

ከዚያ ፡ ንጉሡ ፡ ከሉበት ፡ ሥፍራ ፡ (አንጻኪያ–ይፋት) ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ አገር ፡ ጉዞ ፡ ሲገሥግሩ ፡ መላክተኞቹም ፡ አብረው ፡ ተጓዙ ። ለነርሱም ፡ ክብትም ፡ ስንቅም ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ እንዳይጐድላቸው ፡ ንጉሡ ፡ በልደረበ ፡ ሰጥ ተው ፡ በጥብቅ ፡ አዘውላቸው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ መካከል ፡ አጉዞ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ መላክተኛ ፡ ዶሞ ፡ ሮድሪግና ፡ ምክትሉ ፡ ጆርጂዎ ፡ አብሬን ፡ ? እርስ ፡ በርሳ ቸው ፡ ተጣልተው ፡ ጭቅጭቅ ፡ አነሡ ፡ ንጉሡም ፡ ራሳቸው ፡ በነገሩ ፡ ገብ ተው ፡ እንዲታረቁ ፡ አሳሰበው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሳይሆንላቸው ፡ ቀርቶ ፡ አለቅዮውና ፡ ምክትሉ ፡ ሠራራቸውንና ፡ ጉዞአቸውን ፡ ለየብቻ ፡ አድርገው ፡ ተለያዩ ። ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ ተጉዘው ፡ መካነ ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደርሰው ፡ ያባታቸውን ፡ ያፄ ፡ ናዖድን ፡ ዐጽም ፡ ወደዚሁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ በክብር ፡ አስቀብረው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ቅዳሴ ፡ ቤት ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ተመርቆ ፡ ተከብሮ ፡ ዋለ ። የፖርቱጋል ፡ መላክተኞ ችም ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራና ፡ ጊዜ ፡ በዕድሜ ፡ ከረጁት ፡ ከግብፃዊው ፡ ጳጳስ ፡ ጋር ፡ ተገናኝተው ፡ የሃይማኖትን ፡ ንግግር ፡ እንዳደረጉ ፡ ጳጳሱም ፡ በነርሱ ፡ መምጣት ፡ መደሰታቸውን ፡ በኢትዮጵያም ፡ ሳሉ ፡ በገር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ ለማስወገድ ፡ ሲጥሩ ፡ ሳሉ ፡ በንጉሡና ፡ በመኳንንቱ ፡ ምክ ንያት ፡ ሳይቻላቸው ፡ መቅረቱን ፡ እያማረሩ ፡ እንደገለጹላቸው ፡ ይኸው ፡ አል ቫሬዝ ፡ ይገልጻል ።

በዚያም ፡ ሳሉ ፡ የገና ፡ በዓል ፡ በዋለበት ፡ ቀን ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ተደራ ጅተው ፡ ትልቅ ፡ የቅዳሴ ፡ በዓል ፡ በደረጉበት ፡ ቀን ፡ ንጉሡና ፡ ባለቤታቸው ፡ (እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ? ) ያረጁት ፡ እቴጌ ፡ እሌኒም ፡ (ከመርጡለ ፡ ማርያም መጥተው ፡ ይሆናል ፡ ? ) መኳንንቱም ፡ በሥፍራው ፡ ተገኝተው ፡ ቅዳሴውን ፡ እያዳመጡ ፡ ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ እየተመለከቱ ፡ መደነቃቸውን ፡ ጨምሮ ፡ ይገልጻል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፬ ።

**ያዜ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ደብዳቤዎች ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ለአማኑኤልና ፡ ለልጁ ፡ ለዮሐንስ–የፖርቱጋልና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መልክተኞች ፡ ወደሊስቦን ፡ መሔድ ።**

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ መልክተኞች ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ ከሹማምንቶቻቸው ፡ ጋር ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ባለመግባባት ፡ እመወቃቀስ ፡ እመራረቅ ፡ ላይ ፡ ደርሰው ፡ ሳለ ፡ በሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የየግላቸው ፡ ዓላማ ፡ እንዳይበላሽ ፡ ያለፈውን ፡ ረስተው ፡ ለወደፊቱ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ለማቋቋም ፡ ጉዳያቸውን ፡ ተገላልጸው ፡ ሲገናኙ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ሲወያዩ ፡ ሰንብተው ፡ ሰላማዊው ፡ መንፈስ ፡ ከተመሠረተ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከራሳቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጨምረው ፡ እነዚህኑ ፡ መልክተኞች ፡ ወደሊስቦንና ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ለመላክ ፡ ውሳኔ ፡ አደረጉ ። ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ እንዲሄድ ፡ የታሰበው ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ የሚባል ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው ።

በንዳንድ ፡ ጽሑፍና ፡ ከዚያውም ፡ በተለይ ፡ በፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እንደሚገኘው ፡ ንጉሡ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ከንጉሡ ፡ ከአማኑኤል ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አድርገው ፡ አሳባቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ እንጂ ፡ ከሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ አላሰቡም ። ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ወዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ በሚመጣበት ፡ በእስክንድርያና ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጥላቻ ፡ ያውቁታል ። በሁሉ ፡ ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስና ፡ ክርስቲያኖች ፡ በቱርክና ፡ በግብጽ ፡ እስላሞች ፡ እየተገዙ ፡ ክብራቸውም ፡ ዝናቸውም ፡ በጣም ፡ የቀዘቀዘ ፡ ቢሆንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ይልቁንም ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ወገን ፡ እስክንድርያ ፡ እናቴ ፡ ማርቆስ ፡ አባቴ ፡ የሚል ፡ የሮማን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳስም ፡ በጠብና ፡ በባላጋራነት ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑን ፡ አያዘነጉትም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በጠገባቸው ፡ ያሉት ፡ እነፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝ ፡ እስላሞችን ፡ ለመቃወም ፡ ከፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ለመወዳጀትና ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማድረግ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በነገሩ ፡ ካልገባበት ፡ አንዳች ፡ ሊከናወን ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ስለአስረዳቸው ፡ ለንጉሡና ፡ ለጳጳሱ ፡ ሁለት ፡ ደብዳቤ ፡ ሁለት ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ መላክተኛ ፡ ለየብቻ ፡ አዘጋጅተው ፡ ለመላክ ፡ እንደተገደዱ ፡ ይታያል ።

መልክተኞቹ ፡ ከፖርቱጋል ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ከመጡ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ አልፏቸዋል ፡ (እንደ ፡ ኤው ፡ ቍጥር ፡ ፲፭፻፳–፲፭፻፳፮) ። አሁን ፡ ግን ፡ የመጡትን ፡ ነገር ፡ ሲነጋገሩ ፡ ይልቁንም ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ ምጥዋ ፡ ድረስ ፡ [illegible]ጥቶ ፡ የሚወስዳቸውን ፡ መርከብ ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ሲጠባበቁ ፡ ኑረው ፡ በመጨረሻ ፡ ለንጉሡ ፡ ለአማኑኤል ፡ የሚሰጠውን ፡ ከሙሉ ፡ ወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ዘውድና ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዘው ፡ ዶም ፡ ሮድሪግን ፡ አስቀድመው ፡ ወደምጥዋ ፡ ልከው ፡ ሳለ ፡ እንደዚ

ሁም ፡ ለጳጳሱ ፡ ለክሌማንት ፡ (ቀሌምንጦስ ፡ ፯ኛ) ፡ የወርቅ ፡ መስቀልና ፡ ደብ ዳቤ ፡ አዘጋጅተው ፡ ለፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝ ፡ ሰጡት ። እርሱም ፡ ወደምጥዋ ፡ ሄዶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መርከብ ፡ አጥተው ፡ ተቸግረው ፡ ከአባ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብና፡ከባ ሕር ፡ ነጋሹ ፡ ጋር ፡ እየተመላለሱ ፡ ከዳባሩአ ፡ ወደአክሱም ፡ ከአክሱም ፡ ወደ ምጥዋ ፡ እየተመላለሱ ፡ የመርከብ ፡ ወሬ ፡ ሲጠይቁ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፤ አሳለፉ ። ይበል ጥም ፡ ጊዜያቸውን ፡ ያሳለፉት ፡ አክሱም ፡ ስለሆነ ፡ እዚያ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ፫ሺ ፡ መስፈሪያ ፡ (ቁና) ፡ እህል ፤ መቶ ፡ ሠንጋ ፤ መቶ ፡ በግ ፤ መቶ ፡ ማሠሮ ፡ ማር ፤ መቶ ፡ ማሠሮ ፡ ቅቤ ፡ ድርጎ ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ድርጎ ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም፡ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ተከታዩና ፡ አጃቢው ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ ንጉሡም ፡ እነዚህን ፡ መላ ክተኞች ፡ ማስደሰት ፡ ስለሚፈልጉ ፡ በየጊዜው ፡ ተሰጥቶ ፡ ይሆናል ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ አማኑኤል ፡ ሞቶ ፡ ልጁ ፡ ዮሐንስ፡ በዙፋኑ ፡ መተካቱ ፡ ስለተሰማ ፡ በፖርቱጋሎቹ ፡ ዘንድ ፡ ኀዘን ፡ ሆኖ ፡ ሰነበተ ። ንጉሡም ፡ ፫ ቀን ፡ በአዋጅ ፡ ኀዘኑን ፡ አከበሩ ። ስለዚህም ፡ እንደገና ፡ ላዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ ሌላ ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፡ በመጨረሻ ፡ የሚጠበቀው ፡ መርከብ ፡ እንደ፡ ኢው ፡ ቍጥር ፡ በ፲፭፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ሂክቶር ፡ ዴ ፡ ሲልቬይራ፡ የሚባል ፡ መኰንን ፡ ይዞ ፡ ምጥዋ ፡ መጥቶ ፡ ፖርቱጋሎቹንና ፡ አባ ፡ ጸጋ ፡ ዘአ ብን ፡ ይዟቸው ፡ ሄደ ።

በንግሥት ፡ እሌኒ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ አሁንም ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ለአማኑኤልና ፡ ለልጁ ፡ ለዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ የላኩ ትን ፡ ደብዳቤ ፡ ትክክለኛ ፡ ቅጅውን ፡ ማግኘት ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ብተመለከትሁት ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ አጋጥሞኝ ፡ አያውቅም ፡ ከአ ራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ የበለጠው ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ትርጕሙ ፡ እንጂ ፡ ዋናው ፡ ፖርቱጋሎቹም ፡ እንዳላቸው ፡ አላረጋግጥም ። ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ በአልቫሬጽና ፡ ይል ቁንም ፡ በዋናው ፡ በፖርቱጋሉ ፡ ደራሲ ፡ በእስጢፋኖስ ፡ ፔሬይራ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ በተገኘ ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዛሬን ፡ ቴምፖራል ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ በየጊዜው ፡ ከቋንቋ ፡ ወደቋንቋ ፡ ተተርጕሟል ። የሥሩን ፡ ጽሑፍ፡ በአበሻ ፡ ቋንቋ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ በግዕዝ ፡ ወይም ፡ በአማርኛ ፡ መሆኑን ፡ አይገ ልጽም ። ነገር ፡ ግን ፡ በንግሥት ፡ እሌኒ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወደአማኑኤልም ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ ወደዮሐንስም ፡ የተጻፈበት ፡ ቋንቋ ፡ ግዕዝ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ መጀመሪያ፡ ከግዕዝ ፡ ወደፖርቱጋል ፡ ተተርጕሞ ፡ ንጉሡ ፡ እንዲመለከተው ፡ ተደረገ ። ቀጥሎ፡ በጉዳዩ ፡ የሚገባው ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ጳጳስ ፡ ይመለከተው ፡ ዘንድ ፡ ወደላቲንና ፡ ወደቶስካን ፡ ተተረጐመ ። በመጨረሻም ፡ ከቶስካን ፡ (ከኢጣልያ) ፡ ቋንቋ ፡ ወደ ቀድሞው ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ ተተረጐመ ። የቀድሞው ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ ከዛሬው ፡ አልፎ፡

አልፎ ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ ቢሆንም ፡ ልብ ፡ አድርጎ ፡ ለሚከታተለው ፡ ትርጉሙ ፡ በጣም ፡ አያስቸግርም ፤ ከዚሁ ፡ ከቀድሞው ፡ የፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ እነሆ ፡ ወደ አማርኛ ፡ ተርጕሜዋለሁና ፡ ቃሉን ፡ እንመ[illegible]ከት ።

«በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘአልበ ፡ ቅድምና ፡ ወበስመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልዱ ፡ ዋሕድ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ .......

ስሜ ፡ ዕጣነ ፡ ድንግል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ ድንግል ፡ ያበራችለት ፡ ይኸም ፡ ስም ፡ የተሰጠኝ ፡ ቅድስት ፡ ጥምቀትን ፡ በተቀበልሁበት ፡ ቀን ፡ ነው ፡ በነገሥሁ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ተባልሁ ። ዳዊት ፡ ፍቁረ ፡ እግዚእ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ የሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ....፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ በሥጋ ፡ የናሁ ፡ (ናዖድ) ፡ ልጅ ። የላይኛውና ፡ የታችኛው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የትልልቆቹም ፡ የነጋሢ ፡ ግዛቶች ፡ የክሰአ ? ፡ ንጉሥ ፡ የከፋታ ፡ (ከፋ) ፤ የፈጠጋር ፡ የአንጎት ፡ የባሩ ፤ የበአሊንገዝ ፣ የእድአ ፤ የቫንግ ፡ (ወንጅ) ፡ ዓባይ ፡ የሚፈልቅበት ፡ የጎዣም ፤ የአማራ ፤ የቢጋሚድሪ ፡ (ቤጌምድር) ፡ የአምቢያ ፡ (ደምቢያ) ፡ የዋኝ ፡ የትግሬመሆም ፡ (ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ወይም ፡ ትግሬ ፡ መሆኔ) ፤ ንግሥት ፡ ሳባ ፡ የወጣችበት ፡ የሳባይም ፡ (ሳበ) ፤ የበርናጋስ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥት ፡ በመጨረሻ ፡ እስከ ፡ ኑብያ ፡ ያለው ፡ ግዛት ፡ ጌታ ፡ እርሱም ፡ ከግብጽ ፡ የሚዋሰን ።

ከፍ ፡ ላለውና ፡ ለኃይለኛው ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ለአማኑኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ የሚኖረው ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ አጽንቶ ፡ የያዘ ፡ የሐዋርያት ፡ የጴጥሮስና ፡ የጳውሎስ ፡ ልጅ ፤ የክ[illegible]ስቲያኖች ፡ ወዳጅ ፡ የእስላሞች ፡ ዋና ፡ ጠላትና ፡ ዳኛ ፤ የአፍሪካ ፡ አገር ፡ የጉኔ ፡ (ጉይኔ) ፡ የፕሮሞንቷር ፡ የሉን ፡ ደሴት ፡ የቀይ ፡ ባሕር ፡ የዐረብ ፡ የፋርስ ፡ የኦርሙስ ፡ የታላቂቱ ፡ ሕንድና ፡ የደሴቶች ፡ ሁሉ ፡ በዙሪያውም ፡ የሚገኙ ፡ አገሮችና ፡ የታላላቅ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ አዳራሾች ፡ ጌታ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ተከላካይ ።

ደጉ ፡ ንጉሥ ፡ አማኑኤል ፡ ሆይ ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ።

እስላሞችን ፤ የክርስቲያኖችን ፡ ጠላት ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ አረመኔ ፡ ታብርራቸው ፡ ትዘርፋቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌታ ፡ ኃይል ፡ ሰጠህ ።

አሁንም ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ለንግሥቲቱም ፡ ለውዲቱ ፡ ጓደኛህ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋውን ፡ የሰጣት ፤ የድንግል ፡ ማርያም ፡ አገልጋይ ፤ ለወንዶች ፡ ልጆችህም ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፤ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ መዓዛው ፡ በሚጣፍጥ ፡ የጽጌረዳ ፡ አበባ ፡ በሞላበት ፡ አትክልት ፡ እንደተቀመጥህ ፡ ሁሉ ፡ ደስታህን ፡ የምታይ ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችህም ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ ሥጋጃው ፡ በተነጠፈበት ፡ የመሳፍንቶችና ፡ ያለቆች ፡ አዳራሽ ፡ በጥሩ ፡ ልብስ ፡ አጊጠው ፡ ለሚታዩት....ለዳኞችህና ፡ ለአማካሪዎችህ ፡ ለጦር ፡ አለቆችህም ፡ ሰላም ፡ ይሁን ።

ከአይሁድና ፡ ከአረመኔዎች ፡ ( እስላሞች ? ) በቀር ፡ ሳገርም ፡ ለሕዝብም ፡ ለከተሞችም ፡ ለዓለምም ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ ቡራኬዬንና ፡ ምኞቱንም ፡ ከመጨረሴ ፡ በፊት ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለታመኑት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ አሜን ።

ጌታዬና ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ በመላክተኞችንና ፡ በወዳጆችን ፡ በግቲዎስ ፡ በኩል ስሜን ፡ በአወቅህ ፡ ጊዜ ፡ የግዛትህን ፡ አማከሪዎች ፡ ጳጳሳትን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትን ፡ የግዛትህን ፡ ቀሳውስት ፡ ስለሰበሰብህና ፡ መላክተኛዬን ፡ በመላኬ ፡ ለጌታ ፡ አምላክ ፡ ምሥጋና ፡ ስለአቀረብህ ፡ በንተ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

መላክተኛውንም ፡ በክብር ፡ መልክም ፡ አቀባበል ፡ አደረጋችሁለት ፡ ፡ በዚህም ፡ ከናንተ ፡ ይበልጥ ፡ እኔን ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገንሁ በግዛቴ ፡ ያለም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ይኸን ቀን ፡ አከበረ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ መላክተኛ ፡ እግዛቴ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ እገዳመ ፡ ራእየ? መሞቱን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ደስታዬ ፡ ወደ ፡ ኀዘን ፡ ተለወጠ ።

እኔ ፡ ወደዚያ ፡ ስለአላክሁትና ፡ ይኸ ፡ ችግር ፡ ስለአልደረሰ ፡ ተጽናንቼ ፡ አለሁ ? በዚያን ፡ ዘመን ፡ አባቴ ፡ ሞቶ ፡ እኔ ፡ ዘውድ ፡ ጭኜ ፡ የነገሥሁ ጊዜ ፡ ዕድሜዬ ገና ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ነበር ፡ ስለዚህም ፡ መንግሥቴ ፡ ይመራ የነበረው ፡ እንደ ፡ እናቴ ፡ በምመለከታት ፡ በንግሥት ፡ እሌኒ እጅ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ የአረመኔዎቹን ፡ አገር ፡ ለማለፍ ፡ ሲል ፡ አብርሃም ፡ የሚባለውን ፡ ስሙን ፡ መለወጡን ፡ አልሰማሁም ፡ በማውራታንያ ፡ አገር ፡ በዳቡል ፡ ክርስቲያን ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ከታሠረ ፡ በኋላ ፡ የኔ ፡ መላክተኛ ፡ መሆኑን ፡ ሲሰሙ ፡ ያንተ ፡ ገዢዎች ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ከታሠረበት ፡ አስፈትተው ፡ እግርማዊነትህ ፡ ፊት ፡ እንዲቀርብ ፡ በመርከብ ፡ አሳፍረው ፡ ላኩት ።

በዚያም ፡ ደርሶ ፡ የተላከበትን ፡ መልእክት ፡ በገለጸልህ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ አለቃህ ፡ ሎፕ ፡ ደ ፡ ሰኪዬሬ ፡ (Lopez de Sequeira) ፡ በላከው ፡ እንዳስታወቀኝ ፡ መላክተኛውን ፡ በመልክም ፡ አቀባበልና ፡ በደግነት ፡ እንደተቀበልኸውና ፡ ስጦታም ፡ እንዳደረግህለት ፡ ሰማሁ ፡ የዚህንም ፡ ወሬ ፡ በደብዳቤ ፡ ያመጡልኝ ፡ ሰዎች ፡ ከኤድዋር ፡ ጋልቭም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጋልቭም ፡ በከሚራን ፡ (ከማራን) ፡ ደሴት ፡ መሞቱ ፡ ያሳዝናል ። ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የትልቅ ፡ ሰው ፡ መሞት ፡ በጣም ፡ አሳዝኖኛል ። ከንተም ፡ ዘንድ ፡ የመጡት ፡ ሰዎች ፡ በደረታቸው ፡ መስቀል ፡ አድርገው ፡ ባይ ፡ የክርስቲያንነታቸው ፡ ምልክት ፡ የቀናችው ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ በመሆናቸው ፡ ደስ ብሎኝ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሥጋና አቀረብሁ ። ከታላቅነትህ ፡ ዘንድ ፡ የመጡ እንደመሆናቸው ፡ ተቀብዬ ፡ አነጋገርሁዋቸው ። እነሱም ፡ በመርከብ ፡ ሲመጡ ፡ የገጠማቸውን ፡ ችግር ፡ ወደኢትዮጵያም ፡ ለመድረስ ፡ ተአምራት ፡ ያደረጉትን ሁሉ ፡ ከነሱ ፡ እየሰማሁ ፡ ደስ ፡ አለኝ ። እነሱም ፡ እንደ ፡ ገለጹልኝ ፡ የጦሩ ፡ አለቃ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲዞር ፡ ቆይቶ ፡ ስለ፡ ነበረ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ አገራችንን ፡ ለማየት ፡ በፍጹም ፡ ተስፋ ፡ አጥቶ ፡ ወደሕንድ ፡ ለመመለስ ፡ አስቦ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለርሱና ፡ ለጓደኞቹ ፡ ስለራራለት ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከተቸገሩ ፡

በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀይ ፡ መስቀል ፡ ምልክት ፡ አሳያቸው ። የቀይ ፡ መስቀሉም ፡ ምልክት ፡ በቀጥታ ፡ እኛ ፡ ወደአለንበት ፡ ቀበሌ ፡ አመጣቸው ። ይኸም ፡ እንደተአምራት ፡ የሚቈጥሩና ፡ የጦር ፡ አለቃው ፡ (ክፒቴኑ) ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅና ፡ ደግ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል ። እግዚአብሔርም ፡ በቅዱሳን ፡ አበውና ፡ በቅዱስ ፡ ፌቅጦር ፡ የሕማም ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆነ ፡ መስፍን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ መጥቶ ፡ እንዲገናኝና ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዲያደርግ ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ገልጿል ።

ይህ ፡ ትንቢት ፡ በዘመኔ ፡ ይፈጸማል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ ሳላደርግ ፡ ፈቃዱ ፡ ሆኖ ፡ ስለፈጸመው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ይመስገን ። እርሱም በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባቴ ፡ ለሆንኸው ፡ ላንተ ፡ ለወዳጄ ፡ ለወደፊቴ ፡ መልእክትና ፡ መላክተኛ ፡ ለመላክና ፡ ….. ፡ በቀናችይቱ ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ እንድንሆን ፡ አደረገን ። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሆነ ፡ ከአንድ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግና ፡ ለመተዋወቅ ፡ አልሆነልኝም ፡ ነበር ። እውነተኛውን ፡ የክርስቶስን ፡ እውቀት ፡ ለማወቅ ፡ ባልተጠሩት ፡ በአረመኔዎችና ፡ በመሐመድ ፡ ልጆች ፡ በተከበብሁበት ፡ ሰዓት ፡ በገሬና ፡ በመሬቴ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ይኸን ፡ ሰዓት ፡ በግምት ፡ እጠባበቅ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ አረመኔዎች ፡ ከመካከላቸው ፡ ግማሾቹ ፡ በዛፍና ፡ በእሳት ፡ ግማሾቹ ፡ በፀሐይ ፡ አንድ ፡ አንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ እባብ ፡ አምላካቸው ፡ እንደሆነ ፡ የሚያምኑ ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ ከእውነተኛይቱ ፡ ሃይማኖት ፡ መንገድ ፡ የወጡ ፡ ምኞች ፡ ውሾች ፡ አድርጌ ፡ ከመቍጠር ፡ በቀር ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ማድረግም ፡ መተዋወቅም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ማድረግም ፡ በፍጹም ፡ አልፈለግሁም ። አሁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ከጠላቶቼ ፡ አርፌ ያለሁ ፡ እነዚህም ፡ የሚያስፈሩት ፡ ጠላቶቼ ፡ ወደወሰን ፡ ሲቀርቡ ፡ የኔ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ እያባረሩ ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አድርገው ፡ ይመልሷቸዋል ። በዚህም ፡ ዳዊት ፡ በመዝሙሩ ፡ የንጉሥን ፡ ምኞት ፡ ፈጽም ፡ ምኞቱ ፡ የቀና ፡ ነውና ፡ እንደሚለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳቴና ፡ ደጋፊዬ ፡ ስለሆነ ፡ እንደማያሳፍረኝ ፡ አወቅሁ ። ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የሚመሰገነው ፡ እርሱ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ። ስለዚህም ፡ ያለእረፍት ፡ ምሥጋና ፡ እያቀረብሁ ፡ ቅዱስ ፡ ቃሉንና ፡ የማያልቀውን ፡ ደግነቱን ፡ የማይመረመረውን ፡ ኃይሉን ፡ አስተምራለሁ ። በዚህም ፡ ባንተም ፡ በኔም ፡ ግዛት ፡ የሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ ዘለዓለማዊውን ፡ ክብር ፡ እንዲወርሱ ፡ እመኛለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ የጌታን ፡ (የክርስቶስን) ፡ ሕግ ፡ አብዝተህ ፡ ከጸናህና ፡ ከሰፋህ ፡ አይቀር ፡ እንደምንም ፡ ብለህ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ጠላት ፡ በሆኑት ፡ በአረመኔና ፡ በእስላሞች ፡ ዛሬ ፡ የተያዘውን ፡ ቅዱስ ፡ መቃብር ፡ የሚገኝበትን ፡ ሥፍራ ፡ (ኢየሩሳሌምን) ፡ ልታስለቅቅ ፡ ይገባል ። ይኸን ፡ ብታደርግ ፡ ስምህ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ይሆናል ።

ወደጉዳያችን ፡ እንመለስና ፡ ከማቴዎስ ፡ ጋር ፡ ከመጡት ፡ መላክተኞችህ ፡ ፫ ፡ ሞቱ ፡ የጦር ፡ ሹሙ ፡ (ክፒቴኑ) ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ማክሱዋ ፡ (ምጥዋ) ፡ የኛ ገበርና ፡ ዜጋ ፡ ከሆነው ፡ ከባርነጋስ ፡ (ከባሕር ፡ ነጋሽ) ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ተነጋግሮ ፡ መላክተኞቼን ፡ ወደኔ ፡ ከሚ

ያማምርና ፡ ደስ ፡ ከሚያሰኝ ፡ ገጹ ፡ በረከት ፡ ጋር ፡ ልኳቸው ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ተቀበልኋቸው ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ደስ ፡ ያለኝ ፡ ስምህን ፡ መስማቴ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የአረመኔዎቹን ፡ አገር ፡ በወዴት ፡ በኩል ፡ ሔዶ፡ ለመውረር ፡ መመከከር ፡ ይዘናል። ከኔ ፡ በኩል ፡ በማናቸውም ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ባለኝ ፡ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ለመሥራት ፡ የተዘጋጀሁ ፡ ነኝ ፡ ከሁኑም ፡ ዠምሮ ፡ ሺ ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ (100.000.000–መቶ ፡ ሚሊዮን) ፡ የወርቅ ፡ ድራህም ፡ (1) ፡ እንደዚሁም ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ብረታ ፡ ብረት ፡ እንጨት ፡ ስንቅ ፡ ለመ ስጠት ፡ ተስፋ ፡ እሰጣለሁ ። ከዚያ ፡ ወዴኔ ፡ የላክኸው ፡ ሮድሪክ ፡ ደ ፡ ሊማ ፡ የሚባለው ፡ ካፒቴንና ፡ የተወደደው ፡ ወዳጃችን ፡ ጠንቃቃውና ፡ ሃይማኖታሙ ፡ ፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝ ፡ ባንድነት ፡ ይገኛሉ ። አልቫሬዝም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብዙ ፡ አንቀጾች ፡ ብንጠይቀው ፡ የተተከከለ ፡ ደንበኛ ፡ መልስ ፡ የሰጠን ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ለዚህ ፡ ላሰብነው ፡ ለታላቁ ፡ ጉዳይ ፡ በመከከላችን ፡ መላክ ተኛ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይኸን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደረጃና ፡ ክብር ፡ ሊያገኝ ፡ የሚገባው ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ በመንግሥቴ ፡ ወሰን ፡ ያሉትን ፡ የማክሱዋን ፡ (ምጥዋ) ፡ የላቃን ፡ (ላክ?) ፡ የዘይላምን ፡ (ዘይላ) ፡ የመሮሬን ፡ (መርዌ?) ደሴ ቶች ፡ ሕዝቦች ፡ እያስተማረ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲያደርጋቸው ፡ በተለይ ፡ ሥልጣን ፡ በእጁ ፡ ሰጥቼዋለሁ ። ለዚህ ፡ ክብርና ፡ ሹመት ፡ የሚገባው ፡ መሆ ኑንም ፡ ከመረመርሁ ፡ በኋላ ፡ የሽልማት ፡ ልብሴን ፡ መስቀሌን ፡ ከፍ ፡ ያለ፡ ሥልጣን ፡ እንዲያገኝ ፡ በትረ ፡ መንግሥቴን ፡ ሰጥቼው ፡ የነዚህ ፡ አገሮችና ፡ ደሴቶች ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ እንዲሆን ፡ ሾሜዋለሁ ። እግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ አሳብህን ፡ እንዲፈጽምልህ ፡ በጠላቶችህም ፡ ላይ ፡ ድልን ፡ እንዲሰ ጥህና ፡ ከእግርህ ፡ በታች ፡ እንዲወድቁና ፡ ምሕረት ፡ እንዲለምኑህ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። እግዚአብሔር ፡ እኛም ፡ ተስፋ ፡ የምናደርገውንና ፡ የምትመኘ ውን ፡ ዘለዓለማዊ ፡ ሕይወት ፡ ይስጥህ ። ደግነትህን ፡ ትሩፋትህን ፡ ተግባርህን፡ ሁሉ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰምቼ ፡ ባይኔ ፡ እንዳየሁና ፡ እንደሰማሁ ፡ ሆኜ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ከተስፋ ፡ አልፎ ፡ ለልቤ ፡ የሰጠኝን ፡ ደስታ ፡ መናገርና ፡ መተረክ ፡ ያቅተኛል ። ዘውድህ ፡ እየጸና ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ጸጋ ውን ፡ ሰጥቶ ፡ በምግባርህ፡ ለላይኛው፡ መንግሥቱ፡ እንዲያበቃህ፡ እለምናለሁ ፡ አሜን ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ አባትና ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ እርስ ፡ በራሳችን ፡ እየተረዳዳን በፍቅር ፡ እንድንኖር ፡ እለምናለሁ ። ከኔ ፡ ወገን ፡ እንደልጅህ ፡ አድርገህ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝህንና ፡ የምታዝዘኝን ፡ እንደ ፡ ልማዴ ፡ ለመፈጸም ፡ ተስፋ ፡ እሰጥሀለሁ ፡ በዚህም ፡ ሌላ ፡ አላስገባም ።

ለመላክተኞችህም በመከከላችን ፡ የሃይማኖት ፡ ልዩነትና ፡ መከፋፈል ፡ እንዳይኖር ፡ ስል ፡ በማክሱአ ፡ በላክ ፡ በወ[illegible]ቹም ፡ ሁሉ ፡ እንደልባቸው ፡

(1) ጥንትነግሪኮች ፡ ይገበያዩበት ፡ የነበረ ፡ የወርቅ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቁጥሩ ፡ መቶ ፡ ሚሊዮን ፡ ስለሚደርስ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወርቅ ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ እንዳሸዋ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ያነጋገር ፡ ልማድ ፡ እንጂ ፡ በዘመኑ ፡ ለጦርነት ፡ የሚሆን ፡ 100,000,000 ሚሊዮን ፡ የወርቅ ፡ ድራም ፡ የማያገኙ ፡ አይመስልም ፡ ወይም፡ ተርጓሚው ፡ ተሳስቶ ፡ ይሆናል ።

እንዲሆኑ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቻቸዋለሁ ። ዋናው ፡ አሳባችንም ፡ እንዲከናወን ፤ ያንተ ፡ ሰዎችና ፡ ወታደሮች ፡ ወደባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ቢመጡ ፡ የኔ ፡ ጦር በሥፍራው ፡ ተገኝቶ ፡ ማናቸውንም ፡ እርዳታ ፡ ለማድረግ ፡ ዝግጁ ፡ መሆኑን ፡ ከኔ ፡ ወገን ፡ አረጋግጥልሃለሁ ። በዚህ ፡ በግዛቴ ፡ ጠረፍ ፡ አንድም ፡ ክርስቲያን ፡ የለም ፡ አንድም ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ አይታይም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ለሰዎችህ ፡ በዚያ ፡ የእስላም ፡ ጐረቤት ፡ በሆነው ፡ አገር ፡ እንዲኖሩ ፡ መፍቀዴ ይኸም ፡ ግዛትህን ፡ ለማስፋት ፡ ብቻ ፡ ሳይህን ፡ ከላይ ፡ በአምላካዊ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ አሰብኸው ፡ ሃይማኖትን ፡ ለመጠበቅና ፡ ለመከላከል ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክቼዋለሁ ።

በተረፈ ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ስእል ፡ (ሀውልት ፡ ወይስ ፡ የገንዘብ ፡ ቅርጽ ?) ፡ መሥራት ፡ የሚችሉ ፡ ጐበዛዝት ፡ የብረታ ፡ ብረትና ፡ የእጅ ፡ ብልሃት ፡ ሥራ ፡ የሚያውቁ ፡ ሠራተኞች ፡ ሊቃውንትና ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ ከሌላውም ፡ ጋራ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻሕፍት ፡ ለማተም ፡ ጥበብ ፡ ያላቸውን ፡ አዋቂዎች ፡ እንድትልክልኝ ፡ እለምንሃለሁ ። እነሱም ፡ ሲመጡ ፡ በቤታችን ፡ በብላሽ ፡ አስቀምጠን ፡ እንደምንችለው ፡ ያህል ፡ በታማኝነት ፡ በውል ፡ እያሳደርናቸው ፡ በፈለጉም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ ነፃነት ፡ ሰጥተን ፡ እንደምናሰናብታቸው ፡ በዚህም ፡ ሥፍራ ፡ በደህና ፡ እንደምናኖራቸው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እምልልሃለሁ ። እንደወዳጅ ፡ በልቆጥርህ ፡ ይኸን ፡ አልጠይቅህም ፡ ነበር ። ለመላክተኛዬ ፡ ለማቴዎስ ፡ ያደረግኸውን ፡ መልከም ፡ አቀባበል ፡ በልዩ ፡ ንጉሣዊ ፡ ችሮታህ ፡ የመንገዱን ፡ ኪሣራ ፡ ሁሉ ፡ እንደከፈልከው ፡ ስለማውቅ ፡ እኔም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በፋንታዬ ፡ ብድር ፡ እንድመልስ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። አባት ፡ ልጁ ፡ የሚለምነውን ፡ እምቢ ፡ አይልም ፤ እንግዲህ ፡ አንተ አባቴ ፡ ነህ ፡ እኔም ፡ ልጅህ ፡ ነኝ ። እንዲት ፡ ደንጊያ ፡ ከሌላዋ ፡ ጋር ፡ ሆና ፡ ሁለቱ ፡ ለሕንፃ ፡ እንደሚያገለግሉ ፡ እኔና ፡ አንተም ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ በአንድነት ፡ ተጣምረን ፡ ባንድ ፡ ልብና ፡ በክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ እንድንጓዝ ፡ አሜን ። »

አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ይኸን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ በ፩ሺ፰፻፷፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሰጥተው ፡ ከአሰናበቷቸው ፡ በኋላ ፡ መላክተኞቹ ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ የሚወስዳቸው ፡ መርከብ ፡ እስኪመጣላቸው ፡ ድረስ ፡ በአክሱምና ፡ በምጥዋ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ በሚጠባበቁበት ፡ ጊዜ ፡ አማኑኤል ፡ ሞቶ ፡ በዙፋኑ ፡ ልጁ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ መንገሡ ፡ ተሰማ ። ስለዚህ ፡ የዚህኑ ፡ ወሬ ፡ ወደአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልከው ፡ ኖሮ ፤ በግዛታቸው ፡ ስለሻቱ ፡ ንጉሥ ፡ ኀዘን ፡ በአዋጅ ፡ ከአደረጉ ፡ በኋላ ፡ ላዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ ለዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ ሌላ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቍ ፡ በ፩ሺ፰፻፷፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለመላክተኞቹ ፡ ደግመው ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ መላክተኞቹ ፡ በ፩ሺ፰፻፷፯ ፡ ዓ፡ ም፡ ፡ ከምጥዋ ፡ ተሳፍረው ፡ ሔዱ ።

ስለዚህ ፡ የሁለቱም ፡ ደብዳቤ ፡ አሳብ ፡ አንድ ፡ ስለሆነ ፡ በመጨረሻ ፡ ለሁለቱም ፡ ደብዳቤ ፡ ጠቅላላ ፡ ሐተታ ፡ እስክናደርግ ፡ ድረስ ፡ አሁን ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ለዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ የጻፉትን ፡ ደብዳቤ ፡ እንደዚያው ፡ እንዳለፈው ፡ ከቀድሞው ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ የተረጐምሁትን ፡ እንመልከት ።

«የሚታየውንና ፡ የማይታየውን ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በፈጠረ ፡ ሁሉን ፡ በሚችል ፤ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፤ የአብ ፡ ነቢይና ፡ መላክተኛ ፡ ልጁም ፡ በሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፤ ሐዋርያት ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብኩ ፡ ዘንድ ፡ በጽናና ፤ በነቢያት ፡ አፍ ፡ በተናገረ ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ ትክክል ፡ በሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ሦስትነታቸው ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ በባሕርም ፡ ፍጹም ፡ በሆነው ፡ በሥላሴ ፡ ስም ፡ አሜን ።

እኔ ፡ ዕጣነ ፡ ድንግል ፡ ትርጓሜውም ፡ ድንግል ፡ ያበረችለት ፡ ይኸም ፡ ስም ፡ የተሰጠኝ ፡ ክርስትና ፡ በተነሣሁበት ፡ ቀን ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ በጨበጥሁ ፡ ጊዜ ፡ የፍቅረ ፡ ንግዚእን ፡ የዳዊትን ፡ ስም ፡ የሃይማኖት ፡ ዓምድ ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ የመጣውን ፡ ስም ፡ ወሰድሁ ። የሺኤል ፡ ነገሥታት ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ ልጅ ፤ የዓምደ ፡ ጽዮን ፤ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የበእደ ፡ ማርያም ፡ የናሁ ፡ (ናዖድ ) ፡ ልጅ ፡ በሥጋ ፡ ልደት ። ለትልቁና ፡ ለኃያሉ ፡ መስፍን ፡ ለዶም ፡ ዮሐንስ ፡ የፖርቱጋልና ፡ የአልጋርብ ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ አማኑኤል ፡ ልጅ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምና ፡ ጸጋ ፡ ከንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ አሜን ።

ያባትህን ፡ ችሎቱንና ፡ ኃይሉን ፡ የልቡንም ፡ ደግነት ፡ የጨከኙን ፡ የመሐመድን ፡ ልጆች ፡ መዋጋቱንም ፡ ሁሉ ፡ ከአዋቂዎች ፡ በየጊዜው ፡ ሰምቼ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ይጠበቅና ፡ ይከበር ፡ ዘንድ ፡ ይስፋፋም ፡ ዘንድ ፡ ይኸንን ፡ ድል ፡ ለሰጠው ፡ ሁሉን ፡ ለሚችል ፡ ለሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሥጋና ፡ አቀረብሁ ። እኔም ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ኃይሌን ፡ ሁሉ ፡ ለመጨመር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደተዘጋጀሁ ፡ ነኝ ። አሁንም ፡ በኔና ፡ በአባትህ ፡ ጊዜ ፡ ተዠምሮ ፡ የነበረው ፡ ወዳጅነትና ፡ አንድነት ፡ ባንተም ፡ ጊዜ ፡ መጽደቁን ፡ ከመላክተኞችህ ፡ በመስማቴ ፡ ከቀድሞው ፡ የበለጠ ፡ በደስታ ፡ ግያለሁ ። ስለዚህም ፡ እነዚህን ፡ በግዛታችን ፡ ጠረፍ ፡ ያሉትን ፡ ክፉ ፡ አረመኔዎችና ፡ አሕዛቦች ፡ ለመውጋት ፡ ማናቸውንም ፡ ዕርዳታ ፡ እሰጣለሁ ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ መተሳሰብ ፡ ዕርዳታዬንም ፡ ለማዘዝ ፡ በፍሥሐ ፡ በለሁበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያሳዝነውና ፡ አደገኛው ፡ ያባትህ ፡ ሞት ፡ ስለደረሰኝ ፡ ትልቁ ፡ ደስታዬ ፡ ወደ ፡ ኀዘን ፡ ተለውጦ ፡ አሳቤና ፡ ምኞቴ ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ እሥር ፡ ገብቶ ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቆርጥ ፡ ሆነ ። በገሬ ፡ ያሉት ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ በገዳማት ፡ የሚገኙት ፡ ሁሉ ፡ በጠቅላላው ፡ ዜጋችን ፡ በሆነው ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ አደገኛ ፡ ወሬ ፡ መራራ ፡ ኀዘንንና ፡ ሰቆቃውን ፡ ( ለቅሶ—ወዮ ) ፡ ጣለበት ። ለኔም ፡ ለራሴ ፡ ከነገሥሁበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ መልክተኛና ፡ ደብዳቤ ፡ የተላላክሁት ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ እርሱ ፡ (አማኑኤል ) ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ በርሱ ፡ ክፉ ፡ ሞት ፡ ልቤ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ አዝኗል ። እርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተልከው ፡ ወደኔ ፡ የመጡት ፡ ጕበዛዝት ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ የጨዋ ፡ ወገኖች ፡ (ባሮን) ፡ ካህናት ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ሊቃውንትም ፡ ወደኔ ፡ አገር ፡ በመጡና ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ወገኖች ፡ ቅዳሴያቸውን ፡ አሳምረው ፡ በአሳዩኝ ፡ ጊዜ ፡ በሥርዓታቸው ፡ ደስ ፡ አለኝ ። እኔም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አክብሬ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቴ ፡ ተቀብዬ ፡ ስጦታም ፡ አድርጌ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ በሚመለሱበ

ትም ፡ ጊዜ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ሰጥቼ ፡ አሰናበትኋቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እቅይ ፡ ባሕር ፡
ዳር ፡ እግዛቴ ፡ ጠረፍ ፡ ሆነው ፡ ሲጠባበቁ ፡ አባትህ ፡ አዘላቸው ፡ የነበረው ፡ ዋናው ፡
የጦር ፡ አለቃ ፡ ሳይመጣላቸው ፡ ቀረና ፡ በዚሁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኖረው ፡ ተመለሱ ።
እኔም ፡ ወዲያው ፡ (መልሼ?) ፡ መላክተኛዬን ፡ ክረስቶፍ ፡ ሊከናትን ? ፡ ሞኞቴን ፡
ሁሉ ፡ እንዲገልጽልህ ፡ ወዳንተ ፡ ልኬ ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ቃዝዥነቴን ፡ ለመግ
ለጽ ፡ ወደ ፡ አባታችን ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ (ሮማ) ፡ ፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝን ፡
ላክሁት ። "ጌታውና ፡ ንጉሡ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ከሚቼ ፡ አባትህ ፡ ዠምሮ ፡ በመካ
ከላችን ፡ ስለተመሠረተው ፡ ወዳጅነትና ፡ መረዳዳት ፡ የምነግርህን ፡ ስማኝ ። ከአባ
ትህ ፡ ግንኙነት ፡ ከዠመርን ፡ አንሥቶ ፡ መላክተኞችም ፡ ደብዳቤም ፡ እየመጣልኝ ፡
ልክ ፡ ከወንድሜ ፡ ዘንድ ፡ እንደመጣልኝ ፡ እየተመለከትሁ ፡ ደብዳቤውን ፡ አነ
በው ፡ ነበር ። በኔ ፡ አሳብ ፡ ይህ ፡ የአደረግነው ፡ ግንኙነትና ፡ ዝምድና ፡ ደንበኛና ፡
አግባብ ፡ ያለው ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ሁለታችንም ፡ ክርስቲያን ፡ በመሆናችን ፡
ይቺን ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ለመከላከል ፡ የሁለታችን ፡ ዝምድና ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።
ክፉዎቹ ፡ እስላሞቹ ፡ አረመኔዎቹና ፡ አሕዛቦቹ ፡ እንኳን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተረ
ዳዱ ፡ በሰላም ፡ የመኖርን ፡ ጸጋ ፡ አግኝተዋል ። ወደፊት ፡ ከግብፅ ፡ ንጉሥም ፡ ከሌላ
ውም ፡ አምባሳደርም ፡ መላክተኛም ፡ እንዳልቀበል ፡ እምልልሃለሁ ፤ አንተን ፡ ግርማ
ዊነትህን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙትን ፡ መልክተኞችህን ፡ ብቻ ፡ እቀበላለሁ ። ከሃይማኖታ
ችን ፡ ስለማይገጥሙ ፡ ከአረመኔዎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ወዳጅነ
ትም ፡ የለኝም ። ወዳጆቼ ፡ ቢመስሉም ፡ ይኸን ፡ ወዳጅነት ፡ አመከኝተው ፡ በግዛቴ ፡
የሚገኘውን ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ በያመቱ ፡ እያመላለሱ ፡ ለመውሰድ ፡ ሲሉ ፡ ነው ። ይኸን
ንም ፡ ሲያደርጉ ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ተለይቼ ፡ የመግ
ቢያና ፡ የመውጫ ፡ ፈቃድ ፡ (ፓስፖር) ፡ ሳልከለክላቸው ፡ መቅረቴ ፡ በዚህ ፡ ተና
ደው ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መቃብር ፡ የሚገኝበትን ፡ የኢየሩሳሌምን ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ያቃጥሉታል ፡ ብዬ ፡ ፈርቼ ፡ ነው ። የነሱም ፡ የዘወትር ፡ አሳባቸ
ውና ፡ ምኞታቸው ፡ በግብፅም ፡ በሱርያ ፡ (ሶርያ) ፡ የሚገኘውን ፡ ቅዱስ ፡ ቦታ ፡ ለመ
ዝረፍ ፡ ነው ። ጌታው ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ከአውሮፓ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡
እስካሁን ፡ ተዋውቄ ፡ በነሱ ፡ ልጽናና ፡ አልቻልሁም ። እነሱም ፡ እርስ ፡ በራሳ
ቸው ፡ እየተጣሉ ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ያደርጋሉ ። ደግሞ ፡ ይበልጥ የማዝነው ፡ ከነ
ዚህ ፡ ከአውሮፓ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ መራራቃችን ፡ ነው ። በግዛቴ ፡
ወሰን አንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ በደስታ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በጓደኝነት ፡
እንኖር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ሁሉ
ንም ፡ በትእግሥት ፡ ማድረግ ፡ ይገባኛል ። ስለዚህ ፡ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ ሁልጊዜ ፡ በደ
ብዳቤህና ፡ በመላክተኛህ ፡ እንድትጐበኘኝ ፡ እለምንሃለሁ ። ደብዳቤዎችህንም ፡ ሳነብ ፡
እንዳየሁህ ፡ ያህል ፡ እቆጥረዋለሁ ። አንድ ፡ ወዳጅም ፡ በሩቅ ፡ ላለው ፡ ወዳጁ ፡
ከቅርብ ፡ ካለው ፡ ይበልጥ ፡ እንደ ፡ ገንዘቡ ፡ አድርጎ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያስበዋል ። ይኸም ፡
ጌታችን ፡ በወንጌሉ ፡ «ነበ ፡ ሀሎ ፡ መዝገብከ ፡ ህየ ፡ ይሄሉ ፡ ልብከ ፡ ገንዘብህ ፡ ወዳ

ለበት ፡ ልብህ ፡ ወደዚያ ፡ ይሆናል» ፡ እንዳለው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንድታስበኝ ? አደራ ፡ እልሃለሁ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ የምነግርህን ፡ ሁሉ ፡ አትዘንጋ ። እንደሰ ማሁት ፡ በእውቀት ፡ እንደሚቼ ፡ አባትህ ፡ አዋቂና ፡ ጥንቁቅ ፡ በመሆንህ ፡ ደስ ፡ ብሎ ኛል ፡ አባትህም ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ የተወውን ፡ መልከም ፡ መታሰቢያ ፡ ሳስታውስ ፡ ኀዘኔ ፡ ይቀሰቀሳል ። አሁንም ፡ «በግዛቱ ፡ መንበር ፡ የተቀመጠው ፡ ጠቢቡ ፡ የንጉሥ ፡ አማኑ ኤል ፡ ልጅ ፡ የተባረከ ፡ ይሁን„ ፡ እያልኩ ፡ ለአምላኬ ፡ ምሥጋና ፡ አቀርባለሁ ። ጌታው ፡ አባትህ ፡ እንዳሰበው ፡ እነዚህን ፡ የማያምኑ ፡ አረመኔዎችን ፡ ለመውጋት ፡ ወደኋላ ፡ እንዳትል ፡ እለምንሃለሁ ። ያንተ ፡ ኃይል ፡ ከአባትህ ፡ ያነሰ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ በዚህ ፡ አሳብ ፡ መቆም ፡ አይረባህም ፡ ታላቅ ፡ ስለሆንህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዕርዳታ ፡ እነዚህን ፡ አረመኔዎች ፡ ታሸንፋቸዋለህ ። እኔም ፡ በበኩሌ ፡ ሰውም ፡ ወርቅም ፡ ስን ቅም ፡ በብዙ ፡ ለመስጠትና ፡ ለመርዳት ፡ ተስፋውን ፡ አረጋግጣለሁ ። ይኸም ፡ ሁሉ ፡ (ሰው ፡ ወርቅ ) ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፤ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ የበ ረከተ ፡ ነው ።እንደዚህ ፡ አድርገን ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ አሻልተን ፡ ከሠራን ፡ የአረመ ኔዎቹንና ፡ የማውሪታንያን ፡ አገር ፡ ( ሰሜን ፡ አፍሪካን)፡ በእጃችን ፡ ለማድረግ ፡ እንች ላለን ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ የምለምንህ ፡ ዜጋዎቼንና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቼን ፡ የጦር ፡ ሥርዓ ትና ፡ የሰልፍ ፡ አጠባበቅ ፡ ደንብ ፡ የሚያስተምሩ ፡ የጦር ፡ ጥበብና ፡ ልምድ ፡ ያላቸ ውን ፡ ሰዎች ፡ እንድትልክልኝ ፡ ነው ። ያንተ ፡ ኃይል ፡ ብዙ ፡ ነው ። ዕድሜ ህም ፡ ከሰሎሞን ፡ የበለጠ ፡ ስለሆነ ፡ ጠንክሩ ፡ ነህ ። ሰሎሞን ፡ ሲነግሥ ፡ ፲፪ ፡ ዓመቱ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከአባቱ ፡ ይበልጥ ፡ ዠግንነትና ፡ ጥበብ ፡ ሠራ ። ሌላም ፡ ምሳሌ ፡ ደግሞ ፡ አባቴ ፡ ናሁ ፡ (ናዖድ ) ፡ ሲሞት ፡ እኔ ፡ ፲፩ ፡ ዓመቴ ፡ ነበር ፡ በእግ ዚአብሔር ፡ ዕርዳታ ፡ ከነገሥሁ ፡ ወዲህ ፡ በግዛቴ ፡ ወሰን ፡ ያሉትን ፡ አገሮችና ፡ መን ግሥቶች ፡ አስገበርሁ ። ስለዚህ ፡ አንተንም ፡ እኔንም ፡ ለረዳን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለ ታችንም ፡ ምሥጋና ፡ እናቅርብ ። ጌታና ፡ ወንድም ፡ ሆይ ፡ ስእል ፡ የሚሠሩ ፤ መጽ ሐፍ ፡ የሚያትሙ ፤ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሚሠሩ ፤ ፕላን ፡ ሠሪ ፤ አናጢ ፤ የመቅደድንና ፡ የአካልን ፡ ባሕል ፡ የሚያውቁ ፡ ሐኪሞች ፡ (ሺሩርዢያንና ፡ ፊዚሲያን) ፡ እንደዚ ሁም ፡ ወርቅን ፡ ብርን ፡ ብረታ ፡ ብረትን ፡ የሚያወጡ ፡ የማዕድን ፡ ሠራተኞች ፡ ቅርጽ ፡ መቅረጽ ፡ የሚያውቁትን ፡ ደህና ፡ ደህና ፡ ሠራተኞች ፡ እንድትልክልኝ ፡ እለምንሃ ለሁ ። ይልቁንም ፡ ፕሎምብ ፡ ማልበስ ፤ ዕጡብ ፡ መሥራት ፡ የሚችሉ ፡ ላክልኝ ። በጠቅላላው ፡ ሁሉም ፡ ሠራተኛ ፡ በየዓይነቱ ፡ ያስፈልገኛል ። ለጊዜው ፡ በጣም ፡ የሚያስፈልገኝ ፡ ሐርከቡዝ ፡ (ረዥም ፡ የጥንት ፡ ጠበንዥ ፡) ታላላቀ ፡ መድፍ ፡ የሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸው ።

ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ ሊረዳው ፡ እንደሚችል ፡ አንተም ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ እርዳኝ ። እንደዚህም ፡ ሲሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳንና ፡ ዋናው ፡ አሳብ ችን ፡ እፍጻሜ ፡ ይደርሳል ፡ የቅዱሳኑን ፡ የአቤልን ፤ የኖህን ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፤ አብርሃም ፡ በሚድያን ፡ ምድር ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ ይስሐቅ ፡ ከመሐላ ፡ ጉድጓድ ፡ የዳነ ፡ ጊዜ ? ፤ ያዕቆብ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፤ ሙሴ ፡ ግብጽ ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፤ አሮን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፤ ኢያሱ ፡ የኑን ፡ ልጅ ፡ በጌልጌላ ፡ በነበረ ፡

ጊዜ ፤ የጌዴዎንን ፤ የሶምሶንን ፡ በድርቅ ፡ መሬት ፡ ወሀ ፡ በጠማው ፡ ጊዜ ፤ ሳሙኤል ፡ ራማ ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፤ ዳዊት ፡ በናዮት ? ፡ የሰሎሞንን ፤ የናታንን ፤ ዮሳፍጥ፡ እጦርነት ፡ ለይ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፤ ምናሴ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ ወደእግዚአብሔር፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፤ ዳንኤል ፡ ከአንበሶች ፡ ጋር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፤ ሲድራክ ፡ ሚሳክ ፡ አብድናጎን ፡ (፫ቱ ፡ ደቂቅ) ፡ በነበልባለ ፡ እሳት ፡ በተጣሉ ፡ ጊዜ ፤ ሐና ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የነበረች ፡ ጊዜ ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ ከዘሩባቤል ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የሠራውን፡ የነህምያን ፤ ማታትያስ ከልጆቹ ፡ (መቃብያን) ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ በዓለም ፡ ሩብ ፡ ላይ፡ በነበረ (በዞረ ?) ፡ ጊዜ ፡ በመጨረሻ ፡ የተባረከውን ፡ . . . . መሥዋዕትና፡ ጸሎት ፡ እንደሰማ ፡ ያንተንም ፡ ጸሎትና ፡ ስለት ፡ እየሰማ ፡ ምኞትህን ፡ በደስታ፡ እየፈጸመ ፡ ከጠላቶችህ ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቅህ ። የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ሁልጊዜ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ። በቅድስና ፡ በፍቅር ፡ ክንድ ፡ ስሜ ፡ እሳለምሃለሁ ፡ እንደ አንተም ፡ አማካሪዎችህን ፡ ጳጳሳትህን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትህን ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናትህን ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ ቡራኬ ፡ ዘወትር ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፡ አሜን ። »

በነዚህ ፡ በአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ደብዳቤዎች ፡ የምንረዳው ፡ ሁለት ፡ ዋና፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው ። ከነዚሁ ፤

፩ኛው ፡ ከክርስቲያኑ ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ የጠበቀ ፡ የቃል ፡ ኪዳን፡ ጓደኝነት ፡ አድርገው ፡ ዘወትር ፡ የሚያሠጉዋቸውን ፡ እስላሞቹን ፡ ለማጥቃት ።

፪ኛው ፡ ከሰለጠነው ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፡ የሚያውቁ ፡ መምህራን ፡ አስመጥተው ፡ አገራቸውን ፡ ለማሠልጠን ፡ ነው ።

በየጊዜው ፡ በደዋሮ ፡ በይፋት ፡ በአዳል ፡ ግዛት ፡ ከእስላሞቹ ፡ ባላባቶች ፡ ከግ ጋር ፡ ዘወትር ፡ ግጭቱ ፡ ባያቋርጥም ፡ እነሱንም ፡ ከሚደግፏቸው ፡ ከቱርኮች ፡ ብጾችም ፡ ጋር ፡ መፈራረትና ፡ መጠባበቅ ፡ ባይቀር ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ከፊት ፡ ዠምሮ ንግሥት ፡ እሌኒም ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ ከእስላሞቹ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ የጉርብትና ፡ ወዳጅነት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ፈትነዋል ። ኢብን ፡ እያስ፡ የሚባለው ፡ እንደጻፈው ፡ በሂጅራ ፡ ፱፻፳፬ ፡ (፲፭፻፲፰ ዓ፡ ም፡ እንደ ፡ ኢት ፡ ቍጥር) ፡ የኢትዮጵያ ፡ መላክተኞች ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ይዘው ፡ ከይሮ ፡ ሄደው ፡ በዚህ ፡ ዘመን፡ ለነበረው ፡ ሡልጣን ፡ ማሜሉክ ፡ ሰጥተው ፡ ሡልጣኑም ፡ በክብር ፡ ተቀብሎ ፡ አነጋግሯቸዋል ። ከነዚሁ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ንግድም ፡ ደብዳቤም ፡ መለዋወጥ ፡ ለጊዜው ፡ አልቀረም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እስላሞቹ ፡ ባለፈው ፡ ለማጎፋገዝ ፡ የሰጡት ፡ እርዳታ ፡ ወደፊት ፡ ደግሞ ፡ ለሚነሣው ፡ ለግራኝ ፡ አህመድ ፡ የሚሰጡት ፡ ለንጉሠ፡ ለአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ስለታወቃቸው ፡ በፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ ችላ ፡ ሊሉት ፡ አስበው ፡ የነበረውን ፡ የፖርቱጋልን ፡ ግንኙነት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አጥብቀው ፡ ፈልገውታል ። በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የፖርቱጋል ፡ የጦር ፡ መኰንኖች ፡ በመርከብ ፡ እስከ ፡ ዘይላ ፡ እስከ ፡ ዛንዚባር ፡ ድረስ ፡ እየመጡ ፡ በእስላሞቹ ፡ በቱርኮች ወታ

ደሮች ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ ጉዳት ፡ ማድረጋቸውን ፡ አጠገባቸው ፡ ከአሉት ፡ ከነአል
ቫሬዝ ፡ ከነቤርሙዴዝ ፡ ስለሰሙ ፡ ከእስላም ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ መስማማትም ፡
ለዘለቄታ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ በመገመት ፡ የዚህኛውን ፡ የዝምድና ፡ መንገድ ፡
ለቀው ፡ በሃይማኖት ፡ ከሚቀርባቸው ፡ የባላጋሮቻቸው ፡ ባላጋራ ፡ ከሆነው ፡ ከፖ
ርቱጋል ፡ ጋር ፡ መሆንን ፡ መርጠዋል ። በደብዳቤያቸው ፡ ውስጥ ፡ ከእንግዲህ ፡
ወዲህ ፡ ከግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ መልክተኛ ፡ አልቀበልም ፡ ሲሉ ፡ ጨርሰው ፡ መቁረ
ጣቸውን ፡ ያስረዳል ። ምናልባት ፡ ለጊዜው ፡ ይህ ፡ ዝንባሌያቸው ፡ በእስላሞቹ ፡
ዘንድ ፡ በግልጽ ፡ እንዳይታወቅ ፡ ፈልገው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ቍጥራቸው ፡
የበዙ ፡ መልክተኞች ፡ በሚመላለሱበት ፡ ጊዜ ፡ አማኑኤል ፡ ሞቶ ፡ ኀዘኑን ፡ በአ
ዋጅ ፡ ሲያከብሩ ፡ ይህ ፡ ቃል ኪዳንና ፡ ዝምድና ፡ ለእስላሞቹ ፡ ሊሠወራቸው ፡
ዝምድናውም ፡ በማን ፡ ላይ ፡ መሆኑ ፡ ሊዘነጋቸው ፡ አይቻልም ። ከሁሉ ፡ የበ
ለጠ ፡ ደግሞ ፡ ፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝን ፡ የእስላም ፡ ነክ ፡ በሆኑት ፡ የጠረፍ ፡
አገሮች ፡ በምጥዋ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ብለው ፡ ሲሾሙት ፡ በርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የብ
ልሃት ፡ መንገድ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ ሁሉ ፡ የእስላሞቹን ፡
ጠብና ፡ ግንጋኔ ፡ እያባሰ ፡ ሊሄድ ፡ የሚችል ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የዚህን ፡ የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከመከታተል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ላገራቸው ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ አለመኖ
ሩን ፡ ብቻቸውንም ፡ ሆነው ፡ የከበደውን ፡ የእስላሞች ፡ ወረራ ፡ እንደማይገፉት ፡
ስለተረዱት ፡ እነሆ ፡ በደብዳቤያቸው ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ አጥብቀው ፡ ይጠይቃሉ ።
ሿሚቱን ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ አማኑኤልን ፡ በሽምግልናው ፡ እንደ ፡ አባት ፡ ልጁን ፡
ዮሐንስን ፡ በወጣትነቱ ፡ እንደወንድም ፡ አድርገው ፡ እርሳቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡
ወታደርና ፡ ስንቅ ፡ እርዳታ ፡ ለፖርቱጋል ፡ ሰጥተው ፡ የሁለቱ ፡ ኃይል ፡ ተባብሮ ፡
የእስላምን ፡ ኃይል ፡ እንዲሰብርና ፡ የአገራቸው ፡ ክርስቲያን ፡ በእረፍት ፡ እንዲ
ኖር ፡ በወሰናቸው ፡ ላይ ፡ ተፋላሚ ፡ ባላባቶች ፡ እንዲደክሙ ፡ የጌታ ፡ መቃብር ፡
የሚገኝበት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከቱርክ ፡ ገዥነት ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ መነኮሳቱና ፡ ምዕመናኑ ፡ እንደልባቸው ፡ እንዲመላለሱ ፡ ተመኝ
ተዋል ። በዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ደግሞ ፡ አማኑኤልንም ፡ ልጁንም ፡ ዮሐንስን ፡ አጥ
ብቀው ፡ ሲጠይቁ ፡ የተመለከትነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብ ፡ የሚያውቁ ፡ ፖርቱጊ
ዞች ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ እንዲመጡና ፡ ሕዝባቸውን ፡ እንዲያሠለጥኑላቸው ፡ ነበር ።
ከሁሉም ፡ አስቀድሞ ፡ ጠበንጃና ፡ መድፍ ፡ ሠራተኞች ፡ አስቀድመው ፡ ይምጡ
ልኝ ፡ ያሉት ፡ የግራኝ ፡ ወራሪነት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ስለተሰማቸው ፡ ባላጋራቸውን ፡
በመሣሪያ ፡ እየተከላከሉ ፡ ለመቆየት ፡ መሆኑ ፡ አያጠራጥርም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ለዮሐንስ ፡ ፫ኛና ፡ ለሮማው ፡ ጳጳስ ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ የሚሰጠ
ውን ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝና ፡ ለዶም ፡ ሮድሪግ ፡
ለአባ ፡ ጺጋ ፡ ዘአብ ፡ ሰጥተው ፡ ከአሰናበቷቸውና ፡ እነሱም ፡ በሄዱ ፡ እንዳ
መለከትነው ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ መርከብ ፡ ሲጠባበቁ ፡ በምጥዋና ፡ በአክሱም ፡ ቆይ

ትው ፡ በ፲፭፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቍጥር ፡ ከምጥዋ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡን ፡ ያጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጉዳይ ፡ በቶሎ ፡ ሄደው ፡ ሊያስፈጽሙላቸው ፡ አልቻሉም ። የዚያን ፡ ዘመን ፡ ጉዞ ፡ በሕሩ ፡ በመርከብ ፡ የብሱ ፡ (መሬቱ) ፡ በከብትና ፡ በእግር ፡ ስለሆነ ፡ አንድ ፡ መላክተኛ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደሊስበን ፡ ደርሶ ፡ እንዲመጣ ፡ቢያንስ ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ያስፈልገዋል። መላክተኞቹ ፡ ከሸዋ ፡ ወደምጥዋ ፤ ከምጥዋ ፡ ወደሕንድ ፡ (ጎአ) ፡ ከሕንድ ፡ ወደ ሊስቦን ፡ መሄድ ፡ አለባቸው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ በየበሩ ፡ የቱርኮቹ ፡ ጥብቅ ፡ መቆጣጠር ፡ ነገሩን ፡ ይበልጥ ፡ ያዘገየዋል ። በነገሩ ፡ የሮማ ፡ ጳጳስ ፡ መግባት፡ ደግሞ ፡ ከሊስበን ፡ ወደሮማ ፡ መመላለስን ፡ ያስከትላልና ፡ ይኸም ፡ ተጨምሮ ፡ ይበልጥ ፡ ጉዳዩን ፡ ይጐትተዋል ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስና ፡ የፖርቱጋልን ፡ ንጉሥ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የበለጠ ፡ በቅርብ ፡ የሚያሳስባቸው ፡ በቱርክና ፡ በፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፤ በፖርቱጋል ፡ ንጉሥና ፡ በሻርል ፡ ፭ኛ ፡ በጀርመንና ፡ በኤስፓኝ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መካከል ፡ በግዛት ፡ በዙፋን ፡ በበላይነትም ፡ ምክንያት ፡ የሚነሣው ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፤ ሉተር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በካቶሊክ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ያመጣው ፡ አዲስ ፡ የፕሮቴስታንት፡ ሃይማኖት ፡ ጠብ ፡ ስለአለ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ችላ ፡ አሰኝቶ ፡ መላክተኞቹ ፡ መልስ ፡ ሳያመጡ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ አለፈ ። አጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ለጳጳሱና ፡ ለፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ስለላኩዋቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጉዳይ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ ከራሱ ፡ ዋና ፡ መላክተኛውንና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተጻፈለትን ፡ ደብዳቤ ፡ አሊዞ ፡ ከአልቫሬዝ ፡ ጋር ፡ ወደሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ልኮ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ መላክተኞች ፡ ከሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ተገናኝተው ፡ በቃም ፡ ነገር ፡ ንግግር ፡ የተዠመረው ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ ፲፭፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መላክተኞቹ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በሄዱ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ማለት ፡ ነው ። የንግግሩን ፡ ሁኔታና ፡ ለሮማ ፡ ጳጳስ ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ወደፊት ፡ እንመለከታለን ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የፖርቱጋልንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሁለት ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ እየሰሙ ፡ እያዩ ፡ ይናደዱ ፡ የነበሩት ፡ የቱርክ ፡ የግብጽ ፡ የዓረብ ፡ አገር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መዠመሪያ ፡ ለማኅፉዝ ፡ ከአደረጉት ፡ የበለጠ ፡ በአዳልና ፡ በሱማሌ ፡ ለሚገኙት ፡ ባላባቶች ፡ የጦር፡ መሣሪያና ፡ የወታደር ፡ እርዳታቸውን ፡ እያፋጠኑ ፡ በመስጠት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማስወረርና ፡ የኢትዮጵያና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የፈረንጅ ፡ መንግሥት ፡ የሚገናኙበትን ፡ በር ፡ በፍጹም ፡ ለመዝጋት ፡ ተነሡ ።

ወደፊት ፡ በዝርዝር ፡ እንደምናነበው ፡ ቱርኮችና ፡ ዓረቦች ፡ ይኸን ፡ አሳብ ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሞከሩት ፡ ማኅፉዝ ፡ መሐመድ ፡ የሚባለውን ፡ ባላባት፡ ይዘው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ ከቱርኮችና ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ ከዘቢድ ፡ ባሻ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የወታደርም ፡ የጦር ፡ መሣሪያም ፡ እርዳታ ፡ አግኝቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወርሮ ፡

የራሱንም ፡ የደጋፊዎቹንም ፡ የቱርኮችን ፡ ምኞት ፡ የፈጸመው ፡ የማኅፉዝ ፡ አማች ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የፖርቱጋሎችን ፡ ግንኙነት ፡ ወደ ፊት ፡ በሥፍራው ፡ እስክነግጠ ፡ ድረስ ፡ መዠመሪያ ፡ ማኅፉዝ ፡ ቀጥሎ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ በየጊዜው ፡ ያደረገውን ፡ ታላላቅ ፡ ጦርነት ፡ በዝርዝር ፡ እንመልከት ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፲ ።

የማኅፉድና ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦርነት—የአረጋዊ ፡ መንፈሳዊና ፡ የዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ መጽሐፍ ፡ መተርጐም—ግራኝ ፡ አህመድ ፡ የተነሣበት ፡ ምክንያት ።

---

በመዠመሪያው ፡ መጽሐፍ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፬-፳፯ ፡ ላይ ፡ የመሐመድንና ፡ የዐረቦችን ፡ አነሣስ ፡ አንብበናል ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዠምሮ ፡ እስ ካሁን ፡ እስካፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መንግሥት ፡ ፲፭፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ዱራድር ፤ ሐቀ ፡ አድ ዲን ፡ (ሐቀ ዲን ፡) ጋማል ፡ አድ ዲን ፡ (ገመል ዲን ፡) ሳብር ፡ አድ ዲን ፡ (ሰብረ ዲን) ፡ ካፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ጋራ ፤ አሊ ፡ የሰበር ፡ አድ ዲን ፡ ልጅ ፡ (የናስር ፡ አድዲን ፡ ልጅ ፡ የሚሉት ፡ አሉ) ፡ ካፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሰይፈ ፡ አርእድ ፡) ጋር ፤ ሐቅ ፡ አድ ዲን ፡ ፪ኛ ፡ ካፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ (ውድም ፡ አስፈሬ) ፡ ጋራ ፤ በድላይ ፡ ሺሀብ ፡ አድ ዲን ፡ መሐመድ ፡ (አርዊ ፡ በድላይ) ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋር ፡ መሐመድ ፡ ቤን ፡ በድላይ ፡ ሰላይማን ፡ አህመድ ፡ ካፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጋር ፡ ሻምስ ፡ አድ ዲን ፡ መሐመድ ፡ ካፄ ፡ እስክንድር ፡ ጋር ፡ እንደምን ፡ ሲዋጉ ፡ እንደኖሩ ፡ በ፪ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በየምዕራፉ ፡ አንብበናል ። እነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ የሚደግፉዋቸው ፡ በበላይ ፡ የቱርክ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ደግሞ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚተዳደሩት ፡ የጅዳህ ፡ የሜካ ፡ የዘቢድ ፡ ሡልጣኖች ፡ በቅርብ ፡ ሆነው ፡ ባሳብም ፡ በመሣሪያም ፡ በሰውም ፡ ይረዱዋቸው ፡ ነበር ።

እነዚህ ፡ የአዳልና ፡ የይፋት ፡ የሐረርጌና ፡ የሱማሌ ፡ ባላባቶች ፡ ከነዚያ ፡ ጋር ፡ በሃይማኖት ፡ በዘር ፡ በጋብቻ ፡ በጥቅም ፡ ተሳስረው ፡ በጥብቅ ፡ ይተሳሰባሉ ፡ እነዚህ ፡ ከወዲህ ፡ ከአገራቸው ፡ የሚገኘውን ፡ ከብት ፡ እህል ፡ ቆዳ ፡ ባሪያ ፡ ሲል ኩላቸው ፡ እነዚያ ፡ ደግሞ ፡ ከወዲያ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥበብና ፡ ጌጥ ፡ የተሠራ ፡ ልብስና ፡ ሸቀጥ ፡ መሣሪያ ፡ ያቀብሉዋቸው ፡ ነበር ። ለፖለቲካ ፡ ለጥቅምና ፡ ለንግድም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ መካ ፡ መዲናን ፡ ለመሣለም ፡ እነዚህ ፡ የይፋትና ፡ ያዳል ፡ የሱማሌ ፡ ባላባቶች ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ በፍቅርና ፡ በወዳጅነት ፡ ተቀብለው ፡ ሲያስተናግዱዋቸው ፡ እዚያም ፡ በሚከርሙበት ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ያላቸውን ፡ ያለፈውንም ፡ የጊዜውንም ፡ ጠብ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ እያነሡ ፡ መወያየታቸው ፡ እነዚህ ፡ ጥቃታቸውን ፡ ሲያወሩ ፡ እነዚያ ፡ አይዟችሁ ፡ አለንላችሁ ፡ ማለታቸው ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ፡

መቀመጫው ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ (እስጣምቡል) ፡ የሆነው ፡ የቱርክ ፡ መንግሥትም ፡ በሳሊም ፡ ፩ኛ ፡ በተከታዩ ፡ በሰሊማን ፡ ዘመን ፡ የክርስቲያኑን ፡ የቁስጥ

ንጥንያን ፡ መንግሥት ፡ አጥፍቶ ፡ በግዛቱ ፡ በሶርያ ፡ በሊባኖስ ፡ በፓለስቲን ፡ በግብጽ ፡ በዐረብ ፡ አገር ፡ ከተተከና ፡ ሥልጣኑን ፡ ከዘረጋ ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትንም ፡ ምጥዋን ፡ ሱዋኪምን ፡ እየያዘ ፡ በያዘው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ግዛቱንም ፡ የእስላምንም ፡ ሃይማኖት ፡ አጸና ። የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ከነውሮፓና ፡ ከህንድ ፡ ኃይሉን ፡ እየቀሰቀሰ ፡ በእግርም ፡ በመርከብም ፡ ቢዋጋው ፡ ሊበገርለት ፡ አልቻለም ። ንግሥት ፡ እሌኒ ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ በላኩት ፡ ደብዳቤ ፡ የባሕር ፡ በር ፡ ስለሌለን ፡ የመርከብ ፡ ወታደር ፡ አዘጋጅተን ፡ እስላሞቹን ፡ ለመቃወም ፡ አልቻልንም ፡ እንዳሉት ፡ ምጥዋን ፡ ኢትዮጵያም ፡ ልትጠቀምበት ፡ አልቻለችም ። የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢይዘው ፡ የቱርክ ፡ ወታደሮች ፡ መልሰው ፡ እጅ ፡ አድርገውታል ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ በዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ይማም ፡ ማኅፉዝ ፡ የሚባለው ፡ የአዳል ፡ በላባት ፡ ገና ፡ ከአዬ ፡ ናዖድ ፡ ዠምሮ ፡ ወደላይ ፡ ወደይፋት ፡ እየወጣ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ እየተዋጋ ፡ ከብትም ፡ ሰውም ፡ እየዘረፈ፡ እየወሰደ ፡ አስፈርቶ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። በየጊዜውም ፡ የቱርኮቹንና ፡ ያረቦቹን ፡ ድጋፍ ፡ አግኝቶ ፡ በሐረር ፡ ባላባትነቱም ፡ ላይ ፡ የዘይላን ፡ ሹመት ፡ ጨምረውለት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያልታየ ፡ አዳዲስ ፡ ጠበንጃና ፡ ጥይት ፡ በየጊዜው ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልብስና ፡ ሽልማት ፡ እንደዚሁም ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ድንኳንና ፡ የነቢዩ ፡ የመሐመድ ፡ ምልክት ፡ ያለበትን ፡ አረንጓዴ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እየላኩለት ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ እንዲደረጅና ፡ እንዲቋቋም ፡ ይረዱት ፡ ነበር ።

ርሱም ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ስጦታና ፡ እርዳታ ፡ በበኩሉ ፡ ያለውን ፡ ወርቅ፤ የዝሆን ፡ ጥርስ ፤ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ እያደረገ ፡ በመላክ ፡ ያስደስታቸው ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዠርባው ፡ የቱርኮችንና ፡ የዐረቦችን ፡ ድጋፍ ፡ በማግኘቱ፡ ይልቁንም ፡ በዕጁ ፡ የያዘው ፡ አዳዲስ ፡ መሣሪያ ፡ ሙሉ ፡ ልብ ፡ ስለሰጠው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ አዳሎቹን ፡ እየላከ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አስጨርሶ፡ ብዙ ፡ ቤትና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ አቃጥሎ ፡ ብዙ ፡ ከብትም ፡ አዘረፈ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ተሰማ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አዬ ፡ ልብነ፡ ድንግል ፡ ዕድሜያቸው ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ስለተጠጋ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ለመምራት ፡ አቅማቸው ፡ ስለሚፈቅድ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ ። ማኅፉዝም ፡ በባላባታቸው ፡ በመሐመድ ፡ የሚመሩትን ፡ የአዳሎችን ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ መጣ ።

እንደ ፡ ኢት ፡ ቍጥር በ፲፭፻፳፯ ፡ ዓ፡ ም፡ በሐምሌ ፡ ወር ፡ በዚሁ ፡ በይፋት፡ አቅራቢያ ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረና ፡ ሠራዊት ፡ ከሠራዊት ፡ ሲዋጋ ፡ አዝማቹ ፡ አሚር ፡ ማኅፉድም ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ እንድርያስ ፡ ከሚባሉት ፡ ኃይለኛ ፡ መነኵሴ ፡ ጋር ፡ በሰይፍ ፡ ውጊያ ፡ ገጠመ ። በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ መነኵሴው ፡

ማኅፉድን ፡ በሰይፍ ፡ በትር ፡ ጣሉት ፤ ራሱንም ፡ ቆርጠው ፡ ለንጉሡ ፡ ለዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አሳይተው ፡ ግዳይ ፡ ጣሉ ። እኚህም ፡ መነኰሴ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ዐፄ ፡ ናዖድ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ በጥፋት ፡ መላሳቸውን ፡ ያስቆረጡዋቸው ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። የኚህ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ በ፪ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ባዔ ፡ ናዖድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ የመኳንንትና ፡ የሊቃውንት ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ።

አዳሎቹ ፡ የዋናውን ፡ መሪ ፡ የማኅፉድን ፡ መሞትና ፡ በመከከላቸው ፡ ብዙ ፡ እልቂት ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጠው ፡ ሸሹ ፡ ተመሩ ፡ ክርስቲያኖቹም ፡ እስከ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ዘልቀው ፡ በዙክራ ፡ ያለውን ፡ የማኅፉድን ፡ ከተማ ፡ አቃጥለው ፡ ያገኙትን ፡ ከብትና ፡ ገንዘብ ፡ ዘርፈው ፡ በሆታና ፡ በደስታ ፡ ተመ ለሱ ። በተመለሱም ፡ ጊዜ ፡ የወጣቱ ፡ ንጉሥ ፡ መሪነትና ፡ ይልቁንም ፡ የመነ ኰሴውን ፡ ዠግንነት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ሕዝቡም ፡ እያደነቀ ፡ በደስታ ፡ ተቀበላቸው ። የማኅፉድም ፡ (ማኅፉዝ ፡) አነሣሥ ፡ በዚህ ፡ ተፈጸመ ። ማፉድ ፡ የምትባል ፡ ገበያ ፡ ያለባት ፡ አገር ፡ በይፋት ፡ ውስጥ ፡ የምትገኘው ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ማኅፉድ ፡ የከትማት ፡ ወይም ፡ ወገኖቹ ፡ የሠፈሩባት ፡ ትሆን ?

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ ከተደረገበት ፡ ከ፲፰፻፲፫ ፡ ዓ፡ ም፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፶፫ ፡ ዓ፡ ም፡ ድረስ ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በገር ፡ ላይ ፡ ሰላምና ፡ ፀጥታ ፡ ሆነ ። እስከ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ መነሣትም ፡ ድረስ ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ በረከተ ፤ ሽፍታም ፡ ሌባም ፡ ጠፋ ፤ እርሻና ፡ ንግድም ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ተስ ፋፋ ፡ ንጉሡ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ እሙሉ ፡ ዕድሜ ፡ ላይ ፡ ስለደረሱ ፡ ሞግዚቶች ፡ የነበሩት ፡ እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ እቴጌ ፡ ናዖድ ፡ ሞገሳ ፡ ቀርተው ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ በሙሉ ፡ ይዘው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ጀመር ። በፍርዳቸውም ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኙት ። ከችሎትና ፡ ከሌላውም ፡ ሥራ ፡ የተረፈውን ፡ ጊዜያቸውን ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ በመመርመርና ፡ ከሊቃውንት ፡ ጋር ፡ በመነጋገር ፡ ያሳልፉ ፡ ነበር ። በርሳቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ የአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አባ ፡ ሚከ ኤል ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ገድል ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተረጐመ ። እን ዲያውም ፡ ዕጨጌ ፡ ዕንባቆም ፡ ትውልዳቸው ፡ ዐረብ ፡ ስለነበረ ፡ ዐረብኛ ፡ በጣም ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ከአባ ፡ ሚከኤል ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፡ መጽሐፍና ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተረጐሙ ።

ቀድሞ ፡ ጳውሎስ ፡ ለዕብራውያን ፡ የጻፈውን ፡ መልእክት ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ስሙ ፡ ጥሩው ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በትርጕም ፡ ሐተታ ፡ እየሰጠ ፡ ያዘጋጀው ፡ ስለሆነ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ከመቅድሙ ፡ ላይ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ « . . . ፍካሬ ፡ ዘይቤ ፡ አቡነ ፡ ኄቢይ ፡ በውስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ርእሰ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ዘሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዘከመ ፡ ፈከረ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እምላካዊ ፡ እንተ ፡ ጸሐፋ ፡ ወፈነዋ ፡ ኀበ ፡ አይሁድ ፡ ወአዕለዋ ፡

እምልሳን ፡ ጽርዕ ፡ ኀበ ፡ ልሳን ፡ ዐረቢ ፡ ሊቅ ፡ ክቡር ፡ ዲያቆን ፡ ኀኑይ ፡ አቢ ፡
እልፋታሕ . . . ››ይልና ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከግሪክ ፡ ወደዐረብኛ ፡ ተተርጉሞ ፡
ሲኖር ፡ በዓፄ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ አባ ፡ ዕንባቆምና ፡ አባ ፡ ሚክኤል ፡
ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ እንደተረጐሙት ፡ ለማስረዳት ፡ ከወደመጨረሻው፡
ላይ ፡ «ወይእዜ ፡ ተተርጐመት ፡ እምልሳን፡ ዓረቢ ፡ ለግዕዝ ፡ በእደ ፡ ዕንባቆም፡
ወአባ ፡ ሚክኤል ፡ (ግብጻዊ) ፡ . . . . እምልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃ
ኒነ ፡ በ፲፻ ወ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ይላል ፡ ዓመቱ ፡ ሺ፭፻ ፡ ዓመ ፡ ምሕ ፡ ያለው ፡
ስሕተት ፡ ነው ፡ ጊዜው ፡ ወደ ፡ ሺ፭፻፲፰ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ ዘመኑ ፡ ዘመነ ፡ ሰላም ፡
ሆኖ ፡ እርሻ ፡ ስለተስፋፋ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በተድላና ፡ በደስታ ፡ በመኖሩ ፡ በዚያ፡
ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ ተድላ ፡ ለማግነንና ፡ በአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መን
ግሥት ፡ መጨረሻ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ ለመግለጽ ፡ ይልቁንም ፡ ግራኝ ፡ ስለመ
ነሣቱና ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ስለማጥፋቱ ፡ በቃለ ፡ አጋ
ኖና ፡ አንክሮ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ በታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡
ተጽፏል ፡ ቃሉ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጐም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነው ።

ለአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል፡ በከነ፡የሚባል፡ከተማ፡ ነበራቸው ፡ ከዚያ ፡ ዘመኑ፡ዘመነ ፡
ሰላም ፡ ስለሆነ፡ በከነ ፡ ጦር ፡ አውርድ ፡ እያሉ ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋር ፡
ጉግስ ፡ በፈረስ ፡ እየተጫወቱ የገዛ ፡ ግንባቸውን ፡ በጦር ፡ ሲወጉ ፡ ግንቡ ፡
እየፈረሰ ፡ ምጽዋት ፡ የሚፈልጉትን ፡ ነዳያን ፡ አጠፋቸው ። ደግሞም ፡ እንደጋላ ፡
ሥርዓት ፡ የፈረሰቻቸውን ፡ ግንባር ፡ የበረንትቻ ፡ ደም ፡ እየቀቡ ፡ ትምባሆ ፡ እየ
ጠጡ ፡ አምልኩ ፡ባዕድን ፡ አድርገው ፡ ነበር ። በመጨረሻውም ፡ ለጣና ፡ ቂርቆስ ፡
ጫን ፡ ዕጣን ፤ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ጫን ፡ ዕጣን ፡ ስለት ፡ ሰደው ፡ አባቶቼ ፡ ይኸን ፡
እያጠናችሁ ፡ ጦር ፡ አውርድለት ፡ ብላችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምኑልኝ ፡
ብለው ፡ ላኩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቄስ ፡ አፄ ፡ ዮሐንስ ፤ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ቃለ ፡ አዋዲ ፤
ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ዘመለኮት ፡ የሚባሉት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መጥ
ተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላትን ፡ አጥፍቶ ፡ አገርን ፡ አስፍቶ ፡ ቢያስገዛዎ ፡ ጦር ፡
አውርድልኝ ፡ ብለው ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጢፍ ፡ ዕጣን ፡ እየላኩ ፡ መሳልዎ ፡
ወዲያውም ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ሆነው ፡ እንደ፡ ጋላ ፡ የበረንትቻ ፡ ደም፡ የፈረስ
ዎን ፡ ግንባር ፡ እየቀቡ ፡ ከአሽከሮችዎ ፡ ጋር ፡ በፈረስ ፡ ጉግሥ ፡ ሲጫወቱ ፡ የገዛ፡
ግንብዎን ፡ በጦር ፡ እየወጉ ፡ ግንቡ ፡ እየተናደ ፡ ምጽዋት ፡ የሚፈልጉትን ፡ ነዳያን ፡
ማጥፋቱ ፡ ትምባሆ ፡ መጠጣትዎ ፡ ይህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ የሚያጣላዎ ፡
ሥራ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በወዳጅነት ፡ ቢመክሯቸው ፡ «ገፋዒ ፡ ነዳያን ፡ አደረጋችሁኝ»
ብለው ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ ገብተው ፡ ግብር ሳያገቡ ፡ አደሩ ።
በበነጋው ፡ ክርስቶስ ፡ በሰውነቱ ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵ
ያዊ ፡ ተነሥቶ ፡ ተዋሕዶዎችን ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ያጣላ ፡ መስሎት ፡ ትምባሆ ፡ አት

ጠጡ ፡ የሚል ፡ መጽሐፍ ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ ወንጌል ፡ ወደ ፡ አፍ ፡ የገባ ፡ ሁሉ ፡
ሰውን ፡ አያረክሰውም ፡ የሚያረክሰው ፡ ከአፍ ፡ የወጣ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ክር
ክር ፡ ቢያነሣ ፡ የዲብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ ከአፍ ፡ ወጣ ፡ የተባለው ፡ አምልኮ
ባዕድና ፡ ገቢረ ፡ ሥራይ ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ቢመልሱለት ፡ ሮማውያን ፡ አሉና
ሮማውያን ፡ በፍርድ አያብሉም ፡ በፍርድ ያስረታኛል ፡ ብለው ፡ ክርክሩ ፡ ሳይፈጸ
ምና ፡ በአደባባይ ፡ ሳይፈረድ ፡ ንጉሡ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ግቢያቸው ፡ ገቡ ።
መነኮሳቱም ፡ ምክራችንን ፡ ካልተቀበሉን ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸውን ፡ ይጕዳሉ ፡ እንጂ ፡
እኛ ፡ ምን ፡ ቸገረን ፡ ብለው ፡ እያዘኑ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተመለሱ ፡ አክሟ
ብና ፡ ኤልዛቤል ፡ ሚስቱ ፡ ነቢያተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስላስገደሉ ፡ ኤልያስ ፡
ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ዘግቶ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ረኃብ ፡ እንዳጸና ፡ በአፄ ፡
ልብነ ፡ ድንግል ፡ የመነኮሳቱን ፡ ምክር ፡ አለመስማት ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለአዘነ ፡
መሐመድ ፡ ግራኝን ፡ አሥነሣባቸው ። አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተቃጠሉ ፡ መጻሕ
ፍት ፡ ተቈነጻጸሉ ፤ ምእመናን ፡ እንደበግ ፡ ታረዱ ፡ ደማቸው ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡
ፈሰሰ ፤ አጥንታቸው ፡ ተከሰከሰ ።

አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ በሠሩት ፡ ጥፋት ፡ ግራኝን ፡ እንደአሥነሣባቸው ፡ ስላ
ወቁ ፡ እየተዋጉ ፡ ሲሸሹ ፡ ሱባዔ ፡ ገብተው ፡ የሠራሁትን ፡ ኃጢአት ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡
እያሉ ፡ አልቅሰው ፡ አዝነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመኑ ። እግዝእትነ ፡ ማርያምንም ፡
ከልጅሽ ፡ አማልጅኝ ፡ ብለው ፡ ቢለምኑአት ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቅዱስ ፡
ራጉኤል ፡ መልአክ ፡ ብርሃናትን ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖ
ትን ፡ አስከትላ ፡ መጥታ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ እስከ ፡ መጨረ
ሻው ፡ ተናገረቻቸው ። ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ‹እኔን ፡ ሳትወደኝ ፡ ለምን ፡ ስሜን ፡ በም
ስጋና ፡ ታነሣለህ ፤ አሁንም ፡ ጸሎትህን ፡ አልሰማም ፡ ያባትህን ፡ የወዳጄን ፡ የናዖ
ድን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሰሃልና ፡ ልጄ ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡ አድሮ ፡ የኃጢአተኞችን ፡
ጸሎት ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ አልሰማህምን» ፡ ብትላቸው ፡ መል
ሰው ፡ «የእኔን ፡ ኃጢአት ፡ ሳትዘክሪ ፡ ያባቶቼን ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብንና ፡ የናዖድን ፡
ነገር ፡ አስበሽ ፡ ከልጅሽ ፡ ከወዳጅሽ ፡ አስምሪኝ ፡ አሏት ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ምሕረት
ልማዱዋ ፡ ስለሆነ ፡ «እንግዲህስ ፡ በነፍስህ ፡ ደስ ፡ ይልሃል ፡ በሥጋህ ፡ ታዝናለህ ፡ በስ
ደት ፡ ትሞታለህ አሁንም ፡ ንስሐ ፡ ግባ ፤ ልጄ ፡ ከናዖድ ፡ ዘር ፡ መንግሥት ፡ እንዳይ
ጠፋ ፡ አድርጓልና ፡ የልጅ ፡ ልጆችህም ፡ እንደ ፡ ናዖድ ፡ የእኔን ፡ ኪዳን ፡ ጠብ
ቀው ፡ ቢኖሩ ፡ መንግሥታቸው ፡ ይጸናል ። ባይጠብቁ ፡ ግን ፡ መንግሥታቸው ፡
ትጠፋለች ፡ አገራቸውም ፡ ለአሕዛብ ፡ ትሆናለች» ፡ አለቻቸው ። አፄ ፡ ልብነ ፡ ድን
ግልም« ፡ የምሞትበት ፡ አገር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ልጆቼስ ፡ ከወዴት ፡ ነው የሚነሡት ፡
ቢሏት ፤ ከእንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ መልአኩ ፡ ራጉኤል ፡ ይነግርሃል ብላ ፡ ከአይና
ቸው ፡ ተሰወረች ፡ ለማለት ፡ «እንከሰ ፡ ይንግርከ ፡ ራጉኤል ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡
ዘሀሎ ፡ ምስሌየ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂላ ፡ ተሠወረት ፡ እምአዕይንቲሁ» ፡ ይላል ።

ስለዚህ ፡ መላእክት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ነቢያት ፡ እየተላኩ ፡ ይነግሯ
ቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደዚሁም ፡ መልአኩ ፡ ራጉኤል ፡ በራእይ ፡ ተገልጾ ፡ ‹አንተ
በስደት ፡ ትሞታለህ ፤ ከልጆችህም ፡ ውስጥ ፡ ገ ፡ ይነግሥ ፡ (ገላውዴዎስ ፡ ይነግሣል) ፡

ሬ ፡ ይመውት ፡ (ሬቅጦር ፡ ይሞታል) ፤ ሚ ፡ ይሆየጥ ፡ (ሚናስ ፡ ይሸጣል) ፤ ያ ፡ ይኀብር ፡ (ያዕቆብ ፡ ይኖራል) ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በራሳቸውና ፡ በልጆቻቸው ፡ የሚደርሰውን ፡ ጨርሶ ፡ ነግሯቸዋል» ይላል ። ይኸ ፡ ሁሉ ፡ በየታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ በተለይም ፡ በድርሳነ ፡ ራጉኤል ፡ ተጽፎ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይነበባል ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተዘረዘረው ፡ ምክንያት ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐመድ ፡ ግራኝን ፡ አስነሣባቸው ፡ ለማለት ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ የኛን ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ደራሲዎች ፡ እንሞሪዩ ፡ ሳይቀሩ ፡ በመጽሐፋቸው ፡ ጠቅሰውታል ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ‹ቦክን ፡ ጦር ፡ አውርድ ፡ እያሉ ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ ጋር ፡ የገዛ ፡ ግንባቸውን ፡ በጦር ፡ ይወጉ ፡ ነበር ፤ ለዱብረ ፡ ሊባኖስና ፡ ለጣና ፡ ቂርቆስም ፡ ጧፍ ፡ ዕጣን ፡ እየላኩ ፡ ቀሰውስቱን ፡ ጦር ፡ አውርድለት ፡ ብላችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምኑልኝ› ፡ እያሉ ፡ ብዕዓትና ፡ ስለት ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፡ ይላል ።

አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ የተድላና ፡ የደስታ ፡ ዘመን ፡ ቢሆንም ፡ በዚሁ ፡ ደስ ፡ ተሰኝተው ፡ ይኸንኑ ፡ ላደረገላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ በመስጠት ፡ ፈንታ ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለ ፡ የእብሪትና ፡ የልጅነት ፡ ሥራ ፡ አደረጉ ፡ ብሎ ፡ የዛሬን ፡ አንባቢ ፡ ለማሳመን ፡ በፍጹም ፡ ሳይቸግር ፡ ይቀራልን ? ከማኅፉድ ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ የተገኘውም ፡ ሰላም ፡ ከዓሥር ፡ ዓመት ፡ አይበልጥም ። ለዚያውም ፡ ቢሆን ፡ የአዳል ፡ አገሮች ፡ በዘመናቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየመጡ ፡ በዘረፋና ፡ በወሰን ፡ ግጭት ፡ ማስቸገራቸው ፡ የታወቀና ፡ የተለመደ ፡ ነው ። በሰላም ፡ ፈንታ ፡ ጦርነትንም ፡ በስለት ፡ ከሚፈልጉ ፡ በቱርክ ፡ ሡልጣን ፡ የሚገዛውን ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ገፍተው ፡ ግብጽን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሒደው ፡ የመንን ፡ ቢወጉ ፡ ጦርነት ፡ ያጡ ፡ ኖሯልን ፡ ? ይኸም ፡ የሚበዛባቸው ፡ ቢሆን ፡ ምጥዋን ፡ አያስለቅቁም ፡ ኖሯልን ? ስለዚህ ፡ ለድሉ ፡ ተሳሉ ፡ ቢባል ፡ ያምራል ፡ እንጂ ፡ ጦርነት ፡ በማጣት ፡ ተቸግረው ፡ ይሳሉ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ የሚመስል ፡ አይደለም ፡ ቢሆንም ፡ በግራኝ ፡ እነሣሥ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በሕዝበ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ላይ ፡ ለመጣው ፡ እልቂት ፡ ምክንያት ፡ በመፈለግ ፡ ያላንዳች ፡ ግፍና ፡ እብሪትም ፡ ይኸን ፡ ያህል ፡ እልቂትና ፡ ስደት ፡ አይደርስባቸውም ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ «ጦር ፡ አውርድልን» ፡ እያሉ ፡ መሬት ፡ ይገርፉ ፡ ነበር ፡ ስለት ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ከልብ ፡ የሚሰማው ፡ ቢቀበለው ፡ የማይሰማውም ፡ ቢተወው ፡ የአንባቢ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በታላላቆች ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ አባቶቻቸው ፡ በነዓዊ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በነዓዊ ፡ ናዖድ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በሥርዓትና ፡ በመንፈሳዊ ፡ አስተዳደግ ፡ ያደጉት ፡ ክርስቲያኑ ፡ አፄ ፡ ልብነ ድንግል «ጦር ፡ አውርድ» ፡ ብለው ፡ መሬትንም ፡ የሚገርፉ ፡ የሚሳሉም ፡ አይደሉም ። ይኸንንም ፡ የጻፉ ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያና ፡ በፖርቱጋል ፡ በፖርቱጋልና ፡ በቱ

ርክ ፤ በቱርክና ፡ በአዳሎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የዘመኑን ፡ የፖለቲክ ፡ ግንኙ ነትና ፡ ጠብ ፡ እውነተኛውን ፡ የግራኝ ፡ አህመድን ፡ እነማሥ ፡ ለማወቅና ፡ ለመረዳት ፡ አቅም ፡ ያጡራቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ወደፊት ፡ ባሉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንደምናነበው ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ እነማሥ ፡ ግን ፡ የታወቀውን ፡ የቱርኮቹን ፡ ወረራና ፡ መስፋፋትን ፡ የተደገፈ ፡ ነው ። የዚ ህም ፡ የወረራ ፡ አደጋ ፡ የአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ መንግሥት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን፡ ግብጽንም ፡ ግሪክንም ፤ ዐረብንም ፤ አርመንንም ፤ ባቢሎንንም ፤ ቡልጋሪንም ፤ ሆንግሪንም ፤ የነምሳንም ፡ አጋማሽ ፡ የቱርኮች ፡ ወራሪነት ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ በዚሁ፡ ዘመን ፡ አልማራቸውም ። ወረራውም ፡ የደረሰባቸው ፡ ሳይሳሉና ፡ ሳይወዱ ፡ በግድ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መንግሥት ፡ ላይም፡ የግራኝን ፡ ወራሪነት ፡ ያመጣው ፡ የርሳቸው ፡ ከፖርቱጋል ፤ የግራኝ ፡ ከቱርክና ፡ ከዐ ረብ ፡ መንግሥታት ፡ መዛመድ ፤ በጠቅላላው ፡ ከፖርቱጋልና ፡ ከቱርክ ፡ ተፎካካሪነት ፡ የመጣ፡ ነው ። በ፪ኛው ፡ መጽሐፌ ፡ ውስጥ ፡ በየምዕራፉ ፡ በዝርዝር ፡ እንደተመ ለከተው ፡ እነዚያ ፡ ሁሉ ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ የይፋት ፡ ወላስሞች ፡ ሲታገሉ ፡ ኖረው ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ብርታት ፡ ታግደው ፡ ተደምስሰው ፡ የኖሩት ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ኃይለኛው አህመድ ፡ ግራኝ ፡ ከቱርኮቹና ፡ ከዐረቦች ፡ ዕርዳታ ፡ አግኝቶ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበ ሩት ፡ ያልቀናቸውን ፡ እርሱ ፡ ተከናወነለት ፡ ብለን ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ በመከ ተል ፡ የአህመድን ፡ እውነተኛውን ፡ እነማሥና ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፯ ፡

## ስለ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ እነማሥ — በርሱና ፡ በአቡበክር ፡ ሡልጣን ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጠብና ፡ ጦርነት ።

ስለግራኝ ፡ አህመድ ፡ እነማሥ ፡ በገራችን ፡ ባማሪኛም ፡ ሆነ ፡ በግዕዝ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪኩ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ መጻፉን ፡ አላየሁም ። ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ጦር ፡ አውርድ ፡ ብለው ፡ ይሳሉ ፡ ነበር ፡ እንደሚለው ፡ የግራኝንም ፡ ልደትና ፡ እድገት ፡ ለመተረክ ፡ ሲሞክር ፡ አሁንም ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ በጭሩ ፡ እንደ ዚህ ፡ ይላል ።

የአዳል ፡ ባላባት ፡ ፲፰ ፡ ነጭ ፡ በቅሎ ፤ ፺ ፡ የወርቅ ፡ ቡችላ ፤ ፴ ፡ ከዜ ፡ ምንጣፍ ፤ ፮ሺህ ፡ ፫፻ ፡ ሻማ ፤ ፪ሺ ፡ ፍሪዳ ፡ ፫ሺ ፡ የፍየልና ፡ የበግ ፡ ሙክት ፡ ለአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በያመቱ ፡ ይገብር ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ የግራኝ ፡ እናት፡ ሺምሺያ ፡ (ፀሐይቱ) ፡ የሐረር ፡ እስላም ፡ ነበረች ፤ እርሷም ፡ በበኩሏ ፡ ግብር ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወረደች ፤ በዚያም ፡ አንድ ፡ መነኮሴ ፡ ተገናኛ ትና ፡ ፀነሰች ፡ መነኮሴውም ፡ ከእርሷ ፡ በተገናኘበት ፡ ሌሊት ፡ የራሱን ፡ ቆብ ፡ ትቶ ፡ የርሷን ፡ ኩፍታ ፡ አማስቶ ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ ደፍቶ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ገባ ፤ ቄሶቹም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ከእስላሚ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተገናኘ ፡ አወቁ በት ፤ ወዲያው ፡ በመቋሚ[illegible] ፡ ደብድበው ፡ ገደሉት ፤ ሴቲቱ ፡ ግን ፡ ወዳገሯ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ተመልሳ ፡ ግራኝን ፡ ወለደች ፤ ግራኝም ፡ ከደገ ፡ በኋላ ፡ ጓደኞቹ ፡ በጫ

ዋታም ፡ በምርም ፡ «አንድ ፡ ጐን» ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ እናት ፡ እንጂ ፡ አባት ፡ የሌለው ፡ እያሉ ፡ ዘወትር ፡ ይሰድቡት ፡ ነበርና ፡ እናቱን ፡ አባቱን ፡ ንገሪኝ ፡ እያለ ፡ ነዘነዛት ፤ እርሷም ፡ አባቱን ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቀሳውስት ፡ ደብድበው ፡ እንደገደሉት ፡ አስረዳችው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የአባቱን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ኢትዮጵያን ፡ ወረረ ፤ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ገዳምና ፡ ሌሎችንም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አቃጠለ ፤ መነኰሳቱንና ፡ ቀሳውስቱንም ፡ ፈጀ ፡ እየተባለ ፡ ይነገራል ። ይኸም ፡ ታሪክ ፡ በግማሹ ፡ እውነት ፡ ቢኖር ፡ እያለፈ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ የሚተረከው ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ ከመሆን ፡ አይዘልም ። ይኸም ፡ ባይሆን፡ ኖሮ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በቀሳውስት ፡ ላይ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ አይጨክንም፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ በመላ ፡ የተፈጠረ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ይኸም ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ቁመናው ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ጐራዴውም ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ጦሩም፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ነበር ፡ ከሚባለው ፡ የተረት ፡ አነጋገር ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ።

የግራኝ ፡ አህመድ ፡ እውነተኛው ፡ ታሪኩ ፡ በፈረንጆችም ፡ በዐረቦችም ፡ በወገኖቼ ፡ በሱማሌዎችና ፡ በሐረርጌዎችም ፡ ዘንድ ፡ ያው ፡ የተቻለው ፡ ያኸል ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ባገራችንም ፤ ቢሆን ፡ ባላየው ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ያልታተመ፡ አንዳንድ ፡ እንደ ፡ ቁንጽል ፡ ያለ ፡ በብራና ፡ የተጻፈ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪኩ ፡ በቤተ ፡ መንግሥትና ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ በገዳም ፡ ወይም ፡ ባንዳንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ አይጠፋም ፡ ይሆናል ። ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ አነጋሥና ፡ ወረራ ፡ ፈረንጅም ፡ ዐረብም ፡ መሠረት ፡ ያደረገው ፡ «ፍቱሕ ፡ አል ፡ ሐበሻ ፡ የሐበሻ ፡ ወረራዎች» ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ ሺሃብ ፡ ኤዴን ፡ አሕመድ ፡ ቢን ፡ አብደል ፡ ቃድር ፡ (ዐረብ ፡ ፈቂሀ ፣) የሚባለው ፡ የዐረብ ፡ ተወላጅ ፡ የጻፈውን ፡ ነው ። ይህ ፡ የዐረብ ፡ ተወላጅ ፡ ግራኝ ፡ በዋለበት ፡ እየዋለ ፡ ባደረበት ፡ እያደረ ፡ ጦርነቱንም ፡ እየተከታተለ ፡ በይኑ ፡ ካየው ፡ አቡበክር ፡ ከሚባለው ፡ አንደበት ፡ እየሰማ ፡ በቀረው ፡ የጦር ፡ ግንባርም ፡ ራሱ ፡ እየተገኘ ፡ ባይኑ ፡ እያየና ፡ እየሰማ ፡ የጻፈ ፡ ነው ። ስለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጉዳይ ፡ በብዙ ፡ የደከሙት ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችንን ፡ ወደፈረንሳይኛ ፡ ማስታወሻ ፡ እየጨመሩ ፡ የተረጐሙት ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ አሁንም ፡ ይኸንኑ ፡ ያረብ ፡ ፈቂህን ፡ መጽሐፍ ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ ከራሳቸው ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ በየጊዜው ፡ እየጨመሩ ፡ ተርጉመውታል ። ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ሺሃብ ፡ አድን ፡ አሕመድ ፡ አብደል ፡ ቃድር ፡ ባጭሩ፡ ደግሞ ፡ ዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ በየመን ፡ ውስጥ ፡ የጂዛን፡ ተወላጅ ፡ ነው ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ግራኝ ፡ አህመድና ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል፡ ተዋግተው ፡ ንጉሡ ፡ የተሸነፉ ፡ ለት ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ዐረብ፡ ሃይማኖቱ ፡ እስላም ፡ ተከትሎ ፡ የመጣው ፡ ግራኝ ፡ አህመድን ፡ ስለሆነ ፡ በአጻጻፉ ፡ ላይ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ ወገን ፡ የማኰሰስ ፡ የእስላሞቹን ፡ ወገን ፡ የማጋነንና ፡ የማድነቅ ፡ አጻጻፍ ፡ በብዙ ፡ ይታይበታል ። ይኸም ፡ በርሱ ፡ ላይ፡ ብቻ ፡ እንዳይፈረድ ፡ የኛ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ወገኖች ፡ ከአዳሎችና ፡ ከሱማሌ ፡ ወገን፡

የተዋጉትን ፡ ሲጽፉ ፡ የነገሥታቱን ፡ የነዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ የነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዛቱም ፡ አዛገሮቹም ፡ ሲጽፉ ፡ የራሳቸውን ፡ ወገን፡ እያጋነኑ ፡ የነዚያን ፡ እያኰሰሱ ፡ መጻፋቸው ፡ የታወቀና ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ የተረጐሙት ፡ ይህ ፡ የዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ በኛ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ የማይገኝ ፡ የጦርነት ፡ ሐተታ ፡ የመሳፍንት ፡ የመኳንንት ፡ ዝርዝር ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ የነበሩትን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ስለሚዘረዝር ፡ ለዛሬ፡ ታሪክ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ስለሆነ ፡ ጸሐፊው ፡ ሊመሰገን ፡ ይገባል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ጽሑፉ ፡ ከሥር ፡ ዠምሮ ፡ እየዘረዘረ ፡ ይጽፍና ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እኽያ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በተለይ ፡ ግራኝ ፡ ለመሞት፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ እቀረው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ የጣና ፡ ባሕርን ፡ ጦርነት ፡ ከተረከ ፡ በኋላ ፡ ያቆማል ። የቀረው ፡ ወደፊት ፡ የሚገኘው ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል፡ ፍጻሜ ፡ ግራኝ ፡ ባፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጦርና ፡ በፖርቱጋል ፡ ጦር ፡ ወታደር ፡ ተመትቶ ፡ መሞቱን ፡ አይተርክም ። ይኸንኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ያጠኑና ፡ የተረጐሙ ፡ ግማሾቹ ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ባለቤት ፡ ባቲ ፡ ድል ፡ ወምበራ ፡ አቃጠለችው ፡ የሚሉ ፡ በድንገተኛ ፡ ቃጠሎ ፡ ተቃጠለ ፡ የሚሉ ፡ ጸሐፊው ፡ ሳይጨርሰው ፡ በመከከሉ ፡ ሞተ ፡ የሚሉ ፡ አሉና ፡ ስለመጨረሻው ፡ ታሪክ ፡ ጉዳይ ፡ የተረጋገጠ ፡ ማስረጃ ፡ አይገኝም ።

ስለዚህ ፡ በዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ እርሱንና ፡ በዘመኑ ፡ የነበሩትን ፡ የፖርቱጋል ፡ ተወላጆች ፡ የነአልቫሬዝን ፡ የነቤርሙዲዝን ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፡ በሚጽፉት ፡ በጀምስ ፡ ብሩስ ፡ በኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ በገሮን ፡ ባቲስት ፡ ኩልቦ፡ በባሴት ፡ ረኔ ፡ በዡል ፡ ፔሩሾ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘውን ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪኩ ፣ ከየአለበት ፡ አጠራቅመን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ጽፈነዋል ።

የግራኝ ፡ አህመድ ፡ አባት ፡ ገራድ ፡ ኢብራሂም ፡ ይባላል ፡ የራሱ ፡ ስም ፡ አህመድ ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ ኤል ፡ ቃዚ ፡ ነው ፡ አድጎ ፡ መሪ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይማም፡ የሚባለውን ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ እየጨመረ ፡ ይጠራል ። በፍጥረቱ ፡ ግራኝ ፡ ስለነበረ ፡ የኛ ፡ ሰዎች ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፣ ሱማሌዎች ፡ ደግሞ ፡ ጉራይ ፡ ይሉት፡ ነበር ፡ አገሩ ፡ ሐባት ፡ (አዳል ፡ ውስጥ) ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ይኸም ፡ ከአዳል ፡ ባላባት፡ ከአቡበከር ፡ ጋር ፡ እየተጣላ ፡ ተዋግቶ ፡ ሲሸነፍ ፡ እየሔደ ፡ የሚደበቅበት ፡ አገር፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ በትክክል ፡ አገሩ ፡ እዚያ ፡ ወይም ፡ ዘይላ ፡ አለዚያም ፡ አዳል ፡ መሆኑ ፡ አይታወቅም ። የአባቱም ፡ የሕይወት ታሪክ ፡ በትክክል ፡ የለም። ግራኝ ፡ አህመድ ፡ የወጣትነቱን ፡ ወራት ፡ በገራድ ፡ አቡን ፡ ቤት ፡ አሳልፏል ። ገራድ ፡ አቡን ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ የአዳልና ፡ የዙሪያው ፡ ገዥ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የራሱን ፡ ግዛት ፡ በሚያስተዳድርበት ፡ ጊዜ ፡ ከላይ ፡ ከሳድ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ (ሰዓዲን ፡) የወረደው ፡ የይፋት ፡ ወላስማ ፡ ባላባት ፡ ሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ አሁን ፡ መደበኛ፡ መቀመጫውን ፡ በሐረርጌ ፡ ያደረገው ፡ ገራድ ፡ አቡንን ፡ አይወድም ፡ ነበርና ፡ አለበት ፡ ድ[illegible] ፡ ሔዶ ፡ ወግቶ ፡ ገደለውና ፡ ግዛቱን ፡ ቀማው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡

ግራኝ ፡ አህመድና ፡ የቀሩት ፡ የገራድ ፡ አቡን ፡ ሰዎች ፡ ሸሽተው ፡ ወደሐባት ፡
ሔደው ፡ ተቀመጡ ። በዚያው ፡ በሐባት ፡ ሳለ ፡ ፋኑኤል ፡ የደዋሮ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡
የአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ያዳልን ፡ አገር ፡ እየመታ ፡ እስከ ፡
ሐባት ፡ ጫፍ ፡ መድረሱ ፡ ከብትም ሰውም ፡ መዝረፉን ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡
ሰማ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግራኝና ፡ አብረውት ፡ ያሉት ፡ የገራድ ፡ አቡን ፡ ሹማ
ምንት ፡ ፋኑኤል ፡ ያደረገባቸውን ፡ ጥቃት ፡ ለመበቀል ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ተመ
ካከረው ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትለው ፡ ለውጊያ ፡ ሲጓዙ ፡ ከፋኑኤል ፡
ጋር ፡ አካም ፡ ከሚባል ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ ተገናኙና ፡ ውጊያው ፡ ተገጠመ ።

ዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ እንደሚለው ፡ ፋኑኤልና ፡ ጓደኞቹ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡
ሰውነታቸውን ፡ በሙሉ ፡ ብረት ፡ ለበስ ፡ የሆነ ፡ ጥሩር ፡ ለብሰው ፡ ከዩናቸው ፡
በቀር ፡ አይታይም ፡ ነበር ። ጦርነቱም ፡ ተዠምሮ ፡ ፈረሰኛው ፡ ከፈረሰኛ ፡ እግ
ረኛው ፡ ከእግረኛ ፡ ተደባልቆ ፡ ሲዋጋ ፡ አቧራው ፡ ሲነሣ ፡ ሰይፍና ፡ ጋሻ ፡
እርስ ፡ በርሱ ፡ እየተማታ ፡ ሲጮህ ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ታላቅ ፡ የወታደር ፡
እልቂት ፡ ተደረገ ። ክርስቲያኖቹ ፡ ተሸንፈው ፡ ሸሹ ፡ እስላሞቹ ፡ ፺ ፡ ፈረሶች ፡
ብዙ ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ አገኙ ። እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ሴቶ
ቻቸውን ፡ ልጆቻቸውን ፡ አስመልሰው ፡ እስላሞቹ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ዚፋህ ፡
(ዚባን) ፡ ተመለሱ ።

ሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ (የገራድ ፡ አቡን ፡ ገዳይ) ፡ የግራኝን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡
መመለስ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ ፤ ሠራዊቱንም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሱማሌ ፡ አገር ፡
ወደ ፡ ኪዳድ ፡ ሔዶ ፡ ሠፈረ ። የዚህን ፡ ወሬ ፡ ግራኝና ፡ ወገኖቹ ፡ ሲሰሙ ፡ ተከ
ታትለው ፡ ሔደው ፡ ከርን ፡ ከሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ አቡበከርን ፡ ገጠሙት ፡
አቡበከርና ፡ ሱማሌዎቹም ፡ ቲንሽ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ ሸሹ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ግራኝ ፡ ከነጦሩ ፡ ሐረርን ፡ (የሰዓዲንን ፡ አገር) ፡ ያዘ ። በኋላ ፡ ግን ፡ አቡበከር ፡
ብዙ ፡ ጦር ፡ አስከትቶ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ መምጣቱን ፡ ሲሰማ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡
ሐረርን ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ሐባት ፡ ዘበርቃ ፡ ሔዶ ፡ ተራራማ ፡ በሆነው ፡ ሥፍራ ፡
ላይ ፡ መሽጎ ፡ ተቀመጠ ። ሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ ይኸን ፡ ሰምቶ ፡ እግር ፡ በእ
ግር ፡ ተከታትሎ ፡ ሔዶ ፡ ግራኝ ፡ ያለበትን ፡ ተራራ ፡ ከቦ ፡ እስከ ፡ አሥር ፡
ቀን ፤ ድረስ ፡ አስጨነቀው ። ግራኝና ፡ ወገኖቹም ፡ ተከበው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡
መቆየት ፡ ስለሰለቻቸው ፡ ከተራራው ፡ ወርደው ፡ ጦርነቱን ፡ ገጠሙ ። ነገር ፡ ግን ፡
ወዲያው ፡ ተሸነፉ ፡ እንደ ፡ መሬ ፡ አድርገውት ፡ የነበረውም ፡ ኡመር ፡ ዲን ፡
ሞቶ ፡ ግራኝና ፡ ወገኖቹ ፡ ሸሹ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግራኝ ፡ ከነሰዉ ፡ ታርቆ ፡
ለአቡበከር ፡ ገባለት ። ግራኝና ፡ ጓደኞቹ ፡ ለአቡበከር ፡ በእርቅ ፡ ገብተው ፡
ቲንሽ ፡ ጊዜ ፡ እንደቆዩ ፡ አቡበከር ፡ እርቁን ፡ አፍርሶ ፡ ሰይፎቻቸውን ፡ ፈረሶ
ቻቸውን ፡ ቀማቸው ፡ ለግራኝም ፡ ከ፩ ፈረስ በቀር ምንም ፡ አልቀረውም ። ኡት
ማን ፡ ቤን ፡ ያሲን ፡ የሚባለውንም ፡ ዋና ፡ ኤሚር ፡ ገድሎ ፡ አገሩን ፡ ዘረ
ፈበት ፡ ሌሎቹንም ፡ ዳኞችና ፡ ሼኮች ፡ (ቀሳውስት) ፡ በጥላቻ ፡ እየጨቆነ ፡ አጉ

ላላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ለሕይወቱ ፡ ስለፈራ ፡ ከሦስት ፡ ፈረሰኞቹ ፡ ጋር ፡ ሌሊት ፡ በድብቅ ከአቡበከር ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ዛክህ ፡ ሔደ ። በዚያም ፡ አራት ፡ የአቡበከርን ፡ ፈረሶች ፡ ከሚጠብቀው ፡ ከሐ ምዱሽ ፡ ቤን ፡ ማኅፉዝ ፡ (አማዱሽ፡የማኅፉዝ ፡ ልጅ ፡) ላይ፡ ፈረሶቹን፡ ቀምቶ ፡ ዛክህን ፡ አገሩን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ፡ ሪባት ፡ ኤል ፡ ባከር ፡ ወደ ፡ ሚባል ፡ ዛፍ ፡ ወደሞ ላባት ፡ በረሀ ፡ ሔደ ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ፈረሰኞች ፡ ሰባት ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ግራኝም ፡ ሖባት ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ከከተማ ፡ ወደከተማ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሲዘዋወር ፡ ቆየ ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ ረዳቶቹ፡ የፊተኛው ፡ ገራድ ፡ አቡበከር ፡ ቤን ፡ ኢስማኤልና ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ኤሚር፡ ሁሴን ፡ ኤል ፡ ጋቱሪ ፡ ናቸው ።

ሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ ግራኝን ፡ ለመግደል ፡ ሲል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሰላይ ፡ እያ ከታተለ ፡ ይልክ ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ አህመድ ፡ ሖባት ፡ ነው ፡ ያለ ፡ ማለትን ፡ ሲሰማ ፡ ገሥግሦ ፡ ሔደ ። በዚያም ፡ የግራኝ ፡ አህመድን ፡ ቤት ፡ አቃጥሎ ፡ ብዙ ፡ ዕቃ ፡ ዘረፈ ። ግራኝም ፡ ይኸን ፡ ሲሰማ ፡ ከሖባት ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሔዶ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ከአቡበከር ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ በየጊዜው ፡ እየተዋጋ ፡ ኖሮ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ግራኝና ፡ ጓደኞቹ ፡ በሽሽትና ፡ በጉዞ ፡ ደክመው ፡ ጂዳር፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ተኝተው ፡ ሳለ ፡ አቡበከር ፡ ከነወታደሩ ፡ ደርሶ ፡ ሊፈጃቸው፡ ሲል ፡ ድንገት ፡ ነቅተው ፡ ምንም ፡ ሳይሆኑ ፡ ሸሹ ። ከዚያም ፡ ተከታትሎ ፡ ዋኪን፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ትንሽ ፡ ሰው ፡ ከገደለባቸው ፡ ወዲህ ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ተበታትኖ ፡ በኋላ ፡ ሖባት ፡ ላይ ፡ ተመልሶ ፡ ተገናኘ ። በዚያም ፡ ሳለ ፡ ኤሚር ፡ ሻንባራ ፡ የሚ ባል ፡ የአቡበከር ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ከፋኛ ፡ ተዋጋቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ አሸንፎ ፡ አባረራቸው ። ኤሚር ፡ ሻንባራም ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ ። የዚህን ፡ ወሬ ፡ ሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ ሲሰማ ፡ ፫ ፡ ኤሚሮች ፡ (መኳንንት) ፡ አስቀ ርቶ ፡ ሐረርን ፡ ትቶ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ግራኝን ፡ ለማበረር ፡ ወደሱማሌ ፡ አገር ፡ ሔደ። ግራኝ ፡ አህመድ ፡ አቡበከር ፡ አገሩን ፡ ለቅቆ ፡ መውጣቱን ፡ ባወቀና ፡ አገር ፡ ለመጠበቅ ፡ የቀሩትም ፡ ኤሚሮች ፡ እነማን ፡ መሆናቸውን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሡልጣን ፡ ግዛት ፡ ወደዛክህ ፡ ሔደ ። የአቡበከር ፡ አማች ፡ ኡሸም ፡ አቡበከር ፡ ከኤ ሚሮቹ ፡ አንዱ ፡ ጦሩን ፡ አደራጅቶ ፡ ግራኝ ፡ ወደአለበት ፡ አገር ፡ ተጓዘ ። በኋላ ፡ ግን ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ሲያይ ፡ ምንም ፡ ሳይዋጋ ፡ ከነጦሩ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሸሸ ። ግራኝም ፡ እሱን ፡ ሳይከታተል ፡ ከነጓደኞቹ ፡ ገሪር ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ሆኖ ፡ ለሐረር ፡ ጉዞ ፡ ምክር ፡ አደረገ ። ብዙዎቹ ፡ «ወደሐረር ፡ ሔደን ፡ እንዋጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድልን ፡ ለፈቀደው ፡ ይስጥ» ፡ ስላሉ ፡ በዚህ ፡ ተወስኖ ፡ ወደ ፡ ሐረር፡ ጉዞአቸውን ፡ ገሠሩ ። የተከተላቸው ፡ ጦር ፡ ፱፻፴ ፡ (ትንሽ ፡ ጭማሪ ?) ፡ ይደር ሳል ። የሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ ጦርም ፡ ደኅና ፡ ለውጊያ ፡ የሚመች ፡ ሥፍራ ፡ ይዞ፡ ሲጠባበቃቸው ፡ ግራኝ ፡ ከነጦሩ ፡ ደረሰና ፡ የጠላቱን ፡ ጦር ፡ አያያዝ ፡ ተመልክቶ ምንም ፡ ሳይዋጋ ፡ ፈርቶ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመልሶ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር። መመለሱን ፡ የአቡበከር ፡ ጦር ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ከኋላው ፡ ተከታተለው ። ሻማ

ዦንድ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ደረሰበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግራኝ ፡ ከነጦሩ ፡
ፊቱን ፡ ወደ ፡ ጠላቶቹ ፡ መልሶ ፡ ይዋጋ ፡ ጀመር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡
ግራኝ ፡ አህመድ ፡ አሸነፈ ። ከአለቆቻቸውም ፡ ብዙዎቹን ፡ ገደለ ። የቀረውም ፡ጦር፡
ሸሸ ፤ ከመቶ ፡ የሚበልጡ ፡ ፈረሶች ፡ ማረከ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐረር ፡ ገብቶ ፡ አገ
ሪቱን ፡ በሕግና ፡ በሥርዓት ፡ ማስተዳደር ፡ ጀመረ ። አዋጅ ፡ ነጋሪም ፡ ወጥቶ ፡
«ሁሉም ፡ በየቤቱ ፡ እንደልማዱ ፡ ይኑር ፡ አትፍሩ ፡ አትዘኑ ፡ በማንም ፡ ላይ ፡
ጥላቻና ፡ ቂም ፡የለንም» ፡ የሚል ፡ እየዞረ ፡ አሰማ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ዋናው ፡ የሐረር ፡ ሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ በሱማሌ ፡
አገር ሆኖ ፡ የፈረሰኛ ፡ የእግረኛ ፡ ጦሩን ፡ ከሱማሌ ፡ አገር ፡ አስከትሎ ፡ ወደ
ሐረር ፡ ተጓዘ ። ግራኝም ፡ ከሐረር ፡ የራሱን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ አቡበክርን ፡ ሊገ
ጥም ፡ ሔደ ። ሁለቱ ፡ ባላጋራዎች ፡ ዳከር ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ተጠጋግተው ፡
ሳሉ ፡ በመከከላቸው ፡ ሽማግሌ ፡ ገብቶ ፡ ግልግል ፡ ዠመረ ። አስታራቂዎቹ ፡
ሺሆችና ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ አቡበከር ፡ ሡልጣንነ
ቱን ፡ እንደያዘ ፡ የበላይ ፡ሆኖ ፡ ገዥነቱን ፡ ይቀጥል ። አህመድ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ
እንደ ፡ አንድ ፡ ኤሚር ፡ የበታች ፡ መኰንን ፡ ሆኖ ፡ አገር ፡ ተሰጥቶት ፡ እየገዛ
ይቀመጥ ፡ ብለው ፡ በዚህ ፡ አስታረቋቸውና ፡ ግራኝም ፡ ይኸንኑ ፡ ለጊዜው ፡ እሺ
ብሎ ፡ ለራሱ ፡ ወደ ፡ ተመደበለት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሲም ፡ ሔደ ። አቡበክርም ፡ ሐረር
ገብቶ ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣኑን ፡ ይዞ ፡ ያስተዳድር ፡ ጀመር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከግዛቱ ፡ ከሲም ፡ ለአቡበክር
የሚገባውን ፡ ግብር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሔደ ። ሽምንገዶ ፡ እሚባል ፡ ሥፍራ
ሲደርስ ፡ ጥቁር ፡ ደመና ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ንብ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ የግራኝ፡
አህመድን ፡ ጭንቅላት ፡ ከቦ ፡ እያነበነበ ፡ እስከ ፡ ሡልጣኑ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ አደረሰው።
ወደ ፡ ሡልጣኑ ፡ ዘንድ ፡ ገብቶ ፡ ግብሩን ፡ ሰጥቶ ተነጋግሮ ፡ ሲወጣ ፡ እንደዚያው ፡
ያው ፡ የንብ፡መንጋ፡ከበሩፍ ፡ ተቀብሎ ፤ እንደከበበው ፡ ሳይነድፈው ፡ እመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡
ድረስ ፡ አጅቦት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ንቡም ፡ ወደ ፡ ዛፉ ፡ ተመልሶ ፡ ሔደ ።
ይኸም ፡ የአህመድን ፡ የወደፊት ፡ ገዥነት ፡ ለመግለጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገው፡
ተአምራታዊ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ዐረብ ፡ ፋቂህ ፡እያጋነነ ፡ ጽፎታል ። ከዚ
ህም ፡ እያይዞ ፡ ሼክ ፡ አህመድ ፤ ሼሪፍ ፡ አቡበከር ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ታላቅ፡
ሼክ ፡ አህመድን ፡ ይማም ፡ በለው ፡ እንጂ ፡ ሡልጣንም ፡ ኤሚርም ፡ በሚባል ፡ የማ
ዕርግ ፡ ስም ፡ አትጥራው ፡ ብለው ፡ በሕልሜ ፡ነገሩኝ ፡ ብሎ ፡ ሼክ ፡ መሐመድ ፡
ቤን ፡ አህመድ ፡ ኤድ ፡ ዳሕማኒ ፡ ኤል ፡ ማግረቢ ፡ እንዳጫወተው ፤ ሌሎች ፡ ደግሞ፡
አሊ ፡ ቤን ፡ ሳላህ ፡ አህመድ ፡ ቤን ፡ ጣሂር ፡ ነቢዩ ፡ መሐመድ ፡ በቀኙ ፡ አቡበከር
ኤስሳዲቅን ፤ በግራው ፡ ኡመር ፡ ቤን ፡ ኤል ፡ ከታብን ፤ በፊቱ ፡ አሊ ፡ ቤን ፡ አቡ ፡
ታሊብን ፡ አድርጎ ፡ በአሊ ፡ ቤን ፡ አቡ ፡ ታሊብ ፡ ግንባር ፡ ደግሞ ፡ አህመድ ፡ ነበ
ርና ፡ ማነው ፡ ይህ ፡ በአሊ ፤ ፊት ፡ የቆመው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ ይህ ፡ ወደፊት፡

አበሻን ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሥልጣን ፡ የተሠጠው ፡ አህመድ ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ በሕልሙ ፡ እንደመሰሰለት ፡ ሕልሙም ፡ የታየው ፡ ግና ፡ አህመድ ፡
ተራ ፡ ወታደር ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻል ።

ይኸን ፡ የመሰለው ፡ የንብ ፡ ተአምራት ፤ የሕልምና ፤ የራዕይ ፡ ምልክት ፡ ብዙ
ጊዜ ፡ በእስያ ፡ በአፍሪካ ፡ በአውሮፓም ፡ በክርስቲያኑም ፡ በእስላሙም ፡ ቤተ ፡ መን
ግሥት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቆየ፡ ነው ።ጥንት ፡ የግብጾችና ፡ የኑብያ ፡ ነገሥታት ፡ ከክ
ርስትና ፡ በፊት ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ምልክት ፡ ሰጠን ፡ የሚሉት ፡ እቡብን ፡ ዘንዶን፡
ነበር ። ስለዚህም ፡ በየዘውዳቸው ፡ ላይ ፡ የእቡብ ፡ ምልክት ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ይኸም
ልማድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ምዕራብ ፡ ባላባቶች ፡ ዘንድ ፡ ሳይገባ ፡ አልቀረም ።
የቀረውም ፡ በአዕዋፍና ፡ በአሞራ ፡ ግግሹ በምድር ፡ አውሬና ፡ እንስሳ ፡ የቀረ
ውም ፡ ሁሉ ፡ በየክፍሉ ፡ ሲኖር ፡ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ጥም
ቀት ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ በመከታተል ፡ ይሁን ፡ ርግብ ፡ ደግሞ ፡ ወደዚሁ ፡ ጉዳይ ፡
ገብታ ፡ እገሌ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አረፈችበት ፡ ይነግሣል ፡ እየተባለ ፡ ይነገርለት ፡ ነበር ።
የዚህ ፡ የንቡ ፡ ተአምራት ፡ እንደዚሁ ፡ በኛም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡
በዜ ፡ ላሊበላ ፡ ልደት ፡ ተተርኮ ፡ ይገኛል ።

ገድለ ፡ ላሊበላ ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ስለላሊበላ ፡ ልደት ፡ እንደዚህ ፡
ይላል ፡ . . . «ወአመ ፡ ወለደቶ ፡ እሙ ፡ መጽኡ ፡ አንህብት ፡ ብዙኃን ፡
ወአገትዎ ፡ ከመ ፡ ዘየዓግቱ ፡ መዓረ ።ወርእያ ፡ እሙ ፡ እሎንተ ፡ አንህብተ ፡ ከመ፡
አገትዎ ፡ ወሐጸርዎ ፡ ለሕፃን ፡ ከመ ዘየዓውድዎ ፡ ሐራሁ ፡ ለንጉሥ ። ወሶበ፡ ርእ
የት ፡ ዘንተ ፡ ወረደ ፡ ኀቤሃ ፡ መንፈሰ ፡ ተንብዮ ። ወትቤ ፡ ንህብኒ ፡ አእመረ፡
ከመ ዓቢይ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ሕፃን ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሰመየቶ ፡ ላሊበላ ፡
ንህብ ፡ አእመረ ፡ ጸጋሁ ፡ ብሂል ። . . . . » ከዚህ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ግዕዝኛ ፡ ቃል፡
የሚያመለክተን ፡ ላሊበላ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ንብ ፡ መጥቶ ፡ ማር ፡ በገኘ፡
ጊዜ ፡ እንደሚከብ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ንጉሡን ፡ እንደሚከብ ፡ እንደዚሁ ፡ ንቡ፡
ላሊበላን ፡ እንደከበበው ። ይኸንንም ፡ እናቱ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ከላይ ፡ የትንቢት፡
መንፈስ ፡ ወርዶላት ፡ ይኸ ፡ ሕፃን ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ እንደሚሆን ፡ ንቦችም ፡
አወቁ ፡ ብላ ፡ ተናግራ ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ስሙን ፡ ላሊበላ ፡ ብላ ፡ እንደሠየ
መችውና ፡ ላሊበላ ፡ ማለትም ፡ ትርጓሜው ፡ ንብ ፡ ጌታውን ፡ (ጸጋውን) ፡ አወቀ፡
ማለት ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሴም ፡ ወይም ፡ የካም ፡ ዘር ፡ ቢሆን፡አማ
ራና ፡ አጻልም ፡ ክርስቲያንና ፡ እስላምም ፡ ቢሆን ፡ ልማዱና ፡ እምነቱ ፡ የሚ
መራው ፡ ባንድ ፡ መሥመር ፡ ስለሆነ ፡ የግራኝ ፡ በንብ ፡ መከበብ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡
ከ፫፻ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበረው ፡ ከዜ ፡ ላሊበላ ፡ ጋር ፡ ተጋጠመ ።
የላሊበላ ፡ ራቅ ፡ ብማለቱ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ገድል ፡ ጸሐፊ ፡
ገድሉን ፡ እንደ ፡ ታሪክ ፡ ሲጽፍ ፡ ማጣራት ፡ ስለማይሆንለት ፡ ነገሩን ፡ ባይኑ ፡
እንዳየ ፡ ያህል ፡ አረጋግጦ ፡ ይጽፋል ። ዐረብ ፡ ፈ ሀም ፡ ባሁኑ ፡ በሺ፩፻፳ ዓ ፡

ምሕረት ፡ ላይ ፡ የግራኝን ፡ ታሪክ ፡ ሲጽፍ ፡ በንብ ፡ መከበቡን ፡ ከሰው ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ራሱ ፡ ያየ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከግራኝ ፡ የተገናኘ ፡ አይ መስልም ። ስለሕልሙ ፡ ግን ፡ ከእገሌ ፡ ሰማሁት ፡ እያለ ፡ ያወሩትን ፡ የሺሆች ፡ ስም ፡ ጠቅሷል ፡ ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ቢከድም ፡ ቢታመንም ፡ እንደአንበ ቢው ፡ ስሜት ፡ ነውና ፡ አሁን ፡ ወደዋናው ፡ ታሪክ ፡ ተመልሰን ፡ እንቀጥል ።

እንግዴህ ፡ ግራኝ ፡ ከቀሳውስቱ ፡ የተሰጠውን ፡ ይማም ፡ የሚባል ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ይዞ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ እየተባለ ፡ በአቡበክር ፡ ሡልጣን ፡ ውስጥ ፡ ያንድ ፡ አውራጃ ፡ (ሲም) ፡ ገዥ ፡ ሆኖ ፡ ከዕለት ፡ ወደዕለት ፡ እየበረታ ፡ ጦርም ፡ እየሰበ ሰበ ፡ ሲኖር ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ መጥቶ ፡ በደዋሮ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ አሸንፎ ፡ ብዙ ፡ የቀንድና ፡ የጋማ ፡ ከብት ፡ ሰውም ፡ ዘረፈ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ደረሰና ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደገና ፡ አሸንፎ ፡ የተወሰደውን ፡ ማስመለስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከግራኝም ፡ ጦር ፡ ብዙ ፡ መሣሪያና ፡ ከብት ፡ ወሰደ ። ከግራኝ ፡ (ይማም) ፡ አህመድ ፡ ጋር ፡ የነበሩም ፡ ፯ ፡ ኤሚሮች ፡ ሁሴን ፡ ኤል ፡ ጋቱሪ ፤ ዛሐርቡይ ፡ መሐመድ ፤ አብደላ ፤ ኡመር ፤ አው ራይ ፡ አህመድ ፤ ጅብራይል ፡ (ሱማሌው) ፡ ተማረኩ ። ከነዚሁ ፡ ከ፯ቱ ፡ ሁሴን ፡ ሊገደል ፡ ሲል ፡ ከሐበሾቹ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ወገኖቹ ፡ ሄደ ፡ የቀሩት ፡ ወደን ጉሡ ፡ ተልከው ፡ ሁለቱ ፡ ተገደሉ ። የቀሩት ፡ ታሰሩ ። ግራኝ ፡ ግን ፡ የተረፈውን ፡ ጦር ፡ እንደያዘ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ተመለሰ ። ከዚያም ፡ ሳለ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከሡል ጣን ፡ አቡበክር ፡ ጋር ፡ እየተጣሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እየታረቁ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ አቡበከር ፡ ግራኝን ፡ እገድላለሁ ፡ እያለ ፡ ሲመኝ ፡ ግራኝ ፡ እርሱን ፡ ገደለና ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ወንድሙን ፡ ኡመር ፡ዲንን ፡ በልጋው ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ።

በዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ እጸጸፍ ፡ ውስጥ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አቡበክር ፡ አመጸኛ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ አገር ፡ በዳይ ፤ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ አክባሪ ፡ መልካም ፡ አስተ ዳዳሪና ፡ የተወደደ ፡ መሆኑን ፡ እየደጋገመ ፡ ይገልጻል ። ምናልባት ፡ ይህን ፡ መጽ ሐፍ ፡ የጻፈው ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሚለው ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ ከሌላ ፡ ከማያደላ ፡ ምስክር ፡ መፈለግ ፡ ያሻ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ያቡበክርን ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪኩን ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ስለአልገ ጠመኝ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ላገባውና ፡ ላመዛዝነው ፡ አልቻልሁም ። ግራኝ ፡ እርሱን ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ሥልጣኑን ፡ በሙሉ ፡ ለራሱ ፡ ጠቅልሎ ፡ በመያዝ ፡ ፈንታ ፡ ለአ ቡበክር ፡ ወንድም ፡ ለኡመር ፡ ዲን ፡ የሰጠው ፡ በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ እንባቢ ፡ እንደሚመለከተው ፡ የአቡበክር ፡ ዘር ፡ ከይፋት ፡ ዠምሮ ፡ ከላይ ፡ ከዋናው ፡ ባላ ባት ፡ ከወላስማ ፡ የመጣ ፡ ስለሆነ ፡ በሐረር ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ያንኑ ፡ የርሱን ፡ ዘር ፡ (ነጋሢ) ፡ ማስቀመጥ ፡ እንጂ ፡ ራሱ ፡ ቢቀመጥ ፡ እንደማይሆንለት ፡ ገምቶ ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ በሐረር ፡ በወላስሞች ፡ አልጋ ፡ የሚቀመጠው ፡ የማዕርግ ፡ ስሙ ፡ ሡል ጣን ፡ ስለሆነ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ በትንቢትና ፡ በንግርት ፡ ከሺሆቹ ፡ (ቄሶቹ) ፡ የተሰ ጠው ፡ ይማም ፡ እንጂ ፡ ሡልጣን ፡ እንዳይባል ፡ ስለታዘዘ ፡ ይኸንኑ ፡ ስሙን ፡

ላለመለወጥ ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ኡመር ፡ ዲን ፡ እንደ፡አቡ በክር ፡ ለግራኝ ፡ አህመድ ፡ እነማ… ፡ እንቅፋት ፡ ሳይሆን ፡ ላዩን ፡ የበላይ ፡ ውስጡን ፡ የበታች ፡ ሆኖ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ፡በኅብረት ፡ ሥራቸውን ፡ ቀጠሉ ። አህመድም ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ይማም፡ አህመድ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራ ፡ ነበር ። እኔም ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ጽሑፍ፡ሁሉ፡ በዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ በራሴ ፡ አነጋገር ፡ ውስጥ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ እያልሁ ፡ ጽፌያለሁ ። በገራችን ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከማለት ፡ ይልቅ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ እየተባለ ፡ ደምቆ ፡ ይጠራል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዋናው፡ ከእስላሞች ፡ ነቢይ ፡ ከመሐመድ ፡ ስም ፡ ላይ ፡ በዝንጋታ ፡ የተወሰደና ፡ የሰው ፡ አንደበት ፡ በልማድ ፡ የወረሰው ፡ እንጂ ። የግራኝ ፡ እውነተኛ ፡ ስሙ ፡ አህመድ ፡ እንጂ ፡ መሐመድ ፡ አይደለም ። ትርጉሙም ፡ መሐመድ ፡ ምስጉን ፡ ሲሆን ፡ አህመድ ፡ አመስጋኝ ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

### በዒ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የነበሩ ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሊቃውንትና ፡ ሹማምንት ።

ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ደርሰው ፡ መንግሥቱን ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ በሚመሩበት ፡ ጊዜ ፡ በወታደርነትም ፡ በአስተዳደርም ፡ በቤተ ፡ ክህነትም ፡ በኩል ፡ ሆነው ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ አለቆችና ፡ ሹማምንቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ አብዛኞቹ ፡ ወደፊት ፡ በዝርዝር ፡ በምናገኘው ፡ በግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጉ ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ ፡ እየቆሰሉ ፡ የተማረኩ ፡ ጥቂቶቹም ፡ የግራኝ ፡ ኃይል ፡ በጣም ፡ እየተጫነ ፡ ሄዶ ፡ ከተሸነፉ ፡ በኋላ ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ እየገቡ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እስከ ፡ መለወጥ ፡ የደረሱ ፡ አሉ ። የነዚህም ፡ ስም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ እንደዚሁም ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱም ፡ ውስጥ ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሰብስቤ ፡ ከዚህ ግርጌ ፡ ዘርዝሬያቸዋለሁ ። ከነዚህ ፡ በዝርዝሩ ፡ ከሚገኙት ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹ ፡ በሁኑ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በወጣትነት ፡ ባሉበት ፡ ሰዓት ፡ የሌሉ ፡ በግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የተነሡ ፡ መሆናቸውን ፡ ላንባቢ ፡ አሳስቤ ፡ ከራሳቸው ፡ ከንጉሡና ፡ ከጳጳሱ ፡ ጀምሮ ፡ ጠቅላላውን ፡ ዝርዝር ፡ እነሆ ፡ አመለክታለሁ ።

| ተራ ቍ | ስ ም ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፩ | ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ | ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ (አንበሳ ፡ ሰገድ )፡ ወይም ፡ ዳዊት ፡ የሚጠሩት ፡ በክርስትና ፡ ስማቸው ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወይም፡ በአማርኛ ፡ ዕጣነ ፡ ድንግል ። ንጉሠ ፡ ነገሥት ። |
| ፪ | አባ ፡ ማቴዎስ ፡ | ጳጳስ ። |
| ፫ | አባ ፡ ስምዖን ፡ | » |
| ፬ | እቴጌ ፡ እሌኒ ፡ | ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም የቀኝ ፡ ሚስት ፡ የደ ዋሮው ፡ ባላባት ፡ የመሐመድ ፡ ልጅ ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የወጣትነት ፡ ዘመን ፡ ሞግዚት፡ ሆነው ፡ ያስተዳድሩ ፡ የነበሩ ። |
| ፭ | እቴጌ ፡ ናዖድ ፡ ሞገሳ ፡ | ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ባለቤት ። |
| ፮ | እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ | ያፄ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ባለቤት ። |
| ፯ | ራስ ፡ ደገልሃን ፡ | ከወለተ ፡ ቀለምሲስ ፡ ቀጥሎ ፡ ያፄ ፡ ልብነ፡ ድንግልን ፡ እህት ፡ ዓመተ ፡ ውጥንን ፡ ያገባል ። ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ መልአከ ፡ ኃይሉ ፡ ለልብነ ፡ ድንግል ፡ ይለዋል ። ትርጓሜው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ በዛሬው ፡ ዘመን ፡ አጠራር ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ ማለት ፡ ነው። የማዕርግ ፡ ስሙ ፡ አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ራስ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አዝማች ፡ ደገልሃን ፡ ይባላል ። በግዛት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ታላቅ፡ አውራጃ ፡ የሚቆጠረውን ፡ ባሌን ፡ ይገዛል ። ከግራኝና ፡ ከጦር ፡ አለቆቹ ፡ ጋር ፡ ያደረገውን፡ ጦርነት ፡ ከታሪኩ ፡ ላይ ፡ እናነባለን ። ታላቅ ፡ ሰው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጦርነት ፡ ጀግንነትና ፡ ድፍረት ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። ለአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ጠቅላይ ፡ አዝማችነት ፡ ቢሾም ፡ ግራኝን፡ በመፍራት ፡ በሚስቱ ፡ በኩል ፡ ውስጡን ፡ ነገር፡ ሰርቶ፡ እንዲለወጥ፡ ማድረጉን፡ ወደፊት፡ እናነባለን ። |
| ፰ | ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ | የዳሞት ፡ ገዥ ፡ ቀጥሎ ፡ ጐጃም ፡ ነጋሽ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ የተከበረና ፡ የተፈራ ፡ የጦር አለቃ ፡ ከንጉሡም ፡ ዝምድና ፡ ያለው ፡ ነው ። እርሱም ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ሞተ ። |

| ተራ ቍ | ስም ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፱ | ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ | አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባጭሩ ፡ ራስ ፡ ወይም ፡ አዝማች ፡ እስላሞ ፡ ይባላል ። የፈጠጋር ፡ አገረ ፡ ገዥ ። በአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ዋና ፡ አዝማች ፡ ሆኖ ፡ የተሸነፈ ፤ በኋላ ፡ በተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ በዛሬ ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጋ ፡ በአቡበከር ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |
| ፲ | ራስ፡በንያት፡ ነቢያት ፡ (ዩኒያት) | የደዋሮ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ መሪ። |
| ፲፩ | ራስ ፡ ማኅፀንቶ ፡ | ያረብ ፡ ፋቂሀ ፡ መጽሐፍ ፡ መሀተንቶ ፡ (ረኔ ፡ በሴት ፡ አምኃ ፡ ጠንት) ፡ ይለዋል ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጋ ፡ አንድ ፡ አዱር ፡ የሚባል ፡ የሱማሌ ፡ ወታደር ፡ በቀስት ፡ ወርውሮ ፡ በፍላጻ ፡ ዓይኑን ፡ ሙትቶ ፡ ገደለው ። የሹመት ፡ ስሙ ፡ ደዋሮ ፡ ነጋሽ ። |
| | አቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ | የንጉሡ ፡ የልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ያ ፡ ይነብር ፡ (ያዕቆብ ፡ ይኖራል) ፡ የተባለ ፡ ባፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፭፻፵፱ ፡ ዓ፡ ም፡ የሞተ ። |
| ፲፪ | አቤቶ ፡ ፊቅጦር ፡ | የንጉሡ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የበኵር ልጅ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ በሚያዝያ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፭፻፴፩ ፡ ዓ፡ ም፡ ገራድ ፡ አትማን ፡ (ገራድ ፡ እስማን) ፡ የገደለው ። ድርሳነ ፡ ራጉኤል ፡ ፊ ፡ (ፊቅጦር) ፡ ይመውት ፡ (ይሞታል) ፡ ያለው ፡ እርሱን ፡ ነው ። |
| | አቤቶ ፡ ገላውዴዎስ ፡ | የንጉሡ ፡ የልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅና ፡ የዙፋን ፡ ተከታይ ። (ገ. ይነግሥ)-ገላውዴዎስ ፡ ይነግሣል ። |
| ፲፫ | አቤቶ ፡ ሚናስ ፡ | የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ በ፲፭፻፴፩ ፡ ዓ፡ ም፡ ኡመር ፡ ንጉሡን ፡ የወጋለት ፡ በእስላሞች ፡ እጅ ፡ ተማረከና ፡ ወደ ፡ ዘቢድ ፡ የተላከ ፡ ከዚያ ፡ በለውጥ ፡ ተመልሶ ፡ ከገላውዴዎስ ፡ ቀጥሎ ፡ ነገሠ ። ድርሳነ ፡ ራጉኤል ፡ ሚ ፡ ይሰየጥ ፡ (ሚናስ ፡ ይሸጣል ፡) ያለው ፡ እርሱን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በምርኮ ፡ ሄዶ ፡ በለውጥ ፡ መመለሱን ፡ እንጂ ፡ ለመሣሪያ ፡ አለመሸጡን ፡ በሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እናመለክታለን ። |
| ፲፬ | ራስ ፡ ዓምዱ ፡ | ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ በአዳሙ ፡ እጅ ፡ የሞተ ፡ የጦር ፡ አለቃ ። |

| ተራ ቍ | ስም ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፲፭ | ፋኑኤል ፡ | ካዬ ፡ ሰይፈ ፡ አርእድ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ዝምድና ፡ አለው ። እናቱ ፡ መግደላዊት ፡ ትባላለች ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ የዋግ ፡ በመጨረሻ ፡ የደዋሮ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ሆኖ ፡ ከእስላሞች ፡ ጋር ፡ በገርግንነት ፡ የተዋጋና ፡ የሞተ ፡ ስንክሳር ፡ ሰኔ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ያነሣዋል ። |
| ፲፮ | አዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ | የትግሬ ፡ የእንጎት ፡ የደሆኖ ፡ ወደብ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በዛሬ ፡ ጦርነት ፡ ጠቅላይ ፡ አዝማች ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጋ ፡ በአደቅ ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |
| ፲፯ | ኀቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ነገደ ፡ ኢየሱስ ፡ | ዓባይ ፡ ዳር ፡ ንጉሡ ፡ ሊማረኩ ፡ ሲሉ ፡ ለጥቂት ፡ አምልጠው ፡ ሲሸሹ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ነገደ ፡ ኢየሱስም ፡ አብሮ ፡ ሲሸሽ ፡ ንጉሡን ፡ ያገኘሁ ፡ መስሎት ፡ አብሳማኑር ፡ ማረከውና ፡ ንጉሡ ፡ አለመሆኑን ፡ ሲያውቅ ፡ ገደለው ። |
| ፲፰ | ጽራግ ፡ ማሠሬ ፡ ተክለ ፡ ሥሉስ ፡ | በጦርነት ፡ የሞተ ። |
| ፲፱ | አዝማች ፡ ተስፋ ፡ ልዑል ፡ | የሠራዌ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ (አቃጽን ፡ ሠራዌ ፡) በትግሬ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ የግራኝን ፡ ሞግዚትና ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ቬዚር ፡ አዶሌን ፡ የገደለ ። ርሱ ፡ ራሱ ፡ ደግሞ ፡ ከቬዚር ፡ አባስ ፡ ጋር ፡ በገርግንነት ፡ ሲዋጋ ፡ ሞቶ ፡ ሕይወቱን ፡ ለወገኖቹና ፡ ላገሩ ፡ የሠዋ ። |
| ፳ | አዝማች ፡ አዳሉ ፡ | ከራስ ፡ ደገልሃን ፡ በኋላ ፡ በባሌ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ መሪ ፤ ሹማምንትንና ፡ የጦር ፡ ወታደሩን ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ለማዋጋት ፡ ሲል ፡ የሚሸሸውን ፡ እያዩ ፡ እንዲታዘቡ ፡ ሚስቶቻችንና ፡ ገረዶቻችን ፡ ከውጊያው ፡ በኋላ ፡ ይሁኑ ፡ ብሎ ፡ በገርግንነት ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። ከፍ ፡ ያለ ፡ ገርብዱ ፡ ሠርቶ ፡ የሞተ ፡ መሆኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሊያውቅለት ፡ ይገባል ። የርሱም ፡ ገርብዱ ፡ ከዓድዋው ፡ ተዋጊ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ገበየሁ ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል ። |
| ፳፩ | ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ | ጐጃም ፡ ነጋሽ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የተከበረ ፡ ትልቅ ፡ የጦር ፡ መሪና ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። |

| ተራ ቍ | ስም ፡ | አንዳንድ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፸፪ | ግን ፡ በለው ፡ ራስ ፡ | ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ሲዋጋ ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ የሞተ ። |
| ፸፫ | ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ሮቤል ፡ | የአምባ ፡ ግሼን ፡ (አምባ ፡ ነገሥት ፡) ሹም ። |
| ፸፬ | ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዘወንጌል ፡ | የድሆኖ ፡ ገዥ ። |
| ፸፭ | ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ | ፖርቱጋሎች ፡ ከሕንድ ፡ አገር ፡ ለእርዳታ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ምጥዋ ፡ ላይ ፡ ተቀብሎ ፡ ያስተና ገደና ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ አምጥቶ ፡ ያገናኘ ። |
| ፸፮ | ብሕት ፡ ወደድ ፡ ሠርጤ ፡ | የንጉሡ ፡ አማች ፡ የራስ ፡ ዓምዱ ፡ ልጅ ። |
| ፸፯ | ተክለ ፡ መድኅን ፡ | የንጉሡ ፡ አማች ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ተማርኮ ፡ በኋላ ፡ ፲፩ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ከፍሎ ፡ ወደ ፡ ወገኖቹ ፡ የተመለሰ ። |
| ፸፰ | አዝማች ፡ ይስሐቅ ፡ | የቤጌምድር ፡ አገረ ፡ ገዥ ፤ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ በአሌ ፡ ማጂራህ ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |
| ፸፱ | አዝማች ፡ ዮሐንስ ፡ | የጸለሞት ፡ ገዥ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ የተዋጋ ፡ በሽሽት ፡ ላይ ፡ ከዛፍ ፡ ወድቆ ፡ የሞተ ። |
| ፹ | አዝማች ፡ ይስሐቅ ፡ | በባሌ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። |
| ፹፩ | አዝማች ፡ ሳውል ፡ | የተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ልጅ ፡ የቤጌምድር ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የወገራን ፡ የጸለሞትን ፡ ጦር ፡ ጨምሮ ፡ ከግራኝ ፡ የተዋጋ ። |
| ፹፪ | ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ | በፊት ፡ ክርስቲያን ፡ የነበረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዞሮ ፡ ሃይማኖቱንም ፡ ለውጦ ፡ ሳለ ፡ ግራኝ ፡ ከሹመቱ ፡ ቢሽረው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተመልሶ ፡ ሹመትም ፡ አግኝቶ ፡ ዘመዶቹውን ፡ ድረውለት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ለንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ ከአቡበከር ፡ ቀጢን ፡ በዠግንነት ፡ ሲዋጋ ፡ ተማረከ ። ግራኝ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደመታያ ፡ ለአደን ፡ ሡልጣን ፡ ልኮ ፡ ሚስቱን ፡ አገባ ፡ ክርስቲያ ፡ ወለደ ። |

| ተራ ቍ | ስም ፡ | አንዳንድ ማመልከቻ ። |
| --- | --- | --- |
| ፹፫ | ፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ | በትግሬ ፡ ያንድ ፡ አውራጃ ፡ ሹም ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ጦርነት ፡ የሞተ ። |
| ፹፬ | አባ ፡ ገብረ ፡ እንድርያስ ፡ | ከአፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዠምሮ ፡ ከሹመት ፡ ወደ ፡ ሹመት ፡ ላይ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ መጥተው ፡ ከፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ማኅፉዝን ፡ የገደሉ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ የተዋጋለት ፡ አብረው ፡ የሞቱ ፡ መነኰሴ ። |
| ፹፭ | ብሕት ፡ ወደድ ፡ በድላይ ፡ | የስሙ ፡ አጠራር ፡ የመሐመድ ፡ በድላይ ፡ ዘር ፡ ይመስላል ። ከብሕት ፡ ወደድነት ፡ ማዕርግ ፡ ጋራ ፡ በግዛት ፡ ደዋሮን ፡ ተሾሞ ፡ በጦርነት ፡ ያገለገለ ፡ ነው ። በአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ የበላይ ፡ አዝማች ፡ በመሆኑ ፡ ተቀይሞ ፡ ነበር ። |
| ፹፮ | ኡስማን ፡ አሊ ፡ አውራይ ፡ | የይፋት ፡ ገዥ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ የተዋጋ ። በባደቂ ፡ ጦርነት ፡ ጠቅላይ ፡ አዝማች ፡ የነበረው ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሲሞት ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ ታርቆ ፡ ለግራኝ ፡ ገብቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ በአምበ ፡ ግሼን ፡ ሲዋጋ ፡ የተገደለ ። |
| ፹፯ | ተስፋዊ ፡ | የተስፋ ፡ ልዑል ፡ ዘመድ ፡ የቴዎድሮስ ፡ ወንድም ፡ አገሩንና ፡ ወገኖቹን ፡ እነተስፋ ፡ ልዑልን ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዞሮ ፡ ሠራዊን ፡ የተሾመ ። |
| ፹፰ | ፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ | ያፄ ፡ እስክንድር ፡ አማች ፡ በአዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በዛሬ ፡ (አይፈርስ ፡) የተዋጋ ። |
| ፹፱ | ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ | በትግሬ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። |
| ፺ | በለው ፡ ሰገድ ፡ | የራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ ወንድም ፡ በዳሞት ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተዋጋና ፡ በኋላ ፡ እናሪያ ፡ ሲደርስ ፡ ወገኖቹ ፡ ከድተው ፡ አሡሩትና ፡ ለአዶሌ ፡ አስረከቡት ፡ አዶሌም ፡ ለግራኝ ፡ አቀረበውና ፡ አስገደለው ። |

| ተራ ቍ | ስም ፣ | አንዳንድ ፣ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፹፩ | በለው ፣ ሰገድ ፣ | የሠራዊው ፣ የተስፋ ፣ ልዑል ፣ ልጅ ፣ የአሮን ፣ ወንድም ፣ በሠራዊ ፣ ካባቱ ፣ ከተስፋ ፣ ልዑልና ፣ ከወንድሙ ፣ ከአሮን ፣ ጋር ፣ ሆኖ ፣ ከእስላሞች ፣ ጋር ፣ ሲዋጋ ፣ የሞተ ። |
| ፹፪ | አሮን ፣ | የተስፋ ፣ ልዑል ፣ ልጅ ፣ የበለው ፣ ሰገድ ፣ ወንድም ፣ በሠራዊ ፣ ሲዋጋ ፣ የሞተ ። |
| ፹፫ | አግብአ ፣ ሚካኤል ፣ | የሮቤል ፣ ወንድም ፣ ኀይለኛና ፣ ተዋጊ ፣ የነበረ ፣ በግራኝ ፣ እጅ ፣ በጦርነት ፣ የሞተ ። |
| ፹፬ | ጃውሔር ፣ ሊቀ ፣ መኳስ ፣ | |
| ፹፭ | መንዴል ፣ ሊቀ ፣ መኳስ ፣ | |
| ፹፮ | ሰሎሞን ፣ | በበሌ ፣ የጦር ፣ አለቃ ። |
| ፹፯ | ተክለ ፣ ሃይማኖት ፣ | የራስ ፣ ደገልሃን ፣ ልጅ ፣ በግድም ፣ ከቬዚር ፣ አባስና ፣ ከግራኝ ፣ ጋር ፣ በሚገባ ፣ ተዋግቶ ፣ የተማረከ ፤ በግራኝ ፣ ትእዛዝ ፣ ሰልሞ ፣ አራት ፣ ወር ፣ ያህል ፣ አብሮ ፣ እንደ ፣ ቆየ ፣ ሲመቸው ፣ ከዘቡል ፣ አምልጦ ፣ ወደ ፣ ወገኖቹ ፣ የሔደ ። |
| ፹፰ | አዝማች ፣ ተክላይ ፣ | የሠራዊ ፣ ሹም ፣ በዝሆን ፣ ዱር ፣ (ዳሞት ፣) ጦርነት ፣ ሼክ ፣ ሚካኤልን ፣ የገደለና ፣ የተማረከ ። |
| ፹፱ | ተክሌ ፣ | |
| ፺ | ሰበሩ ፣ (ሰበሮ) | የተክላ ፣ ልጅ ፣ ፋራቃሐም ፣ የማረከውና ፣ ወደ ፣ ዐረብ ፣ አገር ፣ የላከው ። |
| ፺፩ | ተኪ ፣ | ወደ ፣ ግራኝ ፣ የዞረ ። |
| ፺፪ | ተክለ ፣ ጊዮርጊስ ፣ | የፈረሰኞች ፣ የጦር ፣ አለቃ ፣ ዠግንነቱ ፣ በግራኝ ፣ ዘንድ ፣ የታወቀ ። ከቢር ፣ መሐመድን ፣ የገደለ ፣ በኋላ ፣ ባገሩ ፣ በሾጅራህ ፣ ተዋግቶ ፣ የሞተ ። |
| ፺፫ | አናንያ ፣ | የአውራይ ፣ ኡስማን ፣ ምክትል ፣ ሹም ፣ የነበረ ፣ ከርሱ ፣ ጋር ፣ ለግራኝ ፣ ገብቶ ፣ የገራድነት ፣ ማዕርግ ፣ ያገኘና ወሲል ፣ ድረስ ፣ የግራኝን ፣ ጦር ፣ እየመራ ፣ ወርዶ ፣ ያዋጋ ፣ ወገኖቹን ፣ ክርስቲያኖቹን ፣ ከድቶ ፣ በስለላ ፣ በመምራት ፣ ግራኝን ፣ በጣም ፣ ያገለገለ ። |

| ተራ ቍ | ስም ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፶፬ | አብርሃ ፡ | በራስ ፡ ደገልሃን ፡ ውስጥ ፡ የባሌ ፡ ሹም ፡ |
| ፶፭ | አብርሃም ፡ | የጸለሞት ፡ ገዥ ፡ በዛሬ ፡ (አይፈርስ) ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጋ ፡ በአብሳማ ፡ ኑር ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |
| ፶፮ | ሸንቁር ፡ | በባሌ ፡ የራስ ፡ ደገልሃን ፡ የበታች ፡ ሹም ። |
| ፶፯ | ድል ፡ በኢየሱስ ፡ | ወገኖቹን ፡ ከድቶ ፡ ወገኖቹን ፡ ገድሎ ፡ ለግራኝ ፡ የገባ ። |
| ፶፰ | ወናግ ፡ ዠን ፡ | ቀድሞ ፡ በዔ ፡ ናዖድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይቀር ፡ ኢትዮጵያን ፡ የከዳ ፡ የራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ወንድም ፡ አሁንም ፡ ከድል ፡ በኢየሱስ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ የገባና ፡ ሰልሞ ፡ ግዛት ፡ የተቀበለ ። |
| ፶፱ | ሲሙ ፡ | የከዳተኛው ፡ የወናግ ፡ ዠን ፡ ልጅ ፡ ራሱም ፡ ከድቶ ፡ ከሰበሩ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ የባሌን ፡ ሰው ፡ ለግራኝ ፡ ያሳበረ ፡ ድል ፡ ሰበርን የገደለ ። |
| ፷ | ወናግ ፡ ዠን ፡ | የይፋት ፡ ሹም ፡ ከእስላሞች ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ፋራ ቃሃም ፡ ሳቱ ፡ የገደለው ። |
| ፷፩ | አዝማች ፡ ፍሥሐ ፡ | ከይፋት ፡ ከድቶ ፡ ለግራኝ ፡ ገብቶ ፡ ብዙ ፡ ምሥጢርና ፡ ምክር ፡ የሰጠ ። |
| ፷፪ | አክሊል ፡ | በወረባ ፡ የጦር ፡ አለቃ ። |
| ፷፫ | ጊዮርጊስ ፡ (አዝማች ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ) ። | በደብረ ፡ ብርሃን ፡ (ተጉለት) ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የነበረ ፡ በጀግንነቱ ፡ እስላሞች ፡ ያመሰገኑት ። |
| ፷፬ | ጊዮርጊስ ። | በጐጃም ፡ የጦር ፡ አለቃና ፡ ገዥ ፡ በዛሬ ፡ (አይፈርስ) ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጋ ፡ ተማርኮ ፡ ሳለ ፡ ከዚያ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ገብቶ ፡ የሞተ ። |
| ፷፭ | አዝማች ፡ ሃያቢል ። | የጋቱር ፡ ገዥ ፡ በኋላ ፡ ከድቶ ፡ ለግራኝ ፡ የገባ ። አዝማች ፡ ሃይቢ ፡ የተባለው ፡ ርሱ ፡ ይሆን ? ። |
| ፷፮ | ሐና ። | የላሊበላ ፡ (የይፋቱ ፡ እንጂ ፡ የላስታው ፡ አይደለም) ፡ ገዥ ። |
| ፷፯ | ነገደ ፡ ኢየሱስ ። | የጅናህ ፡ ገዥ ፡ በዛሬ ፡ (አይፈርስ) ፡ ጦርነት ፡ በገራድ ፡ አህማዱሽ ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |

| ተራ ቁ. | ስም ፤ | አንዳንድ ፤ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፷፰ | አዝማች ፤ (አዛዥ)፤ አምኃ | የራስ ፤ ማኅፀንቶ ፤ ልጅ ፤ በደዋሮ ፤ በተምቤን ፤ የተዋጋ ፤ ፈራቃሃም ፤ የሚባለውን ፤ የእስላሞች ፤ የጦር፤ አለቃ ፤ የገደለ ። |
| ፷፱ | ተስፋ ። | የዘቀላህ ፤ (ዝቋላ-ኤል ፤ ማያ) ፤ ገዥ ፤ ሆኖ ፤ ብዙ ፤ ጊዜ ፤ የተዋጋ ፤ በኋላ ፤ ተስፋ ፤ ቆርጦ ፤ ለግራኝ ፤ ገብቶ ፤ የሰለመ ። ዘቃላህ ፤ ሲል ፤ ዝቋላ ማለቱ ፤ ኤል ፤ ማያ ፤ ሲል ፤ ደግሞ ፤ ምንም ፤ አነጋገሩ ፤ ባይቀራረብ ፤ ያሩሲን ፤ አገር ፤ የሚጠቅስ፤ ይመስላል ። |
| ፸ | አዝማች ፤ ዩናዳብ ። | የንጉሡ ፤ አማች ፤ ብዙ ፤ ጊዜ ፤ ከግራኝ ፤ ጦር ጋር ፤ እየተዋጋ ፤ ሲኖር ፤ በመጨረሻ ፤ በዘሀርቡይ፤ እጅ ፤ በአራም ፤ ጦርነት ፤ የሞተ ። |
| ፸፩ | እስላም ፤ ደኃር ። | የከም ፤ ደኃር ፤ ልጅ ፤ ያፄ ፤ እስክንድርን ፤ ልጅ ያገባ፤የዋጅ ፤ (ዋግ?) ፤ ገዥ ፤ አገሩን፤ሞጃሂድ ፤ ከወረረ በት ፤ በኋላ ፤ እስላም ፤ አልሆንም ፤ ብሎ ፤ ሲከራከር ፤ ኖሮ ፤ በኋላ ፤ ከሞጃሂድ ፤ ጋር ፤ ሲዋጋ ፤ተማርኮ ፤ የተገደለ ። |
| ፸፪ | ዘረ ፤ ሠናይ ፤ (ዘርዓ ፤ ሠናይ ?) ። | የሐማሴን ፤ ገዥ ፤ መጀመሪያ ፤ ለንጉሡ ፤ የነበረ ፤ በኋላ ፤ ከድቶ ፤ ለግራኝ ፤ የገባና ፤ ሹመቱን፤ ያጸደቀለት ። |
| ፸፫ | ክፍሌ ። | የተክለ ፤ ኢየሱስ ፤ ልጅ ፤ የቀዳ ፤ ሹም ፤ በዛሪ (አይፈርስ) ፤ ጦርነት ፤ ሲዋጋ ፤ ተማርኮ ፤ ፴ ፤ወቄት፤ ወርቅ ፤ ከፍሎ ፤ ወደ ፤ ወገኖቹ ፤ ተመለሰ ። |
| ፸፬ | ቴድሮስ ፤ (ቴዎድሮስ) ። | ወገኖቹን ፤ ከድቶ ፤ ለግራኝ ፤ የጦር ፤ አለቃ፤ ለአዶሌ ፤ ቢገባ ፤ የሠራዊቱን ፤ ግዛት ፤ ሰጠው ፤ በዚሁ ዘመዱ ፤ ተስፋ ፤ ልዑል ፤ ተዋግቶ ፤ ገደለው ። |
| ፸፭ | ሰበሩ ። | ከሲሙ ፤ ጋር ፤ ሆኖ ፤ የባሌን ፤ ጦርና ፤ ሕዝብ፤ ለግራኝ ፤ ያሳበረ ፤ ከዳተኛ ። |
| ፸፮ | መክተር ፤ (መከትር) ። | የመዘጋ ፤ (ስናር ፤ አጠገብ ፤ ያለ ፤ አገር) ፤ ባላባት ፤ እንደ ፤ ንጉሥ ፤ የሚቆጠር ፤ ወደ ፤ ግራኝ ፤ ከነሕዝቡ ፤ ሊገባ ፤ ሲዘጋጅ ፤ ክርስቲያኖቹ ፤ ተዋጉት ፤ በኋላ ፤ ግን ፤ ከግራኝ ፤ ጋር ፤ በሰላም ፤ በደስታ ፤ ተገናኝቶ ፤ ወዳጅ ፤ ሆነ ፤ ልጁንም ፤ ለግራኝ ፤ ዳረለት ። |

| ተራ ቍ | ስ ም ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፻፯ | ጌዴዎን ። | የፈላሾች ፡ ባላባት ፡ በኋላ ፡ ለግራኝ ፡ የዞረ ፡ ቀጥሎ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ ላዔ ፡ ገላ ውዴዎስ ፡ የገባ ፡ ይመስላል ። |
| ፻፰ | ጽራግ ፡ ማሠሬ ፡ ተክለ ፡ ሥሉስ | በጦርነት ፡ የሞተ ። |
| ፻፱ | አቤቶ ፡ ቴዎድሮስ ። | በጦርነት ፡ የሞተ ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ። |
| ፻፲ | ማዕቀ ፡ እግዚእ ። | በጦርነት ፡ የሞተ ። |
| ፻፲፩ | አባ ፡ ተንሥአ ፡ ክርስቶስ፡ | ዘቢዘን ፡ መምህር ፡ ዘደብረ ፡ ሰማዕት ። |
| ፻፲፪ | ሚካኤል ። | |
| ፻፲፫ | ዳርጎት ፡ (ደኃር ፡ ኅይታ) ። | በዳሞት ፡ በጋፋት ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ብዙ ፡ ሹማ ምንቶች ፡ ይዞ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻ ፡ የሞተ ። ልጁ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከባሌ ፡ ተማርኮ ፡ የተገደለበት ። |
| ፻፲፬ | ያዕቆብ ። | |
| ፻፲፭ | ጋድ ። | |
| ፻፲፮ | ጌዴዎን ። | የተማረከ ። |
| ፻፲፯ | ዓመተ ፡ ልዑል ። | የሞተች ። |
| ፻፲፰ | ዮዲት ። | የተማረከች ። |
| ፻፲፱ | ቀኝ ፡ ጌታ ፡ ወሰንጌ ። | ዓባይ ፡ ዳር ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ነገደ ፡ ኢየሱስ ጋር ፡ በአብሳማ ፡ ኑር ፡ እጅ ፡ የተገደለ ። |
| ፻፳ | ግራ ፡ ጌታ ፡ ጊዮርጊስ ። | |
| ፻፳፩ | ዕዝራ ። | ውስጥ ፡ ብላቴና ፡ (የእልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡ አለቃ) ፡ ሚናስ ፡ የተማረከለት ፡ በጦርነት ፡ የሞተ ። |
| ፻፳፪ | ስል ፡ ወናግ ። | |
| ፻፳፫ | ዮሴፍ ። | |
| ፻፳፬ | ዓምደ፡ሚካኤል፡(ዓምዱ)። | በዝሆን ፡ ዱር ፡ (ዳሞት) ፡ ጦርነት ፡ ከአቡበ ከር ፡ ቀጢን ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር የገደለው ፡ የሮቤል ፡ ልጅ ፡ ጀግንነቱን ፡ እስላሞች ፡ ያደነቁለት ። |
| ፻፳፭ | ክፍሉ ። | |
| ፻፳፮ | ባሕርይ ፡ ወልደ ፡ ማርታ ። | |
| ፻፳፯ | ዐርባ ፡ ሸማል ፡ (ሺመል)። | በዛ(ዘ)ሚት ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ በወጭበኅ ፡ (ደዋሮ) ከግራኝ ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ ከቪዜር ፡ አዶሌ ፡ በተ ዋጋ ፡ ጊዜ ፡ በኤሚር ፡ ሞጋሂድ ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |
| ፻፳፰ | ዘምቢል ። | የቡሬ ፡ ሹም ፡ በዛሬ ፡ (አይፈርስ) ፡ ጦርነት ፡ ሲዋጋ፡ በአቡበከር ፡ ቀጢን ፡ እጅ ፡ የሞተ ። |
| ፻፳፱ | ሳማኤል ፡ (ሳሙኤል) ። | የሲሬ ፡ (ሺሬ) ፡ ሹም ፡ በዛሬ ፡ (አይፈርስ ፡) ጦርነት ፡ የሞተ ። |

| ተራ ቍ | ስም ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
| --- | --- | --- |
| ፻ | አዝማች ፡ ሃይቢ ። | የጋቱር ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዞሮ ፡ ሰልሞ ፡ በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሬና ፡ ምክር ፡ እየሰጠ ፡ መንገድ ፡ እየመራ ፡ ለግራኝ ፡ በጣም ፡ ያገለገለ ፡ ከዳተኛ ። |
| ፻፩ | አርኪያህ ። | ከአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ሚስቱ ፡ ብትማረክ ፡ ከንጉሡ ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ገብቶ ፡ የሰለመ፤ ሰላይና ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ አዝማች ፡ ተክለ፡ ኢየሱስን ፡ ያስገደለ ። |
| ፻፪ | ዘርጇ ። | የኤል ፡ ማያ ፡ (በዝቋላ ፡ ዙሪያ)፡ ነገድ ፡ ባላባት ፡ ለንጉሡ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግራኝ፡ገብቶ፡ የሰለመ ። |
| ፻፫ | ድል ፡ ሰበር ፡ | የፋኑኤል ፡ ወንድም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ተዋግቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ቃግማ ፡ (ባሌ)፡ ላይ ፡ ከዳተኛው ፡ ሲሙ ፡ የወናግ ፡ ዣን፡ልጅ ፡ የገደለው ። |
| ፻፬ | ሐጋ ፡ (ሐጋህ) ። | በባሌ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ሲዋጋ ፡ ከኖረ፡ በኋላ ፡ ከባሌ ፡ ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ሲሸሽ ፡ ገራድ ፡ ጐሹ ፡ ማርኮ ፡ የገደለው ። |
| ፻፭ | አዛዥ ፡ ዘኪሩህ ፡ (ዘኪሮስ) ። | አዝማች ፡ አዳሉ ፡ በባሌ ፡ ተዋግቶ ፡ የሞተ ለት ፡ ተማርኮ ፡ ከግራኝ ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ የተገደለ። |
| ፻፮ | አዝማች ፡ አሚር ። | የባሕር ፡ አምባ ፡ አዝማች ፡ አምባ ፡ ግሸን ፡ ላይ ፡ ከግራኝ ፡ ሲዋጋ ፡ ዓይኑን ፡ የተመቃ ። |

## ምዕራፍ ፲፫ ።

## የግራኝ ፡ አህመድ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ዝርዝር ፡ ድሉን ፡ ያከናወኑለት ፡ ዋነኞቹ ፡ ምክንያቶች ።

የግራኝን ፡ የወጣትነቱን ፡ ጊዜ ፡ እንደምን ፡ አሳልፎ ፡ እዚህ ፡ እንደደረሰ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ ተገንዝበን ። በአረብ ፡ ፋቂህም ፡ ቢሆን ፡ በሌላውም ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ የግራኝ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኰሴ ፡ መወለድ ፡ ምልክቱ ፡ የለም ። ተራ ፡ ሰው ፡ ስለነበረ ፡ ቤተ ፡ ሰቡም ፡ ዝቅተኛ ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ መካከለኛ ፡ እንጂ ፡ ትልቅ ፡ ስላልነበረ ፡ የናቱ ፡ ስም ፡ ከነታሪኳ ፡ አልተጻፈም ፡ እንጂ ፡ አባቱ ፡ ኢብራሂም ፡ ኤል ፡ ቃዚ ፡ የሚባል ፡ መሆኑ ፡ ተረጋግጧል ። የወጣትነቱን ፡ ጊዜ ፡ በገራድ ፡ አቡን ፡ ቤን ፡ አዴክ ፡ ቤት ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ በፍቅር ፡ ያሳደገው ፡ ጌታው ፡ ገራድ ፡ አቡን ፡ በአቡበክር ሲገደል ፡ የጌታውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ሸፈተና ፡ ከጌታው ፡ ጠላት ፡ ከሱልጣን ፡ አቡ በክር ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጋ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ታርቆ ፡ ሲገባ ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻው ፡ አቡበክርን ፡ ገድሎ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በአልጋው ፡ ወንድሙን ፡ ማስቀመጡ ፡ ባይቀር ፡ ከአቡበከር ፡ ሞት ፡ ወዲህ ፡ የሐረርና ፡ የዙሪያው ፡ ባለ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የአዳል ፡ የሱማሌ ፡ ቢላባቶችም ፡ በውስጥ ፡ ግዛታቸው ፡ ነፃ ፡ ቢመስሉ ፡ በጠቅላላው ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ አሸናፊነትና ፡ ገናንነት ፡ እያደገ ፡ በመሔዱ ፡ ሁሉም ፡ በውስጡ ፡ ሆነው ፡ በርሱ ፡ የበላይ ፡ አዛዥነት ፡ መመራታቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

ዋናው ፡ ሱልጣን ፡ አቡበክር ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ተገነዘብነው ፡ ሲሞትና ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ የገዥነት ፡ ሥልጣኑ ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ እጅ ፡ ሲወሰድ ፡ በርሱ ፡ (አቡበክር ፡) እኳያ ፡ የነበረው ፡ ሱልጣን ፡ አውራይ ፡ አቡን ፡ በግራኝና ፡ በአቡበክር ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ሱማሌ ፡ አገር ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ የግራኝ ፡ አህመድን ፡ አሸናፊነትና ፡ በሥልጣን ፡ መደላደሉን ፡ ሲመለ ለከት ፡ ከሸሸበት ፡ አገር ፡ ከሱማሌ ፡ መጥቶ ፡ ከግራኝ ፡ አህመድ ፡ ጋር ፡ ታርቆ ፡ ገብቶ ፡ አገር ፡ ተቀብሎ ፡ የግራኝ ፡ ታዛዥና ፡ ጭፍራ ፡ ሆነ ። በዘሩ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ እንደሚመለከተው ፡ ይህ ፡ ሱልጣን ፡ አውራይ ፡ አቡን ፡ ባዬ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ በጦርነት ፡ ከተገደለው ፡ ከበድላይ ፡ ሺሃብ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ አህ መድ ፡ (ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ አርዌ ፡ በድላይ ፡ የሚለው ፡) ዘር ፡ በቀጥታ ፡ የወረደ ፡ ነው ፡ ዝርዝሩም ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይመጣል ።

በድላይ ፡ አህመድ ፡ መሐመድ ፡ በድላይን ፡ መሐመድ ፡ በድላይ ፡ ሰላይ ማን ፡ አህመድን ፡ ሰለይማን ፡ አህመድ ፡ ሱልጣን ፡ አትማንን ፡ ሱልጣን ፡ አት ማን ፡ ኤል ፡ አውራይ ፡ አቡንን ፡ ይወልዳል ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱም ፡ ከዋናው ፡ ባላባት ፡ ከወላስማ ፡ የወረዱትን ፡ ሱልጣን ፡ አቡበክርንና ፡ ሱልጣን ፡

አውራይ ፡ አቡንን ፡ አንዱን ፡ በመግደል ፡ ከስወገደ ፤ አንደኛውንም ፡ አሳምኖ ፡ ከስገበረ ፡ ለወደፊቱ ፡ በግራኝ ፡ ፊት ፡ የሚቆም ፡ ኃይለኛ ፡ ባላጋራ ፡ አይገኝም ። የማኅፉዝ ፡ ቤት ፡ እንዳይነግበትም ባዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር ፡ የሞተውን ፡ የማኅፉዝ ፡ መሐመድን ፡ ልጅ ፡ ባቲያ ፡ ድል ፡ ወንበራን ፡ በደንብ ፡ አገባ ። ወንድሟም ፡ ገራድ ፡ አህማዱሽ ፡ በዚሁ ፡ ይዞታ ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ዋና ፡ ጭፍራ ፡ ሆነ ። የዘመኑ ፡ ባላባቶችና ፡ እርሱ ፡ እየመለመለ ፡ ያሰደጋቸው ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ በረከቱ ።

ስለዚህ ፡ በወዲህ ፡ ባዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ በዝርዝር ፡ እንዳመለከትን ፡ የግራኝ ፡ አህመድን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ከታሪክ ፡ ነገሥታችንና ፡ ይልቁንም ፡ ከአራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የለቀምናቸውን ፡ ስምና ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸውን ፡ እንመልከት ። የማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ የግማሾቹ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከወረረ ፡ በኋላ ፡ ግዛት ፡ እየጨመረ ፡ የሰጣቸው ፡ ነው ።

| ተራ ቍ | ስምና ፡ ማዕርግ ። | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፩ | ይማም ፡ አህመድ ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ ኤል ፡ ቃዚ ፡ | እስላሞች ይማም ፡ አህመድ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ (አህመድ) ፡ ይሉታል ፤ የፖርቱጋል ፡ ተወላጅና ፡ ጸሐፊ ፡ ካስታንሆዞ ፡ የዘይላ ፡ ንጉሥ ፡ ይለዋል ፡ ዝርዝር ፡ ሥራው ፡ ከታሪኩ ፡ ይነበባል ። |
| ፪ | ባቲ ፡ ድል ፡ ወንበራ ፡ | የስሙ ፡ ጥሩው ፡ ባላባት ፡ የማኅፉዝ ፡ ልጅ ፡ የግራኝ ፡ ባለቤት ፡ እንደ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ የመሪነት ፡ ጠባይ ፡ ያላት ፡ ኃይለኛ ፡ ሴት ፡ ናት ። |
| ፫ | ሱልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲን ፡ | የአቡበከር ፡ ወንድም ፡ የሐረር ፡ ሱልጣን ። |
| ፬ | ሱልጣን፡አውራይ፡አቡን ፡ | ከመሐመድ ፡ በድላይ ፡ ዘር በቀጥታ ፡ የወረደው ። |
| ፭ | ቪዚር ፡ አዶሌ ፡ | ከገራድ ፡ አቡን፡ቤት ገሥግሮ ፡ ግራኝን፡ያሰደገ ፡ ሞግዚትና ፡ ዋናው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፤ አቃጅነ ፡ ሠራዊ ፡ (የሰራዬ ፡ ሹም) ፡ የሚባለው ፡ ተስፋ ፡ ልዑል ፡ የገደለው ። |
| ፮ | ማታን ፡ ቤን ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ ካሌድ ፡ | የሱማሌዎች ፡ ጠቅላይ፡መሪ፡የግራኝን ፡ እህት ፡ የገባ ፡ አማቹ ፤ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ በደዋሮ ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ በወሲል ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ ግሼን ፡ አምባን ፡ ከበው ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ የተዋጉና ፡ አህሙሹ፡የተማረከለት፡የተገደለ (፲፭፻፳፱፡ዓ፡ም)። |
| ፯ | ቪዚር ፡ ኑር ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ | በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ ከዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር ፡ የተዋጋ ፡ በኋላ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያምን ፡ ዘርፎ ፡ ያቃጠለ ። |
| ፰ | ኤሚር ፡ ዘበርቡይ ፡ መሐመድ ፡ | የግራኝ ፡ የኅት ፡ ልጅ ። |

| ተራ ቍ | ስምና ፡ ማዕርግ ። | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
| --- | --- | --- |
| ፱ | ሃጅራህ ። | የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሚስት ፡ የንጉሡ ፡ ዘመድ ፡ ግራኝ ፡ ከተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ማርኮ ፡ ከአገባት ፡ በኋላ ፡ የወለደላት ፡ በብዙም ፡ ጦርነት ፡ ተከትላ ፡ ትዞር ፡ የነበረች ። |
| ፲ | ሲዲ ፡ አቡበከር ። | የእስላሞች ፡ ሊቅ ፡ በየባንዲራው ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ ጥቅስ ፡ እያጻፈ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ በተሰበሰበበት ፡ መካከል ፡ የማንቀቂያ ፡ ዲስኩር ፡ እየተናገረ ፡ ጦሩን ፡ ለውጊያ ፡ የሚቀሰቅስ ፡ የሚሞቱትን ፡ የሚቆስሉትን ፡ በንግግሩ ፡ የሚያጽናና ። |
| ፲፩ | አህመድ ፡ ጉራይ ፡ ቤን ፡ ሁሴን ፡ ኤዝ ፡ ሶማሌ ። | የሐብር ፡ መጋዲ ፡ ባላባት ፡ (ሱማሌ ።) |
| ፲፪ | ሡልጣን ፡ መሐመድ ። | ከግራኝ ፡ በበቱ ፡ የሚዛመድ ፡ የዘርባ ፡ ባላባት ፡ ሡልጣንነቱ ፡ በመጠሪያ ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ በማዕርግ ፡ አይመስልም ። |
| ፲፫ | ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ኤል ፡ ጋቱሪ ። | በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ኤሚሮች ፡ ይዞ ፡ በደዋሮ ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ፡ ፈረሰኛ ። |
| ፲፬ | ገራድ ፡ አህሙሹ ። | ስመ ፡ ጥር ፡ የፈረሰኞች ፡ አለቃ ፡ በበደቄ ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ በደዋሮ ፡ በአይፈርስ ፡ በብዙ ፡ በታ ፡ ካዴ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር ፡ የተዋጋ ፡ የአምባ ፡ ግሼንን ፡ ተራራ ፡ ከበ ፡ ሲዋጋ ፡ ቢቶደድ ፡ ሠርፄ ፡ የማረከውና ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ የተገደለ ። |
| ፲፭ | ገራድ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ። | የግራኝ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ገነተ ፡ ጊዮርጊስን ፡ አቃጥሎ ፡ የንጉሡን ፡ ሀብት ፡ የዘረፈ ፡ ቀጥሎ ፡ ጋንዝን ፡ የተሾመ ፡ የሐድያን ፡ ባላባት ፡ እህት ፡ በግራኝ ፡ ፈቃድ ፡ ያገባ ። |
| ፲፮ | ሳብር ፡ አድ ፡ ዲን ። | ከክርስቲያኖቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጋር ፡ ጦርነት ፡ ሊጀመር ፡ ሲል ፡ ይልቁንም ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ እልህና ፡ ንዴት ፡ እየያዘው ፡ የሚቅበጠበጥ ፡ ካልተያዘ ፡ በቀር ፡ በስሬያ ፡ እንደ ፡ ሰከረ ፡ ግመል ፡ አእምሮውን ፡ አጥቶ ፡ በፍንጫው ፡ ደም ፡ የሚወርደው ። (አራብ ፡ ፋቂህ ፡ እንደሚለው ።) |

| ተራ ቍ | ስምና ፡ ማዕርግ ። | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፲፯ | ሡልጣን፡ ፈራ ቃሃም፡ አሊ. | የያምሊ ፡ ባላባት ፡ በተጉለት ፡ በወግዳ ፡ በኩል ፡ የዘመቱና ፡ ያሳመኑ ። |
| ፲፰ | ገራድ ፡ ሲዲቅ ፡ቤን፡ አሊ። | የሻር ፡ ቃህ ፡ ገዥ ። |
| ፲፱ | ኤሚር ፡አቡበከር ፡ቀጢን። | ግዕዝኛው ፡ ቀጭን ፡ አቦከር ፡ ይለዋል ። በብዙ ፡ ቦታ ፡ የተዋጋ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ነው ። ከራስ ፡ ደገልሃን ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ምርከኛ ፡ እናቱን ፡ አስመልሿል ። በቃግማ ፡ ከተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡ በባደቄ ፡ ከአሮን ፡ ጋር ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ፡ ከንጉሡ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ተዋግቶአል ። የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳምም ፡ የተቃጠለው ፡ በርሱ ፡ መሪነት ፡ ነው ። |
| ፳ | ሒራቡ ፡ የጎይታ ፡ ቴድሮስ (ቴዎድሮስ፡) ቤን ፡ አዳም፡ልጅ ። | የግራኝ ፡ ጠበኛ ፡ ሆኖ ፡ በውጊያ ከኖረ ፡ በኋላ፡ ግራኝ ፡ መበርታቱን ፡ ዓይቶ ፡ የገባለት ፡ የሚራይሃን ፡ ባላባት ፡ ሚራይሃን ፡ በማጁርቲንና ፡ በውጋዴን ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ አገር ። |
| ፳፩ | ጃሻ ፡ ኡመር ። | |
| ፳፪ | ተክላይ ፡ ቤን ፡ አኩዋ ። | አባቱ ፡ አበሻ ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ገብቶ ፡ በሻር ካህ ፡ ከብህት፡ ወደይ፡ በድላይ ፡ ጦር፡ ጋር ፡ የተዋጋ ። |
| ፳፫ | አህመድ ፡ ዲን ፡ ቤን ፡ ካሌድ ፡ ቤን ፡ ሀርጋያ ፡ መሐመድ ። | |
| ፳፬ | ጀማል ፡ ኤድ ፡ ዲን ፡ (ገማልዲን) ። | በባሌ ፡ የተዋጋ ። |
| ፳፭ | ገራድ ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ ጀውሔር ። | በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ የተዋጋ ፡ በቤተ ፡ አምሐራ ፡ (ወሲል ፡) ንጉሡን ፡ ሊማርክ፡የነበረ፤ በብዙ ፡ ቦታ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ፊቅጦርን ፡ ተዋግቶ ፡ የገደለ፤ በኋላ ፡ በዜ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጊዜ ፡ የሞተ ፡ የጦር ፡ አለቃ ። |
| ፳፮ | ጆሹ ፡ (ጎሹ) ። | አባቱ ፡ በዜ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ውስጥ ፡ በሹመት ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ በወሲል ፡ ለጦርነት ፡ በተሰለፉ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሡ ፡ ሠልፍ ፡ ሮጦ ፡ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ የተደባለቀ ፡ በኋላም ፡ ገራድ ፡ ተብሎ ፡ ደዋሮን ፡ የተሾመና ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያን ፡ የፈጀ ። |

| ተራ ቍ | ስምና ፡ ማዕርግ ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፳፯ | በሽራህ ፡ የጎሹ ፡ ልጅ ። | ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዘር ፡ ያገለገለ ፡ ቤተ ፡ ሰማያት ንና ፡ ደብረ ፡ ነጕድጓድን ፡ ያቃጠለ ፡ በመጨረሻ፡ ዝቋላ ፡ አጠገብ ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። |
| ፳፰ | ኤሚር ፡ ሞጋሂድ ፡ ቤን፡ አሊ፡ቤን፡ አብደላ፡ ሱሃ። | በብዙ ፡ ቦታ ፡ ሲዋጋ ፡ የኖረ ፡ በዋጅ ፡ (ዋግ) እስላም ፡ ደጎርን ፡ የገደለ ፡ እስከ ፡ ሲዳሞ ፡ ደርሶ ፡ ከዚያ ፡ ተመልሶ ፡ በቤጌምድር ፡ እየተ ዋጋ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዘመን ፡ የኖረ ። |
| ፳፱ | ናቅዲያህ ። | በፊት ፡ እስላም ፡ ሆኖ ፡ የግራኝ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የነበረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ዞሮ ፡ ሲዋጋ የሞተ ። |
| ፴ | ሳይድ ፡ ቤን ፡ ሳበን ። | ዘሩ ፡ ዐረብ ፡ ማህራህ ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ ግራኝን ፡ ለመርዳት ፡ መድፍ ፡ ይዘው ፡ ለመ ጡት ፡ ዐረቦች ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ በአይፈርስ ፡ በመ ድፍ ፡ የተዋጋ ። |
| ፴፩ | ኡመር ፡ ቤን ፡ አብደላ። | ገራድ ፡ ኡመር ፡ የሚባል ፡ በታላቅ ፡ ዠግን ነት ፡ ከፖርቱጋሎች ፡ ሲዋጋ ፡ እንደሞተ ፡ ክስ ታንሐዝ ፡ ይጽፋል ። ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፡ መነኵሴ ፡ እድንኳኑ ፡ እተኛበት ፡ ገብቶ ፡ በጬቤ ፡ ወግቶ ፡ ኡመር ፡ የሚባለውን ፡ እንደገደለው ፡ ሲል ፡ ይኸኑ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በኡመር ፡ የሚጠሩ ፡ ሌሎች ፡ እንዳሉ ፡ አይታወቅም ። |
| ፴፪ | አትማን ፡ ቤን፡ አብደላ ። | የሺ.ም ፡ አበት ፡ |
| ፴፫ | አብሳማ ፡ ኑር ። | በብዙ ፡ ቦታ ፡ የተዋጋ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ነው ፤ በዐባይ ፡ ዳር ፡ ንጉሡን ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ሊማርክ ፡ ሲል ፡ ለጥቂት ፡ አመለጡት ። ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ነገደ ፡ ኢየሱስን ፡ የገደለ ፡ እርሱ ፡ ነው ። |
| ፴፬ | ቪዚር ፡ አባስ ። | የግራኝ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ የባሕር ፡ ነጋሽ ነትን ፡ ሹመት ፡ ተቀብሎ ፡ ሲኖር ፡ ተስፋ ፡ ልዑል፡ የሠራዊው ፡ ቪዚር ፡ አዶሌን ፡ የገደለ ፡ ጊዜ፡ አባስ ፡ መልሶ ፡ ተስፋ ፡ ልዑልን ፡ ስለገደለው ፡ ቪዚር ፡ ተባለ ፡ በኋላ ፡ በገላውዴዎስ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ፡ |

| ተራ ቁ. | ስምና ፡ ማዕርግ ፡ | አንዳንድ ፡ ማመልከቻ ። |
|---|---|---|
| ፴፭ | ገራድ፡ሻሙን(ስምዖን)። | ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ስምዖን ፡ የሚለው ፡ በብዙ፡ ቦታ ፡ የተዋጋ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ ዮናኤልን ፡ ያቆሰለ ፡ ግርማን ፡ የወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ያቆሰለ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ የገደለ ፡ በአምሐራ ፡ ከዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ያሸነፈ ። |
| ፴፮ | አሉሽ፡ቤን፡ኤል፡ሖጀን። | |
| ፴፯ | ገራድ ፡ አቢድ ። | ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ የገደለ ። |
| ፴፰ | በለው ፡ አብድ ። | |
| ፴፱ | ካሊድ ፡ ኤል ፡ ዋራድ ። | |
| ፵ | አዩብ ። | |
| ፵፩ | ኤል ፡ አውራያ ፡ ኑር ፡ ቃልጣ ። | |
| ፵፪ | ገራድ ፡ ካሚል ። | እህቱን ፡ ሙኒማን ፡ ያገባ ፡ የግራኝ ፡ አማች ፡ በፈጠጋር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። |
| ፵፫ | አብደል ፡ ካሪም ፡ ቤን ፡ አትማን ። | |
| ፵፬ | ታኪያህ ። | ግራ ፡ እግሩና ፡ ቀኝ ፡ እጁ ፡ በሌብነት ፡ የተቆረጠ ፡ የፈረስ ፡ ጦር ፡ የሆነለት ፡ በጅራፍ ፡ እየመታሁ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ከፈረስ ፡ እጥላለሁ ፡ እያለ ፡ ይፎክር ፡ የነበረ ፡ |
| ፵፭ | ጎይታ ፡ አላህ ፡ መጀን ። | በብዙ ፡ ቦታ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ ገደላ ፡ አጠገብ ሳሪ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ከአዝማች ፡ አዳሉ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ። |
| ፵፮ | ገራድ ፡ አህማዱሽ ። | የድል ፡ ወንበሩ ፡ ወንድም ፡ የማኅፉዝ ፡ ልጅ ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ በአይፈርስ ፡ በወሲል ፡ የተዋጋ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ያምባ ፡ ግሼን ፡ ጦርነት ፡ ለት ፡ ሸሽቶ ፡ ራሱን ፡ ካዳነ ፡ በኋላ ፡ የትግሬን ጦርነት ፡ የተካፈለ ። |
| ፵፯ | ያኪም ፡ (የሐኪም ፡) | በብዙ ፡ ቦታ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻ ፡ በግራኝ ፡ ፈቃድ ፡ ወረባን ፡ ያስገበረ ፡ አክሊል ፡ የሚባለ ውንና ፡ ራስ ፡ ባንያትን ፡ ከወረባ ፡ ያባረረ ። |
| ፵፰ | ገራድ ፡ ቦርሐን ። | |
| ፵፱ | ሲዲ ፡ መሐመድ ። | በአይፈርስ ፡ በሌላም ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ በወገራ ፡ ጦርነት ፡ ከዔ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ ፡ ሚካኤል ፡ ካስታንሆዞ ፡ እንደጻፈው ፡ ሲዲ ፡ መሐመድ ፡ ወይም ፡ አህመድ ፡ ከፖርቱጋሎቹ ፡ ዋና አዝማች ፡ ከክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ሲዋጉ ፡ ሞቷል ። |

ግራኝ ፡ አህመድ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡ ታዛገሮቹ ፡ ሆነው ፡ ከሕንድ ፡
ውቅያኖስ ፡ እስከ ፡ ባሌ ፡ እስከ ፡ ይፋት ፡ ዳርቻ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ጌታ ፡ ሲሆን ፡
የሱማሌ ፡ የአዳል ፡ የኢሳ ፡ ነገድ ፡ ከነባላባቱ ፡ በውስጡ ፡ ሲያብርለት ፡ ወደፊት ፡
ያለው ፡ ዋናው ፡ ጉዳዩ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ማስገበር ፡ ነው ። ይኸን ፡ ምኞ
ቱን ፡ ባጠገቡ ፡ ያለችው ፡ የሚወዳት ፡ ሚስቱ ፡ ባቲ ፡ ድል ፡ ወምበራ ፡ አባቷን ፡
ይማም ፡ ማኅፉዝን ፡ ያስገደሉትን ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ለመበቀል ፡ ትጎተጉ
ተዋለች ። አያት ፡ ቅድመ ፡ አያታቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ወይም ፡ በመኳ
ንንቶቻቸው ፡ ላይ ፡ እየሸፈቱ ፡ በውጊያ ፡ የሞቱት ፡ ተማርከው ፡ የታሠሩት ፡ ሁሉ፡
ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ልጆቻቸው ፡ በግራኝ ፡ ውስጥ ፡ ተሰብስበው ፡ እንበለው ፡ ይላሉ ።
እንደ ፡ ሲዲ ፡ አቡበከር ፡ ያሉት ፡ የቁራን ፡ መምህራን ፡ የመጻሕፍት ፡ ሊቃውንት፡
የክርስቲያኑን ፡ ንጉሥ ፡ ወናግ ፡ ሰገድን ፡ አሸንፎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ ሕዝ
ቡን ፡ ለማስለም ፡ የሚደረገው ፡ ጦርነት ፡ ከአላህ ፡ (እግዚአብሔር) ፡ ና ፡ ከነቢዩ ፡
ከመሐመድ ፡ የተፈቀደ ፡ ቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ ነውና ፡ በርታ ፡ ጽና ፡ እያሉ ፡ በቃልም ፡
በጽሕፈትም ፡ እየሰበኩ ፡ ግራኝን ፡ ከነጦሩ ፡ ከነመኳንንቱ ፡ መንፈሱን ፡ ለውጊያ ፡
ሞሉት ። ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ደግሞ ፡ ከዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወታደር ፡ ጋር፡ጦርነት ፡ በገ
ጠመበት ፡ በ፲፭፻፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ዕድሜው ፡ ፳፩ ፡ ዓመት ፡ ስለሆነ ፡ ይህ፡
ዕድሜ ፡ የወጣትነትና ፡ የእፍላነት ፡ ጊዜ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ዕድሜ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ፡
ጐበዝ ፡ ወጣት ፡ ሞትን ፡ የሚንቅ ፡ መሸነፍን ፡ የማያምን ፡ መንፈሱና ፡ ምኞቱ ፡
በገዥነት ፡ በሥልጣን ፡ የፈላ ፡ ነውና ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ተፈርቶ ፡ ተከብሮ ፡
ያዳልን ፡ የይፋትን ፡ የእስላም ፡ ባላባቶች ፡ ሲያስገብር ፡ የኖረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡
የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ ለመገልበጥ ፡ ድፍረትን ፡ ሰጠው ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ልንመለከተው ፡ የሚገባን ፡ ያዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግልንና ፡
የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ ነው ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ በዓ
ለም ፡ የታወቁትና ፡ የገነኑት ፡ ክርስቲያኑ ፡ የፖርቱጋልና ፡ እስላሙ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት፡
መሆናቸውን ፡ ባለፈው ፡ ገልጸናል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ በምሥራቅ ፡ በታናሽ ፡ እስያ፡
በባሕሩም ፡ በየብሱም ፡ በወደቡም ፡ በግዛትም ፡ በጥቅምም ፡ በንግድና ፡ በሃይማ
ኖትም ፡ እየተዋጉ ፡ ጠላት ፡ ናቸው ። ቱርኮች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርስቲያንነትና ፡ ነፃ ፡
መንግሥትነት ፡ «አበሻን ፡ አትንኩ» ፡ ያለውን ፡ የነቢዩን ፡ የመሐመድ ፡ ቃል ፡ ለማ
ክበር ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ክርስቲያንም ፡ ቢሆን ፡ ከግዛታችን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጳጳስ ፡
የሚቀበል ፡ ከሮማውያንና ፡ ከጠላቶቻችን ፡ ከፖርቱጋሎች ፡ ጋር ፡ የማይጋጠም ፡ የተ
ለየ ፡ የተዋሕዶ ፡ ክርስቲያንነት ፡ ያለው ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ እኛን ፡ በሥል
ጣን ፡ በኃይል ፡ ለመወዳደር ፡ የማይችል ፡ ታናሽ ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ በማለት ፡
ይሁን ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የዳር ፡ ዳሩን ፡ ግዛት ፡ ምጥ
ዋን ፡ አዱሊስን ፡ ዘይላን ፡ እየከረኳኩሙ ፡ መውሰዳቸው ፡ ባይቀር ፡ ጠቅላላውን ፡
ኢትዮጵያን ፡ ሳይነኩ  ችላ ፡ ብለው ፡ በነፃነት ፡ ትተውት ፡ እስካሁን ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

አሁን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መንግሥት ፡ ከጠላታቸው ፡ ከፖርቱጋል ፡ ጋር ፡ መላክተኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ እየተለዋወጠ ፡ ወዳጅነቱን ፡ ሲያጠና ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መመልከት ፡ አልሆነላቸውምና ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ አነሣሥና ፡ ድርጅት ፡ ስለአጋጠማቸው ፡ ለርሱ ፡ የዓረብ ፡ ወታደርና ፡ አዳዲስ ፡ ባዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር ፡ ዘንድ ፡ የማይገኝ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጠበንጃ ፡ መድፍ ፡ ሰጥተው ፡ በቅርብ ፡ ያለው ፡ የግራኝ ፡ የግሉ ፡ የገዥነት ፡ ምኞት ፡ በሩቅ ፡ ካለው ፡ ከቱርኮች ፡ ምኞት ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ በአንድነት ፡ ያዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ መንግሥት ፡ እነሆ ፡ ሲገለባብጠው ፡ ልንመለከት ፡ ነው ።

ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ የተላኩት ፡ አባ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብና ፡ ዶም ፡ ሮደሪክ ፡ ፍራንቼስኮ ፡ አልቫሬዝ ፡ ገና ፡ ሮማና ፡ ሊስቦን ፡ ሳያደርሱ ፡ ግራኝ ፡ የወረራውን ፡ ጉዳይ ፡ አጋመሰ ። ተመልሰውም ፡ መልስ ፡ ሳያመጡ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑን ፡ ዘረጋ ። እንደዚሁ ፡ ወደፊት ፡ በየምዕራፉ ፡ እንደምናገኘው ፡ ይህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ጦሩ ፡ ዓርባ ፡ ክንድ ፡ ጐራዴው ፡ ዓርባ ፡ ክንድ ፡ ሰውነቱ ፡ ኃጋኖ ፡ ጥይት ፡ የትንኝ ፡ ያህል ፡ የማያመው ፡ እየተባለ ፡ እንደተረተ ፡ የሚነገርለት ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተገለጸው ፡ ሁናቴ ፡ እንደረዳው ፡ እንጂ ፡ ሰውነቱ ፡ ከማንም ፡ መከከለኛ ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ የማይበልጥ ፡ ጦሩም ፡ ጐራዴውም ፡ ከነዚያው ፡ ከጓደኞቹ ፡ የማይበልጥ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። ነገር ፡ ግን ፡ እላይ ፡ ከሰጠነው ፡ ሐተታ ፡ በቀር ፡ ወደፊት ፡ በየምዕራፉ ፡ እንደምናነበው ፡ ለግራኝ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ የሰጡት ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያቶች ፡

ሀ—ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከውጊያ ፡ በፊት ፡ ከጦር ፡ አለቆቹ ፡ ምክርና ፡ መላ ፡ እየጠየቀ ፡ መልካሙን ፡ ወገን ፡ መምረጡ ።

ለ—የጠላቱን ፡ ጦር ፡ አጥብቆ ፡ እያሰለለ ፡ እንደመጠኑ ፡ መግጠሙ ።

ሐ—ለፈረሰኛና ፡ ለእግረኛ ፡ ተዋጊ ፡ ጦር ፡ የሚመቸውን ፡ ሥፍራና ፡ ጊዜ ፡ እየለየ ፡ ማጠቁ ።

መ—በምርኮ ፡ ላይ ፡ አለቆች ፡ እንዳይጣሉ ፡ ከምርኮ ፡ የሚገኘው ፡ ሀብት ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ በሙሉ ፡ ተሰብስቦ ፡ አለቆች ፡ ድርሻቸውን ፡ ካነሡ በኋላ ፡ የቀረው ፡ ለጦርነት ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ እንዲውል ፡ ደንበኛ ፡ ሕግ ፡ ማውጣቱ ።

ሠ—ከሚማረኩት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ውስጥ ፡ ጠቃሚነታቸውን ፡ ሲመለከት ፡ ምሕረት ፡ እያደረገ ፡ ከነርሱ ፡ የጠላትን ፡ አሳብና ፡ ድርጅት ፡ በመጠየቅ ፡ እየተቀበለ ፡ እነርሱንም ፡ እየሾመ ፡ ማስደሰቱ ፡ አደገኛነታቸውን ፡ የተመለከተውን ፡ ያለርኅራኄ ፡ መግደሉ ፡ ነው ።

በጠቅላላው ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ እንደሌሎቹ ፡ የክርስቲያኖችና ፡ የእስላሞች ፡ ታላላቅ ፡ መሪዎች ፡ የመሪነት ፡ እውቀትና ፡ ችሎት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ይኸን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ሥፍራ ፡ የያዘውን ፡ የጦርነትና ፡ ያሸናፊነት ፡ ዕድል ፡ ሰጠው ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ አልፌን ፡ ባዔ ፡ ልብን ፡ ድንግልና ፡ በግ
ራኝ ፡ አህመድ ፡ እንደዚሁም ፡ በጦር ፡ አለቆቻቸውና ፡ ሠራዊቶቻቸው ፡ መካከል ፡
በየጊዜው ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነት ፡ ወደፊት ፡ በሚቀጥሉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንመል
ከት ። በየምዕራፉ ፡ እንደተለመደው ፡ ግራኝን ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡
ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ብለን ፡ መጻፋችን ፡ ስሙ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ቤን ፡ ኢብራ
ሂም ፡ ኤል ፡ ቃዚ ፡ (ይማም ፡ አህመድ ፡ የኢብራሂም ፡ ኤል ፡ ቃዚ ፡ ልጅ) ፡ ስለ
ሆነ ፡ ደንበኛ ፡ ስሙን ፡ አህመድን ፡ ባገራችን ፡ ከተለመደው ፡ ግራኝ ፡ ከተባለው ፡
ጋር ፡ አዛምደን ፡ መሆኑን ፡ ላንባቢ ፡ እያስታወስሁ ፡ መሐመድ ፡ ስሙ ፡ እንዳይ
ደለ ፡ አሳስባለሁ ። ቀጥሎም ፡ ዐረብ ፡ ፈቂህ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ግራኝን ፡ ይማም
አህመድ ፡ ሲለው ፡ እኔ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ወናግ ፡
ሰገድ ፡ ወይም ፡ ያበሻ ፡ ሀፄ ፡ የሚለውን ፡ የርሱን ፡ እንዳጻጻፉ ፡ መጻፌ ፡ ሳይቀር ፡
በራሴ ፡ አጻጻፍ ፡ ውስጥ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ማለቴን ፡ እንደዚሁ ፡ ዐረብ ፡
ፋቂህ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ከታሪኩ ፡ ንግግር ፡ ውጭ ፡ የራሱን ፡ ሐተታ ፡ ወይም ፡
ከቁራን ፡ ብዙ ፡ ጥቅስ ፡ ሲጨምር ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነው ፡ በቀር ፡ የቀረው ፡ ትርፍ ፡
ጊዜ ፡ የሚወስድ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክቼ ፡ መዝለሌን ፤ ፪ኛ ፡ በአጻጻፉ ፡ ውስጥ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹን ፡ «አማናውያን-ሃይማኖት ፡ ያላቸው» ፡ ክርስቲያኖቹን ፡
«ኢአማናውያን-ሃይማኖት ፡ የሌላቸው» ፡ ወይም ፡ «በብዙ ፡ አማልክት ፡ የሚያመ
ልኩ» ፡ ይል ፡ የነበረውን ፡ እኔ ፡ እስላሞቹን ፡ እስላሞች ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ክርስ
ቲያኖች ፡ እያልሁ ፡ መጻፌን ፤ ቀጥሎም ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ሹማምንት ፡
አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላላ ፡ ፓትሪክ ፡ የሚላቸው ፡ ይህ ፡ የማዕርግና ፡ የሹመት ፡
ስም ፡ ባገራችን ፡ ስላልተለመደ ፡ አዝማች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሹም ፡ እያልሁ ፡
ከታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ጋር ፡ እያስተያየሁ ፡ መጻፌን ፡ ሳንባቢ ፡ አስገነዝባለሁ ።

በስም ፡ አጠራር ፡ ውስጥ ፡ በቀጥታ ፡ ዐረብኛውን ፡ በለማወቄ ፡ በውቅም ፡
ኖር ፡ በረብኛ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ በጉሮሮና ፡ በላንቃ ፡ የሚነገሩ ፡ ፊደሎች ፡
ባገራችን ፡ ፊደል ፡ ውስጥ ፡ ስለሌሉ ፡ በጀ ፡ በገ ፡ በከ ፡ በቀ ፡ መካከል ፡
ያለው ፡ ደንበኛ ፡ አጠራር ፡ ተጣርቶ ፡ ሊሳከ ፡ አይቻልም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡
በዐረብኛው ፡ ላይ ፡ ወጀራ ፤ ሙጃሂድ ፤ ራስ ፡ ደጃልሃን ፡ . . . . ሲል ፡ በግ
ዕዙ ፡ ወገራ ፡ ሙጋሂድ ፡ (አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሙቃሂድ) ፡ ራስ ፡ ደገልሃን ፡
እያለ ፡ ይቃወሳልና ፡ በግዕዝ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ሊገኝ ፡ የቻለውን ፡ እንደ ፡
ግዕዙ ፡ እየጻፍሁ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ያረብኛውን ፡ አጠራር ፡ በቅንፍ ፡ ውስጥ ፡
እየጨመርሁ ፡ ጽፌያለሁና ፡ አሁን ፡ ወደጦርነቱ ፡ እንለፍ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

### በራስ ፡ ደገልሃንና ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ መከከል ፡ የተደረገው ፡ የመጀመሪያው ፡ ጦርነት ።

እንደ ፡ ሺሃብ ፡ ኤድን ፡ አህመድ ፡ ቤን ፡ አብድል ፡ ቃድር ፡ (በጭሩ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ) ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ በይሰጥም ፡ የግራኝን ፡ ጦርነት ፡ በጭር ፡ በጭሩ፡ የሚናገር ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ ያገራችን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ አለ ። እርሱም፡ የግራኝን ፡ ጦርነት ፡ ሲጀምር ፡ ከመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ። ‹ወእስከዝ ፡ ጊዜ ፡ ኢተከፍለት ፡ ሀገር ፡ ወኢገብአ ፡ ፀር ፡ ዘይመልክ ፡ ባሕቱ ፡ እሉ ፡ ነገሥታት ፡ ይመውዑ ፡ ለብዙኃን ፡ ነገሥታት ፡ በከመ ፡ ሞዐሙ ፡ ሐፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ለ፲ቱ ፡ ነገሥታት ፡ ሰበ ፡ መጽኡ ፡ በ፩ ፡ ግብተ ፡ እንበለ ፡ ያስተጋብእ ፡ ሠራዊቶ ፡ ባሕቱ ፡ ግብአተ ፡ ሀገርነ ፡ በእደ ፡ ፀር ፡ ተወጥነ ፡ በዘመነ ፡ ንጉሥ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወልዱ ፡ ለሐፄ ፡ ናዖድ ፡ ወስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ወናግ ፡ ብሂል ፡ አንበሳ» ። የዚህም ፡ አሳቡና ፡ ትርጓሜው ፡ ከመጀመሪያ ፡ ይልቁንም ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዠምሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሳትከፈልና ፡ ሳትነካ ፡ መኖሯን ፡ አንዳንድ ፡ የይፋት ፡ ያዳል ፡ የሱማሌ ፡ የእስላም ፡ ባላባቶች ፡ (ነገሥታት) ፡ ቢነሡም ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሳይዘጋጅ ፡ አሥሩን ፡ ነገሥታት ፡ አሸንፎ ፡ እንዳስገበራቸው ፡ እነዚሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሰይፈ ፡ አርእድ ፡ ዳዊት ፡ ይስሐቅ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ እስከን ድር ፡ ናዖድ ፡ እያሸነፉ ፡ ይመልሷቸው ፡ እንደነበረ ፡ ይገልጽና ፡ አሁን ፡ አገር ፡ መደፈር ፡ ጠላት ፡ መግባት ፡ የጀመረው ፡ በዒ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ መሆኑን ፡ የር ሳቸውም ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ወናግ ፡ ማለትም ፡ አንበሳ ፡ መሆ ኑን ፡ ይገልጽልናል ።

ከዚህም ፡ አያያዘ ፡ በ፲ ፡ ወ፱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለልብነ ፡ ድንግል ፡ ንጉሥ ፡ ሖረ ፡ ደገልሃን ፡ መልአከ ፡ ኃይሉ ፡ ምድረ ፡ አዳል ፡ ወማኅረከ ፡ ንዋዮም ፡ ወፄወወ ፡ አንስቲያሆሙ ። ወእምዝ ፡ ዴገኖ ፡ ግራኝ ፡ ወሜጠ ፡ ፄዋሁ ፡ ወምህር ከሁ ፡ እያለ ፡ ይቀጥላል ።

ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በግራኝና ፡ በደዋሮው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በፋኑኤል ፡ መከከል ፡ የሆነውን ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ አይገልጽም ። ከዚያ ፡ ወዲህም ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ተሸንፎ ፡ መመለሱን ፤ ፺ ፡ አሚሮችም ፡ እንደተማረኩበት ፡ አያወሳም ። በራስ ፡ ደገልሃንና ፡ በግራኝ ፡ መከከል ፡ የሆነውን ፡ በጭሩ ፡ የተረከው ፡ ግን ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ ከሚተርከው ፡ ጋር ፡ በትክክል ፡ ይጋጠማል ። ልዩነት ፡ ቢኖረውም ፡ ይህኛው ፡ (አራብ ፡ ፋቂህ) ፡ በዝር ዝር ፡ በመግለጥ ፡ ወይም ፡ የወገኑን ፡ አግንኖ ፡ በመናገር ፡ ያኛው ፡ (ታሪከ ፡ ነገሥቱ) ፡ አሳጥሮ ፡ በመናገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በነገሡ ፡ በ፲፮ኛው ፡ ዓመት ፡ ራስ፡ ደገልሃን ፡ የሚባለው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ (መልአከ ፡ ኃይሉ) ፡ ወደአዳል ፡ ሔዶ ፡ ያዳሎቹን ፡ ሚስቶችና ፡ ሀብታቸውን ፡ ማርኮ ፡ ሊመለስ ፡ ሲል ፡ ግራኝ ፡ ከራስ፡ ደገልሃን ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ምርኮውን ፡ እንዳስመለሰ ፡ ያስረዳል ።

ራስ ፡ ደገልሃን ፡ በዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መኳንንትና ፡ የጦር ፡ አለቆች፡ዝር ዝር ፡ ውስጥ ፡ በ፫ኛው ፡ ቁጥር ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል ። ጽሑፉ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ ራስ ፡ ዴገልሃን ፡ ደጋልሃን ፡ ደገልሃን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አዝማች ፡ ዴጋልሃን ፡ ወይም ፡ በጭሩ ፡ ዴገል ፡ ይለዋል ። እስላሞች ፡ ደጀልሃን ፡ ይሉታል ። ግዕዙ ፡ መልአከ፡ ኃይል ፡ ሲለው ፡ በዛሬው ፡ ዘመን፡አጠራር ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ ይኸም ፡ ቢቀር፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ እንደማለት ፡ ነው ። የስሙ ፡ አጠራር ፡ ደገልሃን፡ከሌ ሎቹ ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፡ ከነፋኑኤል ፡ ከነወሰን ፡ ሰገድ፡ከነተ ስፋ ፡ ልዑል ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ ዘሩ ፡ አማራና ፡ ትግሬ ፡ አይመስልም ። ይሁን፡ እንጂ ፡ በዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተከበረና ፡ የተፈራ ፡ የጦር፡ አለቃ ፡ ነው ። ሚስቱ ፡ ያዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እህት ፡ አመተ ፡ ውጥን ፡ ትባላለች ፡ ግዛቱ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ከታወቁት ፡ ከታላላቅ ፡ አውራጃዎች ፡ አንዱ ፡ ባሌ ፡ ነው ።

ታሪክ ፡ ነገሥቱም ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በነገሡ ፡ በ፲፮ኛው ፡ ዓመት፡ ራስ ፡ ደገልሃን ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ሊዋጋ ፡ ሔደ ፡ ስለሚል ፡ ይህ ፡ ዘመን ፡ ፲፭፻ ፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የነገሡት ፡ በተወለዱ ፡ በ፲፩ ፡ ዓመታቸው ፡ በ፲፭፻ ፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለሆነ ፡ በሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ደርሷል ፡ ማለት ፡ ነው ። ግራኝ ፡ ግን ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፳፩ ፡ ዓመቱ ፡ ስለሆነ ፡ በዕድሜ ፡ ከርሳቸው ፡ አሥር ፡ ዓመት ፡ ማነሡን ፡ እንመ ለከታለን ። እንግዴህ ፡ የራስ ፡ ደገልሃንና ፡ የግራኝ ፡ እህመድን ፡ የመዠመሪያ ውን ፡ ጦርነት ፡ መዠመሪያው ፡ በለፈው ፡ ከተመለከትነው ፡ ሌላ ፡ የግዕዝ ፡ ታሪክ፡ ነገሥታችን ፡ የሚለውን ፡ በቀጥታ ፡ እንመልከትና ፡ ቀጥሎ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ የሚለውን ፡ እናነባለን ። ታሪክ ፡ ነገሥታችን የምንለው ፡ በዔ ፡ ሠርፀ ፡ ድን ግል ፡ ወይም ፡ በዔ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ የተጻፈው ፡ ያዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አጭር ፡ ግዕዝኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። እርሱንም ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ ተር ጉሞ ፡ በማኅተም ፡ አሳትሞ ፡ በአውሮፓ ፡ አራብቶታል ፡ ስለዚህ ይኸው ፡ መጽ ሐፍ ፡ ስለመዠመሪያ ፡ የግራኝና ፡ የራስ ፡ ደገልሃን ፡ ጦርነት ፡ በግዕዝ ፡ እንዲህ ይላል ።

«በ፲ ፡ ወ፱ቱ ፡ ዓመት ፡ እመ ፡ እመ ፡ ነግሠ ፡ ፈነዎ ፡ ለደገልሃን ፡ ወአዘዞ፡ ይሑር ፡ ምድረ ፡ አዳል ፡ ወረሰየ ፡ ምስሌሁ ፡ ሠራዊተ ፡ ድኑዓነ ፡ ወኃያላነ ፡ እለ ፡ የአምሩ ፡ ግብረ ፡ ጸብእ ፡ ወተቃትሎ ፡ አስተጋቢኦ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ አህጉረ ፡ መንግሥቱ ፡ በበ ፡ ነገዶሙ ፡ ወበበ ፡ ሕዝቢሆሙ ፡ ወሢመ ፡ ሊቀ ፡ ሠራዊት፡ፀብእ፡

ላዕሌሆሙ ፡ ለእሉ ፤ ሠራዊት ፡ ብዙኃን ፡ ደንገፀት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብእሲት ፡ እስከ ፡ ድኅፀ ፡ ሕፃን ፡ ዘወስተ ፡ ከርሣ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ምድረ ፡ አዳል ፡ ንጉሥ ፡ ለሀገር ፡ ከመ ፡ ነበልባለ ፡ እሳት ፡ ወጼወወ ፡ ዘውስቴታ ፡ ሰብአ ፡ ወእንስሳ ፡ እስከነ ፡ እሙ ፡ ለቀጭን ፡ አቦክር ፡ (አቡበክር) ፡ ዘትሠመይ ፡ ፋጥ ፡ ወሶበ ፡ አብጽሕዋ ፡ ኀበ ፡ ደገልሃን ፡ ትቤ ፡ አ ፡ ምንተ ፡ ይረብሐክሙ ፡ እኂዞተ ፡ ዚአየ ። ናሁኬ ፡ ይከውን ፡ ደኃሪቱ ፡ ለአንድዶ ፡ ወመዊዖትክሙ ፡ ይትመየጥ ፡ መንገለ ፡ ተመውዖ ። እስመ ፡ ወልድየ ፡ ብእሲ ፡ ተባዕ ፡ ወጽኑዕ ፡ ውእቱ ፡ ጥቡዕ፡ልቡ ፡ ለቀቲል ። ወበሊሕ ፡ እገሪሁ ፡ ለክዒወ ፡ ደም ። እመሰ ፡ ኢፈነውክሙኒ ፡ ኢየአርፍ ፡ ወልድየ ፡ እንበለ ፡ ያንግፊኒ ፡ እምእዴክሙ ። ወእንዘ ፡ ዓዲ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ ውስተ ፡ አፉሃ ፡ በጽሐ ፡ ግብተ ፡ ግራኝ ፡ ወወድቀ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ መብረቅ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊተ ፡ ጸብእ ፡ ነትዑ ፡ በበ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ወኢየአምሩ ፡ ኃበ ፡ የሐውሩ ፡ መስተጽእናን ፡ አፍራስኒ ፡ ኃደጉ ፡ አፍራሲሆሙ ። ወመስተጽእናን ፡ አብቅልትኒ ፡ ኀደጉ ፡ አብቅልቲሆሙ ፡ ዘሀሎ ፡ በአፍአ ፡ ኢቦአ ፡ ኀበ ፡ ማኅደሩ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ዘኮነ ፡ ውስተ ፡ ቤት ። ወውስተ ፡ ገዳም ፡ ሀሎ ፡ ኢተመይጠ ፡ ድኅሬሁ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ልብሶ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ኮነ ፡ በምድረ ፡ ክቦት ። እለኒ ፡ እምሠጡ ፡ እምቀትል ፡ በ ፡ ዘሖረ ፡ እንተ ፡ ፍኖተ ፡ ደዋሮ ፤ ወበ ፡ በፍኖተ ፡ ፈጠጋር ፡ ወበ ፡ በፍኖተ ፡ ኢፋት ፡ ወግድም ፡ እስመ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ኮነ ፡ ዘዘዚአሁ ። ዘኮነሰ ፡ ውስተ ፡ ከተማሆሙ ፡ ዘተማኅረከኒ ፡ እምሀገር ፡ ወዘኮነሂ ፡ ሎሙ ፡ እምቀዳሚ ፡ አልቦ ፡ ዘአምሠጠ ፡ እምሰብእ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ኵሉ ፡ ገብአ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለግራኝ ፡ እስከ ፡ እሙ ፡ ለቀጭን ፡ አቦክር ፡ ዘአንገፋ ፡ እምእዴሆሙ ። ወተቀበላ ፡ በዓቢይ ፡ ክብር ። አሚሃ ፡ ኮነ ፡ ፍሥሐ ፡ ወሐሤት ፡ በከተማሁ ፡ ወኮኑ ፡ ይብሉ ፡ ሠራዊተ ፡ እስላም ፡ በበሕዘቢሆሙ ።

ወልድ ፡ መዊዕ ፡ ተንሥአ ፡ ቃውመ ፡ ለሕዝቡ ፡
ወልድ ፡ ኃያል ፡ ሰለበ ፡ ምህርከ ፡ ኃያላን ፡ ዘሄወውዋ ፡ ለሀገሩ ፡
ወልድ ፡ መስተቃትል ፡ ፈደየ ፡ ምክዕቢተ ፡ እምቀታልያን ፡ ሕዝቡ ፡

በብሂለ ፡ ዝንቱ ፡ ኀለዩ ፡ ማኅሌተ ፡ ድርሳን ፡ ዘይትበሃል ፡ ዝከር፡በልሳነ ፡ ብሔሮሙ ።»

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ የግዕዝ ፡ ቃል ፡ የሚለውና ፡ ግዕዝ ፡ ለማያውቁ ፡ አንባቢዎች ፡ በጭሩ ፡ የምናስረዳው፡አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል፡በነገሡ፡በ፲፱ነኛው ፡ ዓመት ፡ ንጉሡ ፡ ከየአገሩ ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ሰብስበው ፡ የበላይ ፡ አዝማች ፡ ራስ ፡ ደገልሃንን ፡ አድርገው ፡ እንዲዘምት ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ መላካቸውን ፤ ሠራዊቱ ፡ በይፋት ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ሲጓዝ ፡ ከብዛቱና ፡ ከጩኸቱ ፡ የተነሣ፡በሆዷ ፡ ያረገዘችው ፡ ሕፃን ፡ ጨንግፎ ፡ እስኪያስወርዳት ፡ ድረስ ፡ ፩ ፡ ሴት ፡ መደንገጧ ፡ ራስ ፡ ደገልሃን ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡ አገሩን ፡ ከበ ፡ አስጨንቆ ፡ ከብቱንም ፡ ሰዉንም ፤ ፋጥ ፡ የምትባለዋን ፡ የቀጭኑ ፡ አቡበከርንም ፡ እናት ፡ ጭምር ፡ መማረኩን ፤ ያቡበከርም ፡ እናት ፡ ተማርካ ፡ እደገልሃን ፡ ፊት ፡ በቀረበች ፡ ጊዜ ፡ እኔን ፡

ብትማርኩ ፡ ምን ፡ ይጠቅማችኋል ፡ ይልቅስ ፡ የኔ ፡ መያዝ ፡ የቃጠሏችሁ ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆናል ፡ አሸናፊነታችሁም ፡ ወደ ፡ መሸነፍ ፡ ይመለሳል ። ልጇ ፡ ዝግና ፡ ለጦር ነት ፡ ልቡ ፡ የጸና ፤ እግሩም ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ የፈጠነ ፡ ነውና ፡ እኔን ፡ ለቃች ሁኝ ፡ ከልሔድሁ ፡ ከእጃችሁ ፡ ሳያድነኝ ፡ ልጇ ፡ ልቡ ፡ አያርፍም ፡ ብላ ፡ ስት ናገር ፡ ግራኝ ፡ በድንገት ፡ እንደመብረቅ ፡ መጥቶ ፡ በላያቸው ፡ ወድቆ ፡ እንደ ተዋጋና ፡ ወቃደሩ ፡ ሁሉ ፡ (ክርስቲያኖቹ) ፡ ፈረሰኛው ፡ ፈረሱን ፡ በቅሎ ኛው ፡ በቅሎውን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ኋላውም ፡ ተመልሶ ፡ ልብሱን ፡ ሳይዝ ፡ ወደ ፡ ቤትም ፡ (ድንኳን) ፡ ገብቶ ፡ ዕቃውን ፡ ሳያነሳ ፡ ግማሹ ፡ በደዋሮ ፡ ግማሹ ፡ በፈጠጋር ፡ የቀረው ፡ በይፋትና ፡ በግድም ፡ መንገድ ፡ መሸሹን ፡ በሥፈር ፡ የተ ገኘው ፡ ሰውም ፡ እንስሳውም ፡ በሙሉ ፡ በግራኝ ፡ እጅ ፡ መውደቁን ፡ የቀጭኑ ፡ አቡበከርን ፡ እናትም ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ እጅ ፡ አድኒት ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ እንደ ተቀበላትና ፡ በከተማቸውም ፡ ውስጥ ፡ የእስላሞቹ ፡ ወቃደሮች ፡ በደስታ ፡ እንደ ዚህ ፡ እያሉ ፡ ግጥም ፡ እየገጠሙ ፡ መዝፈናቸውን ፡ ያስረዳል ።

ድል ፡ አድራጊ ፡ ልጅ ሕዝቡን ፡ ለመከላከል ፡ ተነሣ ።
ኃያል ፡ ልጅ ፡ የተማረኩትን ፡ ያገሩን ፡ ኃያላን ፡ አስመለሰ ፡ (አስጣለ) ።
ተጋዳይ ፡ ልጅ ፡ የሕዝቡን ፡ ገዳዮች ፡ በእጥፍ ፡ ተበቀላቸው ።

ዋናው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የዘለለውንና ፡ በጭሩ ፡ አመዝመራያው ፡ ላይ ፡ የገለጸውን ፡ ይህኛው ፡ ያዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አጭር ፡ የግዕዝ ፡ ታሪክ ፡ ሰፋ ፡ አድርጎ ፡ እነሆ ፡ አሳይቶናል ። ይኸም ፡ የግዕዝ ፡ ታሪክ ፡ ሺሃብ ፡ ኤድ ፡ ዲን ፡ አህመድ ፡ (አረብ ፡ ፋቂህ) ፡ ከጻፈው ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ ከተረጎሙት ፡ ጋር ፡ ይስማማል ። ስለዚህ ፡ ለአንባቢ ፡ ታሪኩ ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ በበኩሉ ፡ አረብ ፡ ፋቂህ ፡ የሚለውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንመልከት ።

«ጀሬ ፡ የሚባል ፡ የሱማሌ ፡ ነገድ ፡ ሜራይሃን ፡ ከሚባሉ ፡ ከጎረቤቱ ፡ ከሱማሌ ፡ ነገድ ፡ ጋር ፡ ተጣልተው ፡ ሳለ ፡ እነርሱን ፡ ከስታረቀ ፡ በኋላ ፡ (አህመድ ፡ ) ለርሱም ፡ አልገዛም ፡ ያሉትን ፡ እየወጋ ፡ ከስገበረ ፡ በኋላ ፡ ደገልሃን ፡ የሚባል ፡ የንጉሥ ፡ አማች ፡ ከታላላቆች ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አንዱ ፡ በውስጡ ፡ ሌሎች ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ እስላሞች ፡ አገር ፡ ጠረፍ ፡ መጥቶ ፡ አገር ፡ መዝረፉን ፡ ሀብ ታቸውንና ፡ ሴቶቻቸውን ፡ ሀሉ ፡ በምርኮ ፡ መውሰዱን ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ሰማ ። ከምርኮኞቹም ፡ መካከል ፡ ከኤሚሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የአቡበከር ፡ ቀጢን ፡ እናት ፡ ነበረች ። ጠላት ፡ ከ፺፻ ፡ የበለጠ ፡ የፈረሰኛ ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ የበረከተ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ነበረው ። ይማም ፡ አህመድ ፡ እነሱን ፡ ሊወጋ ፡ ተዘጋጀ ። የእ ስላሞች ፡ ጦር ፡ ፫፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ነበር ።

ይማም ፡ ፈረሰኞቹን ፡ ወደፊት ፡ ላካቸው ። እነርሱም ፡ የማታ ፡ ጸሎት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ተነሥተው ፡ በማግስቱ ፡ ዝምበር ፡ ስትጠልቅ ፡ አከም ፡ ከሚ ባል ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ደረሱ ። ይማም ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ለማሰለል ፡ ሰው ፡ ልኮ፡

ነበር ። ምንም ፡ ወሬ ፡ ሊያመጣላት ፡ የቻለ ፡ የለም ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሴን ፡
ኢል ፡ ጋቱር ፡ የሚባለውን ፡ ኤሚር ፡ (የጦር ፡ አለቃ) ፡ ከሰባት ፡ ፈረሰኞች ፡ ጋር ፡
ላከው ፡ እርሱም ፡ ወደጠላት ፡ ሠፈር ፡ ተጠግቶ ፡ ብዙ ፡ መሆናቸውን ፡ ሰልሎ ፡
ተመልሶ ፡ ለይማም ፡ አህመድ ፡ ነገረው ። ይማም ፡ አህመድ ፡ ከነጦሩ ፡ ወደጠላት ፡
ተጠጋ ፡ በርሱና ፡ በጠላቶቹ ፡ መካከል ፡ የሚያስፈራ ፡ ድንጋያማ ፡ ተራራ ፡ ነበ
ርና ፡ ይማም ፡ ራሱ ፡ ከአራት ፡ ፈረሰኞች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡
ከርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ፈረሰኞች ፡ ቪዚር ፡ አዶሌ ፤ ኤሚር ፡ ባራዳ ፤
ኤሚር ፡ አሊ ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡ እተራራው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ቍልቍል ፡ ኤዱር ፡
(ይፋት?) ፡ ላይ ፡ የሰፈሩትን ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ተመለከትዋቸው ። ከዚያ ፡ ይማም ፡
ወደ ፡ ጦሩ ፡ ተመልሶ ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ለጦርነት ፡ ሲዘጋጅ ፡ አደረ ። በማግስቱ ፡
የጠላት ፡ ጦር ፡ ከለበት ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ለመመለስ ፡ ሲጓዝ ፡ ይማም ፡
አህመድ ፡ ከኋላ ፡ ይከተለው ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ተከታትለው ፡ ሲሔዱ ፡ ከጠ
ላት ፡ ወገኖች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እስላሞቹን ፡ ሲከተሉአቸው ፡ አዩና ፡ ለወገኖ
ቻቸው ፡ ነገሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ ለጦርነት ፡ ተደ
ራጅተው ፡ ይጠብቁ ፡ ዠመር ። ይማም ፡ አህመድም ፡ በማህል ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡
የሚዘምተውን ፡ ጦሩን ፡ አሰለፈና ፡ ወደፊት ፡ ተጓዘ ። በመዠመሪያ ፡ በጠላት ፡
ላይ ፡ ገሥግሦ ፡ ገብቶ ፡ ጦርነቱን ፡ የዠመረው ፡ ፋራቃሃም ፡ ሡልጣን ፡ ነው ።
እርሱም ፡ ዠግና ፡ የፈረሰኛ ፡ ተዋጊ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ «አላህ ፡ ታላቅ ፡ ነው» ፡
ብሎ ፡ ጮኸ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ገብቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ወገኖቹም ፡ ገብተው ፡ ጦርነቱን ፡
ዠመሩ ። ሡልጣን ፡ ፋራቃሃም ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ ገድሎ ፡ የጦር ፡ አለቃውን ፡
የተክላን ፡ ልጅ ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ሰበሩን ፡ ማረከውና ፡ ለይማም ፡ አስረከ
በው ፡ ይማምም ፡ ወደ ፡ ዐረብ ፡ አገር ፡ ላከው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፈረሰኛው ፡
ከፈረሰኛ ፡ እግረኛው ፡ ከእግረኛ ፡ ዠግናው ፡ ከዠግና ፡ ተደባልቆ ፡ ሲዋጋ ፡ ብዙ
ጭንቅላቶች ፡ ከሰውነት ፡ ላይ ፡ እየተቆረጡ ፡ ሲወድቁ ፡ ብዙ ፡ ክንዶች ፡ በአየር ፡
ላይ ፡ ሲበሩ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። እስላሞቹ ፡ ሲጯጯሁ ፡ ................
መሬት ፡ ከነርሱ ፡ በታች ፡ ትንቀጠቀጥ ፡ ነበር ............ በመጨረሻ ፡ ኢአማ
ኖውያኑ ፡ (ክርስቲያኖቹ) ፡ ተበታትነው ፡ ሸሹ ። ብዙ ፡ ሺህ ፡ የሚቆጠር ፡ ሰው ፡
በዚህ ፡ ጦርነት ፡ አለቀ ። የኛዎቹ ፡ ፈረሱንም ፡ በቅሎውንም ፡ ሁሉንም ፡ ማረኩ ፡
፩፻፹፩ ፡ ሰው ፡ ማረኩ ። ቀድሞ ፡ በምርኮ ፡ የተወሰደውንም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አስ
መልሰው ፡ ለየባለቤቶቻቸው ፡ አስረከቡ ። ከኛ ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ አልሞተም ።
አንዳንድ ፡ የቆሰሉትም ፡ በቀላል ፡ ዳኑ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ምርኮኞቹን ፡
አራቱ ፡ አስመጥቶ ፡ ግማሾቹን ፡ ለኤሚር ሰለይማን ፡ ወደ ፡ ዘቢድ ፡ ላካቸውና ፡
ለርሱ ፡ ባሮች ፡ ሆኑ ፡ ግማሾቹንም ፡ ገደላቸው ..................... እንደዚህ ፡
አድርጎ ፡ ይማም ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ በደስታ ፡ በክብር ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡
ሐረር ፡ ተመለሰ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ፳፩ · ዓመት ፡ ሆኖት ፡ ነበር ። »

ከፋትኤል ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ በ፲፭፻፳፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ግራኝ ፡ ከራስ ፡ ደገልሃን፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ጦርነት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይፈጸማል ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ ታሪከ፡ ነገሥት ፡ ባጭሩ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ በዝርዝር ፡ የሰጠው ፡ አተራረክ ፡ ይስማማል ። አራብ ፡ ፋቂህ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ ዘሩ ፡ ዐረብ ፡ ሃይማኖቱ ፡ እስላም ፡ እን ደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የጦርነቱን ፡ አኳኋን ፡ የግራኝን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ዠግን ነት ፡ እያገነነ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ እያሳነሰ ፡ በጽሑፉ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል ። ይልቁንም ፡ እግረኛው ፡ ከእግረኛው ፡ ፈረሰኛው ፡ ከፈረሰኛው ፡ ተደባልቆ ፡ ሲዋጋ ፡ ያለቀው ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ መቆጠሩን ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ መልሶ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ወገን ፡ ከመቍሰል ፡ በቀር ፡ የሞተ ፡ የለም ፡ ሲል ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ ወይም፡ እውነቱን ፡ ለመሠወር ፡ የሞከረ ፡ ይመስላል ።

ከምርኮኞቹ ፡ ውስጥ ፡ ግማሾቹን ፡ ገድሎ ፡ ግማሾቹን ፡ ለዘቢዱ ፡ አገረ ገዥ ፡ ለኤሚር ፡ ሰለይማን ፡ መላኩ ፤ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ቱርኮች ፡ ግብ ጾች ፡ ዐረቦች ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ከግራኝ ፡ አህመድ ፡ ጋር ፡ መተባበራቸውን፡ በግልጽ ፡ ያሳያል ። ዘቢድ ፡ በየመን ፡ ውስጥ ፡ ከሞካ ፡ ከሰናዓ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚገኝ ፡ የዐረቦች ፡ ከተማ ፡ ናት ። ግብጽ ፡ በማሚሉኮች ፡ በምትገዛበት ፡ ጊዜ ፡ የመጨረሻው ፡ ሡልጣን ፡ ማሚሉክ ፡ ከንሱኤል ፡ ጉሪ ፡ ሰለይማን ፡ ራይ ስን ፡ ልክ አስገብሯት ፡ ይኖር ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የግብፅ ፡ ማሚሉክ ፡ በቱርኮች ፡ ኃይል ፡ ሲወድቅ ፡ ሰለይማን ፡ ከግዛቱ ፡ ከዘቢድ ፡ ጋር ፡ በውስጥ ፡ አገሩ ፡ በራሱ ፡ እየተዳደረ ፡ ለቱርኮች ፡ አምኖ ፡ የገባና ፡ እየገበረ ፡ የተቀመጠ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዘቢድ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የታወቀች ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ናት ፤ ሡልጣኑም ፡ የከበረ ፡ ነው ። ያዜ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ሚናስም ፡ ተማርኮ የተላከው ፡ ወደ ዘቢድ ፡ መሆኑን ፡ ወደፊት ፡ እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

### በግራኝና ፡ በኤሚሮቹ ፡ መከከል ፡ ጦርነቱን ፡ የመተውና ፡ የመቀጠል ፡ ምክር ፡ —ከአርባ ፡ ሻማል ፡ (ሺመል ፡) ና ከወናግ ፡ ዠን ፡ ጋር ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ፡ —ስለድል ፡ ወምበራ ።

ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከራስ ፡ ደገልሃን ፡ ከመዋጋቱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከሱማሌ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ እንደገጠመው ፡ ዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገ ልጻል ። „ይማም ፡ አህመድ ፡ ወደ ፡ ሀበሻ ፡ አገር ፡ ለውጊያ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ሂራብ ፡ የሚባለው ፡ ሱማሌዎቹን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ለመምጣት ፡ መን ገድ ፡ ዠምሮ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የይማምን ፡ ወደ ፡ አበሻ ፡ አገር ፡ መዝመት ፡ ሲሰማ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ገባ ። ከሱማሌዎቹም ፡ ውስጥ ፡ ሀብር ፡ የሚባለው ነገድ ለይማም ፡ ግብር ፡ ከልክሎ ፡ መንገድም ፡ እየቆረጠ ፡ አገርም ፡

እየዘረፈ ፡ አስቸግሮ ፡ ነበር ። ይማም ፡ አህመድ ፡ ወደ ፡ ነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ አገራቸውን ፡ እየመቻ ፡ እነርሱንም ፡ ለባሕር ፡ የአንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ እስኪ ቀረው ፡ ድረስ ፡ አብርሮ ፡ ተመለሰ ። . . . . በኋላ ፡ ግን ፡ ሱማሌዎች ፡ ሁሉ ፡ ሂራቡን ፡ ባላባታቸውን ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ለግራኝ ፡ ገቡና ፡ እርቅና ፡ ሰላም ፡ ሆነ„ ።

በለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ አከም ፡ ላይ ፡ ከተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ አረብ ፡ ፋቂህ ፡ የራስ ደገልሃንን ፡ ሁኔታ ፡ አይገልጽም ። ነገር ፡ ግን፡ወደፊት ፡ ባሉት ፡ ጦር ነቶች ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ራስ ፡ ደገልሃን ፡ ከንጉሡ ፡ ከአጼ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጋር ፡ ስለነበረ ፡ ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ ሠራዊቱ ፡ ሲሸነፍበት ፡ ርሱ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መሄዱን ፡ ያስረዳል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሁንም ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ራስ ፡ ደገልሃንን ፡ ማሸነፍና ፡ ቀድሞ ፡ የተወሰደበትን ፡ ምርኮ ፡ ማስመለስ ፡ በቂው ፡ አልሆነም ። ስለዚህ ፡ እንደገና ፡ ከገሩ ፡ ከሐረር ፡ የበረከተ ፡ የእግረኛና ፡ የፈረ ሰኛ ፡ ጦር ፡ አስከትቶ ፡ ወደ ፡ ፈጠጋር ፡ በተለይ ፡ ዋዲህ–መሸከ ፡ ወደሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ መጣ ። ፈጠጋር ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ አንባቢ ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ እንደሚመለከተው ፡ ከደዋሮ ፡ (ሐረርና ፡ ዙሪያው ፡) ከባሌ ፡ በስተምዕራብ ፡ ያለው ፡ ከዛሬው ፡ ቡልጋና ፡ ምንጃር ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ አሩሲ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ የዛሬው ፡ የናዝሬት ፡ ግዛት ፡ የሚባለውን ፡ ግድም ፡ ይመስላል ። አሩሲም ፡ እራሱ ፡ በዚ ያን ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ በፈጠጋር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። ስለዚህ ፡ ዐራብ ፡ ፋቂህ ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት ። «ይማም ፡ አህመድ ፡ ፈጠጋር ፡ መጥቶ ፡ ዋድሁ፡ መስክ ፡ ሰፈረ ፡ እርሱና ፡ ያበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ባለበት፡ መከከል ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ተግማሽ ፡ የግር ፡ መንገድ ፡ ይሆናል ። እዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ሳሉ ፡ በእስላሞቹ ፡ መከ ከል ፡ ምክር ፡ ተደረገ ። በምክሩ ፡ ውስጥ ፡ ይማም ፡ አህመድና ፡ ግማሾቹ ፡ ኤሚሮች ፡ ለኛ ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ መዝረፍ ፡ ወይም ፡ ራሳችንን ፡ ለሞት ፡ ሰውተን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ማግኘት ፡ አሳባችን ፡ ከነዚህ ፡ ከሁ ለት ፡ አንዳቸው ፡ ስለሆነ ፡ በግሥጋሤ ፡ ሄደን ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ እንውደቅበትና ፡ እንውጋው ፡ አሉ ። አብዛኛው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ግን ፡ ይብቃን ፡ ወደአገራችን ፡ እንመለስ ፡ እስላሞች ፡ በብዙ ፡ ምርኮ ፡ ከብረዋል ፡ አሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ወታደሩ ፡ እንመለስ ፡ በማለቱ ፡ አዝኖ ፡ ዓይኑ ፡ እስኪቀላ ፡ ድረስ ፡ አለቀሰ ። ከዚያ ፡ ተመልሶ ፡ ወደሐረር ፡ ሄደ ፡

በሐረር ፡ ትንሽ ፡ ጊዜ ፡ እንደተቀመጠ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ለኤሚር ፡ ማን ሡር ፡ ቤን ፡ ማኅፉዝ ፡ ኤል ፡ ጋቲሪ ፡ መቶ ፡ የፈረሰኛ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ የግረኛ ፡ ጦር ፡ ከባንዲራ ፡ ጋር ፡ ሰጥቶ ፡ ወደአበሻ ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ከይጌ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ እንዲዋጋ ፡ ላከው ። ርሱም ፡ ወደዚሁ ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ የሚቋቋመው ፡ ጦር ፡ ሳያገኝ ፡ ብዙ ፡ ባሮችና ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ ዘርፎ ፡ ወደአገሩ ፡ ተመለሰ ። እንደ ዚሁም ፡ ሌላ ፡ ባንዲራ ፡ ለቪዚር ፡ አዶሌ ፡ ሰጥቶ ፡ አምስት ፡ መቶ የፈረሰኛ ፡ ሺ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ጨምሮ ፡ እስከ ፡ ደዋሮ ፡ በተለይ ፡ ወንበሪያ ፡ (ወምበራ?)

ድረስ ፡ ዘልቆ ፡ እንዲዋጋ ፡ አዘዘው ። ርሱም ፡ ወደዚሁ ፡ አገር ፡ ከማንም ፡ ሳይ ዋጋ ፡ ደርሶ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ማርኮ ፡ ሲመለስ ፡ የደዋሮ ፡ ሰዎች ፡ ፈረሰኛዉም ፡ እግረኛውም ፡ ከኋላ ፡ ተከታትለው ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙትና ፡ ፈረሰኛው ፡ ከፈረሰኛ ጀግናው ፡ ከጀግና ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ ይዋጋ ፡ ጀመር ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ አለቃ ፡ አርባ ፡ ሻማል ፡ (፩ ፡) የሚባል ፡ ረጅም ፡ ሰው ፡ ነው ። ጦርነቱ ፡ ተገምግሞ ፡ የጦር መሣሪያ ፡ እስኪሰባበር ፡ ክንድ ፡ እስኪዝል ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ኤሚር ፡ ሙጃሂድ ፡ የሚባል ፡ (የአሊ ፡ ቤን ፡ አብደላ ፡ ሲሃ ፡ ልጅ ፡) . . . . የጦር ፡ አዝማች ፡ አርባ ፡ ሻማልን ፡ በኃይል ፡ መታና ፡ አመሬት ፡ ጣለው ፡ እንደዚሁም ፡ ኑር ፡ የሚባለው ፡ ሌላውን ፡ ሲገድል ፡ ትልቅ ፡ ውጊያ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ክርስቲ ያኖቹ ፡ ሸሹ ። ቪዚር ፡ አዶሌም ፡ ምርኮውን ፡ ይዞ ፡ ወደሐረር ፡ በደስታ ፡ ተመ ለሰ ፡ . . . . . ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ሌላ ፡ የጦር ፡ ዝግጅት ፡ አደ ርጎ ፡ ሲጨርስ ፡ ለሁሴን ፡ ኤል ፡ ጋቱሪ ፡ ቀይ ፡ ባንዲራና ፡ መቶ ፡ ፈረሰኛ ፡ . . . ለቪዚር ፡ ኑር ፡ (የኢብራሂም ፡ ልጅ ፡) ነጭ ፡ ባንዲራ ፡ ሰጠው ። የራሱ ፡ የይ ማም ፡ አህመድ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ባንዲራው ፡ ብጫ ፡ ነበር ። በእርሱም ፡ ዙሪያ ፡ ከጐበዛዝት ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑት ፡ በጦርና ፡ በሰይፍ ፡ የመዋጋት ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ፈረሰኛ ፡ ወታደሮች ፡ ነበሩት ። የእግረኛው ፡ ጦር ፡ ሰባት ፡ ሺ ፡ ስለሆነ ፡ አምስት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ አንዱን ፡ ለናቅድያህ ፡ በኋላ ወደክርስቲያኖች ፡ ለዞረውና ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ለሞተው ፡ ሁለተኛውን ፡ ለአ ብደል ፡ ከሪም ፡ ቤን ፡ አትማን ፡ በኋላ ፡ ደዋሮ ፡ ተብሎ ፡ ለተሰየመው ፡ ሦስተ ኛውን ፡ ለኡመር ፡ አብደላ ፡ አራተኛውን ፡ ለአትማን ፡ ቤን ፡ አብደላ ፡ አምስተ ኛውን ፡ ለመሀመድ ፡ ሰጣቸው ፡ እነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ በውጊያ ፡ ጊዜ ፡ ዡርባቸ ውን ፡ ለጠላት ፡ እንዳይመልሱ ፡ አደራ ፡ አላቸው ፡ . . . . እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ጉዞው ፡ ተገምግሞ ፡ እስከ ፡ ዘሚርዲን ፡ (ስመርማ ፡ ? የግዕዙ ፡) ድረስ ፡ ዘለቁ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ምክር ፡ ተደረገ ። ሁሉም ፡ ደዋሮን ፡ እንዝመትበት ፡ ብሎ ፡ ተስማማ ። . . . . . እስከ ፡ ከሃልበሪ ፡ ድረስ ፡ ግማሹ ፡ ጦር ፡ ዘለቀ ፡ አጠቢብ ፡ መንገድም ፡ ላይ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ተዋግተው ፡ አሸነፉ ። አንዲት ፡ ዛሁራቅ ፡ የምትባል ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩዋትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቃ ጥለው ፡ ተመለሱ ። በዚህ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ጦር ፡ በቁብ ፡ (ቆቦ ?) ተሰብስቦ ፡ ነበር ቁብ ፡ የሚገኘውም ፡ በክርስቲያኖቹና ፡ በእስላሞቹ ፡ አገር ፡ መከከል ፡ ነበር ። እዚህ አገር ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ እስላሞቹ ፡ ምክር ፡ አደረገው ፡ ግማሾቹ ፡ ክርስቲያኖ ቹን ፡ እንውጋ ፡ ሲሉ ፡ የቀሩት ፡ ወደአገራችን ፡ እንመለስ ፡ አሉ ። ሌሊቱን ፡ እን ዳንዶቹ ፡ አምልጠው ፡ ሲሄዱ ፡ ይማም ፡ በፈረስ ፡ ተከታትሎ ፡ በግድ ፡ መለሳቸው ።

ቁብ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ተሰብስበው ፡ ሚስትህ ፡ ድል ፡ ወንበራ ፡ ወደእስላም ፡ አገር ፡ (ሐረር ፡) ካልተመለሰች ፡ ወደሀበሻ ፡ አገር ፡ አንዘምትም ። ከንተ በፊት ፡ የቀደሙት ፡ ኤሚሮች ፡ አንዱም ፡ ሚስቱን ፡ አስከትሎ ፡ አያውቅም ፡

(፩) ፡ ከቁመቱ ፡ ርዝማኔ ፡ የትነሣ ፡ አርባ ፡ ሺማል ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ስቱ ፡ ከድል ፡ ወምበሩ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ውስ
ጡን ፡ ተመለከቱ ፤ ሀብት ፡ በውስጡ ፡ አልተገኘበትምና ፡ ወዲያው ፡ አቃጥለው ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያኒን ፡ አፈረሱዋት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከአዶሌ ፡ ዘንድ ፡ መላክተኛ ፡
መጥቶ ፡ የቪዚር ፡ አዶሌን ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ የወናግ ፡ ዣንን ፡ መሞት ፡ ተናገረና ፡
በእስላሞች ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። ደስታቸውንም ፡ በከበሮና ፡ በቲምባል ፡
(ነጋሪት) ፡ ገለጹ ። ከዚያ ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ የዘመተው ፡ ቪዚር ፡ ኑርም ፡ ቪዚር ፡ አዶ
ሌም ፡ አንጾኪያ ፡ (ደፋት) ፡ ገብተው ፡ ከይማም ፡ ተገናኙ ፡ . . . . . ። ከዚያ ፡
ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ ከአንጾኪያ ፡ ወደ ፡ ግንደበሎ ፡ በኤሚር ፡ አህሙሽ ፡ እየተ
መራ ፡ ጉዞ ፡ ዠመረ ፡ መንገዱ ፡ ጠባብ ፡ ስለነበረ ፡ ለጉዞ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡
ነበር ፡ . . . . . ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሚስቱ ፡ ድል ፡ ወምበሩ ፡ በሰው ፡ ትከሻ ፡ ስት
ጓዝ ፡ ዋለች ፡ ሲመሽ ፡ ሚት ፡ በብዙ ፡ ከሚገኝበት ፡ ዳክ ፡ ከሚባል ፡ ሥፍራ ፡ ሠፈር ፡
ሆነ ። . . . . . ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ በጉዞ ፡ ደክሞ ፡ ስለነበረ ፡ ራቱን ፡ ሳይበላ ፡ ጦሙን ፡
አደረ ። በማግስቱ ፡ በባዝመሌ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ግንደበሎ ፡
ከሚባለው ፡ ከአበሾች ፡ አገር ፡ ገቡ ። በዚህ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ እስላሞችም ፡
ሞልተውበት ፡ ነበርና ፡ ለአበሻ ፡ ንጉሥ ፡ እየገበሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አሁን ፡
ግን ሸኩና ፡ መንደረተኛው ፡ ሁሉ ፡ ነጋዴውም ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጥተው ፡
አክብረው ፡ ተገናኙት ፡ ፳ ወቄት ፡ ወርቅም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ሰጡት ። በዚህ፡
ጊዜ ፡ ይማም ፡ ደሀ ፡ ነበር ፡ ሹማምንቱ ፡ እነሑሴን ፡ ኤል ፡ ጋቲሪ ፡ ቪዚር፡
አዶሌ ፡ ከዚህ ፡ ወርቅ ፡ ላይ ፡ አንሥተው ፡ ለባለቤቱ ፡ ለድል ፡ ወምበሩ ፡
ለመስጠት ፡ ቢሞክሩ ፡ ይማም ፡ ይህ ፡ ወርቅ ፡ በሙሉ ፡ ለዚህ ፡ ለምናደር
ገው ፡ ቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ እስላምን ፡ ለመርዳት ፡ ወጭ ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ እንጂ፡
ለርዷ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ከለከለ ፡ አጥብቀውም ፡ ቢለምኑትም ፡
አልተበገረም ። . . . . . . . ወርቁንም ፡ ወደ ፡ ሸሪፍ ፡ መሐመድ ፡ ኤቅ ፡ ሻቲሪ፡
ልኮ ፡ መቶ ፡ ሰይፍ ፡ አስገዛ ፡ በዚያም ፡ እስላሞቹ ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡
(ወደፊት ፡ የሚገኘው) ፡ ጦርነት ፡ እስላምን ፡ በመርዳት መሰከሩበት ።

ይማም ፡ ግንደበሎ ፡ ሳለ ፡ የንጉሡን ፡ ሀብት ፡ የያዙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አግኝቶ ፡
እነርሱን ፡ እከተማው ፡ ውስጥ ፡ ገድሎ ፡ ሀብታቸውን ፡ ከብታቸውን ፡ ቀማ ፡ ከዚያ ፡
ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የንጉሡን ፡ ሀብት ፡ እንደያዘ ፡ ወደ ፡ እስላሞች ፡ አገር ፡ ተመ
ልሶ ፡ አዋሽ ፡ ደረሰ ። ከዚያ ፡ በብዙ ፡ ችግር ፡ ወሀ ፡ በማይገኝበት ፡ በረሀ ፡ አድርጎ ፡ . . .
. . . . . . በመጨረሻ ፡ ሐረር ፡ ገባ ፡ በዚያም ፡ የምርኮ ፡ ክፍያ ፡ ሆኖ ፡ አም
ስተኛውን ፡ ዕጣ ፡ሲያነሣ ፡ ለርሱ ፡ ፳፻ ፡ ባርያ ፡ ሺ ፡ ከብት ፡ ደረሰው ።>

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ሂራቡና ፡ ሐብር ፡ የሚባሉ ፡ የሱማሌ ፡ ባላበ
ቶች ፡ በግራኝ ፡ ላይ ፡ ሸፍተውበት ፡ እንደነበረ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ በፌጠ
ጋር ፡ ሳሉ ፡ በምክር ፡ ላይ ፡ አብዛኛው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ይብቃን ፡ ወዳ
ገራችን ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ እንመለስ ፡ ሲሉ ፡ ጦርነት ፡ የጣመው ፡ ግራኝ ፡ በዚሁ
ዓይኖቹ ፡ እስኪቀሉ ፡ ማልቀሱን ፡ ከዚያ ፡ ከፈጠጋር ፡ ወደደዋሮ ፡ ተላል

ፈው ፡ ግማሾቹ ፡ ከአርባ ፡ ሺመል ፡ ግማሹ ፡ ጦር ፡ ወደይፋት ፡ ተዛውሮ ፡ ከወናግ ፡ ዣን ፡ (የንጉሥ ፡ አንበሳ) ፡ ጋር ፡ ተዋግተው ፡ ማሸነፋቸውን ፡ እንመለከታለን ።

በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ሴት ፡ ወደጦርነት ፡ አትሄድምና ፡ ሚስትህ ፡ ድል ፡ ወንበሬ ፡ ወደአገሯ ፡ ትመለስ ፡ ቢሉ ፡ ያባቷን ፡ የማኅፋዝን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ጦርነት ፡ የናፈቃት ፡ ድል ፡ ወንበራ ፡ እንቢ ፡ ብላ ፡ ክፉውን ፡ ሥፍራ ፡ በሰው ትከሻ ፡ የቀረውን ፡ በከብት ፡ እየተዘዋወረች ፡ የጦርነቱን ፡ ጊዜ ፡ መከፈሏን ፡ እንገነዘባለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ሹማምንት ፡ በንብሕት ፡ ወደድ ፡ ሠርፄ ፤ በራስ ፡ ማኅፀንቶ ፤ በአውራይ ፡ አትማን ፤ በተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ እንደዚሁም ፡ በግራኝ ፡ አህመድና ፡ በሹማምንቱ ፡ መካከል ፡ በአማጃህ ፡ በበደቄ ፡ (ዱከምና ፡ ሞጆ ፡ አጠገብ ?) ፡ በየጊዜው ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ።

ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሔዶ ፡ እንደገና ፡ ለመመለስ ፡ ትልቅ ፡ ዝግጅት ፡ ሲያደርግ ፡ እንደዚሁ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በበኩላቸው ፡ ግራኝን ፡ ለመውጋትና ፡ ለማጥፋት ፡ ዝግጅት ፡ ሲያደርጉ ፡ መሰንበታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በደዋሮ ፡ እንደ ፡ ዐርባ ፡ ሽመል ፡ በይፋት ፡ እንደወናግ ፡ ዣን ፡ ያሉት ፡ ቢሞቱ ፡ ሌሎች ፡ ታላላቅ ፡ መኳንንትና ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፡ ራስ ፡ ደገልሃን ፤ ራስ ፡ ባንያት ፤ ራስ ፡ ማኅፀንቶ ፤ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፤ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ ያሉት ፡ ከነጦራቸው ፡ አሉ፤ቸው ። ከይኸኖ ፡ እምላክ ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ከሱማሌና ፡ ከአዳል ፡ የሚቀሰቀሰው ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ሽፍትነት ፡ የመሰለ ፡ አገር ፡ ዘርፎ ፡ ከብት ፡ ነድቶ ፡ መመለስ ፡ እንጂ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ እየተመላለሰ ፡ በርትቶ ፡ የሚዋጋ ፡ የእስላም ፡ ጦር ፡ በአባቶቻቸው ፡ ዘመን ፡ አልነበረም ። የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ እነሐቅ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ እነሳብር ፡ አድ ፡ ዲን ፡ የአዳልን ፡ የሱማሌን ፡ ሕዝብ ፡ ከነባላባቱ ፡ በሙሉ ፡ አስነሥተው ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ላይ ፡ ቢነሡብት ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ እስከ ፡ አገራቸው ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ዘልቆ ፡ አሸንፎ ፡ እንደ ፡ አስገበራቸው ፡ ያውቃሉ ።

ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በመሐመድ ፡ በድላይ ፡ ላይ ፤ ራሳቸውም ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በይማም ፡ ማኅፉዝ ፡ ላይ ፡ ያገኙትን ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ስለሚያውቁ ፡ አሁን ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ አዝማችነት ፡ የተጀመረው ፡ ጦርነት ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለታላቁ ፡ ንጉሠ ነገሥት ፡ እየገበረ ፡ የሚኖረው ፡ የሐረርና ፡ የሱማሌ ፡ የአዳል ፡ ሕዝብ ፡ ዘርፎ ፡ እንደተለመደው ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ በግራኝ ፡ ውስጥ ፡ አብሮ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ለመውረር ፡ ይመኛል ፡ ብለው ፡ በትክክል ፡ የሚያ

ስቡ ፡ አይመስልም ። ቢያስቡም ፡ ይኸንኑ ፡ ወረራ ፡ ለመመለስ ፡ የሚያኩራ ፡ በያለበት ፡ ያላቸው ፡ ወታደር ፡ (ጪዋ) ፡ የትግሬ ፡ የበጌምድር ፡ የሸዋ ፡ የዳሞት ፡ የደዋሮ ፡ የባሌ ፡ የይፋት ፡ መኳንንት ፤ ከነጦሩ ፡ መመከት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ወደሐረር ፡ ገብቶ ፡ ቁጭት ፡ እንደሚወጣላቸው ፡ ያም ፡ ቢቀር ፡ የክርስቲያኑ ፡ ጦር ፡ የእስላምን ፡ ወረራ ፡ በርትቶ ፡ እንደሚያቆም ፡ ሳይተማመኑ ፡ አልቀረም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለሁሉ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ እንደሚባለው ፡ ድል ፡ ለማድረግም ፡ ለመሆንም ፡ ለማጥቃትም ፡ ለመጠቃትም ፡ ለመዝረፍም ፡ ለመዘረፍም ፡ ጊዜ ፡ አለውና ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ተጠቂ ፡ ተዘራፊ ፡ ተማራኪ ፡ ገባሪ ፡ የነበረው ፡ የአዳልና ፡ የሱማሌ ፡ ሕዝብ ፡ በግራኝ ፡ እየተመራ ፡ የኖረ ፡ ጥቃቱን ፡ ሊመልስ ፡ አልሰልምም ፡ ያለውን ፡ ክርስቲያኑን ፡ እየፈጀ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱን ፡ ገዳማቱን ፡ ሁሉ ፡ እየዘረፈ ፡ ለማቃጠል ፡ ቆርጦ ፡ ተነሥቷል ።

ለዚህ ፡ የግራኝ ፡ የበላይ ፡ መሪነት ፡ የየበላበቱና ፡ የየነገዱ ፡ ኅብረት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልንና ፡ የፖርቱጊዞቹን ፡ ግንኙነት ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ ይመለከቱ ፡ የነበሩት ፡ የቱርክና ፡ የዐረብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሰፊው ፡ የሚሰጡዋቸው ፡ መሣሪያና ፡ የሰው ፡ እርዳታ ፡ ድሉን ፡ ሊያረጋግጥላቸው ፡ ቻለ ። የግራኝ ፡ የባለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ጓደኞች ፡ የሃይማኖት ፡ ወገኖች ፡ የመን ፡ ዛቢድ ፡ ከቅርቡ ፡ አገራቸው ፡ በዘይላ ፡ በኩል ፡ ወታደርና ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መሣሪያ ፡ ሲያቀብሉና ፡ የቅርብ ፡ ርዳታቸው ፡ ሲጠቅማቸው ፤ ለወዳጅነትና ፡ ለርዳታ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ መንግሥታቸው ፡ ተስፋ ፡ ያደረገበት ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ርቀቱ ፡ ከ፳ሺ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ይበልጣል ። የመልእክት ፡ መልስ ፡ እንኳን ፡ ለማምጣት ፡ ፪ ፡ ዓመት ፡ ማስፈለጉን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተናግረናል ። ስለዚህ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ ፖርቱጊዞች ፡ የወጠኑት ፡ ወዳጅነት ፡ ጠላትን ፡ ቀስቅሶ ፡ ከመጉዳት ፡ በቀር ፡ ለልጃቸው ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ ለርሳቸው ፡ በጊዜያቸው ፡ የጠቀመው ፡ ነገር ፡ የለም ።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ለንጉሡ ፡ ላፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የቀራቸው ፡ ጦራቸውን ፡ ሰብስበው ፡ ራሳቸው ፡ በቀጥታ ፡ ከግራኝ ፡ መዋጋት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ እነሆ ፡ በዝርዝር ፡ ልንመለከት ፡ ነው ። የዘመኑ ፡ ሊቃውንትና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ እንዴት ፡ እንደተዘጋጁ ፡ እንደምን ፡ ተዋግተው ፡ እንደተሸነፉ ፡ በዝርዝር ፡ ጽፈው ፡ ስለአላቆዩን ፡ ላሁኑ ፡ ለበደቂው ፡ ጦርነትና ፡ ወደፊት ፡ ላለው ፡ ለሽምብራ ፡ ኵሬው ፡ ጦርነት ፡ ለመጥቀስ ፡ አልተቻለንም ። የሽምብራ ፡ ኵሬውን ፡ ባጭሩ ፡ ሲጠቅስ ፡ ከራስ ፡ ደገልሃን ፡ በኋላ ፡ ከሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ እንብሕት ፡ ወደድ፡ ሠርጌ ፤ እንአውራይ ፡ አትማን ፤ እንተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ እንሮቢል ፡ አማጃህና ፡ ይልቁንም ፡ በደቂ ፡ (ሞጆና ፡ ዱከም ፡ አቅራቢያ) ፡ ላይ ፡ የተዋጉትን ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ አላወሳውም ። የሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ የሚጻፍ ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ ከሁኑ ፡ ከበደቂ ፡ ምዕራፍ ፡ ጋር ፡

የተያያዘ ፡ ስለሆነ ፡ ስለሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ በጭሩ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የተጻፈውን ፡ እንመልከት ።

«ወእምዝ ፡ በ፱ ፡ ዓመት ፡ በ፳ወ፩ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለልብነ ፡ ድንግል ፡ መጽአ ፡ ግራኝ ፡ እስከ ፡ ሰመርማ ፡ ወተፃብዓ ፡ ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወሰደዶ ፡ እስከ ፡ ሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ መዲናሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ወገብሩ ፡ ፀብዓ ፡ በህየ ፡ አመ ፡ ፲ ፡ ወ፩ ፡ ለመጋቢት ወኀልቁ ፡ ብዙኃን ፡ መኳንንት ፡ ወሞቱ ፡ እለኀዱግ ፤ ራስ ፡ ማኅፀንቶ ፤ ወገብረ ፡ መድኅን ፤ ሽዋ ፡ ራስ ፡ ዓምዱ ፤ ጸሐፊ ፡ ላም ፡ ሮቤል ፤ ወእሴር ፤ ወከልአን ፡ ብዙኃን» ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ከራስ ፡ ዱጋልሃን ፡ ጋር ፡ በ፲፰ ፡ ፻፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በ፲፰፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመጋቢት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ግራኝ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ከፀሬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጋር ፡ መዋጋቱን ፡ በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ስማቸው ፡ የተዘረዘረና ፡ ያልተዘረዘረውም ፡ ሌሎች ፡ መኳንንቶች ፡ ማለቃቸውን ፡ ይገልጽልናል ። ሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ የሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ወዴት ፡ መሆኑ ፡ አልተጣራም ። ሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ የሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ በይፋት ፡ ውስጥ ፡ ዛሬም ፡ መኖሩን ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰምቻለሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በዝርዝር ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ የጻፈው ፡ የዐረብ ፡ ፋቂህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያነቡት ፡ ጦርነቱ ፡ በተደረገበት ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ አገሮች ፡ ዘቃላ ፡ (ዝቀላ) ፤ ማጁ ፡ (ሞጆ) ፡ ዱከም ፡ እያለ ፡ ስለሚያነሣ ፡ ይህ ፡ ንጉሡ ፡ ተዋግተው ፡ የተሸነፉበት ፡ የሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ሥፍራ ፡ በዝቋላ ፡ በዱከም ፡ በሞጆ ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ አቅራቢያ ፡ እንጂ ፡ ወደይፋት ፡ የሚቀርብ ፡ አይመስልም ። እነዚህም ፡ ዝቋላ ፡ ሞጆ ፡ ዱከም ፡ የሚባሉት ፡ ስማቸውን ፡ ሳይለውጡ ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ የደረሱት ፡ ቀበሌዎች ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከታወቁት ፡ ከታላላቅ ፡ አውራጃዎች ፡ ከበሌ በምዕራብ ፡ ከይፋት ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በሚገኘው ፡ ፈጠጋር ፡ በሚባለው ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ። ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በሙሉ ፡ ከአሳተሙት ፡ ውስጥ ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ የሞቱትን ፡ መኳንንት ፡ በግዕዙ ፡ ቃል ፡ ሲዘረዝሩ ፡ የመጀመሪያውን ፡ እለ ፡ ኀዱግ ፡ ራስ ፡ ማኅፀንቶ ፡ የሚለውን ፡ እሰ ፡ እዱግ ፡ ራስ ፡ መይኅዘንቶ ፡ ብለውታልና ፡ በዝንጋታ ፡ መሆኑን ፡ ላገራችንም ፡ ለውጭ ፡ አገርም ፡ አንባቢ ፡ አመለክታለሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ እንተውና ፡ ከሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከንብሕት ፡ ወደድ ፡ ሠርጺ ፡ ጋር ፡ ያደረገውን ፡ የባደቄን ፡ ጦርነት ፡ በዝርዝር ፡ የሚናገረውን ፡ የዐረብ ፡ ፋቂህን ፡ ጽሑፍ ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደፈረንሣዊ ፡ ከተረጐሙትና ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከፈረንሣዊ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ የተረጐምሁትን ፡ ባለፈው ፡ ከተቋረጠው ፡ የሚቀጥለውን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ እንመልከት ።

"በከተማው ፡ (በሐረር ፡ ማለቱ ፡ ነው) ፡ ቲንሽ ፡ ጊዜ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ የጦር ፡ ዝግጅት ፡ አደረገ ። ከሀበሻ ፡ አገር ፡ የተዘረፈውን ፡ ምርኮና ፡ ዕቃ ፡ እየጨመረ ወደ ፡ ሱማሌዎችና ፡ ወደ ፡ [illegible]ቹም ፡ ነገዶች ፡ መላክተኛ ፡ ላከ ። ሁሉን ፡ ለሚያ

ውቀው ፤ ንጉሥ ፤ (እግዚአብሔርን ፤ ሲል ፤ ነው ?) እንዲታዘዙና ፤ ለዚህ ፤ ለተቀደሰው ፤ ጦርነት ፤ እንዲተባበሩ ፤ ደብዳቤም ፤ ጻፈላቸው ። በደብዳቤውም ፤ ውስጥ ፤ ተነሡ ፤ ጉዟችሁንም ፤ ዠምሩ ፤ ሀብታችሁንና ፤ ሕይወታችሁን ፤ ለእግዚአብሔር ፤ ስጡ ፤ የሚል ፤ ጥቅስ ፤ (ከቍራን ፤ ማለቱ ፤ ነው) ፤ እየጨመረ ፤ ጻፈላቸው ። ወደ ይባሬ ፤ ነገዶች ፤ የተላከው ፤ አሊ ፤ ጐይታ ፤ አባቱ ፤ በሡልጣን ፤ አህመድ ፤ ጊዜ ፤ በሌ ፤ ላይ ፤ የሞተው ፤ ሌላው ፤ ሁለተኛው ፤ መላክተኛ ፤ ወደ ፤ ጂሬ ፤ ነገዶች ፤ ባላባታቸው ፤ የይማም ፤ አህመድ ፤ አማች ፤ ወደ ፤ ሆነው ፤ ወደ ፤ ማታን · ቤን ፤ አትማን ፤ ...... ፤ ሦስተኛው ፤ መላክተኛ ፤ በሂራብ ፤ በጎይታ ፤ ቴድሮስ ፤ ልጅ ፤ ውስጥ ለሚተዳደሩ ፤ መራይሃን ፤ ለሚባሉት ፤ ነገዶች ፤ ነው ። ይማም ፤ ለዚህ ፤ ለቅዱስ ፤ ጦርነትና ፤ ለእግዚአብሔር ፤ መንገድ ፤ ለማሳበር ፤ በያለበት ፤ ሰበከ ።

የሐበሻ ፤ ንጉሥ ፤ የናዖድ ፤ ልጅ ፤ የወናግ ፤ ሰገድ ፤ ሰዎች ፤ ወርቅ ፤ ኡአርስ (የእህል ፤ ወይም ፤ ያትክልት ፤ ዓይነት?) ፤ የዝሆን ፤ የአውራሪስ ፤ ጥርስ ፤ ጥርኝ ፤ ባርያ ፤ ሌላም ፤ ብዙ ፤ ሀብት ፤ ወደ ፤ አደን ፤ ድረስ ፤ በባሕር ፤ እየተመላለሱ ፤ የሚነግዱ ፤ ነበሩትና ፤ የነርሱን ፤ እጉዘ ፤ ላይ ፤ መሆን ፤ ኢሚሩ ፤ ሰምቶ ፤ ሁሉንም ፤ ቀምቶ ፤ ለየነገዱ ፤ አከፋፈለውና ፤ ለዚህ ፤ ለጦርነት ፤ ጉዳይ ፤ . . . . . ጠቀመ ።

ከዚህ በኋላ ፤ ነገዶችም ፤ አለቆችም ፤ ...... ሁሉ ፤ የጦር ፤ ዝግጅታቸውን ፤ ጨርሰው ፤ የጦር ፤ መሣሪያቸውን ፤ ይዘው ፤ እየተከታተሉ ፤ ሥጡልህ ፤ የሚሉ ፤ ሁለት ፤ መልክተኞች ፤ ወደ ፤ ይማም ፤ መጡ ። በመጀመሪያ ፤ ይማም ፤ አህመድ ፤ ዘንድ ፤ የደረሰው ፤ ነገድ ፤ የሐብር ፤ ማጋዲ ፤ ነው ፤ ባላባታቸው ፤ አህመድ ፤ ጉራይ ፤ ቤን ፤ ኤዝ ፤ ሱማሌ ፤ ይባላል ። እነዚህም ፤ ነገዶች ፤ በሐረር ፤ ሸለቆ ፤ በላይኛው ፤ በኩል ፤ በተለይ ፤ ካሻ ፤ በሚባለው ፤ ሥፍራ ፤ ሠፈሩ ። በእነርሱም ፤ ውስጥ ፤ የፈረሰኛና ፤ የእግረኛ ፤ ድንቅ ፤ የሆኑ ፤ የጦር ፤ ወታደሮች ነበሩባቸውና ፤ መሣሪያቸውንና ፤ ሰልፋቸውን ፤ በፈረስ ፤ ሆነው ፤ አሳምረው ፤ አሳዩ ። የነርሱም ፤ መምጣት ፤ ይማም ፤ አህመድን ፤ በጣም ፤ አስደስተው ፤ ለነርሱ ፤ ይማም ፤ መልክም ፤ አቀባበልና ፤ ክብር ፤ አደረገላቸው ። ለአለቃቸው ፤ ለአህመድ ፤ ጉራይ ፤ የሚያምር ፤ ሽልማት ፤ አልብሶ ፤ ሸለመው ።

ቀጥሎ ፤ የጂሬ ፤ ነገዶች ፤ በባላባታቸው ፤ በማታን ፤ ቤን ፤ ኡስማን ፤ እየተመሩ መጡ ። እነርሱም ፤ በፈረስ ፤ ሆነው ፤ መሣሪያቸውን ፤ ሰልፋቸውን ፤ ለይማም ፤ አሳዩ ። እነርሱንም ፤ ይማም ፤ ሲም ፤ ወደ ፤ ሚባለው ፤ ሥፍራ ፤ አስቀድሞ ፤ ላካቸው ። አለቃቸውም ፤ ሚስቱን ፤ ፌርዳውሳህ ፤ የምትባለውን ፤ የይማምን ፤ እህት አስከትሎ ፤ መጥቶ ፤ ነበር ።

ከዚያ ፤ የዘርባ ፤ ነገዶች ፤ መጡ ፤ የነርሱም ፤ አለቃ ፤ የይማም ፤ ያባቱ ፤ እህት (ያክስቱ) ፤ ልጅ ፤ ሡልጣን ፤ መሐመድ ፤ ይባላል ። ያስከተለውም ፤ ጦር ፤ አርባ ፈረሰኛ ፤ ሺ ከ ፫ ፤ የእግረኛ ፤ ወታደር ፤ ነበር ፤ እነርሱንም ፤ ይማም ፤ በሐረር ፤

ሆኖ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀበላቸው ። በእንርሱም ፡ ደስ ፡ ተሰኝቶ ፡ ፈውል ፡ አምላክን ፡ አመሰገነ ። የጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ ሁሉ ፡ በከተማዪቱ ፡ (በሐረርጌ) ፡ ዙሪያ ፡ ሠፈሩ ። አንዱ ፡ ሠፈረተኛ ፡ ከሌላው ፡ አይገናኝም ፡ ነበር ።

ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ (ከተላከበቻው ፡ ውስጥ) ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የቀረና ፡ የሰነፈ ፡ የመራሂሃን ፡ ነገድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። አለቃቸውም ፡ ሂራቡ ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ የሚወድ ፡ ተንከለኛ ከዳተኛ ፡ ነበር ። ይማም ፡ ከወታደሮቹ ፡ ውስጥ ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ሂራቡና ወደ ፡ መራሂሃን ፡ ነገድ ፡ ሄደና ፡ «በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ተቀደሰው ፡ ጦርነት ፡ ለመምጣት ፡ የዘገየኸው» ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ አለቅዬው ፡ ችግሩንና ፡ ድኅነቱን ፡ አመከኝቶ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ ፡ ይማምም ፡ «ጦርነቱን ፡ በመጐተት ፡ (በማራዘም ፡) ምንም ፡ የምትጠቀመው ፡ ነገር ፡ የለም» ፡ ብሎ ፡ ይቅርታ ፡ አደረገለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሂራቡ ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ የበላይ ፡ አድርጎ ፡ የመራሂሃንን ፡ ነገድ ፡ ከይማም ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ እንዲተባበር ፡ ሰጠው ። የነርሱም ፡ ቊጥር ፡ ፺ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፺፻ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ነበር ። ሂራቡን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ትቶ ፡ ይማም ፡ የመራሂሃንን ፡ ነገድ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ተመለሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሀበሻን ፡ አገር ፡ ለመውጋት ፡ ተዘጋጀ ። የቤቱን ፡ ዕቃ ፡ ለራሱ ፡ አንድም ፡ ሳያስቀር ፡ የሚስቶቹንም ፡ ጌጥ ፡ እየሸጠ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ እየገዛ ፡ ለየነገዱ ፡ ለየወታደሩ ፡ አድሎ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ አደራጀ ። ለራሱ ፡ ምንም ፡ ሳያስቀር ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ወጭ ፡ ለዚህ ፡ ለቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ ማውጣቱ ከአምላኩ ፡ የሚያስደስተውን ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትንና ፡ ከሚያማምሩት ፡ ቆነዣዥት ፡ ዓይናቸው ፡ ከጠቋቆረው ፡ ሴቶች ፡ አንዷቱን ፡ ለማግኘትና ፡ በጠቅላላው አምላክን ፡ ለማስደሰት ፡ ብሎ ፡ ነው ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከደረገ ፡ በኋላ ፡ ጉዞውን ፡ በይፋ ፡ አስታውቆ ፡ ከነጦሩ ፡ መንገድ ፡ ጀመረ ። ጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ ነገዱም ፡ ሁሉ ፡ ተቀጣጥሎ ፡ በሰልፍ ፡ ተከተለው ። የጦርነት ፡ አላማም ፡ (ሰንደቅ ፡ አላማም) ፡ ተዘረጋ ። ይማም ፡ ከሚስቱ ፡ ከድል ፡ ወንበራ ፡ ከኤሚር ፡ ማኅፉዝ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ። በዚህም ፡ ወራት ፡ ድል ፡ ወምበራ ፡ እርጉዝ ፡ ነበረች ። ተጕዘውም ፡ ዚፋህ ፡ ወደ ምትባለው ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ፡ በዚችም ፡ ከተማ ፡ ለሲሳይ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አገኙ ። በዚያም ፡ ከገራድ ፡ ዲን ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ (ያገሩ ፡ ባላባት) ፡ ጋር ፡ ተገናኙ። እርሱም ፡ ደሀ ፡ ወዳድ ፡ ጻድቅ ፡ ነበር ። የነቢዩን ፡ (የመሐመድን) ፡ ስም ፡ ደጋግሞ ፡ ማንሣት ፡ ይወድ ፡ ነበር ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ገራድ ፡ ሻሙን ፡ (ስምዖን ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አጠራር) ፡ ገራድ ፡ ከሚል ፡ የይማም ፡ እማች እህቱን ፡ ሙኂሣህን ፡ ያገባው ፡ ኤሚር ፡ ሞጃሂድ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ይማምን ፡ አብሳማ ፡ ኑርን ፡ (አባ ፡ ኤስማን ፡ ኑር ፡ እንደ ፡ ኢት) ፡ በክብር ፡ ተቀብለው ፡ አስተናገድዋቸው ። ይማም ፡ አህመድ ፡ ከነጦሩ ፡ በዚፋህ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ በሰነበተበት ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡ ድል ፡ ወምበራ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፡ ስሙም

መሐመድ ፡ ተባለ ። ስለዚህም ፡ ድል ፡ ወምበራ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ከግራኝ ፡ እህት ፡ ከሙኒሣህ ፡ ዘንድ ፡ ቀርቻ ፡ ነበር ። እስላሞቹ ፡ ጉዟቸውን ፡ ወደፊት ፡ ቀጥለው ፡ ወሀ ፡ እሞላበት ፡ ኤዲር ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ ፡ በዚያም ፡ ቷንሹም ፡ ትልቁም ፡ ወደ ፡ ዠግኖቹ ፡ እየመጣ ፡ ተደባለቀ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ያበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ በደቂ ፡ እሚባል ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ እስላሞች አገርህን ፡ እየዘረፉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትህን ፡ እያቃጠሉ ፡ ወደፊት ፡ ይገሠግሣሉ ፡ ጦራቸውም ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ነጋሪ ፡ መጣለት ። ይኸን ፡ ሲሰማ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ መኳንንቱን ፡ ሹማምንቱን ፡ አስ ከትሎ ፡ የግዛቱ ፡ አማካይ ፡ ሥፍራ ፡ ወደሆነው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ አምሐራ ፡ (አማራ ፡ ሳይንት) ፡ ሄደ ። ይኸም ፡ አገር ፡ ለርሱም ፡ ላባቶቹና ፡ ለቀድም ፡ አያቶቹ ፡ መኖ ሪያና ፡ መደበኛ ፡ ሥፍራቸው ፡ ነው ። ለበደቂ ፡ አገር ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ ደር ፡ አሊን ፡ (አውራይ ፡ አትማን) ፡ ትቶት ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። ይኸም ፡ ሹም ፡ በሡልጣን ፡ መሐመድ ፡ ጊዜ ፡ ከናባቱ ፡ ተማርኮ ፡ ሔዶ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለውጦ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ተጸጽቶ ፡ ተመልሷል ።

ንጉሡ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ቤተ ፡ አምሐራ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ሰበሰበ ። የትግሬ ፤ የአገው ፡ የጐጃም ፡ የቤጌምድር ፡ የአንጎት ፡ የቅዳ ፡ የጋኝ ፡ ክርስቲያ ንና ፡ የባሕር ፡ ዳር ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በዙሪያው ፡ ተሰበሰበ ። የትግሬ ፡ የታወቁት ፡ መኳንንቶች ፡ ብቻ ፡ ቊጥራቸው ፡ ፳፬ ፡ ይደርሳል ። እያንዳንዱ ፡ መኰንን ፡ በውስጡ ፡ የሚታዘዘው ፡ ጦር ፡ ነበረው ፡ እንደዚሁም ፡ የቤጌምድሩ ፡ የአንጎቱ ፡ የቅዳው ፡ የጋኙ ፡ ብዛታቸው ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ ስለሚመስል ፡ ከእግዚአብሔር በቀር ፡ ሊቆጥ ራቸው ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ። የክርስቲያኖቹ ፡ ወታደሮች ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ ተዘጋጁ ፡ በያለቃቸው ፡ በየደረጃቸው ፡ ሆነው ፡ በቤተ ፡ አምሐራ ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ። አባስ ፡ የሚባል ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለውጦ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ የነበረ ፡ በኋላ ፡ የተመለሰው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ አምሐራ ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ነበርና ፡ የነገረኝን ፡ አስታውሳለሁ ፡ (ያራብ ፡ ፋቂህ ፡ ቃል) ። እርሱንም ፡ ንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ «አባስ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ፡ ጦር ፡ ሠራዊታችንን ፡ ይማም ፡ ሲያይ ፡ የሚዋጋ ፡ ይመስልሃል ፡ ወይስ ፡ አይመስልህም» ፡ የአባስ ፡ መልስ ፡ «እርሱ ፡ ከሁለት ፡ አንዳቸው ፡ መልከም ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ መያዙ ፡ አይቀርም ፡ ጦሩ ፡ ግን ፡ የሚያደርገውን ፡ አላውቅም ፡» ንጉሡ ፡ «እውነት ፡ አልህ ፡ ጦሩ ፡ ይመከታል ፡ ብትለኝ ፡ ኖሮ ፡ እንደ ፡ ውሸታም ፡ እቆጥርህ ፡ ነበር ፡ ብን ተም ፡ እምነት ፡ አይኖረኝም ፡ ነበር ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አላውቅም ፡ ማለትህ ፡ ደግ ፡ አደረገህ ። » (፩)

፩) ፡ እንደሙሴ ፡ ባሴት ፡ ረኔ ፡ ኔራዚኒ ፡ የሚባለው ፡ ጣልያን ፡ የተረጐመው ፡ ከዚህ ፡ ለየት ፡ ይላል ፡ "ይማም ፡ ይኸን ፡ ጦር ፡ ሲያይ ፡ ይመክታል ፡ ወይስ ፡ ይሸሻል ፤ ቢሉት ፡ ይማም ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ አስር ፡ እጥፍ ፡ ጦር ፡ ቢያይም ፡ መግጠሙን ፡ አይተውም ፡ አላቸው ።" ንጉሡም ፡ እውነት ፡ ተናገርህ ፡ ጉሽ ፡ አሉት ።

በበኩሉ ፡ በደቄ ፡ ላይ ፡ ንጉሡ ፡ ትተውት ፡ የሔዱት ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ የደ ዋሮን ፡ የባሌን ፡ የወናግ ፡ (ጃዳብ?)፡ የወናግ፡ አምባን ፡ የኤል ፡ ማያን ፡ የአርአን ፡ የጋንጽን ፡ የፈጠጋርን ፡ የጸለምትን ፡ ሠራዊት ፡ ሰበሰበ ። ዋና ፡ ዋኖቹም ፡ አለቆች ፡ ሰባት ፡ ናቸው ፡ እነርሱም ፡ በውስጣቸው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ብዙ፡ጦር ፡ አላቸው ። በንጉሡ ፡ አያት ፡ (በበዕደ ፡ ማርያም) ፡ ዘመን ፡ በፈጠጋር ፡ የበላዩ ፡ ሹም ፡ የሚ ሾመው ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ያሁኑ ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ እየ ተፎካከሩ ፡ እስላሞችን ፡ እንዲወጉለት ፡ ሰባት ፡ ሹማምንት ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። የክ ርስቲያኖቹም ፡ ጦር ፡ ብዛት ፡ ሲታይ ፡ በመላው ፡ ግዛት ፡ (በኢትዮጵያ ፡ ባላገር )፡ አንድም ፡ ሰው ፡ የቀረ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ። ክርስቲያኖቹም ፡ ባገራቸው ፡ እስ ላም ፡ እንዳይገባ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቸውንም ፡ እንዳይጠጋ ፡ ይልቁንም ፡ በባ ደቄ ፡ ያለውን ፡ የንጉሡን ፡ ቤትና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመከላከል ፡ ተሰብስ በው ፡ ነበር ። ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲነጋገሩም ፡ «ይማም ፡ ይቺን ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ለማቃጠል ፡ ፈልጓል ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ሁላችንም ፡ ጨርሰን ፡ ሳናልቅ ፡ አናስደርሰውም» ፡ ብለው ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ የባደቄው ፡ አዝማች ፡ (አውራይ ፡ አትማን) ፡ ይማምን ፡ ሲጠብቅ ፡ የሀበሻው ፡ ንጉሥ ፡ በቤተ ፡ አምሐራ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ።

እስላሞቹ ፡ ኤዲር፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ሳለ ፡ ከዚያ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ተጉዘው ፡ በቁልዛር ፡ (፩) ፡ ከሚባለው ፡ ወሀ ፡ ከሞላበት ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ጦሩን ፡ ለውጊያ ፡ ማሰለፍ ፡ ዠመረ ።

፩ኛ– ለቪዚር ፡ አዶሌ ፡ በውስጡ ፡ የሲምን ፡ ሕዝብ ፡ የአህመድ ፡ ጉራይንና የሁብር ፡ ማጋዲን ፡ የሱማሌ ፡ ነገዶች ፡ አድርጎ ፡ የሚዘምትበት ፡ ነጭ ፡ ሰንደቅ፡ ዓላማ ፡ ሰጠው ። ከርሱ ፡ ጋር ፡ ፪፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ የእግረኛ ፡ ወታ ደር ፡ ነበር ። የፈረሰኛ ፡ ወታደር ፡ አለቆች ፡ መለሳይ ፡ (፪) ፡ ነበሩ ፡ እነሱም ፡ ኤሚር፡ሙጃ (ጋ) ሂድ፡ ሱሀ፡አብሳማ ፡ ኑር ፡ ገራድ ሻሙን ፡ ገራድ ፡ ቦርሃን ፡ በለው ፡ አብድ ፡ አሉክ ፡ ቤን ፡ ኤል ፡ ሐይጀን ፡ ኑር ፡ አዩብ ፡ ከሴድ ፡ ኤል ፡ ዋራዲ ፡ ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ መንገድ ፡ መሪም ፡ ነበር ፡ ከፈረሰኞች ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ ዠግና ፡ ፈረሰኛ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ከጐበዛዝት ፡ ውስጥ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ሰብ ስቦ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ኤል ፡ አውራይ ፡ ኑር ፡ ቃልታ ፡ የኡመር ፡ ልጅ፡ የገራድ ፡ ማኅፉዝ ፡ አማች ፡ ፈራቃሃም ፡ አትማን ፡ የማጅ ፡ አማጀድ ፡ አህመድ፡ ቤን ፡ ኤል ፡ ሁሴን ፡ ሳር ፡ አቡበኮር ፡ ሙሚናት ፡ አቡበከር ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ የሲም ፡ ፈረሰኛ ፡ ሹም ፡ ዋርዳይ ፡ ሃይጀን ፡ አትማን ፡ ዋርዳይ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከልባቸው ፡ እስላም ፡ ሆነው ፡ ይኸን ፡ ጦርነት ፡ ለመፈጸም ፡ . . . . . . . ፡ የተ ነሡ ፡ ነበሩ ። ከነርሱም ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ ጌታ ፡ ስለሃይማኖቱ ፡ የሚሞተው ፡ ዋሸራ ፡ ሼክ ፡ ሐምድ ፡ እነዚህን ፡ ፈረሰኞች ፡ ከሚከተሉት ፡ ጻድቃን ፡ ውስጥ ፡ አብሮ ፡ ነበር።

(፩) ቀድሞ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ደራደርን ፡ የወጋበት ፡ ሥፍራ ፡
(፪) የነገድ ፡ ወይም ፡ የሹማምንት ፡ ጠቅላላ ፡ ስም ፡ ይመስላል ።

፪ኛ– ፡ ለሱማሌዎች ፡ አለቃ ፡ ለአትማን ፡ ቤን ፡ ከሊድ ፡ ልጅ ፡ ለአማቹ ፡ ለማታን ፡ በውስጡ ፡ ፩፻፲ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፫ሺ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ አድርጎ ፡ ቀይ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ሰጠው ። እርሱም ፡ የጉበዞች ፡ ጉበዝ ፡ ስለነበረ ፡ የሀርቲን ፡ የጂራን ፡ የማዝራን ፡ ሱማሌ ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡ እንዲያዝ ፡ ጨመረለት ።

፫ኛ ለቪዚር ፡ ኑር ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ በውስጡ ፡ የሸዋን ፡ (፩) ፡ በይማም፡ ወንድም ፡ በመሐመድ ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ የሚመሩትን ፡ የሀርጋይን ፡ ነገዶች፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ (ከናቱ ፡ ወይም ፡ ከባቱ ? ፡) የሚወለደው ፡ በሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲን ፡ ወንድም ፡ የሚታዘዙትን ፡ የጀሪርን ፡ ሰዎች ፡ አድርጎ ፡ ቀይና ፡ ብጫ ፡ የተደበለቀበትን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ሰጠው ። የነርሱም ፡ ቁጥር ፡ ፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፪ሺ ፡ እግረኛ ፡ ነበር ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚታዘዙት ፡ የታወቁት ፡ ፈረሰኞች ፡ ሼክ ፡ ዳውድ ፤ ሼክ ፡ ዘማላህ ፤ ገራድ ፡ አሊ ፡ ፈንጋላህ ፤ ጎይታ ፡ ኢብራሂም ፡ የገዳይ ፡ (አገር) ፡ ጌታ ፤ ፋራቃሃም ፡ ወስንጌ ፤ ጎይታ ፡ አትማን ፡ ነበሩ ።

የይማም ፡ አህመድ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ደግሞ ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡ በቀይ ፡ ተከፍፎ ፡ መካከሉ ፡ ነጭ ፡ ነበር ። ዳር ፡ ዳሩን ፡ በቀዩ ፡ ክፈፍ ፡ ላይ ፡ «በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ላንተ ፡ ስንል ፡ ያማረ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ አመጣንልህ ። በዚህ ፡ ያለፈና ፡ የዛሬውን ፡ ኃጢአትህን ፡ ይቅር ፡ እንዲልህ ፡ ደገኛ ፡ ሥራውን ፡ እንዲያድልህ ፡ ወደቀጥተኛው ፡ መንገድ ፡ እንዲመራህ ፡ ፡ . . . .» የሚል ፡ ጥቅስ ፡ ተጽፎበት ፡ (ተጠልፎበት) ፡ ነበር ። በመካከሉም ፡ አራት መሥመር ፡ ተከታትሎ ፡ እረፍት ፡ አድርጉ ፤ ለጸሎት ፡ ተዘጋጁ ፡ ምጽዋት ፡ ስጡ . . . . »የሚል ፡ አንደኛው ፡ በሕያው ፡ በዘለዓለማዊው ፡ አጸናሁዋችሁ ፡ በማይሞተው ፡ ሕማምን ፡ ከራሳችሁ ፡ ላይ ፡ አስወገድሁ ፡ . . . . . »የሚል ፡ በሁለተኛው ፡ «ሌላዩቱ ፡ ሕይወት ፡ (መንግሥተ ፡ ሰማያትን) ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለሚፈራ ፡ ትገባዋለች ። የአዳም ፡ የሁለቱን ፡ ልጆቹን ፡ መሥዋዕት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ ተረከላቸው ፡» የሚል ፡ በሦስተኛው ፡ «ጦርነት ፡ የጀመርህ ፡ እንደሆነ ፡ ስንፍናን ፡ አታግባ ፡ በሽብር ፡ ጊዜ ፡ ጽና ፡ ሞት ፡ በዕድል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይደርስም» ፡ የሚል ፡ በራተኛው ፡ መሥመር ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ።

እነዚህን ጽሑፎች ፡ ያዘጋጀው ፡ ቅዱስ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ አዋቂው ፡ የእስላሞቹ ፡ ሙፍቲ ፡ ሲድ ፡ አቡበከር ፡ የናስር ፡ ኤዲን ፡ ልጅ ፡ . . . . ነው ። እርሱም ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ጦርነት ፡ ከይማም ፡ አህመድ ፡ አልተለየም ። በሌሎቹም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ሲሄድም ፡ ተቀምጦም ፡ ቆሞም ፡ እፈረስም ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ቊራንን ፡ ከመድገም ፡ አያቋርጥም ፡ ነበር ። ለእስላሞችም ፡ ሁሉ ፡ ሰባኪና

(፩) አዋሽ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ እስላሞች ፡ ያሉበትን ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ ሸዋ ፡ የሚባለውን ፡ አገር ፡ አይመስልም ።

መምህር ፡ ነበር ። ቍራንን ፡ በሚደግምበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ስለጦርነት ፡ የሚናገረውን ፡ ክፍል ፡ እየጠቀሰ ፡ በመናገር ፡ ለጦርነት ፡ እየቀሰቀሰ ፡ እስላሞቹን ፡ ሁሉ ፡ ውጊያ፡ እንዲያምራቸው ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

የእስላሞቹ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ (ግራኝ) ፡ በመክከል፡ ሆኖ ፡ በዙሪያው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ፈረሰኛና ፡ አሽከር ፡ ይዞ ፡ የተጫኑ ፡ ፈረሶ ቹን ፡ አስከትሎ ፡ ይጓዝ ፡ ነበር ። ከስመ ፡ ጥሩዎቹ ፡ ፈረሰኞች ፡ ውስጥ ፡ ሁሴን፡ ኤል ፡ ጋቱሪ . . . ፡ ኤሚር ፡ ዘሀርቡይ ፡ መሐመድ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ክርስቲያኖች፡ ማርከውት ፡ በኋላ ፡ አምልጦ ፡ የመጣው ፡ . . . ፡ ኩሽም ፡ አቡበከር ፡ . . . ፡ ገራድ ፡ አህ ሙሹ ፡ . . ፡ ገራድ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ . . . ፡ ሳብር ፡ ኤድ ፡ ዲን ፡ ክርስቲ ያኖችን ፡ ሲያይ ፡ ክልትያዝ ፡ በቀር ፡ የማይቆመው ፡ እልሁ ፡ ከመገንፈሉ ፡ የተ ነሣ ፡ ከፍንጫው ፡ ደም ፡ የሚንቆረቆረው ፡ ለጦርነት ፡ ቃላቅ ፡ የፍቅር ፡ ሕመም፡ ያለው ፡ ፋራቃሃም ፡ ሡልጣን ፡ ቤን ፡ አሊ ፡ ጓደኛው ፡ ኑር ፡ ቤን ፡ ናስር ፡ ቤን፡ አሊ ፡ ገራድ ፡ ሳዲቅ ፡ ቤን ፡ አሊ ፡ . . . ፡ ፋራቃሃም ፡ ዲን ፡ . . . ፡ ኤል ፡ አውራይ ፡ መሐመድ ፡ ቤን ፡ አብደል ፡ ዋሀድ ፡ ኤሚር አቡበከር ፡ ቀጭን ፡ . . . ፡ ጎይታ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ቤን ፡ አዳም ፡ ጃሻ ፡ ኡመር ፡ . . ፡ ቃክላ ፡ ቤን ፡ አኩዋ ፡ አህመድ ፡ ዲን ፡ ቤን ፡ ከሊድ ፡ ገራድ ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ ጃው ፡ ሄር፡ ኤል ፡ አውራይ ፡ አቡን ፡ ቤን ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ ሰለይማን ፡ የሡልጣን ፡ መሐ መድ ፡ ቤን ፡ በድላይ ፡ ልጅ ፡ . . . ፡ በካሬ ፡ ቤን ፡ ጀሹ ፡ (ጎሹ) ።

እስላሞቹ ፡ ከባቂል ፡ ዛር ፡ ተነሥተው ፡ ኩብ ፡ እሚባለው ፡ ወንዝ ፡ ደረሱ። ለአዋሽ ፡ ገና ፡ ሁለት ፡ ጣቢያ ፡ ይቀራል ። ወሀ ፡ በሌለበት ፡ በረሀ ፡ ሲጓዙ ፡ ከበረሀነቱ ፡ የተነሣ ፡ ግማሹ ፡ በሌሊት ፡ እንጓዝ ፡ እኩሉ ፡ በቀን ፡ እንጓዝ ፡ እያለ፡ ሲከራከር ፡ ቆይቶ . . . በቀን ፡ ለመጓዝ ፡ ቁርጥ ፡ ሆነና ፡ ወሀ ፡ ወዲት ፡ እንደሚ ገኝ ፡ ሳያውቁ ፡ እንደዚሁ ፡ ጉዞዋቸውን ፡ ገሠሩ ። ቀጥለው ፡ ወሀ ፡ ያለበትን፡ ሥፍራ ፡ አግኝተው ፡ ሰውም ፡ ከብቱም ፡ ጠጣ ። በማግስቱም ፡ አዋሽ ፡ ደር ሰው ፡ ሰፈሩ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መሪዎቹ ፡ ከሊድ ፡ ኤል ፡ ዋራዲ ፡ ጂማ ፡ አሊ፡ አዛሪ ፡ ቤን ፡ ዳልማሲና ፡ ወንድሙ ፡ አዋሽ ፡ በደረሱበት ፡ ቀን ፡ ከነዚህ ፡ ውስጥ፡ አንዱ ፡ ኢብን ፡ ዳልማሲ ፡ የአቡን ፡ ደዋሀን ፡ ፈረስ ፡ ሰርቆ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያ ኖቹ ፡ ጠፍቶ ፡ ሄደ ። የፈረሱ ፡ ጌታ ፡ ይኸንኑ ፡ ለይማም ፡ ነገረውና ፡ ሁሉም ፡ ተሰብስበው ፡ በሰራቂው ፡ ላይ ፡ ፋትሃህ ፡ (ያጥፋው ፡ የሚል?) ደገሙበት ። የጸ ሎት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ፈረሱ ፡ ብቻውን ፡ መጣ ፡ ሌባው ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አልታወቀም ፡ ግማሹ ፡ ያዋሽ ፡ ወሀ ፡ ወሰደው ፡ የቀረው ፡ ሰው ፡ ገደለው ፡ ይላል . . . . ከዚያ ፡ እስላሞቹ ፡ አዋሽን ፡ ትተው ፡ ማርጃህ፡ ማርዮጂ ፡ (ጌ) ፡ የሚባል ፡ አገር ፡ ደርሰው ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ ፡ በዚያ ፡ ሳሉ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ለስንቅ ፡ የሚሆን ፡ እህል ፡ እንዲሰበስቡና ፡ እንዲሰልሉ ፡ ጂልቢ ወደሚባለው ፡ ወዳበሻ ፡ ስፍራ ፡ ቪዚር ፡ አዶሴን ፡ ከሰዎች ፡ ጋር ፡ ላከ ውና ፡ በከሰም ፡ መንገድ ፡ አድርጎ ፡ አማጃህ ፡ ደረሰና ፡ ብዙ ፡ ስንቅ ፡ ሠንጋም፡

ሰበሰበ ፡ ከዚያ ፡ ይማም ፡ ሌሎቹም ፡ በአማጻህ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ይህቺም ፡ አገር ፡ የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ፡ ናት ። በውስጧ ፡ ግን ፡ እስላሞች ፡ አሉ ። የከተማ ፡ ነዋሪዎቹ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጡና ፡ "ያበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ኀልቆ ፡ መሳፍርት ፡ የሌለው ፡ ጦር ፡ አለው ። ፈረሰኛውን ፡ እግረኛውን ፡ . . . . ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ቈጥሮ ፡ የሚያደርሰው ፡ የለም ። አባቶችህን ፡ አያት ቅድም ፡ አያቶችህን ፤ አማትህ ፡ ኤሚር ፡ ማኀፉዝንም ፡ ኤሚር ፡ አሊን ፡ የሳዓድ ፡ ዲን ፡ አገር ፡ የጥንት ፡ ሡልጣኖችም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያበሻውን ፡ ንጉሥ ፡ አገሩና ፡ እቤቱ ፡ ድረስ፡ መጥቶ ፡ ሊወጋው ፡ የደፈረ ፡ የለም ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በገራቸው ፡ ወሰን ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወረራ ፡ አድርገው ፡ ምርኮ ፡ ዘርፈው ፡ ይመለሳሉ ። ከክርስቲያኖች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ የተከታተላቸው ፡ እንደሆነ ፡ የያዙትን ፡ እንዳይነጠቁ ፡ ይከላከላሉ ። አንተ ፡ ግን ፡ እዚሁ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ መጥተህ ፡ ያበሻን ፡ ንጉሥ ፡ ልትወጋው ፡ ደፍረሃልና ፡ የእስላሞች ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳይሆን ፡ ተጠንቀቅ» ፡ አሉት ። ይማም ፡ መልሶ ፡ "በእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ ማድረግ ፡ ለኛ ፡ ለአማኞቹ ፡ ከበድ፡ አይደለም ። እኛ ፡ ምኞታችን ፡ ይህን ፡ የተቀደሰ ፡ ጦርነት ፡ መዋጋት ፡ ነው ። ከኛ ፡ መካከል ፡ የሚሞት ፡ ቢኖር ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሳል ። በሕይወት ፡ የሚኖረው ፡ በደስታ ፡ ይኖራል ። ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ቍጥሩ ፡ የበዛ ፡ ጦር፡ እንዳለው ፡ እናውቃለን ። እኛም ፡ ጦሩን ፡ በጦር ፡ ኃይሉን ፡ በኃይል ፡ ተዋግተን ፡ እግዚአብሔር ፡ ላከበራት ፡ ለዚች ፡ ሃይማኖት ፡ መጋደል ፡ እንፈልጋለን»፡ አላቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የአማጻህ ፡ ሰዎች ፡ አለቀሱ ። የቍራንም ፡ ግልባጭ ፡ በራሳቸው ፡ ይዘው ፡ ? እስላሞቹን ፡ ሁሉ ፡ አክብረው ፡ እስተናገዱና ፡ ድል ፡ አድራጊነትንም ፡ እንዲያገኙ ፡ ተሰሉላቸው ።

ባራተኛው ፡ ቀን ፡ በድሆሀር ፡ ጸሎት ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ጉዞ ፡ አድርገው ፡ ዣን ፡ ዘላቅ ፡ እሚባል ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ ከሰም ፡ የሚባል፡ ተራራ ፡ ነበር ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዳሉበት ፡ ተመለከቱ ። ከዚህ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ፴ ፡ ፈረሰኞች ፡ መርጦ ፡ ወደተራራው ፡ አጠገብ፡ ሄደ ። ከተራራውም ፡ ላይ ፡ አራት ፡ የክርስቲያን ፡ አለቆች ፡ ፶ ፡ ፈረሰኞች ፡ እግረኞችም ፡ ጨምረው ፡ ወረዱ ፡ ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ናስር ፡ (በኋላ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ገብቶ ፡ ያገለገለ) ፡ ነበር ። እስላሞቹ ፡ ጠብቀው ፡ እነዚያ ፡ ሲመጡ ፡ ተዋጉዋቸው ፡ ጦርነቱን ፡ የዠመረው ፡ ሙሐመድ ፡ ቤን ፡ አድሩህ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ አንዱን ፡ የክርስቲያን ፡ ፈረሰኛ ፡ ወግቶ ፡ ጣለው ። ከሌድ ፡ ኤል ፡ ዋራዲም ፡ እንደዚሁ ፡ አደረገና ፡ እስላሞቹ ፡ አሸነፉ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሸሹ . . . . ። እስላሞች ፡ ፲፪ ፡ ፈረሶችና ፡ በቅሎም ፡ ሠንጋም ፡ ማርከው ፡ ይህ ፡ የድል ፡ መዠመሪያችን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ወደሠፈር ፡ ተመለሱ ። በሠፈርም ፡ እሳት ፡ እያነደዱ ፡ ግማሹ ፡ ቍራን ፡ ሲደግም ፡ ግማሹ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የቀረው ፡ ነቢዩን፡ ሲያነሣ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ማርኮ ፡ ነበርና ፡ ስለሀበሻው፡ ንጉሥና ፡ ስለጦሩ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡ «አውራይ ፡

አትማን ፡ ቤን ፡ ዳር ፡ አሊ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ከዚህ ፡ አናንተ ፡ ከአላችሁበት ፡
በማይርቅ ፡ ዱከም ፡ በሚባለው ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ይገኛል ፡ . . . . . . . ንጉሡ፡
ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ግን ፡ ጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ በቤተ ፡ አምሐራ ፡ ናቸው ።
የትግሬ የጦር ፡ ሠራዊትም ፡ መጥቶ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡ ያለው ፡ አለ
ቅዮውም ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ . . . ይባላል ። በርሱም ፡ ውስጥ ፡ ሌሎች ፡ ሹማም
ንት ፡ አሉ ፡ ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ ፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፤ ዋሼ ፡ አትማን ፡ ናቸው ።

እስላሞቹ ፡ ከዛን ፡ ዘላቅ ፡ ተነሥተው ፡ . . . . መስክ ፡ . . . . . ደርሰው ፡
አዳር ፡ አደረጉ ። በማግስቱ ፡ የክርስቲያኖችን ፡ ጦር ፡ አዩ ። ለስለላ ፡ ፈረሰኞች ፡
ወደነዚያ ፡ ሔደው ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ማርከው ፡ ተመለሱና ፡ እይማም ፡ ፊት ፡
አቀረቡዋቸው ፡ እነርሱንም ፡ የክርስቲያኖች ፡ ጦር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለው ፡ ብሎ ፡
ጠየቃቸውና ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በሩቅ ፡ አሳዩት ። አሁንም ፡ ጉዛቸ
ውን ፡ ቀጥለው ፡ ማጅ ፡ (ሞጀ) ፡ እሚባል ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ አፈጠጋር ፡ ውስጥ ፡
ደርሰው ፡ አደሩ ፡ ሌሊቱን ፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስና ፡ ብርድ ፡ ነበር ። በማግስቱ ፡
ማሲን ፡ እሚባል ፡ ኡመር ፡ አቡን ፤ (የሀበሻ ፡ ወገን ? ) ፡ መንደር ፡ ደርሰው ፡
መንደሩንም ፡ የንጉሡንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቃጠሉ ፡ . . . . . በ፫ኛው ፡ ቀን ፡
የንጉሡ ፡ መኖሪያ ፡ ወደሆነው ፡ ሀብቱም ፡ ወደሚገኝበት ፡ ወደ ፡ በደቂ ፡ ደረሱ ።
የክርስቲያኑ ፡ ጦር ፡ ወዴት ፡ እንደሚገኝ ፡ ቢጠይቁ ፡ የሚናገር ፡ ጠፋ ። ሁሉም ፡
እዚህ ፡ እበደቂ ፡ ጦር ፡ የለም ፡ ይል ፡ ዠመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስላሞቹ ፡
ከፈረሶቻቸው ፡ ወርደው ፡ እበቅሎ ፡ ላይ ፡ ተጋብተው ፡ (ተራራማ ፡ ስለሆነ ፡ ይሆ
ናል) ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ እያስጐተቱ ፡ ሳይጠነቀቁና ፡ በሥርዓት ፡ ሳይሆኑ ፡ ወደ
ዚቹ ፡ ከተማ ፡ ሊገቡ ፡ ሲሉ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ወታደሮች ፡ በብዛት ፡ መጡብ
ቸው ፡ . . . . ። ንጉሡ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ እስላሞቹ ፡ እከተማዪቱ ፡ ገብተው ፡
ቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ሳይዠምሩ ፡ ውጊያ ፡ እንዳትዠምሩ
ዋቸው ፡ ብሎ ፡ አዞ ፡ ነበር ፡ , . . . . , ። በደቂ ፡ ከሚገኙት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡
ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ሥርጤ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ (ብሕት ፡ ወደድ ፡ ሠርጼ) ፡
ነው ፡ እርሱም ፡ ደረጃው ፡ እንደዚያው ፡ እንደ ፡ አዝማች ፡ (ራስ) ፡ ደጋልሃን ፡
ነው ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ አዝማች ፡ ማኅፀንቴ ፡ (አምሐ ፡ ጥንት) ፡ ደዋሮ ፡ ነጋሽ ፤
ከሐዲው ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ . . . . . ፤ የፈጠጋር ፡ አዝማች ፡ . . . . . ተክለ ፡
ኢየሱስ ፡ የትግሬ ፡ ገዥ ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ በሀሳብ ፡ ተለያይተው ፡ ክር
ክር ፡ ያዙ ። ግማሾቹ ፡ ከንጉሡ ፡ እንደታዘዝነው ፡ እከተማው ፡ ገብተው ፡ ማቃ
ጠል ፡ ሳይዠምሩ ፡ አንውጋቸው ፡ አሉ ። የቀሩት ፡ የትግሬ ፡ ሹማምንት ፡ እነ ፡ ሮቤል ፡
እነ ፡ እሴር ፡ እነ ፡ አሮን ፡ እነፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ እነዋሼ ፡ አትማን ፡ እስላሞ
ቹን ፡ እከተማ ፡ ገብተው ፡ ቃጠሎ ፡ ሳይዠምሩ ፡ እንውጋቸው ፡ ሁላችን ፡ ሳና
ልቅ ፡ ገብተው ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሊያቃጥሉ ፡ አይገባም ፡ ከአለቅን ፡ በኋላ ፡
ግን ፡ የፈቀዱቸውን ፡ ይሥሩት ፡ ብለው ፡ ለውጊያ ፡ ተቀሰቀሱ ። የቀሩት ፡ አይ
ሆንም ፡ ያሉት ፡ ለብቻቸው ፡ ሆኑ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኃይለኛው ፡ ሮቤል ፡ , . . . . ። አፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ የቀሩትም ፡ የትግሬ ፡ ሹማምንት ፡ እነ ፡ አሴር ፡ እነ ፡ ፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ ተከተሉት ። በነርሱም ፡ ውስጥ ፡ የሚታዘዝ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ አለ ፡ ወደፊት ፡ ተጉዘው ፡ እባደቂ ፡ ከተማ ፡ በር ፡ ደረሱ ፡ በነርሱና ፡ በእስላሞቹ ፡ ጦር ፡ መካከል ፡ ሰመርማ ፡ የሚባል ፡ ወንዝ ፡ ነበር ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እወንዙ ፡ ድረስ ፡ እየተጓዙ ፡ መጡ ። ተዋጊውንም ፡ ወታደር ፡ ማጥቂያውንና ፡ መከላከያውን ፡ (ጦር ፡ ወይም ፡ ጐራዴና ፡ ጋሻ) ፡ መጣሪያ ፡ አሲዘው ፡ ለውጊያ ፡ አሰለፉት ።

እስላሞቹ ፡ ግን ፡ ወደከተማዪቱ ፡ ተጠግተው ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ለውጊያ ፡ ተዘጋጅተዋል ። ይማም ፡ አህመድ ፡ „አፈረሶቻችሁ ፡ ላይ ፡ ውጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለውጊያ ፡ አትጣደፉ ፡ በቶሎ ፡ ለፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ለውጊያ ፡ የሚስማማውን ፡ ሥፍራ ፡ መርምራችሁ ፡ ምረጡ» ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ከንግግሩ ፡ በኋላ ፡ ቪዚር ፡ አዶሌ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሆኖ ፡ ከነጦሩ ፡ እፊት ፡ ቀደመ ። ይማም ፡ ፶ ፡ ፈረሰኞች ፡ . . . . ፤ ሁለት ፡ መቶ ፡ የእግረኛ ፡ ወታደሮች ፡ ጉብዝናቸው ፡ የታወቀ ፡ የተሳለ ፡ ሰይፍና ፡ የሕንድ ፡ አገር ፡ ጋሻ ፡ የያዙ ፤ አስከትሎ ፡ ከኋላ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ ፪፻ ፡ ዠግኖች ፡ በማናቸውም ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ከይማም ፡ ኋላ ፡ የማይለዩ ፡ (ጋሻ ፡ ዣግሬዎች) ፡ ናቸው ። ሁሉም ፡ ለውጊያ ፡ ከተሰለፈና ፡ ፈረሰኛውም ፡ እፈረሱ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ስለሃይማኖታቸው ፡ እንዲዋጉ ፡ ሲል ፡ «እናንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ያላችሁ ፡ ሁሉ ፡ ታጋሽ ፡ ሁኑ ፤ ጦርነቱን ፡ አጥብቃችሁ ፡ ቀጥሉ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፤ በደስታ ፡ እንድትኖሩ ፡ እርግጠኞች ፡ ሁኑ„ እያለ ፡ እስላሞቹን ፡ በዲስኩር ፡ አነቃቃቸው ።

ከርሱ ፡ ቀድሞ ፡ የሄደው ፡ ቪዚር ፡ አዶሌ ፡ ግን ፡ ከነጦሩ ፡ ሁለቱን ፡ ጦር ፡ ይለይ ፡ የነበረውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻገረ ። ወንዙን ፡ መዠመሪያ ፡ የተሻገረ ፡ ሳብራህ ፡ የሚባል ፡ የጋንዝ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። እርሱም ፡ . . . . . . ። በክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ ተወርውሮ ፡ ጦርነቱን ፡ ሲዠምር ፡ የቀሩትም ፡ እስላሞች ፡ እንደአንድ ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተባብረው ፡ ገቡለት ፤ እግረኛውም ፡ ከእግረኛው ፡ ተደባልቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። የቀኙ ፡ ዘማች ፡ ሽሽት ፡ ሲዠምር ፡ የግራው ፡ ዘማች ፡ በአለቆቹ ፡ በነሮቤል ፡ በነ ፡ አሴር ፡ በነ ፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ እየተመራ ፡ ጦርነቱን ፡ በመቀጠል ፡ የጦር ፡ ሰንደቅ ፡ አላማውን ገትሮ ፡ ለምዱን ፡ ጥሩሩን ፡ እንደለበሰ ፡ እንደማይገፋ ፡ ተራራ ፡ ሆኖ ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ መከተ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቀጭኑ ፡ አቡበከር ፡ ከአሮን ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ ይደባደቡ ፡ ዠመር ። አቡበከር ፡ በጦር ፡ ክፉኛ ፡ ወግቶ ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ . . . . . ፡ በጉሮሮው ፡ ወጣ ። አሮን ፡ ግን ፡ ከኮርቻው ፡ ሳይወድቅ ፡ ጠብቆ ፡ ይቀጥል ፡ ዠመር ። አንድ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ አለቃ ፡ ደግሞ ፡ አቡበከርን ፡ ገጠመና ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ መትቶ ፡ ሰበረው ። ነገር ፡ ግን እስላሞቹ ፡ አሥረው ፡ እሥፍረው ፡ መለሱለት ። አንዱ ፡ የእስላሞች ፡ አለቃ ፡ ኩሽም ፡ አቡበከር ፡ ከአንዱ ፡ የክርስቲያኖች ፡ አለቃ ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ በሰይፍ ፡ ትከሻውን ፡ ቢመታው ፡ ክርስቲያኑ ፡ ብረት ፡ ለበስ ፡

የሆነ ፡ ጥሩር ፡ ለብሶ ፡ ነበርና ፡ ምንም ፡ አልሆነም ። ደጋግሞ ፡ ሁለተኛም ፡ ሦስተኛም ፡ ቢመታው ፡ አልሆነለትም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሐዲው ፡ ዋሹ ፡ አትማን፡ አቡበከርን ፡ ደረቱን ፡ ቢመታው ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ በጐኑ ፡ ወጣ ፡ አቡበከር ፡ ግን ፡ ከመገመሪያው ፡ አለቃ ፡ ጋር ፡ ሲደቢደብ ፡ ነበር ። ከኮርቻውም ፡ አልተነቃነቀም ። በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ገራድ ፡ መንሱር ፡ ነፃ ፡ ያወጣው ፡ (ባርያ) ፡ ማርፉ ፡ ናስር ፡ ቤን ፡ አዳም ፡ ...... ፤ ኤስ ፡ ሲዲቅ ፤ ዴል ፡ ሳባር ፡ ሞቱ ። ዲል ፡ ሳባር ፡ በእግሩ ፡ ሆኖ ፡ እፊረስ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ክርስቲያን ፡ እግሩን ፡ ይዞ ፡ ዘርጥጦ ፡ ለመጣል ፡ ሲተናነቅ ፡ ከኋላው ፡ አንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ወታደር ፡ ደርሶ ፡ ከጀርባው ፡ በጦር ፡ ቢወጋው ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ በደረቱ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ ወዲያው ፡ ... ። ሞተ ፡ ...... ። አቡበከርና ፡ ኩሽም ፡ ምንም ፡ ቁስላቸው ፡ ቢጸናባቸው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ የሞቱ ፡ መስሏቸው ፡ ገርባቸውን ፡ አዙረው ፡ ሸሹ ። የቀሩትም ፡ እስላሞች ፡ እነሱን ፡ ሲያዩ ፡ እየሸሹ ፡ ሁሉም ፡ ወደይማም ፡ ሄዱ ። ግማሾቹም ፡ ወንዙን ፡ ሲሻገሩ ፡ እየሰጠሙ ፡ ሞቱ ። ክርስቲያኖቹም ፡ ብዙ ፡ ፈረሶች ፡ በምርኮ ፡ አገኙ ።

ይማም ፡ አህመድ ፡ የሚሸሸውን ፡ ጦሩን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣና ፡ እየተማታ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፡ «ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሸሹት ፡ ? ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ርቃችሁ ፡ ትሸሻላችሁን ፡ ? ዕድል ፡ ከወሰነው ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል» ወዲያው ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ እስላሞቹም ፡ ከየፈረሳቸው ፡ እየወረዱ ፡ እርሱን ፡ ከበው ፡ በኀዘን ፡ ይንጫጩ ፡ ገመር ። ይማም ፡ የተቀመጠበት ፡ ቦታ ፡ ለፈረሰኛ ፡ ጦርነት ፡ የማይመች ፡ ጠባብ ፡ ሥፍራ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ «የእስላሞች ፡ ይማም ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ነቢዩ ፡ መሐመድ ፡ ጓደኞች ፡ እንደ ፡ ዐረቦች ፡ እንዋጋለንና ፡ አሁን ፡ ድንኳንህን ፡ አስተክል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ይማም ፡ ድንኳኑን ፡ በዚች ፡ ሥፍራ ፡ አስተከለ ። የሚሸሹት ፡ እስላሞች ፡ የተተከለውን ፡ ድንኳን ፡ ሲያዩ ፡ ግማሾቹ ፡ ልባቸው ፡ ጸና ። ክርስቲያኖቹም ፡ እስከ ወንዙ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ እስላሞቹም ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ መጥተው ፡ እንዳይጠጉ ፡ ፈልገው ፡ እስላሞቹን ፡ ሲወጉ ፡ ተዋጊዎቹም ፡ መልሰው ፡ ሲመክቱ ፡ ቆዩ ፤ የወንዙ ፡ መሻገሪያ ፡ ሥፍራ ፡ ሦስት ፡ ስለነበረ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ጦሩን ፡ ሦስት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ አንደኛው ፡ ያንኑ ፡ ይማም ፡ ያለበትን ፡ የመከከለኛውን ፡ ሥፍራ ፡ ያዘ ። ሁለተኛው ፡ በሱማሌዎቹ ፡ ባላባት ፡ በማታን ፡ የሚመራው ፡ በቀኝ ፡ ያለውን ፡ የላይኛውን ፡ ያዘ ። ቪዚር ፡ አዶሌ ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የታችኛውን ፡ ያዘ ። እነዚህ ፡ ሦስቱም ፡ የየራሳቸውን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በየሥፍራቸው ፡ መዋጋት ፡ ገመሩ ። በቀኝ ፡ በኩል ፡ ማታን ፡ በሚያዝበት ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲገፉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲመለሱ ፡ ከረፋድ ፡ ገምረው ፡ እስከ ፡ ተስያት ፡ ድረስ ፡ ቆዩ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ማታን ፡ እርዳታ ፡ ላክልኝ ፡ ሲል ፡ አቡበከር ፡ የሚባል ፡ ፈረሰኛ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ላከ ። ይማም ፡ አህመድም ፡ ከፈረሰኞች ፡ ውስጥ ፡ ጎበዝና ፡ ምርጥ ፡ የሆኑትን ፡ ፈረሰኞች ፡ ላከ ፡ እነሱም ፡ ዋናዎቹ ፡ ኤሚር ፡ (ገራድ) ፡ አህሙሹ ፤ ቪዚር ፡ ኑር ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፤ ፋራቃሃም ፡ ሡልጣን ፤ ኢውራይ ፡ ኑር ፤ ፋራቃሃም ፡ ዲን ፡ ቤን ፡ አዳም ፤ ናቸው ።

እነሱም ፡ ሔደው ፡ ከማታን ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ምሽት ፡ እስኪገላግላቸው ፡ ድረስ ፡ በርትተው ፡ ተዋጉ ። የዚህ ፡ ቀን ፡ ውጊያ ፡ በጣም ፡ የበረታና ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ የፈሰሰበት ፡ ውጊያ ፡ ነበር ።

ይማም ፡ አህመድ ፡ በዘመተበት ፡ በመካከለኛው ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ጦርነቱ ፡ የበረታ ፡ ነበር ፡ በርሱም ፡ ግንባር ፡ ሆኖ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ይዋጋ ፡ የነበረው ፡ ኀምዛህ ፡ ኤል ፡ ጁፊ ፡ የሚባል ፡ የዐረብ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ከአግረኛ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ ነበር ፡ ኀምዛህ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ እየተዋጋ ፡ በይማም ፡ ፊት ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ብዙዎቹን ፡ እየመታ ፡ ሲጥል ፡ የወንዙ ፡ ወሀ ፡ ከደም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ቀይነት ፡ ተለወጠ ። ይማምና ፡ አጠገቡ ፡ ያሉትም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ሆነው ፡ ስለርሱ ፡ ብርታትና ፡ ደህንነት ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ጸንቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ምሽት ፡ ገላገለው ።

በግራ ፡ በኩል ፡ ቪዚር ፡ አዶሌ ፡ በአዘመተበት ፡ በኩል ፡ በቀስት ፡ የሚዋጉት ፡ መራሂሃን ፡ የሚባሉት ፡ የሱማሌ ፡ ነገዶች ፡ ነበሩ ፡ እነርሱም ፡ ሲሸነፉም ፡ ሲያሸንፉም ፡ ብዙ ፡ ተዋጉ ። ከክርስቲያኖቹ ፡ ወገኖች ፡ ኤልሚያ ፡ የሚባሉ ፡ መርዘኛ ፡ በሆነ ፡ ቀስትና ፡ ፍላጻ ፡ የሚዋጉ ፡ ነበሩ ።

ይማም ፡ «በቀስት ፡ ፍላጻ ፡ የወረወሩባችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እየለቀማችሁ ፡ ያዙት ፡ እመሬት ፡ የተዋችሁት ፡ እንደሆነ ፡ ደግሞ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ አግኝተው ፡ እየለቀሙ ፡ እንደገና ፡ ለውጊያ ፡ ይጠቀሙበታል» ፡ ብሎ ፡ እስላሞቹን ፡ አዞ ፡ ነበርና ፡ ማታ ፡ የጦርነቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሆኖ ፡ ወደሰፈር ፡ መልስ ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ ኢሚር ፡ ብዙ ፡ እቅፍ ፡ ፍላጻ ፡ እየያዘ ፡ ገባና ፡ እይማም ፡ ፊት ፡ አስቀመጠው ። ይማም ፡ እዋናው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ እዳኬል ፡ ዘንድ ፡ ተሰብስቦ ፡ እንዲቀመጥ ፡ አዘዘ ። ወደ ፡ ማታ ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ላም ፡ ታረደችና ፡ ማብሰያ ፡ እንጨት ፡ ጠፉ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዳኬል ፡ ለጓደኞቹ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡ «ይኸው ፡ ፍላጻ ፡ ነገ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ቢማርኩን ፡ አግኝተው ፡ እንደገና ፡ ከሚጠቀሙበት ፡ ለምን ፡ በዚህ ፡ በፍላጻው ፡ እሳት ፡ አንድደን ፡ ሥጋችንን ፡ አናበስልም» ፡ ጓደኞቹም ፡ እውነትህን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በፍላጻው ፡ ሥጋቸውን ፡ ጠበሱ ፡ . . . . . . . ።

የቀኑም ፡ ጦርነት ፡ ለእስላሞቹ ፡ አዋኪ ፡ ሆኖ ፡ ስለዋለ ፡ አንዳንድ ፡ እስላሞች ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እየከዱ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ዘንድ ፡ ገቡና ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኑ ። አንዳንዶቹም ፡ እየጠፉ ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ መመለስ ፡ ሲጀምሩ ፡ ይማም ፡ በነገር ፡ እየቀሰቀሰ ፡ ለጦርነት ፡ መለሳቸው ። ፈረሶች ፡ ከርቻና ፡ ልባብ ፡ ሳይወርድላቸው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ቆዩ ፡ ይማምም ፡ መሸሽ ፡ ለፈለጉት ፡ «በሌሊት ፡ እየጠፋችሁ ፡ አትሒዱ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ስትሸሹ ፡ እመንገድ ፡ አያገኙ ፡ ይፈጁዋችኋል ፡ ምናልባት ፡ አምላክ ፡ እርዳታውን ፡ ይልክላችኋል ፡ ጠንክሩ ፡ በርቱ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ፍሩ ፡ ምናልባት ፡ ሳታሸንፉ ፡ አትቀሩም› ፡ አላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጧት ፡ ሲነጋ ፡ ድምሩ ፡ ወታደር ፡ ሽሽት ፡ ጀመረ ፡ በይማም ፡ አህመድ ፡ አጠገብ ፡ ከዓርብ ፡ የኀበዝ ፡ ፈረሰ

ኞች ፡ ከጎያ ፡ እግረኛ ፡ በቀር ፡ ባጠገቡ ፡ ጠፋ ። ይማምና ፡ ጓደኞቹ ፡ በራሪዎቹን ፡ ለመመለስ ፡ ሮጡ ። ቀጥሎ ፡ ከነጋ ፡ በኋላ ፡ አሊና ፡ ቪዚር ፡ ኑርን ፡ ቀድማችሁ ፡ እሬት ፡ ሒዱና ፡ ሲሸሽ ፡ የምታገኙትን ፡ እስላም ፡ ሁሉ ፡ ግደሉ ፡ አላቸው ። እነር ሱም ፡ በሩጫ ፡ እሬት ፡ ቀድመው ፡ ዱከም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ የመሸሻውን ፡ መን ገድ ፡ ይዘው ፡ እሬት ፡ ሰው ፡ ገደሉ ። ለቀሩትም ፡ ወዲት ፡ ነው ፡ የምትሸሹት ፡ የሸሻችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ልንገድላችሁ ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብለናል ። ስለዚህ ፡ ተመልሳ ችሁ ፡ ጠንክራችሁ ፡ ተዋጉ ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ስትዋጉ ፡ ብትሞቱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በሕይወት ፡ ብትኖሩ ፡ ደስታን ፡ ታገኛላችሁ ፡ እያሉ ፡ ሲሰብኩዋቸው ፡ ይማም ፡ ደርሶ ፡ ብዙ ፡ የሚሸሹትን ፡ አግኝቶ ፡ ገደለ ፡ አንዳንዶቹንም ፡ አቆሰለ ። ሕግ ፡ አዋቂው ፡ ሊቁ ፡ ሲዲ ፡ አቡበክር ፡ አርሹናህ ፡ «በእግዚአብሔር ፡ ፊቃድ ፡ ቷንሽ ፡ ጦር ፡ ብዙውን ፡ ያሸንፋል ፡ እግዚአብሔር ፡ ጦርነትን ፡ ታግሦ ፡ ከሚቀጥ ለው ፡ ጋር ፡ ነው» ፡ ብሎ ፡ ለሚሸሹት ፡ ከቁራን ፡ ቃል ፡ እየጠቀሰ ፡ ተናገረና ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ እንዲመለሱ ፡ አደረጋቸው ። በዚህ ፡ ቀን ፡ ይኸው ፡ ሲዲ ፡ አቡበከር ፡ እወ ንዙ ፡ አጠገብ ፡ በፍላጻ ፡ ተመትቶ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዳነ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ በበ ኩሉ ፡ ‹የእስላሞች ፡ አገር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ አገር ፡ ሩቅ ፡ አይደለምን ፡ አሁን ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰይፋችሁ ፡ ኃይል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መዳኛ ፡ የላች ሁም ። ከክርስቲያኖች ፡ ፊት ፡ እንዴት ፡ ትሸሻላችሁ ፡ . . . . . . .› እያለ ፡ ተናግሮ ፡ አጸናቸው ፡ አበረታቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሱማሌዎቹ ፡ ነገዶች ፡ የሀርላህ ፡ ነገ ዶች ፡ ናቸው ፡ ያጋለጡን ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ የሀላርላህ ፡ ደግሞ ፡ የለም ፡ የሱማሌ ዎቹ ፡ ናቸው ፡ መገመሪያ ፡ ያጋለጡን ፡ ብለው ፡ መለሱ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ከሦስት ፡ ላይ ፡ ከፋፈለና ፡ ሱማሌዎቹን ፡ ለማታን ፡ የሀርላህን ፡ ለሡልጣን ፡ መሐ መድ ፡ ሰጣቸው ። ሦስተኛው ፡ ለውጊያ ፡ የታመነው ፡ የመለሳይ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ የይ ማም ፡ ዘር ፡ ከነርሱ ፡ ነው ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እሥፍራቸው ፡ ሆነው ፡ እግዚአብሔር ፡ እስላሞቹን ፡ ለማንሣት ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ለማዋረድ ፡ አስቦ ፡ በመካከላቸው ፡ ክር ክር ፡ ተፈጥሮ ፡ ነበር ። ግማሾቹ ፡ እስላሞቹ ፡ ይኸው ፡ መከላከላቸውን ፡ ትተው ፡ ሸሽት ፡ ይዘዋልና ፡ እየተከታተልን ፡ እንውጋቸው ፡ ሲል ፡ ግማሹ ፡ እስላሞቹ ፡ እኛን ፡ ከሥፍራችን ፡ ወጥተን ፡ ወደነርሱ ፡ ስንጠጋ ፡ መልሰው ፡ ለመውጋት ፡ ተን ኰል ፡ አስበው ፡ ነውና ፡ የሸሹትን ፡ በንኩተል ፡ ይሻላል ፡ የቀረው ፡ ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ የያዝነውን ፡ ሥፍራ ፡ ብቻ ፡ አጽንተን ፡ እንያዝ ፡ ንጉሡ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ስለሚገቡ ፡ ድንገት ፡ እስላሞቹን ፡ ስናበርር ፡ የተሸነ ፍን ፡ እንደሆነ ፡ እቅርብ ፡ መሆኔን ፡ እያወቃችሁ ፡ እኔን ፡ ሳትጠብቁ ፡ ለምን ፡ ተዋጋችሁ ፡ ብለው ፡ ይቆጡናል ፡ ስለአሉ ፡ ሁሉም ፡ የነዚህን ፡ የመጨረሻዎቹን ፡ አሳብ ፡ ተቀብሎ ፡ ተቀመጠ ።

## ምዕራፍ ፣ ፲፪ ።

### በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ጦርነት ‑ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መሸነፍ ።

በዚህ ፡ በግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ መተባበራቸው ፡ በገርግንነት ፡ መዋጋታቸው ፡ ሳይቀር ፡ የዘመኑን ፡ የጦርነት ፡ መላ ፡ በጥብቅ ፡ የተከተሉት ፡ አይመስልም ። ከዘመኑ ፡ የጦር ፡ መላ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ መግደል ፡ ነው ። የዚህም ፡ ጠቃሚነቱ ፡ አለቅዬው ፡ ሲሞት ፡ የታመነው ፡ ወታደር ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ በግድና ፡ በውድም ፡ እየታዘዘ ፡ የመጣው ፡ ጦር ፡ አለቃው ፡ ሲወድቅለት ፡ ወይም ፡ ሲወድቅበት ፡ መሸሹ ፡ ስለማይቀር ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ለዚያን ፡ ጊዜም ፡ ለዛሬውም ፡ ጊዜ ፡ በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ የሚያስፈልገው ፡ የስለላ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ለማናቸውም ፡ ለግለኛ ፡ ሰው ፡ ለቀለም ፡ ሰው ፡ ስሜት ፡ ላለው ፡ ፍጡር ፡ የስለላ ፡ ሥራ ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ሲመስል ፡ በኃይሌ ፡ በሥልጣኔ ፡ እኖራለሁ ፡ ጠላቴን ፡ አሸንፋለሁ ፡ ለሚል ፡ ንጉሥና ፡ መንግሥት ፡ የስለላ ፡ ሥራ ፡ ዋና ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መንግሥት ፡ ያዳሎቹንና ፡ የሱማሌዎቹን ፡ የጦርና ፡ የውስጥ ፡ ሁኔታ ፡ እያሰለለ ፡ ከስለላ ፡ በሚያገኘው ፡ ፍሬ ፡ በጣም ፡ የተጠቀመ ፡ አይመስልም ። ባንዳንድ ፡ ነገር ፡ ቢጠቀምም ፡ ብዙ ፡ ሳያውቀውና ፡ ሳይጠቀምበት ፡ የቀረ ሞልቷል ።

ከስር ፡ ከመዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የደዋሮ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፤ ፋኑኤል ፡ ከግራኝ ፡ አህመድ ፡ ተዋግቶ ፡ ግራኝ ፡ ሐረር ፡ ከተመለሰ ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከሐረሩ ፡ ሡልጣን ፡ እየተጣሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መዋጋታቸው ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አለያይተህ ፡ ግዛ ፡ የተባለውን ፡ የሮማውያንን ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በሁለቱ ፡ ጠበኞች ፡ በግራኝ ፡ አህመድና ፡ በሡልጣን ፡ አቡበከር ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ላንደኛው ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ የአንደኛውን ፡ ኃይል ፡ ማድከም ፡ ይችሉ ፡ የነበረውን ፡ ጉዳዩን ፡ መፈተን ፡ አለመፈተናቸውን ፡ አናውቅም ። ከዚያ ፡ የበለጠ ደግሞ ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ጠላትነትና ፡ አጥቂነት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየተገለጠ ፡ ሲሔድ ፡ ይልቁንም ፡ ባሁኑ ፡ በበደቄ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ እነብሀት ፡ ወደድ ፡ ሆርፄ ፤ እነአዝማች ፡ ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፤ እነጸሕፈ ፡ ላም ፡ ሮቤል ፡ ክፉኛ ፡ ተዋግተው ፡ የግራኝን ፡ ኃይል ፡ ሰብረው ፡ ድምሩ ፡ የሱማሌ ፡ ወታደር ፡ የጦርነቱን ፡ ግንባር ፡ አፍርሶ ፡ ሸሽቼ ፡ አገሬ ፡ ልግባ ፡ እያለ ፡ ሲሮጥ ግራኝና ፡ ጓደኞቹ ፡ ተመልሰህ ፡ ተዋጋ ፡ እያሉ ፡ ሲደበድቡት ፡ ይኸን ፡ የተዘበረቀውን ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ አሰልለው ፡ እያበረሩ ፡ በመውጋት ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ አልተጠቀሙበትም ። ይኸም ፡ የሚርቅባቸውና ፡ ምሥጢሩን ፡ ማግኘት ፡ የሚያዳግት ፡ ቢሆን ፡ ግራኝ ፡ ያለበትን ፡ ጦር ፡ እንደምንም ፡ በብዛት ፡ አሸንፎ ፡ ግራኝን ፡ ማጥፋት ፡ ይቻል ፡ የነበረውን ፡ እርሱም ፡ ሲጠፋ ፡ ጦሩ ፡ እንደሚበተን ፡ ግልጽ ፡ የነበረውን ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶቻቸውን ፡ ወደፊት ፡ ባደቄ ፡ ልከው ፡ እያዋጉ ፡ እርሳቸው ፡ ብዙውን ፡ ጦር ፡ እንደያዙ ፡ ቤት ፡

እምሐራ ፡ ቆዩ ። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ እንደገና ፡ እያንሠራራ ፡ የፈረሰውን ፡ ጦር ፡ እያረጋ ፡ ያዔ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ጦር ፡ በየተራ ፡ እየተዋጋ ፡ ለማሸነፍ ፡ አገዘው ።

ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ባለ ፋት ፡ ዓመቶች ፡ በ፲፭፻፲፪ ፡ ዓ ም ፡ ፋትኤልን ፤ በ፲፭፻፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ራስ ፡ ደጋልሃ ንን ፡ ቢያሸንፍ ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ በ፲፭፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ በደቂ ፡ ላይ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ያግሬና ፡ የትግሬ ፡ ጦር ፡ ያሸንፋል ፡ ብለው ፡ የጠረጠሩ ፡ አይመስልም ። ምናልባት ፡ ለማሸነፍም ፡ ቢችል ፡ በጣም ፡ ከደከመ ፡ በኋላ ፡ ነውና ፡ በደከመው ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ የእኔ ፡ አዲስ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ መድረስ ፡ ለድሉ ፡ ዘለቄታ ፡ ፍጻሜ ፡ ይሰጠዋል ፤ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ሳያደርጉ ፡ የቀሩ ፡ አይመስልም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በበደቂ ፡ ያሉት ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንት ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተገነዘብነው ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ውጊያ ፡ ገጥመው ፡ እግባረር ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ በማ ሳደድ ፡ ፈንታ ፡ ንጉሣችንን ፡ ብንጠብቅ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ እከተማዬቱ ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ንጉሡ ፡ እከተማዬቱ ፡ ገብተው ፡ ከነርሱ ፡ ተገናኝተው ፡ የሽምብራ ፡ ኵሬን ፡ ጦርነት ፡ በሚዠምሩበት ፡ ጊዜ ፡ መከከል ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ለሽሽት ፡ የፈረሰውን ፡ ጦር ፡ በኃይልም ፡ በመንፈሳዊና ፡ በዠግንነት ፡ አነጋገርም ፡ መልሶ ፡ አረጋው ። ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ የረጋውም ፡ ጦሩ ፡ ሽሽትን ፡ ያላሰበውን ፡ በን ጉሡ ፡ መሪነት ፡ ለድል ፡ አድራጊነት ፡ ይጠባበቅ ፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ጦር ፡ አሸነፈለት ። ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ አስተያየትና ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ የሚመ ራን ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፈው ፡ የአራብ ፡ ፋቂህ ፡ አጻጻፍ ፡ ነው ።

ከክርስቲያኖቹ ፡ ወገን ፡ ዝርዝር ፡ ጽሑፍ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ የትኛው ፡ የስለላ ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ የጦርነት ፡ መላ ፡ ተሞክሮ ፡ ሳይሳክ ፡ ቀርቶ ፡ መሸ ነፍ ፡ እንደመጣ ፡ ነገሩን ፡ ለማመዛዘን ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ወስደን ፡ ምንም ፡ ቢጥሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድልን ፡ ነሣቸው ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ እን ቀርብ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ለመሰለው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ዓይነተኛ ፡ የሆነውን ፡ ጦርነት ፡ በሰፊው ፡ የሚናገር ፡ ያገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለሌለ ፡ አሳባችንን ፡ በዚሁ ፡ በላይኛው ፡ አስተያየት ፡ ለማቆም ፡ እንገደዳለን ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልና ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ የተዋ ጉበትን ፡ የስመ ፡ ጥሩውን ፡ የሽምብራ ፡ ኵሬን ፡ ጦርነት ፡ ከአራብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደሚከተለው ፡ እንመልከት ።

«እስላሞቹ ፡ በሸሹ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ እፊት ፡ ቀድሞ ፡ አንዲት ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ተገኝቶ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ተዋግቶ ፡ ነበር ፤ ሁሉንም ፡ እስላሞቹ ፡ ፈጅተው ፡ ጨረሱዋቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስላሞቹ ፡ ከተራራው ፡ ወደ ፡ አጃሞጃይ ፡ (የላል ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ) ፡ ደረሱና ፡ በፈጠጋር ፡ ውስጥ ፡ ዝቃላ ፡ (ዝቋላ) ፡ ደርሰው ፡ አወንዞ ፡ አጠገብ ፡ ሠፈሩ ። በዚያም ፡ በቅሎና ፡ ፈረሳቸውን ፡ ወሀ ፡ አጠጡ ፤ ምግ

ብም ፡ አገኙላቸው ፤ ከብቶቻቸውም ፡ ከበሉ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሆኗቸው ፡ ነበር ። እስላሞቹ ፡ እዚያ ፡ በደረሱ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ኤል ፡ ማያ ፡ የሚባሉ ፡ ነገዶች ፡ ንጉሡን ፡ ለመርዳት ፡ ቀስትና ፡ መርዝ ፡ ያለበትን ፡ ፍላጻቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ሲጓዙ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስላምን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማቅናት ፡ ስለፈለገ ፡ የክርስቲያን ፡ ሠፈር ፡ መስሏቸው ፡ ወደ ፡ እስላሞቹ ፡ ሠፈር ፡ ገቡ ። ቍጥራቸው ፡ ከ፫ሺ ፡ ይበልጣል ። እነርሱም ፡ እኛ ፡ ሠፈር ፡ ደርሰው ፡ መሳሳታቸውን ፡ ሲያውቁ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሚገኝበት ፡ ወደ ፡ መሲን ፡ ሽሽት ፡ ጀመሩ ፤ የኛዎቹም ፡ እያባረሩ ፡ ፈጁዋቸው ። የተረፉትንም ፡ ማርከው ፡ አምጥተው ፡ ኢይማም ፡ ፊት ፡ ከአቀረብዋቸው ፡ በኋላ ፡ ተገደሉና ፡ ከሞቱት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ መሬቱ ፡ ሁሉ ፡ ሬሳ ፡ ለበሰ ። የኤልማያዎቹ ፡ አለቃ ፡ ኢይማም ፡ ፊት ፡ እንደተያዘ ፡ ቀረበና ፡ በ፪፻ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ እገዛለሁ ፡ (፪፻ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ከፍለው ፡ ወገኖቼ ፡ ያስለቅቁኛል ) ፡ አለ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አህመድ ፡ ያንተ ፡ ወርቅ ፡ አያስፈልገንም ፡ ግደሉት ፡ ይኸ ፡ ውሻ ፡ የውሻ ፡ ልጅ ፡ ብሎ ፡ መለሰለትና ፡ ተገደለ ። እስላሞቹ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ማሸነፍ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ነበር ።

በክርስቲያኖቹ ፡ ዘንድ ፡ የሆነውን ፡ እንመልከት ፡ ንጉሣቸው ፡ በድሆር ፡ የጸሎት ፡ ሰዓት ፡ በደቄ ፡ ደርሶ ፡ ከጦር ፡ አለቆቹ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ ከሌለው ፡ ወታደሩና ፡ ሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ተገናኙ ። እንደዚህም ፡ አላቸው ፡ ለምን ፡ እስላሞቹ ፡ እከተማዬ ፡ ገብተው ፡ እንዲያቃጥሉ ፡ አልተዋጋችኋቸውም ፡ የትግሬ ፡ ጦርም ፡ «የእህታችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መቃጠል ፡ አይገባትም» ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ይህቺን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህና ፡ አድርጋ ፡ ያሠራች ፡ ዘሩዋ ፡ ትግሬ ፡ የሆነው ፡ የንጉሡ ፡ እናት ፡ (ናዖድ ፡ ሞገሳ?) ፡ ነች ። ስለዚህ ፡ የእህታችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልትቃጠል ፡ አይገባትም ፡ ስለርሷ ፡ እንዋጋለን ፡ እንሞታለን ፤ እከተማዬቱም ፡ እስላሞቹ ፡ እንዳይገቡ ፡ ከለከልናቸው ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ ተናገሩ ። ንጉሡም ፡ ስላደረጉት ፡ ውጊያ ፡ አመሰገናቸው ። ለዋናቹም ፡ ሽልማት ፡ ሸለማቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስላሞችን ፡ ለመፈለግ ፡ በስፋቱም ፡ በቁመቱም ፡ መሬትን ፡ የሚያለብሰውን ፡ ጦሩን ፡ አስከትሎ ፡ ከበደቄ ፡ ወጥቶ ፡ እስላሞች ፡ በሠፈሩበት ፡ ጐን ፡ ሠፈረ ። በዚያ ፡ ሳሉ ፡ በማግሥቱ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የእስላሞቹን ፡ ሁኔታ ፡ ለመሰለል ፡ ሰዎች ፡ ልከው ፡ ነበርና ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ተያዩ ። በ፫ተኛው ፡ ቀን ፡ ሰላዮቹ ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ (ወደ ፡ ሠፈራቸው) ፡ ተመለሱ ። በደሆህር ፡ ጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ሞጄ ፡ (ሞጆ) ፡ ወንዝ ፡ ደረሱና ፡ ከፈረስና ፡ ከበቅሏቸው ፡ ወርደው ፡ ወሀ ፡ አጠጡ ። ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ከሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በኵል ፡ ሠፈሩ ። ይህ ፡ ሰዓት ፡ የረቡዕ ፡ ሌሊት ፡ (ለሐሙስ ፡ አጥቢያ) ፡ የ፱፻፴፭ ፡ (ሺ፭፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ የረገብ ፡ (መጋቢት) ፡ ጨረቃ ፡ የተወለደችበት ፡ ሌሊት ፡ ነበር ። እስላሞቹ ፡ ሁሉ ፡ ሌሊቱን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ሲያነሡ ፡ ሲቀድሱ ፡ አደሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ከጓደኞቹ ፡ መከከል ፡ ተነሥና ፤ እግዚአብሔርን ፡ በክብርና ፡ በምሥጋና ፡ እያነሣ ፡ ስለነቢዩም ፡ እየጸለየ ፡ «ብርቱዎችና ፡

ጽኑዎች ፡ ናችሁ» ፡ ብሎ ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ እንዲታጠቁ ፡ አዘዛቸው ። ቀጥሎም ፡ "በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ፡ የርሱንም ፡ ድጋፍ ፡ ፈልጉ» ፡ ሲል ፡ ሠራዊቱ መሣሪያውን ፡ ይዞ ፡ ጉዞ ፡ ዠመረ ፤ ፈረሰኛውም ፡ እፊት ፡ ቀደመ ። በዚህ ፡ ጊዜ፡ ይማም ፡ «አሳባችሁ ፡ ምንድነው» ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ ጓደኞቹም ፡ "ለኛ ፡ ምኞታችንም ፡ አሳባችንም ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ጠላትን ፡ ገትረን ፡ ከመዋጋት ፡ በቀር ፡ የጦርም ፡ የሰይፍም ፡ በትር ፡ ቢበዛብን ፡ እግዚአብሔር ፡ በዳኝነቱ ፡ በመካከላችን ፡ ፈርዶ ፡ እስኪወስደን ፡ ድረስ ፡ አንላላም» ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። በዚህ ፡ ንግግር ፡ ይማም ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ፡ "እግዚአብሔር ፡ ይርዳችሁ ፤ ይምራችሁም ፡ ለጦርነት ፡ ለውጊያ ፡ መሣሪያችሁን ፡ አንሡ» ፡ አላቸው ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ከጸኑ፡ በኋላ ፡ ጧት ፡ ጐህ ፡ ሲቀድ ፡ ሙኤዲን ፡ (ለጸሎት ፡ ቀስቃሹ) ፡ ወደ ፡ ምግባራችሁ ፡ ሲል ፡ እስላሞቹ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ የጧት ፡ ጸሎታቸውን ፡ አደረሱ ። ሊቁ ፡ ሲዲ ፡ አቡበከርም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በብርታትና ፡ በትዕግሥት ፡ የሚገኘውን ጽድቅ ፡ በፍርሃትና ፡ በሽሽት ፡ የሚመጣውን ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ እየገለጸ ፡ ሰበከ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስላሞቹ ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ መካከል ፡ አድርገው ፡ በምሥራቅ ፡ በከኖጥ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ አማጃህ ፡ (አመጃ) ፡ ሲሔዱ ፡ የሐበሻው ፡ ንጉሥ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ የበረከተ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ በቂብላህ ፡ (ሰሜን ፡ ምሥራቅ) ፡ በኩል ፡ እየተጓዘ ፡ ለአለቆቹም ፡ «እንዳያመልጧችሁ ፡ ያዙዋቸው» ፡ ብሎ ፡ አዞ፡ ነበር ፡ . . . . . ። እስላሞቹም ፡ አዩት ። ክርስቲያኖቹም ፡ ጉዞአቸውን ፡ አቁመው ለውጊያ ፡ ሰልፋቸውን ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ረድፍ ፡ ድረስ ፡ አድርገው ፡ ጫፉ ፡ አይታይም ነበር ። እስላሞቹም ፡ እንደዚሁ ፡ ተሰለፉ ። አንድ ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ጦርነት ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ የነበረ ፡ አዝማች ፡ ሃይቢ ፡ የሚባል ፡ እንደኦጫወተኝ ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ ፲፮ሺ ፡ ፈረሰኛ ፤ ቀስትና ፡ ጦር ፡ ጉራዴ ፡ ይዞ ፡ የሚዋጋው ፡ እግረኛ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ነበር ። . . . . . ። ይማም ፡ አህመድ ፡ ፊት ፡ ቀደመና ፡ በመካከል ፡ በቀኙና፡ በግራ ፡ የሚዘምተውን ፡ አሰለፈ ። «እዚህ ፡ ላለነው ፡ ለሁላችንም ፡ ጽናትን ፡ ስጠን ሃይማኖትህንም ፡ እርዳት» ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ። . . . . . ። ከዚያ ሡልጣን ፡ መሐመድን ፡ . . . . . ፤ ሼክ ፡ ኦንስን ፡ . . . . . ። ለሀርላህ ፡ ለዚሙብራህ ለበርዛህ ፤ ለያቆላህ ፤ ለጃሰር ፡ ለአራብ ተከ ፤ ለአልከ ፡ ነገድ ፡ የበላይ ፡ አድርጎ፡ ሾማቸውና ፡ የቀኙን ፡ ክፍል ፡ ያዙ ። የጂሪ ፤ የመራሂሃን ፤ የዶበሪ ፤ የሱማሌ ፡ ነገዶች ፡ ከባላባቶቻቸው ፡ ከአህመድ ፡ ጀሪ ፡ ጋር ፡ ሐርቲ ፡ ማያቲ ፤ ጂረን ፡ ማዛር ፡ ቤርሱበ ፡ ሁሉም ፡ የሱማሌ ፡ ነገዶች ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ እንዲዘምቱ ፡ አደረገ ። እያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ በየአለቃው ፡ ይታዘዝ ፡ ነበር ። በመካከል ፡ ራሱ ፡ ይማም ፡ አህመድ፡ የኢብራሂም ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ የሚያስፈሩትን ፡ ፈረሰኞቹን ፡ ይዞ፡ ተሰለፈ ። ከዋነኞቹ ፡ ፈረሰኞች ፡ ውስጥ ፡ ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ቤን ፡ አቡበከር ፤ ኤሚር ፡ ዘሀርቡይ ፡ መሐመድ ፡ ፋራቃሃም ፡ አሊ ፤ ወዚር ኑር ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ ኤሚር ሙጋ ፡ ሂድ ፡ ፋራቃሃም ፡ ሡልጣን ፤ አብድ ፡ ኤን ፡ ናስር ፤ ሼክ ፡ ደዋህ ፤ ኤሚር ፡ አቡበከር ፡ ቀጭኑ ፤ ፋራቃሃም ፡ ዲን ፡ ለነዚህም ፡ ይማም ፡ ከቁራን ፡

እየጠቀሰ ፡ ዲስኩር ፡ ተናገራቸው ፡ . . . . . . . ። ከነዚህም ፡ ጋር ፡ የድል ፡ ወምበሬ ፡ ወንድም ፡ የማኅፉዝ ፡ ልጅ ፡ ገራድ ፡ አህማዱሽ ፡ አውራይ ፡ አህመድ ፡ ዴን ፤ ገራድ ፡ ሻሙን ፡ በሻርህ ፤ ሳብር ፡ ኤድ ፡ ድን ፤ ጋሻ ፡ ኡመር ፡ . . . . . ፡ እነዚህን ፡ የመሰሰሉ ፡ ነበሩ ። ይማም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ጦርነት ፡ የዋሉትን ፡ ከርሱ ፡ የማይለዩትን ፡ የውጊያ ፡ ልማድ ፡ ያላቸውን ፡ ፭፻ ፡ ፈረሰኞች ፡ ከፊቱ ፡ አስቀደመ ። እነዚህ ፡ ሃምዛህ ፡ ኤል ፡ ጁፊ ፡ . . . . . ፡ የእግረኛ ፡ ጦር አለቃ ፡ ፊንጂ ፡ ሳባር ፡ . . . . . ። በዚህ ፡ ቀን ፡ ከይማም ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ጦር ፡ ፭፻፷ ፈረሰኛ ፤ ፲፪ሺ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ነበር ። በግራ ፡ የሱማሌ ፡ የሀርቲ ፡ የማይት ፡ ባለሰይፍ ፡ ጦር ፡ ፫፻ ፡ . . . . . ። እንደዚሁም ፡ የይበሪ ፡ ነገድ ፡ ፬፻ ፡ ባለቀስተኛ ፡ ጦር ፡ እነዚህ ፡ ለግምባር ፡ ቀደሙ ፡ ፭፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ጨመረና ፡ ፖፍራችሁን ፡ አጠንክራችሁ ፡ ያዙ ፡ ከመካከላችሁ ፡ አንድም ፡ ጦረኛ ፡ አይራቅ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ . . . . . ። እነዚህም ፡ ደክመው ፡ ስለነበረ ፡ ጽናትን እንዲያገኙ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ (ረቃአህ) ፡ ተጸለየላቸው ። አብደላ ፡ የሚባለው ፡ መንፈሳዊ ፡ ጻድቅ ፡ አዋቂ መምህር ፡ ከበቅሎው ፡ ወርዶ ፡ ጋሻና ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ተንበርክኮ ፡ ጸለየ ። ክርስቲያኖቹን ፡ ሲያይ ፡ እንዳበደ ፡ ግመል ፡ የሚቁነጠነጠው ሀምዛ ፡ ኤል ፡ ዡፊን ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አጥብቀው ፡ ይዘውት ፡ ነበር ። የሀርቲ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በሙሉ ፡ እንደርሱ ፡ ተቅበጥብጠው ፡ ነበሩና ፡ የቀሩት ፡ ቆዩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ወደኛ ፡ ጠጋ ፡ ይበሉ ፡ እያሉ ፡ ይጋብዟቸው ፡ ነበር ።

ክርስቲያኖችም ፡ በሰባት ፡ ረድፍ ፡ ጦራቸውን ፡ አሰልፈው ፡ ወደኛ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ፤ የሐበሻው ፡ ንጉሥ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ከጦሩ ፡ በስተኋላ ፡ ሆኖ ፡ ያዘዝምት ፡ ነበር ። እርሱንም ፡ የሚጠብቁ ፡ ዘበኞች ፡ ፬፻ ፡ በቀኝ ፡ ፬፻ ፡ በግራ ፡ ነበሩትና ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ በየጦሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንዲዋጉ ፡ ከፋፍሏቸው ፡ ነበር ። የደለበውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፤ የዳዊት ፡ ጥሩር ፤ የግብጻውያን ፡ ሰይፍ ፡ የከትን (ሕንድ?) ጦር ፡ አውጥቶ ፡ ለየ ፡ ወታደሩ ፡ አድሎት ፡ ነበር ። የፈረሰኛውም ፡ ጦር ፡ የማይቆጠር ፡ ነው ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የያንዳንዱ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ሰልፈኛ ፡ ወታደር ፡ የእስላማቹን ፡ ፰ ፡ ያህል ፡ ነበር ። ይኸም ፡ ምሳሌው ፡ በአንድ ፡ በጥቁር ፡ ኮርማ ፡ በሬ ፡ ገላ ፡ ላይ ነጭ ፡ እንደፈነጠቀበት ፡ ዓይነት ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አንሥ ፡ እነሱን ፡ (ክርስቲያኖቹን) ፡ አትመልከቱ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተራድኢነት ፡ ለምኑ ፤ በርቱ ፡ ጽኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለእስላሞቹ ፡ ተናገረ ። ክርስቲያኖቹ ፡ ወደ፡ እስላሞቹ ፡ መጠጋት ፡ ሲዠምሩ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ትልቅ ፡ ደመና ፡ በሰማይ ፡ ላይ፡ አንጃበ ፡ ከላቸው ፡ እስላሞቹን ፡ ግን ፡ የሚያቃጥል ፡ ፀሐይ ፡ ይመታቸው ፡ ዠመር። ይኸን ፡ ሲያይ ፡ ይማም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተዋርዶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጸለየ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለዓለማዊው ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ፈጣሪ ፡ የተከበርኸው ፡ ቸሩ ፡ ሆይ ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ የመላክተኛህ ፡ (የመሐመድ) ፡ ና ፡ የነቢያትህ ጠላቶች ፡ ናቸው ፡ አንተ ፡ የምትሰጣቸውን ፡ እየተመገቡ ፡ ከንተ ፡ ውጭ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ ያመልካሉ ፡ አሁን ፡ እነሱን ፡ በደመና ፡ ከልለህ ፡ እኛን ፡ እፀሐይ ፡ ላይ፡ አጋለጥኸን ። »

ይማም ፡ ጸሎቱን ፡ ሳይጨርስ ፡ በክርስቲያኖች ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡
ደመና ፡ ወደ ፡ እስላሞች ፡ መጥቶ ፡ ከፀሐይ ፡ ከለላቸው ፡ ይኸንንም ፡ ክርስቲያ
ኖች ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ተዋጊው ፡ ሰልፈኛ ፡ እየተጠጋጋ ፡ ሄደ ፤ ጦሮች ፤
ወደፊት ፡ አፈጠጡ ። ካህኑ ፡ አቡበከር ፡ እግራኝ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡
እስላሞቹን ፡ ለውጊያ ፡ እየለመነ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ የተናገረው ፡ ዲስኩር ፡
የሰውን ልብ ፡ ሁሉ ፡ አንቃንቀው ፡ ዓይንንም ፡ በእንባ ፡ አራሰ ። "የእስላም ፡ ሠራ
ዊት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያበራል ፤ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ተዘግቷል ። መላእክት ፡
ከላይ ፡ ከሰማይ ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከቷችኋል ፤ ዓይናቸው ፡ የጠቋቆረው ፡ ቆንጆ
ኘሮች ፡ ሴቶች ፡ (ሁሪ ፡) አጊጠዋል ፤ በዘለዓለማዊው ፡ ሕይወት ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። „

ከዚያ ፡ ከቁራን ፡ ውስጥ ፡ «እግዚአብሔር ፡ አማኞችንና ፡ ሀብታቸውን ፡ በመ
ንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለወጠው ፤ በእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ይዋጋሉ ፡ ይገድላሉ ፡
ይገደላሉ ፡ . . . . . . . . » የሚለውን ፡ አውጥቶ ፡ ደገመ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስ
ላሞቹ ፡ "እንግዲህ ፡ ሮጠን ክርስቲያኖቹን ፡ እንግጠማቸው„ ፡ ብለው ፡ ይማ
ምን ፡ ጠየቁት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ «እነርሱ ፡ ሲዋጉዋችሁ ፡ ተቀበሉ ፡ እንጂ ፡ እና
ንተ ፡ አትገምሩ„ ፡ ሲል ፡ ከለከለና ፡ ይልቅስ ፡ «ሥፍራችሁን ፡ አጠንክራችሁ ፡
ያዙ ፡ ጦራችሁን ፡ ደግኑ ፡ በጋሻችሁ ፡ ሰውነታችሁን ፡ ከልሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ስም ፡ ሳታነሡ ፡ አንድም ፡ እርምጃ ፡ አትራመዱ ፡ እስላም ፡ ሆይ ፡ ድልን ፡ የሚ
ያገኙ ፡ ታጋሾች ፡ ጽኑዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ፈሪና ፡ ልል ፡ ወራዳ ፡ ተሸናፊ ፡
መሆኑን ፡ እወቁ ፡ ጽኑውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረደዋል ፡ ዛሬ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ የሰ
ይፍን ፡ ውጊያ ፡ ቃማሰ ፡ የጻና ፡ ነገ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ከዚያም ፡
ወዲያ ፡ ድካም ፡ የለበትም ፡ . . . .„ እያለ ፡ እየደጋገመ ፡ ሲናገር ፡ ክርስቲያ
ኖቹ ፡ ሥፍራቸውን ፡ ለቀው ፡ ለውጊያ ፡ መጡ ፡ ብዙ ፡ ሆነው ፡ ሰይፋቸውን ፡ እያ
ብለጨለጩ ፡ ሲመጡ ፡ እስላሞቹ ፡ አዩዋቸው ። ንጉሡ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ . , .
. . «ተዋጉ» ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ እንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሆነው ፡ ከእስላም ፡
ጦር ፡ ከቀኙ ፡ ዘማች ፡ ጋር ፡ ገጠሙና ፡ ይወጉዋቸው ፡ ገመር ፡ እስላሞቹም ፡ ጸን
ተው ፡ ያዙ ። እንደዚሁም ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ የቀኝ ፡ ዘማች ፡ ከእስላሞቹ ፡ ከግራው ፡
የሱማሌ ፡ ዘማች ፡ ጋር ፡ ተጋጠመ ። የትግሬ ፡ ጦር ፡ ከነሹማምንቱ ፡ ይማም ፡
ያለበትን ፡ መከከለኛውን ፡ ሰልፍ ፡ ገሥግሰው ፡ ይዘው ፡ ይዋጉ ፡ ገመር ። ይማ
ምና ፡ ጓደኞቹም ፡ የእስላምነት ፡ ልባቸውን ፡ አጠንክረው ፡ ተቀበልዋቸው ። የጦር ፡
ሠራዊት ፡ ተደበላለቀ ፤ ሰይፎች ፡ ተመዘዙ ፤ ጦሮች ፡ ተገተሩ ፡ መለዮና ፡ የጦር ፡
ምልክት ፡ ተሰቀሉ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማዎች ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ አውለበለቡ ። ልጓም ፡
ከልጓም ፡ ተጋጨ ። ፈረሶች ፡ ጮኹ ፡ (አስካኩ) ። ትልቅ ፡ አቧራ ፡ ተነሣ ። ከመ
ሣሪያው ፡ ክብደት ፡ የተነሣ ፡ በተዋጊው ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ላብ ፡ ተንቆረቆረ ።
ይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ድምጡ ፡ እያስተጋባ ፡ የሚሰማው ፡ የሁለቱም ፡ ጦር ፡ ሠራ
ዊት ፡ የሰውና ፡ የፈረስ ፡ ጩኸት ፡ ልጓምና ፡ ልጓም ፡ እየተጋጨ ፡ ሰይፍና ፡ ጋሻ ፡
እርስ ፡ በርሱ ፡ ተደበልቆ ፡ ሲራኮት ፡ በዚህ ፡ መከከል ፡ አንድ ፡ ተናጋሪ ፡ «የመ

ሐመድ ፡ ወገኖች ፡ ቲንሽ ፡ በርቱ ፡ ብዙ ፡ ታገኛላችሁ ፤ ዓይናቸው ፡ የጠቆረው ፡ ቆንገዦች ፡ ሴቶች ፡ (ሁሪ) ፡ በሰይፋችሁ ፡ ጥላና ፡ በጦራችሁ ፡ ጫፍ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ጮኽ ፡ ተናገረ ።

ይማም ፡ አህመድና ፡ ጓደኞቹ ፡ ጠንክረው ፡ ያዙ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ይማም ፡ የክርስቲያኖች ፡ ጦር ፡ በዝቶ ፡ ወደሚዋጋበት ፡ ወገን ፡ ዘሎ ፡ ሄደና ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጨረሰ ፡ የድሉ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ ይውለበለብ ፡ ነበር ። በግራ ፡ በኩል ፡ የሱማሌው ፡ ተዋጊ ፡ ግን ፡ ጦርነቱ ፡ መበርታቱን ፡ ሲያይ ፡ ሸሽት ፡ ዠመረ ። ክርስቲያኖቹም ፡ እየተከታተሉ ፡ ብዙ ፡ ፈጁላቸው ። ብዙም ፡ ማረኩ ። የሞቱት ፡ ፫ሺ ፡ ይደርሳሉ ፡ አለቆቻቸው ፡ የይማም ፡ አማች ፡ ማታን ፡ ቤን ፡ ኦትማንና ፡ ሌሎቹም ፡ እንአህመድ ፡ ጉራይ ፤ እንኦሊ ፡ ገራድ ፡ የማታን ፡ ወንድም ፡ . . . . . በጉብዝና ፡ ተዋጉ ። እነሱም ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ትተዋቸው ፡ ሲሸሹ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ተዋጉ ። የሀርላህ ፡ ነገዶች ፡ በሚዋጉበት ፡ በቀኙ ፡ መሥመር ፡ የመዠመሪያው ፡ የሁለተኛው ፡ የሦስተኛው ፡ ረድፍ ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ እየተከታተለ ፡ ወጋቸው ፡ ጦርነቱም ፡ እንደወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ ይዞር ፡ ዠመር ። የተዋጊዎቹ ፡ ጭንቅላት ፡ ተደበደበ ፡ ሀበሾችም ፡ በቀኙ ፡ የእስላም ፡ ዘማች ፡ ላይ ፡ ጸንተው ፡ ተዋጉ ፤ እነሱም ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ተከላከሉ ። ሌላ ፡ አዲስ ፡ የክርስቲያኖች ፡ ጦር ፡ እየጨመረ ፡ ስለ ወጋቸው ፡ እያፈገፈጉ ፡ የይማም ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ እስከ ፡ ሚገኝበት ፡ እስከ ፡ መከከል ፡ ድረስ ፡ መጡ ። እዚያ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ ተደረገ ። የባሕር ፡ ወታደሮች ፡ (ቱርኮችና ፡ ዐረቦች ፡ ሲል ፡ ነው) ፡ የፈረሶቻቸው ፡ ቅልጥም ፡ እስኪታጠፍ ፡ (በድካም) ፡ ወፍራም ፡ አቧራ ፡ ቆሞ ፡ እስኪሄድ ፡ ድረስ ፡ በኃይል ፡ ተዋጉ ። እስላሙም ፡ ክርስቲያኑም ፡ ጓደኛውን ፡ አያውቅም ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ አያይም ፡ ነበር ። ሀበሾቹ ፡ በሚያባርሩዋቸው ፡ እስላሞች ፡ ላይ ፡ እስኪወድቁ ድረስ ፡ ጦርነቱ ፡ ዘገየ ። በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቆጠር ፡ ሰው ፡ ሞቶ ፡ መሬቱ ፡ በሰው ፡ሬሳ ፡ ተሸፈነ ። በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ቁስለኛው ፡ በረከተ ፡ ይልቁንም ፡ በክርስቲያኖቹ ዘንድ ፡ . . . . . ። ጦርነቱ ፡ ከጧት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አስር ፡ ጸሎት ፡ (ማታ) ፡ ድረስ ፡ ቆየ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታላቅነትና ፡ አንድነት ፡ እያነሱ ፡ ጮኹ ፡ ለመሐመድም ፡ . . . . . ሰላምታ ፡ አቀረቡ ። እግዚአብሔርም ፡ ድል ን ፡ ሰጣቸው ፡ በጠላቶቻቸውም ፡ ልብ ፡ ፍርሃትን ፡ አሳድሮ ፡ እንዲሸሹ ፡ አደረጋቸው ፡ . . . . . . . . ።

በዚህ ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ የክርስቲያን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ሞቱ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ አዝማች ፡ (ጸሐፊ ፡ ላም) ፡ ሮቤል ፡ (ትግሬው) ፡ በይማም ፡ አሽከር ፡ በአራዲ ፡ እጅ ፡ ሞተ ። ኤግበ ፡ (ዕቁበ፡ወይም፡አግብአ?) ሚከኤል ፡ የሚባለው ፡ ጉበዙና ፡ አስፈሪው ፡ የሮቤል ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ፡ ይማም ፡ ራሱ ፡ በጦር ፡ የገደለው ፡ . . . . . . . ፤ ሁለት ፡ የንጉሡ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ (ስልቦች) ፡ ስማቸው ፡ ጃውሄርና ፡ መንዲል ፤ ሁለቱም ፡ የንጉሡን ፡ ባንዲራ ፡ በራሳቸው ፡ ይዘው ፡

ነበር ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ አድርገው ፡ ይገምቷቸዋል ፡ (ሊቃነ ፡ መኳስ ፡ ናቸው ፡ ማለቱ ፡ ነው) ፡ ጃውሄርን ፡ የገደለው ፡ ኤሚር ፡ መሐመድ ፡ የኤሚር ፡ መሐመድ ፡ ቤን ፡ ዘሀርቡይ ፡ አትማን ፡ ልጅ ፡ መንዲልን ፡ የገደለው ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ የሚባል ፡ የሲም ፡ ፈረሰኛ ። የሲሬን ፡ (ሺሬ) ፡ ሹም ፡ ገራድ ፡ ዲን ፡ ገደለው ። ለንጉሡ ፡ በናቱ ፡ በኩል ፡ የሚዘመደው ፡ ትልቁ ፡ አዝማች ፡ ዮናኤል ፡ የሚባለውን ፡ ገራድ ፡ ሻሙን ፡ እጁን ፡ ቆረጠው ፡ በኋላውም ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ በጦር ፡ ወግቶት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አምልጦ፡ ሄደ ። አትማን ፡ ሼክ ፡ ዣን ፡ በለው ፡ ራስ ፡ ከሚባለው ፡ ጥሩር ፡ ከለበሰው ፡ ጋር ፡ ተማቶና ፡ አትማን ፡ ጥሩሩን ፡ በሰይፍ ፡ ሲመታው ፡ ግማሹ ፡ እሰውነቱ፡ ላይ ፡ ቀርቶ ፡ ግሚሱ ተቆርጦ እመሬት ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። የጸለምትን ፡ ሹም ፡ አንድ ፡ እስላም ፡ ገደለው ፤ አዝማች ፡ ገብረ ፡ መድኅንን ፡ አንድ ፡ ጥርስ ፡ የሌለው፡ አውማይደህ ፡ ገደለው ። አዝማች ፡ ዘመንጃ ? ፡ የሚባለውን ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ዘመድ ፡ ሺዚር ፡ አዶሌ ፡ ገደለው ። አዝማች ፡ (ራስ) ፡ ማኅፀንቴን ፡ አንድ ፡ የቀስተኞች ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ አዳም ፡ የሚባል ፡ ሱማሌ ፡ ገደለው ። . . . . . . . አዝማች፡ ዋጋሙህ ፡ በተክላይ ፡ እጅ ፤ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዘወንጌል ፡ የድሆኖ ፡ ጌታ ፡ በአብድር፡ እዘክ ፡ ቤን ፡ ሶሃል ፡ እጅ ፡ ተገደለ ። የአንጎሜ ፡ የሸጋራ ፡ (ወገራ) ፡ ሹም ፤ የተምቤን ፡ ሹም ፡ ሞቱ ። የአበርጋሌ፡ ሹም ፡ አዝማች ፡ (ራስ) ፡ አምዱ ፡ በአንድ ፡ የእስላም ፡ የእግረኛ ፡ ወታደር ፡ አዳሙ ፡ በሚባል ፡ እጅ ፡ ተገደለ ። የሞቱት ፡ የትግሬ ፡ ሹማምንት ፡ ብቻ ፡ ቁጥራቸው ፡ ፶፯ ፡ የተራው ፡ የትግሬ ፡ ወታደር ፡ ፲ሺ ፡ ይደርሳል ። ፻፳፫ ፡ የሌላ ፡ አውራጃ ፡ ሹማምንት ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ጦርነት ሞቱ ። እነዚህም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንዱ ፡ ፩ሺ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሌላው ፡ ፭፻ ፡ አንዱ ፡ ፯፻ ፡ ወታደር ፡ የየራሳቸው ፡ ጭፍራ ፡ ነበራቸው ። ፈረሰኛ ፡ ተደባልቆ ፡ በሚዋጋበት ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ፯፻ ፡ የክርስቲያኖችን ፡ የፈረስ ፡ ቋንዣ ፡ በሰይፍ ፡ ሰበሩ ።

ከእስላሞች ፡ ወገን ፡ የሞቱት ፡ ሀምዛሀ ፡ ኤል ፡ ጁፊ ፤ ሀዲድ ፡ (ጀዲድ) ኮርጁህ ፤ ከቢር ፡ ኢብራሂም ፡ . . . . . . . . . ፤ የሲም ፡ ወገን ፡ ሕግ ፡ አዋቂና ፡ ሰባኪው ፡ መሐመድ ፤ ዳሉ ፡ ባሊ ፤ መሐሙድ ፡ ደዋሮ ፤ የሞተው ፡ የሱማሌ ፤ የሀርላህ ፡ የመለሳይ ፤ የዐረብ ፡ ወታደር ፡ ቁጥር ፡ ፭፻ ፡ ይደርሳል ።

ቁጥር ፡ ሥፍር ፡ የሌለው ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ፈረስ ፤ ጥሩር ፤ ሰይፍ ፤ ጦር ፡ እስላሞቹ ፡ ማረኩ ። አንድ ፡ የንጉሡ ፡ አማች ፡ የሆነ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ተክለ ፡ መድኅን ፡ የሚባል ፡ ተማርኮ ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ አገር ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ወገኖቹ ፡ ፭፻ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ከፍለው ፡ አስመለሱት ። ስለዚህ ፡ ይማም ፡ መሐመድ ፡ ይኸን ፡ አሸናፊነት ፡ ከአገኘ ፡ ወዲህ ፡ በደስታ ፡ በክብር ፡ ተመልሶ ፡ በረጅብ ፡ ወር ፡ ሐረር ፡ አገሩ ፡ ገባ ። ወደ ፡ ሐረር ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ ይኸን ፡ (የሽምብራ ፡ ኩሬ) ፡ ድል ፡ ወዲያው ፡ እንዳገኘ ፡ ባጠገቡ ፡ ላሉት ፡ የእስላም ፡ ሹማምንት ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፡ «ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ ረድቶ ፡ ጠላቶ

ቻችንን ፡ አዋረደ ፤ አሁን ፡ የንጉሡ ፡ ከተማ ፡ ወደሆነችው ፡ ወደ ፡ ባደቄ ፡ እንሂድና ፡ እናፈራርሳት ፡ ባገሪቱም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቀምጠን ፡ እየመታን ፡ እየተዋጋን፡ ጠላቶቻችንን ፡ እናድክማቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሹማምንቱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱ ፡ «የእስላሞች ፡ ይማም ፡ ሆይ ፡ የደረሰብንን ፡ ሁሉ ፡ አታይምን ፡ እነሆ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮቻችን ፡ ሞቱ ፤ እኛም ፡ በቁስል ፡ ተሸፍነናል ፤ ያለን ፡ ስንቅ ፡ ቲኒሽ ፡ ነው። አሁን ፡ ይበቃናልና ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ተመልሰን ፤ አገራችን ፡ አርፈን ፡ እንደገና ፡ ወታደሮቻችንን ፡ አደራጅተን ፡ ሁለተኛ ፡ መጥተን ፡ እንዋጋለን ። ቀርተን፡ እንዋጋለን ፡ ብለህ ፡ ካዘዝኸን ፡ ግን ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ እንቀራለን።»

የዚህን ፡ መልስ ፡ ሲሰማ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ከሹማምንቱና ፡ ከጦሩ ፡ ጋር ፡ ተመልሶ ፡ ሐረር ፡ ገባ ፡ በዚያም ፡ የሸባንን ፡ የራማዳንን ፡ በዓል ፡ ውሎ ፡ እስከ ፡ ሻዋል ፡ አጋማሽ ፡ ድረስ፡(ሚያዝያ ፡ ግንቦት ፡ ሰኔ፡ አጋማሽ ፡) ቆየ»።

የሽምብራ ፡ ኵሬን ፡ ጦርነት ፡ እነሆ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እየተረከ ፡ ይጨርሳል ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ የተደረገበት ዘመን ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ፡ መጋቢት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ሺ፭፻፳፩ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ በሆነው ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ የጦርነት ፡ አውድማ ፡ ላይ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር ላይ ፡ አሸናፊነትን ፡ ማግኘቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ላፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ገና ፡ ያልተሸነፈ ፡ ጦር ፡ በባሌ ፡ በደዋሮ ፡ በፈጠጋር ፡ አላቸው ። በዚህ ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ ንጉሡ፡ ተሸነፉ ፡ ግራኝ ፡ አሸነፈ ፡ ቢባልም ፡ የተጋጠመው ፡ ጦር ፡ የተለያየበትን ፡ ሁኔታ፡ ለመግለጽ ፡ ነው እንጂ ፡ አሸናፊው ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ተሸናፊውን ፡ የንጉሡን ፡ ጦር፡ እንኳን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ማባረር ፡ ይቅርና ፡ ለጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ቅርብ ፡ የሆነውን፡ የባደቄን ፡ ከተማ ፡ እንኳን ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ለመያዝም ፡ ለማፍረስም ፡ አልሆነለትም። ይኸንንም ፡ ከተማ ፡ ከመፍረስ ፡ ያዳነው ፡ ባለፈው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደተገነዘብነው ፡ የንጉሡ ፡ የጦር ፡ ወታደር ፡ ይልቁንም ፡ የትግሬ ፡ ሹማምንት ፡ ከነጭፍሮቻቸው ፡ በእስላሞቹ ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ጉዳት ፡ የተነሣ ፡ ሹማምንቱ ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ ባለመቻላቸው ፡ ነው ። ባለፈው ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ግራኝ፡ አህመድና ፡ ሰባኪው ፡ ሊቅ ፡ ሲዲ ፡ አቡበክር ፡ የበረከተውን ፡ የሱማሌ ፡ የአዳል፡ ነገድ ፡ ባንድ ፡ በግራኝ ፡ ውስጥ ፡ እንዲያብር ፡ ከማድረጋቸውም ፡ በቀር ፡ በውጊያ፡ ሰዓት ፡ ድልን ፡ የሚያስገኘው ፡ ዋነኛው ፡ ጉዳይ ፡ ጸንቶ ፡ በርትቶ ፡ ውጊያውን ፡ መቀጠል ፡ መሆኑን ፡ በየጊዜው ፡ ተዋጊው ፡ ጦር ፡ የሚያምንበትን ፡ መንግሥት ፡ ለማያትንና ፡ በዚያ ፡ የሚገኙትን ፡ ቆነጃጅትን ፡ ተስፋ ፡ እያስደረጉ ፡ በመንፈሳዊም፡ በሥጋዊም ፡ ምክር ፡ አንጸውታል ። እንኳን ፡ ከውጊያው ፡ በፊት ፡ ሁለቱ ፡ የጠላት፡ ወታደሮች ፡ እግረኛው ፡ ከእግረኛ ፡ ፈረሰኛው ፡ ከፈረሰኛ ፡ ተደባልቆ ፡ በሚከታከትበት ሰዓት ፡ አንድ ፡ የእስላም ፡ ተናጋሪ፡ «የመሐመድ ፡ ወገኖች ፡ ትንሽ ፡ በርቱ፡ ብዙ ፡ ታገኛላችሁ ፡ ዓይናቸው ፡ የጠቆረው ፡ (የተኳለው) ፡ ቆንዣዥቱ ፡ ሴቶች ፡ (ሁሪ) ፡ በሰይፋችሁ ፡ ጥላና ፡ በጦራችሁ ፡ ጫፍ ፡ ናቸው» ፡ ብሎ ጮኸ ፡ በመና

ገር ፡ ተዋጊዎቹን ፡ ለውጊያ ፡ እንዳጸናቸው ፡ እንብበናል ። ይህ ፡ የሰማያዊ ፡ ኑሮ ፡ ተስፋ ፡ ለተዋጊው ፡ ወታደር ፡ ሊሸነፍ ፡ ለቀረበውም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ የተዋጊ ነት ፡ መንፈስ ፡ ይቀሰቅስለታል ። ከክርስቲያኖቹ ፡ ወገን ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ቄስ ፡ ሐጼው ፡ ንጉሡም ፡ ራሳቸው ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ክርስቲያናዊና ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ የተዋጊውን ፡ ወታደር ፡ መንፈስ ፡ አነቃቅተውት ፡ እንደሆነ ፡ አናውቅም ። ያለዚያ ፡ እስላሞቹ ፡ በደረጉት ፡ ቲንሽ ፡ ብርታት ፡ ላይ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ደግሞ ፡ የራሳቸውን ፡ ቲንሽ ፡ ጽናት ፡ ጨምረው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የድል ፡ አድራጊነቱ ፡ ዋንጫ ፡ በነሱ ፡ እጅ ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር ፡ ሳይበረክት ፡ አይቀርምና ፡ የበረከተውን ፡ ጦር ፡ የጦር ፡ መላና ፡ ጉብዝና ፡ ጽናት ፡ ሲተባበርበት ፡ ድልን ፡ ከማግኘት ፡ አይዘልም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የግራኝ ፡ መሐመድና ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ መሪነት ፡ ለየቅሉ ፡ የሆነ ፡ ይመስላል ። ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሱ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ እንደሚያስረዳን ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜአቸውን ፡ ሁሉ ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ በማን በብ ፡ ወይም ፡ ስለመጽሐፍና ፡ ስለቀለም ፡ ጉዳይ ፡ ከሊቃውንት ፡ ጋር ፡ በመ ነጋገር ፡ ሲያሳልፉ ፡ የኖሩ ፡ ከጦር ፡ ሰውነት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ቀለም ፡ ሰውነት ፡ ያዘነበሉ ፡ ሲሆን ፡ ወጣቱ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ግን ፡ ከቀለም ፡ ሰውነት ፡ ይልቅ ፡ የተዋጊነትና ፡ የአዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ የሞላው ፡ የእስላሞቹን ፡ ተጠቂነት ፡ የክርስ ቲያኖችን ፡ አጥቂነት ፡ ለመበቀል ፡ ከሚስቱ ፡ ከድል ፡ ወምበራና ፡ ከሹማምንቱ ፡ ጋር ፡ ከልብ ፡ ቆርጦ ፡ የተነሣ ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከነአቡበከር ፡ ሡልጣን ፡ ጋር ፡ ባገር ፡ ውጭ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ከነፋኑኤል ፡ ከነደጋልሃን ፡ ጋር ፡ ያለዕረፍት ፡ እየተ ዋጋ ፡ መሸነፍ ፡ ተስፋ ፡ የማያስቆርጠው ፡ ማሸነፍን ፡ ክብርን ፡ ሥልጣንን ፡ ግዛትን፡ ገና ፡ ያልጠገበ ፡ ምኞቱን ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ያላደረሰ ፡ አፍላ ፡ የጦር ፡ መሪ፡ ነውና ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለ ፡ ልዩነት ፡ በሁለት ፡ መሪ ፡ መከከል ፡ ሲገኝ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የድል ፡ አዝማሚያውና ፡ ዝንባሌው ፡ አፍላና ፡ ፈቃደኛ ፡ ደፋርና ፡ ወጣት ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወገን ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እስክንድርም ፡ ናፖሌዎንም ፡ ወደድል ፡ ጐዳና ፡ የተጓዙት ፡ በዚህ ፡ መሥመር ፡ ነው ።

የግራኝ ፡ አህመድን ፡ ዓይነት ፡ መንፈስ ፡ ጉብዝናና ፡ ድፍረት ፡ የነበረው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ነበር ። ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ተነሥቶ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እውነተኛው ፡ የመረረ ፡ ወይም ፡ የከረረ ፡ ጦርነት ፡ ሆኖ ፡ የመጨረሻው ፡ ዠግና ፡ ይለይ ፡ ነበር ።

እንዳሁኑ ፡ እንደ ፡ ግራኝ ፡ ሳብር ፡ አድ ፡ ዲን ፡ (ሰብረዲን) ፡ መሐመድ ፡ የይፋትን ፡ የአዳልንና ፡ የሱማሌን ፡ ነገድ ፡ በሙሉ ፡ አሥነስቶ ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ወጣቱና ፡ ዠግናው ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ በየጦሩ ፡ ጐራ ፡ ላይ ፡ አሸንፎ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ እስከ ፡ አልደረሱበት ፡ እስከ ፡ ሱማሌ ፡ አገር ፡ ዘልቆ ፡ አሳምኖ ፡ እንደተመለሰ ፡ ታሪኩን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በ፪ኛው ፡ መጽሐፌ ፡ ከገጽ ፡ ፺፩-፺፯ ፡ ገጽ ፡ ድረስ ፡ ተመልክተናል ።

አፄ፡ ዓምደ ፡ጽዮን፡ ድሉን፡ እስከ፡ መጨረሻ፡ ለማዝለቅ፡ ጠላቶቹን ፡ ድሉን ፡ እስከ፡ ፍጻሜ ፡ አሸንፎ ፡ ለማስገበር ፡ ወደፊት ፡ እንግፋ ፡ ሲል ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ያለፈን ፡ ድል ፡ አድራጊነትንና ፡ የወደፊቱን ፡ የበረሀ ፡ ጉዞ እያመከኙ ፡ እንግዴህ ፡ ይበቃናል ፡ ያሉትን ፡ አሁንም ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ጦርነቱን ፡ እንቀጥል ፡ ሲል ፡ ሹማምንቱ ፡ ይብቃን ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ እንመለስ ፡ ከሚሉት ፡ ጋር ፡ ስናመዛዝነው ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ የግራኝ ፡ አህመድን ፡ የጉብዝና ፡ ተመሳሳይነት ፡ ወደ መገንዘብ ፡ እንደርሳለን ።

ጦርነቱ ፡ ሊዠመር ፡ ሲል ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ የወታደሩን ፡ ወኔ ፡ ወይም ፡ መንፈስ ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግሣፅና ፡ ምክር ፡ የጦር ፡ መላና ፡ ዘዴ ፡ በተደባለቀበት ፡ አነጋገር ፡ የሰበከውን ፡ እናስታውስ ።

«የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ሳትነሡ ፡ አንድም ፡ እርምጃ ፡ ወደፊት ፡ አትራመዱ ። በጠላቶቻችሁ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እርዳታ ፡ ጠይቁ ።

ውጊያውን ፡ ተቀበሉ ፡ እንጂ ፡ እናንት ፡ አትዠምሩ ። ዛሬ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ታግሦ ፡ የተዋጋ ፡ ነገ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።»

በዋናው ፡ መሪ ፡ በግራኝ ፡ ንግግር ፡ ጐን ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪ ፡ ካህኑ ፡ አቡበከር ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለናንት ፡ ለምትዋጉት ፡ ክፍት ፡ ነው ፤ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ተዘግቷል ፤ መላእክት ፡ ከሰማይ ፡ ሆነው ፡ ቁልቁል ፡ ይመለከቷችኋል ፤ ዓይናቸው ፡ የጠቋቆረው ፡ ቆንዦችት ፡ በዘለዓለማዊው ፡ ሕይወት ፡ ተጊጠው ፡ ይጠብቋችኋል ፡ እያለ ፡ ሥጋ ፡ ለባሲ ፡ የሚፈልገውን ፡ ተስፋ ፡ በመስጠት ፡ የሁለቱ ፡ የሥጋዊና ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪዎች ፡ ንግግር ፡ ተባብሮ ፡ ተዋጊውን ፡ የሱማሌና ፡ የአዳል ፡ ሕዝብ ፤ ለእርዳታ ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ የመጡትን ፡ ጭምር ፡ መንፈሳቸውን ፡ ቀስቅሶ ፡ ጠንክረው ፡ እንዲዋጉ ፡ ድልንም ፡ እንዲያገኙ ፡ አደረጋቸው ።

ጸሐፊው ፡ አራብ ፡ ፈቂህ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ የውጊያውን ፡ ታላቅነት ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ ጽኑ ፡ ግድያ ፡ ሲተርክ ፡ «ልጓም ፡ ከልጓም ፡ ሰይፍና ፡ ጦር ፡ ጐራዴና ፡ ጋሻ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ እየተጋጨ ፡ የፈረሶች ፡ ማስካካት ፡ ከወታደሩ ፡ ጩኸት ፡ ጋር ፡ እያስተጋባ ፡ አየሩ ፡ በአቧራ ፡ እስኪሸፈን ፡ ድረስ ፡ ወታደር ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተራከቦተ ፡ » በሚል ፡ በጥሩ ፡ የንግግር ፡ ቅርጽ ፡ ገልጾታል ። በአርበኝነት ፡ የሞቱትን ፤ የራሱን ፡ ወገኖች ፡ ከነሣ ፡ በኋላ ፡ ከኛ ፡ ወገን ፡ በገርግንነት ፡ የሞቱትን ፡ አልዘነጋቸውም ።

አዝማች ፡ ሮቤል ፡ (የትግሬው ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ?)
እግበ ፡ (ዕቁበ ፡?) ሚካኤል ፡ የሮቤል ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ።
ዣን ፡ በለው ፡ ራስ ።
ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዘወንጌል ።

አዝማች ፡ አምዱ ።

አዝማች ፡ ገብረ ፡ መድኅን ።

አዝማች ፡ ዘመንጋን ፡ ? የራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ዘመድ ።

መንዲልና ፡ ጃውሂር ፡ የሚባሉ ፡ የንጉሡ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ (ስልቦች ።)

ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ስማቸውን ፡ መጥቀስ ፡ ያልሆነለትን ፤ የጸለምት ፡ ሹም ፡ የአጋሜ ፡ ሹም ፤ የተምቤን ፡ ሹም ፡ የሾጀራህ ፡ (ወገራ ፡ ?) ሹም ፤ (ሸዋ ፡) የአበርጋሌ ፡ (ቤጌምድር ፡) ሹም ፡ በዚህ ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ጦርነት ፡ ገዳዮቻቸውን ፡ ጭምር ፡ እየጠቀሰ ፡ መሞታቸውን ፡ ገልጾታል ።

ከአረቦቹ ፡ ወገን ፡ ይኸው ፡ አራብ ፡ ፈቂህ ፡ ካዘጋጀው ፡ በቀር ፡ ታላላቅ ፡ የትግሬና ፡ በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መኳንንትና ፡ ሹማምንት ፡ ከነወታደሩ ፡ የተላለቀበት ፡ የዚህ ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ በኛ ፡ በኩል ፡ በግዕዝ ፡ እንደአራብ ፡ ፈቂህ ፡ ሰፋ ፡ አድርጎ ፡ የተጻፈ ፡ ስለሌለ ፡ የግራኝን ፡ የሹማምንቱን ፡ ዝግጅታቸውን ፡ ንግግራቸውን ጸንተው ፡ መዋጋታቸውን ፡ በተመለከትንበት ፡ አኳኋን ፡ የራሳችንን ፡ ወገን ፡ ለመመልከት ፡ ሐተታውንም ፡ ለመስጠት ፡ አልተቻለንም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ዝርዝሩን ፡ ብናጣውም ፡ በዚያው ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ አያያዝ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ጸንተው ፡ መዋጋታቸው ፡ የተወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ መጽሐፍ ፡ ለሁሉ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ እንደሚለው ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (፲፮፻፰ ዓ. ም.) ዠምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ፲፰፻፹፩ ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ድረስ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ነገሥታት ፡ ሁልጊዜ ፡ አሸናፊ ፡ ዘወትር ፡ አስገባሪ ፡ ሆነው ፡ የኖሩት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እንደግራኝ ፡ አህመድ ፡ ያለ ፡ ብርቱ ፡ መሪ ፡ ተነሥቶ ፡ የረጋውንና ፡ የጸናውን ፡ መንግሥት ፡ ቢያርገደግደው ፡ አያስደንቅም ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ያመለከትነው ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ንና ፡ የፖርቱጋልን ፡ ነገሥታት ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ የገነገኑት ፡ የቱርክ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከአረብ ፡ አገርና ፡ ከሌላውም ፡ ግዛታቸው ፡ እያጠራቀሙ ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ ለግራኝ ፡ የሚሰጡት ፡ የወታደርና ፡ የመሣሪያ ፡ ርዳታ ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ በበለጠ ፡ እንዳጠቃውና ፡ ግራኝን ፡ እንደጠቀመው ፡ በትክክል ፡ መገንዘብ ፡ አለብን ። አራብ ፡ ፈቂህ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ «የባሕር ፡ ወታደሮች ፡ የፈረስቻቸው ፡ ቅልጥም ፡ እስኪታጠፍ ፡ ድረስ ፡ ወፍራም ፡ አቡዋራ ፡ ቆሞ ፡ እስኪሄድ ፡ ይረስ ፡ በኃይል ፡ ተዋጉ ፡» ያላቸው ፡ እነሱን ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦር በዚህ ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ጦርነት ፡ የድል ፡ ጊዜ ፡ ቢያጋድልበት ፡ ጨርሶ ፡ ሊወድቅ ፡ አልቻለም ። በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፡ ቢያልቁ ፡ የዳሞቱ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፤ የይፋቱ ፡ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፤ ራስ ፡ ደገልሃን ፤ ቢትወደድ ፡ መሐመድ ፡ በድላይ ፤ የቃግማው ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሡራዌው ፡ አዝማች ፡ ተስፋ ፡ ልዑል ፡ ሌሎችም ፡ እነአዝማች ፡ አዳሉ ፤ እነተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡

ቃላላቅ ፡ የገዢግንነት ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ እንመለከታለን ። ግራኝና ፡ ጦሩም ፡
አንዱን ፡ አውራጃ ፡ አስገበርሁ ፡ ቹሙን ፡ ማረክሁ ፡ አሰለምሁ ፡ ገደልሁ ፡ ሲል ፡
ሌላው ፡ ተነሥቶ ፡ የርሱን ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ እየገደለ ፡ ሲያውክበት ፤ ንጉሡንም ፡
ለመማረክ ፡ ቢፈትንም ፡ ሳይሳክለት ፡ ቀርቶ ፡ ቃመው ፡ መሞታቸውን ፤ የግራኝም ፡
ሞት ፡ በልጃቸው ፡ በዜ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዘመን ፡ መፈጸሙን ፡ ወደፊት ፡ የሚከ
ታተሉት ፡ ምዕራፎች ፡ ያስረዱናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

በግብር ፡ የተነሣ ፡ የግራኝና የኤሚሮቹ ፡ ጠብ ─ ከአይፈርስ ፡ (አይፈርስ ፡
አምባ ፡ ) በሬት ፡ የደዋሮና ፡ የቃግማ ፡ የባሌ ጦርነት ፡ ─ የገዢግናው ፡ የተክለ፡

## ሃይማኖት ፡ ፍጻሜ ።

የሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ጦርነት ፡ በአራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደ
ዚህ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ሲገኝ ፡ በኛ ፡ በግዕዙ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም፡
እንደጠቀስነው ፡ « ወእምዝ ፡ በ፲፱ዓመት ፡ ወበ፳ ፡ ወ፩ዓመቱ ፡ መንግሥቱ ፡
ለልብነ ፡ ድንግል ፡ መጽአ ፡ ግራኝ ፡ እስከ ፡ ሰመርማ ፡ ወተፃብዓ ፡ ንጉሥ ፡
ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወሰደዶ ፡ እስከ ሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ መዲናሁ ፡ ለንጉሥ ፡
አመ ፲ ፡ ወ ፩ ፡ ለመጋቢት ፡ ወኃልቁ ፡ ብዙኃን ፡ መኳንንት ···· »ከሚለው ፡
በቀር ፡ የዚህ ፡ ክፍ ፡ ያለውን ፡ የሽምብራ ፡ ኩሬን ፡ ጦርነት ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ፡
ታሪክ ፡ ነገሥቱን ፡ ያዘጋጁት ፡ ሊቃውንት ፡ አላቆዩንም ። ወይም ፡ ከዲፋት ፡
በኋላ ፡ በሚቀጥሉት ፡ ዘመናት ፡ የተተኩት ፡ የጦርነትና ፡ የዘረፋ ፡ ጊዜዎች ፡
አጥፍተውት ፡ እንደሆን ፡ አይታወቅም ።

የሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ጦርነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ በቅርብ ፡ በሚከታ
ተሉት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ነው ። ዮዲት ፡ በ፲
ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ በአክሱሞቹ ፡ ነገሥታት ፡ ላይ ፡ ከደረገችው፡
ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ተደፍሮ ፡ የማያውቀው ፡ በንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ የተመራው ፡ የኢ
ትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ድል ፡ የሆነበት ፡ ስለሆነ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ ክሌ
ሎቹ ፡ ከብዙዎቹ ፡ የጦርነት ፡ ሥፍራዎች ፡ አጋንነው ፡ ይመለከቱታል ። በገራ
ችን ፡ እላይ ፡ እንደአመለከትሁት ፡ የዚህ ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ከፈረንጅም ፡
ከአረብኛም ፡ እየተተረጐመ ፡ ተስማምቶ ፡ በዝርዝር ፡ ተጽፎ ፡ በማተሚያ ስላል
ወጣ በጠቅላላው ፡ የግራኝ ፡ አንሣስና ፡ ጦርነት ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ጕልቶ ፡
ሲወራ ፡ ንጉሡ ፡ ድል ፡ የሆኑበትን ፡ ይኸን ፡ የሽምብራ ፡ ኩሬን ፡ ጦርነት፡
የሚያውቁ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ያነበቡ ፡ ያገራችን ፡ አንባቢዎች ፡ በመ
ጠን ፡ ናቸው ።

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ያዤ ፡ ልብነ ፡
ድንግልን ፡ ጦር ፡ በዚህ ፡ ሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ በሚል ፡ ከዝቋላ ፤ ከዱከም ፡

ከሞጆ ፡ ለማይርቅ ፡ ቦታ ፡ ካሸነፈ ፡ በኋላ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ ባደቄ ፡ (፩) ሲያፈገፍጉ ፡ ግራኝም ፡ እንደገና ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ተከታትሎ ፡ ለማጥቃት ፡ ሲያስብ ፡ የሹማምንቱ ፡ ምክር አስገድዶት ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ወደ ሐረርጌ ፡ ተመለሰ ። ከዚያ እንደገና ፡ በዋቢ ፡ ሸበሌ ፡ ወንዝ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ተመለሰ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በደዋሮ ፡ ያለ ውን ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ ማስወጋቱን ፡ የንጉሡ ፡ ሹማምንቶች ፡ እነራስ ፡ በንዮት ፡ እነአቤል ፡ እነክፍሌ ፡ እነዚን ፡ እነካውሌ ፡ (ቃውሌ ?) እነበለው ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ እየመከቱ ፡ ግማሾቹ ፡ ሲሞቱ ፡ የቀሩትም ፡ ሲማረኩ ፡ ወደርሱም ፡ ሲገቡ ፡ ከቆዩና ፡ ግራኝ ፡ አገሩ ፡ ሐረር ፡ እንደገና ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ በግብር ፡ የተነሣ ከሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲንና ፡ ከየአውራጃው ፡ የእስላም ፡ ባላባቶች ፡ ጋር መጣላቱን ፡ በኋላም ፡ ከሡልጣኑ ፡ ታርቆ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ተመልሶ ፡ የደዋሮ ፡ የባሌ ፡ ሕዝብና ፡ ጦር ፡ እንገብርም ፡ ብሎ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ብርታት ፡ እንደተዋጋው ፡ የዚሁ ፡ የአራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ በዝርዝር ፡ ይገልጽልናልና ፡ ከተቋረጠበት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን፡ እንመልከት ።

«ይማም ፡ አህመድ ፡ ከዚያ ፡ (ሐረር) ፡ ወደሀበሻ ፡ አገር ፡ ለመዝመት ፡ ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ሔደ ። ሲሔድም ፡ ብዙ ፡ አዘ ፡ በሚገኝበት ፡ በደዋሮና ፡ በባሌ ፡ መከከል ፡ እየፈሰሰ ፡ አልፎ ፡ በሞከዳሾ ፡ (ሞቃዲሾ) ፡ በኩል ፡ ወደሚገኘው ፡ የጨው ፡ ባሕር ፡ (ሕንድ ፡ ውቅያኖስ) ፡ በሚደበለቀው ፡ ዋቢ ፡ በሚባለው ፡ ትልቅ ፡ ወንዝ ፡ አድርጎ ፡ ነው ። ሌሊት ፡ እየተጓዘ ፡ ደዋሮ ፡ ደረሰ ። እዚያ ፡ ላይ ፡ ጦሩን ፡ እሁለት ፡ ላይ ፡ ከፈለና አንዱን ፡ ለወዚር ፡ ኑር ፡ ቤን ፡ ኢብራሂም ፡ ሰጥቶ ፡ ሁለተኛውን ለራሱ ፡ አስቀርቶ ፡ ደዋሮን ፡ ይወጋ ፡ ዠመር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚገጥመው ፡ ሰው ፡ ሳያገኝ ፡ ምርኮ ፡ ብቻ ፡ አገኘ ። ከፈረሰኞቹ ፡ ውስጥ ፡ ፳ ፈረሰኞች ፡ ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ እነ ፡ ኩሽም ፡ አቡበከር ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ ተለይተው ፡ ሲሔዱ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ለጦርነት ፡ ወደ ፡ ሚዘጋጁበት ፡ ሸለቆ ፡ ደረሱ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ገሥግሠው ፡ ጦርነት ፡ ገጠሟቸው ፡ ብዙ ፡ ስለነበሩ ፡ እስላሞቹ ፡ ሸሹ ። ኩሽም ፡ አቡበከር ፡ ግን ፡ · · · · · · · ገጠመና ፡ ደህና፡ አድርጎ ፡ በጎግንነት ፡ ሲዋጋ ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞተ ። ርሱም ፡ የሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ ለት ፡ ሲዋጋ ፡ ውሏል ፡ · · · · በማግስቱ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ልኮ ፡ አስመታ ፡ ወታደሩም ፡ ጃዋቲር ፡ ጨዋ ጦር ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ መሬት ፡ ደረሰና ፡ አገር ፡ እየዘረፈ ፡ ማረከ · · · · · ከዚያ ፡ አዳል ፡ መብረቅ ፡ (፪) እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ደርሶ ፡ እንደዚሁ ፡ አደረገ ። የአዳል ፡ መብረቅ ፡ ሹም ፡ አቤል ፡ ይባላል ፤ ርሱም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ፡ አገሩን ፡ እስላሞች ፡ እንዳይዙበት ፡ ተዋጋ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ጦሩ ፡ ሸሸ ፤ እርሱም ፡ ተማረከና ፡ እይማም ፡ ፊት ፡ ቀረበ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ወገኖቹ ገዝተው ፡

(፩) ባደቄ ፡ የሚባለው ፡ የኛዎቹ ፡ የረር ፡ ወይም ፡ ቦከን ፡ የሚሉትን ፡ ይሆን ? ባደቄ ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ከሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ መቅረቡ ፡ ሲገለጽ ፡ የረርና ፡ ዝቋላም ፡ መቃረቡ ፡ ያስመስለዋል ።

(፪) የጨዋ ፡ ወታደር ፡ የሚቀመጥበት ፡ (ምሪት) ሥፍራ ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ታሪክ ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፌ ፡ ተመልከት ።

አስመለሱት ፡ እርሱንም ፡ የማረከው ፡ እስላም ፡ በጥፋት ፡ ይማም ፡ እጁንና ፡ እግሩን ፡ ያስቆረጠው ፡ ቃኪያ ፡ የሚባለው ፡ ነው ⋯⋯ ፡ እስላሞችም ፡ አዳል፡ መብረቅን ፡ አመድ ፡ እስኪትሆን ፡ ድረስ ፡ ዘርፈው ፡ አቃጥለው ተውዋት ።

በደዋሮ ፡ ራስ ፡ ባንያት ፡ (በሌላ፡ ጽሑፍ ፡ ራስ ፡ ነብያት ፡ ዲኒያት ) የሚባል፡ ታላቅ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በሌሎቹ ፡ (በደዋሮ ፡ ግዛት ፡ ባሉት ) ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የነበረው ፡ ጥብቅና ፡ ኩሩ ፡ ሰው ፡ ነው ፡. . . . . . . የደዋ ሮን ፡ መዝረፍና ፡ እስላሞች ፡ ወዳገሩ ፡ እንደሚኅዙ ፡ ሲሰማ ፡ ጦሩን ሰብስቦ ፡ አንዲት ፡ ጠባብ ፡ የሆነች ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ይጠባበቅ ፡ ገመር ። ለእስላሞቹ፡ መተላለፊያ ፡ ከዚያች ፡ ለፈረስ ፡ ጉዞ ፡ ከማትመች ፡ መንገድ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስላልነበራቸው ፡ ምክር ፡ ያዙ ። ግማሾቹ ፡ መመለስ ፡ ወደ ፡ ማንችልበት ፡ በቃ፡ አልፈን ፡ ራቅን ፡ ሲሉ ፡ ኖቀሩት ፡ ደግሞ ፡ እምነታችንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አድርገን ፡ ጉዟችንን ፡ እንቀጥል ፡ ሲባባሉ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ምርኮኛው፡ አቤል ፡ እንደታሠረ ፡ አብሮ ፡ ነበርና ፡ ይማም ፡ አሬቱ ፡ አስመጣና ፡ "ክርስቲ ያኖች ፡ መንገዳችንን ፡ ቆርጠው ፡ የተዋጉን ፡ እንደሆነ ፡ አንተን ፡ ገድለን ፡ እኛ፡ ስለሃይማኖታችን ፡ እንሞታለን ፡ » አለው ፡ «እኔ ፡ ሌላ ፡ መላ ፡ አለኝ ፡ „ብሎ፡ ሲመልስ ፡ ይማም ፡ «ምንድነው» ፡ ብሎ ፡ ጠየቀውና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ። «በዚያ ፡ የሚገኙትን ፡ የንጉሡን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ላታቃጥሉ ፡ ቃል ፡ ግቡልኝና ፡ ወደነሱ ፡ ልኬ ፡ የተዘጋውን ፡ መንገድ ፡ ላስከፍትላችሁ ፡ ይማም ፡ ይሁን ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ይኸን ፡ ውለታ ፡ ስለተቀበለው ፡ አቤልም ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ባንያት ፡ እንደዚህ ብሎ ፡ ላከ ፡ «እስላሞቹ ፡ የንጉሡን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላያ ቃጥሉ ፡ አንተም ፡ መንገዱን ፡ ልትለቅላቸው ፡ በዚህ ፡ ተዋውያለሁ ፡ ይኸን ፡ እምቢ ፡ ያልህ ፡ እንደሆነ ፡ ድሉ ፡ ለእስላሞች ፡ ይሆናል ፡ የንጉሡም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይቃጠላል ፡ በዚህም ፡ ቅጣት ፡ ያገኝሃል ። ስላንተ ፡ ብዬ ፡ ይኸን፡ የሰላም ፡ ውል ፡ አድርጌአለሁና ፡ ለእስላሞቹ ፡ ራት ፡ (መጥን) ፡ ለይማም ፡ እህ መድም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ላክ »

ይኸን ፡ ቃል ፡ ይዞ ፡ መልክተኛ ፡ ወደራስ ፡ ባንያት ፡ ሔደ ። ራስ ፡ ባንያትም፡ «አቤል ፡ በመካከላችን ፡ ያዋዋለንን ፡ ቃል ፡ እሺ ፡ ብያለሁ ፡ መጥንም ፡ ገጸ ፡ በረ ከትም ፡ እልካለሁ ፡ ከልወጋችሁንም ፡ ግብር ፡ እንከፍላችኋለን › ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጨምሮ ፡ መላክተኛ ፡ ላከ ። ይማምና ፡ እስላሞቹ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ወደፊትም ፡ ተጉዘው ፡ ራስ ፡ ባንያት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሠፈሩ ። ርሱም ፡ አክብሮ ፡ መብል ፡ መጠጥም ሰጣቸው ፡ ለይማምም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሰጠ ። እስላሞቹም ፡ የርሱንና ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡ ውል ፡ የተባበረውን ፡ አገር ፡ ሳይነኩ ፡ አልፈው ፡ ማስሂብ ፡ ወደሚ ባል ፡ ወደ ፡ ወረቀሎ ፡ ግዛት ፡ ደረሱ ፡. . . . . . . ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ማይ ፡ ፈላህ፡ ወደሚባለው ፡ ወደ ፡ ዡን ፡ አምባ ፡ ግዛት ፡ ደረሱ ፡. . . . . . ። በዚህም ፡ አገር፡

ራጂህ ፡ (ራጌ ?) ፡ የሚባል ፡ እስላም ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገብቶ ፡ ክርስትናን ፡ ተቀብሎ ፡ የሹመት ፡ አገርም ፡ ተሰጥቶት ፡ የእስላሞችን ፡ አገር ፡ እየዘረፈ ፡ ይኖር፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ዛግባህ ፡ በሠፈረ ፡ ጊዜ ፡ «አንተ ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምረው ፡ ስለሃይማኖታቸው ፡ ሲዋጉ ፡ የነበሩት ፡ የእስላሞች ፡ ልጅ ፡ ራስ ህም ፡ እስላም ፡ ነህ ፡ እስከሁን ፡ ያደረግኸው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያዘው ፡ ይሆናል ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ ሥራህ ፡ ተጸጽተህ ፡ ወደኛ ፡ ወደ ፡ ወገኖችህ ፡ ወደ ፡ እስላሞች ፡ መጥተህ ፡ ወንድማችን ፡ አትሆንምን ? በእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ ተስፋ ፡ አትቁረጥ» ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። ራጅህም ፡ ይኸን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ፡ «የኔ ፡ ጥፋት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ገደልሁ ፡ የእስላሞችን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ ዘረፍሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ለመምጣት ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋቴ ፡ ያንተን ፡ ቅጣት ፡ እፈራለሁ» ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ላከ ። ይማምም ፡ «ምረንሃል» ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ላከበት። እርሱም ፡ «እንግዲህ ፡ ክርስቲያኖቼና ፡ ሀብታቸው ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ እየመራሁ ፡ የምወስደው ፡ አንድ ፡ ኤሚር ፡ ከብዙ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ላክልኝ» ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ራጂህም ፡ አገሩንም ፡ መንገዱንም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ያውቀው ፡ ነበርና፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ወዚር ፡ አዶሌን ፡ ከነጦሩ ፡ ላከውና ፡ ከራጂህ ፡ ጋር ፡ ተገናኙ። በርሱም ፡ መሪነት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ወደ ፡ ተደበቁበት ፡ ሔደው ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ሲገድሉ ፡ ሲዘርፉ ፡ ሰንብተው ፡ የማረኩትን ፡ ሀብትና ፡ ፈረስ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፡ . . . . , . ሁሉ ፡ ይዘው ፡ ወዚር ፡ አዶሌና ፡ ራጂህ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጡ ። ይማም ፡ አህመድ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከዛግባህ ፡ ወደ ፡ ታርፋር ፡ ሔዶ ፡ ሠፍሮ ፡ ነበርና ፡ እዚያ፡ ሔደው ፡ ተገናኙት ። ራጂህም ፡ እይማም ፡ ፊት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡ ሽልማት ፡ ሸለመው ፡ «ሃይማኖት ፡ የሌላቸው ፡ (ክርስቲያኖች) ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ ተስፋ ፡ የሚቆርጡ» ፡ የሚለውን ፡ የቁራንንም ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ አክብሮ ፡ ተቀበለው ።

ከዚያ ፡ ይማም ፡ ከታርፋር ፡ ተነሥቶ ፡ የፈረሰኛ ፡ የጦር ፡ አለቆቹን ፡ እነፋራቃሃምን ፡ - . . . . ይዞ ፡ አገር ፡ እየዘረ ፡ ሲፈትሽ . . . . . . . . . የደዋሮው ፡ ሹም ፡ ፋትኤልና ፡ ሌሎቹም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ያሉበትን ፡ ሸለቆ ፡ ተመለከተ ። ወደሠፈራችን ፡ ከመመለስ ፡ እነዚህን ፡ እንውጋቸው ፡ ብሎ ፡ ከበቅሎ ፡ ወርዶ ፡ ከኤሚር ፡ አሊ ፡ ጋር ፡ እፈረሶቻቸው ፡ ላይ ፡ ወጡና ፡ ጭፍራቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሲገሠግሡ ፡ በእነዚያ ፡ ልብ ፡ ፍርሃት ፡ ገባና ፡ መመከቱን ፡ ትተው ፡ ሸሹ ፡ . . . . . , ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ከነጓደኞቹ ፡ ወደ ፡ ሠፈሩ ፡ ተመልሶ ፡ ግማሾቹ ፡ የሸሹትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተከታትለን ፡ እንውጋ ፡ ሲሉ ፡ ይማም ፡ በቀን ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ መውጋት ፡ አንተውና ፡ ሰላይ ፡ እንላክ ፡ ስላለ ፡ በዚሁ ፡ ተስማም ተው ፡ አንድ ፡ በገንዘብ ፡ የተገዛ ፡ ሰላይ ፡ ተላከ . . . . . ሰላዩም ፡ በክርስቲያኖቹ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ሲጓዝ ፡ ውሎ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ሰልሎ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ተመለሰና ፡ «ክርስቲያኖቹ ፡ ቡር ፡ እሚባል ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ሌሊት ፡ እያደሩ ፡ ቀኑን ፡ እተራራ ፡ ላይ ፡ እየወጡ ፡ ይውላሉ» ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ አመጣ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉትን ፡ ፪፻ ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደሮች ፡
፳፻ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ጨምሮ ፡ የበላይ ፡ አገግማች ፡ ራጂህን ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፊት ፡
አስቀደመ ። እነዚህም ፡ በሌሊት ፡ ጉዞ ፡ ከዠመሩ ፡ በኋላ ፡ መንገድ ፡ ጠፍቷቸው ፡ ወደ ፡
ሠፈር ፡ ተመለሱ ። ይማም ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ሳያውቅ ፡ ፴ ፡ ምርጥ ፡ ፈረሰኞች ፡ ይዞ ፡ ለብ
ቻው ፡ ተጓዘ ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ እነአህመድ ፡ ጎይታ ፤ አነዘሀርቡይ ፡ አትማን ፡ ነበሩ ።
አገር ፡ መሪውም ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ የሚባል ፡ ያገሩ ፡ ተወላጅ ፡ (ክርስቲያን ፡ የነበ
ረና ፡ የከዳ) ፡ ነበረ . . . . . . ብዙ ፡ ጉዞ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሠፈር
ሲጠጉ ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ «እነዚያው ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የሚያነዱት ፡ እሳት ፡ ይታያል ፡
ብሎ ፡ ለይማም ፡ ነገረው ። ይማም ፡ የቀደመው ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ መመለሱን ፡ ሳያ
ውቅ ፡ በዚያ ፡ የሚገኝ ፡ መስሎት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ከሥፍራው ፡ ሲያጣቸው ፡
"እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሻላል„ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፡ ገራድ ፡ ሳዲቅ ፡ የሚባለው ፡ የሸር
ቃህ ፡ ገዥ ፡ ።እምነታችንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አድርገን ፡ እንዋጋ ፡
ድል ፡ እናደርጋለን ፡ አለና ፡ ሁሉም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ . . . . . . . . ሊነጋ ፡
ሲል ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ "አላህ ፡ ትልቅ ፡ ነው» ፡ እያሉ ፡ ጮኸው ፡ በክርስቲያኖቹ ፡
ላይ ፡ ገሥግሠው ፡ ጦርነቱን ፡ ዠመሩና ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ጠንክረው ፡ ተዋጉ ።
ፋኑኤል ፡ ኤሚር ፡ አህመድን ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ገጠመው ፡ . . . . . በኋላ ፡ ግን ፡
ሸሸ ። የርሱንም ፡ መሸሽ ፡ ጭፍሮቹ ፡ ሲያዩ ፡ ፊታቸውን ፡ አዙረው ፡ ተከተሉት ።
ክፍሌ ፡ የሚባለውን ፡ ሹም ፡ ገራድ ፡ አህሙሹ ፡ ማረከው ። አንደኛው ፡ ዚን ፡ የሚ
ባለው ፡ አለቃ ፡ ተማረከ ። በርሱም ፡ ላይ ፡ ይማም ፡ «ሥፍራህ ፡ ላይ ፡ ቁም ፡ (አት
ላወስ)» ፡ ብሎ ፡ ቢጮህ ፡ ደንግጦ ፡ ቆመ ። ይማም ፡ ሒድና ፡ ያዘህ ፡ አምጣው ፡
ብሎ ፡ ጋሻ ፡ ዠግሬውን ፡ ላከ ። ጋሻ ፡ ዠግሬውም ፡ ሹሙን ፡ ዚንን ፡ ለመያዝ ፡
ሲጠጋው ፡ ሹሙ ፡ ጋሻ ፡ ዠግሬውን ፡ በጩቤ ፡ ወጋው ። በኋላ ፡ ግን ፡ አንድ ፡
የተማረከ ፡ ክርስቲያን ፡ ታዞ ፡ ሔደና ፡ ወጊውን ፡ አመጣው ፡ እርሱም ፡ እይማም ፡
ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ከታሠረ ፡ ወዲህ ፡ ወገኖቹ ፡ ገዝተው ፡ አስመለሱት ። ከውሊ ፡
የሚባል ፡ ሹም ፡ እንደዚሁ ፡ ተማረከ ።

በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ሠፈር ፡ ሆኖ ፡ ይማም ፡ የተለመደ ፡ ጸሎቱን ፡ እወንዝ ፡ዳር ፡
ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እዛፍ ፡ ሥር ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ፈረሰኛ ፡ እየሮጠ ፡ ሲመጣ ፡
በሩቅ ፡ ታየ ። እነኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ‹ከባረርናቸው ፡ ክርስቲያኖች ፡ አንዱ ፡ ይሆናል ፡
አሉ ። ይማም ፡ ግን ፡ «የለም ፡ ይኸ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በአቧራና ፡ በላብ ፡ የጠቆረ ፡
ይሆን ፡ ነበር ። እስቲ ፡ ለማናቸውም ፡ ልናየው ፡ ነው» ፡ ሲል ፡ ፈረሰኛው ፡ እስላ
ሞቹ ፡ ሠፈር ፡ ደረሰ ። ለካ ፡ ከኋላ ፡ ፺፻ ፡ የሚሆን ፡ ፈረሰኛና ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ በራስ ፡
ባንያት ፡ እየተመራ ፡ ያባርረው ፡ የነበረ ፡ እስላም ፡ ኖሯል ፡ ክርስቲያኖቹም ፡ አንድ
ተራራ ፡ ይዘው ፡ የናዳ ፡ ድንጋይ ፡ እየሰደዱ ፡ ሲመቷቸው ፡ እስላሞቹ ፡ የዛፍ ፡
መከታ እየሰጡ ፡ ዳኑ ። ይማምና ፡ ወገኖቹ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ማለቃችን ፤ ነው ፡
ብለው ፡ በፍጹም ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ነበር ።

ክርስቲያኖቹም ፡ „እስከሁን ፡ የበላኸውና ፡ ያደረግኸው ፡ ይበቃሃል ፡ አሁን ፡
ግን ፡ ከእጃችን ፡ የሚያድንህ ፡ የለም› እያሉ ይጮሁ ፡ ነበር ። . . . በኋላ ፡ ግን ፡ ክርስ

ቲያኖቹ ፡ የሚሰዱት ፡ ናዳ ፡ በዛፍ ፡ ምክንያት ፡ ምንም ፡ አለመግደሉን ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ወርደው ፡ ጦርነቱን ፡ ገጠሙ ። ይማምና ፡ ወገኖቹም ፡ ሲያመነቱ ፡ ቆይተው ...... ተጋጠሙ ። የኛን ፡ ፺፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፺ ፡ የእስላም ፡ ፈረሰኛ ፡ አባረራቸው ፡ ቢባል ፡ ንጉሣችን ፡ ምን ፡ ሊሉ ፡ ነው ፤ ብሎ ፡ ጭፍሮቹን ፡ ተቆጥቶ ፡ እንደገና ፡ ሰይፉን ፡ ከጭንቅላቱ ፡ በላይ ፡ እያወዛወዘ ፡ «የወርቅ ፡ ተራራ» ፡ በሚባለው ፡ ፈረሱ ፡ ተቀምጦ ፡ እየጋለበ ፡ መጣና ፡ ውጊያው ፡ እንደገና ፡ ተዠምሮ ፡ ሳለ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ከነበሩት ፡ ፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ አሊ ፡ ዋርዳይ ፡ የሚባለውን ፡ የጋዋቲር ፡ (ጨዋ ጦር ?)ን (፩) ፡ ሹም ፡ መትቶ ፡ ጣለው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ተደባልቀው ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሲዋጉ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሸሹ ። እስላሞቹም ፡ አዋውልዳህ ፡ እስከሚባለው ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ አባርረው ፡ ምሽት ፡ ገላግሏቸው ፡ ተመለሱ ። ራስ ፡ ባንያትም ፡ ፈረሱ ፡ ደክሞበት ፡ ለጥቂት ፡ አመለጠ ። ..... እስላሞቹ ፡ ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ድንኳን ፡ አገኙ ። ይማም ፡ አህመድ ፡ ከነሰዎቹ ፡ ጋፋት ፡ አዋውልዳህ ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ አገር ፡ መጥቶ ፡ በለው ፡ የሚባለው ፡ ሹም ፡ ይቀመጥበት ፡ በነበረው ፡ ቤት ፡ ፺ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ አረፍት ፡ አድርጎ ፡ ሰነበተ ። ....

ይማም ፡ አህመድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቀምጦ ፡ አገሪቱን ፡ በሙሉ ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ አስቦ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ ኑ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ አበሻን ፡ እንውጋ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ አገር መልክት ፡ ልኮ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ኤሚሮቹና ፡ ወታደሮቹ ፡ ሁሉ ፡ «አባቶቻችንም ፡ አያቶቻችንም ፡ በሀበሻ ፡ የክርስቲያን ፡ አገር ፡ መቀመጥ ፡ ልምድ ፡ የላቸውም ። ሁልጊዜ ፡ ከየወሰኑ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ከብትና ፡ ሰቃ ፡ ዘርፈው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ይመለሳሉ ፤ እኛም ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ለመቀመጥ ፡ ልማድ ፡ የለንም» ፡ ብለው ፡ አሳቡን ፡ እንዲለውጥ ፡ አስገድደውት ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ለመመለስ ፡ አወሰን ፡ ላይ ፡ ኤዲር ፡ እሚባል ፡ አገር ፡ ሲደርስ ፡ ወደ ፡ ሀበሻ ፡ አገር ፡ ዘምቶ ፡ ከነበረው ፡ ከኤሚር ፡ ዘሀርቡይ ፡ ተገናኘ ። በዚህም ፡ በኤዲር ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ድንኳኑን ፡ አስተክሎ ፡ ተቀመጠ ። በምርኮ ፡ ከተገኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፭ኛውን ፡ ዕጣ ፡ አንስቶ ፡ ከቡር ፡ አቡን ፡ ... ለሚባለው ፡ እንዲጠብቅ ፡ ሰጠውና ፡ እርሱ ፡ ከኤዲር ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ተመለሰ ። ....... በዚያም ፡ ሳለ ፡ አገሪቱን ፡ ለሚያስተዳድሩት ፡ ለአቡበክር ፡ ወንድም ፡ ለሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲንና ለኤሚሮቹ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ። “እስላምን ፡ ከፍ ፡ ስላደረገና ፡ ኃይል ፡ ሰጥቶ ፡ ስላከበረ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሥጋና ፡ ይሁን ፡ አባቶቻችን ፡ አድርገው ፡ አግኝተውት ፡ የማያውቁትን ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ምርኮና ፡ ሀብት ፡ አገኘን ። ይኸም ፡ ሀብት ፡ ለኑሮአችንና ፡ ለጦር ፡ መሣሪያ ፡ መግዣ ፡ ይበቃናል ። ከገር ፡ የሚወጣውን ፡ ግብር ፡ ግን ፡ ስምንት ፡ (፪) ፡ ላይ ፡ ይከፈላል ” ።

ሡልጣኑና ፡ ኤሚሮቹ ፡ ከፍርሃት ፡ የተነሣ ሳይቃወሙ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ተቀበሉት ። እርሱም ፡ ግብር ፡ ከገር ፡ ላይ ፡ የሚያወጡትን ፡ ሠራተኞቹን ፡ ላከ ፤ ወታደሩንም ፡ “በያገራችሁ ፡ ግቡ ፡ ፈረሶቻችሁን መግቡ ፤ ሁለተኛ ፡ መጥቼ ፡

(፩) ሙሴ ፡ ባሴት ፡ ጃቲር ፡ ወይም ፡ ጋቱር ፡ ማለቱ ፡ ይሆናል ፡ ብለዋል ፡ ለኔ ፡ የሚመስለኝ ፡ «ጨዋ ፡ ጦር ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

(፪) እስምንት ፡ ላይ ፡ ተከፍሎ ፡ ለደኃ ፡ ለእስረኛ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ይሰጥ ፡ ለማለት ፡ ነው ።

ለጦርነት ፡ እስክልካችሁ ፡ ድረስ ፡ ተጠንቀቃችሁ ፡ ተዘጋጅታችሁ ፡ ተቀመጡ ። እኔ ፡ ወደ ፡ ዘርባህ ፡ ሄጄ ፡ ሉማሌዎቹን ፡ አስማምቼ ፤ ወታደር ፡ ሰብስቤ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመለሳለሁ ።» አላቸውና ፡ ወታደሮቹ ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ በያገራቸው ፡ ገቡ ። ይማምም ፡ ወደ ፡ ዘርባህ ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ መካከል ፡ ሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲን ፡ ከኤሚሮቹ ፡ ከወዚር ፡ ኑር ፤ ከገራድ ፡ አህሙሹ ፤ ከቀጢን ፡ አቡበከር ፡ . . . . . . ጋር ፡ ስለግብሩ ፡ ነገር ፡ ተነጋገረ ። «ይማም ፡ ከየግዛታችን ፡ ግብር ፡ እንዳንቀበል ፡ ሊከለክለን ፡ ነው ፤ ከጥንት ፡ ከሳአድ ፡ ዲን ፡ ዠምሮ፡ የነበረንን ፡ ግብር ፡ ሊሠርዝ ፡ ፈልጓል ፤ እኛ ፡ ግን ፡ አንተውም ፤ በኛ ፡ ላይ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ እነሱን ፡ ይዘን ፡ እንዋጋለን ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ አገሪቱን ፡ ለኛ ፡ ትቶ ፡ እርሱ ፡ ሚስቱን ፡ ድል ፡ ወምበራን ፡ ይዞ ፡ ቢፈልግ ፡ ወደ ፡ ዐረቢያ ፡ ያለዚያ ፡ ወደ ፡ መካ ፡ ይሂድ ፤ አንፈልገውምና ፡ ሁለተኛም ፡ ወደ፡ አገራችን ፡ አይመለስ» ። እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩና ፡ ሐረር ፡ የተዋቸውን ፡ አሽከሮቹን ፡ ሌሊት ፡ ወግተው ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ቀሟቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕግ ፡ አዋቂው ፡ አቡበከር ፡ ኤል ፡ አልሹሪ ፡ ወደ ፡ ሡልጣኑና ፡ ወደ ፡ ኤሚሮቹ ፡ ሄዶ ፡ ምንድነው ፡ ይህ ፡ የምትሠሩት ፡ የከፋት ፡ ሥራ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፡ «ደግ ፡ አድርገናል ፤ ሂድና፡ ለይማም ፡ ሌሎቹን ፡ ፈረሶችና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዲያስረክበን ፡ ንገረው ። እርሱም ፡ ከነሚስቱ ፡ ወደ ፡ ፈቀደበት ፡ ይሂድ ፡ እንጂ ፡ ወደኛ ፡ አይምጣ ። የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ እንገድለውና ፡ ከርሱ ፡ ጭቅጭቅ ፡ እንገላገላለን» ፡ ብለው፡ መለሱለት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቡበከር ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ሄደና ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጠው ። እርሱም ፡ በዘርባህ ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገር፡ ሳያውቅ ፡ ከገበሬዎች ፡ ጋር፡ „ይኸን ፡ አድርጉ ፡ ይኸን ፡ አታድርጉ» ፡ እያለ ፡ በጽሞና ፡ ሲነጋገር ፡ ነበርና ፡ ደብዳቤውን ፡ ከአቡበከር ፡ ተቀብሎ ፡ አንብቦ ፡ ነገሩን፡ ሲረዳው ፡ ደህና ፡ ነው ፡ ክፋት ፡ ካሰቡ ፡ ያሰቡትን ፡ ይፈጽሙ ፤ እኔም ፤ አገሩን ፡ ትቼላቸው ፡ እሄዳለሁና ፡ ይኸንኑ ፡ ተመልሰህ ፡ ንገራቸው» ፡ አለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ሑሴን ፡ ቤን ፡ አቡበከር ፡ ኤል ፡ ጋቱሪ ፡ ተነሣና ፡ «እንደዚህ ፡ አይሆንም ፡ ጦርነት ፡ ፈልገው ፡ እንደሆነ ፡ የሲምን ፡ የሱማሌን ፡ የጂሪን ፤ የሀብር ፡ ማጋዲን ፤ የሀርላህን ፡ ነገድና ፡ የተበታተነ ፡ ወታደር ፡ ሰብስበን ፡ እንወጋቸዋለን ፡ እንጂ ፡ የፈቀዱትን ፡ ያድርጉ ፡ ብለን ፡ አገሪቱን ፡ አንተውላቸውም» ፡ ብሎ ፡ ለይማም ፡ ሲናገር ፡ የቀሩትም ፡ እዚያ ፡ የነበሩት ፡ እነ ፡ ኤሚር ፡ አሊ ፤ እነ ፡ አውራይ ፡ አህመድ ፡ ዲን ፡ እነ ፡ ገራድ ፡ ዘሀርቡይ ፡ መሐመድ ፡ . . . . . እነ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ እነ ፡ አህመድ ፡ ጎይታ ፡ . . . . . . . እየተነሡ ፡ " የሁላችንም ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ሑሴን ፡ አቡበከር ፡ ነው ፡ „ ብለው ፡ እየተነሡ ፡ ተናገሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ከዘርባህ ፡ ተነሥቶ ፡ የአራት ፡ ቀን፡ ጉዞ ፡ አድርጎ ፡ ጊናሲር ፡ ደርሶ ፡ ከዚያ ፡ ሜት ፡ እሞላበት ፡ ዊልክም ፡ (ውልቃም ፡ ?) እሚባለው ፡ አገር ፡ ደረሰ ። ይኸም ፡ አገር ፡ ከሀበሻም ፡ ከትግሬም፡

የሚመጡ ፡ እስላሞች ፡ የሚቀመጡበት ፡ ሥፍራ ፡ ነው ። ከታመኑት ፡ ኤሚሮች ፡ ውስጥ ፡ መገሥመሪያ ፡ መጥቶ ፡ የተገናኘው ፡ ገራድ ፡ ናስር ፡ ነው ። ሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲን ፡ የይማምንና ፡ የጦሩን ፡ መምጣት ፡ ሲሰማ ፡ ሼሪፎችንና ፡ ሼኾችን ፡ (ቀሳውስት) ፡ እኔንና ፡ ይማምን ፡ አስታርቁን ፡ ብሎ ፡ ጐትጒቶ ፡ ላካቸው ። እነርሱም ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጥተው ፡ ነገሩት ። እርሱም ፡ እሺ፡ ብሎ ፡ ከታረቀ ፡ በኋላ ፡ በደስታ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ሐረርጌ ፡ ገባ ።

በዚሁ ፡ መከከል ፡ ሂራቡ ፡ የሚባል ፡ የመራሂሂን ፡ ሱማሌ ፡ ባላባት ፡ የሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲንን ፡ አሽከር ፡ ስለገደለ ፡ ይማምና ፡ ሡልጣን ፡ እርሱን ፡ ሊወጉ ፡ ሄዱ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ . . . . . . . . የደም ፡ ዋጋና ፡ ያሉትን ፡ ፈረሶቹን ፡ አስረከበ ፡ ከመወጋት ፡ ዳነ ፡ . . . . . . . ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊመለሱ ፡ ሲሉ ፡ ሡልጣኑ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ እንመለስ ፡ አለ ፤ ይማም፡ ደግሞ ፡ ባሌን ፡ እንውጋ ፡ አለ ፤ ሡልጣኑ ፡ አንተ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ጦርና፡ የቀሩትን ፡ ሹማምንት ፡ ይዘህ ፡ ሂድና ፡ ተዋጋ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ወታደሬ ፡ ደክሟልና፡ ወደ ፡ ሀገሬ ፡ እመለሳሁ ፡ ብሎት ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሔደ ። ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ በኪዳድ፡ ሠፈረ ። በዚያም ፡ ሳለ ፡ ሹማምንቱና ፡ ወታደሩ ፡ ስንቅ ፡ የለንም ፡ እንደምን ፡ ወደ፡ ባሌ ፡ እንዘምታለን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። እርሱም ፡ ካገር ፡ ጌቶችና ፡ ከባላገር ፡ ላይ ፡ አስመጥቼ ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ አላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ የአላዊ ፡ ቤን፡ አሊን ፡ . . . . . ሌሎቹንም ፡ ሸሪፎች ፡ ቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ የምናደርግበት ፡ ስንቅ ፡ ስጡን ፡ እርዱን ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሰጡት ። . . . . ከዚያ፡ ቀጥሎ ፡ ኪዳድን ፡ ትተው ፡ እስላሞቹ ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ ተጓዙና ፡ ደልፋይ ፡ ጀልብ፡ (ገልብ) ፡ ከሚባል ፡ የእስላሞች ፡ አውራጃ ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ሠረዳ ፡ ያሉት ፡ ሸሪፍ ፡ ሐኪም ፡ ቤን ፡ ኡመር ፡ . . . . . . . ሸሪፍ ፡ ሼኽ ፡ ቤን ፡ አብደላ ፤ ሸሪፍ፡ ሐኪም ፡ ቤን ፡ ኤዝ ፡ ዘፋይ ፡ . . . . . . . . . ይማምን ፡ ከነጦሩ ፡ ተቀብለው ፡ አስተናገዱት ።

በደልፋይ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ አርፈው ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ ጉዟቸውን ፡ ቀጥለው ዋቢ ፡ ወንዝ ፡ ደረሱ ። . . . . በመከከልም ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ስንቅ ፡ አልቆ ፡ ረሀብ ፡ ሆነ ። ከ፳ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሚዛ ፡ እሚባል ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱና ፡ ሠፈር፡ ሆነ ። በዚህ ሳለ ፡ ይማም ፡ ወታደሩን ፡ እሁለት ፡ ከፈለው ። አንዱንም ፡ ክፍል፡ ለአውራይ ፡ አቡን ፡ ሰጠና ፡ አዳል ፡ ገለት ፡ ላይ ፡ እንገናኝ ፡ ብሎ ፡ ላከው ፤ አውራይ ፡ በሰረገዳ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ቃግማ ፡ (ቃጅማ) ፡ ሄደ ። አንደኛው ፡ በአቅራ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ ሄደ ። ይማም ፡ ግን በባሌ ፡ መንገድ፡ ጉዞውን ፡ ዠምሮ ፡ ሲጓዝ ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ አገር ፡ ወርደው ፡ ለመስለም ፡ የሚፈልጉ ፡ የባሌ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በመንገድ ፡ አገኘና ፡ " የወዴት ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ናችሁ ? „ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡ እነሱም ፡ " የባሌ ፡ ሰዎች ፡ ነን ፡ አሁን ፡ እንደናንተ ፡ እስላም ፡ ለመሆን ፡ ወደ ፡ ጃ (ጋ) ልብ ፡ እንሄዳለን ፡ „ አሉት ፡ . . . . . ስለኛ ፡ ምን ፡ ትሰማላችሁ ፡ ቢላቸው ፡ "ምንም ፡ አልሰማ

ንም ። ስለናንተ ፡ የሚናገርና ፡ የሚያወራ ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ የለም ፡ አሉት ። አገሩስ እንደምንድነው ?፡ አገሩን ፡ የሚያስተዳድር ፡ ሹም ፡ ማን ፡ ይባላል ? ። ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፤ ያገሩ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ የንጉሡ ፡ እማች ፡ አዝማች ፡ ደጋልሃን ፡ ይባላል ፡ አሁን ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ባገሩ ፡ ያለው ፡ የርሱ ፡ ሹም፡ ሻንቁር ፡ የሚባለው ፡ ነው ፤ ብለው ፡ መለሱ ። የሚቀመጥበትንም ፡ ሥፍራ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ሻንቁር ፡ በዛላህ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በቃግማ ፡ ይገኛሉ ፤ ብለው ፡ መለሱለት ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እስላም ፡ ነበር ፡ (፩) ። ገራድ ፡ አቡን ፡ ወዜር ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬው ፡ ነበር ። ጌታው ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ ከይማም ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ አገር ፡ ግዛትም ፡ አግኝቶ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ አገር ፡ በድሎ ፡ ይማም ፡ ቢሽረው ፡ ሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ገብቶ ፡ የቃግማ ፡ ገራድ ፡ ተብሎ ፡ በሹመት ፡ የነበረ ፡ ነው ።

ይማም ፡ ተክለ ፡ ሃይምኖት ፡ በላይኛው ፡ ወይስ ፡ በታችኛው ፡ ቃግማ ፡ ነው ?፡ የሚገኘው ፡ ብሎ ፡ እነዚህኑ ፡ ሰዎች ፡ ቢጠይቃቸው ፡ በፊት ፡ ከላይኛው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ወርዷል ፤ ብለው ፡ መለሱለት ። ልተ መሩኝ ፡ ትችላላችሁን ፡ ቢላቸው ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ አሉት ። አሁን ፡ ከዚህ ፡ ስንነሣ ፡ እርሱ ፡ ዘንድ ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ እንደርሳለን ፡ ቢላቸውም ፡ ሊነጋጋ ፡ ሲል ፡ እንደርሳለን ፡ አሉት ። ስለዚህ እዚሁ ፡ እሥፍራህ ፡ ቆይ ፡ ለማለት ፡ ወደ ፡ አውራይ ፡ አቡን ፡ ላከና ፡ እርሱ ፡ የታወቁትን ፡ ጉበዛዝት ፡ እነድል ፡ ሰገድን ፡ እነ ፡ ዘሀርቡይ ፡ አሊን ፤ እነፋራቃሃም ፡ ሳቱን ፤ እነገራድ ፡ አህሙሹን ፡ እነቀጢን ፡ አቡበከርን ፡ ······· በጠቅላላው ፡ ፴ የሚሆኑ ፡ ፈረሰኞች ፡ መረጠና ፡ የሚዋጋበትን ፡ ባንዲራ ፡ ጨምሮ ፡ ለአቡበከር ፡ ቀጢን ፡ ሰጠው ። እነዚያንም ፡ ሁለት ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዳይሸሹ ፡ አሳሰረና ፡ ይኽን፡ ጦር ፡ እተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድረስ ፡ አድርሱ ፤ ይኸን ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛችሁን ፡ ነገር ፡ እናደርግላችኋለን ፡ አላቸውና ፡ እነሱም ፡ እሺ፡ አሉ ። ወደ ፡ ቀጢን ፡ አቡበከር ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ « ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዘህ ፡ ያላመጣህልኝ ፡ እንደሆነ ፡ ከደንበኛ ፡ ተዋጊ ፡ አልቆጥርህም ፡ በመካከላችሁ ፡ በክርስቲያኖች ፡ ያልተበደለ ፡ ማን ፡ ይገኛል ፡ » ሲል ፡ ሁሉም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ጮሁ ። ········ ከእኩለ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ ወደ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲጓዙ ፡ ይማም ፡ ····· አቅራ ፡ ወደ ሚባል ፡ አገር ፡ ከዚያም ፡ የክርስቲያኑን ፡ አገር ፡ እየዘረፈ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ጃላት ፡ በደጋው ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ቃግማ ፡ ዘመተ ። አቡበከር ፡ ቀጢን ፡ ግን ፡ እነዚያን ፡ ሁለቱን ፡ መሪዎችን ፡ እንደታሠሩ ፡ እፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ሲጓዝ ፡ አድሮ ፡ ሊነጋ ሲል ፡ መሪዎቹ ፡ ቆም ፡ ብለው፡

(፩) ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ የዞረው ፡ ማለቱ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ያለዚያ ፡ ለእስላሞች ፡ ሥያሜ ፡ ሊጠራው ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ሲመለከቱ ፡ ? በኋላችሁ ፡ ምን ፡ ይታያችኋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነሱም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ ከነእሳቱ ፡ ይታየናል ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኤሚሩና ፡ ፡ ጓደኞቹ ፡ ምክር ፡ ይዘው ፡ ገሚሶቹ ፡ ከበን ፡ እንውጋው አሉ ። አቡበክር ፡ ቀጢን ፡ ግን ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እጁን ፡ ይገዤ ፡ ለይማም ፡ ለማቀረብ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቻለሁ ። ከበን የወጋነው ፡ እንደሆነ፡ በጭለማ ፡ ሊያመልጠን ፡ ይችላልና ፡ እስኪነጋ ፡ ብንቆይ ፡ ይሻላል ፤ ብሎ ፡ መለሰ ። የቀሩትም ፡ አንተ ፡ አለቃችን ፡ ነህና ፡ የሚመስልህንና ፡ የተሻለውን ፡ አድርግ ፤ ብለውት ፡ በዚሁ ፡ ተስማምተው ፡ ከበቅሎቻቸው ፡ ወርደው ፡ እመሬት ፡ ተቀመጡ ፤ ኤሚሩም ፡ እንግዲህ ፡ የያሲንን ፡ ሱራት፡ድገሙ ፡ (፩) ፡ አላቸው ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሌሊቱን ፡ ጊዜ ፡ በመጠጥ ፡ አሳልፎ ፡ ነበር ። · · · · · · · · በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ በዘመተበት ፡ በኩል ፡ የእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ አየና ፡ ይህ ፡ የማየው ፡ እሳት ፡ ምንድነው ፡ ? ብሎ ፡ አጠገቡ ፡ ያሉትን ፡ ቢጠይቅ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ ተላላፊ ፡ ሽፍታ ፡ ቤት ፡ አቃጥሎ ፡ ይሆናል ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። እርሱ ፡ ግን አይመስለኝም ፡ የጠላት ፡ (የእስላሞች) ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ወታደር ፡ ነው ፤ ፈረሶቻችሁን ፡ ጫኑ ፤ ሄደን ፡ እንዋጋለን ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። አቡበክር ፡ አጠገቡ ፡ መሆኑን ፡ አያውቅም ፡ ነበር · · · · ከዚህ ፡ በኋላ፡ አቡበክር ፡ ቀጢን ፡ ከታሠሩት ፡ ሁለት፡ ሰዎች ፡ አንዱን ፡ አሥሮ ፡ አስቀርቶ ፡ ሁለተኛውን ፡ ከሦስት ፡ እስላሞች ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ እተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሠፈር ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ ሰልለው ፡ እንዲመለሱ ፡ « እተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሠፈር ፡ ሂዱና ፡ ተኝቶ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ መርምራችሁ ፡ ተመለሱ ። ጓደኛህ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ይቀራል ፡ የከዳኸን ፡ እንደሆነ ፡ እርሱን ፡ እዚህ ፡ ገድለን ፡ እንዋጋለን ፡ ድልም፡ እናደርጋለን ፡ » ብሎ ፡ ላካቸው ። እነሱም ፡ በድብቅ እተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሠፈር ፡ ድረስ ፡ ሄደው ፡ ፈረሶቹ ፡ መጫናቸውን ፡ ተመልክተው ፡ ተመለሱና ፡ ለአቡበክር ፡ ነገሩት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ፋቲሀህ ፡ (ጸሎት) ፡ እየደገሙ፡ ድልን ፡ ለማግኘት ፡ ጸለዩ ። ከዚያ ፡ ሲነጋ ፡ አቡበክር ፡ ቀጢን ፡ ሞባራቅ ፡ (ሙብረቅ) ፡ እሚባለው ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ጥሩሩን ፡ ለብሶ ፡ ረዥም ፡ ጦሩንም ፡ ያዘ ። የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ አደረጉና ፡ ጦራቸውን ፡ እሹለው፡ የፈረሶቻቸውን ፡ ልባብ ፡ (ልጓም)፡ ለቀው ፡ · · · · ወደ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ሠፈር፡ ገቡ ። ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እነሱን ፡ ሲያይ ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ ወታደሩ ፡ አጥሩ ፡ ውስጥ ፡ እንደነበረ ፡ እርሱ ፡ እበራፍ ፡ ሆኖ ፡ አቡበክር ፡ ጦር ፤ እርሱ፡ ሰይፍ ፤ እንደያዘ ፡ ተመታቱ ። ነገር ፡ ግን ፡ አቡበክር ፡ ከውጭ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከውስጥ ፡ ስለነበረ ፡ አልተጐዳዱም ።

እስላሞቹም ፡ ገብተው ፡ ለመዋጋት ፡ በሩ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ሆነባቸው ፡ ተቸግረው ፡ ሳለ ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ የተባለው ፡ ፈረሰኛ ፡ ከጓሮ ፡ ዞሮ ፡ አጥሩን ፡ በፈረሱ ፡ ጥሶ ፡ የሲም ፡ ፈረሰኛ ፡ እያለ ፡ ፎክሮ ፡ ገብቶ ፡ ጦርነቱን ፡ ሲዠምር ፡

(፩) ፡ በጭንቅ ፡ ጊዜ ፡ የሚደገም ፡ የቁራን ፡ ጸሎት ።

ጓደኞቹ ፡ ተከትለው ፡ ገቡና ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ወታደር ፡ ተደባልቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር ። ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ አቡበከርም ፡ እንደዚያው ፡ እንደዠመሩ ፡ ሲዋጉ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሽሽት ፡ ዠመሩ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ወደነርሱ ፡ ዞሮ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሸሹት ፡ እያለ ፡ ሲቆጣ ፡ አቡበከር ፡ ወደውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ቻለ ። ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ገጠመው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ፈረሰኛ ፡ ለጌታው ፡ ረድቶ ፡ አቡበከርን ፡ ሊመታው ፡ ሲል ፡ ዘሀርቡይ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መታና ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ጣለው ። . . . . . . አቡበከርም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ መትቶ ፡ ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ገለበጠውና ፡ ማረከው ። . . . . . . . ጌታቸውም ፡ ሲማረክ ፡ የተረፉት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሸሹ ። የቀሩትም ፡ ሞቱ ። በዚያ ፡ የነበሩት ፡ ፈረሶች ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ሳይሉ ፡ በጥር ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ተገኝተው ፡ ተወሰዱ ።

አቡበከር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንና ፡ ሚስቱን ፡ ወስዶ ፡ እይማም ፡ ፊት ፡ አቀረባቸው ። ይማም ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለአደን ፡ ሡልጣን ፡ ላከለትና ፡ ሚስቱን ፡ ለራሱ ፡ ዕቁባት ፡ አደረጋት ። ስሟም ፡ ሃጂራ ፡ ተብሎ ፡ ተሰየመ ፤ እርሷም ፡ የሀበሻን ፡ አገር ፡ ድል ፡ በመታበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ትከተለው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስላሞች ፡ ወደ ፡ ዋበናት ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ዘሀርቡይ ፡ መሐመድ ፡ ለሚባለው ፡ ለአጎቱ ፡ ልጅ ፡ ፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ብዙ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ባንዳራ ፡ ጨምሮ ፡ ሰጠውና ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ ማህል ፡ ወደ ፡ መሉዋ ፡ (ማሉአ ፡ ማሉ) ፡ እንዲዘምት ፡ ላከው ። እርሱም ፡ በየመንገዱ ፡ ያገኘውን ፡ እየዘረፈ ፡ እያቃጠለ ፡ ወደፊት ፡ ሲሄድ ፡ የክርስቲያን ፡ ፈረሰኞች ፡ እየጋለቡ ፡ ሲመጡ ፡ አሊጋራህ ፡ የዘርባው ፡ የሚባል ፡ ፈጣን ፡ ፈረሰኛ ፡ የራሱን ፡ ፈረስ ፡ ልጓም ፡ ለቆ ፡ ወደነሱ ፡ ሽምጥ ፡ ለቆ ፡ ሲጋልብ ፡ ኰርቻው ፡ ተበጥሶ ፡ ወደቀበት ። እሱም ፡ እንደ ፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ ተወርውሮ ፡ ወደቀና ፡ አንድ ፡ ፈረስ ፡ ልቡን ፡ ረግጦ ፡ ገደለው ። . . . ፡ በባሌ ፡ ሻንኩር ፡ (ሸንቁር) ፡ የሚባል ፡ የራስ ፡ ደጋልሃን ፡ እንደራሴ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የባሌንም ፡ መዘረፍ ፡ ስለሰማ ፡ ወታደሩን ፡ አሰልፎ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ጉዞ ፡ ዠመረ ። በተጠጋም ፡ ጊዜ ፡ ለስለላ ፡ የላካቸው ፡ ፳ ፡ ፈረሰኞች ፡ ፈረስ ፡ ይዘው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ የተቀመጡትን ፡ እስላሞች ፡ አግኝተው ፡ ገደሏቸው ። እስላሞቹ ፡ ግን ፡ ተጨዋጨኸው ፡ (ወገኖቻቸው ፡ እንዲሰሙ) ፡ ነበርና ፡ ይማም ፡ ይኸን ፡ ሲሰማ ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ሲጋልብ ፡ የቀሩት ፡ ተከተሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ አላገኙም ፡ . . . በባሌ ፡ የሚገኙ ፡ ዓረቦችና ፡ ሸሬሮች ፡ መጥተው ፡ ከይማም ፡ ተገናኙ ። እርሱም ፡ በደህና ፡ ተቀብሎ ፡ የሽልማት ፡ ልብስ ፡ አለበሳቸው ። . . . ከዚያ ፡ አቡበከር ፡ ወደ ፡ ዋቢ ፡ ሄደ ፡ አውራይ ፡ አህመድ ፡ . . . . . እሬት ፡ ሲጓዝ ፡ ከኋላ ፡ ይማም ፡ ተከትሎት ፡ ነበር ። ሸንቁር ፡ ጦሩን ፡ እሮት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ አንዱን ፡ እፊት ፡ ፪ተኛውን ፡ ከማህል ፡ ፫ተኛውን ፡ ደጀን ፡ ሆኖ ፡ እንዲዋጋ ፡ አሰልፎት ፡ ነበር ። የመዠመሪያውም ፡ ጦር ፡ እፊት ፡ ቀድሞ ፡

ከአውራይ ፡ አህመድ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ትልቅ ፡ ውጊያ ፡ ተገመረ ። ክርስቲያኖች ፡ ብዙ ፡ ስለነበሩ ፡ እስላሞቹ ፡ ወደኋላ ፡ አፈገፈጉ ፤ አህመድ ፡ ዲን ፡ ግን ፡ ገትሮ ፡ ሲዋጋ ፡ በ፫ጦር ፡ (፫ ፡ ጊዜ) ፡ ተወግቶ ፡ ቆስሎ ፡ ከሞት ፡ ተረፈ ።

ይማም ፡ ከኋላ ፡ ሆኖ ፡ የነዚህን ፡ መዳከም ፡ ሲያይ ፡ ገሥግሦ ፡ ደረሰላቸው ። . . . . ክርርቲያኖቹም ፡ የርሱን ፡ ጦር ፡ መምጣት ፡ ሲያዩ ሸሹ ። . . . . ቢሆንም ፡ በዚያው ፡ ዙሪያ ፡ ብዙ ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ፡ , . . ይማም ፡ ለጓደኞቹ ፡ እንደ ዚህ ፡ አላቸው ። እዚህ ፡ በባሌ ፡ የአለንበት ፡ ቦታ ፡ አደገኛ ፡ ነው ። የባሌም ፡ ሕዝብ ፡ ሰይጣን ፡ ነው ፤ የባሌን ፡ ሰዎች ፡ የጦርነት ፡ መላ ፡ የሚያውቅ ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። አጠገቡ ፡ ያሉትም ፡ ገራድ ፡ ከሚል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። ገራድ ፡ ከሚልም ፡ እህቱን ፡ ሙጂሣህን ፡ ያገባ ፡ የይማም ፡ አማች ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ የባሌ ፡ ሕዝብ ፡ እያለፈ ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡ እንጂ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሰልፎ ፡ አይዋጋም ፡ ተሰልፈህ ፡ ብትጓዝ ፡ ከኋላ ፡ ያለውን ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ይወጋሉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ብትገጥማቸው ፡ ሩቅ ፡ ሳይሄዱ ፡ ይሸሻሉ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የባሌ ፡ ጦርና ፡ ሕዝብ ፡ የጦርነት ፡ አሳብና ፡ መላ ፡ ሲል ፡ ለይማም ፡ አስረዳው ። ይማም ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እኛም ፡ ተንከል ፡ ሠርተን ፡ እናታልላቸዋለን ፡ አለና ፡ ለኤሚሬ ፡ አቡበከር ፤ ኤሚሬ ፡ ሙጋሂድን ፤ አብሳማ ፡ ኑርን ፤ ገመልዲንን ፡ ፳ ፡ ፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ሰጠውና ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ እየሄዳችሁ ፡ እፊታችሁ ፡ ካገኛችሁት ፡ ጋር ፡ ብቻ ፡ ተዋጉ ፡ ተመልሳችሁ ፡ እኛን ፡ ለመርዳት ፡ አታስቡ ። እኛም ፡ እናንተን ፡ አንረዳም ፡ ብሎ ፡ እነርሱን ፡ አስቀድሞ ፡ ላከና ፡ እርሱ ፡ የቀረውን ፡ ጦር ፡ ከብትና ፡ ጓዝ ፡ ይዞ ፡ ከኋላ ፡ ይጓዝ ፡ ገመር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የክርስቲያኖች ፡ ጦር ድንገት ፡ . . ደረሰና ፡ አራት ፡ ላይ ፡ ተከፍሎ ፡ ሁለት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ወደነ፡ አቡበከር ፡ ሄዱና ገጠሙ ፡ ፬ ፡ ሰዓት ፡ ውጊያው ፡ እንደ ፡ ቆየ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ አዝማች ፡ ሰሎሞን ፡ በአህመድ ፡ ዲን ፡ እጅ ፡ ተመትቶ ፡ ሞተ ። ሌላው ፡ ሹም ፡ ደግሞ ፡ በአቡበከር ፡ እጅ ፡ ሲሞት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሸሹ ።

ይማም ፡ ባለበት ፡ በኩል , . . . ሲሙ ፡ (ስምዖን ፡) የሚባል ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የሚመራው ፡ ጦር ፡ . . . . . ከይማም ፡ ጋር ፡ ተጋጠሙ ፡ ሲሙ ፡ የወናግ ፡ ዝን ፡ ልጅ ፡ ነው ። ይኸም ፡ ወናግ ፡ ዝን ፡ ቀድሞ ፡ እሡልጣን ፡ መሐመድ ፡ ዘንድ ፡ (ሐረር ፡) ወርዶ ፡ እስላም ፡ ሆኖ ፡ ሡልጣኑም ፡ የእንከርሳህን ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ሰጥቶት ፡ በክበሬታ ፡ አስቀምጦት ፡ ነበር ። ወደባሌም ፡ ለዘመተው ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዘርፏል ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ አይለው ፡ እስላሞቹ ፡ ተሸንፈው ፡ ሲሸሹ ፡ ወናግ ፡ ዝን ፡ ተማረከ ፤ እርሱንም ፡ ወስደው ፡ እወናግ ፡ ሰገድ ፡ አባት ፡ እናዖድ ፡ ፊት ፡ አሥረው ፡ አቀረቡት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ (ዳሞት ፡ ነጋሽ ፡) ወንድሙ ፡ አማልዶ ፡ አስፈታውና ፡ የባሌን ፡ ግዛት ፡ ከንጉሡ ፡ ተቀብሎ ፡ በጣም ፡ ተከብሮ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ወታደሮቹም ፡ እንደልቡ ፡ ይታዘዙት ፡ ነበር ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ የመጣልኝ ፡ የምነግራችሁ ፡ ነገር ፡ አለኝና ፡ ተሰብሰቡ ፡ ብሎ ፡ ፳ ፡ ለሚሆኑ ፡ ተዋጊ ፡ አለቆች ፡ ቢልክ ፡ ሁሉም ፡ ተሰበ

ሰቡለት ፡ በመጡም ፡ ጊዜ ፡ ግቡ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መጠጥ ፡ እንጠጣ ፡ አላቸው ፤ በገ
ቡም ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ የኖረ ፡ ኃይለኛ ፡ መጠጥ ፡ እያጠጣ ፡ ሰክራቸውን ፡ በየ ፡
ጊዜ ፡ ጓደኛውን ፡ ድል ፡ በኢየሱስን ፡ "እንግዲህ ፡ ምን ፡ እናድርጋቸው ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በጃችን ፡ ጥሏቸዋል› ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። እሱም ፡ "እነዚህን ፡ እ ሶ ር ፡ እንደ
በግ ፡ ማረድ ፡ ነው» ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በስካር ፡ መዳከማቸውን ፡
ተመልክቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣና ፡ አሽከሮቹን ፡ ወደቤት ፡ ግቡና ፡ እነዚህን ፡ ጠፍራ
ችሁ ፡ አሥራችሁ ፡ እንደ ፡ በግ ፡ እበራፉ ፡ ላይ ፡ እረዱዋቸው› ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። እን
ሱም ፡ የታዘዙትን ፡ ፈጸሙ ፡ ፈረሶቻቸውንም ፡ ማረኩ ። ወናግ ፡ ዟንም ፡ የዚህን ፡
ወሬ ፡ ዳከር ፡ ለሚገኘው ፡ ለሡልጣን ፡ መሐመድ ፡ እኔ ፡ አገልጋይ ፡ ነኝ ፡ እነሆ ፡
በክዳት (በተንኮል) ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ፈጅቼ ፡ ተበቀልሁ ፡ ብሎ ፡ እርሱም ፡ እንዲ
መጣለት ፡ ላከበት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወናግ ፡ ዟን ፡ ‹እንግዲህ ፡ ሁላችሁም ፡ ስለሙ ፤ እስላሞቹም ፡
ያረዱትን ፡ ብሉ ፡ እምቢ ፡ ያላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እንደአለቆቻችሁ ፡ እገድላችኋ
ለሁ» ፡ ቢላቸው ፡ ሁሉም ፡ ሰለሙ ። አሁንም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ወናግ ፡ ዟን ፡ ና ፡
የሚል ፡ ቃል ፡ ለሡልጣን ፡ መሐመድ ፡ ላከበት ። ኤሚሮቹ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የሀጋይ ፡
ወራት ፡ ስለሆነ ፡ በትሔድ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ መከሩት ። አሁንም ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡
እንደገና ፡ ልጁን ፡ ሲሙን ፡ (ስምዖንን) ፡ ልኮ ፡ እንዲመጣለት ፡ ጐተጐተው ። ሡል
ጣን ፡ መሐመድም ፡ ሲሙን ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ አልቅሶ ፡ የኤሚሮቹን ፡ ምክር ፡ ጥሶ ፡
ወደ ፡ ባሌ ፡ ተጓዘ ። ወናግ ዟን ፡ ግን ፡ ልጁን ፡ ሲሙን ፡ ወደ ፡ ሡልጣን ፡ መሐ
መድ ፡ ከላከ ፡ ወዲህ ፡ በአዝማች ፡ ገብረ ፡ እንድርያስ ፡ የሚታዘዝ ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡
መጥቶበት ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ከተዋጋ ፡ በኋላ ፡ መሸነፉን ፡ ሲያ
ውቀው ፡ ዕቁባቶቹንና ፡ ጓዙን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ አገር ፡ ሲመጣ ፡ ዋቢ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡
ሲደርስ ፡ ሞተ ፤ መቃብሩም ፡ የታወቀ ፡ , , . . ነው ። ሡልጣን ፡ መሐመድም ፡
ሲመጣ ፡ ሞቶ ፡ ስላገኘው ፡ አለቀሰለት ። ከዚያም ፡ ሡልጣኑ ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ ጉዞውን ፡
ቀጠለ ፤ ገብረ ፡ እንድርያስም ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሸሸ ። ሡልጣኑም ፡ በባሌ ፡
ሁለት ፡ ወር ፡ እንደተቀመጠ ፡ በባሌ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አድርጎበት ፡ ወዳገሩ ፡ ተመለሰ ።
የሾማቸውም ፡ የገራድ ፡ ሙጋሂድን ፡ አባት ፡ ገራድ ፡ አሊን ፤ አውራይ ፡ ሰበርዲንን ፤
ጉይታ ፡ አብርሃን ፤ ዋሹ ፡ አትማንን ፤ ድል ፡ በኢየሱስን ፡ ነው ፡ ሹመታቸውም ፡ ከ፪ ፡
ወር ፡ አልበለጠም ።

የሀበሻው ፡ ንጉሥ ፡ ራሱ ፡ ወርዶ ፡ እስላሞቹን ፡ ለመውጋት ፡ ቆረጠ ። ወሰን ፡
ሰገድ ፡ ግን ፡ አይሆንም ፡ የእስላሞቹ ፡ ንጉሥ ፡ ወዳገሩ ፡ ተመልሷልና ፡ አትሒድ ፡
እኔ ፡ ራሴ ፡ እሔዳለሁ ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ መጣ ። ከእስላሞቹም ፡ ጋር ፡ ኃይ
ለኛ ፡ ጦርነት ፡ አደረገ ። እስላሞቹ ፡ ሳይሸሹ ፡ ሁሉም ፡ እየፈረስ ፡ ኮርቻቸው ፡ ላይ ፡
ሞቱ ። ሸሪፍ ፡ ኑር ፡ ቤን ፡ አህመድ ፡ ሆዱ ፡ ተቀዶ ፡ ተማረከ ። ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ግን ፡
ሰፍቶ ፡ አዳነው ።

ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ የወናግ ፡ ዟንን ፡ ልጅ ፡ የሲሙን ፡ ሁኔታ ፡ እንመል
ከት ፡ እርሱም ፡ ከሡልጣን ፡ መሐመድ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ መጥቶ ፡ ሡልጣኑ ፡

የገራድነት ፡ ሹመት ፡ ሰጥቶ ፡ በከበሬታ ፡ አስደስቶ ፡ አስቀመጠው ። በኋላ ፡ ግን ፡ ወደ
ክርስቲያኖች ፡ አገር ፡ ዘምቶ ፡ ከድል ፡ ማይዳ ፡ ጦርነት ፡ ተማረከና ፡ ከእስላምነት ፡
ወደ ፡ ክርስቲያንነት ፡ ዞረ ። በአባቱም ፡ እግር ፡ ተሾመ ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ (ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡)
እስላሞችን ፡ ሊወጋ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ የመጣው ። ይማም ፡ አህመድ ፡ ሊዋጉ ፡ የመጡትን ፡
ክርስቲያኖች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ . . .  . . ጦሩን ፡ አሰለፈ ፡ የመራሂሃን ፡ የጎርጎራ ፡ የኤል ፡
ሐውያህ ፡ የቀስት ፡ ጦረኞች ፤ በሺ ፡ የሚቆጠሩ ፡ እንደዚሁም ፡ ኩሽም ፡ ኑር ፤ ገራድ ፡
ናስር ፤ ድል ፡ ሰገድ ፡ . . . . , ያሉበት ፡ ፺ ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩት ። ጦርነቱንም ፡ የገ
መረው ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ ነው ። እርሱም ፡ አሥራት ፡ ከሚባለው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡
ጋር ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ገጥመው ፡ ሲዋጉ ፡ ድል ፡ ሰገድ ፡ አሥራትን ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ገል
ብጦ ፡ ሲጥለው ፡ ናስር ፡ የሚባለው ፡ በሰይፍ ፡ መትቶ ፡ ጭንቅላቱን ፡ ከአካሉ ፡
ለይቶ ፡ ገደለው ። የቀሩትም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሸሹ ። ይማም ፡ አህመድ ፡ በበኩሉ ፡
ከብት ፡ ሊማርኩ ፡ ከነበሩት ፡ የክርስቲያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ ሲዋጋ ፡
ከርሱም ፡ ጋር ፡ እነፋራቃሃም ፡ ሁሴን ፡ እነኤሚር ፡ መሐመድ ፡ ዘሀርቡይ ፡ . . . . .
እየተጯጯሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እያነሡ ፡ ተዋግተው ፡ አሸነፉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡
በየግንባራቸው ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ያሸነፉት ፡ እስላሞች ፡ ድልበድ ፡ ከሚባል ፡ ሥፍራ ፡
ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ስለአገኙት ፡ ድል ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለን ፡ ሲባ
ባሉ ፡ . . . , . ቆይተው ፡ ከዚያ ፡ ምርኮአቸውን ፡ ሰብስበው ፡ በጀዳህ ፡ በኖጎብ ፡ በኩል ፡
አድርገው ፡ ሁሉም ፡ በየአገራቸው ፡ ተመለሱ ። ይማም ፡ አህመድም ፡ በድል ፡ አድ
ራጊነት ፡ በደስታ ፡ ሐረር ፡ ገብቶ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ። የማረከውንም ፡ ምርኮ ፡
ለየጓደኞቹ ፡ አከፋፈለ» ።

በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ በረዥሙ ፡ ሲተርክልን ፡
የምንመለከተው ፡ ግራኝ ፡ ከሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ጦርነት ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ እንደተመለሰ ፡
ከዚያ ፡ ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ተጉዞ ፡ ጦር ፡ እየላከ ፡ ከአዳል ፡ መብረቅ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡
ከነአቤል ፡ መዋጋቱን ፡ ከራስ ፡ ባንያት ፡ ጋር ፡ በዚሁ ፡ በአቤል ፡ አማካይነት ፡ ተስማ
ምቶ ፡ ለጦርነት ፡ የማትመቸዋን ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ በዘዴ ፡ አስለቅቆ ፡ ደዋሮ ፡ እን
ደልቡ ፡ መግባቱን ፡ ነው ። ራስ ፡ ባንያት ፡ የንጉሡ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ እንደመ
ሆኑ ፡ መጠን ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ባለፈው ፡ ሁሉ ፡ ጦርነት ፡ በወገኑና ፡ በንጉሡ ፡
ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ጉዳት ፡ ሲያውቅ ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ ያገሩ ፡ ጠላት ለፈረስና ፡
ለጦርነት ፡ እማትመች ፤ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ተገኝቶ ፡ በአቤል ፡ በኩል ፡ እሳልፈኝ ፡
የሚል ፡ ቃል ፡ ሲልክበት ፡ በሚያውቃት ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ጠላቱ ፡ መቸ
ገሩን ፡ ሲያውቅ ፡ ቢቻል ፡ አድፍጦም ፡ ፊት ፡ ለፊትም ፡ ተዋግቶ ፡ ሊያጠፋው ፡ ባይ
ቻል ፡ ሊመልሰው ፡ ይገባው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የጦር ፡ መሪነቱን ፡ ተግባር ፡ ሳይፈ
ጽም ፡ በዕርቅ ፡ ተደራድሮ ፡ መንገድ ፡ ለቆ ፡ ግራኝን ፡ በአገሩ ፡ አስገባ ። ይኸን ፡ የመ
ሰለው ፡ መላላት ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ወታደራዊ ፡ ሥርዓት ፡
የሞት ፡ ፍርድ ፡ ያስፈርዳል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ራስ ፡ ባንያት ፡ መንገድ ፡ መልቀቁ ፡
ለግራኝ ፡ ረዳው ፡ እንጂ ፡ ራሱ ፡ ባንያት ፡ ግን ፡ ከነጦሩ ፡ ለግራኝ ፡ አልገባም ። እንዲያ

ውም ፡ ባለፈው ፡ ተጸጽቶ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ለንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ በወሲል ፡ በአማራ ፡ ሳይንት ፡ አውራጃ ፡ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ እንመለከታለን ።

ግራኝ ፡ ከራስ ፡ ባንያት ፡ በስምምነት ፡ ከገባ ፡ ወዲህ ፡ የሆን ፡ አምባ ፡ ገኘ ፡ (እስላም ፡ የነበረውን) ፡ ራጂህን ፡ አባብሎ ፡ ከአስገባ ፡ በኋላ ፡ በርሱና ፡ በእዶሌም ፡ ጦር ፡ እነፋኑኤልን ፡ እነክፍሌን ፡ እነራስ ፡ ባንያትን ፡ ከአስወጋና ፡ ራሱም ፡ ከተዋጋ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ተመለሰ ። እንደተመለሰ ፡ ከሕዝብ ፡ ላይ ፡ የሚወጣው ፡ ግብር ፡ እስምንት ፡ ላይ ፡ እየተከፈለ ፡ ለደሀ ፡ ለወታደር ፡ ለእስረኛ ፡ ይሰጥ ፡ በማለቱ ፡ ከሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲንና ፡ ከኤሚሮቹ ፡ ጋር ፡ መጣላቱን ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ።

ግራኝ ፡ አህመድ ፡ በዚህ ፡ ይዞታው ፡ ሡልጣኑንና ፡ ጥቂቶቹን ፡ ኤሚሮች ፡ እየተጫነ ፡ ብዙውን ፡ ሕዝብና ፡ ደሀን ፡ አስደስቶ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ለድል ፡ አድራጊነቱ ፡ ምኞት ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ለማሳበር ፡ እንደቃጣ ፡ ያስረዳል ። ይኸን ፡ አሳቡን ፡ ለሐረር ፡ ግዛት ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ የሚቆጠረው ፡ ሡልጣን ፡ ኡመር ፡ ዲንና ኤሚሮቹ ፡ ቢቃወሙትም ፡ የራሱን ፡ የአዳልና ፡ የዓረብ ፡ ጦር ፡ ይልቁንም ፡ የሱማሌን ፡ ነገድ ፡ ይዞ ፡ በጦርነት ፡ አስፈራርቶ ፡ ሐረር ፡ ገብቶ ፡ ጠላቶቹን ፡ ዝም ፡ አሰኝቶ ፡ የወራሪነት ፡ ፈቃዱን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳደረሰ ፡ ይታወቃል ። ሌሎቹ ፡ ኤሚሮች ፡ ከሡልጣኑ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ሲያድሙበት ፡ ሱማሌዎች ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ መታመናቸው ፡ የግራኝ ፡ እህት ፡ የሱማሌዎች ፡ ባላባት ፡ የማታን ፡ ሚስት ፡ መሆኗ ፡ ግራኝ ፡ ዘሩ ፡ ሱማሌ ፡ እንኳን ፡ ጨርሶ ፡ ባይሆን ፡ ከሱማሌ ፡ ዘር ፡ ያለው ይመስላል ። አድመኞቹም ፡ ቢፈልግ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ መካ ፡ ይሂድ ፡ ወደኛ ፡ ግን ፡ ቢመጣ ፡ እንወጋዋለን ፡ ማለታቸውም ፡ አገሩን ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ ማድረጋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ስደተኛ ፡ የሚቀመጥበት ፡ መካ ፡ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ ባለፈው ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ዘር ፡ መለሳይ ፡ ከሚባለው ፡ ወገን ፡ መሆኑን ፡ እየገለጸ ፡ መለሳይም ከሱማሌ ፡ ውስጥ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ነገድ ፡ አስመስሎታል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ጽሑፉ ፡ «ለክፉ ፡ ከፈለጉኝ ፡ እሔዳለሁ» ፡ ማለቱን ፡ ቢገልጽልን ፡ ባጠገቡ ፡ ያሉት ፡ የሚሉትን ፡ ለመስማትና ፡ ለመታዘብ ፡ ያደረገው ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ በአሳቡ ፡ እንኳን ፡ የአዳልንና ፡ የሐረርጌን ፡ ግዛት ፡ ሀበሻንም ፡ ድል ፡ አድርጌ ፡ እገዛለሁ ፡ ብሎ ፡ ቆርጦ ፡ የተነሣ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ በብልሃትም ፡ በጦርነትም ፡ በግድም ፡ በውዴታም ፡ ሡልጣኑንም ፡ ኤሚሮቹንም ፡ ሸሪፎቹንም ፡ ሽኾቹንም ፡ ነገዶቹንም ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡ አሳብሯል ። ነገዱንም ፡ ባላባቱንም ፡ አለቆቹንም ፡ ሁሉ ፡ የቆየ ፡ ቂማቸውን ፡ በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ እንዲበቀሉ ፡ ምክርም ፡ ትእዛዝም ፡ እያደረገ ፡ ባዲስ ፡ ኃይልና ፡ በጋለ ፡ መንፈስ ፡ በርሱ ፡ መሪነት ፡ ቀሰቀሷቸዋል ።

ስለዚህ ፡ ከሡልጣኑ ፡ ከታረቀ ፡ ወዲህ ፡ ከሐረር ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ እንደገና ፡ ዘምቶ ፡ ራሱ ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ እየተዋጋ ፡ እየዘረፈ ፡ አቡበከር ፡ ቀጢንን ፡

ወደ ፡ ቃግማ ፡ ልክ ፡ ዡግናውን ፡ የቃግማ ፡ ገዥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን አስወግዶ ፡ እንዳስማረከ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖትንም ፡ በአሳብ ፡ በመዛሪያ ፡ ከሚረዱት ፡ ሡልጣኖች ፡ ላንዱ ፡ ለአደኑ ፡ ሱልጣን ፡ እንደ ፡ መታያ ፡ ልክ ፡ ሚስቱን ፡ ለራሱ ፡ ዕቁባት ፡ እንዳደረጋት ፡ ከርሷም ፡ ልጅ ፡ እንደወለደ ፡ አንብበናል ። የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሚስት ፡ ከንጉሡ ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወይም ፡ ከታላቅ ፡ ቤተሰብ ፡ የምትወለድ ፡ ሳትሆን ፡ አትቀርም ። እርሷንም ፡ እንደ ፡ ዕቁባት ፡ ከዚያም አልፎ ፡ እንደሚስት ፡ አድርጎ ፡ መያዙ ፡ በዚህ ፡ ጋብቻና ፡ በርሷ ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ለመሳብና ፡ አገር ፡ ለማሳመን ፡ ስለምትረዳው ፡ ያሆናል ። ወይም ፡ የመልኳ ፡ ውበት ፡ ስለአማረው ፡ ይሁን ፡ ምክንያቱን ፡ በትክክል ፡ ለመረዳት ፡ አልቻልንም ። የሆን ፡ ሆኖ ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሚስት ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ በብዙ የጦርነት ፡ ጉዞው ፡ ላይ ፡ ያስከትላት ፡ ስለነበረ ፡ እንደ ፡ ድል ፡ ፀምበራ ፡ የወደዳትና ፡ ያከበራት ፡ ይመስላል ።

ስለከዳተኛው ፡ ወናግ ፡ ዡን ፡ አራብ ፡ ፋቂህ የሚተርክልን ፡ የአተራረኩ ፡ አኳሆን ፡ በፄ ፡ ናዖድ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገ ፡ እንጂ ፡ በፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ የተደረገ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ወናግ ፡ ዡን ፡ የስሙ ፡ ትርጓሜ ፡ የንጉሥ ፡ አንበሳ ፡ የስሙ ፡ ጥሩው ፡ የዳሞት ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ የወሰን ፡ ሰገድ ፡ ወንድም ፡ ሲሆን ፡ ወገኖቹን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አስቀያሚ ፡ መንገድ ፡ አታሎ ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ያሳረደበትና ፡ ይኸንንም ፡ ደግ ፡ እንደሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለሡልጣኑ ፡ ፎክሮ ፡ ራሱም ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ የዞረበት ፡ ምክንያት ፡ አይታወቅም ። ምናልባት ፡ በፄ ፡ ናዖድ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሙ ፡ ዳሞትን ፡ ያህል ፡ አገር ፡ እየገዛ ፡ እርሱ ፡ ግዛት ፡ አንሶት ፡ በዚሁ ፡ ተቀይሞ ፡ ይሆን ፡ አይታወቅም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸም ፡ ሁሉ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ርሱና ፡ እንደተባበሪው ፡ እንደ ፡ ድል ፡ በኢየሱስ ፡ አገርን ፡ ወገንን ፡ እየከዱ ፡ በተንኮል ፡ በክዳት ፡ በአመፃ ፡ የሚደሰቱ ፡ በየአገሩ ፡ በየዘመኑ ፡ አልፎው ፡ አልፎው ፡ አንዳንዶች ፡ አመፀኞች ፡ ይገኛሉ ። ይኸም ፡ በሚያምር ፡ የስንዴ ፡ አዝመራ ፡ መካከል ፡ እንክርዳድ ፡ እንደማይጠፋ ፡ ወናግ ፡ ዡንና ፡ ጓደኛው ፡ ድል ፡ በኢየሱስም ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። ከግራኝ ፡ አህመድና ፡ ከጦሩ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግተው ፡ እየደከሙ ፡ ጦርነቱንም ፡ ለመቀጠል ፡ የንጉሡ ፡ መድከም ፡ የግራኝ ፡ መበርታት ፡ ተስፋ ፡ ያስቆረጣቸው ፡ ሹማምንት ፡ ባለፈውም ፡ ወደፊትም ፡ በሚሆነው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ እንመለከታለን ። በነዚህም ፡ አለቆች ፡ ላይ ፡ ጨርሶ ፡ መፍረድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። የገዢግንነት ፡ የቁጭት ፡ የድፍረት ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ጸንቶ ፡ የመሞት ፡ መንፈስ ፡ ሁሉ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልምና ፡ አይፈረድባቸውም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከዳተኞቹ ፡ ወናግ ፡ ዡንና ፡ ድል ፡ በኢየሱስ ፡ መዛሪያና ፡ ጦራቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ለሡልጣኑ ፡ መግባት ፡ አነሡና ፡ በሹመትና ፡ በሥልጣናቸው ፡ ታግዘው ፡ በጓደኝነትና ፡ በግብዡ ፡ አታለው ፡ የዘርና ፡ የሃይማኖት ፡ ወገኖቻቸውን ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ሲያሳርዱ ፡ ፈጽሞ ፡ የከዳተኛ ፡ ጨካኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳናል ። ሌላ ፡ ማድረግ ፡ እንኳን ፡ ባይቻል ፡ ጊዜው ፡ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ገጽ ፡ ዛሬ ፡ ስማቸውና ፡ አፅማቸውን ፡ መውቀስ ፡ ይገባዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

### የዛሬ ፡ ጦርነት—የራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድና ፡ የአዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ፍጻሜ–ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ላዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የጻፈው ፡ ደብዳቤ ።

የግራኝ ፡ አህመድ ፡ መነሣት ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ ተገዝቶ ፡ የመጣው ፡ አዳዲስ ፡ መሣሪያና ፡ ይልቁንም ፡ መድፉ ፣ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ባዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በጦር ፡ አለቆቻቸውና ፡ በወታደሩ ፡ በነጋዴውም ፡ በገበሬውም በካህኑም ፡ በመነኰሴውም ፡ በሴቱም ፡ በልጁም ፡ ትልቅ ፡ መከራና ፡ ፍዳ ፡ አውርዶበታል ። የጦር ፡ አለቆች ፡ በየጦሩ ፡ ግንባር ፡ እየተጋፈጡ ፡ ሲዋጉ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ የሚሞተው ፡ ተማርኮ ፡ የሚገደለው ፡ እንደበሪያ ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ የሚሸጠው ፡ ለየአውራጃው ፡ ሡልጣን ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ተቆጥሮ ፡ መታያ ፡ የሚቀርበው ፡ ብዙ ፡ ነው ። መኳንንቱና ፡ ሹማምንቱ ፡ ተሸንፈው ፡ በሞቱ ፡ በተማረኩ ፡ ቍጥር ፡ የሚወዷቸው ፡ ሚስቶቻቸው ፡ በእስላሞቹ ፡ እጅ ፡ ይወድቃሉ ። የጨከነውና ፡ ያልወደደው ፡ የእስላም ፡ አለቃ ፡ የነዚያን ፡ ሚስት ፡ ለእስላሚቱ ፡ ሚስቱ ፡ ገረድና ፡ ፈጭ ፡ አድርጎ ፡ ይሰጣታል ። መልኳ ፡ አምሮት ፡ ደስ ፡ ያሰኘችው ፡ እንደሆነ ፡ አስልሞ ፡ ዕቁባት ፡ ያደርጋታል ። ክርስቲያኒቱም ፡ የማትፈቅደውን ፡ ሃይማኖት ፡ በግድ ፡ መያዝ ፡ የማትወደውን ፡ እስላም ፡ ባልና ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ ማድረግ ፡ ትገደዳለች ። ባጭሩ ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ በምርኮ ፡ የሚገኙ ፡ ሚስት ፡ ገረድ ፡ አሽከር ፡ ልክ ፡ እንደከብት ፡ እንደ ፡ ሸቀጥ ፡ ተቆጥረው ፡ እስላሞቹ ፡ የሚወዱትን ፡ ለራሳቸው ፡ እያስቀሩ ፡ የቀረውን ፡ ይገበያዩበታል ። ክርስቲያኑ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ በተማረከ ፡ ጊዜ ፡ ማራኪው ፡ የእስላም ፡ አለቃ ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ ግራኝ ፡ ቢጨክን ፡ ይገድለዋል ። አለዚያ ፡ አሥሮ ፡ ወሬ ፡ ነጋሪ ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ ያደርገዋል ። አንዳንዱን ደግሞ ፡ እንደበቅሎና ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ ዋጋ ፡ ውጣ ፡ ውረድ ፡ ተብሎ ፡ ከዘመዶቹ ፡ እየተከራከረ ፡ ብዙ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ እየተቀበለ ፡ ይለቀዋል ።

የግራኝ ፡ አህመድ ፡ አነሣሥ ፡ ያለፈን ፡ ሁሉ ፤ በቀል ፡ ለመመለስ ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ለመግዛት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርስቲያንነት ፡ አጥፍቶ ፡ እስልምናን ፡ ለመተከት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ተሸንፎም ፡ አሸንፎም ፡ የገባውን ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ እስላም ፡ እንዲሆን ፡ ይጠይቀዋል ። እምቢ ፡ ሲል ፡ ያስገድለዋል ። እሺ ፡ ብሎ ፡ የሰለመውን ፡ ትናንሽ ፡ ሹመት ፡ በመስጠት ፡ ምርኮኛ ፡ ሚስቱንና ፡ ልጁን ፤ በመመለስ ፡ ትንሽ ፡ አስተያየት ፡ ያደርግለታል ። በተረፈ ፡ በግራኝና ፡ በጦር ፡ አለቆቹ ፡ ፊት ፡ የተገኘ ፡ ገዳምና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሀብት ፡ ሙልጭ ፡ ብሎ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃጠልና ፡ አመድ ፡ ይሆናል ። ይኸም ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚጸልዩበት ፡ የሚገናኙበት ፡ የሚመኩበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ገዳም ፡ ከፊታቸው ፡ ጨርሶ ፡ ሲጠፋ ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ለመመለስ ፡ ይቀናል ፡ ተብሎ ፡

ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በዝርዝር ፡ እንደምናየው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያና ችው ፡ ቀናዒ ፡ የሆኑት ፡ መነኰሳትና ፡ ካህናት ፡ እንኳን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ሊለውጡ፡ ገዳማቸው ፡ ሲቃጠል ፡ በነበልባሉ ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ በመቃጠል ፡ የሃይማኖታ ቸውን ፡ ጽናት ፡ አሳይተዋል ።

እስላሞቹም ፡ በደረሱበት ፡ አውራጃና ፡ ወረዳ ፡ ቀበሌና ፡ መንደር ፡ ሁሉ ፡ እየገቡ ፡ መማሪያ ፡ የያዘውን ፡ እየገደሉ ፡ የቀረውንም ፡ ነጋዴና ፡ ገበሬ ፡ የሆነውን፡ በክርስቲያንነቱ ፡ ብቻ ፡ ሲፈጁት ፡ ሲዘርፉት ፡ ሲያምሱት ፡ ግራኝ ፡ ያልደረሰባቸው፡ አውራጃዎች ፡ ባለፈው ፡ ተስፋ ፡ ሳይቆርጡ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ለጦርነት ፡ ይዘጋጃሉ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተዋጉትም ፡ ያልተዋጉትም ፡ የክርስቲያን ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ከን ጉሣቸው ፡ እየታዘዙ ፡ የራሳቸውም ፡ ቁጭትና ፡ እልህ ፡ እየያዛቸው ፡ የወገ ንም ፡ ጥቃትና ፡ በደል ፡ እየተሰማቸው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እነአዝ ማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ እነራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሌሎችም ፡ ብዙ ፡ መኳንንትና ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ የሚያደርጉትን ፡ ውጊያና ፡ ትግል ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንመለከታለን። ግራኝ ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስንና ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድንም ፡ ከአሸነፈ ፡ ወዲህ ፡ ሸዋን ፡ እልፎ ፡ ወሎ ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ በጌምድርና ፡ ትግሬ ፡ ከዘለቀም ፡ ወዲህ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ የየአውራጃ ፡ ገዥዎች ፡ ባለፈው ፡ በክርስቲያኖች ላይ ፡ የደረሰው ፡ ድል ፡ መሆን ፡ በግራኝም ፡ እጅ ፡ ያለው ፡ በእነርሱም ፡ እጅ ፡ የሌለው ፡ የመድፍ ፡ መሣሪያ ፡ ተስፋ ፡ ሳያስቆርጣቸው ፡ ያለ ፡ ዕረፍት ፡ እየገጠሙ ስለሀገራቸው ፡ ስለ ፡ ንጉሣቸው ፡ ስለሃይማኖታቸውና ፡ ስለክብራቸው ፡ ጠንክረው ፡ እየተዋጉ ፡ የእስላሞቹን ፡ ጦር ፡ የመለሱበት ፡ አለቆቹን ፡ የገደሉበት ፡ ወይም ፡ማር ከው ፡ ለንጉሣቸው ፡ የላኩበት ፡ ቀን ፡ አለ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በግራኝ ፡ ጥብቅ ፡ ተዋጊነ ትና ፡ በመሣሪያው ፡ ጥራት ፡ ጠቅላላው ፡ ድል ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የእስላሞቹ ፡ ነበር። እስላሞቹም ፡ አሸንፈው ፡ በገቡበት ፡ አገር ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱን ፡ ገዳማቱን ፡ የንጉሡን ፡ ከተማዎች ፤ የሕዝቡን ፡ መንደር ፡ እየዘረፉ ፡ በማቃጠል ፡ ክርስቲያናዊ ውን ፡ ወገን ፡ በመፍጀት ፡ የልባቸውን ፡ ሲሠሩ ፡ ኖሩ ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፡በነዓዊ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በነዓዊ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ወደ ፡ አዳልና ፡ ወደ ፡ ሱማሌ ፡ አገር ፡ ባላባቱ ፡ ሸፍቶ ፡ ለዘ መቻ ፡ በሔዱ ፡ ጊዜ ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ ግፍ ፡ በተማረኪው ፡ እስላም ፡ በቤተ ፡ ሰቡም ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ መሥራታቸው ፡ መስጊዱንም ፡ መንደሩንም ፡ ማቃጠላቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባላባቱ ፡ ገበርሁ ፡ ካለ ፡ ወዲህ ፡ ያንኑ ፡ ግብር ፡ ከመቀበል ፡ በቀር ፡ ሃይማኖቱን ፡ ጨርሶ ፡ ለማጥፋት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በጊዜያቸው ፡ አሁን ፡ እስላሞቹ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ያህል ፡ ጨክነው ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ያሠቃዩ ዋቸው ፡ አይመስልም ። አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ወደዋናው ፡ ታሪክ ፡እን መለስ ።

ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ ከአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ተሸንፎ ፡ ዛሬ ፡ እሚባል ፡ ለጦርነት የማ ይመች ፡ አባራሬ ፤ የማይደርስበት ፡ ሥፍራ ፡ ሆኖ ፡ እስላሞቹ ፡ ሳይዘጋጁ ፡ በድን

ገት ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ እንደወጉትና ፡ እንዳሸነፉት ፡ ለንጉሡ ፡ ለዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድን ግል ፡ ላኩ ። ንጉሡም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ጽናት ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ ባይዘነጉት ፡ በዚህ ፡ በአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እንደሚገባው ፡ ሳይዋጋና ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡ ሳይ ጥል ፡ መሸነፉ ፡ ቅር ፡ እንዳሰኛቸው ፡ በዓረብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ይታያል ።

ስለዚህ ፡ ዋናውን ፡ ጦር ፡ አዝማችነት ፡ ለአዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ሰጥ ተው ፡ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድም ፡ በደረጃው ፡ መዋረድ ፡ ቅር ፡ ሳይለው ፡ ከአዝማች ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ በኅብረት ፡ እንዲሠራ ፡ በደብዳቤ ፡ አስጠንቅቀው ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ ከብዙ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ዛሬ ፡ ላኩ ።

ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ የትግሬ ፡ የአንጎት ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ የደሆኖ ፡ ወደብ ፡ ሹም ፡ ነው ። በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ ከግራኝ ፡ ተዋግቷል ። እነሆ ፡ በሚ ቀጥለው በርሱ ፡ አዝማችነት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ በዛሬ ፡ ተዋግተው ፡ እንደምን ፡ እንደተሸነፉ ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስና ፡ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድም ፡ እንደምን ፡ እንደሞቱ ፡ ልንመለከት ፡ ነው ። ዛሬ ፡ የሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ከዚሁ ከአይፈርስ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የማይርቅ ፡ ደዋሮ ፡ በሚባል ፡ ውስጥ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ስለዚሁ ፡ ጦርነት ፡ በቀጥታ ፡ አረብ ፡ ፋቂህ ፡ የሚለውን ፡ ቀጥለን ፡ እንመልከት ።

«ይማም ፡ አህመድ ፡ ከነጦሩ ፡ ወደ ፡ አንዱራ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ እስላሞቹ ፡ እስላሞን ፡ «እስላም ፡ ሰገድን» አሸንፈው ፡ እንዳባረሩት ፡ ጦሩም ፡ እንደፈረሰ ፡ የወሰን ሰገድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደተቃጠለች ፡ ሰምቶ ፡ ትልቅ ፡ ኀዘን ፡ ተሰማው ። የጦር ፡ አለቆቹን ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሹማምንቱን ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ እስላሞች ፡ በደዋሮ ፡ የሠሩትን ፡ ዘረፋ ፡ የጦራችንንም ፡ መሸሽ ፡ ሰማችሁን ፡ አላቸው ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ልከ ፡ አለቆች ከነጦራቸው ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አደረገ ። ብዙ ፡ ጦር ከብዙ ፡ ሹማምንት ፡ ጋር ፡ ከተሰበሰቡ ፡ በኋላ ፡ ለሁሉም ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ አዝማች ፡ (፩) ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ የአንጎቱን ፡ ገዥ ፡ ሾመ ።

ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ ንጉሡ ፡ በአንጎት ፡ በትግሬ ፡ በደሆኖ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ ሾሞ ፡ በጣም ፡ ይወደው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ሄደህ ፡ እስላ ሞችን ፡ ውጋ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ እስላሞ ፡ ይማም ፡ ከአንጾኪያ ፡ ከአበረረው ፡ ወዲህ ፡ ዛሬ ፡ በሚባል ፡ መግቢያው ፡ በሚያስቸግር ፡ ሥፍራ ፡ ሆኖ ለንጉሡ እንደዚህ ፡ የሚል .... ደብዳቤ ፡ ልኮ ፡ ነበር ። «ጦሬን ፡ በእስላሞቹ ፡ ፊት ፡ አሰልፌ ፡ ሳለ ድንገት ፡ ብቻዬን ያለጦር ፡ በነበርኩበት ፡ ሰዓት ፡ አድብተው ፡ በተንኮል ፡ አደጋ ፡ ጣሉብኝ ፡ ቢሆንም ፡ እስላሞቹ ፡ የማረኩብኝ ፡ ፈረሶች (፪) ፡ ጥቂቶች ፡

(፩) የተሩት ፡ ሁሉ ፡ ጦር ፡ በማገዝመታቸው ፡ አዝማች ፡ ሲባሉ ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ በተለይ ፡ የማዕርግ ፡ ስሙ ፡ ነበር ።

(፪) አረብ ፡ ፋቂህ ፡ ፈረስ ፡ ሲል ፡ ፈረሰኛውን ፡ ከነጦሩ ፡ ከንመሣሪያው ፡ ማሳየት ፡ ሲፈልግ ፡ ነው ።

ናቸው ፡ «ንጉሡም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ መለሰ» ፡ ከአንበጣ ፡ «የበረከተ ፡ ጦር ፡ ሰጥቼህ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልተጠቀምህበትም ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ ልኬልሀለሁና ፡ ተከተለው ። የሚያዝህንም ፡ ትእዛዝ ሁሉ ፡ እየሰማህ ፡ ታዘዘው ፡ እንጂ ፡ እንዳትቃወመው ፡ እስላሞቹን ፡ ለማጥፋት ፡ ረዳት ፡ ሁነው„ ።

ስለዚህ ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ጦሩን ፡ አስከትሎ ፡ ጉዞ ፡ ዠመረ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ፍቅረ ፡ ኢየሱስ ፡ ያዒ ፡ እስክንድር ፡ ( ልጃቸውን ፡ ያገበ ) አማች ፡ የትግሬው ፡ አሚር ፡ የሽሬውና ፡ የሠራዬ ፡ ሹማምንት ፡ ነበሩ ። በጠቅላላው ፡ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ያላቸው ፡ ፴ ፡ የትግሬ ፡ ሹማምንት ፡ ነበሩ ፡ ከነር ሱም ፡ ጋር ፡ የአንጎት ፡ ሕዝብ ፡ አብሮ ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ ተጉዘው ፡ አዋሽን ፡ አልፈው ፡ በዛሬ ፡ ከእስላም ፡ ጋር ፡ ተገናኙ ። ከዚያ ፡ የበላይነት ፡ መሾሙን ፡ የሚያስረዳውን ፡ የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ ለእስላሞና ፡ ለጦሩ ፡ አነበበ ። እስላሞም ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ቃል ፡ እታዘዛለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃሉን ፡ አሜን ፡ ብሎ ፡ ተቀበለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ሰላዮች ፡ እስላሞቹ ፡ አንዱራ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጹለት ። እስላሞቹም ፡ ወደሀገራቸው ፡ የሚመለሱ ፡ ስለመሰለው ፡ ለወታደሮቹ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ። እዚህ ፡ እስፍራችን ፡ እንዳለን ፡ እስላሞቹ ፡ ወደአገራቸው ፡ ለመመለስ ፡ ደልማ ይዳ ፡ ሲደርሱ ፡ ገስግሰን ፡ እንወጋና ፡ እንጨርሳቸዋለን ። ወታደሮቹም ፡ ጥሩ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ እንከተልሃለን ፡ ብለው ፡ አሳቡን ፡ ተቀበሉት ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ አንዱ ፡ ኢመር ፡ አንዱ ፡ ሰክር ፡ የሚባሉ ፡ ሰዎች ነበሩ ።

እነሱም ፡ እስላሞች ፡ ሆነው ፡ ሲኖሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ዞረው ፡ ከንጉሡም ፡ ተገናኝተው ፡ በሻርቃህ ፡ አገር ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ያንን ፡ እያስገበሩ ፡ በደስታ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ሚስቶቻቸውም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነበሩና ፡ እስላሞቹ ፡ ሻርቃህ ፡ የነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ማርከው ፡ ወስደውባቸው ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ የጦርነት ፡ አሳቡን ፡ በተረዱ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ መጥተው ፡ «ባለፈው ፡ ሁሉ ፡ በጠፋነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተጸጽተናል ፡ „ብለው ፡ የተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ አሳብ ፡ ገለ ጹለት ። ይማም ፡ አህመድ ፡ „ግድ ፡ የላችሁም ፡ አትፍሩ ፡ ብሎ ፡ ሚስቶቻቸውን፡ መለሰላቸው ። ቀጥሎም ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ወደኛ ፡ መምጣታችሁን ፡ ያውቃሉን ፡ አላቸው ፡ እነሱም ፡ ምንም ፡ „አያውቁም„ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከናንተ ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ እንድታደርጉልኝ ፡ እፈልጋለሁ ፡ አላቸው ፡ ምን ፡ ምን ፡ ብለው ፡ መለሱ ፡ ሰክር ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ እዚሁ ፡ ቅር ፡ ጓደኛህ ፡ ኢመር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ተመልሶ ፡ እመካከላቸው ፡ ገብቶ ፡ ነገሩን፡ ሁሉ ፡ ሰልሎ ፡ ሄዶን ፡ የምንዋጋበትን ፡ ሰፈውንና ፡ የሚመቸውን ፡ መንገድ ፡ ተመልሶ ፡ ይንገረን ፡ ይኸን ፡ ያደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለፈውን፡ ስሕተታችሁን ፡ ይቅር ፡ ይላችኋል ፡ አላቸው ። እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሰክር

ከወዚር ፡ አዶሌ ፡ ዘንድ ፡ ቀረ ፡ ኡመር ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡
በመካከላቸው ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ አድሮ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ የአሦር ፡ (የተሲያት)
ጸሎት ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወዚር ፡ አዶሌ ፡ መጣ ፡ ወዚሩም ፡ ይዞት ፡
ወደ ፡ ይማም ፡ ወስዶ ፡ አገናኘውና ፡ ይማም ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ ወሬ ፡ ጠየቀው ፡
እርሱም ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ መካከል ፡ ገብቼ ፡ አየሁዋቸው ፡ መንገዳቸውንም ፡ ተረ
ዳሁ ፡ ከአለፈው ፡ አሳባቸው ፡ ምንም ፡ አልለወጡም ፡ አለ ፡ „ቍጥራቸው ፡ ስንት ፡
ይሆናል„ ። ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ከአንጾኪያው ፡ ሽሽት ፡ ወዲህ ፡ የባሌ ፡ የደዋሮ ፡
የወናግ ፡ አምባ ፡ የወናግ ፡ ጀደብ ፡ (ገደብ) ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ ወደአገራቸው ፡ ተመ
ልሰው ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ አለቆቻቸው ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰ„ ፡ ቢሆ
ንም ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ ጦር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ንገረኝ ፡ „ቢለው„ ፡ የት
ግሬ ፤ የአንጎት ፡ የፈጠጋር ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ አለ ። ስንት ፡ ፈረስ ፡ አላቸው ፡ ብሎ ፡ ቢጠ
ይቀው ፡ ፳፻ ፡ የሚሆኑ ፡ የሪፍ ፡ ፈረሰኞች ፡ ሁሉም ፡ ብረት ፡ ለበስ ፡ (ጥሩር)
የሆነውን ፡ እንደለበሱ ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ያሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ሰፌ ፡ ነው ፡
ጠባብ ፡ ለፈረሰኛ ፡ ጦርነት ፡ ይመቻል ፡ አይመችም ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ከዚህ ፡
አሁን ፡ ካለንበት ፡ ተነስተን ፡ ወደእነሱ ፡ ብንሔድ ፡ እሰፌ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ እና
ገኛቸዋለን ፡ ከንድ ፡ ቁልልቃ ፤ ከለበት ፡ ወገን ፡ የመጣንበቸው ፡ እንደሆነ ፡
ግን ፡ እየገፋናቸው ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ እንወርዳለን ፡ ክርስቲያኖቹም ፡ የያዙት ፡ የላ
ይኛውን ፡ ሾረት ፡ ነው ። እነሱ ፡ የሰፈሩት ፡ እቁልልቃው ፡ ጫፍ ፡ ስለሆነ ፡
ከግርጌው ፡ ትልቅ ፡ ገደል ፡ አለ ፡ ብንወጋቸውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ (አላህ) ፡
ፈቃድ ፡ ድሉን ፡ ብናገኝ ፡ ከቁልልቃዋ ፡ ላይ ፡ ሊሸሽ ፡ የፈለገ ፡ ሁሉ ፡ ገደል ፡
ገብቶ ፡ ይሰባበራል ፡ እንጂ ፡ መሸሻ ፡ ቦታ ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ አስረዳው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ፈረሰኞቹን ፡ አስጠራና ፡ ከሰላይ ፡ የሰማውን ፡
ገለጸላቸው ፡ ከእነሱም ፡ መካከል ፡ ግማሹ ፡ እዚህ ፡ እንዳለን ፡ ክርስቲያኖቹን ፡
ጠብቀን ፡ እንውጋ ፡ የቀረው ፡ አሉበት ፡ ድረስ ፡ ሔደን ፡ እንውጋቸው ፡ ሲባባሉ ፡
ይማም ፡ የናንተ ፡ አሳብ ፡ በፍጹም ፡ አይረባም ፡ ብሎ ፡ እዚሁ ፡ ቀርተን ፡ ክርስ
ቲያኖቹ ፡ ሲመጡብን ፡ እንዋጋ ፡ ያሉትን ፡ ነቀፈና ፡ ይልቅስ ፡ የማግረብ ፡ ጸሎት ፡
ከደረግን ፡ በኋላ ፡ እንጓዝ ፡ አለ ፤ እነሱም ፡ ፈቃዳችን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለ
ሱለት ። ስለዚህ ፡ ሰፈሩን ፡ መድፉን ፡ ከነጓዙ ፡ እንዲጠብቅና ፡ በማግሥቱ ፡ ጧት ፡
እንዲከተለው ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስርን ፡ አዘዘውና ፡ ጉዞው ፡ ተጀመረ ። ይማም ፡
እንደ ፡ ጎርፍ ፡ የሚፈሰውን ፡ ሠራዊቱን ፡ አፊት ፡ አስቀድሞ ፡ እርሱ ፡ ከኋላ ፡
ሆኖ ፡ ከማታ ፡ ዠምሮ ፡ ጎሕ ፡ እስኪቀድ ፡ ድረስ ፡ ተጓዘ ። ፋቂህ ፡ አቡብ
ከር ፡ (አርሹናህ) ፡ በሠራዊቱ ፡ መካከል ፡ ሆኖ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ቁራን ፡ እየደ
ገመ ፡ ንግግር ፡ (ዲስኩር) ፡ ሲያደርግ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡
ከበ ፡ (እየሔደ?) ፡ ያዳምጥ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ እየተጓዙ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጉብታ ፡
ሥፍራ ፡ ሲደርሱ ፡ መንገድ ፡ መሪው ፡ ቆመና ፡ ይኸውና ፡ አሁን ፡ ክርስቲያኖቹ ፡
አሉበት ፡ ደርሰናል ፡ ፀሐይ ፡ እስኪፈነጥቅ ፡ ድረስ ፡ እዚህ ፡ እንቆይ ፡ ስለአለ ፡
ሁሉም ፡ ከየበቅሎው ፡ እየወረደ ፡ ከድካሙ ፡ ለማረፍ ፡ ተኛ ። ይማም ፡ መንገድ ፡

መሪውን ፡ ልክ ፡ እፊቱ ፡ አስመጣና ፡ አብረን ፡ እንሂድና ፡ መንገዱን ፡ እየመረ
መርን ፡ ሥፍራውን ፡ እንሰልል ፡ ቢለው ፡ እኔ ፡ በጣም ፡ ደክሜአለሁ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ አንድ ፡ አርኪያህ ፡ የሚባል ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ የዞረ ፡ የክርስቲያን ፡ ሹም፡
መንገዱን ፡ የሚያውቅ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ይማም ፡ አርኪያህን ፡ አስመጣና፡
እርሱን ፡ እንደያዘ ፡ ሌሊቱን ፡ ሔደ ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ ገራድ ፡ ሻሙንና ፡
ማታን ፡ ነበሩ ። .........፡ እንደ ፡ ሔዱም ፡ የውሻ ፡ ጬኸት ፡ የመሰለ ፡
ሰሙና ፡ የምን ፡ ጬኸት ፡ ነው ፡ እየተባባሉ ፡ ሲጠያየቁ ፡ እናንተ ፡ እዚህ ፡ ቆዩ፡
እኔ ፡ መርምሬ ፡ እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ጬኸት ፡ ወደሰማበት ፡ በኩል ፡ ሲሔድ፡
ውሻ ፡ የሚጬኽበት ፡ መንደር ፡ አየ ። አርኪያህም ፡ እናንተ ፡ የመንደር፡ ሰዎች፡
ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ተጣራ ፡ እነርሱም ፡ እረ ፡ ማነህ ፡ በጭለማ ፡ የምትጣራ ፡
ቢሉት ፡ እኔ ፡ ከደዋሮ ፡ የመጣሁ ፡ ሹም ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡ እኋ
ላህ ፡ ያሉት ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ ቢሉት ፡ ወታደሮች ፡ ናቸው ፡ ተክለ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ እስላሞችን ፡ ለመውጋት ፡ እንድትረዳኝ ፡ ወታደርህን ፡ ይዘህ ፡ እንድት
መጣ ፡ ብሎ ፡ ልኮብኝ ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ መለሰ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንደረተኞቹ፡
ወደ ፡ ኋላህ ፡ ተመለስና ፡ እስከ ፡ ጉብታው ፡ ድረስ ፡ ሂድና ፡ እዚያ ፡ ስትደርስ፡
ወደ ፡ ሸለቆው ፡ ሥር ፡ ወርደህ ፡ ወደ ፡ ቁልልታው ፡ ስትወጣ ፡ ተክለ ፡ ኢየ
ሱስን ፡ እዚያው ፡ ሠፍሮ ፡ ታገኘዋለህ ፡ አሉት ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ተመልሶ ፡ ነገረው ። ክርስ
ቲያኖቹ ፡ እዚያው ፡ የመዠመሪያው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ እተናገረበት ፡ ሥፍራ ፡
ላይ ፡ መሆናቸውን ፡ ጨምሮ ፡ ገለጸለት ። ስለዚህ ፡ እስላሞቹ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡
ሰፈራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ለጓደኞቻቸው ፡ ነገሩና ፡ ጨርሶ ፡ እስኪነጋ ፡ እዚሁ ፡
ቆይተው ፡ ሲነጋ ፡ የጧት ፡ ጸሎታቸውን ፡ አድርሰው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወዚር ፡ አዶሌ ፡
ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ ከነጠሩ ፡ መንገድ ፡ መሪው ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ እየ
መራ ፡ ጉዞውን ፡ ዠመረ ፡ እነርሱም ፡ ከጉብታው ፡ ወርደው ፡ እሸለቆው ፡ ሲደ
ርሱ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ ድንኳን ፡ አዩ ። ክርስቲያኖቹም ፡ እስላሞቹ ፡ ወደ ፡ ሸለ
ቆው ፡ ሲሸቆለቆሉ ፡ አይተዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ከርቻቸውን ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ እስላ
ሞቹ ፡ መጡ ።

ይማም ፡ ሌላው ፡ ወታደር ፡ እስኪለጥቅ ፡ ድረስ ፡ እሸለቆው ፡ ሆኖ ፡ ይጠ
ብቅ ፡ ነበር ። እነሰበርዲን ፡ እነአሊ ፡ እነአብደላ ፡ እነአደቅ ፡ ሌሎችም ፡ ፳ ፡ የሚ
ሆኑ ፡ ይማምን ፡ ሳይጠብቁ ፡ ወንዙን ፡ ተሻግረው ፡ ነበር ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ እነ፡
ፈንጅ ፡ ሰበር ፡ ያሉበት ፡ ፴ ፡ የሚሆን ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ ነበርና ፡ እነዚህ ፡ ከክ
ርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ጦርነቱን ፡ ዠመሩ ። .. .፡ ወዚር ፡ አዶሌ ፡ ግን ፡ ይማም ፡
እስኪደርስለት ፡ እሸለቆው ፡ ሆኖ ፡ ሲጠብቅ ፡ በደረሰለት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ እፈ
ረሶቻቸው ፡ ተጋቡና ፡ ሽቅብቱን ፡ ወጥተው ፡ እሜፍ ፡ ከሉት ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡
ጋር ፡ ተጋጠሙ ። ጦርነቱን ፡ የዠመረው ፡ ሰበርዲን ፡ ነው ፡ ከርሱም ፡ ቀጥሎ
አሊ ፡ ኢል ፡ ዋራዲና ፡ አብደላ ፡ ተከታትለው ፡ እጠላት ፡ ጦር ፡ መካከል ፡ ገቡ።

አደቅ ፡ ቤን ፡ ማሂና ፡ አሊ ፡ ጎይታም ፡ ሁለቱ ፡ በንድነት ፡ ገሥግሠው ፡ ተክለ፡ ኢየሱስን ፡ ውጊያ ፡ ገጠሙትና ፡ አደቅ ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ በሰይፍ ፡ በትር ፡ አንገቱን ፡ መትቶ ፡ ጭንቅላቱን ፡ ከሌላው ፡ አካሉ ፡ ለይቶ ፡ ጣለና ፡ ገደላው ፡ . . . . ። ይማምና ፡ ጓደኞቹም ፡ ከሌሎቹ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ጋር ተጋጥመው ፡ ብጥብቅ ፡ ሲዋጉ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሽሽት ፡ ዠመሩ ። እስላሞቹም ፡ እየተከታተሉ ፡ መግደልና ፡ መማረክ ፡ ዠመሩ ። እስላሞ ፡ (ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ) በገራድ ፡ ይማጅ ፡ ልጅ ፡ በአቡበከር ፡ እጅ ተገደለ ። ናስር ፡ የሚባለው ፡ የመርጋ (ጃ) ሹምና ፡ ሹተላይ ፡ የሚባለው ፡ ሹም ፡ በፉራቃሃም ፡ አሊ ፡ እጅ ፡ ተማረኩና ፡ ሹተላይና ፡ ናስር ፡ ወዲያው ፡ እስላም ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደሚገኘው ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ጋር ፡ እየተዋጉ ፡ ሹተላይ ፡ ሞተ ።

በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ነገደ ፡ ኢየሱስ ፡ የሚባለው ፡ የጂናህ ፡ (ጊና ፡ አገር ?) ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በገራድ ፡ አህሙሹ ፡ እጅ ፡ ዘምቢል ፡ የሚባለው ፡ የቡሬ ፡ ሹም ፡ በአቡበከር ፡ እጅ ፤ የሲሬ (ሺሬ) ፡ ሹም ፡ ሳሙኤል ፡ ባንድ ፡ እስላም ፡ እጅ ፤ አብርሃም ፡ የሚባለው ፡ የጸለሞት ፡ ( አገው ፡ ውስጥ ፡) ሹም ፡ በአብሳማ ፡ ኑር ፡ እጅ ፤ የሐማሴን ፡ ሹም ፡ በሳሊህ ፡ እጅ ፤ ተገደሉ ። አሰር ፡ (አሥራት? ) ፡ የሚባለውን ፡ ሹም ፡ ጣህር ፤ ክፍሌ ፡ የሚባለውን ፡ የቀዳ ፡ ሹም ፡ (የተክለ ፤ ኢየሱስ ፡ ልጅ ፡) ፡ ሐሰን ፤ ጊዮርጊስ ፡ የሚባለውን ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ የፈራቃሃም ፡ አሊ ፡ ወታደር ፡ ማረኩዋቸው ። ይስሐቅ ፡ የሚባለው ፡ የቤጌምድር ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ አሊ ፡ ማጅራህ ፡ በሚባል ፡ ሱማሌ . . . . . እጅ ፡ ሞተ ። በዚህ ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ የሞቱት ፡ የትግሬና ፡ የአማራ ፡ መኳንንት ፡ ቍጥራቸው ፡ ፩፻፷ ፡ ነው ። የሞተው ፡ የፈረሰኛና ፡ የእግረኛ ፡ ወታደር ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ሺ . . . . . . የሚቆጠር ፡ ነው ። ፳ ፡ ፈረሰኛ ፡ ብቻ ፡ ሲያመልጥ ፡ ፭፻ ፡ ፈረሶች ፡ ድንኳኑ ፡ ባሪያው ፡ በቅሎው ፡ ዕቃው ፡ ሁሉ ፡ በእስላሞች ፡ እጅ ፡ ወደቀ ።

ወዚር ፡ አዶሌ ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ እዚሁ ፡ እክርስቲያኖቹ ፡ ሠፈር ፡ እቁልልታው ፡ ላይ ፡ ሠፈሩን ፡ አድርጎ ፡ ሲቀመጥ ፡ ይማም ፡ ፶ ፡ ፈረሰኛ ፡ ይዞ ፡ የሸሹትን ፡ እስከ ፡ አዋሽ ፡ ድረስ ፡ አባሮ ፡ ዴል ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አደረ ፡ በማግስቱ፡ አብድ ፡ ኤን ፡ ናስርን ፡ ከጓዝ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ተመበት ፡ ወደ ፡ አንዱራህ ፡ ሔደና ፡ ከዚያ ፡ ከናስር ፡ ጋር ፡ ጃሚት ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ሔደ ። ወዚር ፡ አዶሌም ፡ ከነበረበት ፡ ሠፈሩ ፡ ተነሥቶ ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ወደዚሁ ፡ ወደ ፡ ጃሚት ፡ (ሀሚት ) መጣና ፡ ሁሉም ፡ ሰላምታ ፡ እየተሰጣጡ ፡ ተገናኙ ፡ ስለአገኙትም ፡ ድል ፡ በደስታ ፡ እየተነጋገሩ . . . . . . . ሌሊቱን ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ አሳለፉ ።

በማግስቱ ፡ ይማም ፡ የተማረከውን ፡ ሰውና ፡ ፈረስ ፡ መሣሪያ ፡ አቅርቡልኝ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። ፭፻ ፡ ፈረሶች ፡ በቀይ ፡ የተጠለፈ ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ጮራ ፡ በሚያበሩ ፡ በወርቅ ፡ ዕቃ ፡ የተጫኑ ፡ ከርቻቸው ፡ ሐር ፡ የለበሱትን ፡ አቀረቡለት ። ዳዊት ፡ (የእሥራኤል ፡ ንጉሥ) ፡ ይለብሰው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ የጥሩር ፡ ልብስ ፡ በራስ ፡ ላይ ፡ የሚደፉ ፡ እንደ ፡ ሳቡር ፡ (አገር ፡) ያለ ፤ የግብጽ ፡ አገር ፡ ሥራ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰይፍ ፤ ነጭ ፡ ቀርጫት ፡ የሚመሳሰል ፡ የሀበሾቹ ፡ ጋሻ ፡ ቀረበ ። ይማም ፡

ልዑል ፡ አምላኩን ፡ አመሰገነ ። ከምርከው ፡ ሁሉ ፡ ከበቅሎም ፡ አምስተኛውን ፡ ዕጣ ፡ እያስነሣ ፡ በቅሎውን ፡ ፈረሱን ፡ ስለሃይማኖታቸው ፡ ለሚዋጉት ፡ አደለው ። በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ጦርነት ፡ የዋለው ፡ አንድ ፡ ተናጋሪ ፡ «ከይማም ፡ ጋር ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ውያለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ የሚያምሩና ፡ የሚበረክቱ ፡ በቅሎና ፡ ፈረሶች ፡ በፍጹም ፡ አላየሁም» ፡ ብሏል ።

ከእስረኞቹም ፡ የሾተላይና ፡ የአሰር ፡ (አሥራት) (፩) ጭንቅላት ፡ ተቆረጠ ። ክፍሌ ፡ በ፴ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ወገኖቹ ፡ ገዙት ፤ ጊዮርጊስ ፡ የሚባለው ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ታስሮ ፡ እንደ ፡ ቆየ ፡ እግር ፡ ብረቱን ፡ ሰብሮ ፡ ጠፋና ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ሔዶ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ክርስቲያን ፡ ገደለው ። ለጊዮርጊስ ፡ ወንድም ፡ ይማም ፡ ምሕረት ፡ አድርጎለት ፡ ከዚያም ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጥቶ፡ «ይኸን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዘህ ፡ ሔደህ ፡ መልሱን ፡ አምጣልኝ» ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ወደ ፡ ሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ላከው ፡ ደብዳቤውም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነው ።

«በእግዚአብሔር ፡ በመሐሪውና ፡ በይቅር ፡ ባይው ፡ ስም ፡ (በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል) ፤ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ደኅንነትና ፡ ቡራኬ ፡ ለነቢዩ ፡ ለመሐመድ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ለማይነሣው ። የተላከ ፡ ከይማም ፡ አህመድ ፡ የኢብራሂም ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የሚዋጋ ፡ ይድረስ ፡ ለሀበሻ ፡ ንጉሥ ፤ ከሰላምታ ፡ በኋላ ፡ ለላይኛው ፡ ንጉሥ ፡ (ለእግዚአብሔር) ፡ ቀጥ ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ የሚታዘዘው ፡ ? ፡ (፪) ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ እንደደረሰህ ፡ ፋኑኤል ፡ የማረካቸውን ፡ አቡበከር ፡ ቤን ፡ ሞስሊምንና ፡ ጃልቲን ፡ ላክልኝ ፡ እኔም ፡ በነርሱ ፡ ምትክ ፡ ጊዮርጊስን ፤ ክፍሌን ፤ ናስርን ፡ የኤል ፡ ሜርጃይ ፡ ጌታ ፤ ሹተላይን ፡ አራቱን እልክልሃለሁ ። እስላም ፡ እስላምን ፡ ክርስቲያን ፡ ክርስቲያንን ፡ ስለሚረዳው ፡ እኔ ፡ ሁለት ፡ ስጠይቅህ ፡ ላንተ ፡ የምሰጥህ ፡ አራት ፡ ናቸው ። እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባገር ፡ ገብተን ፡ ተመልሰን ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ የምንመለስ ፡ አይምስልህ ፡ አገሪቱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በሙሉ ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ እስክንይዝ ፡ ድረስ ፡ እንዳንመለስ ፡ ወይም ፡ እዚሁ ፡ ለመሞት ፡ ቆርጠናል ፡ ስለዚህ ፡ እውነተኛው ፡ ዳኛ ፡ በመካከላችን ፡ ይፈርዳል »

ይቺን ፡ ደብዳቤ ፡ አጣጠፈና ፡ ወስደህ ፡ ለንጉሡ ፡ ስጥ ፡ ብሎ ፡ እስረኛውን ፡ የጊዮርጊስን ፡ ወንድም ፡ ላከውና ፡ ሔደ ። እርሱም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ደርሶ ፡ ደብዳቤውን ፡ አስረከበ ። ንጉሡም ፡ ደብዳቤው ፡ የሚለውን ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ በኩራት ፡ እየተሳደበ ፡ ፊቱ ፡ ፍም ፡ እስኪመስል ፡ ድረስ ፡ በታላቅ ፡ ኃይል ፡ ተቆጥቶ ፡ ዘውዱን ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ እመሬት ፡ ወረወረው ። በንዴትም ፡ ምርኮኞቹን ፡ እስላሞች ፡ እፊቱ ፡ አስመጥቶ ፡ አስገደላቸው ፡ ለደብዳቤውም ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠም» ።

(፩) ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተናገራቸውን ፡ ይደጋግማል ፡ በዚያ ፡ ስለሙ ፡ ይልና ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ አንገታቸው ፡ ተቆረጠ ፡ እያለ ፡ ይጽፋል ።

(፪) እዚህ ፡ ላይ ፡ የጐደለ ፡ ወይም ፡ ያልተካከለ ፡ ጽሑፍ ፡ አለ ።

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ በመጣሪያ ፡ ልዩነት ፡ በሥፍራ ፡ አመራረጥ ፡ ድሉን ፡ ማረጋገጡን ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ በአሁኑ ፡ ምዕራፍ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀር ፡ በሰላይ ፡ በኩል ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ መጠቀሙን ፡ እናያለን ። እንዚያ ፡ ኡመርና ፡ ሳከር ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ እስላሞች ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ወገን ፡ መስለው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አብረው ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ገብተው ፡ ብዙ ፡ ምሥጢርና ፡ ወሬ ፡ ሲነግሩት ፡ ለግራኝ ፡ ጦር ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ለግራኝም ፡ ሁለቱ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መግባታቸው ፡ እስከዚህም ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያወቁትና ፡ የነገሩት ፡ ሳይበቃው ፡ ቀርቶ ፡ ከሁለት ፡ አንዳቸውን ፡ ሳከርን ፡ እንደመያዣ ፡ አስቀርቶ ፡ ኡመርን ፡ መልሶ ፡ ወደ ፡ ተክሌ ፡ ኢየሱስ ፡ ሠፈር ፡ ልኮ ፡ ሲያስልል ፡ ግራኝ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የጠላቱን ፡ የተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ አሳብና ፡ በትክክል ፡ የሚገኝበትን ፡ ሥፍራ ፡ የጦሩን ፡ ቍጥር ፡ ለማወቅ ፡ እንደፈለገ ፡ ኡመርም ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ መከከል ፡ እንደ ፡ ወገን ፡ አብሮ ፡ እየተጫወተ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ የጦር ፡ ፕላን ፡ ሲሰበስብ ፡ መንገድና ፡ ለጦርነት ፡ ምቹ ፡ ሥፍራ ፡ የሆነውን ፡ ሲያጠና ፡ ሰንብቶ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ወገኖቹ ፡ ተመልሶ ፡ ያየውን  የሰማውን ፡ ለግራኝ ፡ ነገረው ። እንደዚህ ፡ ያለውም ፡ ስለላ ፡ በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ አገልጋይ ፡ በመሆኑ ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በዓለም ፡ ያሉ ፡ መንግሥታት ፡ የየጠላታቸውን ፡ ምሥጢርና ፡ አሳብ ፡ ለመረዳትና ፡ ለነገሩ ፡ መድኃኒትና ፡ መውጫ ፡ ለመፈለግ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እያፈሰሱ ፡ ይታገሉበታል ።

ግራኝ ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ አኳኋን ፡ ከግጥሚያው ፡ በፊት ፡ እወታደሩ ፡ መከከል ፡ የራሱ ፡ ወታደር ፡ የነበረውን ፡ ኡመርን ፡ እየላከ ፡ ምሥጢሩን ፡ ሲቀዳበት ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ወይም ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ የግራኝን ፡ አሳብና ፡ ምሥጢር ፡ ለማወቅ ፡ ያደረጉትን ፡ የስለላ ፡ ሥራ ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስለአላገኘን ፡ መጠኑን ፡ ልናመዛዝነውና ፡ ልንረዳው ፡ አልቻልንም ። መጠኑ ፡ ዓይነቱ ፡ ትጋቱ ፡ ከግራኝ ፡ ያነሰ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ አስጊ ፡ ጠላታቸውን ፡ ማሰለላቸው ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። አራብ ፡ ፋቂህም ፡ በንዳንድ ፡ በታ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ዝርዝሩ ፡ ሳይገባ . . . ፡ የክርስቲያን ፡ ስላዮች ፡ ላለቆቻቸው ፡ እንደዚህ ፡ አሉ ፡ እያለ ፡ ጫፉን ፡ ያነሣል ።

ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ተጠግተው ፡ በሚኖሩት ፡ እስላሞች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ግራኝ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ በተማረኩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መጠቀሙን ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ ተገንዝበናል ። አሁንም ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ አዝማች ፡ አርኪያህ ፡ ወገኖቹን ፡ ከድቶ ፡ የተማረከች ፡ ሚስቱን ፡ ለማግኘትና ፡ ከአሸናፊው ፡ ጋር ፡ ለመለጠፍ ፡ ሲል ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ እስላሞቹን መርቶ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የጦር ፡ ሠፈር ፡ እንደ ፡ ወሰደ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ መንደረተኞች ፡ ''እኔ ፡ አርኪያህ ፡ የደዋሮ ፡ ሹም ፡ ነኝ ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ ልረዳ ፡ መጥቼ ፡ መንገድ ፡ ጠፋብኝ'' ፡ እያለ ፡ እየጮኸ ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ የሠፈረበትን ፡ ለማወቅ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እንደአታለላቸው ፡ ተመልክተናል ። ስለ

ዚህ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር በነበሩት ፡ እስላሞች ፡ የሃይማኖት ፡
ወንድምነትን ፡ እያሳየ ፡ ለተማረኩት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሹሙትን ፡ ሚስትንና ፡
ልጅን ፡ በመመለስ ፡ መልካም ፡ ኑሮን ፡ እያመለከተ ፡ በጊዜና ፡ በአጋጣሚ ፡ ነገር ፡
መጠቀም ፡ የሚያውቅ ፡ ትጉህና ፡ ጠርጣሪ ፡ መሪ ፡ መሆኑን ፡ እንገነዘባለን ። እንደዚህ
ያለውም ፡ ጠባይ ፡ ከጥብቅ ፡ ተዋጊነትና ፡ ከጀግንነት ፡ ጋር ተደባልቆ ፡ በአንድ ፡
ሰው ፡ እጅ ፡ ሲሆን ፡ በመሣሪያ ፡ በጀግንነት ፡ በትጋት ፡ የሚበልጠው ፡ እስኪገኝ፡
ድረስ ለዚህ ፡ ሰው ሁል ፡ ጊዜ ፡ የአሸናፊነት ፡ በር ፡ እንደ ፡ ተከፈተለት ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ አልፈን ፡ ግራኝ ፡ ላዬ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡
ስንመለከት ፡ አገሪቱን ፡ በሙሉ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ለመውረር ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡
አድርጎ ፡ መነሣቱን ፡ እንረዳለን ። በአራት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁለት ፡ እስላሞች ፡
ለመለወጥ ፡ ማሰቡ ፡ የእስላሞቹን ፡ ሕይወት ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ማስበለጡን ፡
ለማሳየት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ዛሬ ፡ የምለቃቸው ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነገ ፡ ተመ
ልሰው ፡ በእጄ ፡ መውደቃቸው ፡ አይቀርምና ፡ እስከዚያ ፡ በተማረኩት ፡ በሁለት
የእስላም ፡ ሹማምንት ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስባቸው ፡ ላድናቸው ፡ ብሎ ፡ ይሆን ? ፡
አናውቅም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አፄ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ስመ ፡
መንግሥታቸው ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ምንም ፡ በብዙ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ እንደቀናው
ቢያውቁ ፡ ለግራኝ ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ አሳባቸውን ፡ አላላሉም ። እንዲያውም ፡
ይህ ፡ የንጉሥነት ፡ ዘር ፡ የሌለው ፡ ጊዜና ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ያነሣው ፡ ሰው ፡ ይኸን
የመሰለ ፡ የዛቻ ፡ ደብዳቤ ፡ ደፍሮ ፡ በመጻፉ ፡ በጣም ፡ ተናደው ፡ ሌላ ፡ ምንም፡
ማድረግ ፡ ባይችሉ ፡ ከንጉሥነታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ዘውዳቸውን ፡ ከራሳቸው ፡
አንስተው ፡ ወርውረው ፡ ለዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ለዚህ ፡ መደፈር ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን
እስላሞች ፡ አስገድለዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ለደብዳቤውም ፡ መልስ ፡ አለመስጠታቸው
ከርሱ ፡ ጋር ፡ በመጻጻፍ ፡ ንጉሣዊ ፡ ክብራቸውን ፡ ለርሱ ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡
ላለማዋረድና ፡ በጠቅላላው . . „አላውቅህም„ . . ለማለት ፡ ያሰቡ ፡ ይመስላል ።

ይኸም ፡ ሁናቴ ፡ ባንድ ፡ ተከብሮ ፡ ተፈርቶ ፡ በኖረ ፡ ንጉሥና ፡ ጊዜ ፡ ባነሣው
ተራ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ሲፈጸም ፡ የኖረ ፡ ነውና ፡ አያስደንቅም ። አፄ ፡ ልብነ ፡
ድንግል ፡ ከሰሎሞናዊው ፡ ዘር ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የወረዱ ፡ አባቶቻቸው ፡
እነ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እነ ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰፊውን ፡ የኢትዮጵያን ፡
መንግሥት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ሲገዙ ፡ የይፋትን ፡ የዓዳልን ፡ የእስላም ፡ ባላባት ፡
እንደሌላው ፡ አውራጃ ፡ እንደ ፡ ደዋሮ ፡ እንደ ፡ ሐድያ ፡ ሲያስገብሩ ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ።
ራሳቸው ፡ ባባቶቻቸው ፡ አልጋ ፡ ከተቀመጡ ፡ ወዲህ ማህፉዝ ፡ የሚባለውን ፡ የግ
ራኝን ፡ ሚስት ፡ የድል ፡ ወንበራን ፡ አባት ፡ ከአሸነፉ ፡ ወዲህ ፡ ይኸው ፡ ያባቶቻ
ቸው ፡ ሥልጣንና ክብር ፡ በርሳቸው ፡ እጅ ፡ በሆነበት ፡ ዘመን ፡ በጦር ፡ ግንባር
መሸነፍን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይታሰብ ፡ እንደመዓት ፡ የጣለባቸው ፡ ብቻ ፡ መሆ
ኑን ፡ ቢያምኑም ፡ ካንድ ፡ ዘሩ ፡ ካልታወቀ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ከሚባል ፡ ጋር
ደብዳቤ ፡ መጻጻፍ ፡ ግን ፡ ሊዋጥ ፡ የማይቻል ፡ መራራ ፡ ጉርሻ ፡ ሆኖባቸዋል ፡
ማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፣ ፲፰ ።

### የግራኝ ፡ አህመድ ፡ መቃመም—ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ለግራኝ ፡ የላከው ፡ ደብዳቤና ፡ የመጣለት ፡ መልስ—የዝሆን ፡ ዱር ፡ (ዳሞት) ጦርነት ።

የዛሬ ፡ ጦርነት ፡ ከተፈጸመ ፡ ወዲህ ፡ የአራብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገልጽልን ።

ሀ—አህመድ ፡ ከነጦሩ ፡ ከገሚት ፡ ወደቃንቡራህ ፡ (ከደዋሮ ፡ ገበያ ፡ በላይ ፡) በሔደ ፡ ጊዜ ፡ በገበያ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በክብር ፡ ተቀብሎ ፡ እንዳስተናገደው ፡ ...... የሱማሌ ፡ ወታደር ፡ እንግዲህ ፡ በብዙ ፡ ምርኮና ፡ ገንዘብ ፡ ከበርን ፡ ከይማም ፡ ተደብቀን ፡ ወዳገራችን ፡ እንገባለን ፡ ማለታቸውን ፡ ግራኝ ፡ ሰምቶ ፡ ስላይ ፡ በመካከላቸው ፡ ማስቀመጡን ።

ለ—አዝማች ፡ ሀይቢ ፡ (ሃይብ) ፡ የሚባለው ፡ የጋቱር ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ንጉሡ ፡ ሽረውት ፡ የነበረና ፡ አሁን ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ መሞቱን ፡ ሰይሰሙ ፡ ንጉሡ ፡ ተክለ ፡ ኢየሱስን ፡ እርዳ ፡ ብለው ፡ ልከውት ፡ ሳለ ፡ ከድቶ ፡ ለግራኝ ፡ ገብቶ ፡ ሰልሞ ፡ ለግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከማናቸውም ፡ ሰው ፡ ይበልጥ ፡ በጦርነትም ፡ ማስረጃ ፡ በመስጠትም ፡ እንደረዳው ።

ሐ-አንድ ፡ አምዱ ፡ የሚባል ፡ በግራኝ ፡ ጦር ፡ እጅ ፡ የነበረ ፡ ምርኮኛ ፡ በግራኝ ፡ አህመድና ፡ በደዋሮ ፡ ሹማምንት ፡ በአዳሉ ፤ በፋንኤል ፡ በጊዮርጊስ ፡ በድል ፡ ሰበር ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ግራኝ ፡ ግብሩን ፡ ሊቀበል ፡ እንጂ ፡ ደዋሮን ፡ ላያጠፋ ፤ እነሱም ፡ ሊገብሩ ፡ እንጂ ፡ ላይዋጉ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሳይሰማ ፡ እርቅ ፡ ተደራድረው ፡ መገበራቸውን ፡ የመጨረሻውንም ፡ ስምምነት ፡ እፍጻሜ ፡ ያደረሰ ፡ ዚን ፡ የሚባል ፡ መሆኑን ፡ ይገልጽልናል ። ከዚሁ ፡ አያይዞ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ንጉሡን ፡ እስከ ፡ ዳሞት ፡ ድረስ ፡ ተከታትሎ ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ መዋጋቱንና ፡ ሌላውንም ፡ ሁሉ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይተርካል ።

«የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ በዛሬ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ መሸነፍ ፡ ገበርጌ ፡ (ዋጅ ፡ በአዋሽና ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ መካከል) ፡ ሳለ ፡ ሰምቶ ፡ በጣም ፡ አዘነ ፤ አሁንም ፡ እስላሞቹ ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ ስላገኙ ፡ ወዳገራቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ መስሎት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እስላሞቹ ፡ በአይፈርስ ፡ በኩል ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ እልማያ ፡ (በዝቋላ ፡ ዙሪያ) ፡ ተጓዙ ። ወደዚህም ፡ አገር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ለጓደኞቹ» ፡ የኤልማያ ፡ አገር ፡ ከበሬ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የለውምና ፡ መንገዱ ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ አገሩ ፡ በጦርና ፡ በመርዛማ ፡ ቀስት ፡ እየወጋ ፡ እንዳያስቸግረን ፡ ከብቱን ፡ አትንኩበት ፡ «ብሎ ፡ አዘዘ ፡ .... ፡ ከዚያም ፡ እስላሞቹ ፡ በምርኮ ፡ የሰበሰቡትን ፡ አየ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ፸፤ ፡ በቅሎና ፡ በሪያ ፡ ነበረው ። ወታደሩንም ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበና» ፡ ምንድነው ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የሰበሰባችሁት ፡ የእርድ ፡ ከብት ፡ በቅሎ ፤ ባሪያ ፡ ሁሉ ፡ ወዴት ፡ ትወስዱታላችሁ ፡ «አላቸው ፡ እነሱም" ፡ አገራችን ፡ ይዘን ፡ ለመግባት ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ወደምትሔድበት ፡ ይዘን ፡ እንከተልሃ

ለን ፡ "ቢሉት" ፡ አሳባችን ፡ ቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከብ
ትና ፡ በቅሎ ፡ ዕቃ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ነው ። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ይዛችሁስ ፡ እንደምን ፡
አድርጋችሁ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ትዋጋላችሁ ? ‹አላቸው› ፡ ታዲያ ፡ ምን ፡
እናድርገው ፡ "ብለው ፡ ቢጠይቁት» ፡ ቆዩ ፡ እኔ ፡ ማድረግ ፡ የሚገባችሁን ፡ አሳያች
ሁአለሁ„ ፡ ብሎ ፡ ጉዞው ፡ ቀጠለና ፡ እተራሮች ፡ መከከል ፡ እሚገኝ ፡ ጠባብ ፡
መንገድ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ እኋላ ፡ ያለው ፡ በርሱ ፡ እስኪደርስበት ፡ ድረስ ፡ ጠበቀ ።
ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ ሲደርስ ፡ „በሉ ፡ የያዛችሁትን፡ሁሉ፡ጣሉ ፡ በሪያና ፡ በቅሎ ፡ ያለው ፡
ብቻ፡ እበቅሎው ፡ ላይ ፡ ይጫን ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ በእጁ ፡ አይሸከም ፡ ትእዛዜን ፡
የተላለፈ ፡ ቢገኝ ፡ ጭንቅላቱን ፡ እቆርጠዋለሁ„ ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡
ሁሉ ፡ እያለቀሰ ፡ በኤል ፡ ማያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ጣለ ። ሸለቆውና ፡ መንገዱ ፡ ሁሉ ፡
በዕቃ ፡ በባሪያ ፡ ተሞላ . . . . . . ።

ከዚያ ፡ እስላሞቹ ፡ ኤል ፡ ማርዚር ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ ደረሱ ፤ ይኸም ፡
አገር ፡ ዛቃላህ ፡ (ዝቋላ) ፡ እሚባል ፡ ተራራ ፡ ስር ፡ ነው ። በርሱም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡
ትልቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለ ፡ . . . . . እስላሞቹ ፡ ሲጠጉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡
ጠባቂ-ዘበኞች ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ዕቃና ፡ ልብስ ፡ ሰብስበው ፡ ወደተራራ ፡
ወጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የእስላሞቹ ፡ ወታደሮች ፡ ተከታትለው ፡ ዕቃውን ፡ ቀምተው ፡
ሰዎቹንም ፡ ገደሏቸው ። እስላሞቹም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ ሠፍረው ፡ ሌሊ
ቱን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እሳት ፡ ለቀቁበት ። . . . . የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ሁለት ፡
ቀን ፡ የሚያስሔድ ፡ ርቀት ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ሆኖ ፡ ቃጠሎውን ፡ ሲመለከት ፡ እስ
ላሞቹ ፡ ወደርሱ ፡ እንደሚጓዙ ፡ ተገነዘበና ፡ "እስላሞች ፡ ወደኛ ፡ ይጓዛሉና ፡ ድረስ„
ብሎ ፡ ዳሞት ፡ ለሚገኘው ፡ ለወሰን ፡ ሰገድ ፡ ላከበት ። እንደዚሁም ፡ ከተማረከ ፡
ወዲህ ፡ በግድ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፤ ወደ ፡ ሰለመው ፡ ወደአውራይ ፡
አትማን ፡ ላከበትና ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡' (አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡)
መጣ ፤ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ግን ፡ አገሩ ፡ ዳሞት ፡ ሩቅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እስ
ላሞቹ ፡ በበኩላቸው ፡ ከዛቃላ ፡ ተነሥተው ፡ ወደባደቂ ፡ ለመሔድ ፡ ዱከም ፡
ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ላሊበላ ፡ (ፈጠጋር ፡ ውስጥ ፡) እሚባል ፡ አገር ፡ ሔደው ፡
ሠፈሩ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ እንደተዋጋው ፡ አሁንም ፡ ከተማ
ውን ፡ (ባደቄን ፡) ለመከላከል ፡ ሳይዋጋ ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ አስበው ፡ ነበርና ፡
ይማም ፡ „ወደ ፡ ባደቄ ፡ ከተማ ፡ እንግባ ፡ ንጉሡም ፡ ሲመጣ ፡ እዚያው ፡ ላይ ፡
እንወጋዋለን» ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በከተማው ፡ መከከል ፡ አንድ ፡ የእ
ሳት ፡ ቃጠሎ ፡ አዩና ፡ ይማም ፡ ወደእስልምና ፡ የዞረውን ፡ ሃይቢን ፡ «ምንድነው ፡
ይኸ ፡ ቃጠሎ» ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ እርሱም ፡ ‹አላውቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እዚሁ ፡
እንደርና ፡ ነገ ፡ ወሬውን ፡ እንሰማለን» ፡ ብሎ ፡ የዚህኑ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያሰላስሉ ፡ ለን
ጉሡ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያገቡ ፡ የነበሩ ፡ የባደቄ ፡ የእስላም ፡ ነጋዴዎች ፡ መጥተው ፡ ገን
ዘቡን ፡ ለይማም ፡ ሰጡት ፡ ይማም ፡ የቃጠሎውንና ፡ እንደዚሁም ፡ ስለንጉሡ ፡ ጠየ
ቃቸው ፡ እነሱም ፡ ንጉሡ ፡ ያለው ፡ ገበርጌ ፡ ነው ፡ አንዱን ፡ ሹሙን ፡ «እስላ

ሞቹ ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ አቃጠልን ፡ እንዳይሉ ፡ በደቂ ፡ ከእስላሞቹ ፡ በፊት ፡ ቀድመህ ፡ ሒድና ፡ የኔንና ፡ የወንድሞቼን ፡ ቤት ፡ አቃጥለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ግን ፡ በመጽሐፍ ፡ የተከለከለ ፡ ስለሆነ ፡ አታቃጥለው፡፡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘውና ፡ እንደምታዩት ፡ መቃጠሉ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስረዱት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ፋራቃሃም ፡ አሊን ፡ ማታንን ፡ ሱማሌውን ፡ ልከ ፡ „ሒዱና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አቃጥሉ፡፡ ፡ ብሎ ፡ ላካቸውና ፡ ደርሰው . . . . መገርመሪያ ፡ በውስጡና ፡ በጉልላቱ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ወርቅ ፡ እንሥተው ፡ ሲጨርሱ ፡ አቃጠሉት ። እከተማው ፡ ውስጥ ፡ በ፫ ፡ ጉድጓድ ፡ ደብቀውት ፡ የነበረውን ፡ ልብስ ፡ ወሰዱ ፡ . . . . . . ከዚያ ፡ ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ ከዱከም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ንጉሡ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ አንዶጥናህ ፡ (እንጦጦ ?) ሔዱ ፤ በዚያም ፡ ውስጡ ፡ በቀይ ፡ በሰማያዊ ፡ በብጫ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ የተሣለ ፡ የሰው ፡ የአንበሳ ፡ የአዕዋፍ ፡ ስእል ፡ ወዳለበት ፡ ወደንጉሡ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ እያዩ ፡ ከተደነቁ ፡ በኋላ ፡ አቃጠሉት ። ንጉሡ ፡ ቃጠሎውን ፡ በቅርብ ፡ ሆኖ ፡ ተመልክቶ ፡ በደቂ ፡ ከነበረው ፡ ቤቱ ፡ ይበልጥ ፡ ለዚህ ፡ ቤቱ ፡ ቃጠሎ ፡ ከልብ ፡ ያለፈ ፡ አዘነ ፡ ፡እስላሞቹ ፡ እከተማዬ ፡ ገብተው ፡ መኖሪያ ፡ ቤቴን ፡ አቃጠሉት ፡ ለኔ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከማየት ፡ መሞት ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር፡፡ ፡ ብሎ ፡ ለሹማምንቱ ፡ ተናግሮ ፡ አለቀሰ ። ወዲያው ፡ ጦሩን ፡ አሰልፎ ፡ እስላሞቹን ፡ ለመውጋት ፡ መጣ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእስላሞቹና ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የአዋሽ ፡ ወንዝ ፡ ሞልቶ ፡ ነበርና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ማለፍ ፡ አልቻሉም ፡ . . . . . . ከዚያ ፡ ንጉሡን ፡ ከነጦሩ ፡ ያዩት ፡ እስላሞች ፡ ለቪዚር ፡ አዶሌ ፡ ቪዚሩ ፡ ለይማም ፡ ነገረውና ፡ ፴ ፡ ፈረሰኞች ፡ ነገሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ላከ ፡ . , . . እነሱም ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ማዶ ፡ ለማዶ ፡ ሆነው ፡ እየተያዩ ፡ ተሰዳደቡ ። ከዚያ ፡ እስላሞቹ ፡ ወደይማም ፡ ተመልሰው ፡ ያዩትን ፡ አዝማቹ ፡ ራሱ ፡ ንጉሡ ፡ መሆኑን ፡ ነገሩት ። በዚህ ፡ መካከል ፡ ንጉሡ ፡ ከነጦሩ ፡ አዋሽ ፡ ዳር ፡ ሳሉ ፡ እንግዴህ ፡ እስላሞቹ ፡ ወደኛ ፡ እኛም ፡ ወደነሱ ፡ መሔድ ፡ ካልቻልን ፡ እንሒድ ፡ አሉ ፤ ወደ ፡ ወረባ ፡ ሔደው ፡ ሠፈሩ ። ንጉሡም ፡ ከአዋሽ ፡ ዳር ፡ ሲሔድ ፡ እኋላ ፡ በቀሩት ፡ የእስላም ፡ ወታደሮች ፡ ዘንድ ፡ ፍርሃት ፡ ተነሣ ፤ የያዙትንም ፡ ስምንት ፡ መድፍ ፡ እመንገድ ፡ ጣሉት ፤ እስላሞቹ ፡ ሁሉ ፡ በዝናም ፡ ምክንያት ፡ ቆይተው ፡ በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ አዋሽ ፡ ደረሱና ፡ ሠፈር ፡ አደረጉ ። ከዚያም ፡ ይማም ፡ ስንቅ ፡ ይሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ ገራድ ፡ ጁሻህን ፡ ላከውና ፡ ወደበረህ ፡ ሔዱ ። በዚያም ፡ የአድማስ ፡ (፩) ፡ ልጅ ፡ ናዖድ ፡ ያሠራት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረች ፡ እስላሞቹ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ የመጡት ፡ ሠንጋ ፡ ለመሰብሰብ ፡ እንጂ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መኖሩን ፡ አላወቁም ፡ ነበርና ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በገቡ ፡ ወርቅ ፡ ሞልቶበት ፡ አገኙ ፤ ተጠፍጥፎ ፡ ከወርቅ ፡ ለብቻው ፡ የተሠራ ፤ የወርቅ ፡ ስንና ፡ ብርት ፡ የብርም ፤ የሐር ፡ ልብስ ፡ በብዙ ፡ አግኝተው ፡ ሰብስበው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደይማም ፡ ተመልሰው ፡ ሔዱና ፡ በበረህና ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ የወርቅ ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡

(፩) አድማስ ፡ የሚለው ፡ አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ነው ።

ዘርዝረው ፡ ነገሩት ፡ . . . . . . . . ፡ በዚህ ፡ መከከል ፡ ይማም ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ቃሞ ፡ እሠፈር ፡ ተኛ ፡ እስላሙ ፡ ሁሉ ፡ ስለርሱ ፡ ደህንነት ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ፡ . . . በዚህ ፡ አገር ፡ ግራኝ ፡ ቀኝ ፡ እስላሙ ፡ ሁሉ ፡ በዙሪያው ፡ እየዘመተ ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ልብስ ፡ ሰብስቦ ፡ ቲንሹም ፡ ትልቁም ፡ ሀብታም ፡ ሆነ ። በዚያም ፡ ፩ ፡ የግብጻዊው ፡ ጳጳስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረችና ፡ ሀብቷን ፡ ዘርፈው ፡ . . . . . . ሲጨርሱ ፡ አቃጠሏት ።

የሐበሻው ፡ ንጉሥ ፡ ከዳሞት ፡ የመጣውን ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ አገኘና ፡ የስንዴ ፡ የገብስ የፍሬ ፡ የወይን ፡ ያትክልት ፡ አገር ፡ የነበረችውን ፡ በሐበሻ ፡ አገር፡ እንደርሷ ፡ የሌለውን ፡ ወረባን ፡ እስላሞች ፡ እንደምን ፡ አድርገው ፡ ዘርፈው ፡ እንዳጠፏት ፡ ተረከለት ፤ ንጉሡን ፡ ከነጠሩ ፤ በምግብ ፡ ረገድ ፡ ችላ ፡ የምትኖር፡ ይቺው ፡ ወረባ ፡ ነበረች ። ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ስለ ፡ ወረባ ፡ ጥፋት ፡ በጣም ፡ አዘነ፡ ወደንጉሡም ፡ እጅ ፡ እየነሣ ፡ ተናገረና ፡ ከዚያ ፡ ለእዚያ ፡ ለሚገኙት ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንት ፡ እንደዚህ ሲል ፡ ዲስኩር ፡ ተናገረ ። እስላሞች እንደምን እንደዚህ ሊያደርጓችሁ ቻሉ ? ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ አባቶቻችሁ ፡ አያቶቻችሁ ፡ ከናንተ ፡ በፊት ፡ ሞተዋል ። ይህ ፡ ሰው ፡ (ግራኝ) ፡ እንዳደረጋችሁ ፡ ያለ፡ አንድም ፡ የእስላም ፡ ተወላጅ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አላደረገም ። ይህም ፡ የደረሰው፡ እናንተ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ በሠራችሁት ፡ በድልና ፡ ግፍ ፡ የተነሣ ፡ ነው ። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ፡ አገራችሁን ፡ በነዚህ ፡ በእስላሞች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠና ፡ እናንተ ፡ እያላችሁ ፡ ደዋሮ ፤ ፈጠጋር ፤ ባደቂ ፡ የንጉሡ ፡ ከተማ ፡ የበረሀ ፡ መሬት፡ ተበዘበዘ ። ጳጳሳችሁ ፡ ከነቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ተቃጠሉ ፤ አሁን ፡ እስላሞቹ ፡ ከገራችን ፡ ውስጥ ፡ ገነት ፡ እሆነችዋ ፡ እወረባ ፡ ገብተዋል ፤ ሀብቷንና ፡ ፍሬዋንም፡ አይተዋልና ፡ እንግዲህ ፡ ሊወጡ ፡ አይችሉም ።

ይኸን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ መኳንንቱና ፡ ሹማምንቱ ፡ በኀዘን ፡ ተነኩ ፤ እንደዚህም ፡ አሉት ፡ ። እስካሁን ፡ የምንጠብቀው ፡ አንተን ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ከመጣህልን ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ እየተዋጋን ፡ እንሞታለን ። ወሰን ፡ ሰገድ፡ በመካከላቸው ፡ በጣም ፡ የተከበረ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ ሁሉም ፡ ከንጉሡ ፡ ይበልጥ ፡ ይፈሩት ፡ ነበር ፤ ተመጽሐፋቸው ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ጻፉት ፡ የድሐ፡ አባት ፡ ብለው ፡ ሠይመውት ፡ ነበር ። ለሹማምንቱም ፡ ።እንግዲህ ፡ ያለፈው ፡ አልፏልና ፤ አሁን ፡ ለወደፊቱ ፡ ሰው ፡ ሁኑ ፤ ለአገራችሁ ፡ ለሃይማኖታችሁ ፡ ለንጉሣችሁ ፡ ስትሉ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ፡ ።አላቸውና ፡ ለይማም ፡ አህመድ ፡ ደብዳቤ ፡ አዘጋጀ ፤ በደብዳቤውም ፡ መገምረያ ፡ ላይ ፡ የይማምን ፡ አረመኔነት ፡ ሃይማኖት ፡ የሌለው ፡ መሆኑንም ፡ ጠቅሶ ፡ ከዚያ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነበር ፡ ።እናንተ ፡ እስላሞች ፡ እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡ ቀድሞ ፡ ባገራችሁ ፡ ላይ ፡ መጥተን ፡ አገራችሁን ፡ ዘርፈን ፡ ቤታችሁን ፡ አቃጥለን ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ለናንተ ፡ ኃይል ፡ ሰጥቶ ፡ አሸነፋችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ አይገኝምና ፡ እስከ ፡ አሁን ፡

ያደረግኸው ፡ ይበቃሃል ፤ ወደ ፡ አገርህ ፡ ተመለስ ። መቼም ፡ ንጉሡን ፡ በሽምብራ፡ ኵሬ ፡ አሸንፌ አባረርሁ ፡ በአንጻኪያ ፡ በዛሬ ፡ ይኸን ፡ ይኸን ፡ አደረግሁ ፡ የንጉሡንም ፡ ጦር ፡ ጨረስሁ ፡ እያልህ ፡ መላልሰህ ፡ እየተናገርህ ፡ መመከትህ ፡ አይቀርም ። አሁን ፡ ግን ፡ አታብዛው ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ተቋቁሟል ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ዓይተኸውም ፡ ሰምተኸውም ፡ የማታውቅ ፡ የጕራጌ ፤ የጋፋት ፤ የዳሞት ፤ የእናርያ ፡ የኤዝ ፡ ዘይት ፡ (በጕጃምና ፡ በወሊጋ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ?) የጅማና ፡ እነሱን ፡ የመሳሰሉት ፡ አገሮች ፡ ሕዝብ ፡ የንጉሡ፡ አገልጋዮች ፡ ከሆኑት ፤ ጋር ፡ አብረው ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ እስከሁን ፡ የሰበሰብኸውን ፡ ምርኮና ፡ ወርቅ ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ አገርህ ፡ ተመለስ ። እምቢ ፡ ካልህ ፡ ቅዳሜ፡ እንገናኛለን ። ካንተ ፡ በዕድሜ ፡ የሚበልጠውን ፡ ወንድምህን ፡ ገራድ ፡ አቡንን ፡ የኢብራሂምን ፡ ልጅ ፡ የገደልሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ጦሩን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በታትኜ ፡ ያባረርሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ እስከሁን ፡ እንደተዋጋሃቸው ፡ ያሉ ፡ ሹማምንት ፡ እንዳልመስልህ ፡ እኔ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ነኝ» ።

ይኸን ፡ ጽፎ ፡ ሰጥቶ ፡ የላከው ፡ መላክተኛ ፡ እወዚር ፡ አዶሌ ፡ ዘንድ ፡ መጣ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ታሞ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፡ ወዚር ፡ አዶሌ ፡ ወደ ርሱ ፡ ሄዶ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ነገረውና ፡ ‹እንዴት ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ? ፡ መላክተኛው ፡ እንደዚህ ፡ ታመህ ፡ መተኛትህን ፡ ያየ ፡ እንደሆነ ፡ ለጓደኞቹ ፡ ተመልሶ ነግሮ ፡ ልባቸውን ፤ መልሶ ፡ ያጠነክረዋል ፡ አለ› ፤ በዚያ ፡ ከነበሩት ፡ አንዱ ፡ «ያጐትህ ፡ ልጅ ፡ ዘሀርቡይ ፡ መሐመድ ፡ ባንተ ፡ ፋንታ ፡ ይቀመጥና ፤ መላክተኛው ፡ ሲመጣ ፡ ይማም ፡ ይኸውልህ ፡ እንለዋለን» ፡ ብሎ ፡ ቢናገር ፡ የቀሩት ፡ ‹ይኸ ፡ ጥሩ ፡ ምክር ፡ አይደለም ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ ይማምን ፡ ያውቁታል ። መላክተኛውም ፡ ወደነሱ ፡ ተመልሶ ፡ ይማምን ፡ አግኝቼ ፡ አነጋግርሁት፡ ሲላቸው ፡ ምን መሳይ ፡ ነው ፡ ማለታቸው ፡ አይቀርም ፤ እርሱም ፡ ይኸን ፡ ይመስላል ፡ ብሎ ፡ የዘሀርቡይን ፡ መልክ ፡ የገለጸላቸው ፡ እንደሆነ ፡ የሁለታችሁን ፡ የመልክ ፡ ልዩነት ፡ የሚያውቁት ፡ ይማም ፡ ስለሞተ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ የሚመስለውን ፡ ሰው ፡ አስቀምጠው ፡ አነጋገሩ ይላሉና ፡ ይኸኛው ፡ ደኅና ፡ ምክር ፡ አይደለም ፤ ይልቅስ ፡ ይማም ፡ ልብሱን ፡ ይልበስና ፡ በርትቶ ፡ ይቀመጥ ፤ መላክተኛውም ፡ ገብቶ ፡ ያነጋግረው» ፡ አሉ ፡ ይማምም ፡ «የተሻለው ፡ ምክር ፡ የናንተ ፡ ነው» ፡ አላቸው ።

በማግስቱ ፡ የእስላሞቹ ፡ ጦር ፡ ፈረሱን ፡ ጭኖ ፡ የጦር ፡ መሣሪያውንና ፡ ጋሻውን ፡ ይዞ ፡ ተሠልፎ ፡ እንደቆመ ፡ መላክተኛው ፡ ገባና ፡ ደብዳቤውን ፡ ለይማም፡ አቀረበለት ። ይማምም ፡ በደብዳቤ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ከተገነዘበ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን፡ ለጓደኞቹ ፡ አስረዳቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ሹማምንት ፡ አንዱ ፡ በለው ፡ አብዱ ፡ የሚባለው ፡ ለመላክተኛው ፡ ‹ሂድና ፡ ለጌታህ ፡ እንደዚህ ፡ በለው ፡ እነዚህ ፡ ይዋጋሉ ፡ ያልኻቸውን ፡ የዳሞትና ፡ የጕራጌ ፡ ሰዎች ፡ ችሎታቸውን ፡ እናውቀዋለን ፤ እነሱም ፡ ሥራቸው ፡ እርሻ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ዛፍ ፡

እየቆረጡ ፡ ወደኛ ፡ አገር ፡ ከማመላለስ ፡ በቀር ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ በፍጹም ፡ አይተው ፡ አያውቁምና ፡ በምናውቃቸው ፡ በሮች ፡ በከንቱ ፡ አታስፈራራን፡ አንተ ፡ ግን ፡ እንደምትለው ፡ ጉበዝ ፡ ከሆንህ ፡ በመሬትህና ፡ በገርህ ፡ ላይ ፡ ነንና ፡ ተዋጋን ፤ «ብሎ ፡ ነገረው ። እርሱም ፡ ሲጨርስ ፡ ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ የሚባለው ፡ ተነሥቶ ፡ ቅዳሜ ፡ እገጥማችኋለሁ ፡ ያልኸውን ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አንተ ፡ እንደምትሞት ፡ ሺሆቻችን ፡ አረጋግጠውልናል» ፡ ብለህ ፡ ለጌታህ ፡ እንድትነግረው ፡ አለው ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ይማም ፡ እህመድ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ለመላክተኛው ፡ ነገረው ፡ ‹እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ አለበት ፡ ድረስ ፡ እንደምናባርረው ፡ ለጌታህ ፡ ንገረው› ወደአገራችሁ ፡ ተመለሱ ፡ ያለውንም ፡ አንስማማበትም ፡ ጦርነቱንም ፡ ለማድረግ ፡ ፈቃዳችንና ፡ ፍላጎታችን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚዋጋን ፡ ሰው አላገኘንም ። እስከ ፡ አሁንም ፡ የያዝነውን ፡ አገር ፡ በመልቀቅ ፡ ፈንታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነቢዩ ፡ (መሐመድ) ፡ መሬት ፡ ለኔ ፡ ተጠቀለለች ፡ ምሥራቅና ፡ ምዕራብንም ፡ አየሁ ፤ ወገኔ ፡ ዓይኔ ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡ ይገዛል ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ እንደተሰጠን ፡ ሀበሻን ፡ በሙሉ ፡ እንገዛለን »

መላክተኛው ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ቃል ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ከይማም ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ መልክቱን ፡ ለወሰን ፡ ሰገድ ፡ ነገረው ። እርሱም ፡ ፍርሃት ፡ ስላደረበት ፡ «መዠመሪያ ፡ የላኩብህ ፡ መልእክት ፡ ንጉሡንና ፡ ሹማምንቱን ፡ ፈርቼ ፤ ነው · · · · መንከሳትም ፡ በእጅህ ፡ እንደምወድቅ ፡ ነግረውኛልና ፡ ይኸ ፡ ነገር ፡ ተፈጽሞ ፡ በእጅህ ፡ ብወድቅ ፡ እንድትራራልኝ» የሚል ፡ የቃል ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ላከ ። መላክተኛውም ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፡ ስቆ ፡ ይሁን ፡ በእጃችን ፡ ቢወድቅ ፡ እንራራለታለን ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የበራራህ ፡ እስላሞች ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጥተው ፡ ለሕይወታችን ፡ ፈርተናልና ፡ የሚጠብቀን ፡ ሰው ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ አመለከቱት ፤ እርሱም ፡ አብሳማ ፡ ኑር ፡ የሚባለውን ፡ ሰጣቸውና ፡ እርሱን ፡ ይዘው ፡ ወደአገራቸው ሄዱ ፡ . . . በዚሁ ፡ ሰሞን ፡ የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ከከሐዲው ፡ ከአውራይ ፡ አትማን ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የእስላሞችን ፡ ሁኔታ ፡ ለመሰለል ፡ ሰዎች ፡ ወደበራራህ፡ ላከ ፤ እነሱም ፡ መጥተው ፡ ባገሩ ፡ አራት ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦርና ፡ አለቃቸው ፡ አብሳማኑር ፡ ብቻ ፡ መኖራቸውን ፡ ሰሙ ፡ . . . . . . ወደዚያው ፡ ሄደው ፡ ገጣሟቸው ፤ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ እንደተዋጉ ፡ አብሳማኑር ፡ አሸንፎ ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ ተሸንፎ ፡ ሸሸ ፡ . . . . ግማሾቹም ፡ ተማረኩ ። የተማረኩትንም ፡ ክርስቲያኖች ፡ አብሳማ ፡ ኑር ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ወስዶ ፡ አቀረባቸውና ፡ ተገደሉ ። የወሰን ፡ ሰገድ፡ መላክተኛም ፡ ይኸንኑ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።

የረማዳን ፡ ፳፫ኛው ፡ ቀን ፡ ፱፻፴፯ ፡ ዓመት ፡ (ሂጂራ) ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ከሕመሙ ፡ ድኖ ፡ ተነሣ ፤ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ አገር ፡ ለመንገዝ ፡ ቆረጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሹማምንቱ ፡ «እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ተጓዝን ፤ አሁን ፡

ግን ፡ ዳሞት ፡ የሚባለው ፡ አገር ፡ ሩቅ ፡ ነው ። ከመካከላችንም ፡ መንገዱን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፡ መንገድ ፡ መሪም ፡ አናገኝ ፡ የወረባም ፡ አገር ፡ እንደዚሁ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ከረሱት ፡ በቀር ፡ አገሩ ፡ ጠጠርና ፡ ማጥ ፡ (ጭቃ) ፡ ነው ፡ ፈረሶችና ፡ በቅሎቻችን ፡ ከመውደቅ ፡ በቀር ፡ ሊጓዙበት ፡ አይችሉም» ፡ ብለው ፡ አመለከቱት ። ይማም ፡ ግን ፡ «አገራችሁ ፡ ለመመለስ ፡ ፈልጋችሁ ፡ ይኸን ፡ ያመጣችሁትን ፡ ሰበብ ፡ ተውት አለና ፡ ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘውን ፡ ወደእስልምና ፡ የዞረውን ፡ አንድ ፡ ሰውዬ እፊቱ ፡ አስጠርቶ ፡ አስመጣና ፡ ስለመንገዱ ፡ ጠየቀው ። እርሱም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል መለሰ ፡ «የሀበሻን ፡ አገር ፡ መንገድ ፡ በሙሉ ፡ አውቃለሁ ፡ የወረባንም ፡ የዳሞትንም ፡ የጎጃምንም ፡ እስከ ፡ አክሱም ፡ ድረስ ፡ ወደፈቀዳችሁበት ፡ ሥፍራ ፡ ልመራችሁ ፡ እችላለሁ» ፡ ይማም ፡ ሰውዬውን ፡ የክብር ፡ ልብስ ፡ ሸለመው ። ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ጉዞው ፡ ተገሠገረና ፡ ወደወረባ ፡ አገር ፡ በተለይ ፡ ወደዞረሬ ፡ ከተማ ፡ (፩) ደረሱ ። በዚች ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ከግብጽ ፡ ከሶርያ ፡ የሚመላለሱ ፡ የክርስቲያኖች ነጋዴዎች ፡ ይገኙበታል ፡ ከሀበሾቹም ፡ ውስጥ ፡ በአየሯ ፡ መልካምነት ፡ የተነሣ ፡ ይሰበሰቡባታል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወሰን ፡ ሰገድና ፡ የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ባንድነት ፡ ነበሩና ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ለንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ አለው ፡ «አሁን ፡ እስላሞቹ ፡ ያሉት ፡ በኋላችን ፡ ነው ሁላችንም ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ የሄድን ፡ እንደሆነ ፡ አገሩ ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ ተከታትለው ሊያስቸግሩን ፡ ይችላሉ ። ስለዚህ ፡ እርስዎ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ይሂዱ ፡ እኔ ፡ ግን በእስላሞቹ ፡ ኋላ ፡ አድርጌ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እጓዛለሁ ። ይኸንንም ፡ ሲያውቁ ፡ ተመልሰው ፡ ወደአገራቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ እስከ ፡ ደዋሮ ፡ ድረስ ፡ ከአስጓዝኋቸው ፡ በኋላ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ተበታትነው ፡ ወደ ፡ የክፍለ ፡ አገራቸው ፡ መግባታቸው ፡ አይቀርምና እኔም ፡ ተመልሼ ፡ ወደርስዎ ፡ እመጣለሁ» ፡ ንጉሡም ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ምክር ሰማና ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ሄደ ፡ ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ወደደዋሮ ፡ አቅጣጫ ፡ አመራና ፡ ዋጅ እሚባል ፡ አገር ፡ ደረሰና ፡ እስላሞቹ ፡ ከሚገኙበት ፡ በኋላ ፡ ከኤልማያ ፡ ላይ ፡ ሠፈረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የይማም ፡ ሰላዮች ፡ መጡና ፡ ይኸንኑ ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ብልሃትና ፡ ተንኮል ፡ ገለጡለት ። . . . .

ስለዚህ ፡ ይማም ፡ «እንግዲያው ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ንጉሥ ፡ እስከሚሄድበት ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ዳሞት ፡ ድረስ ፡ እንከታተለው ፡ ይኸን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጌታውን ፡ ለመርዳት ፡ መመለሱ ፡ አይቀርም ። ወይም ፡ አሁን ፡ ያለበትን ፡ ሥፍራ ፡ ይዞ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ይጠብቃል ፡ ወዳገራችን ፡ (ወደሐረርጌ) ፡ ለመሄድ ፡ ከቻለ ፡ ይሂድ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ አለበት ፡ ድረስ ፡ እያበረርን ፡ እንውጋ» ፡ ብሎ ፡ ለእስላሞቹ ፡ ተናገረ ፡ ወደፊትም ፡ ጉዞው ፡ ተገሠገረና ፡ ኡይዝ ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ፡ በዚያችም ፡ ከተማ ፡ ከአበሻ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ትልቅ ፡ ገበያ ፡ አለ ፡ በዚችም ፡ ገበያ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚገበያየው ፡ በወርቅ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደቆብ ፡ (ቆቦ? ) ፡ ከቆብ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ምስር ፡ ምሽግ ፡ በነሱ ፡ ቋንቋ ፡

(፩) አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተወለዱበት ዞረሬ ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ ይሆንን ?

ጠባብ ፡ በር) ፡ ደረሱ ። ምስር ፡ ምሽግ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ «ይቺን ፡ በር ድንጋዩን ሰባብራችሁ ፡ ዛፉን ፡ ቆራርጣችሁ ፡ ሰፊ፡ መንገድ ፡ አውጡላትና ፡ እለፉ» ብሎ ፡ አዘዘ ። እነሱም ፡ እንደትእዛዙ ፡ ፈጽመው ፡ አለፉና ፡ ሌሊቱን ፡ ወደ ፡ ሱቅ ወይዘሮ ፡ ደረሱ ።

የሀበሻ ፡ ንጉሥ ፡ እስላሞቹ ፡ ዳሞት ፡ ግዛት ፡ መግባታቸውን ፡ ሲሰማ ፡ ወደ አንዲት ፡ ተራራ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ። ወደዚች ፡ ተራራ ፡ የሚያስወጣው ፡ መን ገድ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ስለነበረ ፡ ማንም ፡ ሊደርስበት ፡ አይችልም ፡ ነበር ። የዚ ችም ፡ መንገድ ፡ ዋናው ፡ በር ፡ ስሙ ፡ ጀራጂ ፡ (ጎራጊ)፡ ይባላል ። ስለዚህ ፡ ንጉሡ የራሱን ፡ ጦር ፡ አሰልፎ ፡ ዝሆን ፡ ዱር ፡ በሚባለው ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ጐን፡ ተቀመጠና ፡ ዋናውን ፡ በር ፡ እንዲጠብቅ ፡ የፊጠጋሩን ፡ ገዥ ፡ አውራይ ፡ አትማ ንን ፡ አዘዘው ።

እስላሞቹም ፡ ከሱቅ ፡ ወይዘሮ ፡ ተንሥተው ፡ ወደ፡ ጀራጂ ፡ ጊርጌ ፡ ሰፈሩና ፡ ከክ ርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ይሰላለሉ ፡ ገመር ። ክርስቲያኖቹ ፡ በላይ ፡ በኩል ፡ መሥፈራቸውን ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ምክር ፡ ያዙ ። አዶሊና ፡ ባለው ፡ አብድ ፡ ከጓደኞቻ ቸው ፡ ጋር ፡ «ከፊታችን ፡ በሩ፡ ተይዞብናል ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መሄጃ ፡ መን ገድ ፡ የለም ፡ እዚሁ ፡ ሌሊቱን ፡ እናሳልፍና ፡ በመድፍ ፡ እየተኰስን ፡ መትተን ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ ውጊያውን ፡ እንዠምር» ፡ አሉ ። ኤሚር ፡ ዘሀርቡይ ፡ መሐመድና ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፤ ገራድ ፡ አህሙሹ ፡ ግን ፡ «እዚህ ፡ ሌሊቱን ፡ ያደርን ፡ እንደ ሆነ ፡ ከኋላችን ፡ መጥቶ ፡ የምስር ፡ ምሽግን ፡ በር ፡ ይይዝብናል ፡ ይኸም ፡ ሲሆን ወደ ፡ ተራራ ፡ መውጣትም ፡ ወይም ፡ መመለስ ፡ ሳንችል ፡ በሁለት ፡ ተራራ ፡ መካ ከል ፡ እንቀራለን ።

ስለዚህ ፡ ድሉን ፡ እግዚአብሔር ፡ አይነሣንምና ፡ ውጊያውን ፡ አሁኑኑ ፡ እንዠምር» ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ይማም ፡ አህመድም ፡ «አሁን ፡ መልካም ፡ ምክር አመጣችሁ» ፡ ብሎ ፡ ጦሩን ፡ ለውጊያ ፡ አሰለፈና ፡ አውራይ ፡ አቶማን ፡ ወደሚ ጠብቀው ፡ በር ፡ ተጠጋ ። ከዚያ ፡ በበሩ ፡ በኩል ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ እንዲጠባበቅ ፡ ቢዚር ፡ አዶሌን ፡ ተወና ፡ ይማም ፡ የራሱን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቅሆንዱር ፡ (ዝሆን ዱር) ሄደ ። ንጉሡ ፡ በዚህ ፡ በጠባብና ፡ ማንም ፡ በማያውቀው ፡ መንገድ ፡ እስ ላሞቹ ፡ ይመጣሉ ፡ ብሎ ፡ በፍጹም ፡ አልጠረጠርም ፡ ነበር ፤ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ወደ ዝሆን ፡ ዱር ፡ ማንም ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ፡ እያለ ፡ አረጋግጦለት ፡ ነበር ።

ይማም ፡ ከነሰዉ ፡ ወደ ፡ ዝሆን ፡ ዱር ፡ ሲደርስ ፡ በዛፍና ፡ በእሾህ ፡ የተዘጋ ፪ ፡ በር ፡ አገኘ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሻምሱ ፡ ለሚያዛቸው ፡ ለእግረኛ ፡ ወታደሮች ፡ «ጋሻችሁን ፡ እሾሁ ፡ ላይ ፡ እያስቀመጣችሁ ፡ እርሱን ፡ እየረገጣችሁ ፡ ግቡ» ፡ ብሎ ፡ አዘዘና ፡ እርሱ ፡ እንዳለው ፡ ጋሻቸውን ፡ እየረገጡ ፡ አልፈው ፡ ሊተነፍሱ ወደቻሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ገብተው ፡ አጥሩን ፡ አነሡና ፡ ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ አብሮ ፡ ገባ ንጉሡም ፡ እስላሞቹ ፡ ሳይቀድሟችሁ ፡ ሂዱና ፡ በሩን ፡ ያዙ ፡ ብሎ ፡ ለትግሬ ፡

ጦር ፡ አገዘ ፡ ነበርና ፡ ቢመጡ ፡ እስላሞቹ ፡ ቀድመው ፡ ይዘውት ፡ ደረሱ ። ቢሆንም ፡ እዚያው ፡ አጠገብ ፡ አጠባብ ፡ ሥፍራ ፡ እንዳሉ ፡ እስላሞቹ ፡ አዩዋቸውና ፡ ሼክ ፡ ሚካኤል ። ሱማሌው ፡ ማታን ፤ ሲዲ ፡ ሞሐመድ ፤ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ አውራይ ፡ አቡን ፤ ኤሚር ፡ አቡበከር ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ አሌ ፤ ከባር ፡ ሞሐመድ ፡ ሌሎችም ፡ በድምሩ ፡ አርባ ፡ የሚሆኑ ፡ ፈረሰኞች ፡ በፊታቸው ፡ ያላቸውን ፡ ቲንሽ ሸለቆ ፡ አልፈው ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ኃይለኛውን ፡ ውጊያ ፡ ዠመሩ ። ተክሉ ፡ የሚባለው ፡ የሦራዊቱ ፡ ሹም ፡ ገሥግሦ ፡ መጣና ፡ ሼክ ፡ ሚካኤልን ፡ በጦሩ ፡ ቢመታው ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ አጥንቱን ፡ ሰብሮ ፡ እግሩን ፡ ቀዶት ፡ ወጣና ፡ ይታይ ዠመር ፡ ቁስለኛውም ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡ . . . . ፤ አባቱ ፡ ሮቤል ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ጦርነት ፡ የሞተው ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ (ዓምዱ) ፡ እንደዚሁ አቡበከር ፡ ቀጢንን ፡ ገጥሞ ፡ በጦር ፡ ሲደባደቡ ፡ ዓምዱ ፡ በጦሩ ፡ አቡበከር የተቀመጠበትን ፡ የፈረሱን ፡ አንገት ፡ ቢወጋው ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ በንድ ፡ ወገን ፡ ብቅ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ላይ ፡ ጦሩን ፡ ነቅሎ ፡ የአቡበከርን ፡ ቀኝ ፡ ቅልጥም ፡ መታው አቡበከር ፡ ቀጢንም ፡ በጦሩ ፡ ዓምዱን ፡ ልቡን ፡ ቢለው ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ በጀርባው ፡ ታየና ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ቢሆንም ፡ የጦሩ ፡ ብትር ፡ ቢያመውም ከአቡበከር ፡ ጋር ፡ ተጨባብጠው ፡ ሲደባደቡ ፡ የዓምዱ ፡ ዘመድ ፡ ረዳውና ፡ አቡበከርን ፡ ዠርባውን ፡ ሲመታ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ ደግሞ ፡ ክርስቲያኑን ፡ (ረዳቱን) ፡ መታና ፡ ከፈረሱ ፡ ጥሎ ፡ ገደለው ። ዓምዱም ፡ አቡበከር ፡ በመታው ፡ በትር ፡ ሞተ ፡ . . . . . ፡ ጓደኞቻቸው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲሞቱ ፡ የቀሩት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሽሽት ፡ ዠመሩ ። እስላሞቹም ፡ እየተከታተሉ ፡ ገደሏቸው ። ሼክ ፡ ሚካኤልን ፡ የገደለውን ፡ ተክላይን ፡ የሦራዊቱን ፡ ሹም ፡ አውራይ ፡ አቡን ፡ ማረከው ፡ የሾጃራሁን ፡ ሹም ፡ የገራድ ፡ ሲዲቅ ፡ ጋሻ ፡ ዠግሬ ፡ ማረከው ። ከእስላሞቹ ፡ አንድ ብቻ ፡ ሲሞት ፡ የትግሬ ፡ ሹማምንት ፡ ስምንት ፡ ሞቱ ። ፳ ፡ ፈረሶችም ፡ ተማረኩ ዋናው ፡ አዝማች ፡ ዮናኤል ፡ የተረፈውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ወደንጉሡ ፡ ሄዶ ፡ እስላሞቹ ፡ በሩን ፡ አልፈው ፡ ያደረጉትን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ። በሰማ ፡ ጊዜ ፡ «ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ የሮቤል ፡ ልጅ ፡ ሞተ ? » ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። ምክንያቱም ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ያባቱን ፡ የሮቤልን ፡ ማዕርግና ፡ ደረጃ ፡ ይዞ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ዠግና ፡ ተዋጊነቱም ፡ በክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነበርና ፡ ነው ። አባቱ ፡ ሮቤል ፡ እሬቱ ፡ የሚዋጋለት ፡ ፻፶ ፡ የሚሆኑ ፡ የኑብያ ፡ የፈረሰኛ ፡ ባሮች ፡ ነበሩት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ የዳሞትን ፡ ግዛት ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ዋጅ ፡ (ዋግ–ወግ) ፡ ሄደ ። አውራይ ፡ አትማንም ፡ የንጉሡን ፤ መሄድ ፡ ሲሰማ ፡ የጆራጂን ፡ በር ፡ መጠበቁን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሄደ ። እሱን ፡ ይጠባበቅ ፡ የነበረው ፡ ቢዚር ፡ አዶሌም ወደ ፡ ዝሆን ፡ ዱር ፡ ወጥቶ ፡ ከይማም ፡ ጋር ፡ ተገናኙና ፡ ባንድነት ፡ ሆነው ፡ ንጉሡን ፡ ይከታተሉ ፡ ዠመር ።

ይህ ፡ ጊዜ ፡ የሐጋይ ፡ ወራት ፡ ነው ። በዚህም ፡ ወራት ፡ ሀበሾች ፡ አራት ፡ ወር ፡ በቤታቸው ፡ መቀመጥ ፡ ልማድ ፡ ነበራቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ብር ድና ፡ ዝናም ፡ በበረከተበት ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ንጉሡን ፡ ሲያባርሩ ፡ የዝናቡ ፡ ብዛት ፡ መሬቱን ፡ ሁሉ ፡ ጭቃ ፡ አደረገው ። ስለዚህ እስላሞቹና ፡ መድፍ ፡ የተ ሸከሙት ፡ ግመሎች ፡ በጣም ፡ ደከሙ ። መድፎቹንም ፡ መጣል ፡ አስፈለገ ። እስላሞቹ ፡ ፯ ፡ ነበራቸው ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ የማረኩት ፡ አምር ፡ ነበርና ፡ ከድካም የተነሣ ፡ ፲፯ቱን ፡ መድፍና ፡ የተማረከውን ፡ ድንኳን ፡ ሁሉ ፡ ከድካ ምና ፡ ከችግር ፡ ከመንገዱም ፡ መጥፎነት ፡ የተነሣ ፡ ተጣለ ። ከዚያ ፡ እስላሞቹ ፡ ንጉሡን ፡ እያባረሩ ፡ ኡኢሁ–ያህር ፡ እምትባል ፡ ከተማ ፡ አደረሱት ። ክርስቲያ ኖቹ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የዝናምና ፡ የብርድ ፡ ብዛት ፡ ከመካከላ ቸው ፡ ፫፻ ፡ ሰው ፡ ገደለ ።

ክርስቲያኖቹ ፡ በብርድ መሞታቸውን ፡ ሲሰማ ፡ ይማም ፡ ወደዚች ፡ አገር ፡ መሄዱን ፡ አቆመ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ሳያድር ፡ ወደፊት ፡ ገሥ ግሦ ፡ ወደ ፡ ገበርጌ ፡ ምድር ፡ ደረሰ ። ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ዋጅ ፡ (ዋግ ፡) ነበረና ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ገበርጌ ፡ መጥቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ተገናኘ ። ንጉሡም ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነትና ፡ መሸነፍ ፡ አጫወተው ፡ ወሰን ፡ ሰገድም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ የጦር ፡ ሹማምንቱን ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ወቀሰ ።

«እንዴት ፡ ብታደርጉ ፡ ይህ ፡ ደረሰ ፡ በውነት ፡ ሰንፋችኋል ። የዳሞት ፡ ግዛት ፡ ተራራ ፡ የሞላበት ፡ መንገዱ ፡ ጠባብ ፡ ሳለ ፡ በሩን ፡ ይዛችሁ ፡ በመከላከል ፡ ፈንታ ፡ እስላሞቹ ፡ እያባረሯችሁ ፡ አገሩን ትታችሁ ፡ ሸሻችሁ ፤ ሞትን ፡ ትፈራላ ችሁን ? ፡ አባቶቻችሁ ፡ አያቶቻችሁ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ከመሞት ፡ በቀር ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ውርደት ፡ (ሃፍረት ፡) ደርሶባቸው ፡ አያውቅም ። አሁን ፡ እናንተ ፡ ደግ ፡ መስሎ ፡ የታያችሁን ፡ አድርጉ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቴ ፡ ተዋግቼ ፡ እሞታለሁ» ። ይኸን ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ‹አንተ ፡ ከሞትህ ፡ ሃይማኖታችንም ፡ መሞቱ ፡ ነውና ፡ ሞትን ፡ አያድርስብህ ፡ አንተም ፡ መሪያችን ፡ ነህና ፡ እሞታለሁ ፡ አትበል» ። ሲሉ ፡ መለሱለት ።

«እስላሞቹን ፡ ወዴት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ተዋችኋቸው» ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ «አገሩን ፡ እማናውቀው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የተውናቸው ፡ እነሱም ፡ ከኋላችን ፡ ይከተሉን ፡ ነበር» ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት ። «የዋጅ ፡ ገዥ ፡ እስላም ፡ ዳሃር ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለው» ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። ይኸም ፡ እስላም ፡ ዳሃር ፡ የወናግ ፡ ሰገድን ፡ እኅት ፡ ያዔ ፡ እስክንድርን ፡ ልጅ ፡ ያገባ ፡ ነው ። እርሱም ፡ አወሰን ፡ ሰገድ ፡ ፊት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ «ይኸው ፡ አሁን ፡ ንጉሡ ፡ ያሉት ፡ በግዛትህ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ባገርህ ፡ ያለውን ፡ ጠባብና ፡ እንደ ፡ ምሽግ ፡ የሆነውን ፡ ሥፍራ ፡ እንድን ሠፍርበት ፡ ንጉሡ ፡ የሚያልፉበትን ፡ አመልክተን ። እስላሞቹም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እኔና ፡ አንተ ፡ እንወጋቸዋለን» ፡ አለው ። እስላም ፡ ዳህርም ፡ ‹መልካም ፡

(፩) የላስታው ፡ አይመስልም ።

ነው ፡ አሁን ፡ ያላችሁበት ፡ ሥፍራ ፡ ገበርጌ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ወደ ፡ ዊዝ ፡ ገበያ ፡ ውረዱና ፡ በዚያ ፡ ሥፈሩ ፡ እስላሞቹ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ መጥቼ ፡ ማንም ፡ ወደ ፡ ማይደርስበት ፡ ሥፍራ ፡ መርቼ ፡ እወስዳችኋለሁ» ፡ አላቸውና ፡ በዚሁ ፡ ተስማሙና ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ አመለከተበት ፡ ገበያ ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ።

በበኩላቸው ፡ እስላሞቹ ፡ እብርዱ ፡ አገር ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ አድረው ፡ ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ገበርጌና ፡ ዋጅ ፡ አጠገብ ፡ ወደሚገኘው ፡ ወረብ ፡ ወደሚባለው ፡ አገር ፡ ገቡ . . . . ከዚያም ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ለአብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ ፪፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሰጥቶ ፡ «ወደ ፡ ገበርጌ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ አገር ፡ ሂድና ፡ ወሬ ፡ ሰብስብና ፡ ይዘህ ፡ ና» ፡ ብሎ ፡ ላከው ። እርሱም ፡ ወደ ፡ ገበርጌ ፡ ሄዶ ፡ ሳለ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ሰላዮች ፡ ጋር ፡ በሩቅ ፡ ተያየ ። እነርሱም ፡ እርሱን ፡ ሲያዩ ፡ በቅሏቸውን ፡ ትተው ፡ በሩጫ ፡ ወደ ፡ ሠፈራቸው ፡ ተመልሰው ፡ እስላሞቹ ፡ እኋላችን ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሩት ። አብድ ፡ ኢን ፡ ናስርም ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ መስኋቸው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ «ዮኸው ፡ እስላሞቹ ፡ ደርሰዋልና ፡ እንግዴህ ፡ እመራችኋለሁ ፡ ወደ ፡ አልኸው ፡ ሥፍራ ፡ ውሰደን» ፡ ብሎ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ እስላም ፡ ደሀርን ፡ ጠየቀው ። እስላም ፡ ደሀርም ፡ ዋጅ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ ወደማይደርስበት ፡ ጠባብ ፡ ሥፍራ ፡ እየመራ ፡ ወሰደው ።

አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ በበኩሉ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ተመልሶ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ገለጸለት ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እስላሞቹ ፡ ወረብ ፡ ውስጥ ፡ ወደሚገኘው ፡ ወደ ፡ ቃራሩቃት ፡ ሄደው ፡ ይማከሩ ፡ ጀመር ። አንድ ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ የዞረ ፡ ሃይቢ ፡ (የጋቱር ፡ ሹም ፡) የሚባል ፡ ‹ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዋጅ ፡ ከገባ ፡ መውጫ ፡ የለውምና ፡ ለኛ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ሆነልን ። ከዋጅ ፡ ወደ ፡ ጉራጌ ፡ አገር ፡ ለመሸሽ ፡ ቢፈልግም ፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ጠላቱ ፡ ነውና ፡ አይቀበለውም ፡ ወደደዋሮ ፡ ቢሄድም ፡ እንከታተለዋለን ፡ ከዚህ ፡ ብንነሣ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እንደርስበታለን» ፡ ብሎ ፡ ምክር ፡ አቀረበ ። እስላሞቹ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ እርሱን ፡ መከታተል ፡ ይቅርብን» ፡ ሲሉ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ «ወደደዋሮ ፡ ቢሄድም ፡ ልንከታተለው ፡ ችግር ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ወደዚያ ፡ የሄድን ፡ እንደሆነ ፡ ወታደራችን ፡ ሁሉ ፡ ተበታትኖ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይገባል ። ስለዚህ ፡ ሁሉንም ፡ ትተን ፡ የንጉሡ ፡ ሀብትና ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ወደሚገኝበት ፡ ወደሸዋ ፡ እንሂድ» ፡ ስላሉ ፡ ይማም ፡ የብዙዎቹ ፡ አሳብ ፡ ወደዚሁ ፡ ማዘንበሉን ፡ ተመለከተና ፡ ሃይቢን ፡ ‹አንተ ፡ ዝም ፡ በል ፡ የነዚህ ፡ ምክር ፡ ነው ፡ የሚሻለው› ፡ ብሎ ፡ ጉዞው ፡ ተጀመረና ፡ በዊዝ ፡ (ኡኢዝ ፡) መንገድ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ይማም ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ሰጥቶ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስርን ፡ እንደ ፡ ገብጣን ፡ (ሸዋ ፡) ወደሚባል ፡ አገር ፡ ላከው ። ይኸም ፡ እንደ ፡ ገብጣን ፡ የአዋሽ ፡ ወንዝ ፡ የሚመነጭበት ፡ ሥፍራ ፡ ነው ። በዚያም ፡ ብዙ ፡ ሀብትና ፡ ገንዘብ ፡ ያለባት ፡ የጥንት ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩዋት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረች ። ስለዚህ ፡ ይማም ፡ ወደዚያ ፡ ሄዳችሁ ፡ ሀብቱን ፡ ዝረፉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ አቃጥሉ ፡ ሰዎቹንም ፡ ፍጁ ፡ ብሎ ፡

አዘዘና ፡ ላከቻው ። እንደዚሁ ፡ በኤሚር ፡ ሁሴን ፡ የሚታዘዝ ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ደራድባኒ ፡ ላከ ። በዚያም ፡ አንዲት ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ አሠርቶ ፡ ለልጁ ፡ ለፊቅ ጦር ፡ የሰጠው ፡ ትልቅ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚሁ ፡ በፊቅጦር ፡ ስም ፡ የም ትጠራ ፡ ነበረች ። በውስጧም ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ጥዋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የግምጃ ፡ ልብስ ፡ ነበረባት ።

አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ ወደ ፡ ተላከበት ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኒቱን ፡ ብቻ ፡ ከማቃጠል ፡ በቀር ፡ ወርቅና ፡ ሀብት ፡ አላገኘባትም ። ከርሱ ፡ መድረስ ፡ በፊት ፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝቦች ፡ ሀብቷን ፡ በሙሉ ፡ ይዘው ፡ ሸሽተው ፡ ነበር ። በበኩሉ ፡ ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ሲጓዝ ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ ከኋላ ፡ ነበር ፡ ከናስር ፡ ጋር ፡ ፩መሪ ፡ ሰው ፡ ነበር ። እርሱም ፡ «ከኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ቀድመን ፡ የምንሄድበትን ፡ መንገድ ፡ አውቃለሁ» ፡ ብሎ ፡ ለአብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ ነገረው ። እርሱም ፡ «ደግ ፡ ነው ፡ ምራን» ፡ አለው ። ከዚያ ፡ ተመራር ተው ፡ በሌላ ፡ አቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ከኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ቀድመው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንዋ ፡ ደርሰው ፡ በውስጧ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ወስደው ፡ አቃጠሏት ።

ቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ በምትቃጠልበት ፡ ጊዜ ፡ ኤሚር ፡ ሁሴን ፡ ደረሰና ፡ በር ሱና ፡ በአብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ መከከል ፡ ትልቅ ፡ ጠብ ፡ ተፈጠረ ፤ ሁሴን ፡ «ይማም ፡ እንድመጣ ፡ ወደ ፡ አዘዘኝ ፡ ቦታ ፡ አንተን ፡ ምን ፡ አመጣህ» ፡ ቢለው ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስር ፡ "ይህ ፡ ቡብዙ ፡ አማልክት ፡ የሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ (ክርስቲያን) ፡ አገር ፡ ነው ፡ ከእኛ ፡ እያንዳንዳችን ፡ የተመቸውን ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል„ ፡ ብሎ ፡ መለሰለትና ፡ ወዲያው ፡ ከምርከው ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ሰጠውና ፡ ከቁጣው ፡ አበረደው ፡ ከዚያ ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ተመለሱ ፤ ግማሹን ፡ አብድ ፡ ኢን ፡ ናስርና ፡ ጓደኞቹ ፡ ተከፋፍለው ፡ የቀረውን ፡ ለይማም ፡ ሰጡት ። ከዕቃው ፡ ውስጥ ፡ የብር ፡ ሳህን ፡ የእንስሳ ፡ የአእዋፍ ፡ ስእል ፡ ያለበት ፡ የብር ፡ ሥራ ፤ በውስጡ ፡ ሁለት ፡ መጋረጃና ፡ ብዙ ፡ ልብስ ፡ ነበር ። የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ ዐረቦችም ፡ ፋርሶችም አያውቁም ። በዋጋ ፡ ቤት ፡ ፫ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ያወጣል ። ይማም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ ከአዋሽ ፡ ምንጭ ፡ በላይ ፡ አባራት ፡ እሚባል ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ በዚ ያም ፡ ሳለ ፡ የወረብ ፡ የሸዋ ፡ ሕዝብ ፡ እየመጣ ፡ እየገበረለት ፡ ሁሉም ፡ በየአገሩ ፡ ተመልሶ ፡ በሰላም ፡ ተቀመጠ ።

እስላሞቹ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ በየመንገዳቸው ፡ ልብስ ፤ ብር ፤ ወርቅ ፡ እየ ዘረፉ ፡ ወደ ፡ በራራህ ፡ (በረሬ ?) ፡ ለመድረስ ፡ ዓሥር ፡ ቀን ፡ ተጓዙ ። በዚችም ፡ ከተማ ፡ የንጉሡ ፤ የከርቻ ፡ ግላስ ፡ ሰፈሮች ፡ ነበሩ ። እነሱም ፡ ንጉሡ ፡ በሔደበት ፡ አብረው ፡ ይሔዱ ፡ ነበሩ ። አሁን ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዋጅ ፡ የሔደ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ በራ ራህ ፡ ተመልሰው ፡ እስላሞቹን ፡ አስተናግደው ፡ አክብረው ፡ ተቀበሉ ። በዚች ፡ ከተማ ፡ እስላሞቹ ፡ ሠፍረው ፡ ሳሉ ፡ ታላቅ ፡ የሚያስፈራ ፡ ዝናምና ፡ ታላቅ ፡ ነፋስ ፡ መጣ ፡ ሰማዩ ፡ በጨለማ ፡ ተዘጋ ፤ አንዲት ፡ ኮከብ ፡ እንኳ ፡ አትታይም ፡ ነበር ። ነፋሱና ፡ ዝናሙ ፡ በላያቸው ፡ (በላያችን ፡ የጸሐፊው ፡ ቃል) ፡ ላይ ፡ ሲወርድ ፡ ከስ

ልቻ ፡ አፍ ፡ እንደሚወርድ ፡ ይመስላል ። (፩) ነፋሱ ፡ አንዱ ፡ ድንኳን ፡ ከተተከለበት ፡ ተነቅሎ ፡ በሌሎቹ ፡ ድንኳኖች ፡ ዓየር ፡ ላይ ፡ ሲያንገዋብብ ፡ ቃየ ። የቀረው ፡ ሁሉ ፡ ድንኳን ፡ ምንቅርቅሩ ፡ ወጣ ። ይማምና ፡ ሚስቱ ፡ ሐጂራህ ፡ ከሁለቱ ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ በዚች ፡ ሥፍራ ፡ ለማለቅ ፡ ቀናቸው ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አምነው ፡ ድንኳናቸውን ፡ አንቀው ፡ ይዘው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታላቅነትና ፡ አንድነት ፡ እያነሡ ፡ ጮሁ ። እግዚአብሔርም ፡ ነፋሱንና ፡ ዝናሙን ፡ ከላያቸው ፡ ገፈፈላቸው ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ እይማም ፡ ዘንድ ፡ ተሰብስበው ፡ የዚህን ፡ ሌሊት ፡ ነገር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲወያዩ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ይኸስ ፡ የኖኅ ፡ የጥፋት ፡ ውኃ ፡ (ማየ ፡ አይኅ) ፡ ነው ፡ አሉ" ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የምንመለከተው ፡ ግራኝ ፡ ንጉሡን ፡ እግር ፡ በግር ፡ እየተከታተለ ፡ ንጉሡን ፡ ለመማረክ ፡ ወይም ፡ ለመግደል ፡ ያለውን ፡ ጽኑ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። በንጉሡና ፡ በሠራዊታቸው ፡ ዘንድ ፡ የተገመተው ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ስንሔድ ፡ የዳሞት ፡ አገር ፡ ተራራማ ፡ መንገዱ ፡ ጠባብ ፡ በመሆኑ ፡ እኛን ፡ ለመከላከል ፡ ሲመቸን ፡ ለእንግዳ ፡ ጠላት ፡ ግን ፡ አይመችም ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ በግልጽ ፡ ይታያል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግራኝና ፡ ጦሩ ፡ ለዳሞትም ፡ ለቀረውም ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ እንግዳ ፡ አልሆነም ፡ ከሽምብራ ፡ ኰሬና ፡ ከአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ከልብ ፡ ክርስቲያን ፡ የነበረው ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ሲገባ ፡ ክርስቲያንነታቸው ፡ ወይም ፡ እስላምነታቸው ፡ ያልለየላቸው ፡ የደዋሮ ፡ የባሌ ፡ የጋቱር ፡ ባላባቶች ፡ በእስላሞች ፡ መነሣትና ፡ ማየል ፡ ደስታ ፡ እየተሰማቸው ፡ በግራኝና ፡ በሹማምንቱ ፡ ዙሪያ ፡ ሆነው ፡ በእሽናፌው ፡ ፊት ፡ ሞገስና ፡ ሹመት ፡ ለማግኘት ፡ በንጉሡና ፡ በክርስቲያናዊው ፡ ሠራዊታቸው ፡ ላይ ፡ ወሬ ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ መሩ ፡ ናቸው ። መጽሐፉ ፡ የአዝማች ፡ ሃይቤን ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ቢጠቅስም ፡ እንደርሱ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ለግራኝና ፡ ለሹማምንቱ ፡ ደኅና ፡ ደኅና ፡ ምክር ፡ ለመንገር ፡ አቋራጭ ፡ መንገድ ፡ ለመምራት ፡ የሚሿሙት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ከነርሱም ፡ ጋር ፡ ከሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ከአይፈርስ ፡ ከዛሬ ፡ ጦርነት ፡ የተማረኩት ፡ የክርስቲያን ፡ ሹማምንቶች ፡ እንደ ፡ ቃሠሩ ፡ በዘቡኛ ፡ እየተጠበቁ ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ የሚያውቁትን ፡ ነጋሪ ፡ ናቸውና ፡ ግራኝ ፡ ንጉሡ ፡ እደረሱበት ፡ ለመድረስ ፡ በፍጹም ፡ የሚያስቸግረው ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ማንም ፡ ሊደርስበት ፡ አይችልም ፡ የተባለውን ፡ የዝሆን ፡ ዱርን ፡ ጦርነት ፡ የሾሁን ፡ አጥር ፡ ጋሻ ፡ እያስነጠፈ ፡ ጦሩን ፡ አሳልፎ ፡ ገብቶ ፡ ለማሸነፍ ፡ የቻለው ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ባላጋራነት ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ከአዳልና ፡ ከሱማሌ ፡ ባላባቶች ፡ ባላጋራነት ፡ የተለየ ፡ ነው ። እነዚያ ፡ አንድ ፡ አውራጃ ፡ ዘርፈው ፡ ሰዉን ፡ ከነከብቱ ፡ ማርከው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ መመለስን ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሙሉ ፡ ድል ፡ አድርገን ፡ ለዘለቄታ ፡ መኖር ፡ ምኞት ፡ አልነበራቸውም ። ሰብረዲንና ፡

(፩) ፡ ጸሐፊው ፡ ታላቅ ፡ ነፋስ ፡ አየሁ ፡ ዝናም ፡ ወረደብን ፡ የሚለውን ፡ እኔ ፡ ለጽሑፍ ፡ እንዲመችል ፡ በሁሉም ፡ እስላሞች ፡ ስም ፡ እርሱ ፡ እንደሚተርከው ፡ አድርጌዋለሁ ።

ሐቅ ፡ ዲን ፡ ቢነሡም ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በብርታቱ ፡ መለሳቸው ። ግራኝ ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገኙትን ፡ የክርስቲያን ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንት ፡ ከንጉሡ ፡ ፊጅቶ ፡ ገዳማቱንና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱን ፡ አቃጥሎ ፡ እርሱ ፡ የንጉሡን ፡ ሥፍራ ፡ ሹማምንቱ ፡ የሹማምንቶቹን ፡ ሥፍራ ፡ ወስደው ፡ ኢትዮጵያን ፡ የእስላም ፡ አገር ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ጥገኛ ፡ ወይም ፡ ተከታይ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ምኞቱ ፡ ንጉሡን ፡ እንደምንም ፡ ብዬ ፡ ከገደልሁ ፡ ወይም ፡ ከማረክሁ ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ ይገዛልኛል ፡ ብሎ ፡ ጧትና ፡ ማታ ፡ ንጉሡ ፡ ያሉበትን ፡ የደረሱበትን ፡ እግር ፡ በእግር ፡ እየተከታተለ ፡ እመዋጋት ፡ ላይ ፡ ነው ።

ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ግራኝ ፡ ያለ ፡ አስጨናቂና ፡ ከባድ ፡ ባላጋራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አልተነሣም ። ድል ፡ ለማግኘት ፡ ግዛቱን ፡ ለማቃናት ፡ ሲል ፡ ለማንም ፡ ሕይወት ፡ አይሳሳም ፤ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ተከታትሎ ፡ ቢገጥመው ፡ የማይጠግብ ፤ በምርኮ ፡ የተገኘ ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ሀብት ፡ ለግሉ ፡ የማያጓጓው ፡ ስለሆነ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ድል ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ሌላውን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚገጥመውን ፡ ከማጥበቅና ፡ ወደዚያው ፡ ከመቀጠል ፡ በቀር ፡ ልመለስ ፡ የማለት ፡ አሳብ ፡ በአእምሮው ፡ አይጸነስም ። በርሱ ፡ ፊት ፤ እንመለስ ፡ ይብቃን ፡ የሚል ፡ ጠላቱ ፡ ነበር ። በወርቁና ፡ በብሩ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ተገዝቶበት ፡ ጦር ፡ ተደራጅቶበት ፡ የተረፈውን ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ እናባርር ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ይኽን ፡ የተገኘውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይዤ ፡ አገሬ ፡ ተመልሼ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ልኑር ፡ የሚል ፡ ስሜት አይመጣበትም ፤ እንደማናቸውም ፡ ጦርነት ፡ ወዳድ ፡ ወጣት ፡ ደግሞ ፡ በእልህና ፡ በንዴት ፡ እጦርነት ፡ መከከል ፡ አይገባም ፡ በዙሪያው ፡ ሰውነቱን ፡ የሚጠብቁ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ የተዋጊ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሮች ፡ ስላሉት ፡ እነሱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ አይለዩም ። የሚዋጋውም ፡ የሚያዋጋውም ፡ አስቀድሞ ፡ የጠላቱን ፡ መጠንና ፡ አቅም ፡ ገምቶ ፡ ምቹውን ፡ ሥፍራ ፡ አስመርምሮ ፡ ነው ። ባስፈለገበት ፡ ቦታ ፡ ደግሞ ፡ ድፍረቱና ፡ ጭከኔው ፡ የዚያን ፡ ያህል ነው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ የተሰለፈበትን ፡ ቦታ ፡ እየተወ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ምርጥ ፡ ተዋጊ ፡ ይዞ ፡ እየመራ ፡ ድንገት ፡ በጠላቶቹ ፡ ሠፈር ፡ አደጋ ፡ እየጣለ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ መፍጀቱን ፡ የአይፈርስና ፡ ያሁኑ ፡ የዝሆን ፡ ዱር ፡ ጦርነት ፡ ይገልጻል ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ እንለፍና ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፡ የመጨረሻ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ትምክህት ፡ የሆነው ፡ ትልቁ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ተዋግቶ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ በሚቀጥሉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንመልከት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

## የታላቁ ፡ ገዳም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መቃጠልና ፡ የመነኰሳቱ ፡ አሟሟት ።

ከራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦርነት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቃጠሎ ፡ ይቀድማል። ታሪከ ፡ ነገሥታችን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ ሳይጨምር ፡ ጉዳዩን ፡ ብቻ፡ አንሥቶ ፡ ሲያልፍ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ «. . . . ወአመ ፡ ፳ወ፬ ፡ ለሐምሌ ፡ (ግራኝ) ፡ አውዓያ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወአመ ፡ ፰ ፡ ለነሐሴ ፡ ሞተ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ . . . . » በዓራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ቃጠሎ ፡ ፫ ፡ ወይም ፡ ፰ ፡ ድዙል ፡ ሂጂጃህ ፡ (ወደ ፡ ፲ ፡ ነሐሴ) ፡ ላይ ፡ ያደርገዋል ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ከራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦርነትና ፡ ሞት ፡ በፊት፡ የስመ ፡ ጥሩውን ፡ ገዳም ፡ የቃጠሎ ፡ አኳኋን ፡ እንመለከታለን ።

የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ታሪኩን ፡ ቢቀር ፡ ስመ ፡ ጥሩነቱን ፡ የማያውቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አይገኝም ። ትክሉ ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጨረሻ ፡ ወይም፡ በ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተነሡ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አባቶች ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ዓጽም ፡ ከአሳረፉበት ፡ ወዲህ ፡ ገዳሙ ፡ ይበልጥ ፡ እየገነነ ፡ ሄደ ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባዔ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክና ፡ ባዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ የቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ደብረ ፡ አስቦ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዘመናቸው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የሚል ፡ አዲስ ፡ ሥያሜ ፡ አወጡለት። ይህም ፡ ገዳም ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዓጽም ፡ ካረፈበት ፡ ወዲህ ፡ በነገሥታቱም ፡ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ እየከበረ ፡ ሄደ ። በገዳሙ ፡ አጠገብ ፡ ድውይ፡ ይፈውሳል ፡ የሚባለውን ፡ ጠበል ፡ ለመነከር ፡ ገዳሙን ፡ ለመሳለም ፡ ከየአውራጃው፡ የሚሰበሰበው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ ነው ። ሕዝቡና ፡ መኳንንቱም ፡ በዚህ ፡ ገዳም ፡ ለበዓል ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰበሰቡበት ፡ ባመት ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፩ኛው ፡ ታህሣሥ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተወለዱበት ፡
፪ኛው ፡ ግንቦት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ዓጽማቸው ፡ የፈለሰበት ፡
፫ኛው ፡ ነሐሴ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ያረፉበት ፡ ነው ።

እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ እንደሚደረገው ፡ በነዚህ ፡ ቀኖች ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ የሚደረገው ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ ታላቅ ፡ ነው ። ጠበሉን ፡ የሚጠመቀው ፡ ስለት ፡ የሚያገባው ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ገዳም፡ የመንግሥቱ ፡ መደብ ሸዋ ፡ በነበረበት ፡ ወደ ፡ ጐንደርም ፡ በዞረበት ፡ ጊዜ ፡ ከደብረ ፡ ዳሞና ፡ ከደብረ ፡ ቢዘን ፡ ይበልጥ ፡ በሸዋ ፡ የተከበረ ፡ ገዳም ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ ግራኝ ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ አሸንፎ ፡ ደዋሮን ፡ ባሌን ፡ ይልቁንም ፡ ሸዋን ፡ ከወረረ ፡ በየአውራጃው ፡ የሚገኙትን ፡ ገዳማትና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ከአቃጠለ፡ ወዲህ ፡ ይኸንንም ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ገዳም ፡ አቡበከር ፡ ቀጢን ፡ የሚባለውን ፡ የጦር ፡ አለቃውን ፡ ልኮ ፡ ሲያቃጥል ፡ እንመለከታለን ። ኤሚር ፡ አቡበከር ፡ ሀብቱን ፡ በሙሉ ፡

ወስዶ ፡ ከመንኰሳቱና ፡ ከዙሪያው ፡ ሕዝብ ፡ ግብር ፡ ተቀብሎ ፡ በመንኰሳቱ ፡ ልመና ፡ ገዳሙን ፡ ከቃጠሎ ፡ ለማዳን ፡ ከጅሎ ፡ ነበር ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከበጅያ ፡ (በለው) ፡ ወደ ፡ ሱማሌ ፡ አገር ፡ ከወረደ ፡ በለው ፡ ኡብደላ ፡ ከሚባለው ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ከአለቃው ፡ ተደብቆ ፡ ገዳሙን ፡ እሳት ፡ ለኰሶ ፡ አቃጠለው ። ገዳማቸውን ፡ አጥብቀው ፡ የሚያፈቅሩ ፡ መነኰሳት ፡ በፈቃዳቸው ፡ እሳቱ ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ አብረው ፡ ተቃጥለው ፡ በሰማዕትነት ፡ አረፉ ። ዝርዝር ፡ የታሪኩን ፡ ትርጕም ፡ ከዓረብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እነሆ ፡ እንመልከት ። «እስላሞቹ ፡ በበራራህ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ በሰነበቱበት ጊዜ ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ አጠገብህ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (ገዳም) ፡ አለች ፡ ብለው ፡ ለይማም ፡ ነገሩት ፡ እርሱም ፡ «ወዴት ፡ አገር» ፡ ቢል ፡ ግራርያ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ አውርማህ ፡ በሚባል ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ነው ። ስሙም ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ይባላል ። ክርስቲያኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ወደዚያ ፡ እየሄዱ ፡ ተሰብስበው ፡ ያከብሩታል ፡ በያይነቱ ፡ ልብስ ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ጥዋ ፡ እንደዛፍ ፡ ግንድ ፡ የወፈረ ፡ ጧፍ ፡ ይሰጡታል ። በአበሻ ፡ አገር ፡ ከተሠሩት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እርሱ ፡ አንደኛ ፡ ነው ። ከአክሱምና ፡ ከላሊበላው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቀር ፡ የሚተካከለው ፡ የለም» ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡ ከዚህ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ ያስኼዳል„ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ያስኼዳል ፡ አሉት ።....

ስለዚህ ፡ ኤሚር ፡ አቡበክር ፡ ቀጢንን ፡ አስጠርቶ ፡ እነኤሚር ፡ ሞጋሂድ፤ እነአብሳማ ፡ ኑር ፤ እንድል ፡ ሰገድ ፡ ያሉበትን ፡ ፫፻ ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ሰጥቶ ፡ እንዲዘምት ፡ ላከው ። እርሱም ፡ ከነጦሩ ፡ ወደዚያው ፡ (ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡) ኼዶ ፡ በአቅራቢያው ፡ ሠፈረ ። ይኸን ፡ ሲሰሙ ፡ መነኰሳቱ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ማይደርስበት ፡ ተራራ ፡ ሸሽተው ፡ ኼዱ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ግማሾቹ ፡ «ገዳማችን ፡ ሲቃጠል ፡ ከመሸሽ ፡ አብረን ፡ ብንቃጠል ፡ ይሻላል„ ፡ ብለው ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ገዳማቸው ፡ መጡና ፡ እሳቱ ፡ እስኪለኰስ ፡ ድረስ ፡ እገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። የቀሩት ፡ መነኰሳት ፡ ደግሞ„ ፡ ይኸን ፡ ገዳም ፡ በማቃጠል ፡ የምትጠቀሙበት ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ይልቅስ ፡ እኛም ፡ እንደምትፈልጉት ፡ ያህል ፡ ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ልብሱን ፡ እናስረክብ በገዳሙ ፡ ዙሪያ ፡ የሚገኘውም ፡ ሕዝብ ፡ ግብር ፡ ያግባልህና ፡ ገዳሙን ፡ ከቃጠሎ ፡ አድንልን ፡ „ብለው ፡ ወደ ፡ ኤሚር ፡ አቡበክር ፡ ቀጢን ፡ (ቀጭኑ ፡ አቡበክር) ፡ ላኩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቡበክር ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ምክር ፡ ያዘ ። ግማሹ ፡ "ሐብቱን ፡ ወስደን ፡ ገዳሙን ፡ እንተወው„ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ገዳም ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የከበረ ፡ ስለሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ ይቅርብን„ ፡ አሉ ። አቡበክር ፡ ግን ፡ ሀብቱን ፡ ወስደን ፡ ገዳሙን ፡ እናቃጥል ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች አሳብ ፡ ደግፎ ፡ መላክተኛውን ፡ ጠራና„ ፡ መልክም ፡ ነው ፡ ሐብቱን ፡ ካስረከባችሁ ፡ ገዳሙን ፡ ትተናል ፡ ስለዚህ ፡ ጓደኞችህ ፡ ይምጡና ፡ የምንፈልገውን ፡ ሀብት ፡ እናስታውቃቸዋለን ፡ ከሰጡንም ፡ በኋላ ፡ ገዳሙን ፡ ከማቃጠል ፡ እንተዋለን ፡ „ብሎ ፡ ነገረው ፡ መልክተኛውም ፡ ተመልሶ ፡ ኼዶ ፡

ለጓደኞቹ ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ወደ ፡ አቡበክርም ፡ መጥቶ፡ ተገናኙና ፡ ይኸን ፡ የደስታ ፡ ወሬ ፡ ስለአሰማቸው ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ የ፱ ፡ ወቂት ፡ ወርቅ ፡ ክብ ጌጥ ፡ (ፕላክ) ፡ ያለበት ፡ ሁለት ፡ ልብስ ፡ እንደዚሁ ፡ የ፬ ፡ ወቂት ፡ ንጹሕ ፡ ወርቅና ፡ ብርም ፡ አቀረቡለትና„ ፡ ይህ ፡ ያሁን ፡ ስጦታችን አላቃጥልም ፡ ብለህ ፡ ለነገርኸን ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ የሚሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ በሰላም ፡ ወርቅም ፡ ብርም ፡ ሊገብርህ ፡ የሚገባውን ፡ ቁረጥና ፡ ንገረን„ ፡ ብለውት ፡ የዚህኑ ፡ ጉዳይ ፡ ከአቡበክር ፡ ጋር ፡ ሲነጋገሩ ፡ አንድ ፡ አውራይ ፡ አቡበክር ፡ የሚባል ፡ ነገዱ ፡ በለው ፡ (ማሐዌራህ ?) ፡ የሆነ ፡ ከአገሩ ፡ ከትግሬ ፡ ወደ ፡ ሰአድ ፡ ዲን ፡ አገር ፡ (አዳል ፡) ወርዶ ፡ ልጁን ፡ ያገባው ፡ የበለው ፡ አብደላ ፡ ዘር ፡ ነው ። ከርሷ ፡ (ከሰአድ፡ ዲን ፡ ልጅ ፡) ና ፡ ከርሱ ፡ (ከበለው) ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ ወንዶቹ ፡ አውራይ ፡ (አውራ ?) ፡ ሴቶቹ ፡ ባቲያ ፡ (ባቲ) ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ከነርሱ ፡ ዘር ፡ የመጣው ፡ ይህ ፡ እስላም ፡ (አውራይ ፡ አቡበክር) ፡ በድብቅ ፡ የችቦ ፡ እሳት ፡ ይዞ ፡ ሄዶ ፡ ገዳሙን ፡ ለኩሶ ፡ አቃጠለው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መነኰሳቱ ፡ ከአቡበክር ፡ ቀጢን ፡ ጋር ፡ ሲነጋገሩ ፡ ዘወር ፡ ቢሉ ፡ ቃጠሎውን ፡ አዩ ። ነበልባሉም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ፤ መነኰሳቱ ፡ ይኸን ፡ ሲያዩ ፡ የሰላም ፡ ድርድራቸውን ፡ አቋርጠው ፡ እሳቱ ፡ ላይ ፡ ለመውደቅ ፡ አምርቸው ፡ እየሮጡ ፡ ሄደው ፡ ጥቂቶቹ ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡ የቀሩት ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እራት ፡ እነበልባሉ ፡ ውስጥ ፡ ተወረወሩ ።

ኤሚር ፡ አቡበክር ፡ ቀጢን ፡ አውራይ ፡ አቡበክርን ፡ አስጠርቶ ፡ አስመጣውና ፡ «እኔ ፡ የሰላም ፡ ነገር ፡ ስደራደር ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ አቃጠልህ » ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ እርሱም «እኔ ፡ ነኝ ፡ ያቃጠልሁት ፡ የፈቀድኸውን ፡ አድርገኝ ፡ ይማም ፡ የላከን ፡ እንድናቃጥል ፡ እንጂ ፡ በገንዘብ ፡ የሰላም ፡ ውለታ ፡ እንድናደርግ ፡ አላከንም » ብሎ ፡ መለሰለት ። ኤሚር ፡ አቡበክርም ፡ እርሱንና ፡ የተገኘውን ፡ ምርኮ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ዘንድ ፡ መልስ ፡ ሆነ ። ፲፪ ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ እንደተጓዙ ፡ እይማም ፡ ዘንድ ፡ ደረሱና ፡ ኤሚር ፡ አቡበክር ፡ አውራይ ፡ ገዳሙን ፡ ማቃጠሉን ፡ ነገረው ። እርሱም ፡ "ደግ ፡ አደረገ ፡ እኔም ፡ የላክኋዋችሁ ፤ እንድታቃጥሉ ፡ ነው ፡ ለእናንተም ፡ ከዚህ ፡ (ከማቃጠል) ፡ የሚበልጥ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ የለም ። አሁንም ፡ ሂድና ፡ እሠፈርህ ፡ አደርና ፡ የምነግርህ ፡ ጉዳይ ፡ አለኝና ፡ ነገ ፡ ተመለስ ፡ አለው » ሲል ፡ አረብ ፡ ፋቂህ ፡ ይተርካል ።

ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ሊዘምት ፡ የመጣው ፡ ይህ ፡ አቡበክር ፡ ቀጢን ፡ በግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ራሱ አዝማች ፡ እየሆነ ፡ ለብቻው ብዙም ጊዜ ፡ በግራኝ ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ በብዙ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ተዋግቷል ። ባዬ ፡ ሱስንዮስ ዘመን ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ እንደሚተርክልን ፡ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በ፲፰፻፺፱ ዓ፡ም ፡ ደጋልሃን ፡ አዳልን ፡ ወርር ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ የማረከ ፡ ጊዜ ፡ የአቡበክር ፡ ቀጢን እናት ፡ ፋጥ ፡ የምትባለው ፡ ተማርካ ፡ ሳለ ፡ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ በድንገት ፡ መጥተው ፡ በራስ ፡ ደጋልሃን ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ አሸንፈው ፡ አቡበክር ፡ እናቱን ፡ አስመ

አደጋ ፡ ጥለው ፡ አሸንፈው ፡ አቡበከር ፡ እናቱን ፡ አስመለሰ ። ግዕዝኛው ፡ ታሪክ ስሙን ፡ ቀጭን ፡ አቦከር ፡ ይለዋል ። ዐረብኛውና ፡ ግዕዙ ፡ አማርኛውም ፡ ተስ ማምተው ፡ ቀጭኑ የሚሉት ፡ ሰውነቱ ፡ ረዥም ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፡ ከንጉሡ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ተዋግቷል ። በባደቂ ፡ ከአሮን ፡ ጋር ፡ በቃግማ ፤ ከተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በአይፈርስ ፡ ጦርነት ፡ ከነራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ አሸንፏል ። ዘምቢል ፡ የተባለውን ፡ የክርስቲያን ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የገደለው ፡ እርሱ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በዝሆን፡ ዱር ፡ ዝግናውን ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ አዝማች ፡ ዓምደ ፡ ሚከኤልን ፡ እንደገደለ ፡ ተመልክተናል ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ለዘመተው ፡ ጦር ፡ የበላይ ፡ አለቃ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ መነከሳቱ ፡ የገዳሙን ፡ ሀብት ፡ ከስረከቡን ፡ በዙሪያው ፡ ያለው፡ ሕዝብ ፡ የጠየቀነውን ፡ የሚገብር ፡ ከሆነ ፡ ገዳሙን ፡ ከማቃጠል ፡ መተው ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ ከመነከሳቱ ፡ ጋር ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ መደራደሩ ፡ ያስተዋይነት ፡ ሥራ ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አውራይ ፡ ተደብቆ ፡ ስለአቃጠለው ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አል ቻለም ። ሊቀጣውም ፡ ፈልጎ ፡ ግራኝን ፡ በመፍራት ፡ የተወው ፡ ይመስላል ። በግራኝ ፡ መንፈስ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የማቃጠል ፡ የመደምሰስ ፡ የማጥፋት ፡ መንፈስ ፡ ከዚያኛው ፡ ይበልጥ ፡ እርሱ ፡ ያውቃል ። ያኛውም ፡ አለቃው ፡ ለእርቅ ፡ በሚደራደርበት ፡ ጊዜ ፡ ደፍሮ ፡ ማቃጠሉ ፡ በዋናው ፡ ጠቅላይ ፡ መሪ ፡ በግራኝ ፡ ፈቃድና ፡ መንፈስ ፡ በመተማመን ፡ ነው ።

አቡበከር ፡ ገዳሙን ፡ ለመተው ፡ ሲፈልግ ፡ ያኛው ፡ ለማቃጠል ፡ የቸከ ለበትን ፡ ምክንያት ፡ ስንፈልግ ፡ እርሱ ፡ ሳይሆን ፡ ከትግሬ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ተዛውሮ ፡ የባላባቱን ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ የተቀመጠው ፡ የበለው ፡ ዘር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቂምና ፡ ጥላቻ ፡ ከትግሬና ፡ ካማራ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ጋር ፡ ስለነበረውና፡ የቂሙ ሐረግ ፡ እስከዚህ ፡ እስከ ፡ አውራይ ፡ አቡበከር ፡ ደርሶ ፡ ያንኑ ፡ ቂም ፡ ለመወጣት ፡ ያደረገው ፡ ይመስላል ። የቦጎስ ፡ የቢለን ፡ የአገው ፡ (የበጆያ) ፡ ዘር ፡ ከሴማዊው ፡ ዘር ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከወረደው ፡ ከአማራና ፡ ይልቁንም ፡ ከትግሬ ፡ ዘር ፡ ከቀድሞ ፡ ከአኵስም ፡ መንግሥት ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በቋንቋ ፡ በልማድ ፡ በሃይማኖትና ፡ በዘር ፡ የተለያዩ ፡ ስለሆነ ፡ የዘወትር ፡ ግጭታ ቸውና ፡ ጦርነታቸው ፡ የበረታ ፡ ነው ። በዛጕዬ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍት ፡ ያገኙ ፡ ቢመስልም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ መጠቃታቸው ፡ የቀረ ፡ አይመስልም ። በለው ፡ አብድ ፡ አላ ፡ የዚህ ፡ ያቃጣዩ ፡ ዘር ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ከነ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ዘሮ ፡ መቀመጡ ፡ ጥቃትና ፡ ጠብ ፡ ሰልችቶት ፡ ይሆናል ። አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ አልፈን ፡ ከገዳሙ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ ተቃጠሉት ፡ መነከሳት ፡ ጉዳይ ፡ እንተላለፍ ።

የአራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ባለፈው ፡ እንዳነበብነው ፡ ከዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ የመነከሳቱን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መሞት ፡ ሲነግረን ፡ የራሳችን ታሪክ ፡ ነገሥት ፡

ወአመ ፡ ፳ ፡ ወ፬ ፡ ለሐምሌ (ግራኝ)፡ አውዓያ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ብሎ ፡ ከማ ለፍ ፡ በቀር ፡ የመነኮሳቱን አስደናቂ ፡ ሰማዕትነት ፡ አያነሣውም ። ባ፪ ፡ ሥርዐ ፤ ድንግል ፡ ወይም ፡ ባ፪ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ የተጻፈ ፡ የሚመስል ፡ አጭር ፡ ያ፪ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ታሪክ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ወደ ፡ ኢጣልያን ፡ ተርጕሞ ፡ ያሳተመውም፡ „ወእምቅድመ ፡ ኅልፈተ ፡ ይእቲ ፡ ዓመት ፡ (፲፭፻፳፫ ፡ ዓ. ም.) አውዓያ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መቃብረ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አሐቲ ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ አመ ፡ እሥራ ፡ ወረቡዑ ፡ ለሐምሌ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ይሄዳል ። ስለዚህ ፡ ለሃይ ማኖታቸውና ፡ ለገዳማቸው ፡ ጥብቅ ፡ ፍቅርና ፡ ቅናት ፡ ያላቸው ፡ መነኮሳት ፡ የዚ ህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ንቀው ፡ ማንም ፡ ሳያስገድዳቸው ፡ በፈቃዳቸው ፡ እሚቃጠ ለው ፡ ነበልባል ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ሲሞቱ ፡ ስማቸውን ፡ ከነዝናቸው ፡ በዚህ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ላይ ፡ ለመዘርዘር ፡ ባለመቻሌ ፡ አዝናለሁ ። እንዲያውም ፡ ይኸን ፡ የመሰለ፡ ተጋድሎ ፡ የፈጸሙ ፡ መነኮሳት ፡ አሁን ፡ በሚገኘው ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም፡ እዋናው ፡ መግቢያ ፡ በሩፍ ፡ ላይ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ እንኳ ፡ በይቻል ፡ በሁ ሉም ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ነዋሪ ፡ ሐውልት ፡ ሊሠራላቸው ፡ ይገባል ። ስማቸው ፡ በገዳሙ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ምናልባት ፡ ቢገኝ ፡ ሊዘረዘር ፡ ቢጠፋ ፡ በጭሩ፡ «ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የወረረ ፡ ጊዜ ፡ በ፩ሺ፭፻፳፫ ፡ ዓ ም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ሲቃጠል ፡ በፈቃዳቸው ፡ አብረው ፡ የተቃጠሉ ፡ መነኮሳት ፡ መታሰቢያ» ፡ ተብሎ ፡ ሊቀረጽላቸው ፡ ይገባል ።

## ም ዕ ራ ፍ ፲፯ ።

## የራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦርነትና አማሟት ፡ – የግራኝ ፡ በግዛት ፡ መመሥረት ።

የግራኝ ፡ አሳብ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ከነቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ መነኮሳቱን፡ ከነገዳማቸው ፡ ለማጥፋት ፡ ታጥቆ ፡ የተነሣበት ፡ ስለሆነ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ መቃጠል ፡ ያሳዝናል ፡ እንጂ ፡ አያስደንቅም ። ወደፊትም ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በወሎ ፡ በአማራ ፡ ሳይንት ፡ በጐጃም ፡ በትግሬ ፡ የሚገኙት ፡ የመካነ ፡ ሥላሴ ፤ የደብረ ፡ ነጐድጓድ ፤ የቤተ ፡ ሰማያት ፤ የአትሮንስ ፡ ማር ያም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሲቃጠሉ ፤ ሐይቅ የቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ገዳም፡ ሲበረበር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንመለከታለን ። አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳት ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ እንመለስ ።

በትግሬ ፡ በጐጃም ፡ በበጌምድር ፡ ያሉ ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንት ፡ ገና ፡ አላለቁም ፡ ቢሆንም ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ የንጉሡም ፡ የመኳንንቱም ፡ የሕዝቡም፡ የወታደሩም ፡ ተስፋ ፡ ያደረው ፡ በራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ነው ። ራስ ፡ ወሰን፡ ሰገድ የገኘነት ፡ ስሙ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ጐጃም ፡ ነጋሽ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ዳሞት ፡ ነጋሽ ፡ ይለዋል ። ምናልባት ፡ ሁለቱን ፡ አገር ፡ ባንድነት ፡ ጠቅሎ ፡ ይሁን፡ ወይም ፡ በየተራ ፡ ይግዛ ፡ በትክክል ፡ አልታወቀም ። ነገር ፡ ግን በንጉሡ ፡

ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ በመኳንንት ፡ ዘንድ ፡ የተከበረ ፡ ታላቅ ፡ የጦር ፡ አለቃና፡ መኰንን ፡ ነው ። በፊተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ሹማምንቱን ፡ በዲ ስኩር ፡ መውቀሱ ፡ ሹማምንቱ ፡ እንግዲህ ፡ ከንተ ፡ ጋር ፡ እንሞታለን ፡ ሲሉ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ በስሙ ፡ የዛቻና ፡ የማስፈራሪያ ፡ ቃል ፡ ሲጽፍ ፡ በጠቀላላው፡ ከንጉሡ ፡ በታች ፡ ከነራስ ፡ ደጋልሃን ፡ የበለጠ ፡ ማዕርግና ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ይመስላል ። ግራኝ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አንዳንድ ፡ እልኸኞች ፡ ከመቃወምና ፡ ከመጋደል ፡ ባያርፉ ፡ ሸዋን ፡ ይፋትን ፡ ፈጠጋርን ፡ ደዋሮን ፡ ባሌን ፡ በሙሉ፡ አሳምኖ ፡ ንጉሡን ፡ እየተከታተለ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ መዝለቅ ፡ የቻለው ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ ከአሸነፈ ፡ ወዲህ ፡ ነው ። ወሰን፡ ሰገድ ፡ ሲሸነፍ ፡ ንጉሡና ፡ መኳንንቱ ፡ ሸዋ ፡ ላይ ፡ ለመከላከል ፡ በፍጹም፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ መሸሻቸውን ፡ እንመለከታለንና ፡ አሁን ፡ የጦርነቱን ፤ ሁኔታ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት ።

"አቡበከር ፡ ከመመለሱ ፡ በፊት ፡ የበራራህ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጡና ፡ ባደቂ ፡ ያለው ፡ የንጉሡ ፡ ዕቃ ፡ የሚገኝበትን ፡ ሥፍራ ፡ እናውቃለንና እናመልክትህ, ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ ስለዚህ ፡ ወዚር ፡ አዶሌን ፡ ከነጦሩ ፡ ወደ ፡ ባደቂ ፡ ልከት ፡ በፈጠጋር ፡ በማሲን ፡ (ባደቂ) ፡ የተገኘውን ፡ የንጉሡ፡ ሀብት ስምንት ፡ ቀን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ተመለሰና ፡ የሰበሰበውን ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ዕቃ ፡ (ፕላክ, ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ ያለውን ፡ የሐር ፡ ልብስ ፡ አስረከበው ። እርሱም ፡ እንደሌሎቹ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ዘረፋ ፡ ሳይሄድ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ አጠገብ ፡ ለማይለዩት ፡ ለማሀራህ ፡ (፩) ፡ ተዋጊዎች ፡ ሰጣቸው ፡ . . . . ቀጥሎም ፡ አዶሌ„ ፡ ንጉሡ ፡ በዋጅ ፡ ነው፡ ያለው ፡ በኛና ፡ በርሱ ፡ መካከል ፡ የሁለት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ አለ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የአዋሽ ፡ ወንዝ ፡ ሞልቷል ፡ ብሎ ፡ ስለንጉሡ ፡ ነገረው ።

ንጉሡ ፡ በበኩሉ ፤ ይማም ፡ በራራህ (በረህ ?) መኖሩን ፡ ሲሰማ ፡ እነዚህ ፡ እስ ላሞች ፡ በራራህ ገብተው ፡ አገሩን ፡ ዘርፈዋልና ፡ አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ አገራ ቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ስለዚህ ፡ አዋሽን ፡ ተሻግሬ ፡ አንድ ፡ ሥፍራ ፡ ይገፔ ፡ እወጋ ቸዋለሁና ፡ ባገራችሁ ፡ እንደምትሠሩት ፡ ያለ መሻገሪያ ሥሩልኝ ፡ ብሎ ፡ አጠ ገቡ ፡ ለሚገኙት ፡ አርባ ፡ ፈረንጆች ፡ ነገራቸው ፡ እነሱም ፡ ቲናንሽ ፡ ጀልባ ፡ ሠሩለት ። ያገሩንም ፡ ተወላጆች ፡ በክረምት ፡ ለመሻገሪያ ፡ መሥራት ፡ የለመዳ ችሁትን ፡ ሥሩ ፡ ብሎ ፡ አዝዞ ፡ በነርሱ ፡ ቋንቋ ፡ ለጋ ፡ የሚባለውን ፡ ፳፪ ፡ ሠሩለት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ወሰን ፡ ተነሣ ፡ መሬት ፡ ስሞ ፡ (እጅ ፡ ነሥቶ) ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ያዘዝኸውን ፡ ሁሉ ፡

(፩) ፡ ማህራን ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ የመጡት ፡ ምርጥ ፡ ወታደሮች ፡ የራሱ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬዎችና ፡ ራስ ፡ ጠባቂ ዎች ፡ መድፈኞችም ፡ ናቸው ።

ፈጽመናል ፤ እኔ ፡ አገልጋይህ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ሄጄ ፡ እዋጋለሁ ። የአማጺ ህንም ፡ በር ፡ ይገፍ ፡ ቢመጡ ፡ እዋጋለሁ ፤ የገደሉኝም ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ የምትፈቅደውን ፡ ታደርጋለህ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ አይሄድም ፤ የነገሥታቱም ፡ ደንብ ፡ አይፈቅድም ። ስለዚህ ፡ ስላንተ ፡ ሆኜ ፡ እዘምታለሁ ።

ይኸን ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ ንጉሡና ፡ በዚያ ፡ ያሉት ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ አመሠገኑት ። መኳንንቱም ፡ «አንተ ፡ አባታችን ፡ ነህ ፡ ጉዳያችንንም ፡ እያወቅህ ፡ በፍቅርና ፡ በብልሃት ፡ ታስተዳድረናለህ ፡» አሉት ። ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ የደዋሮን ፤ የጐጃምን ፡ የፈጠጋርን ፤ የይፋትንም ፡ ጦር ፡ ከአለቃቸው ፡ ከአውራይ ፡ አትማን ፡ ከከሐዲው ፡ ጋር ፡ እንዲያገዝ ፡ ለወሰን ሰገድ ፡ ሰጠውና ፡ ተሰናብቶ ፡ በዝልባው ፡ እየተማፈሩ ፡ አዋሽን ፡ ተሻግረው ፡ እፈጠጋር ፡ ግዛት ፡ ገብተው ፡ ቃርቃራህ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ሠፈሩ ።

ወዚር ፡ አዶሌ ፡ ከባደቄ ፡ ወደ ፡ በራራህ ፡ ሲመለስ ፡ ንጉሡና ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ያደረጉትን ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ አዋሽን ፡ ተሻግሮ ፡ ቃርቃራህ ፡ መስፈሩን ፡ ለይማም ፡ ነገረው ፡ ቀጥሎም ፡ «ልዋጋቸው ፡ አስቤ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያልፈቃድህ ፡ ስለሆነ ፡ ፈርቼ ፡ ተውሁ» ፡ ብሎ ፡ ጨምሮ ፡ ነገረው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ከጦር ፡ አለቆቹ ፡ ጋር ፡ ምክር ፡ ያዘ ። ሁሉም ፡ አሁን ፡ የዝናም ፡ ወራት ፡ (ክረምት) ፡ ነው ። አሁን ፡ ጉዞ ፡ የዠመርን ፡ እንደ ሆነ ፡ በከንቱ ፡ እንደክማለንና ፡ ክረምቱ ፡ ሲያልቅ ፡ እንዋጋለን ፡ › አሉትና ፡ በየሠፈራቸው ፡ ተለያዩ . . . . . . . ቀጥሎም ፡ ሐቀኛ ፡ ምክር ፡ የሚሰጠውን ፡ ገራድ ፡ አህሙሽን ፡ ለብቻው ፡ ጠራና ፡ . . . . ምን ፡ ይሻላል ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ እስላሞቹ ፡ ሁሉ ፡ የክረምቱን ፡ መውጣት ፡ ይጠብቃሉ ፡ ሲወጣ ፡ ና ፡ ሄደን ፡ እንዋጋ ፡ ይሉሃል ፤ ወደጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ጠላትን ፡ ያገኙ ፡ እንደሆነ ፡ ይዋጋሉ ፡ ያጡ ፡ እንደሆነ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ መሄድ ፡ ይፈልጋሉና ፡ ፍቀድልን ፡ ይሉሃል ፤ እሺ ፡ ብትል ፡ አገራቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ባትፈቅድም ፡ በፈቃዳቸው ፡ በየአገራቸው መግባታቸው ፡ አይቀርምና ፡ አንተ ፡ ብቻህን ፡ መቅረትህ ፡ ነው „አለው„ ታዲያስ ፡ ምን ፡ ይሻላል ፡ "ብሎ ፡ ቢጠይቀው «አቡበከር ፡ ቀጢን ፡ እስኪመለስ ፡ እዚሁ ፡ እንቆይ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ሠፈራችንን ፡ ይጠብቃል ፡ ከዚያ ፡ እኛ ፡ ሄደን ፡ እንዋጋና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ንጉሡን ፡ የገደልነው ፡ እንደሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ እስላም ፡ ይሆናል ። የአዋሽ ፡ ወንዝም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ይሞላልና ፡ እስላሞቹ ፡ አገራቸው ፡ ለመግባት ፡ አይችሉም ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ እዚሁ ፡ ቀርተው ፡ ስለዘረፉ ፡ ብቻ ፡ ያስባሉ ፡ ሳንዋጋ ፡ በመካከል ፡ በጋ ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ እስላሞቹን ፡ ማገድ ፡ በፍጹም ፡ አይቻልም ፡ ምክንያቱም ፡ ኤሚሮቹም ፡ ቲንሹም ፡ ትልቁም ፡ ወዳገሩ ፡ መመለስ ፡ ናፍቆታል» ፡ ብሎ ፡ ምክሩን ፡ ገለጸለት ። ይማምም ፡ አመሰገነውና ፡ እንግዴህ ፡ አቡበከር ፡ እስኪመጣ ፡ ይኸን ፡ ምሥጢራዊ ፡ ምክር ፡ ለማንም ፡ አታውጣ ፡ አለው . . . .

ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ኤሚር ፡ ሑሴንን ፡ ጠርቶ ፡ ከገራድ ፡ አህሙሹ ፡ የተነጋገረበትን ፡ ገለጸለት ' . . . ኤሚር ፡ ሑሴንም ፡ ጥሩ ፡ ምክር ፡ ነው ፡ ውለህ ፡ ሳታድር ፡ ነገውኑ ፡ ሒደህ ከወሰን ፡ ሰገድ ፡ የተዋጋህ ፡ እንደሆነ ፡ ትገድለዋለህ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ሀበሻን ፡ ትገዛለህ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ያደርህ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ገራድ ፡ አህሙሹ ፡ ያለው ፡ ይፈጸማል ። የሁሉም ፡ እስላም ፡ አሳብ ፡ ያዘነበለው ፡ ወደየአገሩ ፡ ለመመለስ ፡ ነው ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ሒዶ ፡ ለመውጋት ፡ ቆረጠ ። ኤሚሮቹንም ፡ ሁሉ ፡ ጠርቶ ፡ የሰማሁት ፡ ወሬ ፡ አለኝና ፡ ነገ ፡ የፈረሰኛ ፡ የእግረኛ ፡ ጦራችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይዛችሁ ፡ ወደኔ ፡ እንድትመጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። በማግስቱ ፡ መለከት ፡ እያስነፉ ፡ ነጋሪት ፡ እያስመቱ ፡ ሹማምንቱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ ለመውጋት ፡ አስቤአለሁና ፡ ምን ፡ ይመስላችኋል ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡ እነሱም ፡ የኛ ፡ አሳብ ፡ ክረምት ፡ ሲወጣ ፡ ለመውጋት ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ አዲስ ፡ የጦርነት ፡ አሳብ ፡ ምነው ፡ አመጣህብን ፡ "አሉት ፡ እርሱም ፡ ዝም ፡ በሉ ፡ እናንተ ፡ ምንም ፡ አታውቁም ፡ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ አውቃለሁ ፡ ጠላታችንን ፡ የምንወጋው ፡ በዚህ ፡ በክረምቱ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ሀብትና ፡ ጓዛችንንስ ፡ እንይዛለን ፡ ወይስ ፡ እንተዋለን" ፡ ቢሉት ፡ "ይኸ ፡ ጉዳያችን ፡ አይደለም ፡ "ብሎ ፡ መለሰና ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ አቡበከር ፡ ቀጢን ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ "ይህ ፡ ያመጣኸው ፡ ልብስና ፡ ዕቃ ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ በሰፈር ፡ ሆነህ ፡ ሴቶቻችንና ፡ ሀብታችንን ፡ ጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ፩፻፷ ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደር ፡ ሰጥቶ ፡ "ከዚህ ፡ አትሂድ ፡ ንጉሡ ፡ ቢመጣብህ ፡ ተዋጋው ፡ ታሸንፈውማለህ ፡ „ብሎ ፡ አስጠንቀቀውና ፡ ይማም ፡ የፋጢሃህን ፡ ድግምት ፡ እየደገመ ፡ ጉዞውን ፡ ጀመረ ። ኤሚሮቹም ፡ በየፈረሳቸው ፡ ወጥተው ፡ ተከተሉት ፡ መንገድ ፡ መሪው ፡ ከሁሉ ፡ ፊት ፡ ቀደመ ፡ ዝናም ፡ ይወርድ ፡ ነበር ፡ መንገዱም ፡ ሁሉ ፡ ጭቃ ፡ በመሆኑ ፡ ግማሹ ፡ ከፈረስ ፡ ግማሹ ፡ ከበቅሎው ፡ ይወድቅ ፡ ነበር ፡ ሹማምንቱም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከፈረስና ፡ ከበቅሎአቸው ፡ እየወረዱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየወጡ ፡ በፈረስና ፡ በበቅሎአቸው ፡ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ተጕዘው ፡ ሌሊቱን ፡ እክርስቲያኖቹ ፡ ሠፈር ፡ ተጠግተው ፡ አደሩ ።

የወሰን ፡ ሰገድም ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ይኸው ፡ ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ መጥቶ ፡ አጠገብህ ፡ ሰፍሯል ፡ "ብለው ፡ ነገሩት ፡ እርሱም ፡ አሰት ፡ ነው ። እስላሞች ፡ በዚህ ፡ በዝናምና ፡ በጭቃ ፡ በአረፋ ፡ በዓላቸው ፡ ጊዜ ፡ ጕዞ ፡ አይጓዙም ፡ ማለትን ፡ ሰምቻለሁ ፡ አለና ፡ "ወዲያው ፡ ባጠገቡ ፡ ያለውን ፡ ከሐዲ ፡ አውራይ ፡ አትማንን ፡ "እስላሞች ፡ በአረፋ ፡ በዓላቸው ፡ ጊዜ ፡ ይጓዛሉን ፡ በዚህ ፡ ከብት ፡ በሚያደክም ፡ በጭቃስ ፡ ይጓዛሉን ፡ "ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ "እኔ ፡ ቀድሞ ፡ በመካከላቸው ፡ ባገራቸው ፡ የነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ በክረምትና ፡ ይኸን ፡

በመሰለ ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ አይጓዙም ። አሁን ፡ ግን ፡ የሚያደርጉትን አላውቅም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሚካኤልና ፡ ሮቤል ፡ የሚባሉትን ፡ ሁለት ፡ የዳዋሮ ፡ አገር ፡ ፈረሰኞች ፡ አስጠራና ፡ «ያገሩ ፡ ሰው ፡ ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ መጥቶ ፡ እዚህ ፡ አጠገብ ፡ ሰፍሯል ፡ ብለው ፡ ነግረውኛልና ፡ እስኪ ፡ እናንተ ፡ ፈረሳችሁን ፡ ጭናችሁ ፡ ሂዱና ፡ እስላሞቹ ፡ ያሉበትን ፡ ሰልላችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ ላካቸው ። እነሱም ፡ ለመመርመር ፡ በሚጓዙበት ፡ ጊዜ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ወገን ፡ ደላን ፡ የሚባለው ፡ ከአራት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ እንጨት ፡ ፍለጋ ፡ ሲሄዱ ፡ ሚካኤልን ፡ አገኘውና ፡ "አንተ ፡ ሰው ፡ እስላሞችን ፡ አይተሃልን" ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ እርሱም ፡ የምን ፡ እስላሞች ፡ «ቢለው» ፡ የሚዋጉት ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሚካኤል ፡ ከላይ ፡ ሆኖ ፡ ወደታች ፡ ቢመለከት ፡ የእስላሞችን ፡ ሠፈር ፡ አየ ፡ ደላንንም ፡ እስላም ፡ መሆኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ ሊሸሽ ፡ ሲል ፡ ዳላን ፡ የበርኖሱን ፡ ጫፍ ፡ ይዞ ፡ ከፈረስ ፡ አውርዶት ፡ በሰይፍ ፡ መታና ፡ ማረከው ፡ ጓደኛው ፡ ግን ፡ ሸሽቶ ፡ ወደሠፈሩ ፡ ተመለሰ ። ዳላንም ፡ ምርኮኛውን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ወስዶ ፡ አቀረበውና ፡ አስገደለው ።

ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሸሽቶ ከመጣው ፡ ሰውዬ ፡ ላይ ፡ የእስላሞቹን ፡ በቅርብ ፡ መኖር ፡ ሲሰማ ፡ ጦሩን ፡ ሰብስቦ ፡ ይኸው ፡ እስላሞቹ ፡ በኛ ፡ ዙሪያ ፡ ነውና ፡ ያደሩት ፡ እንግዴህ ፡ ሊጐበኙዋችሁ ፡ መምጣታቸው ፡ ነውና ፡ ለውጊያ ፡ ተዘጋጁ" አላቸው ፡ እነሱም ፡ «በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ተዋጉ ፡ ብለህ ፡ አትዘዘን ፡ "ብለው ቢለምኑት ፡ «ታዲያስ ፡ ቃልተዋጋችሁ ፡ ምን ፡ ልታደርጉ ፡ ነው ፡ "አላቸው ፡ እነሱም" አንተ ፡ የሃይማኖት ፡ መሪያችን ፡ ነህ ፡ አንተ ፡ የሞትህ ፡ እንደሆነ ፡ ሃይማኖታችን ፡ ጠፋች ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ቦሰት ፡ ተራራ ፡ እንሂድና ፡ በዚያ ፡ አንተ ፡ እየመራኸን ፡ እኛም ፡ እየተከተልንህ ፡ እስከ ፡ መጨረሻችን ፡ ድረስ ፡ የተዋጋን ፡ እንደሆነ ፡ የሃይማኖታችን ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆናል ፡ አገራችንም ፡ ይበዘበዛል» ፤ እያሉ ፡ አጥብቀው ፡ ከፊቱ ፡ ቆመው ፡ ለመኑትና ፡ እሺ ፡ አሰኙት። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የጦሩን ፡ አጋማሽ ፡ ለአውራይ ፡ አትማን ፡ ከፍሎ ፡ ስጠና ፡ አንተ፡ ደጀን ፡ ሆነህ ፡ ጠብቅ ፡ ብሎት ፡ እርሱ ፡ የቀረውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ተራራው፡ ሲሄድ ፡ እስላሞቹ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሠፈር ፡ መጥተው ፡ ድንኳኑን ፡ ሲያስነቅል ፡ በአውራይ ፡ አትማን ፡ ደረሱበት ፡ እርሱም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ሳይዋጋ ፡ ድንኳኑንና ፡ ሠፈሩን ፡ ትቶ ፡ ሸሸ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ "ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሠፈሩን ፡ ከነሀብቱ ፡ ትቶ ፡ የሸሸው እኛ ሀብቱን ፡ ለመከፈል ፡ ስንዘነጋ ፡ ድንገት ፡ በተንኮል ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ሊዋጋን ፡ ነው ፡ አንዳንዶቹ ፡ የለም ፡ በርግጥ ፡ ሸሽቷል ፡ ሲባባሉ ፡ ገራድ ሻሙን ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እሠፈሩ ፡ ቢገኝ ፡ ግደሉኝ ፡ እርሱ ፡ በፍጹም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ አዋሽ ፡ ሄዷል ፡ ቢል ፡ ይማም ፡ የነዚያን ፡ ትቶ ፡ የርሱን ፡ አመነና ፡ ጦሩ ፡ ተከፋፍሎ ፡ አንደኛው ፡ የአውራይ ፡ አትማንን ፡ ሁለተኛው ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፍለጋ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሄዱ ። ፫ኛውን ፡ ጦር ፡ ይማም ፡ ይዞ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሄደ ።

ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እስላሞቹ ፡ እንደተጠጉት ፡ በወቀ ፤ ጊዜ ፡ የብረት ፡ አልጋዬን ፡ (ወምበር ?) ዘርጉልኝ ፡ ብሎ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠና ፡ ነጋሪት ፡ እያስመታ ፡ ወገኖቹን ፡ ለጦርነት ፡ ቀሰቀሳቸው ፡ የደረሱበት ፡ እስላሞቹ ፡ ብዙ ፡ አልነበሩም ፡ ቢሆንም ፡ ጦርነቱን ፡ ዠምረው ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ተዋጉ ። በዚህ ፡ ውጊያ ፡ ላይ ፡ ዋናው ፡ ዠግና ፡ የፈረሰኛ ፡ ተዋጊ ፡ ትግሬ ፡ አብደላ ፡ ሞተ ። ገዳዩም ፡ የጎጃም ፡ ነጋሽ ፡ ልጅ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ሲሆን ፡ እስላሞቹ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ ፡ እኋላ ፡ የነበሩት ፡ ፈረሰኞች ፡ ደረሱና ፡ «ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሸሹት ፡ ደርሰንላችኋልና ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ተመለሱ» ፡ አሏቸውና ፡ እንደገና ፡ ዠምረው ፡ እነዚህም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲገፉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲሸሹ ፡ በመካከል ፡ ቃላላቆቹ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የፈረሰኛ ፡ ጀግኖች ፡ እነ ፡ ገራድ ፡ ሻሙን ፤ አሊ ፡ ኡል ፡ ዋራዲ · · · ፤ አውራይ ፡ ኡመር ፡ ዲን ፤ ገራድ ፡ አቢድ ፡ ሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ ደረሱና ፡ የሚሸሹትን ፡ እስላሞች ፡ ‹ማነው ፡ እንደዚህ ፡ ያባረራችሁ› ፡ አሏቸው ፡ እነሱም ፡ “አለቃዬው ፡ (ወሰን ፡ ሰገድ) ፡ ጦሩን ፡ አሰልፎ ፡ ገጥሞን ፡ አሸነፈን ፡ ትግሬውን ፡ አብደላንም ፡ ገደሉብን ፡ እንደገና ፡ አራት ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ብንመለስም ፡ አልሆነልንም» ፡ ብለው ፡ መለሱ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ገራድ ፡ ሻሙንና ፡ አውራይ ፡ ኡመር ፡ ዲን» ፡ እንግዴህ ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ ደርሰንላችኋል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደደረሱላችሁ ፡ ዓይነት ፡ ያለን ፡ አይምሰላችሁ ፡ እንግዴህ ፡ እኛ ፡ ከፊት ፡ ሆነን ፡ እንዋጋለን ፡ እናንተ ፡ ከኋላችን ፡ ተከተሉን ፡ “ብለው ፡ በመዠመሪያ ፡ ገራድ ፡ ሻሙን ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ አቋርጦ ፡ ገባና ፡ ከአዝማቹ ፡ (ከወሰን ፡ ሰገድ) ፡ ወንድም ፡ ከገሪማ ፡ (ግርማ ፡ ግሩማ ?) ፡ ጋር ፡ ተጋጠመና ፡ ክርስቲያኑ ፡ በጦር ፡ ሊወጋው ፡ ሲል ፡ ሻሙን ፡ በሰይፍ ፡ እጁን ፡ ከነጦሩ ፡ ሰብሮ ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ገለበጠው ። አውራይ ፡ ኡመር ፡ ዲንም ፡ (የሱልጣን ፡ መሐመድ ፡ ልጅ) ፡ ካንድ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ አጠገብ ፡ ከቆመ ፡ ሹም ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ፡ . . . . ፤ አሊ ፡ ኡል ፡ ዋራዲም ፡ ባንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ሹም ፡ ላይ ፡ ገሥግሶ ፡ ተጋጠመና ፡ በሰይፍ ፡ በትር ፡ ጭንቅላቱን ፡ ከአንገቱ ፡ ቆርጦ ፡ ወረወረው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ማፈግፈግ ፡ ዠመሩ ። ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ‹ወዴት ነው ፡ የምትሸሹት› ፡ ብሎ ፡ ሲጮኽባቸው ገራድ ፡ አቢድ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ እየሰደበ ፡ ቀረበው ፡ ወሰን ፡ ሰገድም ፡ የፈረሱን ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ገራድ ፡ መለሰና ፡ ተጋጠመው ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጦር ፡ እስላሙ ፡ ሰይፍ ፡ ነበር ፡ የያዙት ። ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አቢድን ፡ መትቶ ፡ የግራ ፡ እጁን ፡ አቆሰለው ። እስላሙም ፡ ጥሩር ፡ ለብሶ ፡ ነበርና ፡ የጦሩ ፡ ጫፍ ፡ እብረቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ለማውጣት ፡ ሲስብ ፡ ተሰበረ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጦሩን ፡ ትቶ ፡ ሰይፉን ፡ ከአፎቱ ፡ ለማውጣት ፡ ሲተናነቅ ፡ ገራድ ፡ አቢድ ፡ በሰይፍ ፡ ከማዥራቱ ፡ ቲንሽ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ኳፍ ፡ አድርጎ ፡ መቃው ፡ ወሰን ፡ ሰገድም ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወድቆ ፡ ‹እኔ ፤ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ነኝ ፡ አትግደለኝ ፡ አትግደለኝ› ፡ አለ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ መውደቁን ፡ ሲያዩ ፡ ገራድ ፡ አቢድም ፡ የወደቀው ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳ» ፡ አዝ

ማቻቸው ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ መሞቱን ፡ ለክርስቲያኖቹ ፡ ንገሩ" ፡ ብሎ ፡ ለጓደኞቹ ፡ ጮኸ ። እነሱም ፡ "ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሞተ» ፡ እያሉ ፡ ጮሁ ። እርሱም ፡ እንደቆሰለ፡ ተኝቶ ፡ ‹ሕያው ፡ ነኝ ፡ ጦርነቱ ፡ ይቀጥላል ፡ (1) ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ክርስቲያኖች የአለቃቸውን ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ሞት ፡ ሲሰሙ ፡ ተዘበራርቀው ፡ በየበኩላቸው ፡ ሸሹ ፡ እስላሞቹም እየተከታተሉ ፡ ግማሾቹን ፡ እየገደሉ ፡ ግማሾቹን ፡ ማረኩ ።

ይማም ፡ በበኩሉ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ በዘቃላ ፡ (ዝቋላ) ፡ በኩል፡ አድርጎ ፡ ሲጓዝ ፡ ከወዚር ፡ አዶሌ ፡ ጋር ፡ ተገናኘ ፡ ከወዚር ፡ አዶሌም ፡ ጋር፡ዣን ናሃድ ፡ (አዳል ፡ አንበሶ)፡ የሚባለው ፡ ተማርኮ ፡ አብሮ ፡ ነበር ፡ ይማም ፡ ፊት፡በቀ ረበ ፡ ጊዜ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ ይቆይ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ጦርህን ፡ ሰብስብና፡ ሰንደቅ ፡ አላማህን ፡ ዘርጋና ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እንፈልግ ፡ ብሎ ፡ ለወዚሩ ፡ ነገረ ውና ፡ አፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ወዚሩ ፡ "አንተ ፡ በባንዲራህ ፡ አጠገብ ፡ ቆይ ፡ ክር ስቲያንን ፡ ስላንተ ፡ ሌያበር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ይሂድ» ፡ ብሎ ፡ ስለሚወደው ፡ (ስለ ሚሳሳለት) ፡ ይማምን ፡ መከረው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይማም ፡ ንግግሩን ፡ አልተቀበለው ምና ፡ አፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ከሑሴን ፡ ከገራድ ፡ አህሙሹ ፡ ጋር ፡ ይሄድ ፡ ዠመር። ክርስቲያኖቹንም ፡ ቀድመው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲጓዙ ፡ አንድ ፡ እረኛ ፡ ከመንገድ፡አግ ኝተው ፡ ስለወሰን ፡ ሰገድ ፡ የሚያውቀውን ፡ ጠየቁት ፡ እርሱም ፡ በስሕተት ፡ ማያ ውቅ ፡ በጧት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ቀድሞ ፡ ሄዷል ፡ ብሎ ፡ ተናገረና ፡ ወደፊት ፡ ተጉ ዘው እሰፊ ፡ መንገድ ፡ ሲደርሱ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ያለፉበት፡የፈ ረስ ፡ ኮቴና ፡ የእግር ፡ ምልክት ፡ የለምና ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በእርግጥ ፡ በኋላችን ፡ ናቸው" ፡ ተባባሉ ፡ . . . . ፡ ከዚያ ፡ ይማምና ፡ ጓደኞቹ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተሸሸ ገው ፡ ሲመለከቱ ፡ ከወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦርነት ፡ የሸሸው ፡ ጦር ፡ ሲመጣ ፡ ጓደኞቹ፡ አዩና ፡ እነዚያው ፡ ሸሽተው ፡ ይመጣሉና ፡ ከፊታቸው ፡ ቀድመን ፡ እንዋጋቸው ፡ አሉ ፡ ይማም ፡ ግን ፡ "እኛ ፡ አራት ፡ እነሱ ፡ ብዙ ፡ ስለሆኑ ፡ ቲንሽ፡መሆናችንን፡ ሲያውቁ ፡ ተዋግተው ፡ ሊገድሉን ፡ ይችላሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ አሳልፈን ፡ ከኋላቸው ፡ የገጠምናቸው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ያው ፡ ያሸነፉቸው ፡ ጦር ፡ ደርሶ ፡ የሚዋጋቸው ፡ ይመስላቸዋልና ፡ ለኛ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ «ብሎ ፡ ቢመልስ ፡ በምክሩ ፡ መልካምነት ፡ አመሰገኑት ፡ . . . , ጦሩ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ አለቃ ፡ ገጠመው ፡ ገራድ ፡ አህሙሹና ፡ አሎ ሽም ፡ እንደዚሁ ፡ ሌሎቹን ፡ አለቆች ፡ እየተዋጉ ፡ ገደሏቸው ፡ . . . . አንድ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፡ የሚባል ፡ የገዥነት ፡ ስሙ ፡ ጐጃም ፡ ነጋሽ ፡ ንጉሡና ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ የሚያከብሩት ፡ ነበር ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ ኤሚር ፡ ሑሴን ፡ ተጋጠመና ፡ ሁለቱም ፡ ተናንቀው ፡ ኤሚሩ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ከኮርቻው ፡ ላይ ፡ ጣለው ፡ ፈረሱም ፡ ሸሸ ። ኤሚሩም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ተከታተለና ፡ ፈረሱን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኑ ፡

(፩) አላክህ ፡ በላ ፡ አላክ ፡ ፀላ ፡ ሲል ፡ ትርጓሜው ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፡ ጦርነቱ ፡ ይቀጥላል ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ፋቂህ ፡ ተርጕሞታል ፡ አይመስለም ።

ተመለሰ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ እሚካ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ቆመ ። ይማም ፡ ይኸውልህ ፡ አንተ ፡ ፈረሱን ፡ ስታባርር ፡ አለቀዮው ፡ እሚካ ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ለሑሴን ፡ ነገረው ፡ ሑሴንም ፡ ይማምም ፡ በየተራ ፡ ጦራቸውን ፡ ቢወረውሩ ፡ የዛፉን ፡ ግንድ ፡ ከመምታት ፡ በቀር ፡ እርሱን ፡ አላገኙ ፡ አሉት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሑሴን ፡ ከፈረስ ፡ ወርዶ ፡ በእግሬ ፡ ሄጄ ፡ ልግጠመው ፡ ቢል ፡ ይማም ፡ "ተው ፡ ቆይ» ፡ ብሎት ፡ ሳለ ፡ በዚሁ ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መጡ ፡ ያንዱ ፡ ስም ፡ አቡበከር ፡ ይበላል ። እርሱንም ፡ ከፈረስህ ፡ "ውረድና ፡ በጦርህ ፡ ይኸን ፡ ክርስቲያን ፡ ውጋው„ ፡ ብሎ ፡ ይማም ፡ አዘዘው ፡ ከፈረሱም ፡ ወርዶ ፡ ተጠግቶት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ቢመታው ፡ ምንም ፡ ሊያደርገው ፡ አልቻለም ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግን ፡ እጁ ፡ ላይ ፡ ጅራፍ ፡ (ትልቅ ፡ አለንጋ ፡) ነበርና ፡ ወደፊት ፡ ተራምዶ ፡ አቡበክርን ፡ በጅራፉ ፡ መትቶ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ አርቆ ፡ ወረወረው ። ደግሞ ፡ ለሁለተኛው ፡ ሰበዲን ፡ ለሚባለው ፡ "ውረድና ፡ ይኸን ፡ ክርስቲያን ፡ ግደል„ ፡ ብሎ ፡ ይማም ፡ አዘዘው ፡ ሰበዲንም ፡ ዋና ፡ የተፈራ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆነ ፡ ባለሰይፍ ፡ ወታደር ፡ ነበርና ፡ ከበቅሎው ፡ ወርዶ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በትር ፤ ጣለውና ፡ ከዛፉ ፡ ውስጥ ፡ ጐትቶ ፡ አውጥቶ ፡ ገደለና ፡ ገፈፈው ፡ ከዚያ ፡ የቀረውንም ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ ገድለው ፡ ምርኮውን ፡ ሁሉ ፡ ከማረኩ ፡ በኋላ ፡ . . . . . ሁሉም ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ተገናኙና ፡ ስላገኙት ፡ ድል ፡ አምላካቸውን ፡ አመሰገኑ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ እንዳላየው ፡ ገደልኸው» ፡ ብሎ ፡ ይማም ፡ ጋራድ ፡ አቢድን ፡ ጠየቀው ፡ እርሱም ፡ «ምን ፡ ያደርግልሃል ፤ . . . . የተማረከ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ እወስድሃለሁ ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተኝቶ ፡ አደራህን ፡ እዚሁ ፡ ጨርሰኝ ፡ ብሎ ፡ ተማጥኖ ፤ ቢለምነኝ ፡ ገደልሁት ፡ ብሎ ፤ መለሰለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ምርኮኞቹን ፡ አቅርቡልኝ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤ ከምርኮኞቹም ፡ ውስጥ ፡ አዶሌ ፡ የማረከው ፡ ገርንናሃድ ፤ ቃሲም ፡ የገርን ፡ አሞራ ፡ ገዥ ፡ ነበሩ ፡ ቃሲም ፡ እስላም ሆኖ ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ ከድቶ ፡ ለንጉሡ ፡ የገባና ፡ በትግሬና ፡ በአንጎት ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ግዛት ፡ ተቀብሎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጦርነት ፡ እስላሞቹን ፡ ያስጨነቀ ፡ ሰው ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ ጋር ፡ ሐና ፡ የላሊበላ ፡ ገዥ ፡ በጠቅላላው ፴ ፡ ሹማምንት ፡ ነበሩና ፡ ሁሉንም ፡ ይማም ፡ አስገደላቸው ።

እንደዚሁም ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፤ ድል ፡ የሆነ ፡ ጊዜ ፡ ገብረ ፡ እንድርያስ ፡ የሚባለው ፡ (፩) ተማርኮ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ «በሀበሻ ፡ አገር ፡ ከአድማስ ፡ (አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡) ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ (ልብነ ፡ ድንግል ፡) ድረስ ፡ ያልገዛሁት ፡ አገር ፡ ያልተሾምሁት ፡ አውራጃ ፡ የለም ፡ እያለ ፡ ይመካ ፡ ነበርና ፡ እርሱም ፡ ተገደለ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፤ ዕድሜው ፡ ፺ ፡ ዓመት ፡ ነበር ።

ከወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ አገሩ ፡ ተገዛ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ ተዋረደ ፡ ወደፊትም ፡ እንደምናነሣው ፡ ከሕዝቡም ፡ አብዛኛው ፡ ክፍል ፡ እስልምናን ፡

(፩) አባ ፡ ገብረ ፡ እንድርያስ ፡ ክፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዠምሮ የታወቁ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ናቸው ፡ ማኅፉዝን ፡ የድል ፡ ወንበራን ፡ አባት ፡ የገደሉትም ፡ እርሳቸው ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ።

ተቀበለ» ፡ ሲል ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ፍጻሜ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ያሳየናል ።

ወደኋላ ፡ ተመልሰን ፡ በራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ጦርነት ላይ ፡ የምንመለከተው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለ ።

፩ኛ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ለግራኝ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ እስካሁን ፡ ያደረግኸው ፡ ይበቃሃል ፡ ያለዚያ ፡ እስካሁን ፡ ያላያሃቸውን ፡ የዳሞትን ፡ የጉራጌን ፡ የጋፋትን ፡ የእናርያን ፡ . . . ጦር ፡ ይዤ ፡ እመጣለሁ ፡ ቅዳሜ ፡ ጠብቀኝ ፡ ብሎ ፡ ቢጽፍለት ፡ ከግራኝ ፡ ሹም ፡ አንዱ ፡ በዳሞትና ፡ በጉራጌ ፡ ነገድ ፡ አታስፈራራን ፡ እነርሱ ፡ እርሻ ፡ ከማረስ ፡ እስከ ፡ አገራችን ድረስ ፡ እንጨት ፡ እየቆረጡ ፡ እያመጡ ፡ ከመነገድ ፡ በቀር ፡ ጦርነት አያውቁም ፡ ሲል ዛሬ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ባሕር ፡ ዛፍ ፡ ከባለቦታ ፡ እየገዙ አጠናውን ፡ ወይም ፡ ሽንሽኑን ፡ በዝርዝር ፡ ሲሸጡ ፡ ይኸን ፡ ሥራ ፡ ከቀድሞ  ዘመን ፡ የጀመሩት ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን ።

፪ኛ ፡ ለቅዳሜ ፡ ጠብቀኝ ፡ ብሎ ፡ የቅዳሜን ቀን ፡ መምረጡ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ግራኝን ፡ ታሸንፈዋለህ ብለው መነኮሳትና ፡ ናዝራውያን ፡ (ደብቁ ፡ ) ነግረውታል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ከእስላሞቹ ፡ ሹም ፡ ኤሚር ፡ ሑሴን ፡ የኛ ፡ ሺሆች ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ እንደምትሞት ፡ አረጋግጠውልናል ፡ ብሎ ፡ ሲመልስ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ አዋቂ ፡ መጠየቅን ፡ እንዳስለመዱ ፡ በትክክል ፡ ይታወቃል ። የዚህም ፡ ልማድ ፡ በነርሱ ፡ የተጀመረ ፡ አይደለም ።

ጥንት ፡ በእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ ነገሥታቱ ፡ እነሳዖል ፡ እነዳዊት ፡ እነሕዝቅያስ ፡ እነአክአብ ፡ በጐረቤታቸው ፡ ካሉት ፡ መንግሥታት ፡ ከነፍልስጥኤም ፡ ከነሞአብ ፡ ከነአማሌቅ ፡ ለመዋጋት ፡ ጉዞ ፡ ከማድረጋቸው ፡ በፊት ፡ በየዘመናቸው ፡ የተነሡትን ፡ ነቢያት ፡ ሳሙኤልን ፡ ወይም ፡ ኤልያስን ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ . . . ሞዓባውያንን ፡ ወጥቼ ፡ ልውጋን ፡ ብሎ ፡ " ሳይጠይቅና ፡ " ውጋው ፡ ታሸንፈዋለህ ፡ "የሚባለውን ፡ መልስ ፡ ሳያገኝ ፡ ከጠላቱ ፡ አይዋጋም ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ የግሪኮቹም ፡ የሮማውያኖቹም ፡ ቄሣሮች ፡ አዋቂዎቻቸውን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሳይጠይቁ ፡ መዋጋት ፡ አይሆንላቸው ፡ ነበር ፡ ከጣዖት ፡ አምልኮ ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፌን ፡ በየምዕራፉ ፡ ተመልከት ።

በተረፈ ፡ አራብ ፡ ፋቂህ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ "ስማረክ ፡ እንድትራራልኝ ፡ የሚል ፡ የቃል ፡ መልክት ፡ ደግሞ ፡ መላኩን ፡ ይገልጻል ። ምናልባት ፡ በዚህ ፡ አመካኝቶ ፡ የጠላቱን ፡ የግራኝን ጦር ፡ ለማሰለል ፡ ሰው ፡ ልኮ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ የመሰለ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ክብሩንና ፡ ጀግንነቱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስገምትበትን ፡ መልእክት ፡ ወደፊት ፡ ሊዋጋው ፡ ለሚዘጋጀው ፡ ጠላቱ ፡ የሚልክ ፡ አይመስልም ። ደግሞ ፡ የዚህ ፡ የፍርሃትና ፡ የመላላት ፡ መንፈስ ፡ ቢኖረው ፡ ኖሮ ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ በርትቶ ፡ መዋጋትም ፡ ጦሩም ፡ ሊሸሽ ፡ ሲል ፡ እፊ

ረሱ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሸሹት ፡ ብሎ ፡ በቁጣና ፡ በጩኸት ፡ መመለስ ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ግራኝና ፡ ጦሩ ፡ ባለፉት ፡ ጦርነቶች ፡ የራስ፡ ደገልሃንን ፤ የንጉሡንና ፡ የራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድን ፡ ጦር ፡ ያሸነፈ ፡ በቅርቡ ፡ ንጉሡ ፡ ባሉበት ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ አሸንፎ ፡ ንጉሡን ፡ ማባረር ፡ የቻለ ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቅ ፡ በወሰን ፡ ሰገድ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ እሸነፋለሁ ፡ እሞታለሁ ፡ የሚል ፡ ሥጋት ፡ መመላለሱ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጐን ፡ ደግሞ፡ በርትቼ ፡ ብዋጋው ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ማሸነፍ ፡ የቻለውን ፡ ግራኝን ፡ በእግዚአብሔር፡ ፈቃድ ፡ አሸንፈው ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ መንፈሱን ፡ ማጽናናቱ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ተፈራራቂ ፡ የሆነ ፤ የድል ፡ መሆን፡ ሥጋትና ፡ የድል ፡ ማድረግ ፡ ተስፋ ፡ ዝግና ፡ በሆኑት ፡ በዓለም ፡ መሪዎች ፡ ዘንድ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ራስ ፡ ወሰን ሰገድም ፡ ይኸን ፡ ጦርነት ፡ የፈጸመ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ሥፍራውም ፡ የጦር ፡ መሣሪያውም ፡ ያደላው ፡ ለእስላሞቹ ፡ ነውና ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ያለፈውን ፡ ሁሉ እወጣ ፡ ይሆናል፡ ብሎ ፡ በክርስቲያናዊ ፡ እምነቱ ፡ ተደግፎበት ፡ የነበረው ፡ ተስፋ ፡ አልተፈጸመለትም። ቢሆንም ፡ እርሱ ፤ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ሸሽቶ ፡ ለማምለጥ ፡ ሳይሞክር ፡ እንደ ዝግና ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ራሱ ፡ በጦር ፡ ከባላጋራው ፡ ጋር፡ ተደባድቦ ፡ ደንበኛ ፡ አማሻት ፡ ሞተ ። አሁንም ፡ ያራብ ፡ ፋቂህን ፡ ጽሑፍ ፡ ስንመለከት ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ አማሻት ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ ይገልጽልናል ። አንደኛው፡ ተመትቶ ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ሲወርድ ፡ "እኔ ፡ ወሰን ' ሰገድ ፡ ነኝ ፡ አትግደለኝ» ፡ አለው፡ ይላል ። ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ‘ እባክህን ፡ እዚሁ ፡ ጨርሰኝ ፡ « ብሎ ፡ ባላጋራውን ፡ ገራድ ፡ አቢድን ፡ አጥብቆ ፡ እንደለመነውና ፡ እንደገደለው ፡ ይገልጻል ። የዚህም፡ የልዩነቱ ፡ ምንጭ ፡ ከአራብ ፡ ፋቂህ ፡ ስሕተት ይሁን ፡ ወይም ፡ በርግጥ ፡ መዠመሪያ ፡ አትግደለኝ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ የቁስሉን ጽናት ፡ በማየት ፡ ወይም ፡ እግራኝ ፡ ፊት፡ ቀርቦ ፡ የመታየቱን ፤ ውርደት ፤ ስለጠላው ፡ ይሁን ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሞት ፡ በንጉሡም ፡ በተረፈውም ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ቃላቅና ፡ የመጨረሻ ፡ ተስፋ ፡ አስቆረጠ ። ከንጉሡ ፡ ዝምሮ ፡ የተጠቃው፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ልብ ፡ ድል ፡ የናፈቀው ፡ ዓይናቸው ፡ ያረፈው ፡ በራስ ፡ ወሰን፡ ሰገድ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ሲሞት ፡ መራራ ፡ ኀዘን ፡ ገጠማቸው ። ሃይማኖታቸውን፡ ንጉሣቸውን ፡ የሚወዱት ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀሩ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ያወላውል ፡ ከነበረው ፡ ጋር ፡ እየተሰለፉ ፡ ለግራኝ ፡ ገቡለት ። እርሱም ፡ አውቆ ፡ የገባለትንም፡በምርኮ ፡ ያገኘውንም ፡ እያሰለፈ ፡ በጅምላ ፡ አሰለመው ። እንገዛለን ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ አንለውጥም ፡ ያሉትን ፡ በጦርና ፡ በጐራዴ ፡ በሰይፍ ፡ አስፈጃቸው ። ግራኝ ፡ በበኩሉ ፡ ይኸን ፡ ሲያደርግ ፡ ሹማምንቱ ፡ እነወዚር ፡ ኦዶሌ ፤ እነአቡበከር ፡ ቀጢን፡ እነኤሚር ፡ ሞጃሂድ ፡ . . . . ፡ በየአውራጃው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ይኸንኑ ፡ ፈጸሙ ። በዚህ ፡ በአረብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኘው ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ እየተያዘ ፡ ሲሰልም ፡ አንድ ፡ አይበስ ፡ ለሃቲ ፡ (ለሐዬ) ፡ በናቱ ፡

ከንጉሡ ፡ የሚዛመድ ፡ የቀወት ፡ ሹም ፡ ታደሩና ፡ ባላገሩ ፡ ሲሰልም ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ እምቢ ፡ አለ ። እግራኝ ፡ ፊት ፡ ቢያቀርቡት ፡ ‹እስላም ፡ አልሆንም ፡ አባቶቼ፡ አያቶቼ ፡ የሞቱበትን ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ለመለወጥ ፡ አልመጣሁም› ፡ ብሎ፡ ተናገረ ። ግራኝም ፡ "እነዚሁ ፡ ሁሉ ፡ ጭፍሮችህ ፡ ሲሰልሙ ፡ ያንተ ፡ መጽናት፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ ቢሆንም ፡ ከነርሱ ፡ ትሻላለህ" ፡ ቢለው ፡ "እነርሱ ፡ የማያረቡ ፡ እንስሶች ፡ ናቸው ፡ የራሳቸውንም ፡ ሃይማኖት ፡ የናንተንም ፡ ሃይማኖት ፡ አያውቁም፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ሲለውጡ ፡ ውርደት ፡ አይሰማቸውም ። እይበስ ፡ ለሐዜ ፡ ሰለመ፡ ተብሎ ፡ ለኔ ፡ በንጉሡም ፡ በመኳንንቱም ፡ ዘንድ ፡ ቢሰማብኝ ፡ ለኔ ፡ ትልቅ ፡ ውር ደት ፡ ነውና ፡ ሃይማኖቴን ፡ አልለውጥም ፡ ‹ብሎ ፡ መለሰ ። ከትክለ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ላይ ፡ የተማረከችው ፡ የግራኝ ፡ ሚስት ፡ ሃጂራህ ፡ ለዚህ ፡ ለሰውዬው ፡ ትዛ መደው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ግራኝም ፡ እርሷን ፡ ይወዳት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ "ባንተና ፡ በእኛ ፡ መከከል ፡ ዝምድና ፡ አለ ፡ ከክርስቲያኖቹም ፡ መካከል ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ስለሆንህ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ታገለግላለህና ፡ እምቢታህን ተው ፡ "ብሎ ፡ አጥብቆ ፡ ቢጠይቀው ፡ «ዘመድህ ፡ አገልጋይህ ፡ እሆናለሁ ፡ ነገር ግን ፡ ሃይማኖቴን ፡ አልለውጥም ፡ ከእ ስላም ፡ ወይም ፡ ከክርስቲያን ፡ ጋር ፡ ብትዋጋ ፡ ያንተ ፡ ረዳት ፡ ነኝ ፡ «ብሎ ፡ መልሰ ፡ በሃይማኖቱ ፡ ጸና ። ግራኝም› ፡ ግን ፡ በል ፡ ለኔ ፡ የክርስቲያን ፡ እርዳታ፡ አያሻኝም ፡ ልታገለግለንም ፡ ልትጎዳንም ፡ ትችልም ፡ ይልቅስ ፡ ፈረስህንና፡የጦር፡ መሣሪያህን ፡ አስረክብና ፡ ሃይማኖትህን ፡ ይዘህ ፡ ተቀመጥ» ፡ ብሎ ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ መልሰ ፡ ተወው ።

ከርሱ ፡ ከተለያየ ፡ በኋላ ፡ የሰለሙት ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡ ተሰብስበው ፡ ግራኝ ፡ ቢተውህ ፡ ሌሎቹ ፡ ሕይወትህን ፡ አይምሩትም ፡ ያውስ ፡ ሃይማኖቱን ፡ አል ለውጥም ፡ የምትለው ፡ ከኛ ፡ በልጠህ ፡ ነውን ፡ ስለምና ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ ፡ አለዚያ ፡ አንድ ፡ ተንከል ፡ ሠርተን ፡ እኛው ፡ እናስገድልሃለን ፡ ‹ብለው ፡ ስለ ፡ አስፈ ራሩት ፡ ሰለመና ፡ ፫ወር ፡ ከግራኝ ፡ ጋር ፡ እንደተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ አምልጦ፡ወደ፡ ንጉሡ ፡ ሄዶ ፡ ክርስቲያንነቱን ፡ አጸደቀ ። በደብረ ፡ ብርሃን ፡ (ተጉለት) ፡ ዙሪያ ፡ ያለውንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ እነገራድ ፡ ናስርን ፡ እነገራድ ፡ አቢድን ፡ እየላከ ፡ አገ ሩን ፡ ሁሉ ፡ አሰለመ ። የቀረው ሁሉ ፡ ሲሰልም ፡ እምቢ ፡ ያሉት ፡ ሁለት ፡ ሹማ ምንቶች ፡ ከነጭፍራቸው ፡ ገራድ ፡ ናስር ፡ ይዟቸው ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዘንድ ፡ አም ጥቶ ፡ አቆማቸው ፡ ግራኝም ፡ „አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ሲሰልም ፡ የእናንተ ፡ እምቢታ ፡ ምን ድን ፡ ነው ፡ "ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው„ ፡ ያለንበትን ፡ ሃይማኖት ፡ ልንለውጥ ፡ አል መጣንም ፡ የመጣነው ፡ ስለሃይማኖታችን ፡ አንገታችንን ፡ ለማስቆረጥ ፡ ነው » ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡ በዚህ ፡ መልስ ፡ ግራኝ ፡ ተገረመ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ ምኞት ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ማስለም ፡ ስለሆነ ፡ በመንፈሳቸው ፡ ጽናት ፡ ከመ ገረም ፡ በቀር ፡ ምሕረት ፡ ሊያደርግላቸው ፡ አልፈለገምና ፡ «ደግ ፡ ነው„ ፡ ብሎ ፡ ወዲ ያው ፡ አስገደላቸው ።

ስለዚህ ፡ ይኸን በመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ የሸዋን ፡ የዳሞትን ፡ የጉራጌን ፡ የባሌን፡ የደዋሮን ፤ የፈጠጋርን ፡ የይፋትን ፡ አገር ፤ እሰለመ ። በየአውራጃው ፡ የራሱን ፡ ሹማምንት ፡ እየደለደለ ፡ ሾመ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የተረፈ ፡ እልኸኛ ፡ የክርስቲያን፡ ሹም ፡ ገና ፡ ስለአገሬ ፡ ስለሃይማኖቴ ፡ እዋጋለሁ ፡ ቢልም ፡ በሹማምንቱ ፡ እያስፈጀ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ የራሱ ፡ ግዛት ፡ አደረጋቸው ። እንግዲህ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የምንመለከተው ፡ በየተራ ፤ የወሎን ፡ የትግሬን ፡ የበጌምድርንና ፡ የጐጃምን ፡ ጦርነት ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ ሰፊ፡ ናት ፡ በያውራጃው ፡ የሚገኙት ፡ የጦር ፡ ሹማምንቶቿዋም ፡ የማያልቁ ፡ ያለፈ ፡ ዕልቂት ፡ ተስፋ ፡ የማያስቆርጣቸው፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ የግራኝ ፡ ሥልጣን ፡ በቆየበት ፡ በ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ያለዕረፍት ፡ ትግሉ ፡ መቀጠሉን ፡ በየምዕራፉ ፡ እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

## የደቡብ ፡ አገሮች ፡ በግራኝ ፡ ስለመገዛታቸው ፡ የአሙራይ ፡ አትማን ፡ ለግራኝ ፡ መግባት ።

ከ፲፰፻፲፱ ፡ እስካሁን ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፷፬ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ ባለፈው ፡ ሁሉ ፡ በተመለከትነው ፡ ያራት ፡ ዓመት ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ታላላቅ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ከነጭፍራቸው ፡ አልቀዋል ። በባደቄ ፤ በሽምብራ ፡ ኰሬ ፤ በአይፈርስ ፤ በዝሆን ፡ ዱር ፡ ጦርነት ፡ ከወደቁ ፡ ታላላቅ ፡ አለቆች ፡ ውስጥ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዘወንጌል ፤ አዝማች ፡ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ የሮቤል ፡ ታናሽ ፡ ወንድም ፡ ጸሐፊ ፡ ላም ፡ ሮቤል ፡ ራስ ፡ ማኅፀንቶ ፡ ራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ (እስላሞ) ፤ አዝማች ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ የሮቤል ፡ ልጅ ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ታላቁና ፡ የተከበረው ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ መሞታቸውን ፡ እነሆ ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ። ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ የሸዋን ፡ የዳሞትን ፡ የደዋሮን ፡ የባሌን ፡ የፈጠጋርን ፡ የይፋትን ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ ባላባቶች ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ተስፋ ፡ ያስቆረጠ ፡ ወደ ፡ ግራኝም ፡ እመግባትም ፡ እመስለምም ፡ ያደረሰ ፡ የራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሞት ፡ ነው ። እጥፋት ፡ እመውደቅ ፡ ላይ ፡ ያዘነበለውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ እርሱ ፡ ያነሣው ፡ ይሆን ፡ ተብሎ ፡ ጥርጣሬ ፡ ያለበት ፡ ተስፋ ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ መኰንን ፡ ተጥሎ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በማንሣት ፡ ፈንታ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ሲወድቅ ፡ ነገሩን ፡ በጥርጣሬ ፡ ይመለከት ፡ የነበረው ፡ የእስላም ፡ ነክነት ፡ ያለው ፡ ክርስቲያንና ፡ ፍጹም ፡ ክርስቲያን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ እየገባ ፡ መስለም ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። ግማሹም ፡ ለሃይማኖቱ ፡ ለሀገሩ ፡ ለንጉሡ ፡ ቀናተኛ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እየሄደ ፡ ተደባለቀ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ያ ሁሉ ፡ መኳንንት ፡ ቢያልቅ ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ታላላቅ ፤ መኳንንት ፡ ንጉሣቸውን እየሄዱበት ፡ እየተከተሉ ፡ ከአደጋ ፡ እየጠበቁ ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ለመሞት ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ እነራስ ፡ ደገሃልን፡ እነራስ ፡ ባንያት ፡ እነ፡ፀሐት ፡ ወደድ ፡ ሠርጤ ፡ አሉ ። ከነርሱም ፡ ጋር ፡ ንጉሡ ፡ ወደፊት ፡ ሊሄዱበት ፡ ባሰቡት ፡ በወሎና ፡ በጐጃም ፡ በትግሬና ፡ በበጌምድር ፡ የቀ

ድሞዎቹ ፡ አለቆች ፡ ቀድሞ ፡ መጥተው ፡ እየተዋጉ ፡ ቢሞቱም ፡ በሚቆቹ ፡ እግር ፡
የተተኩት ፡ አለቆች ፡ ይልቁንም ፡ ትግሬዎቹ ፡ እንተስፋ ፡ ልዑል ፡ በታላላቅ ፡
አስደናቂ ፡ ጦርነት ፡ የግራኝን ፡ ጦርነት ፡ ሲመክቱ ፡ እናያለን ። በዚህም ፡ ግራኝ ፡
እስካሁን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በያዘው ፡ በሸዋና ፡ በባሌ ፡ እልህና ፡ ወኒ ፡ እየቀሰቀ
ሳቸው ፡ አንገዛም ፡ ብለው ፡ እየተዋጉ ፡ የሞቱት ፡ እንተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እን
አጓሉ ፡ አሉ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ የተረፈ ፡ ጦራቸውንና ፡ ቤተ ፡ ሰባቸውን ፡ ይዘው ፡ ከሸዋ ፡
ወደ ፡ ወሎ ፡ (ቤተ ፡ አምሐራ ፡) ይጓዛሉ ። በአሁኑም ፡ ሰዓት ፡ ግራኝን ፡ ለመው
ጋት ፡ ከሚዘጋጀው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የሚሸሸው ፡ ወይም ፡ ወደግራኝ ፡ ለመግባት ፡
የሚዘጋጀውና ፡ የሚላላከው ፡ ይበልጣልና ፡ አሁን ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ የሚባ
ለው ፡ ከምክትሉ ፡ ከአናንያ ፡ ጋር ፡ ንጉሡን ፡ መከተል ፡ ትተው ፡ እንደምን ፡
ወደ ፡ ግራኝ ፡ እንደገቡ ፡ እንመልከት ።

አውራይ ፡ አትማን ፡ ቤን ፡ ዳር አሊ ፡ የይፋት ፡ ወይም ፡ ያዳል ፡ ተወላጅ ፡
መሆኑ ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም ። አራብ ፡ ፋቂህ ፡ በሱልጣን ፡ መሐመድ ፡ ጊዜ ፡
ከጦርነት ፡ ተማርኮ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ለንጉሡ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆነ ይለዋል ።

የሆነ ሆኖ ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ እንደሚገልጸው ፡ እስላም ፡ የነበረና ፡ ከን
ጉሡ ፡ ጋር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በክርስቲያንነት ፡ መኖሩ ፡ በንጉሡም ፡ ውስጥ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ የፈጠጋርን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የይፋትን ፡ ግዛት ፡ እየተሾመ ፡ በነዚ
ያም ፡ አገሮች ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ እያዘመተ ፡ ለንጉሡ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ ከግራኝ ፡
ጦር ፡ ጋር ፡ ተዋግቷል ። በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ጦርነት ፡ በዱከም ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡
ጦር ፡ ይመራ ፡ ነበር ። በራራህ ፡ (በረህ? ፡) በሚባለው ፡ አገር ፡ ከአብሟማ ፡ ኑር ፡
ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ ተሸነፈ ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ (ዳሞት ፡) ንጉሡ ፡ የሰፈሩ ፡ ጊዜ ፡ ዋና
ውን ፡ በር ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ይጠብቅ ፡ የነበረው ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በመጨረሻ ፡ ለራስ ፡
ወሰን ፡ ሰገድ ፡ እንደረዳት ፡ ሆኖ ፡ ዘምቷል ። በጥብቅና ፡ በገዥግንነት ፡ መዋጋቱን ፡
አራብ ፡ ፋቂህ ፡ ባያወሳለትም ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ለን
ጉሡ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ ማገልገሉና ፡ መዋጋቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡
እንኳን ፡ የእስላም ፡ ነክነት ፡ ያለው ፡ እርሱ ፡ ይቅርና ፡ ክርስቲያኖቹም ፡ ተስፋ ፡
ቆርጠው ፡ ወደግራኝ ፡ የሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ነውና እርሱና ፡ ምክትሉ ፡ አናንያ ፡
የይፋትን ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ የገቡበትን ፡ አኳሆንና ፡
የንጉሡን ፡ ወደወሎ ፡ መጓዝ ፡ ከአራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ እንመልከት ።

‹. . . . . የይፋትን ፡ ግዛት ፡ ላንተ ፡ ነውና ፡ የምሰጥህ ፡ ሂድና ፡ አገሪቱን ፡
ያዝ ፡ ብሎ ፡ ይማም ፡ ለባሕር ፡ ጦር ፡ ( አረቦች ፡) መሪ ፡ ለሻምሱ ፡ ነገረው ፡ ሻም
ሱም ወደ ፡ ይፋት ፡ ሄደ ። አገሩም ፡ ለፈረስ ፡ አይመችም ፡ ነበርና ፡ በእግር ፡ ሄዶ ፡
ከአገሬው ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ። ሕዝቡም ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ እንደተከበበ ፡

ሲዋጋ ፡ ቆይቶ ፡ መጨረሻውን ፡ ተሸነፈና ፡ ሁሉም ፡ እየገባ ፡ ሰለመ ። በዚያም ፡ አንድ ፡ የቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡ አፄ ፡ እስክንድር ፡ ያሠራት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረች ፡ በውስጧ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ ነበር ። ቀድሞውንም ፡ ንጉሡ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ አሠርቶት ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ በወርቅ ፡ ሥራ ፡ የተጠረዘ ፡ . . . . . ትልቅ ፡ ወንጌል ፡ ነበር ። እርሱንም ፡ ከመሬት ፡ ለማንሳት ፡ ሁለት ፡ ጠንካራ ፡ ሰው ፡ ያስፈልግ ፡ ነበር ። ሻምሱ ፡ ወደ ፡ ውስጧ ፡ ገብቶ ፡ በውስጧ ፡ የሚገኘውን ፡ ሁሉ ፡ የ፶ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ጌጥ ፡ ያለበት ፡ ያፄ ፡ እስክንድር ፡ በርኖስ ፡ (ካባ፡) ጭምር ፡ ወስዶ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አቃጥሎ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ተመለሰና ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ አስረከበው ። ይማምና ፡ ጓደኞቹም ፡ የወርቁን ፡ ወንጌልና ፡ ስዕሉን ፡ እያዩ ፡ አደነቁ ።

ኤሚር ፡ አሊ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ ዳርጃህ ፡ (ዳርጌ ፡) በኩል ፡ አገሩን ፡ እያስገበረ ፡ ግብር ፡ እየቆረጠ ፡ ሄዶ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሠፍሮ ፡ ይማምን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ። ይማም ፡ ደግሞ ፡ ገራድ ፡ አህሙሹን ፡ እኔ ፡ ከኋላ ፡ እከተልሃለሁና ፡ እሬት ፡ ቀድመህ ፡ በሙሉ ፡ አምነው ፡ እስኪገቡ ፡ ድረስ ፡ የደፋትን ፡ ሕዝብ ፡ ውጋ ፡ (1) ብሎ ፡ ከማታን ፡ ጋር ፡ ላከውና ፡ እርሱ ፡ ፳ ፡ ፈረሰኛ ፡ ይዞ ፡ ቀረ ። ያለበት ፡ ሥፍራ ፡ ለይፋት ፡ ቅርብ ፡ ነበር ። እስላሞቹም ፡ ሁሉን ፡ በያለበት ፡ ልከህ ፡ ከ፳ ፡ ፈረሰኛ ፡ ጋር ፡ ብቻህን ፡ ቀረህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አትዝምር ፡ ብለው ፡ ወቀሱት ። ገራድ ፡ አህሙሹም ፡ ተመለሰ ፡ አገር ፤ እንዲያስገብሩ ፡ በያውራጃው ፡ የላካቸው ፡ የኤሚሮች ፡ (የጦር ፡ ሹማምንቶች ፡) ቍጥር ፡ ፶ ፡ ይሞላል ።

ከሀዲው ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ የሞተ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚህ ፡ ወደ ፡ ግዛቱ ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ መጥቶ ፡ ተቀምጦ ፡ የጋፋትን ፡ የወናግ ፡ ጃራን ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ይማም ፡ አቡናህ ፡ የገባ ፡ ጊዜ ፡ «እስላሞቹን ፡ እወጋለሁ ፡ እንጂ ፡ በአገሬ ፡ (በይፋት) ፡ አላስገባቸውም» ፡ ብሎ ፡ ለወታደሮቹ ፡ ተናገረ ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ከወታደሮቹ ፡ በድብቅ ፡ አድርጎ ፡ ጥንት ፡ ዘሬም ፡ እኔም ፡ እስላም ፡ ነን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ወስደው ፡ ክርስቲያን ፡ አደረጉኝ ። ልቤ ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ ከእስላምነት ፡ አልተለየም ። አሁን ፡ ግን ፡ ወዳላህና ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወዳንተም መመለስ ፡ ስለምፈልግ ፡ ባለፈው ፡ ጥፋቴ ፡ የማትቀጣኝ ፡ እንደሆነ ፡ ወዳንተው ፡ እገባለሁ ፡ እዚህ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ያለውንም ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ አንድ ፡ ተንኮል ፡ (ብልሃት) ፡ ሠርቼ ፡ ወዳንተ ፡ ገብተው ፡ እስላም ፡ እንዲሆኑ ፡ አደርጋለሁ ብሎ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ በይፋት ፡ እስላሞች ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ይማም ፤ ላከ ። ይኸንንም ፡ ምሥጢር ፡ ለማንም ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳትገልጹ ፡ ብሎ ፡ አስጠነቀቀ ።

ይማም ፡ ከመልክተኞቹ ፡ ደብዳቤውን ፡ ተቀብሎ ፡ ነገሩን ፡ ከተረዳ ፡ ወዲህ ፡ ወሬ ፡ አግኝቻለሁና ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ገራድ ፡ አህሙሹ ፡ ልኮ ፡ አስ

(፩) ምናልባት ፡ ሻምሱ ፡ ሳያስገብር ፡ ስለተመለሰ ፡ ማለቱ ፡ ይሆናል ።

መለሰው ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ የይፋት ፡ ሕዝብ ፡ መሪያቸውን ፡ እስላሞን ፡ አስ ቀድመው ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ መጡና ፡ ሰለሙ ፡ እስላሞ ፡ ግን ፡ ይማም ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ የዘመተ ፡ ጊዜ ፡ እስላምነቱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሄደ ። ይማም ፡ የአውራይ ፡ አትማንን ፡ ደብዳቤ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ከአመፃቸው ፡ ተመ ልሰው ፡ የክህደትን ፡ ሥራ ፡ ለማይሠሩት ፡ ያለፈ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ይሠረይላቸዋል ፡ የሚለውን ፡ በቁራን ፡ የተጻፈውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ በአለ ፈው ፡ ይቀጣኛል ፡ ብለህ ፡ አትሥጋ ፡ አትፍራ ፡ ስለዚህ ፡ ጦብያ ፡ ላይ ፡ እንገ ናኝ ፡ ብሎ ፡ የመተማመኛ ፡ ምልክት ፡ ላከለት ። ደብዳቤውም ፡ በምሥጢር ፡ ደረሰ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይሻላል ፡ ብቻዬን ፡ ነኝ ፡ ብቻዬን ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ብገባ ፡ ባለፈው ፡ በእስላሞች ፡ ላይ ፡ በሠራሁት ፡ ሥራ ፡ ያሥፈራ ኛል ፤ እነዚህን ፡ ያሉኝን ፡ የክርስቲያን ፡ ወታደሮች ፡ እስላም ፡ ሁኑ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ብላቸው ፡ ይገድሉኛል ፡ ወይም ፡ አሥረው ፡ ምርኮኛ ፡ ያደርጉኛል ፡ እያለ ብቻ ውን ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ቆይቶ ፡ ሹክርና ፡ ያቄም ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ እስላሞች ፡ እፊቱ ፡ አስመጣ ፡ ከነዚህም ፡ ከሁለቱ ፡ ሹክር ፡ በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ያቄም ፡ በእዳ ምክንያት ፡ · · · ከይማም ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገብተው ፡ በሹመት ፡ በይፋት ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። እነሱንም ፡ ይማም ፡ ይኸው ፡ እቅርባ ችን ፡ ነው ፡ ያለው ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ገብቶ ፡ ይዘርፈናል ። ስለዚህ ፡ ጦራችንን ፡ ይዘን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እንሽሽ ፡ ወይስ ፡ እዚሁ ፡ ተዋግተን ፡ ንእንሙት ፡ የትኛው ፡ እንደሚሻል ፡ እስኪ ፡ ምክር ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡ እነሱም ፡ እኛ ፡ አገልጋዮችህ ፡ ነን ፡ እንሽሽ ፡ ወይም ፡ እንዋጋ ፡ አለዚያም ፡ እንስለም ፡ ብትለን ፡ እንደፈቃድህ ፡ ከመፈጸም ፡ በቀር ፡ የምንሰጥህ ፡ ምክር ፡ የለም ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። እሱም ፡ እኔ ፡ ከነሣሁት ፡ ከመዋጋቱም ፡ ከመሸሹም ፡ የተሻለው ፡ ይኸው ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መግባቱና ፡ መስለሙ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሄደን ፡ ላለፈው ፡ ጥፋታችን ፡ ይቅ ርታ ፡ እንዲያደርግልን ፡ እንለምነዋለን ። እኔም ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌለት ፡ . . . ለኔም ፡ ለናንተም ፡ የሚሆነን ፡ የመተማመኛ ፡ ምልክት ፡ (፩) ፡ ና ፡ መልስ ፡ ልኮልኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የያዝነውን ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር እንደምን ፡ እናደርገዋለን ፡ እኛንስ ፡ ተከትሎ ፡ እንደምን ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ይገባል ፡ እያለ ፡ ጠየቃቸው ፡ አንተ ፡ ለሕይወታችን ፡ ዋስትና ፡ ከሰጠኸን ግድ ፡ የለም ፡ ለዚህ ፡ እኛ ፡ እንበቃ ለን ፡ አሁንም ፡ አገልጋይህን ፡ አናንያን ፡ ጥራውና ፡ ይምጣ ፡ አሉት ።

አናንያ ፡ ከአውራይ ፡ አትማን ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ ጦሩን ፡ የሚያዝ ፡ የክርስቲ ያን ፡ ሹም ፡ ነው ። ስላዚህ ፡ «አናንያ ፡ ይኸንን ፡ አሳባችንን ፡ ቢሰማ ፡ የሚቀ በለን ፡ ይመስላችኋልን ፡ "ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ "እርሱ ፡ አንተ ፡ እሳትም ፡ ልግባ ፡ ብትለው ተከትሎህ ፡ ይገባል„ ፡ አሉትና ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አናንያ ፡ ተፈ ልጎ ፤ መጣና ፡ አውራይ ፡ እንደዚህ ፡ አለው ፡ "አንተ ፡ ልጄ ፡ ምክትሌ ፡ ነኸ ፡

(፩) ፡ የጃ ፡ በትር ፡ ወይም ፡ ጭብጥ ፡ እህል ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የደረሰብንን ፡ አይተሃል ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ የሚሻል ፡ ይመስልሃል ፡
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አናንያ ፡ እኔ ፡ በእጅህ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለሁ ፡ ምርኮኛ ፡ ወደም
ትሄድበት ፡ እሄዳለሁ ። እንዋጋ ፡ ብትለኝም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሸሽተን ፡ እንሂድ ፡
ብትለኝም ፡ የምታዘኝን ፡ ብቻ ፡ እፈጽማለሁ ። ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። አውራይም ፡
በል ፡ በፊቴ ፡ ከቃሌ ፡ ላትወጣ ፡ ማልልኝ ፡ ቢለው ፡ ማለለት ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡
ይማም ፡ ለመግባትና ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ ለመመለስ ፡ ማሰቡን ፡ ገለጸለት ። እር
ሱም ፡ «እኔም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ወደ ፡ መርጃይ ፡ አገር ፡ ሾመህ ፡ የላከኝ ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ ይማም ፡ ተላልኬ ፡ ለመስለም ፡ አስቤ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳላደርግ ፡
የቀረሁት ፡ ላንተ ፡ ፍቅር ፡ ስል ፡ ነው» ፡ ሲል ፡ መለሰ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አው
ራይ ፡ ትልቅ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ፡ ታዲያሳ ፡ ለጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ እንዴት ፡ አድ
ርጎ ፡ መንገር ፡ ይሻላል ፡ ቢለው ፡ "የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ለኔ ፡ ተወው ። መዠመሪያ ፡
ባንተ ፡ ዙሪያ ፡ የሚያገለግሉህንና ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ የሚሆኑትን ፡ ነገሩን ፡
ገልጬ ፡ እነግራቸዋለሁ ፡ እሺ ፡ ቢሉ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እምቢ ፡ ቢሉ ፡ እንዋ
ጋቸዋለን» ፡ ብሎ ፡ መለሰና ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ለ፺ ፡ ፈረሰኞች ፡ ለ፪ሺ ፡ የእግ
ረኛ ፡ ወታደሮች ፡ ቢገልጽላቸው ፡ «እኛ ፡ ጌታችን ፡ እሳት ፡ ቢገባ ፡ እንገባለን ፡
የኛ ፡ ጉዳይ ፡ የእርሱን ፡ ትእዛዝ ፡ መከተል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ መለሱለት ፡
ይኸንንም ፡ ቃል ፡ ወስዶ ፡ ለአውራይ ፡ አስታወቀ ፡ . . . . ፡ ወናግ ፡ ጃራ ፡ የሚያ
ዛቸው ፡ ፩ሺ ፡ የሚሆኑ ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ነጭ ፡ ተራራ ፡ መስለው ፡
ይታዩ ፡ ነበር ፡ በባሕር ፡ አምባ ፡ እነሱን ፡ የመሰለ ፡ ጦር ፡ የለም ።

አውራይ ፡ አትማን ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወርዶ ፡ ጦሩን ፡ ያሰለፈ ፡ ጊዜ ፡ የወናግ ፡
ጃራ ፡ ጦር ፡ ወዴት ፡ ሄደ ፡ ምነው ፡ አይታየኝ" ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ ከተራራቸው ፡
አልወረዱም ፡ አሉት ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ለውጊያ ፡ ተሰል
ፈው ፡ አያቸው ፡ ከዚያ ፡ «ምን ፡ ሆናችሁ ፡ እኔስ ፡ ምን ፡ በደልኋችሁና ፡ ተለ
ያችሁ ፡ „ብሎ ፡ መላክተኛ ፡ ቢልክባቸው“ ፡ ያንተን ፡ አሳብህንና ፡ ንጉሡን ፡
መክዳትህን ፡ አውቀንብሃል ፡ እኛ ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ አገልጋይና ፡ በፊቱ ፡ የምንሞት ፡
ነን ። ስለዚህ ፡ ወዳንተ ፡ አንመጣም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ ፈልገህ ፡ እንደሆን ፡
ወደ ፡ ተራራው ፡ ብቅ ፡ በል ፡ "የሚል ፡ መልስ ፡ ላኩለት ። ይኸን ፡ ከላኩለት ፡
በኋላ ፡ እነሱ ፡ ጋሻቸውን ፡ እየራሳቸው ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡
(ወደ ፡ ንጉሡ) ፡ ጉዟቸውን ፡ ያዙ ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ ያገሩን ፡ ሰው ፡ እስላ
ሙን ፡ ሁሉ ፡ በሙሉ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ጦብያ ፡ ሄዶ ፡ ይማምን ፡ ይጠባበቅ ፡ ዠመር ።

ይማም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከመኖሪያው ፡ ሥፍራ ፡ አቡናህ ፡ ነበርና ፡ ከአውራይ ፡
አትማን ፡ ለመገናኘት ፡ ወደ ፡ ጦብያ ፡ ሄዶ ፡ በሩቅ ፡ የአውራይን ፡ የተተከለ ፡
ድንኳን ፡ ተመልክቶ ፡ በዚያው ፡ አቅራቢያ ፡ ሠፈረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አውራይ ፡
አትማን ፡ ያለበትን ፡ ሥፍራ ፡ ትቶ የፈረሰኛ ፡ ወታደሩን ፡ አሰልፎ ፡ የሚያማ
ልዱትን ፡ ሺኾችና ፡ ሊቃውንት ፡ ከፊቱ ፡ አሳቀድሞ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ መጣ ..

ወደ ፡ ድንኳኑም ፡ ገብቶ ፡ እጁን ፡ ሳመው ፡ ይማም ፡ አህመድም ፡ በመልካም ፡ ተቀ ብሎ ፡ ወዳያው ፡ «አትፍራ» ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ወታደሮቹም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ እንግ ዲህ ፡ እስላም ፡ ሁኑ ፡ አላቸው ።

ከእኩለ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ፀሐይ ፡ እስክት ፡ ጠልቅ ፡ ድረስ ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ ሁሉም ፡ ሲሰልሙ ፡ አመሹ ። ቍጥራቸው ፡ 20, 000 ፡ ይደርሳል ። ይማም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ። አውራይንም ፡ በረከው ፡ . . . ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ለመመለስ ፡ የሚፈልጉትንም ፡ ኤሚሮች ፡ ሁሉ ፡ ዝቋላ ፡ ይዞ ፡ በተቀመጠው ፡ በወ ዚር ፡ አዶሊ ፡ ውስጥ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ከአደረገ ፡ በኋላ ፡ . . . ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ይጠባበቅ ፡ ለነበረው ፡ ለፈራቃሃም ፡ አሊ ፡ የአውራይን ፡ መግባት ፡ ከገላጸለት ፡ በኋላ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥራ ፈትቶ ፡ እንዳይቀመጥ ፡ ወደ ፡ ተጉለት ፡ ወደ ፡ ወግዳ ፡ ወደሙገር ፡ እየዘመትህ ፡ እስከ፡ጊብር ፡ ድረስ ፡ ውጋው ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፡ እርሱም ፡ ራሱ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ለመሄድ ፡ ከአሰበ ፡ በኋላ ፡ በአውራይ ፡ አትማንና ፡ በአዝማች ፡ ሃይቢ ፡ ምክር ፡ ወደ ፡ ግድም ፡ ሄዶ ፡ የዚህን ፡ አውራጃ ፡ አሰለመ ።

በአጥቂና ፡ በተጠቂ ፡ ጊዜ ፡ በሰጠውና ፡ በጕደለበት ፡ መካከል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሲፈጸም ፡ እንደኖረው ፡ ወደፊትም ፡ እንደሚኖረው ፡ አጥቂውና ፡ ጊዜ ፡ የሰጠው ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ ከድል ፡ ወደ ፡ ድል ፡ እየተረማመደ ፡ የደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ይፋትን ፡ ሸዋን ፡ ደዋሮን ፡ ፈጠጋርን ፡ . . . በሥልጣኑ ፡ ውስጥ ፡ አደረገ ። የንጉሡን ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ግማሾቹን ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ በመግደል ፡ የቀሩትንም ፡ እየተላላከ ፡ በማስገባት ፡ የጠላቱን ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድን ግልን ፡ ጦር ፡ እያላላ ፡ የራሱን ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ አደረጀ ፡ የራሳቸው ፡ እየጐደለ ፡ ሲሄድ ፡ የርሱ ፡ እየሞላ ፡ ሄደ ።

ቢሆንም ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በየቀኑ ፡ የጦር ፡ አለ ቃቸውን ፡ መሞት ፡ የሠራዊታቸውን ፡ መሸነፍ ፡ ሲሰሙ ፡ እገሌ ፡ ከዳ ፡ እገሌ ፡ ሞተ ፡ እየተባለ ፡ በየቀኑ ፡ የሚደርሳቸው ፡ አሳዛኝ ፡ ወሬ ፡ ጨርሶ ፡ ተስፋ ፡ ሊያስቆርጣቸው ፡ አልቻለም ። ይኸም ፡ ከሆነ ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ከረዳው ፡ ከጠላቴ ፡ ጋር ፡ ልታረቅ ፡ ልስማማው ፡ የሚሉ ፡ ስሜት ፡ በአሳባቸው ፡ አልመጣም ። በሸዋና ፡ በይፋት ፡ እንራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ እን ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ቢሞቱ ፡ አውራይ ፡ አትማንም ፡ ከድቶ ፡ ቢገባ ፡ በወሎ ፡ በአማራ ፡ ሳይንት ፡ በትግሬ ፡ እንደነ ፡ ተስፋ ፡ ልዑል ፡ ያለ ፡ ተዋጊ ፡ ጦር ፡ አላቸው ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የመሸነፍ ፡ አደጋ ፡ እየተከታተለ ፡ ከደረሰባቸው ፡ ከጦር ፡ ሠራዊታቸውም ፡ አብዛኛው ፡ ከአለቀና ፡ ከተበታተነባ ቸው ፡ በኋላ ፡ ለርሳቸው ፡ የቀራቸው ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንት ከዚያ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ መከላከል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በዚሁ ፡ መከላከል ፡ የግራኝ ሥልጣን በተስፋፋበት ፡ በደቡብ አገር ፡ የወገንና ፡ የሃይማኖት ፡ ፍቅር ፡ የሥግንነትና ፡ የአርበኛነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ሹማምንት ፡ የባሌው ፡ አዝማች ፡ አዳሉ ፡ የዋጅ ፡ ዮናዳብ ፤ የደብረ ፡ ብርሃኑ ፡ አዝማች ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ንጉሡ አገሩን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ የግራኝ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ኤሚሮቹ ፡ በሹመት ፡ ተደላድለው ፡ በያዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በጅምላ ፡ ወደነሱ ፡ እየገባ ፡ በሚሰልምበት ፡ ጊዜ ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ምን ፡ በመሰለ ፡ ጉብዝና ፡ እንደ ፡ ተቋቋሙት ፡ ወደ ፊት ፡ እንመለከታለን ። አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አድርገን ፡ የንጉሡን ፡ ጉዞ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ አማራ ፤ የግራኝን ፡ እየተከታተለ ፡ መዋጋት ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመልከት ።

## ም ዕ ራ ፍ ፳፩ ።

**አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡ ሄደው ፡ እንደተቀመጡ ፡ ግራኝ ፡ እስከ ፡ ወሲል ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ተዋግቶ ፡ እንዳሸነፋቸው ።**

ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ተዋግቶ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዋጅ ኢተባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ነበሩ ። ይህ ፡ አገር ፡ በዳሞትና ፡ በሸዋ ፡ መካከል ፡ ወደሰሜን ፡ ግድም ፡ የሚገኝ ፡ አገር ፡ ይመስላል ። ትክክለኛ ፡ ስሙንና ፡ ሥፍራውን ፡ ከዛሬው ፡ ጋር ፡ አገናኝቼ ፡ ለማጣራት ፡ አልቻልኩም ። ስለዚህ ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ ጦራቸው ፡ ከተሸነፈ ፡ በኋላ ፡ ከዳሞት ፡ ወደ ዚሁ ፡ አገር ፡ በተዘዋወሩበት ፡ ጊዜ ፡ የራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድን ፡ ሞት ፡ ሰምተው ፡ ማዘናቸውን ፡ ከዚያም ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡ መጓዛቸውን ፡ ከአረብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍ ፡ ትርጉሙን ፡ እንመልከት ።

«ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ንጉሡ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ በዋጅ ፡ አገር ፡ ክረምቱን ፡ ሁሉ ፡ አሳለፈ ። በዚሁም ፡ አገር ፡ ሳለ ፡ የወሰን ፡ ሰገድን ፡ ሞት ፡ በሰማ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ተሰማው ። ከዚያ ፡ የጦር ፡ ሹማምንቱን ፤ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ አገልጋዮቹን ፡ ሰበሰበና ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ። እናንተስ ፡ ምን ፡ ትመክሩኛላችሁ ፤ የትኛውስ ፡ አገር ፡ ይቀበለናል ?» ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። የዚህኑ ፡ ነገር ፡ እያወጡ ፡ እያወረዱ ፡ ሲመካከሩ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡፡ ያባቶቻችን ፡ ያያቶቻችን ፡ የነገሥታቱ ፡ መደበኛ ፡ ሥፍራ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡ ሄደን ፡ በዚያ ፡ እንቀመጥ ። እስላሞቹ ፡ እስከሁን ፡ ድል ፡ የመቱትን ፡ አገር ፡ እንተውላቸው ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ቤተ አምሐራ ሆነን ፡ በር ፡ በሩን ፡ ይዘን ፡ ከእስላሞቹ ፤ ጋር ፡ እየተዋጋን ፡ እንሙት» ፡ ይኸን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሹማምንቱ» ፡ ንጉሥ ሆይ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ እዚያ ፡ ሆነን ፡ እየተዋጋን ፡ እፊትህ እንሞታለን» አሉት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በክረምቱ ፡ ወራት ፡ ሳያርፍ ፩ ወር ፡ ተጉዞ ፡ ቤተ ፡ አምሐራ ፡ ደረሰ ። ይኸም ፡ አገር ፡ ሰፊ ተራራማ ፡ መንገዱ ፡ ጠባብ ፡ ነው ፡

ከተማው ፡ የነገሥታት ፡ መቀመጫ ፡ ነው ። ከዓባዊ ፡ (ዓባይ) ፡ ዠምሮ ፡ እስከ አንጎት ፡ እስከ ፡ ሐይቅ ፡ ድረስ ፡ ኻያ ፡ ቀን ፡ የሚያስኼደው ፡ አገር ፡ በተራራ የተከበበ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አገር አንዱ ፡ በወላቃይ ፡ (ወልቃይት?) አንዱ ፡ በአኪ ፡ አፋጊ ፡ አንዱ ፡ በመንዝ ፡ አንዱ ፡ በማያት ፡ አንዱ ፡ በግድም ፡ ፭ በር ፡ አለው ። ከነዚህም ፡ ተከላከል ፡ በዚህ ፡ በር ፡ ማንም ፡ መጥቶ ፡ አያውቅም ፡ ብሎ የማያትን ፡ በር ፡ ለአማቹ ፡ ለደገልሃን ፡ ሰጠው ። እርሱም ፡ የግድምን ፡ አጋ ማሽ ፡ የትግሬን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ በመንገዱና ፡ በተራራው ፡ በላይ ፡ በኩል ፡ በመ ንገዱና ፡ በበሩ ፡ መከከል ፡ የሚያስፈራ ፡ ጉድጓድ ፡ አስቆፈረ ።

፪ኛ የመንዝን ፡ በር ለራስ ፡ ባያንች ፡ ሰጠው ፡ እርሱም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ጉድጓድ ፡ አስቆፈረ ።

የአኪ ፡ አፋኪን ፡ በር ፡ ግን ፡ ለመከላከል ፡ ስድስት ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ስለ ሚበቃ ፡ እንደዚሁ ፡ ተወው ። ለወልቃይ ፡ በር ፡ ዳሀረጐት ፡ (ዳሀር ፡ ኀይታ)ለሚ ባለው ፡ ሰጠው ።

በዚህ ፡ ቤተ ፡ አምሐራ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ በሀበሻ ፡ ምሳሌ ፡ የሌላት አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለች ። እርሷንም ፡ ያሠራት ፡ የወናግ ፡ ሰገድ አባት ፡ ንጉሡ ፡ ናዖድ ፡ ነው ። የርሷ ፡ ሥራና ፡ ጌጧ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ፈጀበ ትና ፡ ሳያስጨርስ ፡ እርሱ ፡ ስለሞተ ፡ ልጁ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ከአባቱ ፡ አስበ ልጦ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ አሠርቶ ፡ አስጨረሳት ። ሁለመናዋ ፡ በወርቅ የተለበጠ ፡ ስለሆነ ፡ እንደ እሳት ፡ ታንጸባርቃለች ። በውስጡ ፡ ያለው ፡ ጻሕል ፡ ሰንና ፡ ብርት ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ነው ። ስፋቷ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ጐኗ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ቁመቷ ፡ ግን ፡ ከመቶ ፡ ሃምሣ ፡ ክንድ ፡ ይበልጣል ፡ ሁለመናዋ ፡ በጌጠኛ ፡ እንጨትና ፡ ደንጊያ ፡ በወርቅና ፡ በከበረ ፡ ደንጊያ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው ስሟም ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ቋንቋ ፡ መካነ ፡ ሥላሴ ፡ ትባላለች ፡ ትርጓሜውም ፡ የሦስቱ ፡ አማልክት ፡ መቀመጫ ፡ የሆነ . . . . ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ አም ላክ ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደላይ ፡ ነው ፡ ያለው ፡ ራሱ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ (ዋሕድ) ፡ የማይወለድ ፡ ያልተወለደ ፡ እኵያም ፡ የሌለው ፡ ነው ።

በዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የአድ ማስ ፡ (በእደ ፡ ማርያም ) ፡ ልጅ ፡ የናዖድ ፡ መቃብር ፡ አለ ። ከዚያም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ያለፉ ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩት ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲ ያናት ፡ አሉ ፡ ቢሆንም ፡ እንደዚች ፡ (እንደ ፡ መካነ ፡ ሥላሴ) ፡ አይሆኑም ።

ንጉሡ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ጦሩን ፡ በየበሩ ፡ ከደለደለ ፡ ወዲህ ፡ ወደዚች ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ ውስጧን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተመለከተና ፡ እስ ላሞች ፡ ይችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የነገሥታት ፡ መቀመጫ ፡ የሆነችውን ፡ ሊያቃጥሏት ፡ ይፈልጋሉ ,, ብሎ ፡ ቢናገር ፡ ሹማምንቱ ፡ "ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እስላሞች ፡ መጥተው ፡ ይችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያቃጥላሉ ፡ ብለህ ፡ አት ጨነቅ ፡ ስለርሷ ፡ እየተዋጋን ፡ እንሞትላታለን ፡ «አሉት ፡ እርሱም ፡ እንደ

ዚህ ፡ ከቆረጣችሁ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ በራችሁን ፡ ተጠንቅቃችሁ ፡ ጠብቁ ፡ ብሏ
ቸው ፡ እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ በየክፍላቸው ፡ ተለያይተው ፡ ሄዱ ። ንጉ
ሡም ፡ ወደወሲል ፡ ሄዶ ፡ በሩን ፡ ይዞ ፡ ተቀመጠ ።

ይማም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጎይታ ፡ ኑርን ፡ ልኮ ፡ በግድም ፡ ውስጥ ፡ (ቂሳያህ) ያላቸውን ፡ የጥንት ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቃጠለ ፡ በውስጧም ፡ ሺ ፡ መነኮሳት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ ይማምና ፡ አብጃድ ፡ ወደቂሳያህ ፡ (ግድም) ፡ ሄዱ ፡ ከክርስቲያኖችም ፡ ወገን ፡ ወሰን ፡ ዡን ፡ የሚባል ፡ ፭፻ ፡ የእግረኛ ፡ ጦር ፡ (ባለነጭ ፡ ጋሻ) ፡ የሚባሉትን ፡ እንደያዘ ፡ ወደይማም ፡ ገብተው ፡ ሰለሙ ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ንጉሡ ፡ አክብሮ ፡ ያስቀመጠው ፡ እስላም ፡ በአርሹናህ ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ እስላም ፡ ሆኜ ፡ ንጉሡን ፡ በማግልገሌ ፡ እንዳይቀጣኝ ፡ እፈራለሁና ፡ ከይማም ፡ ዘንድ ፡ ለሕይወቴ ፡ መረጋገጫ ፡ አሰጠኝ ፡ (አማልደኝ) ፡ «የሚል ፡ ቃል ፡ አሲዞ ፡ ለሕግ ፡ አዋቂው ፡ ለአቡበከር ፡ ኤል ፡ አር ሹኒ ፡ ላከ ፡ አቡበከርም ፡ ወደይማም ፡ ገብቶ ፡ ተነጋግሮ ፡ ቃል ፡ ተቀበለለት ፡ ይማምም ፡ ያገሩን ፡ ሰው ፡ ከቢር ፡ ኑርን ፡ ላከለትና ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ይህ ሻፉ ፡ የሚባል ፡ እስላም ፡ ወደይማም ፡ መጣና ፡ ለንጉሡ ፡ ይገቡ ፡ የነበሩትን ፡ የሚ ያማምሩ ፡ በቅሎችና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለይማም ፡ አቀረበለት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ንጉሡ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ በቤተ ፡ አምሐራ ፡ ነው ፡ ያለው ፡ በዚያ ፡ ጦሩን ፡ ከፋፍሎ ፡ በር ፡ በሩን ፡ ይዞ ፡ ተቀምጧል ። ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ የወሲልን ፡ በር ፡ ይዞ ። የማያትን ፡ ለአማቹ ፡ ለራስ ፡ ደጋልሃን ፡ ሰጥቶታል ። ደጋልሃንም ፡ ወደኔ እንድትመጣ ፡ ብሎ ፡ ልኰብኝ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የናንተን ፡ ወደዚህ ፡ ወደማያህ ፡ (ግድም) ፡ መምጣታችሁን ፡ ስለሰማሁ ፡ ወደዚያ ፡ መሄዴን ፡ ትቼ ፡ ወደዚህ ፡ መጣሁ » ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

« በኛና ፡ ንጉሡ ፡ ባለበት ፡ መካከል ፡ ርቀቱ ፡ ስንት ፡ ይሆናል » ፡ ብሎ ቢጠይቀውም ፡ ንጉሡ ፡ ያለበት ፡ ፯ ፡ ቀን ፤ ደጋልሃን ፡ ያለበት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ያስሄዳል ። ራስ ፡ ባንያት ፡ ያለበት ፡ ቀን ፡ ይኸን ፡ አስፈሪ ፡ ተራራ ፡ አልፎ ፡ በንድ ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ ይደረሳል» ፡ ሲል ፡ መለሰ ። ይማም ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሰምቶ ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ “አገሩን ፡ ትተህ ፡ በፍጥነት ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ ታስፈልገኛለህ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኤሚር ፡ አሊ ፡ ላከ ፡ መላክተኛው ፡ ግን ፡ በመን ገድ ፡ ሳለ ፡ ተገደለ ። ይማም ፡ የመላክተኛውን ፡ መሞት ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ቀጥሎ ፡ አብሳማ ፡ ኑርን ፡ ጦር ፡ ጨምረህ ፡ ላክልኝ ፡ ብሎ ፡ ለወዚር ፡ አዶሌ ፡ ዱብዳቤ ፡ ጻፈለት ፡ እርሱም ፡ አብሳማ ፡ ኑርን ፡ ከ፳ ፡ ፈረሰኞች ፡ ጋር ፡ አድ ርጎ ፡ ዱብዳቤ ፡ ጨምሮ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ላከ ። በዱብዳቤው ፡ ላሊበላ ፡ (ፊጠ ጋር ፤ ውስጥ) ፡ መሆኑን ፡ ገለጸለት ።

አብሳማ ፡ ኑር ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ አደረገ ለት ። ቀጥሎ ፡ የመላክተኛውን ፡ እመንገድ ፡ መሞት ፡ አያውቅም ፡ ነበርና ፡ ኤሚር ፡ ኑር ፡ እንዲመጣ ፡ ልኬበት ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሆነውን ፡ አላውቅም

መልስም ፡ አላገኘሁም ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ወዚር ፡ አዶሌ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ብዙውን ፡ ሠራዊት ፡ ከፍሎ ፡ እንዲልክልኝ ፡ ልጻፍለት ፡ ብሎ ፡ እን ደዚህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ላከበት ።

፡፡በመሐሪውና ፡ በይቅር ፡ ባዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ለዓለም ፡ ጌታ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፤ ሰላምና ፡ ደህንነትም ፡ ለጌታችን ፡ ለመሐመድና ፡ ለቤተ ፡ ስቡ ፡ ይስጠው ።

የተላከ ፡ ከአህመድ ፡ ቤት ፡ ኢብራሂም ፡ የእስላሞች ፡ ይማም ፡ ስለሃይማኖቱ ፡ የሚዋጋ ፡ ይድረስ ፡ ከወዚር ፡ አዶሌ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለሁ ፡ ከርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ (አምላክ) ፡ የለምና ፡ ቡራኬና ፡ ሰላም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለነቢዩ ፡ ለመሐመድ ፡ ይሰጠው ።

አሁን ፡ ያለነው ፡ ግድም ፡ ውስጥ ፡ ከሳያህ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ፡ አዶሌ ሆይ ። ንጉሡ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ወደቤተ ፡ ማርያም ፡ ሄዶ ፡ ጦሩን ፡ ከፋፍሎ ፡ በሩንና ፡ መንገዱን ፡ ዘግቶ ፡ ይጠብቀናል ። ወደኤሚር ፡ አሊ ፡ ወደኔ ፡ እንዲመጣ ። ትእ ዛዝ ፡ ጽፌለት ፡ ነበር ። መልስም ፡ አላከብኝ ፡ ያለበትንም ፡ ሥፍራ ፡ አላውቅም ። ከኔ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ወታደር ፡ ቲንሽ ፡ ነውና ፡ ኤሚር ፡ አቡበከርን ፡ ኤሚር ፡ ሙጃሂ ድን ፡ ፬፻ ፈረሰኛ ፡ አድርገህ ፡ የእግረኛ ፡ ጦርና ፡ የባሕርን ፡ ተዋጊዎች ፡ (ከዓረብ ፡ አገር ፡ የመጡትን ፡ መድፈኞች ፡ ) እንድትልክልኝ ፡ ይሁን ፤ ላንተና ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ላሉት ፡ እስላሞች ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ ፡፡

መልእክተኛው ፡ ያለዕረፍት ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ተጉዞ ፡ በአስረኛው ፡ ቀን ዘቃላ ፡ (ዝቋላ) ፡ ደርሶ ፡ ደብዳቤውን ፡ ለወዚር አዶሌ ሰጠ ። እርሱም ፡ እስላ ሞቹን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ደብዳቤውን ፡ አነበበላቸው ፡ ከዚያ ፡ ፪፻ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፳፻ ፡ እግረኛ ፡ የባሕር ፡ ወታደር ፡ ሌላም ፡ ቍጥራቸው ፡ የበረከተ ፡ ነገድ ፡ ጨምሮ ፡ አቡበከርንና ፡ ሙጃሂድን ፤ የበላይ ፡ አድርጎ . . . . . ወደይማም ፡ ላካቸው ።

ይማም ፡ እነርሱን ፡ ሲጠብቅ ፡ በከሣያህ ፡ ፩ ፡ ወር ፡ ከ፲ ፡ ቀን ፡ የተበ ተነውን ፤ ወታደሩን ፡ እየሰበሰበ ፡ ተቀመጠ ። በመዠመሪያ ፡ ሻምሱ ፡ ፲፰ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሺ ፡ እግረኛ ፡ ይዞ ደረሰ ። ፡ ኤሚር ፡ አሊ ፡ (ፋራቃሃም) ፡ ግን ፡ በተጉ ለት ፡ በወግዳ ፡ በሙገር ፡ እየተዘዋወረ ፡ ቆይቶ ፡ በኋላ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሆኖ ፡ የይማምን ፡ ወሬ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ ሰው ፡ ላከ ፡ ጦብያም ፡ ደር ሰው ፡ የገራድ ፡ አህምሹን ፡ ምልክት ፡ አግኝተው ፡ ከተነጋገሩ ፡ በኋላ . . . . . አሊ ፡ ደብረ ብርሃን ፡ መሆኑን ፡ ገልጾላቸው ፡ መልሶ ፡ ወደደብረ ፡ ብርሃን ፡ «፫ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ መላክተኛ ፡ ልኰብህ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፫ ፡ ጊዜም ፡ መላ ክተኞቹን ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ገደሏቸው ። አሁንም ፡ ይማም ፡ ከሣያህ ፡ ነውና ፤ ያለው ፡ ይህ ፡ መልክት ፡ እንደደረሰህ ፡ በቶሎ ፡ ወደርሱ ፡ እንድትሄድ ፡ ይፈልግሃል» የሚል ፡ መልክት ፡ አሲዞ ፡ ላካቸው ።

ይኸን ፡ መልክት ፡ ሲሰማ ፡ ይማምን ፡ ያለጦር ፡ ብቻውን ፡ በመተዌ ፡ አኖ ፍቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ፍርሃትና ፡ ሥጋት ፡ አደረበት ፡ ከዚያ ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ተነ

ሥቶ ፡ በ፲ረኛው ፡ ቀን ደረሰ ፡ ... "ይማም ፡ ወታደሬን ፡ ወስደህ ፡ ያደ
ረግኸውን ፡ አደረግህ ፡ እስቲ ፡ የቱን ፡ አገር ፡ አቀናህ" ፡ ብሎ ፡ ወቀሰው ፡ እር
ሱም ፡ «ጌታዬ ፡ አጥፍቻለሁ» ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ ...... ከዚህ ፡ ኤሚር አቡበከርና ፡
ጓደኛው ፡ ጦራቸውን ፡ እንደያዙ ፡ በሰልፍ ፡ ገብተው ፡ ከይማም ፡ ተገናኙ ፡ ይማ
ምም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ አክብሮ በደስታ ፡ ተቀበላቸው ፡ ...... ከዚያ ፡ የንጉ
ሡን ፡ ነገር ፡ እንሥተው ፡ ሲነጋገሩ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ የቀሩትንም ፡
ሰብስቦ ፡ "አሁን ይኸው ፡ ጦራችን ፡ ተሰብስቧል ፡ እንግዲህ ፡ ስለቤተ ፡ አም
ሐራ ፡ ምክር ፡ አምጡ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ንጉሡን ፡ ለመውጋት ፡ ቆርጫለሁ ፡ "አላቸው ፡
ከቢር ፡ መሐመድ ፡ "ሁላችንም ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡ ለመሔድ ተዘጋጅተናል ፡
ነገር ፡ ግን ፡ በኋላችን ፡ ያለው ፡ የሾ ፡ ገራህ አገር ፡ እስላም ፡ ከሆነ ፡ ጥቂት ፡
ጊዜ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ሳንትው ፡ ሁላችንም ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡ የኼድን ፡ እን
ደሆነ ፡ ወዲያው ፡ እስላምነታቸውን ፡ ይተዋሉ ። አሁንም ፡ ወይኔ ፡ ወይም ፡
ሻምሱ ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ እንድንመለስ ፡ ያስፈልጋል" ፡ ሲል ። "እውነትህ ፡
ነው ፡ አሁንም ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ የዞሩትን ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡
ይዘህ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ተመልሰህ ፡ ጠብቅ ፡ ከአገራችን ፡ ከመጡት ፡ የጥንት ፡
እስላሞች ፡ አንድም ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አይሂድ" ፡ ብሎ ፡ መርቆ ፡ ሰደደው ።
ከቢር ፡ መሐመድ ፡ ወደሾጃራህ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ፩ ፡ ሰው ፡ ወደርሱ ፡ መጥቶ ፡
ሻምሱ ፡ አቃጠለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ ንጉሥ ፡ እስክንድር ፡ አስቀም
ጦት ፡ የነበረ ፡ ወርቅ ፡ አለ ፡ መንገዱንም ፡ እነዚህ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ የተሰለፉት ፡ ሰዎች፡
ያውቃሉ ፡ ብሎ ፡ በእጁ ፡ አመለከተው ፡ ከቢር ፡ መሐመድም ፡ እነዚህኑ ፡
ሰዎች ፡ ይዞ ፡ እያጉላላ ፡ ፲፪ ፡ ጠፍጣፋ ፡ ወርቅ ፡ ተቀበላቸው ፡ ቀጥሎም ፡ "ሌላስ
ያለ ፡ የምታውቀው ፡ የለህምን ፡ ብሎ ፡ እንደገና ፡ ቢጠይቀው ፡ አዎን ፡ ፺፱ ፡
የወርቅ ፡ ጥፍጥፍ ፡ እያንዳንዱ ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ የሚከብዱ ፡ ሁለት ፡ ትልልቅ ፡
ጥምዝ ፡ ወርቅ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ከቢር ፡ መሐመድም እነዚህኑ ፡ ሰዎች ፡ የቀረውንም ፡ ወርቅ ፡ አምጡ ፡
ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡ እነርሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሲመካከሩ ፡ "ንጉሥ ፡ እስክንድር ፡
ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰጡትን ፡ ይኸን ፡ ወርቅ ፡ አስረክበን ፡ በኋላ ፡ እስላሞቹ ፡
ወደ ፡ አገራቸው ፡ የተመለሱ ፡ ወይም ፡ እዚሁ ፡ አገር ፡ ሞተው ፡ ያለቁ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ንጉሡ ፡ አምጡ ፡ ብለው ፡ ይቀጡናል ፡ ስለዚህ ፡ ይኸን ፡ ሰው ፡ (ከቢሩን)
ለመግደል ፡ ብልሃት ፡ እንፍጠር ፡ በዚህም ፡ ነገር ፡ ጓደኞቻችን ፡ እንዲረዱን ፡ እን
ላክባቸው ፡ ተባብለው ፡ ተስማሙ ፡ .... ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ ለወገ
ኖቻቸው ፡ ልከው ፡ በጫካ ፡ ያሉትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ጠቀሷቸው ፡ እነሱም ፡
ከተራራ ፡ ወርደው ፡ ሲመጡ ፡ ታዩ ፡ ከቢር ፡ መሐመድም ፡ እንዚህ ፡ ምንድና
ቸው ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ እንተን ፡ ሊወጉ ፡ የሚመጡ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ፡
ብለው ፡ ወገኖቹ ፡ ነገሩት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈረሱን ፡ አስጭኖ ፡ ወታደሮቹን ፡
ይዞ ፡ ወደነዚያ ፡ ሄዶ ፡ ሲዋጋ ፡ .... ሞተ ።

ይማም ፡ ግን ፡ ከከሳያህ ፡ ተነሥቶ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጋንቡራ ፡ ደርሶ ፡ ሠፈረ ፡ ከዚያም ተነሥቶ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ማያት ፡ ደርሶ ፡ ከዚያም ፡ ደጋልሃን ፡ ወደሚጠብቀው ፡ በር ፡ ተጠጋ ። ደጋልሃንም ፡ እስላሞቹን ፡ ሲያይ ፡ ጦሩን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ አስለፈ ፡ መለከቱንም ፡ አስነፋ ፡ „ወርዳችሁ ፡ ተዋጉ» ፡ ብሎ ፡ መርዝ ፡ ባለበት ፡ ቀስት ፡ የሚዋጉትን ፡ ወታደሮቹን ፡ አስቀደማቸው ። ይማም ፡ ወደተራራው ፡ ተጠግቶ ፡ አንዲት ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ቆሞ ፡ እግረኛን ፡ ብቻ ፡ ሊያስሄድ ፡ የሚችለው ፡ መንገድ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ እያየ ፡ ይደነቅ ፡ ነበር ፡ በተራራውም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የእህል ፡ አዝመራ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ሳያውቅ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ የእስላም ፡ የእግረኛ ፡ ወታደር ፡ ወደተራራው ፡ መውጣት ፡ ዠምሮ ፡ ጦርነቱን ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ዠመረ ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ በቀስት ፡ መዋጋት ፡ የሚችሉ ፡ የዓረብ ፡ ወታደሮች ፡ እነአብደሳሌም . . . . . . ነበሩ ፡ ወዲያውም ፡ እስላሞቹም ፡ ክርስቲያኖቹም ፡ ቀስት ፡ እየተወራወሩ ፡ የቀስት ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረ ። ወዲያው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተጠጋጉ ፡ በመጨረሻ ፡ ተደበላልቀው ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ፡ አብድ ፡ ኢስ ፡ ሳሌምና ፡ ጓደኛው ፡ ኤል ፡ ሐጅ ፡ ከጓደኞቻቸው ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ በዠግንነት ፡ ተዋጉ . . . . ከእስላሞቹ ፡ ውስጥ ፡ አቡን ፡ የሚባለው ፡ ከላይ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የለቀቁት ፡ የድንጋይ ፡ ናዳ ፡ ራሱን ፡ ፈጥፍጦ ፡ ገደለው . . . .

ይማም ፡ እሥር ፡ ሆኖ ፡ ወደተራራው ፡ ሲመለከት ፡ እስላሞቹ ፡ አጉል ፡ ቦታ ፡ ሆነው ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ሲዋጉ ፡ ተመለከተና ፡ ማን ፡ ተዋጉ ፡ አላቸው ፡ ብሎ ፡ ተቆጥቶ ፡ አስመለሳቸው ። እነሱም ፡ የአቡንን ፡ ሬሳ ፡ ተሸክመው ፡ ተመለሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ወደሠፈር ፡ ተመልሶ ፡ አውራይ ፡ አትማንና ፡ ሌሎቹንም ፡ መንገድ ፡ መሪዎች ፡ አናንያን ፤ ሃይቢን ፤ አይበስ ፡ ለሐዬ ፡ ከሐዲውን ፡ ሰበሰበና ፡ ምክር ፡ እንዲሰጡት ፡ ጠየቃቸው ፡ ከነዚህ ፡ መካከል ፡ አይበስ ፡ ለሐዬ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። "እንግዲህ ፡ ተራራውና ፡ አስቸጋሪው ፡ መንገድ ፡ እነሆ ፡ ይኸው ፡ በፊታችን ፡ ነው ። ፈረስ ፡ የሚያስሄድ ፡ መንገድ ፡ የለም ። በእግራችን ፡ እንውጣ ፡ ብትሉም ፡ አይቻልም ፡ ወጥታችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አዝማቹን ፡ (ደልገሃንን) ፡ ብታሸንፉትም ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ከቤተ ፡ አምሐራ ፡ ወዲህ ፡ አስቸጋሪ መንገድና ፡ ወንዝ ፡ አለና ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡ መሄድ ፡ አትችሉም ። እንደኔ ፡ አሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ደጋልሃን ፡ የያዘውን ፡ ይኸን ፡ ተራራ ፡ መውጋት ፡ ይቅርና ፡ ንጉሡ ፡ ወደአሉበት ፡ ወደወሲል ፡ በር ፡ ሂዱ ። በዚያም ፡ ሂዳችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ያሸነፋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ የቤተ ፡ ማርያምን ፡ መንገድ ፡ የሚዘጋባችሁ ፡ የለም ። ንጉሡም ፡ ከተሸነፉ ፡ ወዲያ ፡ ደጋልሃን ፡ ብቻውን ፡ እዚህ ፡ ቢቀመጥ ፡ የሚጠቅመው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ስለዚህ ፡ ይኸን ፡ የምሰጣችሁን ፡ ምክር ፡ ብትቀበሉ ፡ ይሻላል ።

እርሱ ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ አናንያ ፡ «አይበስ ፡ ለሐዬ ፡ ይኸን ፡ ምክር ፡ መናገሩ ፡ እውነት ፡ አለው ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ተራራ ፡ ፈረስ ፡ የሚያስሔድ ፡

ምንም ፡ መንገድ ፡ የለም ፡ ንጉሡ ፡ ያሉበት ፡ የወሲል ፡ ተራራ ፡ ፈረስ ፡ ሊወ
ጣበት ፡ ይችላል ፡ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ ለጦር ፡
አለቆቹ ፡ ለነገራድ ፡ አሕሙሽ ፡ ለነኤሚር ፡ ዘሐርቡይ ፡ ለነኤሚር ፡ አቡበከር ፡
ቀጢን ፡ የአይበስ ፡ ለሐዜንና ፡ የአናንያን ፡ ምክር ፡ አካፈላቸው ። እነሱም ፡
፡፡እውነት ፡ ነው ፡ ከራቱ ፡ ሦስቱን ፡ በር ፡ ከመውጋት ፡ አንዱን ፡ (ንጉሡ ፡
ያሉበትን) ፡ እንውጋ ፡ ፡፡ሲሉ ሁሉም ፡ በዚሁ ፡ ተስማሙ ።

በዚሁም ፡ ሌሊት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እየወረዱ ፡ ሱማሌዎች ፡ ባሉበት ፡ ወገን ፡
መውጋት ፡ ዠምረው ፡ ነበር ። ግን ፡ ሹሙ ፡ ማታን ፡ በፈረሱ ፡
ሆኖ ፡ እየወጋ ፡ ወደተራራቸው ፡ መለሳቸው ። ክርስቲያኖቹ ፡ ወደተራራው ፡ ከተ
መለሱ ፡ በኋላ ፡ ደጋልሃን ፡ ለንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ፡
፡፡ይማም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ ተዋጋን ፡ ፻፶ ፡ የእግረኛ ፡ ወታደሩን ፡
ገደልሁበት ፡ ፴ ፡ ፈረሶቹን ፡ ማረክሁ ፡ እስላሞቹም ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ ተመል
ሰው ፡ ቢወርዱ ፡ ሌሊቱን ፡ የትግሬን ፡ ቀስተኛ ፡ ወታደር ፡ ልኬ ፡ከነርሱ ፡
ጋር ፡ ተዋግተው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ፈጇባቸው ። ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ እስላሞቹ ፡
ወደፈጠጋር ፡ ይሸሻሉ ፡ እንጂ ፡ አይመክቱም፡፡ ፡ ይኸን ፡ መልእክት ፡ ሁለት ፡
ሰዎች ፡ በግሥጋሤ ፡ ወስደው ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጡት ፡ ንጉሡ ፡ የተጻፈውን ፡ ተመ
ልክቶ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ። ዘውዱንም ፡ ደፍቶ ፡ እዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ የጦር ፡ አለቆቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ይኸንኑ ፡ ገለጸላቸው ፡ ነጋሪትና ፡ መለከት ፡
እየተነፋ ፡ አለቆችም ፡ ፡፡መስቀልና ፡ (ጌታችን) ፡ እመቤታችን ፡ በጠላቶችህ ፡ ላይ ፡
ድልን ፡ ሰጡህ፡፡ ፡ እያሉ ፡ አመሰገኑት ፡ ንጉሡም፡፡ ፡ አማቹ ፡ ደጋልሃን ፡ የጠበ
ቀሁትን ፡ (ድል) ፡ ፈጸመ፡፡ ፡ እያለ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ በደስታ ፡ ውለው ፡ አደሩ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ ነበር ። ይማም ፡ ያቺን ፡ (ለውጊያ) ፡
ሌሊት ፡ ከአሳለፈ ፡ በኋላ ፡ በማግስቱ ፡ ጦሩን ፡ ከፋፍሎ ፡ ኤሚር ፡ ዘሀርቡይን ፡
ፋራቃሃም ፡ አሊን ፡ አውራይ ፡ ሺሃብን ፡ አራውይ ፡ ኡመር ፡ ዲንን ፡ ገራድ ፡
አህሙሹን ፡ ጨምሮ ፡ የበላይ ፡ መሪ ፡ ወዚር ፡ ኑርን ፡ አድርጎ ፡ ፡፡እናንተ ፡ ከኋላ ፡
ሆናችሁ ፡ ደጋልሃን ፡ የመጣባችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ተዋጉት ፡ እኔ ፡ ከፊት ፡ ሆኜ ፡
እየመራሁ ፡ የሀበሻው ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ እንጓዛለን ፡ ፡፡ብሎ ፡ ነግሯቸው ፡
እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ጉዞው ፡ ተዠመረ ። አናንያ ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ ይመራ ፡
ነበር ። አውራይ ፡ ኦትማን ፡ ግን ፡ ከይማም ፡ ጋር ፡ ሳይለይ ፡ አብሮ ፡ ይጓዝ ፡
ነበር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደጋልሃንም ፡ ያለበትን ፡ ሥፍራ ፡ ትቶ ፡ በመጥፎ ፡ መን
ገድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ጉዞውን ፡ ዠምሮ ፡ ሳለ ፡ በመካከሉ ፡ ወንድሙ ፡ ሐንታዝ ፡
(አንያስ) ፡ የእስላሞቹን ፡ ከተራራው ፡ ሥር ፡ መነሣታቸውን ፡ ሳያውቅ ፡ ወታደሮ
ቹን ፡ ይዞ ፡ ወደደጋልሃን ፡ ለመሄድ ፡ ሲጓዝ ፡ በድንገት ፡ ከእስላሞቹ ፡ ግንባር ፡
ቀደም ፡ ጦር ፡ ከነአናንያ ፡ ተገናኘ ። እነአናንያም ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ከበው ፡ ከፈ
ረስና ፡ ከበቅሏቸው ፡ ጋር ፡ ማረኳቸው ። ሐንታዝ ፡ ግን ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡
ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ አመለጠ ። አናንያም ፡ የማረከውን ፡ ሁሉ ፡ አምጥቶ ፡

ለይማም ፡ ቢያቀርብ ፡ ይማም ፡ ሁሉንም ፡ ለአናንያ ፡ ጌታ ፡ ለአውራይ ፡ ኦስማን ፡ ተወለት ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፡ ለአናንያ ፡ መርቆ ፡ አስደሰተው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ ጎድማህ ፡ ውስጥ ፡ አብሸሉ ዘራፍ ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሠፈረ ፡ እኋላ ፡ ያለውም ፡ ጦር ፡ ሲመሽ ፡ እሠፈር ፡ ገባ ። ይማም ፡ መሪውን ፡ አናንያን ፡ ጠራና ፡ "ይህ ፡ ዛሬ ፡ ያለፍነው ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ምንው ፡ እንደዚህ ፡ ሆነ„ ፡ ቢለው ፡ የነገው ፡ ከዛሬው ፡ የባሰ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ቃዲያስ ፡ ምን ፡ ይሻለናል ፡ ቢለውም ፡ ጦሩን ፡ እሦስት ከፍሎ ፡ መንዝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰና ፡ በማግሥቱ ፡ ከጥበቱ ፡ የተነሣ ፡ ጦሩ ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ሲጓዝ ፡ አንድ ፡ ተራራ ፡ ይማም ፡ አይቶ ፡ "ይህ ፡ የማየው ፡ ተራራ ፡ ምንድነው ? ፡ ብሎ ፡ አናንያን ፡ ቢጠይቀው„ ፡ ንጉሡ ፡ አለበት ፡ የሚባለው ፡ የወሲል ፡ ተራራ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ "ብሎ ፡ መለሰለት ። ቃዲያስ ፡ አሁን ፡ ንጉሡ ፡ በዚያ ፡ ይኖር ፡ ይሆን ? ፡ „ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ እኔ ፡ እንዳንተው ፡ ወሬውን ፡ አብረን ፡ ሰማሁ ፡ እንጂ ፡ በተለይ ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በፈረስ ፡ ሄጀ ፡ ወሬ ፡ ተጠያይቄ ፡ አመጣልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ከአራት ፡ ፈረሰኞች ፡ ጋር ፡ እልፍ ፡ እንዳለ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ እረኞች ፡ አገኙዋቸው ፡ እረኞቹም ፡ "ከወዴት ፡ መጥታችኋል» ፡ ብለው ፡ እነ ፡ አናንያን ፡ ቢጠይቋቸው ፡ "እኛ ፡ የደጋልሃን ፡ ወታደሮች ፡ ነን ፡ አለቃችን ደብዳቤ ፡ ለንጉሡ ፡ አድርሱ ፡ ብሎን ፡ እንጓዛለን ፡ ንጉሡ ፡ ያሉበትን ፡ ታውቃላችሁን ፡ «አሏቸው ። እረኞቹም» ፡ አዎን ፡ እናውቃለን ፡ ንጉሡ ፡ ያሉት ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሀጉዋ ፡ (ሐጓ) ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ያሉት» ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስላሞቹ ፡ እረኞቹን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ አመጧቸው ፡ አናንያ ፡ ይኸው ፡ እነዚህ ፡ እረኞች ፡ ንጉሡ ፡ ያለው ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ብለውን ፡ ይዘን ፡ ወደናንተ ፡ አመጣናቸው ፡ ብሎ ፡ ለይማም ፡ ቢነግረው ፡ "ለክርስቲያኖቹ ፡ ሄደው ፡ ወሬ ፡ እንዳያነግሩ ፡ እነዚህን ፡ መግደል ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ አናንያ ፡ ግን ፡ ‹እነዚህ ፡ እኛ ፡ እስላሞች ፡ መሆናችንን ፡ በፍጹም ፡ የማያውቁ ፡ ባላገር ፡ ናቸው ፡ ይልቅስ ፡ የገደልናቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የመንደሩ ፡ ሕዝብ ፡ እዚህ ፡ መኖራችንን ፡ ያውቅና ፡ ወሬውን ፡ ለንጉሡ ፡ ያደርሳል ፡ ስላለ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ልቀቃቸው ፡ አለው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማምና ፡ ጦሩ ፡ እረኞቹ ፡ ባመለከቱበት ፡ አቅጣጫ ፡ ይጓዙ ፡ ገሥመር ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰው ፡ እመንገድ ፡ ስታገኙት ፡ በቋንቋው ፡ አነጋግሩት ፡ እንጂ ፡ እስላም ፡ መሆናችሁን ፡ ለማንም ፡ አትግለጹ ፡ ሰውም ፡ ሲጠይቃችሁ ፡ የደጋልሃን ፡ ወታደሮች ፡ ነን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እንሔዳለን ፡ በሉት ፡ ብሎ ፡ ለሠራዊቱ ፡ አስጠነቀቀ ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ የተተከለውን ፡ የንጉሥን ፡ ነጭ ፡ ድንኳን ፡ ተመለከቱ ። ከድንኳኑ ፡ ትልቅነት ፡ የተነሣ ፡ የሁለት ፡ ቀን ፡ ጕዳና ፡ ርቆ ፡ ለተመለከተው ፡ ሰው ፡ ይታያል ። እርዝማኔው ፡ ፳ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ቁመቱ ፡ ከ፱ ፡ ክንድ ፡ ይበልጣል ።

እስላሞቹ ፡ ይህ ፡ የሚታየው ፡ የንጉሡ ፡ ድንኳን ፡ መሆኑን ፡ በተረዱ ፡ ጊዜ ፡ እኋላ ፡ ያሉት ፡ የክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ እስኪጠጉ ፡ ድረስ ፡ እርምጃቸውን ፡ ቀን ሰው ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ ይጓዙ ፡ ዠመር ። ሰዎቹም ፡ የለበሱት ፡ የክርስቲያን ፡ ልብስ ነበር ፡ ይማም ፡ "አደራችሁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ በራሳችሁ ፡ ቋንቋ ፡ በኢል ጅጁ ፡ (የደጁ ፡ ቋንቋ ፡ ?) አነጋግሯቸው አለ ። ክርስቲያኖቹም ፡ ወደሥራቸው የሚጓዙ ፡ ነበሩ ፡ አጠገባቸው ፡ ያሉት ፡ እስላሞች ፡ መሆናቸውን ፡ አላወቁም ። እንዲያውም ፡ አንዲት ፡ ሴትዮ ፡ ደጋልሃን ፡ መስሏት ፡ ለይማም ፡ አቤቱታ ፡ አቀ ረበች ። ይማም ፡ እሬቱ ፡ አቅርበ ፡ በኤልጅጁ ፡ ቋንቋ ፡ ሊያነጋግራት ፡ ፈልጎ ሳለ ፡'ዕቃዋን ፡ መልሱላት ፡ ብሎ ፡ በእስላም ፡ ቋንቋ ፡ ስለተናገረ ፡ ንግግሩ ፡ ገባትና ፡ ቀስ ፡ ብላ ፡ ወደኋላዋ ፡ ተመልሳ ፡ ተቀምጣ ፡ "እነዚህማ ፡ እስላሞች ፡ ናቸው „ ትል ፡ ዠመር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እስላሞቹ ፡ የርሷን መረዳት ፡ ሳያጤኑ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠሉ ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ግማሹ ፡ ገበሬ ፡ ወደእርሻው ፡ የሚሄድ ፡ ግማሹ ፡ ልብሱን ፡ የሚያጥብ ፤ ግማሹ ፡ ወደ ንጉሥ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ዱቄት ፡ ጭኖ ፡ ግማሹ ፡ ላቤቱታ ፡ የሚወጣ ፡ ነበር ፡ በአጠገባቸው ፡ የሚጓዘው ፡ የእስላም ፡ ጦር ፡ መሆኑን ፡ ሳይረዱ ፡ እስከ ፡ ተራ ራው ፡ ጥግ ፡ ድረስ ፡ አብረው ፡ ተጉዘው ፡ በመጨረሻ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ አድር ርገው ፡ ወደከተማዩቱ ፡ ወደወሲል ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ ንጉሡም ፡ ጦሩም ፡ እስላሞቹን ፡ አሽንፈ ፡ ወደ ፡ ፈጠጋር ፡ አባረርኋቸው ፡ ብሎ ፡ ደጋልሃን ፡ በጻ ፈው ፡ እየተደሰቱ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ እንጅ ፡ የእስላሞቹን ፡ መጠጋት አል ጠረጠሩም ።

መሪው ፡ አናንያ ፡ ወደ ፡ ይማም ፡ ሂዶ ፡ ይኸውና ፡ እሥፍራው ፡ ደረስን ቢለው ፡ አሳብህን ፡ እስቲ ፤ ንገረኝ ፡ ብሎ ፡ መልሶ ፡ ጠየቀው ። አናንያም ፡ እን ደኔ ፡ አሳብ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የኋለኛው ፡ ጦር ፡ ጨርሶ ፡ እስኪደርስ ፡ እዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ እንደርና ፡ ሲነጋ ፡ ያለንን ፡ መድፍ ፡ ከፈረሰኞቻችን ፡ ፊት ፡ አስቀድመን ፡ የእግረኛው ፡ ጦር ፡ ከኋላ ፡ ሆኖ ፡ ተራራውን ፡ ወጥተን ፡ እንወጋቸዋለን ፡ እግ ዚአብሔርም ፡ ድሉን ይሰጠናል ፡ ብሎ ፡ ቢመልስ ፡ ይማም ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ (የቀድሞቹ) ፡ እስላም ፡ መሆናችንን ፡ አውቀዋል ፡ ወይስ ፡ የደጋልሃን ፡ ጦር ፡ ነው ፡ የመሰልናቸው ፡ ብሎ ፡ እንደገና ፡ ጠየቀው ፡ አናንያም ፡ የለም ፡ የደ ጋልሃን ፡ ጦር ፡ ነው ፡ የመሰልናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ እንግዲያውስ ፡ ካላወ ቁን ፡ ለምን ፡ እስከነገ ፡ እንጠብቃለን ፡ አሁኑኑ ፡ ተራራውን ፡ እንውጣ ፡ አለ ። አናንያ ፡ 'የእግረኛና ፡ የፈረሰኛው ፡ ጦር ፡ አልደረሰምና ፡ ብንጠብቅ ፡ አይሻልምን ። ቢል ፡ አሁን ፡ ያለነው ፡ ፴ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፶ ፡ እግረኛ ፡ ነን ፡ እም ነታችንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አድርገን ፡ ተራራውን ፡ መውጣት ፡ ብንዠምር ፡ እኋላም ፡ ያለው ፡ ጦራችን ፡ ይደርሳል ። እዚህ ፡ ያደርን ፡ እንደሆነ ፡ ሌሊቱን ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ይሰሙና ፡ መውጫ ፡ መንገዳችንን ፡ ይዙብናል ፡ ከዚያም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ከላይ ፡ የድንጋይ ፡ ናዳ ፡ ቢለቅብን ፡ ከኛ ፡ መድፍ ፡

የበለጠ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርግብን ፡ ይችላል ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ እንውጣ ፡ ብሎ ፡ ይማም ፡ ለመውጣት ፡ መቁረጡን ፡ ሲመለከት ፡ አናንያ ፡ እንግዲህ ፡ እኔም ፡ የምሰጠው ፡ አሳብ ፡ የለም ፡ ትእዛዝ ፡ መስጠት ፡ ያንተ ፡ ፋንታ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። በዚህ ፡ መካከል ፡ ኤሚር ፡ አቡበከርና ፡ በለው ፡ አብዶ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አናንያ ፡ እውነቱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢናገሩ ፡ ይማም ፡ ለነሱ ፡ ምንም ፡ ሳይመልስ ፡ ወደአብሳማ ፡ ኑር ፡ ፊቱን ፡ አዞሮ ፡ ደጋልሃን ፡ በያዘው ፡ ተራራ ፡ በኩል ፡ እንውጣ ፡ ብትለኝ ፡ አይሆንም ፡ ከርሱ ፡ የተሻለ ፡ አለ ፡ ብዬህ ፡ የነ በረው ፡ ይኸውልህ ፡ አለው ፡ አብሳማ ፡ ኑርም ፡ ፡እውነትህ ፡ ነው ፡ እንውጣና ፡ ብንሞትም ፡ እንሙት። ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይማም ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣና ። መሣሪያችሁን ፡ ያዙ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ይባርካችሁ ፡ ብሎ ፡ ተናገረና ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ ልብሱን ፡ መልበስና ፡ መሣ ሪያውን ፡ መያዝ ፡ ጀመረ ፡ ከዚህም ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ዋነኞች ፡ አብሳማ ፡ ኑር ፡ ኤሚር ሙጃሂ ፡ ኤሚር ፡ አቡበከር ፡ ቀጢን ፡ አህመድ ፡ ጎይታ ፡ አደሙሽ ፡ አውራይ ፡ አቡ በከር ፡ አሊ ፡ ጎይታ ፡ በለው ፡ አብዶ ፡ አሊ ፡ ታይ ፡ ኢጅር ፡ አውራይ ፡ አትማን ፡ ቤን ዳር ፡ አሊ ፡ ያኪም ፡ አዝማች ፡ ሃይቢ ፡ ፈራሃም ፡ ሶልጣንና ፡ ኢሳ ፡ ነበሩ ፡ ይማም ፡ ሳክብ ፡ እሚባለው ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ እንደሆነ ፡ የእግረኛን ፡ ጦር ፡ አዘዥ ፡ አስጠራና ፡ እግ ረኛው ፡ እሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ በዛፉ ፡ ውስጥ ፡ በተራራው ፡ ጐን ፡ መው ጣት ፡ ይዠምር ፡ እኛ ፡ የመካከለኛውን ፡ መንገድ ፡ ይዘን ፡ ስንወጣ ፡ ድንገት ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተገኝተው ፡ መተላለፊያ ፡ የዘጉብን ፡ እንደሆነ ፡ ይዋጉ ፡ ብሎ ለ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ በፈንጅ ፡ ሳባር ፡ ለሚታዘዘው ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በፈረሶቻ ችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቀድማችሁ ፡ ተጓዙ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ። ወታደሩም ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ በእጁ ፡ እንደያዘ ፡ ጋሻውን ፡ እንዳነገተ ፡ ጉዞው ፡ ተዠመረና ፡ . . . . ተራራውን ፡ መውጣት ፡ ዠመሩ ።

እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በተራራው ፡ ያለው ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ የእስላ ሞቹን በቅርብ ፡ መኖር ፡ አላወቀም ፡ ነበር ፡ ይማም ፡ ከነጦሩ ፡ ግማሽ ፡ መንገድ ፡ እንደተጓዘ ፡ አንድ ፡ በጫት ፡ የሰከረ ፡ (ታማራ.ቃህ ፡ የሚጠጣ) ? ፡ እተራራው ፡ ዶ ር ፡ የነ ረ ፡ እስላም ፡ አጠገቡ ፡ አንዲት ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ አቃጠለ ። ክርስቲያኖቹ ፡ ከላይ ፡ ከተራራ ፡ ቁልቁል ፡ ቃጠሎውን ፡ ተመልክተው ፡ ተሸበሩ ። እስላሞቹም ፡ ወደኋላቸው ፡ ዘወር ፡ ቢሉ ፡ ቃጠሎውን ፡ አዩ ፡ ይማምም ፡ አብሮ ፡ አየና ፡ ይኸን ፡ ያደረገው ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ የረገመው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጮኸና ፡ ወዲያው ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ይኸን ፡ ቃጠሎ ፡ ዓይተው ፡ ሳይሸሹ ፡ ፈረሳችሁን ፡ በለንጋ ፡ እየመ ታችሁ ፡ በችኰላ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ ፈረሰኞቹን ፡ አዘዘ ።

ክርስቲያኖቹም ፡ በበኩላቸው ፡ ግማሾቹ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ሲጭኑ ፡ ግማሹ ፡ ጦርና ፡ ጋሻውን ፡ ሲያዘጋጅ ፡ እፊት ፡ ቀድመው ፡ የነበሩት ፡ እነአብሳማ ፡ ኑር ፡ የፈረሶቻ ቸውን ፡ ልጓም ፡ ለቀው ፡ እየጋለቡ ፡ አላህ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጮኸው ፡

እመከከላቸው ፤ ገብተው ፤ ይዋጉ ፤ ዠመር ። ወደ ፤ ጦሩ ፤ ቀድሞ ፤ የገባው ፤ አዳሙሽ ፤ ካንድ ፤ ክርስቲያን ፤ ጋር ፤ ተጋጥሞ ፤ በጦር ፤ ገደለ ። አብሳማ ፤ ኑር ፤ ግን ፤ እተዋጊው ፤ ወታደሩ ፤ መካከል ፤ ሆኖ ፤ ከአምላካችን ፤ ከአላህ ፤ በቀር ፤ ሌላ ፤ አምላክ ፤ የለም ፤ መሐመድም ፤ የእግዚአብሔር ፤ ሐዋርያ ፤ (መላክተኛ) ፤ ነው ፤ እያለ ፤ እየመላለሰ ፤ ይጮህ ፤ ነበር ። ከክርስቲያኖቹ ፤ ግማሾቹ ፤ ወደ ንጉሡ ፤ ድንኳን ፤ እየሮጡ ፤ ሄደው ፤ ተሰበሰቡ ፤ ግማሾቹ ፤ ወደ ፤ አገኙበት ፤ ሥፍራ ፤ ወደ ፤ ፊታቸው ፤ ሸሹ ። ንጉሡም ፤ ከድንኳኑ ፤ ወጥቶ ፤ እፈረሱ ፤ ላይ ፤ ወጣ ፤ ፴፪ ፤ የሚሆኑ ፤ ፈረሰኞችም ፤ በዙሪያው ፤ ሆነው ፤ ወደ ፤ ርሱ ፤ ሰው ፤ እንዳይቀርብ ፤ ይከላከሉ ፤ ነበር ። እግረኛውም ፤ ጦር ፤ ብዙ ፤ ነው ።

ክርስቲያኖቹ ፤ በንጉሡ ፤ ዙሪያ ፤ የተሰበሰቡ ፤ ጊዜ ፤ እስላሞቹ ፤ ይማም ፤ አህመድ ፤ እስኪደርስ ፤ ድረስ ፤ ይጠብቁ ፤ ነበር ፤ ይማም ፤ ግን ፤ በንጉሡ ፤ ድንኳን ፤ ዙሪያ ፤ የተሰበሰበውን ፤ የጦር ፤ መጠን ፤ ሲመለከት ፤ ኃይለኞቹ ፤ ፈረሰኞች ፤ እንአብድ ፤ ኢን ናስር ፤ እነሰበር ፤ ዲን ፤ . . . . ከኋላው ፤ ደረሱለት ፤ እንደዚህ ፤ ሆነው ፤ እስላሞቹም ፤ ክርስቲያኖቹም ፤ በየሥፍራቸው ፤ ቆመው ፤ ሳሉ ፤ ከክርስቲያኖቹ ፤ መካከል ፤ አንዱ ፤ ተነጥሎ ፤ ፈረሱን ፤ እስነሥቶ ፤ እየጋለበ ፤ ወደ ፤ እስላሞቹ ፤ መጣ ፤ ሳበር ፤ ኤድ ፤ ዲን ፤ ጦሩን ፤ ገትሮ ፤ ሊዋጋው ፤ ወደ ፤ ርሱ ፤ ሲጋልብ ፤ ያኛው ፤ "ከእግዚአብሔር ፤ በቀር ፤ ሌላ ፤ አምላክ ፤ የለም ፤ መሐመድም ፤ የእግዚአብሔር ፤ መላክተኛ ፤ ነው ። ሲል ፤ ሰማውና ፤ ነገሩ ፤ ገርሞት ፤ ሳይወጋው ፤ ተመለሰ ፤ ያኛው ፤ እይማም ፤ ፊት ፤ ቀረበና ፤ ምድነህ ፤ ብሎ ፤ ቢጠይቀው ፤ እኔ ፤ ጆሹ ፤ (ጎሹ) ፤ እባላለሁ ፤ የማምነው ፤ በአላህና ፤ በነቢዩ ፤ በመሐመድ ፤ ነው ፤ ልጄ ፤ በሽራህ ፤ ከናንተ ፤ ጋር ፤ አብሮ ፤ አለ ፤ ብሎ ፤ መለሰ ፤ ይማም ፤ እግዚአብሔር ፤ ታላቅ ፤ ነው ፤ እስላም ፤ ነውና ፤ ልቀቁት ፤ ብሎ ፤ ተለቀቀ ።

ከዚያ ፤ ቀጥሎ ፤ እንግዲህ ፤ እዚህ ፤ ምን ፤ አቆየን ፤ ሂደን ፤ እንዋጋ ፤ ተባብለው ፤ . . . እየተሽቀዳደሙ ፤ እክርስቲያኖቹ ፤ መካከል ፤ ገብተው ፤ ይዋጉ ፤ ዠመር ፤ ፩ ፤ ሰዓት ፤ ያህል ፤ እንደተዋጉ ፤ እግዚአብሔር ፤ በክርስቲያኖቹ ፤ ልብ ፤ ፍርሃት ፤ አስገብቶ ፤ ሽሽትን ፤ ጀመሩ ፤ እስላሞቹም ፤ ሁጉዋ ፤ (ሐን) ፤ እስከሚባለው ፤ ተራራ ፤ ድረስ ፤ እየተከታተሉ ፤ መቱዋቸው ፤ እሸሹበትም ፤ ተራራ ፤ ድረስ ፤ እያባረሩ ፤ በሚዋጉበት ፤ ጊዜ ፤ አው ፤ አቡበከር ፤ ፋኪር ፤ . , , , የሚባለው ፤ አንድ ፤ የንጉሡን ፤ ባለሟል ፤ አግኝቶ ፤ መትቶ ፤ ከፈረሱ ፤ ላይ ፤ ገልብጦ ፤ ጣለውና ፤ ‹አንተ ፤ ንጉሡ ፤ አይደለህምን ፤ ብሎ ፤ ይዞ ፤ ቢጠይቀው ፤ «የለም ፤ እኔ ፤ አይደለሁም ፤ ንጉሡ ፤ ያውና» ፤ ብሎ ፤ በጣቱ ፤ አመለከተ ። አቡበከር ፤ ግን ፤ ‹የለም ፤ ስታታልለኝ ፤ ነው" ፤ እያለ ፤ ከርሱ ፤ ሲነጋገር ፤ የክርስቲያኑ ፤ አሽከሮች ፤ ሮጠው ፤ መጡና ግማሾቹ ፤ ፈረሱን ፤ ይዘው ፤ ግማሾቹ ፤ እርሱን ፤ ደብድበው ፤ ማረኩት ፤ ይማም ፤ እርሱን ፤ ለማስጣል ፤ ወደ ፤ ነርሱ ፤ ገሥግሦ ፤ ተዋግቶ ፤ አስጣለው ። በዚያን ፤ ጊዜ ፤ የሀበሻው ፤ ንጉሥ ፤ ይማምን ፤ ግራኝ ፤ ስለነበረ ፤ ጉራዴውን ፤ በግራ

እጁ ፡ እንደያዘ ፡ እየውና ፡ በፈረሱ ፡ ምልክትና ፡ በግራኝነቱ ፡ ዐውቆት ፡ ፡፡ያውና፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ የተመሰለው ፡ ሰይጣን፡፡ ፡ ብሎ ፡ አጠገቡ ፡ ላሉት ፡ ጓደኞቹ፡ ተናገረ ፡ ወታደሮቹም ፡ ፡፡በመተትህ ፡ (በጥንቆላህ) ፡ ያዝኸን ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ፡፡ ይኸንንም ፡ ማለታቸው ፡ ይማምን ፡ የማፍዘዣ ፡ ዕንጨት ፡ (ዛፍ) ፡ እየቆረጠ ፡ በዚያ፡ እየተዋጋ ፡ በአስማት ፡ ያሸንፋል ፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይዋሻሉ ፡፡

ይማም ፡ እመካከላቸው ፡ ገብቶ ፡ በብርታት ፡ ተዋግቶ ፡ በታተናቸው ፡ እነር ሱም ፡ ወደተራራው ፡ ለመሸሽ ፡ ከፈረሳቸው ፡ ወርደው ፡ ልባቡን ፡ እየሳቡ ፡ በግራ ቸው ፡ ተራራውን ፡ ሊወጡ ፡ መንገድ ፡ ሲፈልጉ ፤ ይማም ፡ ከኋላችሁ ፡ እንደርስባ ችኋለንና ፤ ፈረሳችሁን ፡ ለቃችሁ ፡ ሽሹ ፡ ብሎ ፡ ጮኸባቸው ፡ እነርሱም ፡ ይኸ ንን ፡ ድምፅ ፡ ሰምተው ፡ በፍርሃት ፡ በጉልበታቸው ፡ ጭምር ፡ እየዳሁ ፡ በጣር ፡ ወደ ተራራው ፡ ወጡ ፡፡ አንዳንዱም ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ለመደበቅ ፡ ሲሞክር ፡ ቅርን ጫፉ ፡ እየተሰበረበት ፡ እስላሞቹ ፡ መከከል ፡ እየወደቀ ፡ አግኝተው ፡ ገደሉት ፡፡ ይማም ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ፈረሶች ፡ የሚያማምር ፡ ከርቻና ፡ ቀያይ ፡ ግላስ ፡ እንደተ ጫኑ ፡ ወደቆሙበት ፡ ሰው ፡ ልከ አስወሰዳቸው ፡ ቊጥራቸው ፡ ፸ ይሆናል ፡፡ ከይ ማም ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ አብሳማ ፡ ኑር ፡ ያኪም ፡ አዳሙሽ ፡ ኤሚር ፡ ሙጃሂድ ፡ ገራድ፡ አህማዱሽ ፡ ፋራቅሃም ፡ ሳቱ ፡ አብደላ ፡ ቤን ፡ ሞሀራፇ ፡ የማህራው ፡ (ዓረቡ)፡ ነበሩ ፡ እነዚህም ፡ በየበኵላቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ሲገድሉ ፡ ሲማከሩ ፡ ነበር ፡፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሀበሻው ፡ ንጉሥ ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ እፊት እፊቱ ፡ አራት፡ የተጫኑ ፡ ፈረሶቹን ፡ እያሳበ ፡ ከመንገዱ ፡ መጥፎነት ፡ የተነሣ ፡ ወደፊቱ ፡ በእ ግሩ ፡ ሲጓዝ ፡ ይማም ፡ በበኩሉ ፡ እንደዚሁ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ በእግሩ ፡ ሄደ ፡፡ ሌሎቹ ፡ እስላሞች ፡ እነገራድ ፡ ኦትማን ፡ እነአውራይ ፡ ኦትማን ፤ በመንገድ ፡ ንጉ ሡን ፡ ቀድመው ፡ አለፉ ፡፡ ንጉሡም ፡ እነሱን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ሳያዩት ፡ አጠገቡ ፡ አለው ፡ ዛፍ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ተደበቀ ፡፡ ይማምና ፡ ጓደኞቹም ፡ ንጉሡ ፡ ካለበት ፡ በታች ፡ ቀደም ብለው ፡ ደረሱ ፡ . . . . ፩ ፡ የክርስቲያን ፡ ፈረሰኛ ፡ እየሮጠ ፡ ሲመጣባቸው ፡ አውራይ ፡ ኦትማን ፡ ገጠመውና ፡ ማረከው ፡ ይኸም ፡ ሰው ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ የተከበረ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ፡ በይማም ፡ ትእዛዝ ፡ ተገደለ ፡ . . . . እስላሞቹ ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ (ንጉሡ ፡ ባለበት ፡) እንዳሉ ፡ ወዲያው ፡ ዠምበር ፡ ጠለቀች ፤ ደመናም ፡ ሆነ ፡ ዝናብም ፡ ይዘንም ፡ ዠመር ፡ ኃይለኛ ፡ ብርድም ፡ ተነሣ ፡፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ተመልሰው ፡ ወደጓደኞቻቸው ወደሠፈር ፡ ተመለሱ ፡፡ እነሱም ፡ ሲመለሱ ፤ ንጉሡ ፡ ከነበረ በት ፡ ሥፍራ ፡ (ጫካ) ፡ ወጥቶ ፡ በአምባ ፡ (አምባ ፡ ግሼን ፡) መንገድ ፡ አድርጎ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ሲጓዝ ፡ አደረ ፡፡

እስላሞቹ ፡ ወደ ፡ ሠፈር ፡ ሲመለሱ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ አገኙአቸው ፡ ከዚያ ፡ በደስታ ፡ ወደየክርስቲያኖቹ ፡ ድንኳን ፡ ገቡ ፡፡ ድንኳኑ ፡ ሁሉ ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ በፈረስ ፡ በበቅሎ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሐር ፡ ልብስ፡ ተመልቶ ፡ ነበር ፡፡ ከሐሩም ፡ ልብስ ፡ ውስጥ ፡ በወርቅ ፡ የተጠለፈ ፡ ግማሹ ፡

የንጉሡ ፤ የቀረው ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ነበር ። ከዚሁ ፡ ጋር ፡ በሺ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ቆነዣ
ዥርት ፡ ሴቶች ፤ የሹማምንት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ አብረው ፡ ተገኙ ። የን
ጉሡ ፡ ድንኳን ፡ በውስጡ ፡ ዙፋኑና ፡ መሣሪያው ፡ እንዳለ ፡ እንደተተከለ ፡
ተገኘ ። ይማም ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አገኘው ፡ ድል ፡ አም
ላኩን ፡ አመሰገነና ፡ «በንጉሡ ፡ ድንኳን ፡ የተገኘውን ፡ ምን ፡ አደረጋችሁት» ፡
ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ “የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሆነውን ፡ እስላሞቹ ፡ ተከፋፈሉት ፡ ዙፋ
ኑና ፡ የሐር ፡ ልብሱ ፡ በውስጡ ፡ እንዳለ ፡ ነው» ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡ ከዚያ ፡
ድንኳኑ ፡ አያስፈልገኝምና ፡ ቅደዱት ፡ የሐሩን ፡ ልብስና ፡ ዙፋን ፡ ግን ፤ አምጡ
ልኝ ፡ ብሏቸው ፡ እነሱም ፤ ሄደው ፡ ድንኳኑን ፡ በሰይፋቸው ፡ ቀዳደው ፡ ጣሉት ።

እስላሞቹ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ በደስታ ፡ አደሩ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቀደም ፡
ብሎ ፡ በገራድ ፡ አህሙሽ ፡ የሚታዘዘው ፡ የመካከለኛው ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ጦር
ደረሰ ፡ ተራራውን ። በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ ይማም ፡ ድዙኤል ። ጅናህ ፡ ብሎ ፡
የሠየመው ፡ የአህሙሹ ፡ ፈረስ ፡ አድጦት ፡ ወድቆ ፡ ተሰበረና ፡ እዚሁ ፤ እሠ
ፈር ፡ ሞተ ። አህሙሽም ፡ ስለ ፡ ፈረሱ ፡ ቢያለቅስ ፡ ይማም ፡ ከተማረኩት ፡ ከን
ጉሡ ፡ ፈረሶች ፡ የሚያምረውን ፡ ፈረስ ፡ ተካው ። ደጅን ፡ የነበሩት ፡ ወታደሮች
ጦርነቱን ፡ አልተካፈሉም ፡ ጦርነቱ ፡ የሆነለት ፡ እመንገድ ፡ አድረው ፡ በማግሥቱ
ደረሱ ። እነሱም ፡ ሲደርሱ ፡ ከየጓደኞቻቸው ጋር ፡ ተገናኝተው ፡ ሰላምታ ፡ እየ
ተሰጣጡ ፡ ስለተገኘውም ፡ ድል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፡ ይማም ፡ በውጊ
ያውለት ፡ ሳትደርሱ ፡ ቀርታችሁ ፡ ምንም ፡ አላገኛችሁም ፡ ብሎ ፡ ለየአንዳንዳ
ቸው ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፈረስ ፡ አደላቸው ።

የወሲል ፡ ጦርነት ፡ ዓርብ ፡ ለት ፡ በ፲፮ ፡ ረቢ ፡ ፱፻፴፰ ፡ በሂጀራ ፡ ቍጥር፡
ተፈጸመ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፤ ውስጥ ፡ በጭሩ ፡ የምንመለከተው ፡ ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ልብነ
ድንግል ፡ ጦራቸው ፡ በአለፉት ፡ ዓመቶች ፡ በሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ በአይፈርስ ፡
በዛሬ ፡ በዝሆን ፡ ዱር ፡ ጦርነት ፡ ከተሸነፈ ፡ ከዋና ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ አለቆቻቸው፡
ውስጥ ፡ እነራስ ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ እነራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ሌሎቹም ፡ በየሥ
ፍራቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ከሞቱ ፡ ወዲህ ፡ ሰፊውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የደቡብና ፡ የደ
ቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ ግዛታቸውን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደታላላቅ ፡ አውራጃ ፡ የሚ
ቆጠሩትን ፡ ይፋትን ፤ ፈጠጋርን ፡ (በዛሬው ፡ በናዝሬት ፡ ግዛት ፡ ዙሪያ ፡ የሚገ
ኘው ፡ ሁሉ) ፤ ደዋሮን ፡ (እንደ ፡ ግማሹ ፡ የደንከል ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ያሩሲ )፤
የባሌን ፤ የሸዋን ፡ የዳሞትን ፡ የጉራጌን ፡ ግዛት ፡ ሁሉ ፡ ለኢሸናፊው ፡ ለግራኝ፡
አህመድ ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ አምሐራ ፡ (አማራ ፡ ሳይንትና ፡ ወሎ ፡ መካከል ፡
ሄደው ፡ በዚያ ፡ ወደዚህ ፤ ሥፍራ ፡ የሚያመጣውን ፡ ጠባብ ፡ መንገድና ፡ ዋና ፡
ዋና ፡ በር ፡ የጦር ፡ አለቆቻቸውን ፡ ራስ ፡ ደጋልሃንንና ፡ ራስ ፡ ባንያትን ፡
ጦር ፡ ደልድለው ፡ እያስጠበቁ ፡ ራሳቸው በወሲል ፡ ተራራ ፡ መቀመጣቸውን፡ነው ።

ከዚሁ ፡ ተያይዞ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ተስፋውን ፡ የጣለበት ፡ ራስ ፡ ወሰን፡
ሰገድ ፡ በጦርነት ፡ ሲሞት ፡ ንጉሡ ፡ አገሩን ፡ ለቀው ፡ ወደቤተ ፡ አምሐራ ፡
ሲሸሹ ፡ የደቡብ ፡ አገር ፡ በግራኝ ፡ ሥልጣን ፡ ሲወድቅ ፡ ግማሹ ፡ በፍርሃት ፡
ግማሹ ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጥ ፡ ሕዝቡ ፡ ከነባላባቱ ፡ ከወታደሩም ፡ ውስጥ ፡
ግማሹ ፡ ከነአለቃው ፡ ወደግራኝ ፡ እየገባ ፡ ሲሰልም ፡ ከነዚሁም ፡ ወደግራኝ፡
ከገቡት ፡ ሹማምንቶች ፡ ውስጥ ፡ እነአውራይ ፡ ኡትማን ፡ እነአዝማች ፡ ሃይቢ ፡
እነ ፡ አናንያ ፡ የግራኝን ፡ ባለሟልነት ፡ ለማግኘት ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ የሚያው
ቁትን ፡ የአገሩን ፡ መውጫና ፡ መግቢያ ፡ የሕዝቡን ፡ ጠባይ ፡ የወታደሩን ፡ ብዛትና፡
ማነስ ፡ በዝርዝር ፡ እያስረዱ ፡ መንገድ ፡ እየመሩ ፡ የሚያውቁትን ፡ ምሥጢር ፡
የሚሰማቸውን ፡ መላና ፡ ምክር ፡ እየሰጡ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንዳገለገሉት ፡ ተመ
ልክተናል ። ይልቁንም ፡ አናንያ ፡ የተባለው ፡ ግራኝ ፡ ከነጦሩ ፡ በቅርብ ፡ ያገኘ
ውን ፡ ራስ ፡ ደጋልሃን ፡ በያዘው ፡ በር ፡ በኩል ፡ ጦርነት ፡ ዠምሮ ፡ ሳይከናወ
ንለት ፡ ሲቀር ፡ በዚህኛው ፡ በር ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ልታሸንፍ ፡ አትችልም ፡
ንጉሡ ፡ ባሉበት ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ፈረሰኛም ፡ ስለ ፡ ሚያስወጣ ፡ በዚያ ፡ ሄደን
ንጉሡን ፡ ተዋግተን ፡ እናሸንፍ ፡ ንጉሡ ፡ ሲሸነፉ ፡ የደጋልሃን ፡ መኖር ፡ ከንቱ፡
ነው ፡ እያለ ፡ መልካም ፡ ምክር ፡ እየሰጠ ፡ ጥሩ ፡ መንገድ ፡ እየመራ ፡ እረኛ ፡ እያ
ታለለ ፡ ወገኖቹን ፡ ሲያስፈጅ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ሲያገለግል ፡ ጌታችን ፡ የሰው፡
ጠላቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ነው ፡ ያለበት ፡ ትርጉም ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ይገባናል ። አናን
ያም ፡ ወገኖቹን ፡ ሸጦ ፡ ግራኝን ፡ ባገለገለበት ፡ የገራድነት ፡ ማዕርግና ፡ የመረጃ
ይን ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ አግኝቷል ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ አይታወቅም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡
የዓረብ ፡ ፋቂህን ፡ ጽሑፍ ፡ ስንመለከት ፡ ግራኝ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ረዥም ፡ ጉዞ
አድርጎ ፡ ወሲል ፡ ተራራ ፡ ጥግ ፡ እስኪደርስ ፡ ተራራውን ፡ ሲወጣ ፡ ሁሉ ፤ በዚህ፡
አስፈሪና ፡ አደጋ ፡ በሆነበት ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ የሚያስወጣውን ፡ መንገድ፡
ንጉሡም ሹማምንቱም ፡ በዘብና ፡ በወር ፡ ተራ ፤ በጥብቅ ፡ አለማስጠበቃቸው ፡
የስንፍና ፡ ወይም ፡ የቸልታ ፡ መንገድ ፡ ይታይባቸዋል ።

በጫት ፡ የሰከረው ፡ እስላም ፡ እተራራው ፡ ስር ፡ ያገኘውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ባያቃጥልና ፡ ብርሱ ፡ ቃጠሎ ፡ ባይነቁ ፡ ኖሮ ፤ ከቅምጣቸው ፡ ሳይነሱ ፡ እስ
ላሞቹ ፡ ሊማርኩዋቸው ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ንጉሡን ፡ እግዚአብሔር
በወገኖቻቸው ፡ በነአናንያ ፡ የጐዳቸው ፡ ሲመስል ፡ መልሶ ፡ በጠላታቸው ፡ በአቃ
ጣዩ ፡ እስላም ፡ ጠቅሟቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የእስላሞቹን ፡
መምጣት ፡ አስቀድሞ ፡ ባለማወቅና ፡ ባለመጠንቀቅ ፡ የተነሣ ፡ ድንገተኛ ፡ በሆ
ነው ፡ ጦርነት ፡ መሸነፍና ፡ መሸሽ ፡ ብቻ ፡ ሳይበቃ ፡ ዙፋናቸው ፡ ፈረሶቻቸው ፡
ልብስና ፡ መጓሪያው ፡ የወርቁና ፡ የብሩ ፡ ገንዘብና ፡ ሀብት ፡ ከቤተ ፡ ሰብ ፡ ጭምር፡
ሳይቀር ፡ በእስላሞቹ ፡ እጅ ፡ ተማረከ ። ንጉሡም ፡ ከወሲል ፡ የበሽሎን ፡ ወንዝ ፡
ተሻግረው ፡ ከሸሹ ፡ ወዲህ ፡ እስላሞቹ ፡ እየተበታተኑ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆ
ኑት ፡ የመካነ ፡ ሥላሴ ፤ የአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ የደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ የቤተ ፡

ሰማያት ፤ የገነተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሀብታቸው ፡ እየተዘ ረፈ ፡ ተቃጠሉ ፤ ይኸንንም ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ፡ እንመለከታለን ።

በተረፈ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ እስላሞቹ ፡ ይማም ፡ አህመድ ፡ የሚሉት ፡ እኛ ፡ ግራኝ ፡ አህመድ ፡ የምንለው ፡ በርግጥ ፡ ግራኝ ፡ እንደነበረ ፡ መሣሪያ ውን ፡ ይጨብጥም ፡ ይዋጋም ፡ የነበረው ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ መሆኑ ፡ እነሆ ፡ በአረብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ተረጋገጠ ። የርሱም ፡ አነጋገር ፡ በግዕዝኛ ፡ በአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ (ወይም ፡ ባፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ ) የተጻፈው ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አጭር ፡ ታሪክ ፡ ከሚለው ፡ ጋር ፡ ይጋጠማል ፡ ቃሉም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ‹ወእምድኅረ ፡ ከነ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ በ፪ ፡ ዓመት ፡ ወጽአ ፡ እምሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ውእቱ ፡ አህመድ ፡ ወልደ ፡ ኢብራሂም ፡ ዘተሰምየ ፡ ግራኝ ፡ በእንተ ፡ ዘከነት ፡ እዴሁ ፡ ፀጋማዊት ፡ ከመ ፡ እድ ፡ የማናዊት„ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ (ያለፈውን ፡ ጦርነት ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ) ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ግራኝ ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመው ፡ የኢብራሂም ፡ ልጅ ፡ አህመድ ፡ ከሽምብራ ፡ ኩሬ ፡ ወጣ ፡ ግራኝ ፡ መባሉም ፡ ግራ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ቀኝ ፡ እጁ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ታሪክ ፡ የመላበትን ፡ የወሲልን ፡ ጦርነት ይኸኛውም ፡ ጽሑፍ ፤ ታሪክ ፡ ነገሥታችንም ፡ አያነሣውም ፡ እንደተለመደ ፡ ግን ፡ ጫፉን ፡ ጠቅሶ ፡ ሲያልፍ ፡ ግዕዝኛው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ እንደዚህ ፡ ይላል" . . . ወአመ ፡ ፫ ፡ ለነሐሴ ፡ ሞተ ፡ ራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ። ወእምዝ ፡ በ፪ ፡ ዓመት ፡ ኀለፈ ፡ ንጉሥ ፡ ምድረ ፡ አምሐራ ፡ ወነበረ ፡ በሐን ፡ ወአመ ፡ ፳ ወ፪ ለጥ ቅምት ፡ ተሰደ ፡ እምህየ ፤ ወአመ ፡ ፲ ፡ ለኅዳር ፡ አውዓዮሙ ፡ (ግራኝ ፤) በእሳት ፡ ለመካነ ፡ ሥላሴ ወለደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ . . . "ብሎ ፡ ይፈጽማል ፡ እንጂን ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ ከወሩና ከዕለቱ ፡ በቀር ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ አይጠቅስም ፡ ነገር ፡ ግን አረብ ፡ ፋቂህ ፡ በሂጅራ (የእስላም ፡ ቍጥር ፡) በ፱፻፴፰ ፡ ዓመት ፡ መሆኑን ፡ ስለ ፡ ገለጸ ፡ የዚህ ፡ የወሲል ፡ ጦርነት ፡ የተደረገው ፡ በኤውሮፓ ፡ አቆጣጠር ፡ ሲታሰብ ፡ 1531 ፡ ዓ፡ ም፡ በኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ፡ ፲፭፻፳፬ ፡ ዓ፡ ም ፡ ነው ። ራስ ፡ ደጋልሃን ፡ ከገሠመረው ፡ ከደዋሮው ፡ ጦርነት ፡ አንሥቶ፡ እስከዚህ ፡ እስከ ፡ ወሲል ፡ ጦርነት ፡ ድረስ ፡ የግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ከተዠመረ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሆኑዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፳ ፪ ።

### የ‹ሐንስ ፡ ዣን ፡ ቤርሙዴስ ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለመላኩ ፤–ስለ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዕረፍት ።

በትልቁ ፡ በቱርክና ፡ በየመን ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ የተደገፈውን ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ከገር ፡ ውስጥ ፡ በተገኘው ፡ ወታደርና ፡ መሣሪያ ፡ ብቻ ፡ ለማሸነፍ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ተቻላቸው ፡ ደከሙ ። የገሃድም ፡ የደፈጣም ፡ ጦርነት ፡ ራሳቸውና ፡ ታማኞቻቸው ፡ በየጊዜው ፡ አደረጉ ። በያውራጃው ፡ የሚገኘው ፡ የጐጃም ፤ የዳሞት ፡ የበጌምድር ፤ የትግሬ ፤ የሐማሴን ፡ የዋግ ፡ ሹማምንትና ፡ መኳንንት ፡ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ ያለንጉሡም ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፤ ሲያሸንፉ ፤ ሲሸነፉ ፡ በየጊዜውም ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ እያየለ ፡ ሲያሳድዳቸው ፡ እነሆ ፡ ከዐሥር ፡ ዓመት ፡ ማለፉ ፡ ነው ።

ንጉሡ ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ደጋግመው ፡ ቢወጉ ፡ ብቻቸውን ፡ እንደማይመልሱት ፡ ገና ፡ በፊት ፡ ሳይረዱ ፡ አልቀሩም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ መዠመሪያ ፡ ዶን ፡ አልቫሬጽ ፡ ቀጥሎ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ የሚባሉትን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወደ ፡ ሊስቦን ፡ (የፖርቱጋል ፡ ከተማ) ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ርዳታና ፡ ዝምድናን ፡ ለመጠየቅ ፡ የላኩት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሩቅ ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ በባቡርና ፡ በመኪና ፤ በአይሮፕላን ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ መጠቅለል ፡ በማይመችበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቁንም ፤ በአፍሪካ ፡ ሰሜንና ፡ በሜዲቴራኒ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ የቱርኮችን ፡ ጥብቅ ፡ ፍተሻ ፡ አልፎ ፡ መልክትን ፡ አድርሶ ፡ በፍጥነት ፡ መልስ ፡ ማምጣት ፡ ችግር ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ለዚህም ። ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለዚያን ፡ ጊዜ ፡ መልክት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አልቫሬጽና ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ከሄዱ ፡ ዠምሮ ፡ ቢቈጠር ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ስላለፈው ፡ ለዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ተስፋ ፡ አስቈራጭ ፡ ሁኔታ ፡ ገጠማቸው ። ትልቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከታላላቆቹ ፡ የጦር ፡ አለቆቻቸው ፡ አብዛኞቹን ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ አጥተዋቸው ፡ ከባላቤታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ ከተራራ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፤ ከዋሻ ፡ ወደ ፡ ዋሻ ፤ ከገር ፡ ወዳገር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ የግራኝ ፡ ጦርም ፡ ሲገጥማቸው ፡ በመጨረሻና ፡ በደከመ ፡ ኀይል ፡ እየተዋጉ ፡ ሲመለሱ ፡ ኖሩ ።

ስለዚህ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የተጠየቀውን ፡ የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ለማጣደፍ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በቶሎ ፡ ቢላክ ፡ ይሻላል ፡ ተብሎ ፡ ተቈረጠ ። መልክቱንም ። ይዞ ፡ እንዲሄድ ፡ የተመረጠው ፡ ዣን ፡ ቤርሙዴዝ ፡ የሚባለው ፡ የፖርቱጋሉ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ መልክት ፡ ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኩልበ ፡ በመጽሐፋቸው ፡ ባ104ና ፡ ባ105 ፡ ገጽ ፡ እርሳቸውን ፡ የመሰሉትም ፡ ጸሓፊዎች ፡ ሳይቀሩ ፡ እንደዚህ ፡ ይላሉ ። ‹ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፤ ሃይማኖታቸውን ፡ ለሮማ ፡ መንበር ፤ መንግሥታቸውን ፡ ለፖርቱጋል ፡ መንግሥት አስገዛለሁ ፡ ለማለት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡

ብንጋገራቸው ፡ ወላውለው ፡ የነበረውን ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ተስፋ ፡ በቈረጡበት ፡ ሰዓት ፡ እኔና ፡ መንግሥቴ ፡ በሙሉ ፡ የሊሲቦንና ፡ የሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ተገዥ ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ በገሃድ ፡ በጽሕፈትም ፡ በቃልም ፡ አስታወቁ ። ከእስክንድርያ ፡ የመጡት ፡ አሮጌው ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ጳጳስ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ የጵጵስና ፡ ወንበራቸውን ፡ ይኸንኑ ፡ ቤርሙዴዝን ፡ ቀብተው ፡ እንዲለቁለት ፡ አደረጉ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቤርሙዴዝም ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሄዶ ፡ የርዳታውን ፡ ነገር ፡ አከናወነ» ፡ ይላል ። እውነት ፡ ይሆንን? ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሐሰትም ፡ እውነትም ፡ ቢሆን ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ርዳታው ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ሞቱ ፡ ልጆቻቸው ፡ ገላውዴዎስና ፡ ሚናስም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ መጪዎቹን ፡ ሚሲዮኖች ፡ በመልካም ፡ ዐይን ፡ ቢቀበሏቸው ፡ የሮም ፡ ሃይማኖትን፡ አላተቀበሉም ። ይኸንንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በስፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እንቀጥላለንና ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ ቤርሙዴዝ ፡ ምልክት ፡ እንጽፋለን ።

ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አላይ እንደ ፡ ተባለው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተዘመዱት ፡ መሠረት ፡ ርዳታ ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ይዞ ፡ እንዲመጣ ፡ ደብዳቤ ፡ ጨምረው ፡ በጥድፊያ ፡ ላኩት ። ሆን ፡ ቤርሙዴዝም ፡ በህንድ ፡ በኩል ፡ እንዳይሄድ ፡ መርከብ ፡ ስላጣ ፡ በድፍረት ፡ በኑብያና ፡ በግብጽ ፡ ከዚያም ፡ በኢየሩሳሌም  በኩል ፡ አድርጎ ፡ በግልጽም ፡ በሽሽግም ፡ አለፈ ። ሜዲቴራኔ ፡ ላይም ፡ ቱርኮች ፡ አግኝተው ፡ አስረውት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ አምልጦ ፡ በሽሕ ፡ ፲፻፭፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሮማ ፡ ደረሰና ፡ ደብዳቤውን ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ፫ኛ ፡ አስረከበ ፡ በቃሉም ፡ በኢትዮጵያ ፡ እስላሞቹ ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ጦርነትና ፡ ግፍ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱንና ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሁሉ ፡ ሲያቃጥሉ ፡ በይኑ ፡ ያየውን ፡ እያገነነ ፡ አስረዳ ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፡ ሄዶ ፡ ለሟቹ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ለዮሐንስ ፡ ፫ኛ ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ የቀረውንም ፡ በቃሉ ፡ እየጨመረ ፡ አስረዳ ።

ስለዚህ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ በህንድ ፡ አገር ፡ ለሚገኘው ፡ እንደራሴው ፡ ለዶን ጋርቺያ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ርዳታ ፡ እንዲልክለት ፡ ትእዛዝ ፡ አስተላለፈለት ። እርሱ ፡ ግን ፡ ትእዛዙን ፡ ከመፈጸም ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ለህንድ ፡ እንደራሴነት ፡ በሟቹ ፡ እግር ፡ እስጢፋኖስ ፡ ደጋማ ፡ የሚባለው ፡ ተሾመ ። እስጢፋኖስ ፡ ደጋማ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ (400) ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ አዳዲስ ፡ ብረት ፡ የያዙ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ አደራጅቶ ፡ ለነዚሁ ፡ አለቃ ፡ ወንድሙን ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማን ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ምፅዋ ፡ ሊልክ ፡ ይዘጋጅ ፡ ዠመር ።

ይኸም ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ንጉሡ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ካማራ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ዞረው ፡ ሲዋጉ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ በሽታና ፡ ረኃብ ፡ በየሀገሩ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበር ። ከግራኝም ፡ ጋራ ፡ የተለመደው ፡ የጧትና ፡ የማታ ፡ ጦርነት ፡ አላቋረጠም ። የስቅለት ፡ ለት ፡ ዐርብ ፡ ሚያዝያ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ አቡበከር ፡ ካቲም ፡ የሚባለው ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ተዋጋቸው ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ አዛዥ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡

አዛዥ ፡ እምኀ ፤ አዛዥ ፡ ሚካኤል ፡ ደረሰ ፤ አባ ፡ ትንሣኤ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባሉ ፡ የደብረ ፡ ቢዘን ፡ መነኵሴ ፡ ሞቱ ።

በትግሬና ፡ ባማራ ፡ አገር ፡ ግራኝና ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ሲዋጉ ፡ እንደ ዚሁ ፡ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ እነበታሪክ ፡ አዳሉ ፤ እነተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ እነራስ ፡ ባንያት ፡ እየተነሡ ፡ የግራኝን ፡ ሹማምቶች ፡ እየወጉ ፡ ሰላም ፡ አሳጥተዋቸው ፡ ነበር ። የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ ፊቅጦር ፡ የሚባለው ፡ ልጃቸው ፡ ሸዋ ፡ ሄዶ ፡ በደዋሮ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ። ወንድሙ ፡ ሚናስ ፡ ግን ፡ ከጦርነት ፡ ተማረከና ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋራ ፡ ለዘቢድ ፡ ባሻ ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ባርያ ፡ ተሸጠ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ ከጦርነት ፡ ተማርከው ፡ የነበሩት ፡ ዐሊ ፡ ገራድና ፡ ዑመር ፡ ዲን ፡ የሚባሉት ፡ እስላሞች ፡ በለውጥ ፡ ተላኩና ፡ ሚናስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመለሰ ።

ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ሚናስ ፡ (የነፍጥ ፡ መያዣ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ተላከ ። በኋላም ፡ በካቶሊክነት ፡ ቀብተው ፡ ላኩት) ፡ የሚለው ፡ እውነት ፡ አይመስልም ። ይኸን ፡ አተራረክ ፡ ከዚሁ ፡ ካገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ በቀር ፡ የቀሩት ፡ ባለታሪኮች ፡ አያረጋግጡም ። የዚህንም ፡ አኳኋን ፡ በስፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እናመለክታለንና ፤ አሁን ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ፍጻሜ ፡ እንቀጥላለን ።

ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከታማኝ ፡ አሽከሮቻው ፡ ጋራ ፡ በበጌምድር ፡ እየተዋጉ ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ ባሽከሮቻቸው ፡ ምክር ፡ በጌምድርን ፡ ለቀው ፡ በደብረ ፡ ዳሞ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደማይደፈረው ፡ ተራራ ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ። የዚያም ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ የሚባለው ፡ በመልካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀብሎ ፡ ሲያስተናግዳቸው ፡ ሰነበተ ። ንጉሡም ፡ በደብረ ፡ ዳሞ ፡ ሳሉ ፡ ታመው ፡ ሰነበቱ ። በመጨረሻም ፡ ሕመማቸው ፡ እየበረታ ፡ ሄደና ፡ ባ፩ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ዐረፉ ። ሲሞቱም ፡ ሬሳቸው ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳም ፡ እንዳይቀበር ፡ መነኰሳቱ ፡ ግራኝን ፡ ፈርተው ፡ እንቢ ፡ ስላሉ ፡ ሬሳቸው ፡ ደባሩእ ፡ ቈየ ፡ ይባላል ። በኋላ ፡ ግን ፡ ዐፅማቸው ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ሄዶ ፡ በክብር ፡ ተቀብረ ።

ሲሞቱ ፡ ዕድሜአቸው ፡ ዓርባ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፤ የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ከገጠሙ ፡ አንሥቶ ፡ ሕይወታቸው ፡ እስኪያልፍ ድረስ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ካገር ፡ ወዳገር ፡ እየዞሩ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ሲከላከሉ ፡ በየጦርነቱም ፡ ልጆቻቸው ፡ እነፊቅጦር ፡ እነሚናስ ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ እነራስ ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፤ እነራስ ፡ ማዕጠንቱ ፤ እነራስ ፡ ዴገልሃን ፤ እነራስ ፡ ዐምዱ ፤ እነጸሐፊ ፡ ላሕም ፡ (የወረገኑ ፡ ሹም? ) ፡ ሮቤል ፤ እነዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ነገደ ፡ ኢየሱስ ፤ እነአዝማች ፡ ዮሐንስ ፤ እነአዛዥ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ እነሮም ፡ ሰገድ ፤ እነእስላም ፡ አሰገድ ፤ እነጌዴ

ምን ፡ እነግራጌታ ፡ ዕዝራ ፡ . . . . . . . . . ሲሞቱ ፡ ሲማረኩ ፡ ሲሰደዱ ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ የጦርነትና ፡ የሞት ፡ የመራብና ፡ የመጠማት ፡ የመንከራተት ፡ አደጋ ፡ ከጊዜው ፡ ርዝመት ፡ ጋራ ፡ ተስፋ ፡ አስቆርጦ ፡ መንፈሳቸውን ፡ አላላላውም ። በዚህም ፡ የጠባያቸውን ፡ ብርታት ፡ የሕሊናቸውን ፡ ጥብቅነት ፡ የልባቸውን ፡ ቈራጥነት ፡ እንረዳለን ። ያሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከተድላ ፡ ከደሥታ ፡ ከሞቀ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተለይቶ ፡ በዱርና ፡ በበረሐ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ከኀይለኛ ፡ ባላጋራ ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ቈርጦ ፡ መከላከል ፡ በውነትም ፡ እንደርሳቸው ፡ የመሰለ ፡ ቈራጥ ፡ ጕበዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ቅምጥልነትን ፡ ደስታን ፡ የሚፈልግ ፡ መሪ ፡ ሁሉ ፡ የሚችለውና ፡ የሚሸከመው ፡ አይደለም ።

በጕብዝና ፡ በኵል ፡ ጠንካራነታቸውን ፡ ስንመለከት ፡ ደግሞ ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔርና ፡ እንዲሁም ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ፍጹም ፡ ቀናዒና ፡ ተከላካይ ፡ መሆናቸውን ፡ ከግራኝ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ የተመላለሱት ፡ ንግግር ፡ ያስረዳናል ።

ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ አሸንፎ ፡ በሦስቱ ፡ ሩብ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ግዛቱን ፡ በመሠረተ ፡ ጊዜ ፡ «ከግራኝ ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፡ ከእግዚአብሐር ፡ ጋራ ፡ እንደመዋጋት ይቆጠራል ፡ ይልቅስ ፡ ሴት ፡ ልጅ ምን ፡ ይዳሩልኝና ፡ እንታረቅ ፡ . . . . . . .» ሲል ፡ የዕርቅ ፡ ድርድር ፡ አቅርቦላቸው ፡ ነበር ። እርሳቸውም ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ «ላንድ ፡ ክርስቲያን ፡ ላልሆነና ፡ ሃይማኖቱ ፡ ለልታወቀ ፡ ልጄን ፡ ሰጥቼ ፡ ከመታረቅ ፡ በኀጢአታችን ፡ ምክንያት ፡ በሚቀጣን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መውደቅ ፡ ይሻለናል ። እርሱም ፡ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ ኀይለኞችን ፡ አድክሞ ፡ ለድካማችን ፡ ኀይል ፡ ይሰጣል ፡ . . . . . . .» የሚል ፡ መልስ ፡ ላኩበት ። በዚህም ፡ ፍጹም ፡ የክርስቲያንነትን ፡ መንገድ ፡ ተከታይ ፡ እንደሆኑ ፡ እንረዳለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

ስለ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፤ –ስለ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ መምጣት ፤ -ስለ ፡ አናሳ ፡ (ትግሬ) ፡ ጦርነትና ፡ ስለ ፡ ግራኝ ፡ መሸነፍ ፤–ስለ ፡ ወልፋ ፡ (አሸንጌ) ፡ ጦርነትና ፡ ስለ ፡ ግራኝ ።
ማሸነፍ ፤–ስለ ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ መማረክና ፡ መሞት ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ካገሩ ፡ አብዛኛው ፡ ክፍል ፡ በግራኝ ፡ ቢያዝ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በ፩ ፡ ሺሕ ፡ ፲፭፻፴፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ልጃቸው ፡ ገላውዴዎስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሡ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውም ፡ አጽናፍ ፡ ሰገድ ፡ ተባለ ። በነገሡም ፡ በወሩ ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ከግራኝ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ጀብዱ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ መኳንንቱና ፡ ወታደሩ ፡ በወጣቱ ፡ ንጉሥ ፡ ጕብዝና ፡ ደስ ፡ አላቸው ። በዕድሜም ፡ የበሰሉ ፡ ስላልነበሩ ፡ እናታቸው ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወን

ጊል ፡ በመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሞግዚት ፡ ሆነው ፡ አብረው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ያግዟቸው ፡ ነበር ። የእቴጌይቱም ፡ ትውልዳቸው ፡ ስሜንና ፡ ትግሬ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በቀድሞዎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ እየሸፈቱ ፡ ያስቸግሩ ፡ የነበሩት ፡ የስሜን ፡ አውራጃ ፡ ሕዝቦች ፡ ስለ ፡ እቴጌይቱ ፡ ፍቅር ፡ ለገላውዴዎስ ፡ ቀጥ ፡ ብለው ፡ ተገዙላቸው ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ኀይለኝነት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ተቀነሰ ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በተንቤንና ፡ በሽሬ ፡ የነበረውን ፡ በሔኖክ ፡ ልጅ ፡ በዮናታን ፡ የሚታዘዘውን ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ወግተው ፡ አበረሩ ። አገረ ፡ ገዥ ውን ፡ ዮናታንንም ፡ ገድለው ፡ ከዚያም ፡ የትግሬንና ፡ የስሜንን ፡ ግዛት ፡ ከደላ ደሉ ፡ በኋላ ፡ በክረምቱ ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ሄደው ፡ ተቀመጡ ፡ ስሜ ንም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የናታቸው ፡ አገር ፡ በመሆኑ ፡ ባላባቶቹ ፡ በደኅና ፡ ተቀ በሏቸው ።

በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በናፍቆት ፡ ይጠበቁ ፡ የነበሩት ፡ ፬፻ ፡ (እንደ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ፫፻) ፡ የፖርቱጋል ፡ ወታደሮች ፡ ከህንድ ፡ ተነሥተው ፡ በቤርሙ ዴዝ ፡ እየተመሩ ፡ ምጥዋ ፡ ገቡ ። እነሱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አዳዲስ ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ነበር ፤ ምጥዋም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ የቱርኮችን ፡ ሹም ፡ (ኑር ፡ ኢዶን) ፡ የሚባለ ውን ፡ ጭፍሮቹን ፡ አባረው ፡ እርሱን ፡ ገድለው ፡ ራሱን ፡ ቆርጠው ፡ ለእቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ላኩላቸው ። ከዚያም ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ በሚባለው ፡ እየተመሩ ፡ መጥተው ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ላይ ፡ ከእቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ። የፖርቱጊዞቹም ፡ መምጣት ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ በክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። ኀይላቸውም ፡ ተቀሰቀሰ ። የእስላሞቹ ፡ ኃይል ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደከመ ። ቀድሞ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ እየከዱ ፡ በግዴታም ፡ በፈቃድም ፡ ለግራኝ ፡ ገብተው ፡ የነበሩትም ፡ እየተመለሱ ፡ ለእቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ መግባት ፡ ዠመሩ ። የቀረውም ፡ የጦርነትን ፡ ነገር ፡ እየተወ ፡ በየአገሩ ፡ ይመለስ ፡ ዠመር ።

እቴጌይቱም ፡ እንግዶቹን ፡ በመልካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀብለው ፡ ምግባቸ ውንም ፡ እያዘጋጁ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ አሰኝተዋቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፖርቱጊዞቹም ፡ እቴጌይቱን ፡ ይዘው ፡ ለመጡበት ፡ ጦርነት ፡ ዝግጅት ፡ አደረጉ ።

የዚህንም ፡ ወሬ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከነሕዝባቸው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ግራኝም ፡ ከደባሩአ ፡ ወይም ፡ ከደብረ ፡ ዳሞ ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወን ጌልና ፡ ፈረንጆቹ ፡ ከስሜን ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ መጥተው ፡ የተገናኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልችላቸውም ፡ ብሎ ፡ ሁለቱንም ፡ በየተራ ፡ ለየብቻ ፡ መዋጋት ፡ ፈለገ ። ስለዚህ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ወደ ፡ ሐማሴን ፡ በቶሎ ፡ ተጕዞ ፡ አካለ ፡ ጕዛይ ፡ ደረሰ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በ፩ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻፴፬ ፡ ዓ. ም. በመጋቢት ? ፡ ወር ፡ በተለይ ፡ አናሳ ፡ በሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ከንድ ፡

ወገን ፡ ፖርቱጊዞቹና ፡ የእቴጌ ፡ ሰዎች ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ጦርነት ፡ ገጠሙ ። ፖርቱጊዞችም ፡ ይዘው ፡ የመጡትን ፡ መድፍ ፡ በእስላሞች ፡ ላይ ፡ በተኰሱ ፡ ጊዜ ፡ በእስላሞች ፡ ሰፈር ፡ የመዠመሪያው፡ድንጋጤ ፡ ወረደ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ከልቡ ፡ ዠግንነት ፡ የሚሰማው ፡ ነበርና ፡ ራሱም ፡ በርትቶ ፡ እየተዋጋ ፡ ጭፍሮቹንም ፡ አይዟችሁ ፡ እያለ ፡ ያደፋፍራቸው ፡ነበር ። በመጨረሻም ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አነጣጥረው ፡ ሲተኰሱበትና ፡ በጥይት ፡ እግሩን፡ ተመቶ፡ ሲቈስል ፡ ፈረሱም ፡ በጥይት ፡ በትር ፡ ተመቶ ፡ ሁለቱም ፡ ወደቁ ።

ግራኝንም ፡ እንዳይማረክ ፡ ጭፍሮቹ ፡ በቶሎ ፡ አንሥተው ፡ ወሰዱት ። የግራኝም ፡ ሰዎች ፡ ከሐማሴን ፡ ወደ ዞብል ፡ መጡ ። በዚያም ፡ ሆኖ ፡ ለየመን ፡ ሡልጣን ፡ መሣሪያና ፡ ወታደር ፡ ላክልኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። የየመንም ፡ ሡልጣን ፡ ክርስቲያን ፡ የሆነው ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፤ ክርስቲያን ፡ የሆነውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ መርዳቱን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያውቃልና ፤ ከየመን ፡ ፱ ፡ ሺሕ ፡ ቱርኮችና ፡ ዐረቦች ፡ ላከለት ። እነርሱም ፡ ከመቃዘዛቸው ፡ በላይ ፡ የምርኮ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ እንዳለፈው ፡ ሁሉ ፡ እናገኛለን ፡ በማለት ፡ መሣሪያ ፡ እየያዙ ፡ መጥተው ፡ ከግራኝ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ።

ፖርቱጊዞችና ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ ከአከለ ፡ ጉዛይ ፡ ወደ ፡ ወልፋ ፡ (አሸንጌ) መጡ ። ግራኝም ፡ ከነጭፍራው ፡ በ፭ ፡ ሺሕ ፡ ፳፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ተጋጠማቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መሣሪያው ፡ ከመሣሪያው ፡ ወታደር ፡ ከወታደሩ ፡ ሲመዛዘን ፡ ጦርነቱ ፡ የበረታ ፡ ሆነ ። ቀድሞ ፡ የነበሩትና ፡ አዲስ ፡ የመጡት ፡ እስላሞች ፡ ግራኝን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እየተፎካከሩ ፡ በኀይል ፡ ይዋጉ ፡ ዠመር ።

የፖርቱጊዞቹ ፡ መሪም ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ የታወቀ ፡ ዠግና ፡ ነውና ፤ ጭፍሮቹን ፡ እየመራ ፡ እሬት ፡ ቀድሞ ፡ በታላቅ ፡ ዠግንነት ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ እስላሞች ፡ እሮምታ ፡ ስለ ፡ ተኰሱበት ፡ ክፉኛ ፡ ቈስለና ፡ ወደቀ ። እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልም ፡ ከውጊያው ፡ ኋላ ፡ እየተከተሉ ፡ ቍስለኛውን ፡ እያስታመሙ ፡ ወታደሩን ፡ ያበረታቱ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዶም ክርስቶፎሮስ ፡ ጭፍሮች ፡ ከቀሩት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኀይላቸው ፡ ስለ ፡ ተቀነሰ ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ጊዜው ፡ ስለ ፡ መሸ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማፈግፈግ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ።

ቍስለኛውን ፡ ዶም ፡ ክርስቶፎሮስን ፡ የሚወዱት ጭፍሮቹ ፡ እነሡትና ፡ ወደ፡ ኋላ ፡ ሸሸት ፡ ተዠመረ ። በኋላም ፡ ፖርቱጊዞቹ ፡ ባንድ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ እስቀምጠው ፡ የዶም ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማን ፡ ቍስል ፡ሲያስሩ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ባጠገባቸው ፡ ስታልፍ ፡ አባራሪዎቹ ፡ እስላሞች ፡ እሷን ፡ አይተው ፡ ሲከታተሉ ፡ ወዲያው ፡ ክርስቶፎሮስን ፡ አግኝተው ፡ ማረኩትና ፡ ታላቅ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ዘንድ ፡ ደረሰባቸው ። ይህችን ፡ ሴት ፡ እስላሞች ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ያለበትን ፡ ለማሳየት ፡ ከነቢዩ ፡ መሐመድ ፡ የተላከች ፡ ነች ፡ ይሏታል ። ባንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ ግን ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ እንደ ፡ ወዳጅ ፡ ይዟት ፡ የነበረች ፡ የቱርክ ፡ ሴት ፡ነበረችና ፡ በኋላ ፡ እሱን ፡ ከድታ ፡ የሄደበትን ፡ ዱካ ፡ ለወገኖቿ ፡ ማሳየቷ ፡ ነው ፡

የሚል ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። ምትሀትም ፡ ነች ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፤ ርግጠኛው ፡ ግን ፡ አይታወቅም ።

እስላሞች ፡ ቈስሎ ፡ የደከመውን ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማን ፡ ይዘው ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ ወስደው ፡ በግራኝ ፡ ፊት አቆሙት ፤ ማናቸውንም ፡ ውርደት ፡ ፈጸሙበት። እርሱ ፡ ግን ፡ በጫማ ፡ ጥፊ ፡ ሲደበድቡት ፡ ሲተፉበትና ፡ ሲሰድቡት ፡ ሳይፈራና ፡ ሳይንቀጠቀጥ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ በወታደርነትና ፡ በኵራት ፡ ዐይኖቹ ፡ ይመለከታቸው ፡ ነበር ። እንዲምሩትም ፡ ራሱን ፡ ዝቅ አድርጎ ፡ አልተለማመጣቸውም ፡ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ቈስለው ፡ የነበሩትን ፡ የግራኝ ፡ መሐመድን ፡ አጎትና ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ ቍስላቸውን ፡ እንዲያክምና ፡ እንዲያስታምም ፡ ቢጠይቁት ፡ አላደርገውም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ ፖርቱጊዞችና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሸሹበትን ፡ ስፍራ ፡ አሳየን ፡ ቢሉት ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠም ። ግራኝም ፡ እስላም ፡ ሁንና ፡ ልማርኽ ፡ ብሎት ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ያለ ፡ ቈራጥ ፡ ዠግና ፡ በፍርሃት ፡ ሃይማኖቱን ፡ መለወጥ ፡ አይሆንለትምና ፤ እንቢ ፡ አለ ። እንዲያውም ፡ ግራኝ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ሃይማኖትኽን ፡ በእስላምነት ፡ ለውጥና ፡ ልማርኽ ፡ ሲለው ፡ ምራቁን ፡ እንደ ፡ ቃሰረ ፡ ተፋበት ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በብዙ ፡ ሀይነት ፡ በትር ፡ እየ ደበደቡ ፡ እፊቱም ፡ ላይ ፡ እየተፉ ፡ ከተጫወቱበት ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ራሱ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ በመጥረቢያ ፡ ራሱን ፡ ቈረጠው ። የተቈረጠውንም ፡ የዚህን ፡ የዠግና ፡ ራስ ፡ ወደ ፡ ቆስታንቲኖፕል ፡ (ቍስጥንጥንያ) ፡ ለቱርክ ፡ ሡልጣን ፡ ላከለት ። ለቱርክ ፡ ሡልጣን ፡ መላኩም ፡ ዋና ፡ የርዳታው ፡ ደጋፊ ፡ በመሆኑ ፡ ግዳይ ፡ በመጣል ፡ ደጋፊውን ፡ ለማስደሰት ፡ ሲል ፡ ነው ።

ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሆኖ ፡ ከህንድ ፡ መምጣቱ ፤ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ጦርነቱ ፡ በዠግንነት ፡ ለላከው ፡ መንግሥትና ፡ ለመጣበት ፡ የሃይማኖት ፡ ጕዳይ ፡ ሳያወላውል ፡ መዋጋቱ ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ከምርኮ ፡ በኋላ ፡ በግራኝ ፡ ፊት ፡ በተደ ረገበት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥቃይ ፡ ከሚዛኑ ፡ ባለመራቁ ፡ የጠባዩ ፡ ጽናትና ፡ ጥብቅ ነት ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌነቱ ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

### ስለ ፡ ወገራና ፡ ስለ ፡ ደንቢያ ፡ (ዘንተራ) ፡ ጦርነት ፤—ስለ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ መሞት ፡ —በቤርሙዴዝና ፡ በዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ተነሣው ፡ ክርክር ።

የክርስቶፎሮስ ፡ ሞት ፡ ጦርነቱን ያላላዋል ፡ በማለት ፡ እስላሞች ፡ ሁሉ ፡ ደስታ ፡ አድርገው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ፋንታ ፡ የርሱ ፡ ሞት ፡ ለቀሪዎቹ ፡ የባሰ ፡ ጠላትነትና ፡ እልክን ፡ አተረፈላቸው ። በዚሁ ፡ ሰሞን ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በበኩ ላቸው ፡ ጦራቸውን ፡ ሰብስበው ፡ ከሰሜን ፡ መጥተው ፡ ከናታቸው ፡ ከእተጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልና ፡ ከፖርቱጊዞቹ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ። በአለቃቸው ፡ መሞት ፡ አዝነው ፡ የነበሩት ፡ ፖርቱጊዞችም ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ንጉሡም ፡ ከሞት ፡ ለተረፉት ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ብዙ ፡



ክርስቶፎሮስ ፡ ደገማ ፡ ሊገደል ፡ በግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ (በመላ ፡ የተ ማስ)

የወርቅ ፡ ጉርሻ ፡ ሰጥተው ፡ በክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ ሞት ፡ ማዘናቸውንም ፡ ገለጹላቸው ። ዐፄ ፡ ገላውዴዎስና ፡ ፖርቱጊዞቹ ፡ እቴጌዪቱም ፡ ተገናኝተው ፡ ኀይላቸውን ፡ ማጠንከራቸው ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከሐማሴን ፡ ከትግሬ ፡ ከጐጃም ፡ ከበጌምድር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየመጣ ፡ ተሰበሰበ ። ብዙዎቹም ፡ ግራኝን እየከዱ ፡ መጥተው ፡ ከወጣቱ ፡ ንጉሥ ፡ ተገናኙ ።

ዐፄ ገላውዴዎስም ፡ የግራኝን ፡ ጭንቅላት ፡ ለሚያመጣልኝ ፡ እኅቴን ፡ እድርለታለሁ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ አደረጉ ፡ ይባላል ። በኋላም ፡ በሰሜንና ፡ በደንቢያ ፡ መከከል ፡ ባለው ፡ አገር ፡ በወገራ ፡ ላይ ፡ ከግራኝ ፡ ጭፍሮች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረና ፡ እስላሞች ፡ ድል ፡ ሆኑ ። የግራኝ ፡ መሐመድም ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እነሲዲ ፡ መሐመድ ፤ እነገራድ ፡ ዑስማን ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ፤ የተረፉትም ፡ ሸሹ ። ገሚሶቹም ፡ በንገታቸው ፡ ድንጋይ ፡ እያሰሩ ፡ ምሕረት ፡ እየለመኑ ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ መጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መሐመድ ፡ ግራኝ ፡ አሠርቶት ፡ የነበረውን ፡ ቤትና መስጊድ ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ሰዎች ፡ አፈረሱት ፡ ዕቃቸውና ፡ መሣሪያቸውም ፡ እንዲሁ ፡ ቤትራው ፡ መዘረፍና ፡ መበዝበዝ ፡ ዠመረ ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ግራኝ ፡ ወደ ፡ ዞብል ፡ ሄዶ ፡ ነበርና ፡ በዚያው ፡ ሳለ ፡ ይኽንን ፡ ሁሉ ፡ ሰማ ፡ በቍጣም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ደንቢያ ፡ መጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ የወጣትነት ፡ ዕድሜው ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ሲዘቀዘቅ ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ የነበረውም ፡ አፍለኛ ፡ ጒልበቱ ፡ ከጊዜው ፡ ጋራ ፡ እንዳለፈበት ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ የመጨረሻ ፡ ኀይሉን ፡ ለመግለጽ ፡ ከዞብል ፡ በግሥጋሤ በጣና ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወደሚገኘው ፡ ወደ ፡ ፎገራ ፡ መጥቶ ፡ ከኢትዮጵያውያንና ፡ ከፖርቱጊዞቹ ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ተሰለፈ ። የርሱም ፡ ጦር ፡ በግምት ፡ ከ፲፫ ሺህ ፡ በላይ ፡ ነበር ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ በጠቅላላው ፡ ፰ ፡ ሺህ ፡ የእግረኛ ፡ ፭፻ የፈረሰኛ ፡ ወታደር ፡ ነበራቸው ፡ ጥቂት ፡ ቀንም ፡ እንደ ቈዩ ፡ ጦርነቱ ፡ በሺህ ፡ ፭፻ ፡ ፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ በዚሁ ፡ በፎገራ ፡ ዘንተራ ፡ በተባለው ፡ ተራራ ሥር ፡ ተዠመረ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ከክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ ቀጥሎ ፡ ዶን ፡ አልፎንዝ ፡ ካልዴይራ ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ከፈረስ ፡ ወድቆ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ በርሱ ፡ እግር ፡ የተተካው ፡ አሪዩስ ፡ ዲያዝ ፡ የሚባለው ፡ ጭፍሮቹን ፡ ይዞ ፡ አብሮ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ።

ግራኝም ፡ ጕብዝናውን ፡ አይተው ፡ ጭፍሮቹ ፡ እንዲበረቱ ፡ በመዠመሪያው ፡ ግንባር ፡ ቀድሞ ፡ በዠግንነት ይዋጋ ፡ ዠመር ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ፔድሮስ ፡ ሌዎን ፡ የሚባል ፡ የሻቱ ፡ የክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ አሽከር ፡ ግራኝ መሐመድን ፡ አየውና ፡ አነጣጥሮ ፡ ተኵሶ ክፉኛ አቈሰለው ። ግራኝ መሐመድም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ለሞት ፡ እስኪደርስ ፡ ቢቈስል ፡ ጭፍሮቹ ፡ እሱን አይተው ፡ እንዳይባቡ ፡ «በርቱ» ፡ የሚል ቃል ፡ ተናገረና ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ እየተራመደ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡

በቊጥቋጦ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ። በኋላም ፡ ይኸው ፡ አቊሳዩ ፡ በሩቅ ፡ የሄደበትን፡
ቦታ ፡ ተከታትሎ ጨርሶ ፡ ገደለው ። ፖርቱጊዞችና ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ «የጌታ
ኸን ፡ ደም ተበቀልኸለት» ፡ ብለው ፡ ሌዎንን ፡ አመሰገኑት ። ነገር ፡ ግን ፡ ጭን
ቅላቱን ፡ ቈርጦ ፡ በፈረስ ፡ እየጋለበ ፡ ለንጉሡ ፡ ያመጣው ፡ ፩ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡
ነው ፤ እርሱም ፡ የንጉሡን ፡ እኅት ፡ አገባለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ አድርጎ ፡ ነው ።
ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሬሳ ፡ ራስ ፡ መቊረጥና ፡ ሕይወት ፡ ያለውን ፡ መግደል ለየብቻው ፡
ስለ ፡ ሆነ ፡ ይልቁንም ፡ ፔድሮስ ፡ ሌዎን ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ የግዳዩን ፡
ምልክት ፡ የግራኝን ፡ ገሮሮ ፡ ቈርጦ ፡ ይዞ ፡ ኑሮ ፡ ለንጉሡ ፡ ስለ ፡ አሳየ ፡ ኢትዮ
ጵያዊው ፡ አለመግደሉ ፡ ታወቀ ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ብዙ ፡ የወርቅ ፡
ስጦታ ፡ አገኘ ፡ እንጂ ፡ የንጉሡን ፡ እኅት ፡ ሊያገባ ፡ አልቻለም ። ግራኝም ፡ የሞ
ተበት ስፍራ ፡ እስከሁን ፡ ድረስ ፡ «ግራኝ ፡ በር» ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል ። የገሮግና
ውና ፡ የኃይለኛው የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ሕይወት ፡ በዚህ ፡ ተፈጸመ ።

ግራኝ ፡ መሐመድ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ጭፍሮቹ ፡ ባለቤቱን ፡ ድል ፡ ወንበራን
ተከትለው ፡ ወደ ፡ አትባራ ፡ ከዚያም ፡ በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ ሸሹ ፡ የቀ
ሩትም ፡ በአንገታቸው ፡ ገመድ ፡ እያሰሩ ፡ ድንጋይ ፡ እየተሸከሙ ፡ መጥተው ፡
በንጉሡ ፡ በገላውዴዎስ ፡ ፊት ፡ እየተደፉ ፡ ምሕረት ፡ እየለመኑ ፡ ይቅርታ ፡ ተደረ
ገላቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ዮራም ፡ የተባለው ፡ ክርስቲያን ፡ ጌታውን ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡
ድንግልን ፡ ገና ፡ አስቀድሞ ፡ ከድቶ ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዞሮ ፡ ምሥጢርም ፡ እየገ
ለጸ ፡ መንገድም ፡ እየመራ ፡ ወገኖቹን ፡ በጣም ፡ የጐዳ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምሕረት ፡
አይገባውም ፡ ተባለና ፡ ተገደለ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሙሣሪያውን ፡ እየሰጠ ፡ ተገዥ
ነቱን ፡ አምኖ ፡ ለሚገባ ፡ ምሕረት ፡ አድርጌለታለሁ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ አድር
ገው ፡ ነበርና ፤ እንደዚሁ ፡ የባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ አባት ፡ ወደ ፡ ግራኝ ፡ ዞሮ ፡
ሲኖር ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበረውን ፡ የግራኝን ፡ ልጅ ፡ አስረከበና ፡
ታርቆ ፡ ገባ ። እንደዚሁም ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ውስጥ ፡ ግራኝና ፡ ፖርቱጊዞች ፡
መዠመሪያ ፡ ተዋግተው ፡ ክርስቶፎሮስ ፡ ደጋማ ፡ ቈስሎ ፡ በተያዘበት ፡ ቀን ፡
አብሮ ፡ ክርስቶፎሮስን ፡ በመማረክ ፡ ከእስላሞች ፡ ጋራ ፡ ተባብሯል ፡ የተባለው ፡
ታርቆ ፡ ሲገባ ፡ ንጉሡ ፡ ለሰጡት ፡ ዐዋጅ ፡ ምክንያት ፡ ምሕረት ፡ አድርገውለት ፡
ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ያለቃቸው ፡ መሞት ፡ ጸጸቱ ፡ ከሕሊናቸው ፡
ውስጥ ፡ አልበረደም ፡ ነበርና ፤ ይኸንኑ ፡ ሰው ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡
በጩቤ ፡ ወግተው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ ተልኮ ፡
ፖርቱጊዞችን ፡ ለርዳታ ፡ ባስመጣው ፡ በቤርሙዴዝና ፡ በዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ መካ
ከል ፡ የፖሊቲክና ፡ የሃይማኖት ፡ ጭቅጭቅ ፡ ተነሣ ። ምክንያቱም ፡ ቤርሙዴዝ ፡
ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ተልኮ ፡ ሮማ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡
በኢትዮጵያ ፡ ላይ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ ሥልጣን ፡ ያገኛል ፡ ሲል ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡
ወይም ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ተልኮ ፡ ይሁን ፡ ይኸንኑ ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ነበር ፤

እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ ሊስቦን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ባጋማሹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ገዥነት ፡ በወደቦቿ ፡ በምጥዋና ፡ በኤርትራም ፡ ላይ ፡ ጥቅምን ፡ ያገኛል ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፤ አሁንም ፡ አባትዎ ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ተስፋ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግሚሱ ፡ ለፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይሰጥ ። የኢትዮጵያም ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ አቡን ፡ ከእስክንድርያ ፡ መምጣቱ ፡ ቀርቶ ፡ ከሮማ ፡ ይምጣ ፡ እኔም ፡ የመዠመሪያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አቡን ፡ ልሁን ፡ ብሎ ፡ ገና ፡ ግራኝ ፡ ሳይሞት ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶላቸው ፡ ንጉሡም ፡ በፍጹም ፡ ይህ ፡ ሁለቱ ፡ አሳብ ፡ አይቻልም ፡ ብለውት ፡ የነበረውን ፡ ግራኝ ፡ ከሞተ ፡ በኋላና ፡ ይልቁንም ፡ እንደ ፡ ተለመደ ፡ ግብጻዊ ፡ አቡን ፡ ለጳጳስነት ፡ ከእስክንድርያ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ቀሰቀሰ ፤ እርሳቸውም ፡ መዠመሪያ ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ መልስ ፡ ወዳጅ ፡ ለወዳጁ ፡ እንደሚረዳዳ ፡ እንደዚሁ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ለክርስቲያኒቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ርዳታ ፡ ባደረገበት ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ ለማዛወር ፤ ከመንግሥቱም ፡ ግሚሱን ፡ መሬት ፡ ቈርጦ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ የመጨረሻውን ፡ መልስ ፡ ሰጡት ። ከሊቃውንቱም ፡ ወገን ፡ አባ ፡ ዝክሬና አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ስለ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖትና ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመደባለቅም ፡ እንደማይቻል ፡ አጥብቀው ፡ ተከራከሩት ። እርሱም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ተቈጥቶ ፡ ስድብ ፡ እየጨመረ ፡ በኀይል ፡ ሲናገር ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከሮችና ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ጐትተው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጡት ፡ በዚህ ፡ ሥራው ፡ ቤርሙዴዝ ፡ በእስራት ፡ ስም ፡ ወደ ፡ ከፋ ፡ ተልኮ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዲያዝ ፡ እግር ፡ የተሾመው ፡ አሪዩስ ፡ ሱዛ ፡ ንጉሡን ፡ ስለ ፡ ለመናቸው ፡ ከዚያ ፡ ተለቀቀና ፡ ከሥር ፡ (ወይም ፡ ከስድስት) ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ጋራ ፡ በደባሩአና ፡ በጎአ ፡ በህንድ ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ ፖርቱጋል ፡ ተመለሰ ።

የፖርቱጊዞች ፡ አለቃ ፡ አሪዩስ ፡ ዲያዝ ፡ በፊት ፤ በኋላም ፡ አሪዩስ ፡ ሱዛና ፡ ግሚሶቹ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በዚህ ፡ ባገርና ፡ በሃይማኖት ፤ ጉዳይ ፡ እውነትና ፡ የሚገባ ፡ ክርክር ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ ገልጸው ፡ በሳብና ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተባብረው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ከወገናቸው ፡ ከቤርሙዴዝ ፡ አሳብ ፡ ጋራ ፡ ባሳብ ፡ አልተደረቡም ፡ ነበር ።

ንጉሡም ፡ የቀሩት ፡ ሲሄዱ ፡ እርሳቸውንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ መርጠው ፡ ለቀሩት ፡ ፖርቱጊዞች ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ቸርነት ፡ አደረጉላቸው ።

1| ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ የተማረከውን ፡ ወርቅና ፡ ሀብት ፡ ለቀሩትና ፡ ለተመለሱትም ፡ አደሏቸው ።

2| በግብርም ፡ ጊዜ ፡ በበዓልም ፡ ቀን ፡ እከፍታ ፡ ቦታ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አደረጉ ።

3| ሰፋፊም ፡ መሬት ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ ሰጥተው ፡ ባለጕለት ፡ አደረጓቸው ።

እነሱም ከሄዱት ፡ በቀር ፡ የቀሩት ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ በተደረገላቸው ፡ ደግ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ተሰኝተው ፡ ከወይዛዝሩም ፡ እየመረጡ ፡ በሚስትነት ፡ አግብተው ፡ በደስታ ፡ ተቀመጡ ። ይልቁንም ፡ አለቃቸው ፡ አሬዩስ ፡ ዲያዝ ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ አርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ዞሮ ፡ ስሙ ・ ማርቆስ ፡ ተብሎ ፡ እስከ፡ መጨረሻ ፡ ለንጉሡ ፤ አገልጋይና ፡ ወዳጅ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በመጨረሻውም ፡ ከንጉሡ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ከሸፈቱ ፡ ጋሎች ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ። በር ሱም ፡ እግር ፡ እላይ ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰው ፡ አሬዩስ ሱዛ ፡ ተሾሞ ፡ እርሱም ፡ እንደ ፡ ሹመት ፡ አባቱ ፡ የንጉሡ ፡ ባለሚል ፡ ነበር ።

ቤርሙዴዝ ፡ ቀድሞ ፡ ከሻቹ ፡ ከዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እንደ ፡ ተሰ ጠው ፡ ተስፋ ፡ እኔም ፡ ጳጳስ ፡ ልሁን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ካቶሊካዊት ፡ ትሁን ፡ ብሎ ፡ ንጉሡንም ፡ ዘለፋና ፡ ስድብ ፡ እየጨመረ ፡ በድ ፍረት ፡ እየተናገረ ፡ ባደረገው ፡ ክርክር ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ከተነሡ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓ ፊዎች ፡ ውስጥ ፡ እነ ፡ ሉዶልፍ ፡ እነ ፡ ብሩስ ፡ እነ ፡ ባሴት ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ መሥራቱን ፡ እየገለጹ ፡ ነቅፈውታል ። ዐፄ ፡ ገላውዴዎስንም ፡ ያገራቸውን ፡ሙሉ ፡ ነፃነትና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመጠበቅ ፡ በሚገባ ፡ ተከራክረ ዋል ፡ እያሉ ፡ ጽፈዋል ። ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኩልቦ ፡ የሚባሉት ፡ የካቶሊክ ፡ ሚሲዮናዊ ፡ ግን ፡ ያባታቸውን ፡ ቃል ኪዳን ፡ በመጠበቅ ፡ ፈንታ ፡ ያፈረሱት ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ይነቀፋሉ ፡ እንጂ ፡ ቤርሙዴዝ ፡ አይነቀፍም ፡ ሲሉ ፡ ጽፈዋል ። የፖሊቲክና ፡ የሃይማኖት ፡ ታሪክ ፡ ከሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ፪ኛውን ፡ ቮሊም ፡ ከ፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፻፳፱ ፡ ገጽ ፡ ያለውን ፡ ተመልከት ።

እርሳቸውም ፡ ይህን ፡ መጻፋቸው ፡ የሃይማኖትና ፡ የቅስና ፡ ጓደኛቸውን ፡ ለመደገፍ ፡ ያደረጉት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሕዝቡና ፡ ቤተ፡ ክህነቱ ድንገት ፡ የቤርሙዴዝ ፡ አሳብ ፡ ተፈጽሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት፡ ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ ተለውጦ ፤ አገርም ፡ ተቈርጦ ፡ የተሰጠ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከግራኝ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ሁከት ፡ ተነሥቶ ፡ ይሸበራል ፡ እንጂ ፤ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አንቀበልም ፡ እያሉ ፡ ሲያስቡ ፤ ንጉሡ ፡ ማንኛውንም ፡ ተከራክረው፡ ነገሩ ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ በሰላም ፡ ስላለቀ ፡ ደስታ ፡ ሆነና ፡ ግማሹ ፡ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ ተግባሩ ፡ መመለስ ገሠመረ ።

ፖርቱጊዞች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ወገን ለሆነው ፡ ለኢትዮ ጵያ ፡ መንግሥት ፡ የረዱት ፡ እንግሊዞች ፡ በሺሕ ፡ ፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከረ ዱት ፡ ርዳታ ፡ ጋራ ፡ የሚገናኙበትና ፡ የሚለያይበት ፡ መንገድ ፡ አለው ። የሚለያይበት ፡ የእንግሊዝ ፡ ርዳታ ፡ ከባሕር ፡ ማዶ ፡ ለመጣ ፡ ለውጭ ፡ ጠላት ፡ በመሆኑ ፡ የፖርቱጊዞች ፡ ርዳታ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ በሃይማኖትና፡ በጐሣ ፡ ቢለያይ ፡ የአዳልና ፡ የሱማሌ ፡ ሕዝብ ፡ ከክርስቲያኑ ፡ ያማራና ፡ የትግሬ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በዘር ፡ በወሰን ፡ የሚገናኝ ፡ በኢትዮጵያዊነቱም ፡ ከሚመሳሰለው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በተደረገው ፡ ውስጣዊነት ፡ ባለው ፡ ጦር

ነት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። የሁለቱ ፡ መንግሥታትና ፡ ርዳታ ፡ የሚገናኝበትን ፡ መንገድ ፡ ደግሞ ፡ የፈለግን ፡ እንደሆን ፡ የእንግሊዝን ፡ ርዳታ ፡ የሳበልን ፡ ጀርመንና ፡ ኢጣሊያ ፡ ተባብረው ፡ በእንግሊዝና ፡ በጓደኞቹ ፡ ላይ ፡ በጦርነትም ፡ በጥቅምም ፡ በመነሣታቸው ፡ ሲሆን ፡ የፖርቱጋልንም ፡ ርዳታ ፡ የጨመረልን ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ በየወደቦቹ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ ጥቅም ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ እየተዋጋ ፡ በመርከከሩ ፡ ነው ። ዋናው ፡ የርዳታው ፡መሠረት ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሲዋጋ ፡ ፖርቱጊዞች ፤ በኋላኛው ፡ ዘመን ፡ ደግሞ፡ ከኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሲከራከር ፡ እንግሊዞች ፡ ሲረዱ ፡ በጦርነቱ ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱም ፡ ረዳቶች ፡ ወገን፡ በግልጽም ፡ በምሥጢርም ፡ ክብርና ፡ ጥቅምን ፡ ለማግኘት ፡ ክርክር ፡ ቢቀርብ ፡ የሚያስደንቅ ፡ አይዶለም ፡ የሃይማኖትም ፡ የቃል ፡ ኪዳንም ፡ መተሳሰር ፡ ቢኖር ፡ ያለልዩ ፡ ጥቅም ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ሊረዳው ፡ አለመቻሉ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የታወቀና ፡ የተለመደ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ መከከል ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ የሚነሡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሪዎች ፡

ሀ ርዳታ ፡ የሚመጣበትን ፡ አሳብ ፡ ማወቃቸው ፡

ለ| በርዳታው ፡ ለመጠቀም መቻላቸው ፡

ሐ| ከጦርነቱም ፡ በኋላ ፡ ርዳታው ፤ የሚያስከትለውን ፡ መዘዝ ፡ ለማጥፋት በጥብቅ ፡ መከራከራቸው ፡

መ| ከክርክሩም ፡ በኋላ ፡ አገራቸውን ፡ ከወረራም ፡ከችግርም ፡ አድነው ፡ ሙሉውን ፡ ነፃነት ፡ ለመጠበቅ ፡ መቻላቸው ፡ ያስመሰግናቸዋል ።

ሠ| ኢትዮጵያም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ለደኅንነት ፡ ሰበብና ፡ ምክንያት ፡ ስለሚያጋጥማት ፡ ዕድላምነቷ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።

ወደዋናው ፡ አሳብ ፡ እንመለስ ። እንግዴህ ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ የላከው ፡ ርዳታ ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጋራ ፡ ተባብሮ ፡ ባደረገው ፡ ትግል ፡ ግራኝ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ሲወድቅ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አሳብና ፡ ምኞት ፡ ከልብ ፡ ባይጠፋ ፡ የፖርተጋል ፡ መንግሥት ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እናግኝ ፡ በማለት፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ አጥብቀው ፡ መከራከርም ፤ መዋጋትም ፡ አልፈለጉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ያንዱ ፡ ሰው ፡ የቤርሙዴዝ ፡ ወይም ፡ የጥቂት ፡ ጓደኞቹ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንኳን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የመጡት ፡ አብዛኞቹ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ እንኳ ፡በዚህ ፡ ነገር ፡ አልጸኑበትም ፡ ከነርሱም ፡ መከከል ፡ አላይ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ እየተደረቡ ፡ ወገናቸውን ፡ ቤርሙዴዝን ይከራከሩት ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በበላይ ፡ ሥልጣን ፡ አግኝቶ ፡ መግዛትና ፡ ሃይማኖትን ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ለማስፋፋት ፡ የተሞከረው ፡ ባይቻልም ፤ በሰላምና ፡ በወዳጅነት ፡ ገብቶ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመመሥረት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደሚያስረዳን ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ብዙ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ልከዋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

## አዲስ ፡ ስለ ፡ መጡት ፡ ሚሲዮናውያን ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ መንግሥታቸውን ፡ ከደላደሉ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሰላማዊ ፡ ሥራው ፡ እንዲመለስ ፡ አደረጉ ፤ ወታደር ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ግን ፡ የተረፈውን ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ እንዲከታተል ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡ ። በግራኝ ፡ ጊዜም ፡ የፈረሱትና ፡ የተቃጠሉት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ ገዳማት ፡ ተመልሰው ፡ እንዲሠሩ ፡ ትእዛዝ ፡ በያለበት አስተላለፉ ። ባማራ ፡ ሣይንትም ፡ የተደባበ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባማረ ፡ ጌጥ ፡ ራሳቸው ፡ አሠሩ ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ ቤርሙዴዝ ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ተጣልቶ ፡ ወዳገሩ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መስፋፋት ፡ የተደከመው ፡ ድካም ፡ በከንቱ ፡ እንዳይቀር ፡ በቤርሙዴዝ ፡ ፈንታ ፡ ዐመላቸውና ፡ ትምህርታቸው ፡ ከርሱ ፡ የተሻሉ ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲያስፋፉ ፡ በማለት ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥና ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ መመካከር ፡ ገሥመሩ ።

ላገባብም ፡ እንዲመች ፡ ሲሉ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ፫ኛ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሚሲዮናውያንን ፡ ከመላካቸው ፡ በፊት ፡ ሮማ ፡ ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አጠገብ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ጉዳይ ፡ ያገሩ ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የሚጠናበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲከፈት ፡ አድርገው ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ እየተመረጡ ፡ ገብተው ፡ ያጠኑ ፡ ነበር ። ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ዣን ፡ አኔዝ ፡ ባሬቶ ፡ አንድሬ ፡ አቪዬዶ ፤ ሚልኪዎሬ ፡ ካርኔሮ ፡ የሚባሉ ፡ ከዐሥር ፡ ሌሎች ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ ወንጌል ፡ እንዲሰብኩና ፡ እንደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ አሳብ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቆች ፡ እንዲሆኑ ፡ በ፫ኛ ፡ ጳውሎስ ፡ ተከታይ ፡ በዩልዮስ ፡ ፫ኛ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ዘመን ፡ ተመረጡ ። ከነዚሁም ፡ በመዠመሪያ ፡ ስሙ ፡ የተጠራውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፓትርያርክ ፡ (በትረ ፡ ያሬክ) ፡ ብለው ፡ በራሳቸው ፡ አሳብ ፡ ሾሙት ፡ እንደዚሁም ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ የመዠመሪያው ፡ ፓትርያርክ ፡ ቢሞት ፡ እንደየማዕርጋቸው ፡ በሹመት ፡ እንዲከተሉት ፡ አድርገው ፡ የኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ አሰናበቷቸው ፤ የነሱም ፡ ክፍላቸው ፡ ኢየሱሳውያን ፡ (ጀሱዩት) ፡ ከተባሉት ፡ ወገን ፡ ናቸው ።

ሚሲዮናውያኖቹ ፡ ከሮማ ፡ ተነሥተው ፡ ባ፩ ፡ ሺሕ ፡ ፲፭፻፴፫ ፡ ዓ፡ ም፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ህንድ ፡ ደረሱ ፤ የህንድም ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ደብዳቤ ፡ ለዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ አስቀድሞ ፡ ቀጥሎም ፡ ሚሲዮናውያኑን ፡ ከብዙ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ጋራ ፡ ላከቸውና ፡ መጥተው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስም ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ባደረገው ፡ የወታደር ፡ ርዳታው ፡ ውለታ ፡ ምክንያት ፡ የመጡትን ፡ ኢየሱሳውያን ፡ በመልካም ፡ አቀባበል ፡ ተቀበሏቸው ። ሲመጡም ፡ የመዠመሪያው ፡ ፓትርያርክ ፡ ቀርቶ ፡ እንድርያስ ፡ አቤዶ ፡ ፓትርያርክ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ።

ጥቂት ፡ ቀንም ፡ ውለው ፡ እንዳደሩ ፡ በእንግዶቹና ፡ ከግብጽ ፡ በመጡት ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ በአቡነ ፡ ዮሴፍ ፡ እንደዚሁም ፡ በኢትዮጵያውያኑ ፡ ሊቃውንት ፡ መካከል ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ። እነዚያ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖትና ፡ የሮማን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማስገባት ፡ እነዚህም ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖትንና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስን ፡ ሥልጣን ፡ በመከላከል ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ እየጠቀሱ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሲከራከሩ ፡ ቈዩ ። በዚህም ፡ መካከል ፡ የነፍስና ፡ የአካል ፡ መዋሐድ ፡ ጒዳይ ፡ ተነሥቶ ፡ ሲከራከሩበት ፡ ነበር ።

ንጉሡም ፡ የሁለቱ ፡ ወገን ፡ ጒዳይ ፡ በጉባኤ ፡ እንዲታይ ፡ አድርገው ፡ በጉባኤውም ፡ ራሳቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ጠብ ፡ ሳይቀሰቀስ ፡ ነገሩ ፡ በሰላም ፤ እንዲያልቅ ፡ ይጥሩ ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ በቈስጠንጢኖስ ፡ ዘመን ፡ ፲፯፻፳፰ቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ከቈረጡት ፡ ቀኖናና ፡ እምነት ፡ ከኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታችን ፡ ግራም ፡ ቀኝም ፡ አንልም ፡ ለማለት ፡ «ጸሎተ ፡ ሃይማኖትን ፡ .........» እንብበው ፡ ከዚህ ፡ ከባቶቻችን ፡ ሃይማኖት ፡ በፍጹም ፡ አንወጣም ፡ ብለው ፡ የመጨረሻውን ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ ንጉሡም ፡ ሊቃውንቱም ፡ ለሚሲዮናውያኑ ፡ ነገሯቸው ። እነሡም ፤ እያደር ፡ በስብከት ፡ እንገባለን ፡ በማለት ፡ ለጊዜው ፡ የሃይማኖቱን ፡ ክርክር ፡ አቆሙና ፡ ስብከታቸውን ፡ ብቻ ፡ እንዲቀጥሉ ፡ አስፈቀደው ፡ ጉባኤው ፡ ተበተነ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ ምንም ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ባይለውጡ ፡ ለሚሲዮኖቹ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባደረጉት ፡ መልካም ፡ አስተያየትና ፡ አቀራረብ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሱና ፡ ከቀሳውስቱ ፡ ወገን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ ለውጠዋል ፡ እየተባሉ ፡ ከመታማት ፡ አልዳኑም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

### ስለ ፡ ገራድ ፡ ዐሊ ፡ መማረክና ፡ ስለ ፡ አቤቶ ፡ ሚናስ ፡ መመለስ ፤ ስለ ፡ ኑር ፡ መሐመድ ፡ አነሣሥና ፡ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዕረፍት ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ የተደባበ ፡ ማርያምን ፡ የመካነ ፡ ሰማዕትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሥራ ፡ ካሠሩ ፡ በኋላ ፡ ቀጥሎ ፡ በጐጃም ፡ የምትገኘውን ፡ የደብረ ፡ ወርቅ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ ሲያሠሩ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ መሞት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የጦርነቱን ፡ ሁናቴ ፡ በሙሉ ፡

(1) ኩልበ ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ ፈንታ ፡ ወራን ፡ ዶታ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ ይሰጣሉ ።

ሊደመስሰው ፡ አልቻለም ። እንዲያውም ፡ የግራኝ ፡ መሞትና ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ አሸናፊነት ፡ በአዳሎችና ፡ በሐረርጌዎች ፡ ዘንድ ፡ ቍጭትንና ፡ በቀልን ፡ በሰፌው ፡ ቀስቅሶ ፡ ነበር ። ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በሺሕ ፡ ፭፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ገራድ ፡ ዐሊ ፡ በሚባለው ፡ በሚቴ ፡ በግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ልጅና ፡ ዑመር ፡ ዲን ፡ በራኪት ፤ (1) በሚባል ፡ ሡልጣን ፡ የሚመሩ ፡ እስላሞች ፡ ዳዋሮ ፡ መጥተው ፡ ከንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ አደረጉ ፣ ነገር ፡ ግን ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሁለቱ ፡ መሪዎች ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ እጅ ፡ ተማረኩ ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ ሐረር ፡ ባሉት ፡ እስላሞች ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤን ፡ ፈጠረ ። ይልቁንም ፡ የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ባለቤት ፡ ባቲ ፡ ድል ፡ ወንበራ ፡ ልጇ ፡ ገራድ ፡ ዐሊ ፡ ከተማረከ ፡ እንግዴህ ፡ ይሞትብኛል ፡ ስትል ፡ አጥብቃ ፡ ተጨነቀች ። ስለዚህ ። ምጥዋ ፡ ለሚገኙት ፡ ለቱርክ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እባካችሁ ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጋራ ፡ ተላልካችሁ ፡ በዕርቅ ፡ ልጄ ፡ እንዲመለስ ፡ አድርጉልኝ ፡ ብላ ፡ ተላላከች ፡ እነሱም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ተላልከው ፡ ከተስማሙ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በምርኮ ፡ ሄደው ፡ የነበሩት ፡ አቤቶ ፡ ሚናስና ፡ እኅታቸው ፡ ሮማነ ፡ ወርቅ ፡ ከተሸጡበት ፡ አገር ፡ ከየመን ፡ ለዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ተመልሰው ፡ ስለ ፡ መጡ ፡ እንዲሁም ፡ በንጉሡ ፡ ፈቃድ ፡ ዐሊ ፡ ገራድና ፡ ዑመር ፡ ዲን ፡ ተለቀው ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ሄዱ ። በዚህም ፡ ስምምነት ፡ ዐፄ ፡ ሚናስን ፡ ለማስመለሻ ፡ ሺሕ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጨምረዋል ፡ ይባላል ። ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ተመልከት ።

※ ※ ※

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሺሕ ፡ ፭፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኑር ፡ መሐመድ ፡ (ኑር ፡ ኢብን ፡ ሙቃሂድ) ፡ የሚባል ፡ የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ ተነሥቶ ፡ የሐረርና ፡ ያካባቢው ፡ እስላሞች ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ አድርገውት ፡ ነበር ። እርሱም ፡ የወደቀውን ፡ የግራኝ ፡ መሐመድን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያቆማል ፡ ብለው ፡ እስላሞች ፡ ሁሉ ፡ ተስፋ ፡ አደረጉት ። በጊዜውም ፡ የሐረርን ፡ ግንብ ፡ ስላሠራ ፡ ዝናው በገር ፡ ውስጥ ፣ ተስፋፋ ።

ባቲ ፡ ድል ፡ ወንበራ ፡ ባሏ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፣ በዘንተራ ፡ (ደንቢያ) ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በሽሽት ፡ ሐረር ፡ ገብታ ፡ የባሏን ፡ ደም ፡ የሚበቀልላት ፡ አጥብቃ ፡ ትፈልግ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያባቷን ፡ የማኅፉድን ፡ ደበኛ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ በመዠመሪያው ፡ ባሏ ፡ በግራኝ ፡ እንደ ፡ ተበቀለች ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የባሏን ፡ የግራኝን ፡ ደም ፡ በወጣቱ ፡ በኑር ፡ ለመበቀል ፡ አስባ ፡ እያደር ፡ በፍቅር ፡ መንገድ ፡ ስባ ፡ ወዳጅ ፡ አደረገችው ። ወዳጅነታቸውም ፡ እየጸና ፡ ሲሄድ ፡ በመጨረሻ ፡ ጋብቻ ፡ ጠየቃት ። እርሷም ፣ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ራስ ፡ ቈርጠኸ ፡ የሚቴን ፣ ባሌን የግራኝ ፡ መሐመድን ፡ ደም ፡ ትበቀልልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማልልኝና ፡ ላግባኸ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ባቲ ፡ ድል ፡ ወንበራን ፡ ከልቡ ፡ ስለ ፡ ወደዳት ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ሖቴ ፡ ግራኝ ፡ አጎቱ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡

በዚህም ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ የሃይማኖትና ፡ የነገድ ፡ ልዩነት ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ ቂምና ፡ በቀል ፡ ስላደረበት ፡ በደስታ ፡ ሊበቀል ፡ ማለና ፡ በደንብ ፡ አገባት ። እርሷም ፡ ከፍጥረቷ ፡ ምንም ፡ ሴት ፡ ብትሆን ፡ እንደነ ፡ ክሌዎፓትር ፡ የግብጽ ፡ ንግሥት ፡ እንደነ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ባለቤት ፡ የወንድነትና ፡ የመቄጨት ፡ ባሕርይ ፡ ነበራት ፤ ስለዚህ ፡ በበኩሉዋ ፡ የቀሩት ፡ ባላባቶችና ፡ ሕዝቦች ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ለዚህ ፡ ጦርነት ፡ እንዲተባበሩ ፡ በሥራም ፡ በምክርም ፡ ደገፈችውና ፡ ኑር ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ለመውጋትና ፡ ለመጣል ፡ ታላቅ ፡ ድርጅት ፡ አደረገ ።

ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ስንመለከት ፡ የኑር ፡ መሐመድን ፡ አነሣሥ ፡ በሃይማኖት ፡ መለወጥ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎት ፡ እናገኛለን ። እርሱም ፡ እንደዚህ ፤ ይላል ፡ ‹ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ የካቶሊክ ፡ ጳጳስ ፡ ከጀርመን ፡ (ከሮማን ?) ፡ አገር ፡ አስመጥተው ፡ ከህኑ ፡ ሁሉ ፡ የሮም ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲይዝ ፡ ስላደረጉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቈጥቶ ፡ ኑር ፡ መሐመድን ፡ አስነሣባቸው ፡ «በኋላም ፡ ኑር ፡ ሊገጥማቸው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ለመሳፍንቱና ፡ ለመኳንንቱ ፡ ለሊቃውንቱ ፡ ምን ፡ ይሻላል ። ልዋጋ ፡ ወይስ ፡ ልሽሽ ፡ ሲሉ ፡ አማከሩ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከደብረ ፡ ማርያም ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ መጥተው ፡ ከሰማይ ፡ መንግሥትና ፡ ከምድር ፡ መንግሥት ፡ ምረጥ ፤ ...... የሸሸኽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተመልሰኽ ፡ ትነግሣለኽ ፡ ግን ፡ በነፍስኽ ፡ ትጐዳለኽ ፡ በቶሎ ፡ የገጠምኽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ትሞታለኽ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትገባለኽ ፡ ኑርም ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አይፈልግምና ፤ አንተ ፡ ስትሞት ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሁሉ ፡ ዕረፍት ፡ ያገኛል ፡ ......,.› አሏቸው ፡ ሲል ፡ ከዚህም ፡ እያለዋወጠ ፡ ሲተርክ ፡ እንመለከታለን ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ኑር ፡ ሠራዊቱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥቶ ፡ መገርመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጥሞ ፡ ተሸንፎ ፡ ተመለሰ ። ይኸም ፡ በሆነ ፡ ባምሯኛው ፡ ዓመት ፡ ሚስቱን ፡ ድል ፡ ወንበራን ፡ አስከትሎ ፡ ከቀድሞ ፡ በበለጠ ፡ ኀይል ፡ ተደራጅቶ ፡ ከሐረር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መጥቶ ፡ ፈጠጋርን ፡ (ቡልጋን) ፡ ወረረ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጐጃም ፡ ሆነው ፡ የደብረ ፡ ወርቅን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሠሩ ፡ ነበርና ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በንዴት ፡ ከጐጃም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተሻገሩ ። ቀጥሎም ፡ ወደ ፡ ፈጠጋር ፡ መጥተው ፡ ከኑርና ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ግንባር ፡ ለግንባር ፡ ተሰለፉ ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛው ፡ የጦር ፡ ሠራዊታቸው ፡ በያለበት ፡ ተበታትኖ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ የሠራዊቱ ፡ ቊጥር ፡ ትንሽ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ መኳንንቱና ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ "ያለው ፡ ጦር ፡ ትንሽ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ መግጠማችን ፡ ቀርቶ ፡ ከፋሲካ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ጦር ፡ ጨምረን ፡ ብንዋጋ ፡ ይሻላል» ፡ ሲሉ ፡ ምክር ፡ አቀረቡላቸው ። የሚወዷቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ። እባክዎ ፡ ጃንሆይ ፡ ፋሲካን ፡ በፊት ፡ አብረን ፡ ውለን ፡ በኋላ ፡ ቢዋጉ ፡ ይሻላል ፡ እያሉ ፡ በብዙ ፡ ለመኗቸው ። ርሳቸው ፡ ግን ፡ መሞታቸውን ፡

ያውቁ ፡ ኖሮ ፡ “ፋሲካን ፡ በሰማይ ፡ ከጌታዬ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ እው ላለሁ» ፡ ብለው ፡ ፊታቸውን ፡ ሳይመልሱ ፡ ዐርብ ፡ የስቅለት ፡ ለት ፡ ጦርነቱን ፡ ገጠሙና ፡ እጦርነቱ ፡ ማኽል ፡ ገብተው ፡ ይዋጉ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከጠ ላት ፡ ወገን ፡ በተተኰሰች ፡ ጥይት ፡ ተመቱ ። እንደ ፡ ተመቱም ፡ ወታደሩ ፡ እንዳ ይባባ ፡ ቍስላቸውን ፡ አስረው ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ እያበረቱ ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ የእስላሞች ፡ ፈረሰኞች ፡ መጥተው ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ ጨረሷ ቸውና ፡ በተወለዱ ፡ በ፴፰ ፡ ዓመታቸው ፤ ከሺሕ ፡ ፭፻፴፪ ፡ እስከ ፡ ፩ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻፶፩ ፡ ዓ፡ ም፡ ድረስ ፡ ፲፱ ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ገዝተው ፡ ሞቱ ። ከእርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ አባ ፡ ዮሐንስና ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ ዕጨጌ ፡ ሞቱ ። እስላሞቹም ፡ በኑር ፡ ትእዛዝ ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ሬሳ ፡ ጭንቅላታቸውን ፡ ቈርጠው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያ የው ፡ ሐረር ፡ በር ፡ እትልቁ ፡ ደጃፍ ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ፤ ይኸውም ፡ የባቲ ድል ፡ ወንበሩ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ነገር ፡ ግን ፡ እስላሞቹ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ቢያሸ ንፉ ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ በንጉሡ ፡ አሽከሮች ፡ ተሸንፈው ፡ ነበርና ፤ የቀረውን ፡ የን ጉሡን ፡ ሬሳ ፡ ከጦርነቱ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ጭፍሮቻቸው ፡ ከጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አግኝተው ፡ ራሳቸው ፡ ወዳሠሩት ፡ ወደ ፡ ተድባበ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ወስደው ፡ በክብር ፡ ቀበሯቸው ።

ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ እንደሚያስረዳ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በሐረርና ፡ ባውራጃው ፡ ታላቅ ፡ ረኃብና ፡ በሽታ ፡ ተነሣ ፤ ምክንያቱንም ፡ ባቲ ፡ ድል ፡ ወንበሩ ፡ ከዐዋቂ ዎች ፡ ብትጠይቅ ፡ የክርስቲያኑን ፡ ንጉሦ ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ጭንቅላት ፡ በሐ ረር ፡ በር ፡ ስላሰቀልሽ ፡ ፈጣሪ ፡ ተቈጥቶ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱላት ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጭንቅላታቸውን ፡ አስወርዳ ፡ በነጋዴዎች ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ላከችውና ፡ በክብር ፡ ተቀመጠ ።

ኑር ፡ የጦርነቱን ፡ ድል ፡ አግኝቶ ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ራስ ፡ ቈርጦ ፡ ለባለቤቱ ፡ ለድል ፡ ወንበሩ ፡ በማሳየቱ ፡ ሚስቱና ፡ የአዳል ፡ የሐረር ፡ እስላሞች ፡ በጕብዝናው ፡ አደነቁት ፤ የግራኝንም ፡ ደም ፡ ተበቀለ ፡ ብለው ፡ ምስጋናም ፡ ክብርም ፡ አቀረቡለት ።

በዚህም ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ወገን ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡ በመሞታቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተገጠመላቸው ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጌታን ፡ ተከተለ ፤

ፋሲካውን ፡ ሳይውል ፡ ዓርብ ፡ ተሰቀለ ።
ጌታውም ፡ ሳይረሳው ፡ የፋሲካ ፡ ለታ ፡
አስጠርቶ ፡ አበላው ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡
ባሕር ፡ ዳሩን ፡ ዞረ ፡ ሸዋ ፡ ሲመለስ ፡
አንጾኪያ ፡ ታየ ፡ ብርሃንን ፡ ሲለብስ ። (1)

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በመሠረቱ ፡ የፖርቱጋሎች ፡ ርዳታ ፡ ቢጨመርበት ፡ የግራኝን ፡ ጦር ፡ አሸንፈው ፡ የተወረረውን ፡ አገር ፡ መልሰው ፡ አቋቋሙ ። በግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ጊዜ ከተቃጠሉት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ውስጥ ፡ የተድባበ ፡ ማርያምና ፡ የመከነ ፡ ሰማዕትን ፡ የደብረ ፡ ወርቅን ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ። እንደዚሁም ፡ በሸዋ ፤ ባማራ ፡ ሣይንት ፤ በወሎ ፤ በጐጃም ፤ በበጌምድር ፤ በትግሬ ፡ የተቃጠሉትን ፡

የደብረ ፡ ብርሃንን ፡ ዘረዓ ፡ ያዕቆብ ፡

የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ተ ፡ ሃ ፡

የምስሐል ፡ ማርያምን ፡

የገነተ ፡ ጊዮርጊስን ፡

የደብረ ሕንፀታን ፡

የደብረ ድማኅን ፡

የመከነ ፡ ሥላሴን ፡

የወልደ ነጐድጓድን ፡

የደብረ ፡ ኪሩቤልን ፡

የአትሮንስ ፡ ማርያምን ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡

የኤንድሮስ ፡ ማርያምን ፡

የታዕካ ፡ መንግሥትን ፡

የደብረ ፡ ጽርሐ ፡ ማርያምን ፡

የገነተ ማርያምን ፡

የአባ ጊዮርጊስን ፡ (ዘጋሥጫን) ፡

የደብረ ፡ ቤቴልን ፡

የእግዚአብሔር አብን ፡

የደብረ ፡ እስጢፋኖስን ፡

የመርጡለ ፡ ማርያምን ፡ ንግሥት ፡ እሌኒ ፡

የደብረ ፡ ዘይትን ፡

የናዝሬትን ፡

የአምበር ፡ ቂርቆስን ፡

የገሊላን ፡

የአጥሊሳን

የደብረ ፡ መሢሕን ፡

የጎለተ ፡ ማርያምን ፡

የጎሓ ፡ ጽዮንን ፡

የዋሻ ፡ ሚካኤልን ፡

የደብረ ፡ ከርቤን ፡

አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ ገዳማት ፡ እንዲሠራ ፡ በያለበት ፡ ትእዛዝ ፡ አስ ተላለፉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ በርሳቸው ፡ ዘመን ፡ ሲሠሩ ፡ የቀረው ፡ በመንግሥታቸው ፡ በተከተሏቸው ፡ በጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ በየጊዜው ፡ ተሠራ ።

(1) ከሐረር ፡ ጭንቅላታቸው ፡ መጥቶ ፡ አንጾኪያ ፡ ስላረፈና ፡ በዚሁም ፡ የአንጾኪያ ፡ ሰማዕት ፡ ስለተባሉ ፡ ነው ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ለጠላታቸው ፡ ኀይለኛ ፤ ለወዳጃቸው ፡ የተመቹ ፡ ሰው፡ አክባሪና ፡ ጠባየ መልካም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ በዘመናቸው ፡ የነበሩት ፡ ነጮች ፡ ሳይቀሩ ፡ የጻፉት ፡ ዘሬ ፡ በየመጽሐፉ ፡ ይገኛል ። ደግሞ ፡ እባክዎ ፡ ፋሲካን ፡ አብረን ፡ ውለን ፡ በኋላ ፡ ይዋጋሉ ፡ ብለው ፡ ለለመኗቸው ፡ "ፋሲካን ፡ ከጌታዬ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ እውላለሁ ፡ . . . . ." ብለው ፡ መመለሳቸው፡ ፍጹም ፡ ክርስቲያንነታቸውን ፡ ያስረዳል ።

ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ በርሳቸው ፡ ደጋፊነት ፡ አዛዥ ፡ ጌራና ፤ አዛዥ ፡ ራጉኤል ፡ የድጓን ፡ ምልክት ፡ አበጁ ። መበአ ፡ ጽዮን ፡ የሚባሉት ፡ የራስ ፡ ዐምዱ ፡ ልጅ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበውን ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ግዕዝ ፡ ተረጐሙ ፤ በዚህም ፡ ዐፄ ገላውዴዎስ ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ እንደነ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለጽሑፍ ፡ መስፋፋት ፡ ዝንባሌ ፡ እንደነበራቸው ፡ ይታወቃል ። ነገር ፡ ግን ሃይማኖትም ፡ ምግባርም ፡ ቢበዛ ፡ ባይሆን ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትን ፡ ያወርሳል ፡ እንጂ ፡ ከሞት ፡ አያድንምና ፡ ሞቱ ፤ ታሪካቸው፡ ግን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ይኖራል ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

## የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ስለ ፡ ዐፄ ፡ ሚናስ ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዐስበ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ሰበነ ፡ ጊዮርጊስ ፤ መሢሐዊት ፤ ቅድስት ፡ ሐና ፤ እማሆዴ ፡ የሚባሉ ፡ ልጆች ፡ ነበሯቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከኑር ፡ መሐመድ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ በዙፋኑ ፡ የተከተሏቸው ፡ ወንድማቸው አቤቶ ፡ ሚናስ ፡ ናቸው ።

ዐፄ ፡ ሚናስም ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ የእናታቸውን ፡ የእቴጌ፡ ሰብለ ፡ ወንጌልን ፡ የእቴጌነት ፡ ማዕርግ ፡ ሽረው ፡ ለባለቤታቸው ፡ ለእቴጌ ፡ ሥሉስ ፡ ኃይላ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ «አድማስ ፡ ሞገሳ» ፡ አሰኝተው ፡ ሰጧቸው ። በዚህም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተገረመ ። እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ባለቤት ፡ የነዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ የራሳቸው ፡ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ እናት ፡ ሆነው ፡ ከባላቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ዠምረው ፡ የግራኝን ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ በስደትና ፡ በመከራ ፡ አሳልፈው ፡ በልጃቸው ፡ በዐፄ ፡ ገላውዴዎስም ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ ተከብረው ፡ ሲኖሩ ፡ አሁን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ያልታሰበ ፡ ሽረት ፡ ስላገኛቸው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አዘነላቸው ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ከእቴጌዩቱ ፡ ባለሟሎች ፡ ውስጥ ፡ ጳውሊና ፡ ዝክሬ ፡ የሚባሉ ፡ ቀሳውስት ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ሚናስ ፡ መጥተው ፡ «እናትን ፡ አዋርዶ ፡ ሚስትን ፡ ማክበር ፤ አክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ማፍረስ ፡ አይደለምን ? ፤ አይገባም ፤ አሁንም ፡ ታረቅልን» ፡ ብለው ፡ መከሯቸው ።

እርሳቸውም ፡ «ለናቴ ፡ ከኔ ፡ እናንተ ፡ አትቀርቧትም ፡ በፋንታዋ ፡ ነግሣለች ።
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለርሷ ፡ አክሊሏ ፡ ቆቧ ፡ ነው» ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰጡ ።
ቢገዝቷቸውም ፡ ገዛቾቹን ፡ በእስራትም ፡ በአካልም ፡ ቀጧቸው ፤ . . . . ታሪክ ፡
ነገሥት ፡ ተመልከት ።

ሚናስ ፡ በዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ ከጦርነት ፡ ላይ ፡ የግራኝ ፡ መሐ
መድ ፡ ሰዎች ፡ ማርከዋቸው ፡ ለየመን ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ለዘቢድ ፡ ፓሻ ፡ እንደ ፡
ባሪያ ፡ ሸጠዋቸው ፡ እንደ ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ወታደ
ሮች ፡ ከግራኝ ፡ ልጅ ፡ ከገራድ ፡ ዐሊና ፡ ከዑመር ፡ ባራኪት ፡ ተዋግተው ፤
በማረኳቸው ፡ ጊዜ ፡ ስምምነት ፡ ተደርጎ ፡ እነዚህ ፡ ተፈትተው ፡ በነፃ ፡ ሲለቀቁ ፡
ሚናስና ፡ እኅታቸው ፡ በነፃ ፡ ተለቀው ፡ ወዳገራቸው ፡ መጥተው ፡ እንደተቀ
መጡ ፡ ባለፈው ፡ ተጽፏል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወንድማቸው ፡ ሲሞቱ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ «አድማስ ፡
ሰገድ» ፡ ተብሎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ ይገዙ ፡ ዠመር ።

እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ሲጽፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡
ተደጋግሞ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ አንዳንዱ ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ደግሞ ፡ «ሚና
ስን ፡ እቴጌ ፡ እሌኒና ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ተማክረው ፡ ወደ ፡ ፖርቱጊዝ ፡ መንግ
ሥት ፡ የነፍጥ ፡ መያዣ ፡ አድርገው ፡ ልከዋቸው ፡ ነበርና ፤ በኑር ፡ መሐመድ ፡
ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ ረዳት ፡ ስደዱልን ፡ ብለው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቢልኩ ፡ የፖርቱ
ጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሚናስን ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ አግብቶ ፡ አስቀብቶ ፡ አንግሦ ፡
አንድ ፡ ጳጳስ ፡ ሰጥቶ ፡ ጦር ፡ ጨምሮ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰዶት ፡ ከኑር ፡ መሐ
መድ ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ ኑር ፡ መሐመድን ፡ ድል ፡ ስላደረገ ፡ መንግሥቱን ፡ እጅ ፡
አድርጎ ፡ እንጦጦ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ። ጳጳሱም ፡ ካቶሊክ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡
ሙሉ ፡ ሲቀመጥ ፡ ከጐንደር ፤ ከትግሬ ፤ ከሸዋ ፡ ቅስናና ፡ ዲቁና ፡ ልቀበል ፡ የሚል ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ አልመጣም ። ጐጃሞች ፡ ግን ፡ እምነታቸው ፡ ቅባት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡
መጥተው ፡ ከካቶሊኩ ፡ ጳጳስ ፡ ቅስናና ፡ ዲቁና ፡ ተቀበሉ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከደ
ብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ ውስጥ ፡ ቄስ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፤ ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ዘመ
ለኮት ፡ የሚባሉ ፡ መጥተው ፡ ሃይማኖትኽ ፡ ምንድነው ፡ ብለው ፡ ጳጳሱን ፡ ቢጠይ
ቁት ፡ «ሃይማኖቱ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ፪ ፡ የሰውነትና ፡ የመለኮትነት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ።
በዚህም ፡ መለኮት ፡ የመለኮትነቱን ፡ ሰውነት ፡ የሰውነቱን ፡ ባሕርይ ፡ ይሠራል» ፡
አላቸው ፡ እነርሱም ፡ «የእንጦጦ ፡ መምር ፡ አይናገር ፤ ቢናገር ፡ ባመት ፤ ያውም ፡
ፌት ፡ ብለው ፡ አውግዘውት ፡ ሄዱ ፡ እሱም ፡ ተቀሠፈ» ፡ ይላል ።

ይኸንንም ፡ ባገራችን ፡ ታሪክ ፡ የተጻፈውን ፡ አንባቢ ፡ እንዲያውቀው ፡ ጻፍን ፡
እንጂ ፡ ሙሉውን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመቀበል ፡ ማስቸገሩን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡
በዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ አስታውሰናል ። የነፍጥ ፡ መያዣ ፡
ሆነው ፡ ተልከው ፡ በኋላም ፡ ካቶሊክ ፡ ሆነው ፡ ቢመለሱ ፡ ኖሮ ፡ ካቶሊክ ፡ የሆኑት ፡

የኤውሮፓ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይኸንኑ ፡ ካቶሊክነታቸውን ፡ አጋኖ ፡ ለመጻፍ ፡ ደስ ፡ ባላቸው ፡ ነበር ፡፡ ዐፄ ፡ ሚናስም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምናገኘው ፡ ለአርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናዒ ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ጳጳስ ፡ ከተባለው ፡ ከእንድርያስ ፡ አቢዬዶ ፡ ጋራ ፡ ያን ፡ ያኽል ፡ የከረረ ፡ ጠብ ፡ አያደርጉም ፡ ነበር ፡፡ ደግሞ ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ከ፬ቱ ፡ ፻ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የርዳታ ፡ ጦር ፡ ከፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ፪ኛ ፡ መምጣቱን ፡ የሚናገር ፡ አንድም ፡ መጽሐፍ ፡ የለምና ፡ በካቶሊክነት ፡ አሳምነው ፡ ጳጳስ ፡ ሰጥተው ፡ ጦር ፡ ጨምረው ፡ ላኩት ፡ የሚባለው ፡ የታመነ ፡ አይደለም ፡ የዚህን ፡ ልዩነት ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ለማጣራት ፡ ለመጪው ፡ ጊዜ ፡ ትተን ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ አሳብ ፡ እንራመዳለን ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡፡

## ስለ ፡ ተዝካረ ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡፡

በዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ዘመን ፡ የፈላሻና ፡ የስሜን ፡ ሰው ፡ ሽፍቶ ፡ አስቸግሮ ፡ ነበር ፡፡ እንዲያውም ፡ በዚሁ ፡ በስሜን ፡ ተራራ ፡ ከሚኖሩት ፡ ፈላሾች ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ውስጡን ፡ ከንጉሡ ፡ የሌሊት ፡ ዘበኞች ፡ መከከል ፡ ዐድማ ፡ አድርገው ፡ በሚተኙበት ፡ ሰዓት ፡ እድንኳናቸው ፡ ገብተው ፡ ሊገድሏቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዐድማው ፡ አስቀድሞ ፡ ተገለጸና ፡ እነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ ተይዘው ፡ ተገደሉ ፡፡

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ በያለበት ፡ ባላባቶቹ መሸፈታቸው ፡ አልቀረም ፡፡ የትግሬና ፡ የሐማሴን ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ የሚባለው ፡ የዐፄ ፡ ሚናስን ፡ ወንድም ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብን ፡ ልጅ ፡ ተዝካሮ ፡ (ተዝካረ ፡ ቃል) ፡ የሚባለውን ፡ አንግሦ ፡ በዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ላይ ፡ ሸፈተ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ዘርዓ ፡ ዮሐንስ ፡ በሚባል ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የሚታዘዝ ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባሕር ፡ ነጋሽን ፡ እንዲወጋ ፡ ልከው ፡ ጦርነት ፡ ተጋጠሙ ፡፡ ባሕር ፡ ነጋሽም ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ጦሩን ፡ አባሮ ፡ ዘርዓ ፡ ዮሐንስንም ፡ ገደለው ፡፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአቤቶ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ተዝካሮ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ ከዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ጋራ ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉ ፡፡ በኋላም ፡ ወገራ ፡ ላይ ፡ ተጋጠሙና ፡ ዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ድል ፡ አደረጉ ፡፡ ተዝካሮም ፡ ተማረከና ፡ በለማለሞ ፡ ገደል ፡ (በጌምድር ፡ ውስጥ) ፡ ተወርውሮ ፡ ተገደለ ፡ ይባላል ፡፡

ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ ግን ፡ ተዝካሮ ፡ ከተማረከ ፡ በኋላ ፡ የተዝካረ ፡ ቃልን ፡ ወንድም ፡ ፋሲለደስን ፡ ይዞ ፡ ከዚያ ፡ ተመልሶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጋ ፡ ይመልሳቸው ፡ ከነበሩት ፡ ከቱርኮች ፡ ጋራ ፡ ንጉሡን ፡ ሚናስን ፡ ለመጕዳት ፡ ሲል ፡ ስምምነት ፡ አደረገ ፡፡ ስለዚህ ፡ ቱርኮች ፡ ከአርኪቆና ፡ ከምጥዋ ፡ ዠምረው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የትግሬና ፡ የሐማሴን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ የነበረውን ፡ ደባሩአ ፡ የሚባለውን ፡ ሁሉ ፡ ይዘው ፡ ግዛታቸውን ፡ ለጊዜው ፡ ለማስፋፋት ፡ ቻሉ ፡፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ጣሊያኖች ፡ ያደርጉት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ሁሉ ፡ ቱርኮች ፡ ለባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ ከዐፄ ፡ ሚናስ ፡ የሚከላከልበት ፡ ሰውና ፡ መሣሪያ ፡ በመጠኑ ፡ ሰጡት ፡፡

በዚህ ፡ መካከል ፡ ከዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ፖርቱጊዞች ፡ በነሱ ፡ ርዳታ ፡ ግራኝ ፡ ድል ፡ በመሆኑ ፡ የሚሰማቸው ፡ ትምክሕት ፡ አልበረደም ፡ ነበር ፡ ከነሱም ፡ ውስጥ ፡ ሚሲዮኖች ፡ የሆኑት ፡ በሃይማኖት ፡ የተነሣ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ይከራከሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁም ፡ በዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩ ፡ ወደ ፡ ጠብ ፡ ዞሮ ፡ በክፉ ፡ ዐይን ፡ ይተያዩ ፡ ጀመር ። በወንጌል ፡ ስብከት ፡ እያመከኙ ፡ የዐፄ ፡ ሚናስን ፡ ክፉት ፡ እየጨመሩ ፡ መስበካቸውና ፡ አስቀድሞም ፡ ልባቸውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽና ፡ ወደ ፡ ተዝካረ ፡ ቃል ፡ ማድረጋቸው ፡ በዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ዘንድ ፡ የተሰወረ ፡ አልነበረም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ንጉሡ ፡ እንድርያስ ፡ አቤዶ ፡ የሚባለውን ፡ የሚሲዮኖቹን ፡ ጳጳስ ፡ አስጠርተው ፡ ፩ኛ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዳይሰብክ ፡ ከለከሉት ። እሱም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቴ ፡ እሞታለሁ ፡ እንጂ ፡ መስበኬን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አልተውም ፡ ብሎ ፡ በቊጣ ፡ ቃል ፡ መለሰላቸው ። ንጉሡም ፡ በንዴት ፡ ከመቀመጫቸው ፡ ተነሥተው ፡ ጠ.ሙንና ፡ ጨርቁን ፡ ይዘው ፡ እንዴት ፡ ትናገራለኽ ፡ ብለው ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ መቱት ፡ ወዲያው ፡ በዚያ ፡ የቆመት ፡ ንጉሡን ፡ ለምነው ፡ አስጣሉትና ፡ በግዞት ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጠ ፡ ይባላል ። እንዲያውም ፡ ወዳጅ ፡ የነበሩት ፡ ፖርቱጊዞች ፡ በመጨረሻ ፡ አሳባቸው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጠላትነት ፡ ከሆነ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሉት ፡ ፖርቱጊዞች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሴት ፡ እንዳያገቡ ፡ አዘው ፡ ስብከታቸውንም ፡ በፍጹም ፡ ዘጉባቸው ። እንድርያስ ፡ አቤዶም ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ አትጠብቁ ፡ ብሎ ፡ ለሚመስሉት ፡ ተናገረ ።

ይኸንኑም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ቢጠየቅ ፡ አንገቱን ፡ ገላልጦ ፡ እየመዘዘ ፡ ያውልኽ ፡ ምታኝ ፡ ወይም ፡ እረደኝ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተጠጋ ፡ ንጉሡም ፡ ተቈጥተው ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ከጋሻ ፡ ዦግሬያቸው ፡ ተቀብለው ፡ በሰይፍ ፡ ሊቆርጡት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እቴጌዩቱና ፡ ባለሟሎቻቸው ፡ ከለከሏቸውና ፡ ዳነ ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጳጳሱና ፡ ሚሲዮናውያኖቹ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በግዞት ፡ ተይዘው ፡ ሲጠበቁ ፡ ከግዞት ፡ በታቸው ፡ አምልጠው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ሄደው ፡ ተደባለቁ ። ኦርቶዶክሱንም ፡ መንግሥት ፡ ካቶሊክ ፡ ካላደረግን ፡ ብለው ፡ በቀሰቀሱት ፡ ጠብ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ተናደዱም ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ከቱርኮች ፡ ጋራ ፡ ተስማሙ ።

በመጨረሻ ፡ ንጉሡ ፡ ሚናስም ፡ ሄደው ፡ ከባሕር ፡ ነጋሽና ፡ ከሚሲዮናውያኖቹ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚሁ ፡ ድል ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ስለ ፡ ሸሹ ፡ ንጉሡ ፡ ለመግደል ፡ ወይም ፡ ለመማረክ ፡ ስላልቻሉ ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመለሱ ። በሸዋም ፡ በዶባ ፡ በኲል ፡ ጋሎች ፡ ሸፍተው ፡ እነሱን ፡ ሲያባርሩ ፡ ወባ ፡ ይዟቸው ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ በወባ ፡ ታመው ፡ ሞቱና ፡ ተድባበ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክብር ፡ ተቀበሩ ። ግዛታቸውም ፡ ከሺሕ ፡ ፭፻፶፪ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። መንግሥትም ፡ ለመያዝ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በያለበት ፡ ጦርነትና ፡ ግጭት ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ልጃቸው ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ነገሡ ።

## ምዕራፍ ፳፱ ።

## የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

### ስለ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ።

የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ አባት ፡ ዐፄ ፡ ሚናስ ፡ በ፲፭፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሞቱ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ መኳንንቱ ፡ ለምክር ፡ ተሰበሰቡ ። በጉባኤውም ፡ ማን ፡ እንደሚነግሥ ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ተደረገ ። ግማሹ ፡ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ትልቁ ፡ ልጅ ፡ ይንገሥ ፡ አሉ ። ግማሾቹም ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እኅት ፡ የወይዘሮ ፡ ሮማነ ፡ ወርቅ ፡ ልጅ ፡ ሐመልማል ፡ ይንገሥ ፡ አሉ ። በዚህም ፡ ሲከራከሩ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ አለቆች ፡ አዛዥ ፡ ቁሞ ፤ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ክፍለ ፡ ማርያም ፤ አባ ፡ አዕቀ ፡ ድንግል ፤ ሊቁ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፤ አናንያ ፤ የዘበኞች ፡ አለቃ ፡ ትንሹ ፡ ማር ፡ (1)ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ይንገሥ ፡ ሲሉ አሳባቸውን ፡ ወሰኑ ። ከዚህ ፡ በኋላ ሠርፀ ፡ ድንግልን ፡ አስጠርተው ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሚደረገውን ፡ የደንቡን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ አድርሰው ፡ አነገሡዋቸው ። ስመ ፡ መንግሥታቸውስ ፡ ማን ፡ ይሁን ? ብለው ፡ አዛዥ ፡ ቁሞን ፡ ጠየቁ ፤ አዛዥ ፡ ቁሞም ፡ «መለክ ፡ (2)ሰገድ ፡» ይሁን ፡ አለ ። የዚህንም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ውስጡን ፡ በምክር ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ አደባባይ ፡ ወጥተው ፡ «ዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ልጃቸውን ፡ ማር ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልን ፡ ስማቸውን ፡ መለክ ፡ ሰገድ ፡ ብለን ፡ አንግሠናል» ሲሉ ፡ በሀዋጅና ፡ በነጋሪት ፡ ለሕዝቡና ፡ ለወታደሩ ፡ አስታወቁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሹማቹ ፡ ስለ ፡ ዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡ በገሃድ ፡ ኀዘን ፡ ተደረገ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትን ፡ በየስፍራው ፡ ተመልከት ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ሲነግሡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፤ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እያደር ፡ እሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ደርሰው ፡ በስመ ፡ ጥርነት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ፴፬ ፡ ዓመት ፡ ገዝተዋል ፡ ስመ ፡ ጥርነትም ፡ የሰጣቸው ፡ የዘመኑ ፡ ርዝመት ፡ አይደለም ፡ በዘመኑስ ፡ ርዝመት ፡ ባይሠሩበት ፡ ኖሮ ፡ ስመ ፡ ጥርነቱ ፡ የወቀሣ ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ስመ ፡ ጥርነትን ፡ የሰጣቸው ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ያለዕረፍት ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፤ ወደ ፡ ዳሞት ፤ ወደ ፡ እናሪያ ፤ ወደ ፡ ጕራጌ ፤ ወደ ፡ ሐረር ፤ወደ ፡ሰሜን፤ወደ ፡ ትግሬና ፡ ወደሐማሴን ፤ ከገር ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ያለዕረፍት ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ማቅናታቸው ፤ ጠላታቸው ፡ በሆነው ፡ ምጥዋን ፡ በያዘው ፡ በቱርክ ፡ ባሻና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በተደረበው ፡ በባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ ላይ ፡ ያገኙት ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ ነው ። ይኸም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ለጐንደር ፡ መንግሥትና ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ መገርመሪያ ፡ መሥራችና ፡ ቈርቋሪ ፡ የሚቈጠሩት ፡ እርሳቸው ፡ ናቸው ።

(1) መንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ የሚያዘወትር ፡ ማር ፡ ይባላል ።

(2) መለክ ፡ ገዥ ፡ ወይም ፡ ንጉሥ ፡ ማለት ፡ ነው ። መለክ ፡ ሰገድ ፡ ሲል ፡ ነገሥታትን ፡ የሚያሰግድ ለማለት ፡ ነው ።

ዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ እላይ ፡ ስሙን ፡ የጠራነው ፡ ሐመልማል ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ የእህት ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተወላጅ ፡ በመሆኑ ፡ ዙፋኑን ፡ ለመቀናቀን ፡ አጥብቆ ፡ ተነሣባቸው ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ ዘርዓ ፡ ዮሐንስን ፤ የደንቢያው ፡ ሐርቦ ፤ ሌሎቹም እነአዝማች ፡ ተክሉ ፡ እነሮም ፡ ሰገድ ፤ እነእስላም ፡ ሰገድ ፡ የሚባሉት ፡ ጭፍሮቻቸውን ፡ እየያዙ ፡ አብረውለት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ የዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ ሁኔታ ፡ በሙገርመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ወደሚያስፈራ ፡ አኳኋን ፡ ላይ ፡ ነበር ፤ ከዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግልም ፡ ጋራ ፡ አያታቸው ፡ እቴጌ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ባሌቤት ፡ እቴጌ ፡ ሥሉስ ፡ ኀይላ ፡ ወይም ፡ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ የሚባሉት ፡ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ባለቤት ፡ ሆነው ፡ በጸሎትና ፡ በኀዘን ፡ ከመነኰሳቱና ፡ ከቀሳውስቱ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ መንግሥት ፡ አቋቋም ፡ ይጨነቁ ነበር ። ሁሉም ፡ ሲከዳ ፡ አባ ፡ ዘድንግል ፡ የሚባሉት ፡ የተድባበ ፡ ማርያም ፡ አለቃ ፤ አዛዥ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ዐምዴና ፡ ሳዊሮስ ፡ የሚባሉት ፡ ግን ፡ ከዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የመጣውን ፡ እንቀበላለን ፡ ብለው ፡ ቈርጠው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ መከከል ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ሐመልማል ፡ ወደ ፡ ማሸነፍ ፡ ደርሶ ፡ ዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ ከወገኖቻቸው ፡ ጋራ ፡ ነገሡ ፡ ተብሎ ፡ በታወጀበት ፡ ዓመት ፡ ስደትም ፡ መከራም ፡ አግኝቷቸው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ መኳንንትና ፡ ሊቃውንት ፡ እያደር ፡ ስላበሩላቸው ፡ መንግሥታቸው ፡ ወደ ፡ መጽናት ፡ አዘነበለ ። በመጨረሻም ፡ ከጠላቶቻቸው ግማሾቹ ፡ በምርኮ ፡ የቀሩትም ፡ በዕርቅ ፡ ገቡላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በገር ፡ ውስጥ ፡ ሰላም ፡ ተገኝቶ ፡ የሹመት ፡ ድልድል ፡ ሲደረግ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ለነበሩት ፡ ለሐመልማል ፡ ጐጃምን ፤ ለሮም ፡ ሰገድ ፡ ሸዋን ፡ ሰጧቸው ። ሮም ፡ ሰገድ ፡ ሸዋ ፡ ሆኖ ፡ ማስተዳደር ፡ እንደ ፡ ዠመረ ፡ በሸዋ ፡ የነበረው ፡ ለዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ ያልተገዛው ፡ ዐፄ ፡ ገራድ ፡ የተባለው ፡ የእስላሞች ፡ መሪ ፡ በጦርነት ፡ ገደለው ። በዚሁም ፡ ዘመን ፡ ሐመልማልና ፡ እስላም ፡ ሰገድ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፤ ባለፈው ፡ ቂም ፡ የተነሣ ፡ ርሳቸው ፡ አስገደሏቸው ፡ ይሆን ? እየተባሉ ፡ ታምተዋል ። ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ዙፋኑን ፡ የሚቀናቀኑት ፡ ቀንደኛ ፡ የሆኑት ፡ የውስጥ ፡ ጠላቶች ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ የውስጥ ፡ ሁኔታቸውን ፡ ካደላደሉ ፡ በኋላ ፡ በሩቅና ፡ በዙሪያ ፡ የሚገኙትን ፡ ባላባቶች ፡ ለማሳመን ፡ ለጕዞ ፡ ይዘጋጁ ፡ ዠመር ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፴ ።

## ያገር ፡ አከፋፈልና ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚሰጠው ፡ የማዕርግ ፡ ስም ።

ዐፄ ፡ ሡርፀ ፡ ድንግል ፡ ወደ ፡ እናሪያና ፡ ወደ ፡ ጕራጌ ፡ ያደረጉትን ፡ ጕዞ ፡ ከመግለጻችን ፡ በፊት ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ በንድ ፡ ዘመን ፡ እየፈረሰ ፤ በሌላው ፡ እየጸና ፤ ባንድ ፡ ዘመን ፡ እየከበረ ፡ በሌላው ፡ እየተዋረደ ፤ ብብዛኛው ፡ ዘመን ፡ እየተጠቀለለ ፡ ባነስተኛው ፡ ዘመን ፡ እየተለየ ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ የግዛት ፡

አከፋፈል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንጽፋለን ። ይኸውም ፡ካገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ከጥንትና ከቅርብ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከዳልሜይዳ ፤ ከሉዶልፍ ፤ ከፔር ፡ ፖኤዝ ፡ ጽሑፍ ፡ የተገኘ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ሲጽፉ ፡ ቊጥሩን ፡ በማበርከት ፡ ወይም ፡ በማሳነስ ፡ የስሙን ፡ አጠራርም ፡ እየለዩ ፡ በመጻፍ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አይስማሙም ።

ለምሳሌ ፡ ዳልሜይዳ ፡ የተባለው ፡ ጸሐፊ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የነገሥታትነት ፡ ማዕርግ ፡ ያላቸውን ፡ የግዛት ፡ ክፍሎች ፡ እስከ ፡ ፴፮ ፡ ያደርሰዋል ። እነዚህም ፡ ትግራይ ፤ ደንከል ፤ አንጎት ፤ ዶባ ፡ ሰጣን ፤ ሞጣ ፤ አውሳ ፤ አማራ ፡ ወለጋ ፤ ሸዋ ፤ ይፋት ፤ ግድም ፤ ገንጭ ፤ ደዋሮ ፤ ፈጠጋር ፤ ዎይ ፤ ወይም ፡ ዎድ ፤ ባሌ ፤ ሀዲያ ፤ አላማሌ ፤ ዎቅስሎ ፤ ጋንዝ ፤ በተራሞራ ፤ ጕራጌ ፤ ጌራ ፤ ቡግና ፤ ሱፍጋሞ ፤ ባሕርጋሞ ፤ ከምባታ ፤ ቦቅሳ ፤ ጉመር ፤ ጃንጀሮ ፤ እናሪያ ፤ ኮንቻ ፤ ዳሞት ፤ ጐጃም ፤ በጌምድር ፤ ደንቢያ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ፴፮ቱ ፡ የነገሥታት ፡ ግዛት ፡ ሆነው ፡ ከዚህ ፡ የተረፈ ፡ ፲፯ ፡ ደግሞ ፡ ያውራጃ ፡ ግዛቶች ፡ እንዳሉ ፡ ይዘረዝራል ። እንዚህም ፡ ገንደጮ ፤ አረንጭ ፤ ወርጋር ፤ ቃግማ ፤ መርጋይ ፤ ቅዛርጋ ፤ ገማሮ ፤ አሌጽጌ ፤ ጠልቆን ፤ ወገራ ፤ ስሜን ፤ ጠለንቲ ፤ ቦራ ፤ አበርጋሌ ፤ ሰለዋ ፤ ጸገዴ ፤ ቃሌት ፤ ማደጋ ፡ ናቸው ።

ሉዶልፍ ፡ የሚባለው ፡ ጸሐፊ ፡ ደግሞ ፡ ከጥንታዊ ፡ ታሪክ ፡ አገኘሁት ፡ በማለት ፡ የነገሥታቱን ፡ ግዛት ፡ በ፴ ፡ ይከፍልና ፡ ዝርዝሩን ፡ ፩ኛ ፡ አማራ ፤ ፪ኛ ፡ አንጎት ፤ ፫ኛ ፡ በጌምድር ፡ . . . . ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ያደርሰዋል ።

ፔር ፡ ፖኤዝ ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ ፴፫ ፡ የነገሥታት ፤ ፲፰ ፡ ያውራጃነት ፡ ማዕርግ ፡ ያላቸው ፡ አገሮች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፤ ከነዝርዝሩ ፡ ለማስረዳት ፡ ይሞክራል ።

ከነዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ትግሬ ፤ ጐንደር ፤ (አማራ) ፡ ላስታ ፤ ሸዋ ፤ ወይም ፡ ጐጃም ፤ እነዚህ ፡ አራቱ ፡ በወርቅ ፡ ዙፋን ፡ የመቀመጥ ፡ መብት ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ስማቸው ፡ ያልተገለጸ ፡ በብር ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡ ፤ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ከበይና ፡ ካዋሽ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚገኙ ፡ በየግዛታቸው ፡ ንጉሥ ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ በመዳብ ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡ ፡ ነበሩ ፡ ይላል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በየዘመኑ ፡ መዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አኵስም ፤ ቀጥሎ ፡ ላስታ ፤ ቀጥሎ ፡ ሸዋ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ባሁኑ ፡ በሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ጐንደር ፡ የሚቀመጥ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ማዕርግ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እርሱም ፡ ሲያይልም ፡ ሲደክምም ፡ በሌሎቹ ፡ ነገሥታት ፡ ነን ፡ ወይም ፡ ባላባት ፡ ነን ፡ በሚሉት ፡ አውራጃዎች ፡ ላይ ፡ የበላይነትና ፡ ያስገባሪነት ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ቢከፋፈልም ፡ በጠቅላላው ፡ ያው ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ርሱም ፡ ከሰሜን ፡ እስከ ፡ ምጥዋ ፤ ከደቡብ ፡ የውቅያኖስ ፡ ባሕር ፤ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ አውሳ ፡ ጫፍ ፤ በምዕራብ ፡ እስከ ፡ ሱዳን ፡ ጠረፍ ፡ የሚደርሰው ፡ ነው ። በነንግሥት ፡ ሳባ ፤ በነካሌብ ፤ በነዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፤ ከዚህ ፡ ይሰፋ ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ በብዙ መጽሐፍ ፡ ይገኛል ።

በዚህ ፡ በተዘረዘረው ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ የቀድሞዎቹ ፡ በአኵስምና ፡ በላስታ ፡ የነበሩት ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ በሸዋና ፡ በጐንደር ፡ የተዘዋወሩት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ማዕርጋቸው ፡ ላይ ፡ ዐፄ ፡ ዐፄጌ ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩት ፡ ስመ ፡ መንግሥታቶቻቸውን ፡ አንበሳ ፡ ሰገድ ፤ (አንበሳን ፡ የሚያሰግድ) ፡ አድማስ ፡ ሰገድ ፤ (ጠረፍ ፡ የሚያሰግድ) ፡ . . . . . ፡ እያሰኙ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ። የዚህም ፡ ዐይነት ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ከዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ? ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንደ ፡ ቈየና ፡ በኋላ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፪ኛ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አባ ፡ ታጠቅ ፡ አባ ፡ በዝብዝ ፤ አባ ፡ ዳኘው ፡ አባ ፡ ጠቅል ፡ . . . . ፡ የተባለው ፡ ከጋሎች ፡ ልማድ ፡ የተወረሰ ? የፈረስ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ተተካ ፡ ስመ ፡ መንግሥትም ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዮሐንስ ፡ በሚል ፡ አጠራር ፡ እንደ ፡ ተለወጠ ፡ እንመለከታለን ።

የዐፄነት ፡ ስም ፡ ጥንት ፡ ከአኵስሞች ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ጃንሆይ ፡ መባል ፡ ግን ፡ የጀመረው ፡ በኋላ ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ መሆኑን ፡ የራሳቸው ፡ የሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ይገልጽልናል ። አሁን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መጠራት ፡ የተጀመረበትንና ፡ ያቋረጠበትን ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ ለይቼ ፡ ባላውቅ ፡ በግምት ፡ ከ፲፩ኛ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፱ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ከነገሥታቱ ፡ ስያሜ ፡ በኋላ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ለመሳፍንትና ፡ ለመኳንንት ፡ ለሊቃውንትም ፡ የሚሰጠውን ፥ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ከየመጽሐፉ ፡ የሚገኘውን ፡ ለቅሜ ፡ ከሽማግሌም ፡ ጠይቄ ፡ እየተጋጠመ ፡ የተረዳሁትን ፡ በዚህ ፡ ገጽ ፡ እዘረዝራለሁ ።

<u>፩ኛ ፡ ዐፄ-ዐፄጌ ፤—ጃንሆይ ፤-ንጉሠ ፡ ነገሥት ።</u>

ሀ| ዐፄ ፡ ዐፄጌ ፡ (ሐፄ ፡ ወይም ፡ ሐፄጌ) ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በተለይ ፡ የተሰጠ ፡ ስም ፡ ነው ። ይኸ ፡ አጠራር ፡ የመጣበትን ፡ ምንጭ ፡ ሲፈላለግ ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ።

ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሳባ ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ በመጀመሪያ ፡ ዘንዶ ፡ ፬፻ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ፵ ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ነገሠች ። ከርሷ ፡ ቀጥሎ ፡ ልጅዋ ፡ ምኒልክ ፡ ነገሠ ። ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከኛ ፡ በፊት ፡ ማን ፡ ነግሦ ፡ ኖሯል ? ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ "ዕፄ ፡ ትል-ዘንዶ„ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ፡ አሉት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በዕፄ ፡ ዐፄ ፡ ተባሉ ። አንዳንድ ፡ መርማሪዎች ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የላይኛው ፡ ተረት ፡ ነው ። ይልቅስ ፡ ሳባውያን ፡ ካገራቸው ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ ሲመጡ ፡ «ዐጤ„ ፡ የሚባል ፡ ባላባት ፡ ነበራቸውና ፤ በርሱ ፡ ስም ፡ ሳባዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከገቡ ፡ ጀምሮ ፡ ነገሥታቶቻቸውን ፡ „ዐጤ„ ፡ ማለት ፡ አስለመዱ ፡ ይላሉ ።

ለ| ጃንሆይ ፡ መባል ፡ የተጀመረው ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ፈላሾችን ፡ ከደጋ ፡ ስሜን ፡ እያሳ

ደዱ ፡ ጸገዴ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በመንገድ ፡ ሲያልፉ ፡ ብዙ ፡ ባላገር ፡ ተሰብስቦ ፡ «ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ» ፡ ሲል ፡ ሰሙ ። ወዲያው ፡ ጕዟቸውን ፡ አቁመው ፡ ምክንያቱን ፡ ቢጠየቁ ፡ ሰዎች ፡ ጃን ፡ ማለት ፡ ባማራ ፡ ቋንቋ ነጌ-ዝኖን ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ዝሆን ፡ አዝመራ ፡ ሊበላባቸው ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ባላገሩ ፡ ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ ፡ እያሉ ፡ ሲጮኹበት ፡ ይመለሳል ፡ ብለው ፡ አስረዷቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፤ ንግግሩ ፡ ደስ ፡ ስላሰኛቸው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ እኔንም ፡ ደንዞ ፡ ደንዞ ፡ መባሌ ፡ ቀርቶ ፡ ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ ፡ እያላችሁ ፡ ጥሩኝ ፡ እኔም ፡ በችግራችሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኜ ፡ እደርስላችኋለሁ ፡ አሏቸው ....... ይላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ የሊቅ ፡ ንግግር ፡ ለመስማት ፡ ብንከታተል ፡ ስለ ፡ (ጃንሆይ) ፡ ሌላ ፡ ትርጒም ፡ እንደምናገኝ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መባል ፡ የተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አይታወቅም ። ምናልባት ፡ ሌሎቹን ፡ ነገሥታት ፡ መግዛት ፡ በተጀመረበት ፡ በአኵስም ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ።

## ፪ኛ ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ባለቤት ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ደንበኛ ፡ ባለቤቶች ፡ እቴ ፡ እቴጌ ፡ ይባላሉ ። ትርጓሜውም ፡ በዐረብኛ ፡ ትልቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ እንደ ባሎቻቸው ፡ ለነርሱም ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ይወጣላቸው ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ የዐፄ ፡ ናዖድ ፡ ባለቤት ፡ እቴጌ ፡ ሮማን ፡ ወርቅ ፡ (ናዖድ ፡ ሞገሳ) ፤ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ባለ ቤት ፡ እቴጌ ፡ ሥሉስ ፡ ኀይላ ፡ (አድማስ ፡ ሞገሳ) ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ስያሜ ፡ አድማስ ፡ ሰገድ ፡ ከተባለው ፡ ከባለቤታቸው ፡ ከዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ ነው ።

## ፫ኛ ፤ አቤቶ ፡-ማር ።

አቤቶ ፡ አቤቶ ፡ ሁን ፤ የነገሥታት ፡ ልጆች ፡ የሚጠሩበት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ነው ። ዛሬ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አቶ ፡ የሚባለው ፡ ከዚሁ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የጽድቅና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ የሚያዘወትረውን ፡ (ማር) ፡ ይሉታል ። ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ከመንገሣቸው ፡ በፊት ፡ (ማር ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል) ፡ መባላቸው ፡ ከታሪካቸው ፡ ይነበባል ።

## ፬ኛ ፤ ባሕር ፡ ነጋሽ ።

በምጥዋና ፡ በኤርትራ ፡ ጠረፍ ፡ የሚሾመው ፡ (ባሕር ፡ ነጋሽ) ፡ ይባላል ። የርሱም ፡ መቀመጫ ፡ ደባሩአ ፡ ሆኖ ፡ የግዛቱ ፡ ሥልጣን ፡ ከባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ወዲህኛው ፡ ትግሬ ፡ ድረስ ፡ ይዘረጋ ፡ ነበር ። የዚህም ፡ የሹመት ፡ ማዕርግ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የጐጃሙም ፤ (ጐጃም ፡ ነጋሽ) ፡ የዳሞቱም ፤ (ዳሞት ፡ ነጋሽ) ፡ ይባሉ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ የሚሾሙት ፡ ሳይመች ፡ ከሌላ ፡ ዘር ፡ ሲመች ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚወለዱት ፡ ናቸው ።

## ፳ኛ ፤ አዛዥ ፡—አዛዦች ።

በዚሁ ፡ በጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ አራት ፡ ሊቃውንት ፡ ተመርጠው ፡ የአዛዥነት ፡ ማዕርግ ፡ ስም ፡ ይሰጣቸዋል ። እነሱም ፡ በጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ የፍርድ ፡ ጉባኤ ፡ ተቀምጠው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትና ፡ መጽሐፍ ፡ እየጠቀሱ ፡ ይፈርዳሉ ። ማዕርጋቸውም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። እነሱም ፡ ይኸን ፡ ማዕርግ ፡ እንዲያገኙ፡ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ በናታቸው ፡ በኩል ፡ ከመንግሥት ፡ ዘር ፡ እንዲወለዱ ፡ ያስፈልግ ነበር ። በተረፈ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይኸን ፡ የአዛዥነት ፡ ማዕርግ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ፡ ለዘበኞች ፡ አለቃ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለገንዘብና ፡ ለዕቃ ፡ ለመጋዘኛም ፡ ኀላፊዎች ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ፤ ይኸም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲሠራበት ፡ ቆይቷል ።

## ፳፩ኛ ፤ ጸሓፌ ፡ ላሕም—ጸሐፊ ፡ ላም ፡

ጸሓፌ ፡ ላሕም ፤ (ጣፊ ፡ ላም ፤ ጸሐፊ ፡ ላም) ፡ የሚባለው ፤ ላሞችን ፡ ሠንጋዎችን ፡ እየጻፈ ፡ በመዝገብ ፡ የሚይዝ ፤ በኋላም ፡ ለግብር ፡ ለርድ ፡ ለስጦታ ፡ የሚደረገውን ፡ እያደላደለ ፡ የሚያስተዳድር ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ጊዜ ፡ አነጋገር ፡ የወረገኑ ፡ ሹም ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የጸሓፌ ፡ ላሕም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ፡ ማዕርግ ፡ ግን ፡ ከዛሬው ፡ ጊዜ ወረገኑ ፡ በጣም ፡ ይበልጣል ፡ በግዛትም ፡ ታላላቆቹን ፡ ግዛቶች ፡ ዳሞትን ፤ አማራን ፤ ሸዋን ፤ እየተሾመ ፡ የሸዋ ፡ ጸሐፊ ፡ ላም ፤ የዳሞት፡ ጸሐፊ ፡ ላም ፡ ይባላል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ጸሐፊ ፡ ላሕም ፡ በመባል ፡ ፈንታ ፡ «የላም ፡ ራስ» ፡ ይባላል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ ሹመት ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የሚከናወነው ፡ ጮማ በማብላት ፤ ጠጅ ፡ በማጠጣት ስለሆነ ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝብ ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ የሚቀረጠው ፡ በሠንጋና ፡ በላም ፡ በመሆኑ ፡ የዚህን ፡ ክፍል ፡ ኀላፊነት ፡ በመያዙ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ የሚያስቈጥረው ፡ ይሆናል ። ዛሬ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ሚኒስትር ፡ ደላ ፡ አፕሮቪዚዮነማ—ሙጋቤ ፡ ሀገር ፡ የሆነው ፡ ሚኒስትር ፡ ከሌሎቹ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ባንዳንድ ፡ አገር ፡ በልጦ ፡ ይታያል ፡ ይባላልና ፡ ይኸም ፡ ከዚያው ፡ ሳይመሳሰል ፡ አይቀርም ።

## ፳፪ኛ ፤ ጽራግ ፡ (ጅ) ፡ ማሰሬ-ራቅ-ማስሬ ።

ጽራግ ፡ ማሰሬ ፤ ዛሬ ፡ የልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ እንደሚባለው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንግዶቹንና ፡ ማንኛውንም ፡ መኳንንት ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ ከውጭ ፡ ሲመጡ ፡ ተቀብሎ ፡ የሚያስተናግድና ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚያገናኝ ፡ ነው ፡ ይባላል ። በሥርዓት ፡ ንግሥ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥርዓት ፡ ንግሥ ፡ (ቅብዕ) ፡ ሲያደርስ ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬው ፡ ቀርን ፡ ቅብዑን ፤ (የዘይቱን ፡ ቀንድ) ፡ ይዞ ይቆማል ፤ በፍርድም ፡ ጊዜ ፡ በንጉሡ ፡ አደባባይ ፡ ከሌሎቹ ፡ ፈራጆች ፡ ጋራ ፡ ተቀምጦ ፡ ይፈርዳል ።

፰ኛ ፡ ብላታ ፡) ብላቴን ፡ ጌታ ፤—ብላቴንና ፡ ብላቴኖች ፤—ሊቀ ፡ ጥቃቅን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፤ (ሊቀ ፡ ንኡሳን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ) ፤—ታላቅ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፤

(ሊቀ ፡ ዐቢያን ፤ ብላቴን ፡ ጌታ) ።

ብላታ ፡ ወይም ፡ ብላቴና ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡ ነው ። ጥንት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እልፍኝና ፡ እልፍኝ ፡ አዳራሽ ፡ የሚያገለግሉት ፡ ቍጥራቸው ፡ ፴ ፡ የሚሆነው ፡ ወጣቶች ፡ ብላቴኖች ፡ ይባላሉ ፤ ከእልፍኝ ፡ ወደውጭ ፡ ሲወጡም ፡ በጃቢና ፡ በጠባቂ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ብቻቸውን ፡ አይወጡም ። እነሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ባሉት ፡ የነገሥታት ፡ ዘመን ፡ ቍጥራቸው ፡ እስከ ፻፭ ፡ ደረሰና ፡ በ፶ ፡ በ፶ ፡ እምስት ፡ ላይ ፡ ተከፍለው ፡ ግማሾቹ ፡ (ፊረስ ፡ ቤት) ፡ በሚባለው ፡ በዘበኞች ፡ አዳራሽ ፤ ግማሾቹ ፡ (ዘፈን ፡ ቤት) ፡ በተባለው ፡ ንጉሡ ፡ እንግዶችን ፡ በሚቀበልበት ፡ ክፍል ፤ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ (አንበሳ ፡ ቤት) ፡ በሚባለው ፡ በንጉሡ ፡ በግል ፡ እልፍኝ ፡ የሚሠሩ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ራስጌ ፡ ቤቶች ፡ አንጣፊዎች ፤ የእልፍኝ ፡ ዘበኞችና ፡ አሽከሮች ፡ እንደዚሁም ፡ ግማሾቹ ፡ ጭንጫ ፡ አሽከሮች ፡ እንደሚባሉት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

እንደዚሁም ፡ በኋሁ ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እሁለት ፡ ላይ ፡ ተከፍለው ፡ አንደኞቹ ፡ ጥቃቅን ፡ ብላቴኖች ፤ ሁለተኞቹ ፡ ታላላቅ ፡ ብላቴኖች ፡ ተብለው ፡ አለቆቻቸው ፡ የጥቃቅኖቹ ፡ በማርኛ ፡ ጥቃቅን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ በግዕዝ ፡ ሊቀ ፡ ንኡሳን ፡ ብላቴኖች ፤ የትልልቆቹ ፡ ታላቅ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ በግዕዝ ፡ ሊቀ ፡ ዐቢያን ፡ ብላቴኖች ፡ ይባላሉ ። ሥራቸውም ፡ የትንንሾቹ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከርነትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ የውስጥ ፡ አገልግሎት ፡ ሲሆን ፤ የትልልቆቹ ፡ ከእልፍኝ ፡ ውጭ ፡ ዛሬ ፡ ሊጋባ ፡ እንደሚያስተዳድረው ፡ መስሎ ፡ ይታያል ።

በዚህም ፡ ላይ ፤ የማኅተም ፡ ጠባቂነትና ፤ የጸጥታ ፡ ጠባቂነት ፡ (የዘበኛ ፡ አለቅነት) ፡ ሥራ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብአዛዥ ፡ ውስጥ ፡ ይደረብ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

፱ኛ ፡ ከንቲባ ።

ይህ ፡ ስም ፡ ጥንት ፡ ለላይኛውና ፡ ለታችኛው ፡ ሐማሴን ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ የሚሰጥ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ነበር ፤ በኋላም ፡ የደንቢያ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ሲጠራበት ፡ ቈይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ለጐንደርና ዛሬም ፡ ላዲስ አበባ ፡ ከተማ ፡ ገዥዎች ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ረግቷል ።

፲ኛ ፡ ገራድ ፡—መለክ ።

ገራድ ፤ ወይም ፡ መለክ ፡ በዓረብ ? ፡ ሹም ፡ አለቃ ፡ ገዥ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ የእስላም ፡ ወገን ፡ ለሆኑት ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡

ለሱማሌና ፡ ለይፋት ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ የሚሰጥ ፡ ስም ፡ ነው ፤ የግራኝ ፡ መሐመድ ፡ አባት ፡ ኢብራሂምና ፡ ልጁ ፡ ዐቢድ ፡ ገራድ ፤ ኢብራሂም ፡ ገራድ ፤ ዐቢድ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩበት ፡ ነበር ።

## ፲፩ኛ ፤ ትግሬ ፡ መኰንን ።

በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ ሸፍቶ ፡ ከቱርክ ፡ ወዲህ ፡ የርሱን ፡ ሥልጣን ፡ ወስዶ ፡ ? ትግሬን ፡ ለሚገዛው ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ የሚሰጥ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ነው ። በውስጡ ፡ ፲፪ ፡ ባለነጋሪት ፡ አገር ፡ ይገዛ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ከዐድዋ ፡ ምዕራብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሐውዜን ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ ያስተዳድር ፡ ዠመር ። በኋላም ፡ የአጋሜ ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፡ ይኽንኑ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ይዘው ፡ እስከ ፡ ጊዜያችን ፡ ደርሰዋል ።

## ፲፪ኛ ፤ አቃጸን ፡ ሹም ፡ ሠራዌ ፡ (ዬ) ።

ይህ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ከባሕር ፡ ነጋሽ ፡ በታች ፡ ሠራዬን ፡ ለሚገዛ ፡ የሚሰጥ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ሹም ፡ ብሔን ፡ (ቢለን)፡ ሰገድ ፡ ይባላል ። ርሱም ፡ ከአት ፡ ከመ ፡ ምልጋዕ ፡ ከተባለው ፡ ዘር ፡ የወረደ ፡ ነው ።

## ፲፫ኛ ፤ በዓል ፡ ጋዳ–ባልጋዳ ።

በዓል ፡ ጋዳ ፡ ለእንደርታ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ የሚሰጥ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ነው ፤ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከደንከሌ ፡ ጨው ፡ ለሚጭኑ ፡ ተጓዥዎች ፡ አለቃ ፡ ለሆነው ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።

## ፲፬ኛ ፤ ባሻ ፤ ቱርክ ፤ ባሻ ።

ቱርኮች ፤ ምጥዋ ፡ የሚቀመጠውን ፡ ሹማቸውን ፡ ባሻ ፡ ይሉት ፡ ነበር ። በኋላም ፡ የኛ ፡ መንግሥት ፡ እነሱን ፡ ሊወጋ ፡ ከጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚሄደውን ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ባሻ ፤ ወይም ፡ ቱርክ ፤ ባሻ ፡ ይለው ፡ ዠመር ።

## ፲፭ ፤ ሹም ።

በዚህ ፡ ስም ፡ የዋጉ ፤ የሺሬው ፤ የጕራጌው ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፤ ዋግ ፡ ሹም ፤ ሺሬ ፡ ሹም ፤ ጕራጌ ፡ ሹም ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የቀሩት ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ወይም ፡ እየቀረ ፡ ሲሄድ ፡ የላስታው ፤ (የዋጉ) ፡ ዋግ ፡ ሹም ፡ እየተባለ ፡ ይኸው ፡ ከፍ ፡ ባለማዕርግ ፡ እስከ ፡ ጊዜያችን ፡ ደርሷል ፡

## ፲፮ኛ ፤ ቃለ ፡ ሐፄ ።

የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ እየተቀበለ ፡ የሚያስተላልፈው ፡ ቃለ ፡ ሐፄ ፡ ይባላል።

## ፲፯ኛ ፤ ቄስ ፡ ዐፄ ።

ቄስ ፡ ዐፄ ፤ የተባለው ፡ የንጉሡን ፡ ማዕድ ፡ አሳርጎ ፡ የሚባርክ ፡ ለዘወትሩም ፡ የንጉሡ ፡ የንስሐ ፡ አባት ፡ ነው ።

## ፲፰ኛ ፤ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ።

ንጉሡ ፡ ግብር ፡ በሚቀመጥበት ፡ ጊዜ ፡ በትረ ፡ ወርቅ ፡ ይዞ ፡ ቆሞ ፡ የሕግንና ፡ የሥርዓትን ፡ ነገር ፡ ያከናወናል ።

፲፱ኛ ፤ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡
፳ኛ ፤ ሊቀ ፡ ማእምራን ፡
፳፩ኛ ፤ ሊቀ ፡ ደብተራ ፡
የሚባሉት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ናቸው ።

እነዚህንም ፡ የጥቂቶቹን ፡ ባለፈው ፡ የብዙዎችን ፡ ከዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል፡ ዠምሮ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ባሉት ፡ የነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በየሥራቸው ፡ ሲጠሩ ፡ እንመለከታለን ። የቀረው ፡ የራስነት ፤ የቢቶደድነት ፤ (ብሕት ወደድ)፡ የደጃዝማችነት ፤ የጸሐፌ ፡ ትእዛዝነት ፤ የጃንጥራርነት ፤ (ዠን ፡ ጽራርነት)፡ የበጅሮድነት ፤ የፊታውራሪነት ፤ የቀኛዝማችነት ፤ የግራዝማችነት ፤ . . . . የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ከዛሬው ፡ ዘመን ፡ ስያሜ ፡ ጋራ ፡ ልዩነት ፡ ስለሌለው፡ አዝርዝር ፡ ማግባት ፡ አስፈላጊ ፡ አልመሰለኝም ።

በተረፈ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንደምናየው ፡ መኻል ፡ ሰፋሪ ፤ ውሃ ፡ ሥንቁ ፤ -ጋሻ ፡ ጃግሬ ፤ -ራስጌ ፡ ቤት ፡ እንደሚባለው ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጨዎች -ባለሟሎች - ቍርባን-የሐፄ ፡ ሎሌ ፡ . . . . . "የሚባሉ ፡ አዛገሮቻቸው ፡ እነዚያው ፡ ባለፈው ፡ የጠቀስናቸው ፡ አዛዦችና ፡ ብላቴን፡ ጌቶች ፡ ደግሞ ፡ በግዕዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ዘሸሕ ፤ (የሺሕ ፡ አለቃ) ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ዘምዕት ፤ (የመቶ ፡ አለቃ) ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ።

የነገሥታቱ ፤ የመሳፍንቱ ፤ የመኳንንቱ ፤ የእቴጌዎቹ ፤ የሴት ፡ ወይዛዝሩ ፤ የመጠሪያ ፡ ስም ፡ እንደዚሁ ፡ ከሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በንዳንድ ፡ አኳኋን ፡ ይለያያል ። ለምሳሌ ፡ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ባለቤት ፡ ሥሉስ ፡ ኀይላ ፤ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል፡ ባለቤት ፡ ማርያም ፡ ሥና ፤ የዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ እናት ፡ ሐመልማላዊት ፤ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ልጆች ፡ መሲሓዊት ፤ መለኮታዊት ፤ የዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ልጅ ፡ አምላካዊት ፡ . . . ሲባሉ ፤ ወንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ አፈ ፡ ክርስቶስ ፤ መልክአ፡ ክርስቶስ ፡ አትናስዮስ ፤ ሮም ፡ ሰገድ ፡ . . . ይባላሉ ። ይህን ፡ የመሳሰለውን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስያሜ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ ማመሳሰል ፡ ተለምዶ ፡ ነበር ። ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ስያሜ ፡ ባልሳሳት ፡ ከ፲ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የጥቂቶቹም ፡ እስከ ፡ ጊዜያችን ፡ ሲታይ ፡ ከ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲያ ፡ በላስታ ፡ በአኵስም ፡ ይልቁንም ፡ በናጕታ፡

(መርዌ) ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የነበረው ፡ ስያሜ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ካለው ፡ ወይም ፡ ከዛሬው ፡ አማርኛና ፡ ግዕዝ ፡ ጋራ ፡ ባጠራር ፡ አይገናኝም ፡ ትርጉሙም ፡ አይገባም ። ምናልባት ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ቋንቋ ፡ ከዛሬው ፡ ግዕዝና ፡ አማርኛ ፡ ጋራ ፡ በመለያየቱ ፡ ይሆን ፤? ወይም ፡ መርምሮ ፡ የሚጋጠምበትን ፡ የሚያውቅ ፡ ሊቅ ፡ ይገኝ ፡ ይሆን ? ።

አሁን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ አሳባችን ፡ እንመለስ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ የማዕርግና ፡ የመጠሪያ ፡ ስም ፡ በኋላ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ምን ፡ እንደሚባል ፡ በጥቂቱ ፡ እንመልከት ።

ትልቁን ፡ ነጋሪት ፡ «ድብ ፡ አንበሳ» ፡ መለከቱን ፡ «ምስር ፡ ቃና ፡ ወይም ፡ ንስር ፡ ቃና» ፡ ጉራዴን ፡ «ሾተል» ፡ መናገሻ ፡ ከተማን ፡ «መዲና» ፡ ይሉት ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ አነጋገር ፡ እንደ ፡ ሾተል ፡ እንደ ፡ መዲና ፡ ያለው ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሲነገር ፡ ይሰማል ።

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

## ስለ ፡ ጋሎች ፤–የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ጉዞ ፡ ወደ ፡ እናርያ ።

ስለ ፡ ጋሎች ፡ በሰፊው ፡ አላጠናሁም ፡ ቢሆንም ፡ ጋሎች ፡ በዐፄ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የገቡት ፤ አገባባቸውም ፡ ግራኝ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ አባሮ ፡ ሸዋንና ፡ ያማራን ፡ አገር ፡ ሲይዝ ፡ እነርሱ ፡ ከኋላ ፡ እየተከተሉ ፡ አገሩን ፡ ወረሩ ፡ እየተባለ ፡ ባንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፡ በቃል ፡ የሚተረከው ፡ ከእውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ የዘለለ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ጋሎች ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ከመጡና ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ካልነበሩ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ «ሁሉ ፡ ቢፈራ ፡ ቱሉ ፡ እንዴት ፡ ፈራ ፡» ብለው ፡ የተደነቁበት ፡ ከመኳንንቶቻቸው ፡ አንዱ ፡ አጋፋሪ ፡ ቱሉ ፡ ከወዴት ፡ መጣ ? (1) ቱሉ ፡ ያማራ ፡ ስም ፡ ሊሆን ፡ ነውን ? ። ደግሞ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ታሪክ ፡ በሚዠምርበት ፡ በመዠመሪያዎቹ ፡ ገጾች ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተገለጸው ፡ «ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እንደ ፡ ጋሎች ፡ ሥርዐት ፡ የፈረሶቻቸውን ፡ ግንባር ፡ የበረንትቻ ፡ ደም ፡ እየቀቡ ፡ ትምባኾ ፡ እየጠጡ ፡ አምልኮ ፡ ባዕድ ፡ አድርገው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግራኝ ፡ መሐመድን ፡ ላከባቸው ፡ . . . . . . . . .» ይላል ። እንግዴህ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ከግራኝ ፡ በፊት ፡ ጋሎችና ፡ ሌሎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ አብረው ፡ ከመቀመጣቸው ፡ የተነሣ ፡ የጋሎቹን ፡ ሥርዓት ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ አማሮቹ ፡ መውሰዳቸው ፡ አይዶለምን ? ፤ ይህ ፡ ባይሆን ፡ ይህን ፡ ልማድ ፡ ከወዴት ፡ አመጡት ፡ ሊባል ፡ ነው ? ።

ስለዚህ ፡ ጋሎች ፡ እንደ ፡ ሱማሌዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ነው ፡ እያልን ፡ በምንመክበት ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በየምክንያቱ ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በጥቂቱ ፡ በዐፄ ፡

(1) ይህን ፡ ያሉት ፡ ራስ ፡ ደገዛልንና ፡ አጋፋሪያቸው ፡ ቱሉ ፡ በግራኝ ፡ ጦር ፡ ተሸንፈው ፡ በተመለሱ ጊዜ ፡ ነው ፡

ልብነ ፡ ድንግልና ፡ በግራኝ ፡ መካከል ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በየነገዳቸው ፡ የተከፈሉ ፡ ጋሎች ፡ ቍጥራቸውን ፡ አበርክተው ፡ ከደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ ማኽል ፡ ሸዋ ፡ ወደ ፡ ዳሞትና ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ወደ ፡ በጌምድርም ፡ መግባታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ጥንታዊ ፡ ዘራቸውም ፡ የትግሬና ፡ ያማራ ፤ ከሴም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ የጋሎቹም ፡ የወንድሙ ፡ የካም ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ያማራና ፡ የትግሬ ፡ የሸዋ ፡ አብዛኛው ፡ የዘሩ ፡ ምንጭ ፡ ከሰሜን ፡ ከደቡብ ፡ ዐረብያ ፡ ፈልቆ ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ በትግሬና ፡ በሐማሴን ፡ እንደ ፡ ገባ ፤ ጋሎችም ፡ ጥንት ፡ ከእስያ ፡ ወይም ፡ ከአውስትራሊያ ፡ ? ፈልቀው ፡ በሞዛቢክ ፡ በማዳጋስካር ፡ በታንጋኒካ ፡ በኬንያ ፡ በኩል ፡ እያደረጉ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፡ ከሱማሌዎች ፡ ጋራ ፤ ወይም ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሆነው ፡ በዋቢ ፡ ሸበሌና ፡ በጁባ ፡ ወንዝ ፡ በዛሬው ፡ በሲዳሞና ፡ በቦረና ፡ ባሩሲና ፡ በባሌ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምረው ፡ ሲኖሩ ፡ በዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ በብዛት ፡ ተቀስቅሰው ፡ ወደ ፡ ማኽልና ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘልቀው ፡ ቀድሞ ፡ የዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ በኋላም ፡ የዐፄ ፡ሚናስን ፡ አሁንም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ የሠርፀ ፡ ድንግልን ፡ መንግሥት ፡ አውከዋል ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ የነሱሲልን ፡ የነኢያሱን ፡ መንግሥት ፡ ማወካቸውን ፡ እንመለከታለን ።

ነገር ፡ ግን ፡ በታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ እንደምንመለከተው ፡ ከሁሉ ፡ ነገሥታት ፡ ይበልጥ ፡ በጋሎች ፡ ምክንያት ፡ የተቸገሩ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ናቸው ፤ እሳቸውም ፡ ፴፬ ፡ ዓመት ፡ ሰድሜ ፡ ባለው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ሲያርፉ ፡ የቀረውን ፡ ከጋሎች ፡ ጋራ ፡ በመዋጋት ፡ እንዳሳለፉ ፡ ይነግረናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ የፈላሾቹና ፡ የቱርኮቹ ፡ ወዴት ፡ ሊሄድ ፡ ይችላል ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ የዐፄ ፡ ሚናስ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ የሠርፀ ፡ ድንግል ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ መና ፡ እስራኤል ፡ የምትባል ፡ ወተት ፡ ልትጠጣ ፡ ላሎ ፡ ከሚባለው ፡ ከንዱ ፡ የጋላ ፡ ባላባት ፡ ዘንድ ፡ ሄደች ። ላሎም ፡ የቅቤ ፡ ገንፎ ፡ እያበላ ፡ እያደር ፡ ተላምደው ፡ በሽሽግ ፡ ፯ ፡ ልጆች ፡ ከሷ ፡ ወለደ ። የሰባቱም ፡ ስማቸው ፡ ከረዩ ፤ ሜጫ ፤ ቱሎማ ፤ ወሎ ፤ አልካ ፤ ዱረቲ ፤ አያንቱ ፤ ይባላሉ ። ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ወረሞ ፡ የሚባሉት ፡ ያንድ ፡ ነገድ ፡ ጋሎች ፡ በጣም ፡ በረከቱ ። ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልም ፡ በየጊዜው ፡ ቢዋጉም ፡ ቢያሸንፉም ፡ የጋላ ፡ ዘር ፡ እያደረ ፡ እየተተካ ፡ እየበረከተ ፡ አስቸገራቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቢቸግራቸው ፡ መኳንንቶቻቸውንና ፡ ሊቃውንቶችን ፡ ሰብስበው ፡ ‹እነዚህ ፡ የወረሞ ፡ ዘሮች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንወጋቸዋለን ፤ እንገድላቸዋለንም ፤ ነገር ፡ ግን እየበረከቱ ፡ ያድራሉ ፤ ክርስቲያኑ ፡ ግን ፡ ከማነስ ፡ በቀር ፡ አይጨምርም ፡ ምን ፡ ይሻላል ፡ የዚህን ፡ ዝልሀት ፡ ንገሩኝ ፡ . . . .› አሏቸው ። ከተሰበሰቡት ፡ ውስጥ ፡ መዠመሪያ ፡ የመኳንንቱ ፡ ወገን ፡ «ጋሎች ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የላቸውም ፤ አንድ ፡ ወንድ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ሴት ፡ ያገባል ፡ እነዚህም ፡ ብዙ ፡ እየወለዱ ፡ ይረባሉ ። ክርስቲያኑ ፡ ግን ፡ ተመጻዳቂ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ግማሹ ፡ ድንግ

ላይ ፣ እኩሉ ፣ ቄስና ፣ መነኵሴ ፣ ቈራቢ ፣ እየሆነ ፣ በመኖሩ ፣ አይረባምና ፤ ቍጥሩ
እያደር ፣ ያንሳል ፤ . . . . . በዚህም ፣ ላይ ፣ ከክርስቲያኑ ፣ ወገን ፣ ጦርነት ፣ ከሚ
ሄደው ፣ የማይሄደው ፣ ይበልጣል ፤ ይኸውም ፣ ባላገርና ፣ ነጋዴ ፣ ቄስና ፣ ደብተራ ፣
ነው ። ከወታደር ፣ ውስጥ ፣ እንኳን ፣ ፩ኛው ፣ የክፍል ፣ ጦር ፣ አልጋ ፣ ጠባቂ ፣
እየሆነ ፣ ይቀራል ። ከሄደውም ፣ ውስጥ ፣ ጓዝና ፣ ሰፈር ፣ ጠባቂ ፣ ይሆናል ። ጋሎች
ግን ፣ ከመካከላቸው ፣ ድንግላይ ፣ ቄስ ፣ መነኵሴ ፤ ደብተራ ፤ ባላገር ፤ ነጋዴ ፤
አልጋ ፣ ጠባቂ ፤ ጓዝ ፣ ጠባቂ ፣ የላቸውም ። ሁሉም ፣ በነፍስ ፣ ወከፍ ፣ ለጦርነት ፣
ይሰለፋል ። ከብትና ፣ ቤት ፣ የሚጠብቁ ፣ ሴቶችና ፣ ሕፃናቶች ፣ ናቸው ። ከሴ
ቶች ፣ ውስጥ ፣ እንኳን ፣ ኀይለኞቹ ፣ በሠንጋ ፣ ፈረስ ፣ እየወጡ ፣ ሎጋቸውን ፣
ይዘው ፣ ይዋጋሉ ። ደካሞቹ ፣ ሴቶች ፣ ደግሞ ፣ ባሎቻቸው ፣ ወደ ፣ ጦር ፣ ሲሄዱ ፣
ከጋጣ ፣ ፈረስ ፣ ፈተው ፣ ኮርቻ ፣ ጭነው ፣ ያቀብላሉ ፣ ሲመለስም ፣ በቶሎ ፣ ለከ ፣
ተቀብለው ፣ ኮርቻ ፣ አራግፈው ፣ አስረው ፣ ገፈራ ፣ ሰጥተው ፣ እግር ፣ አጥበው ፣
ያገለግላሉ ። ይኸን ፣ በመሳሰለው ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ጋሎች ፣ በክርስቲያኖቹ ፣
ላይ ፣ ለማየል ፣ የቻሉት ፣ . . . » ሲሉ ፣ ዘርዝረው ፣ ተናገሩ ። መኳንንቱም ፣ ከዚህ ፣
በላይ ፣ ያለውን ፣ ተናግረው ፣ ሲጨርሱ ፣ በተራቸው ፣ ሊቃውንቱ ፣ እንደዚህ ፣
አሉ ፣ « ንጉሥ ፣ ሆይ ፣ ይህ ፣ የተነገረው ፣ ሁሉ ፣ እውነት ፣ አይደለም ። መጽሐ
ፍም ፣ ኢይድኅን ፣ ንጉሥ ፣ በብዝኀ ፣ ሠራዊቱ ፣ (ንጉሥ ፣ በሠራዊቱ ፣ ብዛት ፣
አይድንም ፣ ) ይላል ። ከዚያም ፣ አልፎ ፣ ወክልኤቱ ፣ ይሰድድዎሙ ፣ ለእልፍ ፣
(ሁለቱ ፣ ሺውን ፣ ያበሩታል) ፣ ይላል ። ቄስና ፣ ደብተራ ፣ ባላገርና ፣ ነጋዴም ፣
ባይዋጋ ፣ ወደፈጣሪው ፣ እግዚአ ፣ እያለ ፤ ምህላ ፣ እየያዘ ፣ መሥዋዕት ፣ እያሳረገ ፣
በኀዘን ፣ ፪ ፣ እጅ ፣ ጦርነት ፣ ይረዳል ፣ በዘመነ ፣ መሳፍንት ፣ እስራኤል ፣ ቢጠግቡ ፤ አሶራ
ውያንን ፣ ባቢሎናውያንን ፣ አምነግባቸው ፤ . . . . . ዛሬም ፣ አባቶቻችን ፣ ጠግበው ፣
ጦር ፣ አውርድ ፣ ብለው ፣ ያመጧቸውን ፣ ጋሎች ፣ በብዛት ፣ ነው ፤ በማነስ ፣ ነው ፤ ምን ፣
ያሰኛል ፣ በጥጋብ ፣ የመጣውን ፣ በኀዘን ፣ መመለስ ፣ ነው ፣ . . . . . » ብለው ፣
መኳንንቱ ፣ ለተናገሩት ፣ ንግግር ፣ መልስ ፣ ከሰጡ ፣ በኋላ ፣ ንጉሡ ፣ ዐፄ ፣ ሠርፀ ፣
ድንግል ፣ ከመኳንንቱ ፣ ንግግር ፣ ይልቅ ፣ የሊቃውንቱን ፣ ንግግር ፣ ወደዱ ፣ ይላል ።

የሆነ ፣ ሆኖ ፣ ዐፄ ፣ ሠርፀ ፣ ድንግል ፣ ይኸን ፣ ሁሉ ፣ ከፈጸሙ ፣ በኋላ ፣ በጋፋት ፣ ተነ
ሥቶ ፣ የነበረውን ፣ የፋሲሎን ፣ ሽፍትነት ፣ በጦር ፣ ደምስሰው ፣ አገሩ ፣ ሰላም ፣
ከሆነ ፣ በኋላ ፣ ከበጌምድር ፣ ወደ ፣ እናሪያ ፣ ሄደው ፣ ያልገበረውን ፣ ለማስገበር ፣
ይዘጋጁ ፣ ዠመር ፤ ዝግጅቱም ፣ ሲያልቅ ፣ የጕጃሙን ፣ ገዥ ፣ ዘርዐ ፣ ዮሐንስን ፣
ሌሎቹንም ፣ መኳንንቶቻቸውን ፣ አስከትለው ፣ በጦር ፣ ሠራዊታቸው ፣ ታጅበው ፣
ከበጌምድር ፣ ወደ ፣ ዳሞት ፤ ከዳሞት ፣ ወደ ፣ ጉራጌ ፣ አገር ፣ መጥተው ፣ ያልገበረ
ውን ፣ የጋላ ፣ አገር ፣ እያስገበሩ ፣ አስቀድሞ ፣ ከገበረውም ፣ ግብር ፣ እየተቀበሉ ፣
ከዚያ ፣ አልፈው ፣ ወደ ፣ እናሪያ ፣ መጥተው ፣ ባላባቱን ፣ ሴቤንሂ ፣ የሚባለውን ፣
ወደ ፣ ርሳቸው ፣ ግብር ፣ ይዞ ፣ እንዲመጣ ፣ ላኩበት ። ርሱም ፣ ከጋማ ፣ ከብትም ፣
ከቀንድ ፣ ከብትም ፣ ይዞ ፣ ይልቁንም ፣ አገሩ ፣ የወርቅ ፣ አገር ፣ ስለ ፣ ነበረ ፤ ብዙ ፣

ወርቅ ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ንጉሡን ፡ ተገናኘ ፤ ለመኳንንቱና ፡ ለወታደ ሩም ፡ መጥን ፡ ከየባላባቱና ፡ ከየቆሮው ፡ አስመጥቶ ፡ በደኅና ፡ አስተናገዳቸው ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልም ፡ ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ከጉራጌ ፡ በደቡብ ፡ ከእናሪያ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የከምባታን ፡ የኩሎን ፡ አገርና ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ውን ፡ ሁሉ ፡ ሲያቀኑ ፡ የነዚሁ ፡ አገሮች ፡ ባላባቶች ፡ ግብር ፡ ይዞ ፡ በመምጣት ፡ ፈንታ ፡ በጫካ ፡ እየተደበቁ ፡ በንጉሡ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ስለጣሉ ፡ አገራ ቸው ፡ ተዘረፈ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ አገሩን ፡ እየመቱ ፡ ከስገ በሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያቀኑ ፡ መጥተው ፡ ሸዋ ፡ ገቡ ። የሸዋም ፡ ሕዝብ ፡ ከሐዲያን ፡ ሕዝብ ፡ በቀር ፡ ገበረላቸው ። የሐዲያን ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ይበልጡ ፡ እስ ላም ፡ ስለነበረ ፡ ባላባቱን ፡ ዐፄ ፡ ገራድን ፡ ይዞ ፡ ተዋጋቸው ። ይኸም ፡ ባላባት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ንጉሡ ፡ የሾሙትን ፡ ሮም ፡ ሰገድን ፡ የገደለ ፡ ነው ። በኋላ ፡ ግን ፡ ከነሰዎቹ ፡ ተሸነፈና ፡ ያገር ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ቀርበው ፡ ላገሩና ፡ ለገራድ ፡ ምሕረት ፡ ስለ ፡ ለመኑ ፡ ታርቆ ፡ ገባ ፡ የደንቡንም ፡ ግብር ፡ ገበረ ። ከዚህ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዐፄ ፡ ገራድ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየሸፈተ ፡ ታማኝነት፡ ስላልነበረው ፡ በገሩ ፡ ላይ ፡ ደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የማባለውን ፡ ሾመው ወደ ፡ በጌምድር ፡ ተመለሱ ። በኋላም ፡ ይኸው ፡ ገራድ ፡ ከደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ።

በዚሁ ፡ ዘመን ፡ (በሺሕ ፡ ፭፻፺፪) ፡ ጋሎች ፡ ከደቡብ ፡ መጥተው ፡ ሸዋን ፡ ዘር ፈው ፡ ከዚያም ፡ ዐባይ ፡ ደርሰው ፡ ብዙ ፡ ከብት ፡ ዘረፉ ። ይኸንኑ ፡ ንጉሡ ፡ ስለ፡ ሰሙ ፡ የሸዋውን ፡ ደጃዝማች ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ የጐጃሙን ፡ ዘርዐ ፡ ዮሐንስን፡ አስከትለው ፡ የጋሎችን ፡ ዱካ ፡ እየተከታተሉ ፡ አሩሲና ፡ ጉራጌ ፡ መካከል ፡ ዟይ ፡ ከሚባለው ፡ ሐይቅ ፡ ላይ ፡ ደረሱባቸውና ፡ ትልቅ ፡ ውጊያ ፡ ገጠሙ ። ጋሎቹም ፡ ብዙ ፡ ስለነበሩና ፡ ደግሞ ፡ እየተጠራሩ ፡ ስለ ፡ በረከቱ ፡ ጦርነቱ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ፡ ወሰደ ፡ ይባላል ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ተሸንፈው ፡ እጃቸውን ፡ ሰጡ ፡ የቀሩትም ፡ ሸሹ ። የንጉሡም ፡ ወታደሮች ፡ ጋሎቹ ፡ ቀድሞ ፡ ከጐጃምና ፡ ከሸዋ ፡ ከዘረፉት ፡ ከብት ፡ በቀር ፡ የራሳቸውንም ፡ እየጨመሩ ፡ ዘረፉቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጦር ነት ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ የጐጃም ፡ ገዥ ፡ ዘርዐ ፡ ዮሐንስ ፡ (ጐጃም ፡ ነጋሽ) ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ በንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ ኀዘን ፡ ሆኖ ፡ ሰነበተ ።

## ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

## ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ በሐረር ፡ ሡልጣን ፡ በቱርኮችና ፡ በባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ላይ ፡ ያገኙት ፡ ድል ።

ሐረር ፡ ከግራኝ ፡ በሬት ፡ በወላስሞች ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መሪዎች ፡ በሡል ጣኖች ፡ በሚተዳደርበት ፡ ጊዜ ፡ መቀመጫቸው ፡ ሸዋ ፡ ለነበረው ፡ ነገሥታት ፡ ለነ ዐፄ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ ለነዐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ለነዐፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ እየገ በረ ፡ ሲመቸውም ፡ እንቢ ፡ እያለ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ መከላከሉ ፡ ቀርቶ እንዲያውም ፡ የክርስቲያኑን ፡ አውራጃ ፡ ጐጃምን ፡ በጌምድርን ፡ ትግሬን ፡ ሁሉ ፡

ወሮ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፣ በዚህም ፡ ዐይነት ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ በዐፄ ፡ ገላ
ውዴዎስ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ ኑርም ፡ ቢነግሥ ፡ ለጊዜው ፡ እንኳን ፡ ዐፄ ፡ ገላው
ዴዎስን ፡ መግደል ፡ ቢችል ፡ በርሳቸውና ፡ በዐፄ ፡ ሚናስ ፡ ዘመን ፡ ደቡብ ፡ ሸዋን ፡
እስከ ፯ ፡ ዓመት ፡ ቢገዛም ፡ እንደ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ በሙሉ ፡ ለመግዛት ፡
የዐፄ ፡ ሚናስና ፡ የልጃቸው ፡ የሠርፀ ፡ ድንግል ፡ አያያዝ ፡ አላስቻለውም ።

ስለዚህ ፡ ከኑር ፡ መሐመድ ፡ ወዲህ ፡ የተነሡት ፡ ግማሾቹ ፡ ሡልጣን ፣ ግማ
ሾቹ ፡ ይማም ፣ (የግራኝ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ) ፡ ግማሾቹ ፡ አሚር ፡ እየተባሉ ፡ በዚያው ፡
በሐረርና ፡ በውጋዴን ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ አውሳ ፡ ተዛውረው ፡ ሲገዙ ፡ እዚያው ፣
እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በወላስማ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ለመቀመጥ ፡ ይከ
ራከሩ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ለመግፋት ፡ ችሎት ፡ አላገኙም ። በኋላም ፡
ቀድሞ ፡ በነበረው ፡ በሐረርጌ ፡ በአዳል ፡ በሱማሌ ፡ በውጋዴን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የጋላ ፡
ሕዝብ ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ ተደበለቀና ፡ ስለ ፡ ተዋጋም ፡ አስተዳደሩ ፡ ለጊዜው ፡ ለሡ
ልጣኖቹ ፡ መክበዱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የሐረሩና ፡ የአውሳው ፡ ባላ
ባቶች ፡ ስምምነት ፡ አልነበራቸውም ። የሐረሩ ፡ ባላባት ፡ አሚር ፡ ኡትማንና ፡ የአ
ውሳው ፡ ይማም ፡ ገራድ ፡ ጅብሪል ፡ ባገርና ፡ በሴት ፡ ምክንያት ፡ ተጣልተው ፡ እርስ ፡ በር
ሳቸው ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ የሐረሩ ፡ የአውሳውን ፡ አሸንፎ ፡ ገደለው ።
ከርሱም ፣ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ናሲር ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በሐረር ፡ ግዛት ፡ ቈይቶ ፡ መሐ
መድ ፡ ኢብን ፡ ኢብራሂም ፡ የሚባለው ፡ ከግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ዘር ፡ የወረደው ፡
ከብዙ ፡ ክርክርና ፡ ውጊያ ፡ በኋላ ፡ ሺሕ ፡ ፰፻፸፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሐረር ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡
ተቀመጠ ፡ የማዕርግ ፡ ስሙም ፡ እንደ ፡ ግራኝ ፣ ይማም ፡ መሐመድ ፡ ተባለ ።

እሱም ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ምጥዋ ፡ ከሉት ፡ ቱርክ
ችና ፡ ውስጡን ፡ ከሸፈተው ፡ ከባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ ጋራ ፡ እየተላላከ ፡ ውስጠ ፡
ስምምነት ፡ አደረገ ። ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅም ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከዐፄ ፡
ሚናስ ፡ ጀምሮ ፡ ውስጡን ፡ ከልቡ ፡ መንግሥቱን ፡ ከድቶ ፡ ነበርና ፡ ከሐረሩ ፡
ይማም ፡ በመልክት ፡ እየተስማማ ፡ ላዩን ፡ ደግሞ ፡ ታዛዥ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ለዐፄ ፡
ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ይልክባቸው ፡ ነበር ። መልክቱ ፡ ግን ፡ ከልብ ፡ እንዳልሆነ ፡
ንጉሡ ፡ በሰፊው ፡ ተረድተውታል ። ስለዚህ ፡ የባሕር ፡ ነጋሽን ፡ ጦርነት ፡ ለጊዜው
በዘዴ ፡ (በዲፕሎማሲ) ፡ መንገድ ፡ አቆይተው ፡ እሱ ፡ የሚታመንባቸውን ፡ የሐረ
ርጌን ፡ እስላሞች ፡ ለመውጋት ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረጉ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡
ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ታዛዥ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከልብም ፡ ባይሆን ፡ ሲልክ ፡ ለሱ ፡ የሚያስፈል
ገውን ፡ ሽልማትና ፡ የማዕርግ ፡ ልብስ ፡ እርሳቸውም ፡ ያለልብ ፡ ልከው ፡ ካቀዘቀ
ዙት ፡ በኋላ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ የተስማማውን ፡ ይማም ፡ መሐመድን ፡ ለመውጋት ፡
በሺሕ ፡ ፰፻፸፫ ፡ ወይም ፡ ፯ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ።

ይማም ፡ መሐመድም ፡ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መምጣት ፡
በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሐረርን ፡ እንዲጠብቅ ፡ ወንድሙን ፡ ቢዘር ፡ አሕመድን ፡ ከብዙ ፡
ወታደር ፡ ጋራ ፡ ትቶ ፡ በሺህ ፣ ፰፻፸፱ ዓ ፡ ም ፡ መጥቶ ፡ ለጦርነት ፡ ሩቅ ፡ በሩቅ ፡

ተሰልፎ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ቈዩ ፤ ከዚህም ፡ መካከል ፡ አሳአድ ፡ ዲን ፡ የተባለው ፡ እስላም ፡ ይማም ፡ መሐመድን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥቶ ፡ ታርቆ ፡ ገባ ፤ ንጉሡም ፡ ለሌሎቹ ፡ ምሳሌ እንዲሆን ሲሉ ፡ ሽልማት ፡ ሰጥተው ፡ በማዕርግ ፡ አስቀመጡት ።

በዚህም ፡ ጊዜ መሐመድ ፡ ጦርነቱ ፡ ውሎ ፡ ያደረ ፡ እንደሆን ፡ እያደር ፡ ጭፍራዬ ፡ ሁሉ ፡ ይከዳኛል ፤ ሲል ፡ ጦርነቱን ፡ ዠመረና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲዋጉ ፡ ማንም ፡ ሳያሸንፍ ፡ አደረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በማግስቱ ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለጦርነት ፡ ታጥቀው ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ በትላንትናው ፡ ጦርነት ፡ ተዳክመው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አንዋጋም ፡ እያሉ ፡ ያጕረመርሙ ፡ ዠመር ። ይልቁንም ፡ አሳአድ ፡ ዲን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መግባቱንና በማዕርግ ፡ መቀመጡን ፡ የሰሙ ፡ ሹማምንቶች ፡ እየተገለበጡ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጡ። መሐመድም ፡ ከሃምሳ ፡ ፈረሰኞች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሐረር ፡ አምልጦ ፡ ለመሄድ ፡ ሲያስብ ፡ የገዛ ፡ ሰዎቹ ፡ ይዘው ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጡት ፤ በማግሥቱም ፡ ከታማኞች ፡ አሽከሮቹ ፡ ጋራ ፡ ተፈረደበትና ፡ ተገደለ ። ሐረር ፡ ቀርቶ ፡ የነበረውን ፡ ቪዘርንና ፡ ተከታዩን ፡ መንሱርንም ፡ ጋሎች ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሄደው ፡ ስለ ፡ ገደሉት ፡ የሡልጣኖች ፡ ባላባትነት ፡ በጭራሽ ፡ ወደቀ ። የእስላሞቹም ፡ ዋና ፡ መደብ ፡ ከሐረር ፡ ወደ ፡ አውሳ ፡ ዞረ ። አውሳም ፡ የሡልጣኖቹ ፡ መቀመጫ ፡ ሆነና ፡ ሐረር ፡ በሡልጣኑ ፡ ወኪል ፡ እየተገዛ ፡ ከከበቡት ፡ ጋሎች ፡ ጋራ ፡ እየተከላከለ ፤ እስከ ፡ ግብጾች ፡ መምጣት ፡ ድረስ ፡ ቈየ ።

★ ✶

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ተመልሰው ፡ ከቈዩ ፤ በኋላ ፡ የባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ማመጥ ፡ እየተገለጸ ፡ ስለ ሄደ ፡ ከበጌምድር ወደ ትግሬ ለመሄድ ፡ አሰቡ ። በመካከሉ ፡ ባጠገባቸው ፡ ያሉት ፤ ወይዘሮ ፡ ዮልያና ? ፡ እቴ ፡ ወለቴ ፡ አዛዥ ፡ ሐሊቦ ፡ አዛዥ ፡ በእደ ፡ የሚባሉት ፡ የራስ ፡ ወገኖች ፡ ጭምር ፡ እኛ ፡ በደብዳቤ ፡ ተላልከን ፡ ባሕር ፡ ነጋሽን ፡ አስታርቀን ፡ እናስገባዋለንና ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ መዝመትዎ ፡ ይቅር ፡ ብለው ፡ ተሰብስበው ፡ ለመኑዋቸው ። እሳቸውም ፡ ታርቆ ፡ የሚገባ ፡ ከሆነ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ብለው ፡ ከገባም ፡ በኋላ ፡ ላያጕላሉትና ፡ ከሹመቱም ፡ ላይሽሩት ፡ ቃል ፡ ሰጧቸው ፡ እነዚህም ፡ «ባለፈው ፡ ጥፋትኽ ፡ ቅጣት ፡ እንዳያገኝኽ ፡ ከሹመትኽም ፡ እንዳትሻር ፡ ከንጉሡ ፡ ቃል ፡ አግኝተናልና ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቀኽ ፡ እንድትገባ» ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ አዘጋጅተው ፡ በሚያምነው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ላኩለት ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ከቱርኮቹ ፡ ባሻ ፡ ጋራ ፡ ደባሩአ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ስምምነቱን ፡ ይፈጽም ፡ ነበር ። መልእክተኞቹም ፡ ባሕር ፡ ነጋሽን ፡ አግኝተው ፡ ደብዳቤውን ፡ ሰጥተው ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ ድርድር ፡ እንዲገባ ፡ ቢያባብሉት ፡ ባወላዋይ ፡ ንግግር ፡ አሰንብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ "እኔ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ታርቄ ፡ ለሙግባት ፡ እምነት ፡ የለኝም ፡ ንጉሡንም ፡ ከማሙን ፡ ባሻውን ፡ ማመን ፡ ይሻላል ፡ ስለዚህ ፡ ባንድ ፡ ስጋጃ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን ፡ ከቱ

ርኮቹ ፡ ፓሻ ፡ ጋራ ፡ ታርቀናልና ፡ አልመጣም ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ አሲዞ ፡ መል ክተኞቹን ፡ አሳፍሮ ፡ መለሳቸው ። ይኸውም ፡ ሳይበቃ ፡ ቀርቶ ፡ በቱርኮች ፡ መድፍ ፡ መተማመኑንና ፡ መመከቱን ፡ ለማስረዳት ፡ አንድ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ከደብዳቤው ፡ ጋራ ፡ ጨምሮ ፡ ላከላቸው ፡ ይባላል ። መልክተኞቹ ፡ እያዘኑ ፡ ተመ ልሰው ፡ ይኸንኑ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሩ ። አነጋገሩንም ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ ቀሳ ውስቱም ፡ መኳንንቱም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ መድፈሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መበደሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንጉሡን ፡ ብቻ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ እያዘኑ ፡ እየተቆጩ ፡ ተናገሩ ። ንጉሡም ፡ ለዛቻ ፡ የተላከ ውን ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልከው ፡ ጦርነት ፡ አደርጋለ ሁና ፡ ድሉን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይነሣኝ ፡ ቀኖና ፡ ያዙልኝ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ ። ወዲያውም ፡ «አንተ ፡ በራስኸና ፡ በቱርኮች ፡ ትመከለኽ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ኀይለኞችን ፡ በሚጥል ፡ ደካሞችን ፡ በሚያበረታ ፡ በጌታዬ ፡ በኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመክቼ ፡ እመጣብኻለሁ» ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ አስቀድመው ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተጓዙ ። ለግንባር ፡ ቀደሙም ፡ ጦር ፡ ሹም ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ሾሟቸው ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ እነስምዖን ፤ እነአስገዶም ፤ እነክርስቶሳዊ ፤ እነያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥተው ፡ ተደባለቁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ሥርፀ ፡ ድንግል ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ መምጣታቸውን ፡ ዐውቆ ፡ ሳይጠነቀቅ ፡ በድንገት ፡ ደርሰው ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ብዙውን ፡ ሠራዊት ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በትነው ፡ ከጥቂቶቹ ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ ኼደው ፡ ተንቤን ፡ ደረሱ ፤ ተንቤንም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ያገር ፡ ሕዝብ ፡ እየመጣ ፡ መሣሪያ ፡ እየያዘ ፡ ተከተላቸው ፤ አገረ ፡ ገዢው ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ርሳቸው ፡ ተጨመረ ። ወደ ፡ ኋላም ፡ ቀርቶ ፡ የነበረው ፡ ጦር ፡ ደርሶ ፡ ሁሉም ፡ እንቲጨው ፡ ላይ ፡ ሰፈረ ። ባሕር ፡ ነጋሽም ፡ ቱርኮቹን ፡ ሳይጨምር ፡ ከሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ሊገጥማቸው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ምናልባት ፡ ድል ፡ በማድረግ ፡ ፈንታ ፡ ድል ፡ የሆንኩ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ በሥጋት ፡ ተመለሰና ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ወደ ፡ ደባሩአ ፡ ኼዶ ፡ ቱር ኮች እንዲረዱት ፡ ይጐተጉታቸው ፡ ዠመር ። ከዚያም ፡ የቱርኮቹና ፡ የባሕር ፡ ነጋሽ ይስሐቅ ፡ ጦር ፡ ባንድነት ፡ መጥቶ ፡ በሺሕ ፡ ፭፻፸፩ ፡ ዓ፡ ም፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ በዚሁ ፡ በእንቲጨው ፡ ጦርነቱ ፡ ተዠመረ ።

ንጉሡም ፡ የጦርነቱን ፡ ግንባር ፡ እ፫ ፡ ከፍለው ፡ የመከከለኛውን ፡ አዝማ ችነት ፡ ለራሳቸው ፡ ይዘው ፤ የቀኙን ፡ ለሹም ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የግራውን ፡ ላዝማች ፡ ደሃርጎት ፡ ሰጡ ። ቱርኮችም ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ የሌለ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መድፍ ፡ ይዘው ፡ ነበርና ፡ ይኸንኑ ፡ መድፍ ፡ በንጉሡ ፡ ሠራዊት ፡ ላይ ፡ እየደጋገሙ ፡ በተኰሱት ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ ባለመ ሆኑ ፡ ሠራዊቱ ፡ ፍርሃት ፡ አደረበትና ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ለማፈግፈግ ፡ ይሞክር ፡ ዠመር ። ንጉሡም ፡ የመድፉን ፡ ብርታትና ፡ የሕዝቡን ፡ ድንጋጤ ፡ በዩ ፡

ጊዜ ፡ ፈረሰኛ ፡ ፈረሰኛው ፡ ለብቻው ፡ ተመርጦ ፡ እግረኛው ፡ በኋላ ፡ ሆኖ ፡ እንዲዋጋ ፡ በልበ ፡ ሙሉነት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እያሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሞተው ፡ እየሞተ ፡ የተረፈው ፡ በፈረሱ ፡ ሽምጥ ፡ እቱርኮቹ ፡ መድፍ ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ይዋጋ ፡ ገመር ። ቱርኮችና ፡ የባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ሰዎችም ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ በርትተው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ስለተጐዱ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈገፈጉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ «እቴ ፡ ወለቴ ፡ (የንጉሡ ፡ እክ ስት) ፡ ትምጣልኝና ፡ የልቤን ፡ ለርሷ ፡ ነግሬ ፡ እታረቃለሁ ፡ ሲል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መልክት ፡ ላከ ፤ ንጉሡ ፡ አሁንም ፡ ለባሕር ፡ ነጋሽ ፡ የምሕረት ፡ እጃቸውን ፡ ከመዘርጋጀት ፡ አልበዘኑም ።

ስለዚህ ፡ እቴ ፡ ወለቴ ፡ የሚባሉትን ፡ ከሰፈር ፡ አስጠርተው ፡ «ዕርቅ ፡ ከፈ ለግኽ ፡ ከቱርኮች ፡ ሰፈር ፡ ወጥተህ ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ አንድነትም ፡ ሆነን ፡ የሃይማኖ ታችንን ፡ ጠላቶች ፡ (ቱርኮችን) ፡ እንውጋ ፡ ግዛትኽንም ፡ አልወስድብህም ፤ ይህን ፡ ካላደረግኽ ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ ዋሩ ፡ ነጭ ፡ ቢሆን ፤ ወንዞች ፡ ሽቅብ ፡ ቢፈሱ ፡ ወዳ ጅነት ፡ የለኝም ፡ ብሷል ፡ ብለሽ ፡ ንገሪው» ፡ አሏት ። እርሷም ፡ ወደርሱ ፡ ሰፈር ፡ ሄዳ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ብትነግረው ፡ የራሷንም ፡ የግል ፡ ምክር ፡ ብታቀርብለት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አሳቡ ፡ ተለወጠና ፡ «እንዴት ፡ አድርጌ ፡ እኔን ፡ ሊረዱኝ ፡ የመጡ ትን ፡ ቱርኮች ፡ ልክዳቸው ፡ አላደርገውም ፡ ?» ሲል ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ መለሳትና ፡ የቆመው ፡ ጦርነት ፡ እንደገና ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ ይቀጥል ፡ ገመር። ጦርነቱም ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ በረታ ፤ ከንጉሡ ፡ ወገን ፡ ጂሎ ፡ የሚባለው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ከጠታደሩ ፡ ጋራ ፡ እጦርነቱ ፡ ማኽል ፡ ገብቶ ፡ በጐራዴ ፡ ሲዋጋ ፡ ተመቶ ፡ ወደቀና ፡ ሞተ ። እንደዚሁም ፡ ከነዚያ ፡ ወገን ፡ ራሱ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ እጭፍሮቹ ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ከንጉሡ ፡ አሽከሮች ፡ አንዱ ፡ ገርባውን ፡ በጦር ፡ ክፉኛ ፡ ወጋው ። እርሱም ፡ ደሙን ፡ እያዝረከረከ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመልሶ ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ እጥላ ፡ ሥር ፡ ተኛ ፤ አሽከሮቹም ፡ ልብስ ፡ አለበሱትና ፡ ወዲያው ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈየ ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ተለየች ።

የቱርኮችም ፡ አለቃ ፡ ፓሻ ፡ ከድወርክ ፡ ወይም ፡ ከዳውር ፤ የሚባለው ፡ በወ ርቅ ፡ የተቀባ ፡ የራስ ቍሩን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ደፍቶ ፤ የወርቅ ፡ ሰይፍ ፡ በጐኑ ፡ አንግቦ ፤ የወርቅ ፡ ጦር ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ጨበጠ ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ድል ፡ ለመሆን ፡ ያዘነበለው ፡ ጦሩ ፡ በመጨረሻ ፡ ኀይል ፡ እየተዋጋ ፡ ሲሞት ፡ ይመለከት ፡ ነበርና ፤ አቤቶ ፡ ዮናኤል ፡ የተባለ ፡ ደፋር የንጉሡ ፡ ዘመድ ፡ ወር ሙሮ ፡ ልቡን ፡ በጦር ፡ ወጋውና ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ገለበጠው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮናኤል ፡ ተንደርድሮ ፡ ደረሰና ፡ ዳዊት ፡ በጎልያድ ላይ ፡ እንዳደረገው ፡ የራ ሱን ፡ የፓሻውን ፡ ሰይፍ ፡ ከወገቡ ፡ መዞ ፡ ራሱን ፡ ቈርጦ ፡ ለንጉሡ ፡ ለዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ አመጣና ፡ ፎከረላቸው ። ለርሱም ፡ እንደ ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲ

ሆነው ፡ «የንጉሡ ፡ ሎሌ ፡ ዮናኤል ፡ ባሻውን ፡ ገደለው ፡ በሾተል» ፡ ተብሎ ፡ የድኅ ምልክት ፡ ሆኖለት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይነገርለታል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቱርኮች ፡ በፓሻው ፡ ሞት ፡ የባሕር ፡ ነጋሽም ፡ ሰዎች ፡ በጌታቸው ፡ ሞት ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ቈረጡና ፡ ብዙም ፡ ወታደር ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ስላለቀ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የከዱት ፡ ጉደርና ፡ አስገዶም ፡ የባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ወንድም ፡ ከብዙ ፡ ቱርኮች ፡ ጋራ ፡ እጃቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ተማረኩ ፤ የቀሩትም ፡ ሸሹ ። በእስላሞቹም ፡ ሰፈር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ ዕቃ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልብስና ፡ ጌጥ ፡ በወታደሮቹ ፡ እጅ ፡ የነበረው ፡ መድፍና ፡ ጠመንዣ ፡ ተማረከ ። የምጥዋም ፡ ጠረፍ ፡ ተመልሶ ፡ በንጉሡ ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እጅ ፡ ገባ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ እድንኳናቸው ፡ ተመልሰው ፡ የባሕር ፡ ነጋሽንና ፡ የፓሻውን ፡ የተቈረጠ ፡ ራስ ፡ ባንድ ፡ ስጋጃ ፡ ላይ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አስቀምጠው ፡ «ኑና ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሠራውን ፡ ተአምራት ፡ ተመልከቱ» ፡ ብለው ፡ በዚያ ፡ ለነበሩት ፡ ለታላላቆቹ ፡ ሰዎች ፡ አሳዩዋቸው ። ይኸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ታርቀኝ ፡ ግባ ፡ ላሉት ፡ መልክተኞች ፡ «እኔና ፡ ፓሻ ፡ ባንድ ፡ ስጋጃ ፡ ተቀመጥን ፡ ታርቀናል» ፡ ያለውን ፡ ለመበቀል ፡ ወይም ፡ ለማስታወስ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ርሳቸውን ፡ ከድተው ፡ ወደ ፡ ቱርኮች ፡ የገቡትን ፡ እነመናድሌዎስን ፡ እነከቲባ ፡ እንግዳዜንን ፡ (ጼን-ጽዮን) ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በጉባኤ ፡ እያስፈረዱ ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ቀጧቸው ።

በታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ከዚህ ፡ ፍርድ ፡ በኋላ ፡ በታኅሣሥ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ከአዲ ፡ ቆሮ ፡ ወደ ፡ ደባሩአ ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ፡ የርሳቸውንም ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ የደባሩአን ፡ ከተማና ፡ ምሽግ ፡ የሚጠብቁት ፡ ቱርኮች ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ የንጉሡ ፡ ባሮች ፡ ነን ፡ እዚህም ፡ በእጃችን ፡ ያለው ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ለንጉሡ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፤ ታማኝ ፡ ሰው ፡ ይላኩልንና ፡ እናስረክብ ፡ ብለው ፡ ላኩ ። ንጉሡም ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተረካቢ ፡ ስብሐት ፡ ለአብና ፡ ቍርባነ ፡ ሕይወት ፡ የሚባሉትን ፡ ሹማምንቶች ፡ በመዠመሪያ ፡ አስቀድመው ፡ ላኩ ። በኋላም ፡ አበ ፡ ንዋይ ፡ የተባሉትን ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሊቅነት ፤ ባማካሪነት ፤ በኀይለኛነት ፡ የታወቁትን ፡ ለሁሉም ፡ የበላይ ፡ ተረካቢና ፡ ለጊዜው ፡ አስተዳዳሪ ፡ አድርገው ፡ ላኳቸው ። ቀጥሎም ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው ፡ ወደ ፡ ደባሩአ ከተማ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ ተቀበሏቸው ። ቱርኮቹ ፡ ራሳቸውም ፡ ለራሳቸው ፡ አለቃ ፡ ያደረጉት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ አስፈቅደው ፡ የደስታ ፡ መድፍ ፡ እየተኰሱ ፡ ተቀበሏቸው ። በገቡም ፡ ጊዜ የባሕር ፡ ነጋሽን ፤ የቱርኮቹንና ፡ የፓሻቸውን ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ቀድመው ፡ የሄዱት ፡ ሹማምንት ፡ የተረከቡትን ፡ ካዩ ፡ በኋላ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚገባውን ፡ አስቀርተው ፡ የቀረውን ፡ ለየመኳንንቱ ፡ ለየወታደሩ ፡ አከፋፈሉት ። በማግስቱም ፡ የገናን ፡ በዓል ፤ በዚያው ፡ አክብረው ፡ ዋሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የድሉን ፡ በዓልና ፡ ሥርዓት ፡ ንግ

ማቸውንም ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ በጥንታዊቱ ፡ ከተማ ፡ በአኵስም ፡ ጽዮን ፡ በሚገባ፡ ለማክበር ፡ ከደባሩአ ፡ ተመልሰው ፡ በጥር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ አኵስም ፡ ገቡ ።

አኵስም ፡ ሲገቡ ፡ የተደረገላቸው ፡ አቀባበል ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታቸው በሰፊው፡ ይተርከዋል ። ካህናቱና ፡ ቀሳውስቱ ፡ ያማረ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኒቸውን ፡ ለብሰው ፡ የወርቅ ፡ መስቀልና ፡ ጃንጥላ ፡ ይዘው ፡ ንሴብሖ ፡ እያሉ ፡ በከበሮ ፡ በጸናጽል ፤ መሳፍንቱ ፤ መኳንንቱ ፡ የበዓል ፡ ልብሳቸውን ፡ እንደ ፡ ለበሱ ፡ «የጨዋ፡ ክፍል» ፡ «የቍርባን ፡ ክፍል» ፡ በሚባለው ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ግማሹ ፡ በፈረስ ፡ የቀረው ፡ በበቅሎ ፡ ታጅቦ ፡ "ሳንቲ" ፡ የሚባለው ፡ መለከት ፡ "ንስረ» ፡ ወይም ፡ «ምስረ፡ ቃና» ፡ የሚባለው ፡ ጥሩምባ ፡ እየተነፋ ፤ «ድብ ፡ አንበሳ» ፡ የሚባለው ፡ ነጋሪት ፡ እየተጐሸመ ፤ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የወንዱ ፡ ሆታ ፤ የሴቱ ፡ እልልታ ፡ እያስተጋባ ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ አኵስም ፡ ገብተው ፡ የንግሥና፡ የድሉ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ግብር ፡ ሲያበሉ ፡ ሲሾሙ ፡ ሲሸልሙ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ የልብስ ፡ ስጦታ ፡ ሲያደርጉ ፡ ሰነበቱ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እዚህ ፡ የቈየሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወታደሩም ፡ ሕዝቡም ፡ በምግብ፡ ረገድ ፡ መቸገሩ ፡ አይቀርም ፡ በቀርው ፡ አውራጃም ወስላታ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተነሥቶ ፡ አገር ፡ እንዳያስቸግር ፡ ብለው ፡ ከአኵስም ፡ ንቡረ ፡ እድና ፡ ከመኳንንቱ ፤ ከቀሳውስቱም ፡ ተሰነባብተው ፡ ከአኵስም ፡ ወደ ፡ እንፍራዝ ፡ (ጽ) ፡ ተመለሱ ። በዚያም ፡ መኳንንቶቻቸውን ፡ የዳሞቱን ፡ ጳሕፈ ፡ ላሕም ፤ የሸዋውን ፡ ጳሕፈ ፡ ላሕም ፤ ጐጃም ፡ ነጋሽን ፤ ወሊጋ ፡ ነጋሽን ፤ የባሌን ፡ ገራድ ፤ የጋንዝን ፡ (ገንጭ? ) ፡ ገራድ፡ እያሰናበቱ ፡ የየክፍል ፡ አገራቸውን ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ላኳቸው ።

የዚህን ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልን ፡ ታሪክ ፡ ከጻፈው ፡ ከወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ ጽሑፍና ፡ ከእንግሊዝ ፡ ከጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እየለቀመ ፡ አጠራቅሞ ፡ ከጻፈው ፡ ከኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ መጽሐፍ ፡ ም ፲፭ና፡ ፲፮ ፡ ከ፻፺፯ ፡ ገጽ ፡ እስከ ፡ ፻፫ ፡ ገጽ ፡ ያለውን ፡ ተመልከት ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፴፫ ።

### ስለ፡ ስሜን ፡ ፈላሾች ፤-ስለ ፡ እናሪያ ፡ ጕዞ ፤ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ቱርኮችን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሰሜናዊ ፡ ጠረፍ ፡ ለማጥፋት ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ይኸን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የጦርነት ፡ ድል ፡ በቱርኮችና ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ በተደረበው ፡ ዜጋቸው ፡ በነበረው ፡ በባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ ላይ ፡ አግኝተው ፡ ከደባሩአ ፡ አኵሱም ፤ ከአኵስም ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ረዥም ፡ የሰላም ጊዜ ፡ አላገኙም ። ኢትዮጵያ ሰፊ ፡ ናት ፤ ከዐፄ ፡ ልብ ፡ ድንግልና ፡ ከልጆቻቸው ፡ እወለዳለሁ ፤ ዙፋን ፡ ይገባኛል ፡ የሚለው ፡ ብዙ ፡ ነው ። ከልብነ ፡ ድንግልም ፡ ባይወለድ ፡ ዘሬ ፡ ከፈላሻ ፡ ይሁዲ ፤ ከላስታ ፡ የዛጔ ፡ ዘር ፤ ከሐረርጌ ፡ ወላስሞች ፤ ከትግሬና ፡ ከሐማሴን ፤ ባላባት ፡ የመጣ ፡ ነውና ፤ መንግ

ሥትን ፡ መያዝ ፡ እችላለሁ ። ይኸም ፡ ባይቻል ፡ ለጐንደሩ ፡ መንግሥት ፡ ሳልገ ብር ፡ ባገሬ ፡ በወንዜ ፡ ነፃ ፡ ሆኜ ፡ እቀመጣለሁ ፡ የሚለው ፡ የዚያን ፡ ያኸል ፡ ነው ። በቅርብ ፡ ጊዜ፡ደግሞ ፡ ከደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የፈለቁትና ፡ ቍጥራቸው ፡ የበረከተው ፡ ጋሎች ፡ ግማሾቹ ፡ ተገዥም ፡ ተዋጊም ፡ ሆነው ፡ የንጉሡ ፡ አገልጋይ ፡ ቢሆኑም ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ በየጊዜው ፡ የሚያደርጉት ፡ ወረራ ፡ በመንግሥቱ ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ መፍጠሩ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ደንበኛ ፡ ጸጥታ ፡ ጠባቂና ፡ የክፍል ፡ ደንበኛ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በያውራጃው ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ማስቀመጥ ፡ ባለመቻሉ ፡ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ጊዜ ፡ ፍጥነት ፡ ያለው ፡ የማመላለሻ ፡ መኪናና ፡ መን ገድ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ባለመኖሩ ፡ ቀንደኛ ፡ ባላባት ፡ በያገሩ ፡ ለመነሣት ፡ ለጊዜው ፡ የሚያስቸግረው ፡ ነገር ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ አንደኛውን ፡ አውራጃ ፡ በሠ ራዊት ፡ ብዛትና ፡ ኀይል ፡ ለማቅናት ፡ ሲሄዱ ፡ ሌላው ፡ ይሸፍታል ። ያንንም ፡ በኀይል ፡ ደምስሰው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ የተደመሰሰው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንሰራ ርቶ ፡ ያምጥና ፡ ግብር ፡ ይከለክላል ። ከዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ነገሥታቱ ፡ ብዙውን ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሸፈተው ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ በሚያደርጉት ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ የሚያልቀው ፡ ያንዲቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ ዛሬ ፡ ያለነው ፡ ሕዝቦች ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰን ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ስናነብ ፡ ኀዘን ፡ እንደሚመጣብን ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንደዚህም ፡ በየ ጊዜው ፡ ባያልቅ ፡ ኖሮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በ፫ክፉ ፡ ምንኛ ፡ ኀይለኛ ፡ በሆነ ፡ የሚል ፡ የጸጸት ፡ መንፈስ ፡ ሳይመጣብን ፡ አይቀርም ። የንጉሡም ፡ የዘወትር ፡ አሸናፊነታቸው ፡ ሊያጽናናን ፡ አይችልም ።

ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ከአኵሱም ፡ በሺህ ፡ ፳፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደ ፡ ሌሎቹም ፡ አቈጣጠር ፡ በ፷፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጌምድር ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ከፈላሾች ፡ ጋራ ፡ ያደረጉትን ፡ አሳዛኝ ፡ ጦርነት ፡ ልንመለከት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ ፈላሾች ፡ የተባሉት ፡ እነማን ፡ መሆናቸው ፡ ትዝ ፡ ለማይለው ፡ አንባቢ ፡ መረጃ ፡ የሚሆን ፡ ስለ ፡ ፈላሾች ፡ ጥቂት ፡ መጻፍ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ይመስለኛል ።

ከጥንት ፡ ተያይዞ ፡ ከአኵስም ፡ የመጣው ፡ ታሪክ ፡ እንደሚገልጸው ፡ በቀዳ ማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ (ሺህ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት)፡ ብዙ ፡ እስራኤላውያን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ከካህናቱም ፡ ወገን ፡ አብረው ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የኦሪት ፡ ሕግ ፡ አስተምረው ፡ በጣዖት ፡ ያመልክ ፡ የነበረውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንዲያመልክ ፡ አድርገውታል ። ከኢየሩሳሌም ፡ የመጡትም ፡ የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ በሃይማኖትም ፡ በጋብቻም ፡ ከቀረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅለው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሮማ ፡ አውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባዚን ፡ በነገሠ በት ፡ ዘመን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወለደ ። በጢባርዮስ ፡ ቄሣርም ፡

ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የመሠረተውን ፡ የክርስትና ፡ ትምህርት ፡ ከክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኢትዮጵያ ፡ አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ የሚባሉት ፡ ሁለቱ ፡ ወንድማማች ፡ ነገሥታት ፡ በስምምነትና ፡ በፍቅር ፡ በምክር ፡ አንድነት ፡ በሚገዙበት ፡ ዘመን ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የተባሉት ፡ አባ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ክርስትናን ፡ አስተምረው ፡ ነገሥታቱንና ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ አከባቢ ፡ ሁሉ ፡ የአሪትን ፡ ከህናት ፡ እነእንበረምን ፡ ጭምር ፡ ክርስቲያን ፡ ሲያደርጉ ፡ የቀሩት ፡ ከእስ ራኤል ፡ ወገን ፡ የሆኑት ፡ አሁን ፡ ፈላሾች ፡ የምንላቸው ፡ በዚያው ፡ በአሪት ፡ ሕግ፡ጸን ተው ፡ ክርስትናን ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፡ ለብቻቸው ፡ ወገን ፡ ለይተው ፡ ተቀመጡ ። ይኸም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በዋናው ፡ የእስራኤል ፡ አገር ፡ ሐዋርያት ፡ እንቅዱስ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ እንቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መዠመሪያ ፡ አሪታውያን ፡ ሆነው ፡ በኋላ ፡ በክርስ ቶስ ፡ አምነው ፡ ሐዋርያነትንም ፡ ተቀብለው ለቀሩት ፡ አይሁዶች ፡ ክርስትናን ፡ ቢያስተምሩ ፡ ግማሾቹ ፡ አይሁዶች ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ሲቀበሉ ፡ የቀሩት ፡ እንቢ ፡ ካሏቸውና ፡ በአሪት ፡ ከጸኑት ፡ ጋራ ፡ የሚመሳሰሉ ናቸው ።

በኋላም ፡ በዚሁ ፡ ሃይማኖት ፡ የተነሣ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ቢያውኳቸው ፡ እስራ ኤሎቹ ፡ ዋናውን ፡ ከተማ ፡ አኵስምን ፡ ለቀው ፡ በስሜን ፡ በወልቃዪት ፡ በወገራ ፡ የአሪትን ፡ ሃይማኖት ፡ ይዘው ፡ ይኖሩ ፡ ዠመር ። በኋላም ፡ የእስላሞች ፡ ኀይል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እየተጫነ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ከነዚሁ ፡ ከእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ አገራቸ ውን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እየተዉ ፡ (እየፈለሱ) ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ ወደ ፡ ስሜንና ፡ ወደ ፡ ወገራ ፡ መጥተው ፡ ተቀመጡ ። አገራቸውንም ፡ እየተዉ ፡ ከመምጣታቸው ፡ የተነሣ ፡ ፈላሾች ፡ (ፈላስያን ፡ አገር ፡) ለቀው ፡ (ሂያ ጆች) ፡ ተባሉ ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ከያለበት ፡ ተሰብስበው ፡ ዘራቸው ፡ በበረከተ ፡ ጊዜ ፡ በላያ ቸው ፡ ጌዴዎን ፡ የተባለውን ፡ አንግሠው ፡ ነበረ ፡ በኋላም ፡ የአኵስሙ ፡ ንጉሥ ፡ አንበሳ ፡ ውድም ፡ ሕፃን ፡ በነበረና ፡ ዐቅሙ ፡ ደክም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የጌዴዎን ፡ ልጅ ፡ ዮዲት ፡ የተባለች ፡ በ፰፻፵፫ ፡ ላይ ፡ የአኵስሙን ፡ መንግሥት ፡ ገልብጣ ፡ እርሷ ፡ ዓርባ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ነገሠች ፡ የርሷም ፡ መንግሥት ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ ፡ ዛጔ ፡ የሚባለው ፡ የላስታ ፡ መንግሥት ፡ መቆሙን ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በመዠመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ በ፳ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ጠቅሰናል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዮዲት ፡ ዘመን ፡ መንግሥትን ፡ ለመያዝ ፡ ሞክረው ፡ የነበሩት ፡ ፈላሾች ፡ (ይሁዳዎች) ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ዛጔዎች ፡ (ላስቶች) ፡ መዠመሪያ ፡ ቢያሰ ናክሏቸው ፡ በኋላም ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የወረደው ፡ ይኩኖ ፡ አምላክና ፡ ተከታ ዮቹ ፡ ባያሲዟቸው እነዚሁ ፡ ፈላሾች ፡ ተራራማ ፡ በሆነው ፡ በስሜን ፡ አውራጃ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ አጽንተው ፡ ዘራቸውን ፡ አበርክተው ፡ ከመኖር ፡ አላቋረጡም ።

እነሱም ፡ ሲመቻቸው ፡ ለነገሥታቱ ፡ አንገብርም ፡ እያሉ ፡ በባላባቶቻቸው ፡ መሪነት ፡ እየተዋጉ ፡ ሳይመቻቸውም ፡ እየገበሩ ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ደረሱ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ፀሔ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ከቱርኮች ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ በሺሕ ፡
፩፻፷፱ ፡ ዓ፡ ም፡ ፡ ፈላሾች ፡ ከስሜንና ፡ ከወገራ ፡ መንደራቸው ፡ እያለፉ ፡ የወገራን ፡
አውራጃ ፡ ዘረፉት ፡ ቤቱንም ፡ አቃጠሉት ፡ ሕዝቡንም ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡
እንደ ፡ ባሪያ ፡ ያጉላሉት ፡ ዝመር . . . . . . ፡ »የሚል ፡ መልክት ፡ መጣላቸው ።
ታሪክ ፡ ነገሥታቸው ፡ እንደሚለው ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በንዴት ፡ ተቃጠሉ ፤
ወዲያው ፡ እንደ ፡ ተለመደ ፡ ባዋጁ ፡ ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ በየክፍሉ ፡ እንዲሰበሰብ ፡
አደረጉ ። ከተሰበሰበም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ከጉባኤ ፡ ወደ ፡ ወገራ ፡
ተጓዙ ፡ በቀስታ ፡ ተጕዘው ፡ ከሦስት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ በታኅሣሥ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡
ዋናው ፡ የፈላሾቹ ፡ አዝማች ፡ ጕሺን ፡ (ጕአሺን) ፡ ከነጭፍራው ፡ ወደ ፡ መሸገ
በት ፡ ተራራ ፡ (አምባ) ፡ ተጠጉ ። እንደ ፡ ደረሱም ፡ ፈላሾች ፡ ከተራራው ፡ እየ
ወረዱ ፡ የሚቀዱትን ፡ ውሃ ፡ በዘበኛ ፡ ከበው ፡ ያስጠብቁት ፤ ዝመር ። ይኸም ፡
ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ አዝማች ፡ ዳህራቆት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፤
ሳዊሮስ ፡ የተባለው ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ ሲሆኑ ፤ ዮናኤል ፡ ሹም ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፤
ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፤ ወሰንጌ ፤ አብርሃም ፡ የሚባሉ ፡ ጭፍራ ፡ ጭፍራቸውን ፡ እየ
ያዙ ፤ አምባውን ፡ ከበው ፡ ተቀመጡ ።

በዚህ ፡ መክከል ፡ የፈላሾቹ ፡ (የይሁዲዎቹ) ፡ አለቃ ፡ ሰላማዊነቱን ፡ የሚ
ገልጽ ፡ መልክት ፡ ልኮ ፡ የንጉሡም ፡ ወታደሮች ፡ ይኸንኑ ፡ አምነው ፤ መዋጋቱን ፡
ችላ ፡ ብለው ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ አዘንግቶ ፡ ከተራራው ፡
አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ፈጀ ። በዚሁም ፡ ጦርነት ፡ ዋናውና ፡ የታወቀው ፡
የንጉሡ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ ከብዙ ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ በው
ጊያው ፡ ላይ ፡ ሞተ ። የዕቁበ ፡ ሚካኤልን ፡ ሞት ፡ ንጉሡ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በን
ዴት ፡ ላይ ፡ ንዴት ፡ ተጨመረባቸው ። ወዲያው ፡ ባጠገባቸው ፡ የነበረውን ፡
(መቃቢስ) ፡ (1) ፡ የተባለውን ፡ ሌላ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ አዲስ ፡ ጭፍራና ፡ የውስጥ ፡
ብላቴኖችን ፡ ይዞ ፡ ሄዶ ፤ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ የነበረበትን ፡ ሥፍራና ፡ ውሃ ፡ ጸንቶ ፡
እንዲይዝ ፡ አዘዙት ። እርሱም ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ ሄዶ ፡ ከፈላሾቹ ፡ ጋራ ፡ ባዲስ ፡
ኀይል ፡ ተዋግቶ ፡ አሸንፎ ፡ ውሃውንና ፡ ተራራውን ፡ መልሶ ፡ ያዘ ። ፈላሾችም ፡
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተሸንፈው ፡ ዋናውን ፡ ሠፈራቸውንና ፤ ጓዛቸውን ፡ ወደ ፡ አደረጉ
በት ፡ ከፍተኛው ፡ ተራራ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ ሆነው ፡ በጥብቅ ፡ መከበባቸውን ፡
ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ ገዣቸው ፡ ሆኖ ፡ ያውቁት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ «ዮናኤል ፡ ይም
ጣልንና ፡ ባለፈው ፡ ጥፋታችን ፡ ምሕረት ፡ ተደርጎልን ፡ እንግባ» ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ
የታላላቅ ፡ ብላቴኖች ፡ አዝማች ፡ ለሆነው ፡ ለወሰንጌ ፤ ለጥቃቅን ፡ ብላቴኖች ፡ አዝ
ማች ፡ ለሆነው ፡ ለዚሁ ፡ ለመቃቢስ ፤ እንደዚሁም ፡ በኀይሉና ፡ በተዋጊነቱ ፡
ለታወቀው ፡ ለተዝካሮ ፡ ላኩ ፡ ይባላል ። እነርሱም ፡ ከፈላሾቹ ፡ የመጣውን ፡
ደብዳቤ ፡ ለንጉሡ ፡ አስተላለፉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ አቤቶ ፡ ዮናኤልን ፡

(1) ይህ ፡ አጠራር ፡ ልክ ፡ ይሆን ።

አስጠርተው ፡ ሂደኸ ፡ በቀል ፡ ሳታደርግና ሳታጉላላ ፡ ዕርቅ ፡ ከጠየቁ ፡ ተነጋገራቸው ፡ አሉት ። እርሱም ፡ ወደታችኛው ፡ ተራራ ፡ ወጥቶ ፡ ተገናኛቸው ። የንጉሡንም ፡ ምሕረታዊ ፡ አሳብ ፡ ገለጠላቸው ፤ እነርሱም ፡ በዚሁ ፡ ደስ ፡ ተሰኝተው ፡ እንደ ፡ ቄዩ ፡ ግማሾቹ ፡ ከድተው ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ለማምለጥ ፡ ሲያስቡ ፡ ዮናኤል ፡ አባሮ ፡ ደረሰና ፡ የቆመው ፡ ጦርነት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተዠመረ ። በመጨረሻም ፡ ዮናኤል ፡ አሸንፎ ፡ ማረካቸው ፤ የቀሩትንም ፡ ብዙዎቹን ፡ ፈጃቸው ። እንደዚሁ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ነቢያቸው ፡ የነበረውን ፡ «እንድምርኸ ፡ የፈለግህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ ለምነኝና ፡ ልተውኸ» ፡ ብሎ ፡ ዮናኤል ፡ ቢጠይቀው ፡ የፈላሾቹ ፡ ነቢይ ፡ «አታውቅምን ፡ ለኛ ፡ ለፈላሾች ፡ የማርያምን ፡ ስም ፡ በፋችን ፡ ማንሣት ፡ እንደማይገባን ፤ ይልቅስ ፡ የወገኔን ጥፋትና ፡ ስድብ ፡ ከማይበት ፡ ከዚህ ፡ ከጨለማ ፡ ዓለም ፡ ለኔ ፡ መሞት ፡ ይሻለኛልና ፤ በቶሎ ፡ ግደለኝ» ፡ አለው ። ዮናኤልም ፡ ከመኖር ፡ መሞትን ፡ እንተው ራስኸ ፤ ከፈለግኸ ፡ ጠጋ ፡ በል ፡ ብሎ ፡ በሰይፍ ፡ አንገቱን ፡ መታውና ፡ ገደለው ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ዕርቁ ፡ ፈረሰና ፡ ባንደኛው ፡ ተራራ ፡ ጕሼን ፡ ከነጭፍራው ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ጌዴዎን ፡ የተባለው ፡ የፈላሾቹ ፡ አዝማቾች ፡ ከየተራራዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ቍልቍል ፡ ካሉት ፡ ከንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፤ ለውጊያ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተሰላለፉ ፡ ጌዴዎንም ፡ ከታች ፡ ዙሪያውን ፡ የተራራው ፡ ሥር ፡ ሁሉ ፡ በንጉሡ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መከበቡን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ለጭፍሮቹ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ። «ወገኖቼ ፡ ሆይ ፡ ስሙኝ ፤ ጦር ፤ ሰይፍ ፤ ጠመንዣ ፡ በያዙ ፡ ወታደሮች ፡ ዙሪያችን ፡ ሁሉ ፡ ተከቧል ። አሁን ፡ ተማርከን ፡ ለክርስቲያኖቹ ፡ ባሮች ፡ ከምንሆን ፡ ለኛ ፡ መሞት ፡ ይሻለናል ። የሮማው ፡ የቬስባስኖስ ፡ ቄሣር ፡ ልጅ ፡ ጢጦስ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በጦርነት ፡ ከቦ ፡ ባስጨነቀ ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችን ፡ እስራኤሎች ፡ «በእፍረት ፡ ከመኖር ፡ በክብር ፡ መሞት ፡ ይሻላል ፡ ያሉትን ፡ አልሰማችሁምን ፡ »አላቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፈላሾቹ ፡ ሁሉ ፡ በንግግሩ ፡ ተቀስቅሰው ፡ ግማሾቹ ፡ በዚሁ ፡ በጌዴዎን ፤ የቀሩትም ፡ በጕሼን ፡ አዝማችነት ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉ ። ጕሼንም ፡ በበኩሉ ፡ ተማርኬ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ከምቀርብ ፡ መሞትን ፡ እመርጣለሁ ፡ ሲል ፡ ቈረጠ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዋናው ፡ ጦርነት ፡ ተዠመረና ፡ ከንጉሡ ፡ የተላኩትም ፡ ወታደሮች ፡ እየተራራው ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ ሽቅብ ፡ እየተኰሱ ፡ በጠመንዣ ፡ ሲገድሏቸው እነሱም ፡ ከላይ ፡ ቍልቍል ፡ የናዳ ፡ ድንጋይ ፡ እየሰደዱ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ገደሉ ። በዚህም ፡ ዐይነት ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ተራራ ፡ መውጣት ፡ ችግር ፡ ሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው ፡ ሄደው ፡ በተራራው ፡ ሥር ፡ በሚመች ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ከቱርኮች ፡ የተማረከውን ፡ መድፍ ፡ አስጠመዱና ፡ ሽቅብ ፡ አስተኰሰው ፡ ከፈላሾቹ ፡ መካከል ፡ ሰው ፡ ተመቶ ፡ ሲወድቅ ፡ ፈላሾቹ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ መሆኑን ፡ አላወቁም ፡ ነበርና ። መብረቅ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ የመታቸው ፡ ስለመሰላቸው ፡ ደንግ

ጠው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይበረሩ ፡ ዠመር ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደፋር ፡ የሆነው ፡ የንጉሡ ፡ ወታደር ፡ እየሮጠ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፤ የተመቸው ፡ በእግሩ ፤ ያልተመቸው ፡ በገመድ ፡ ብልኀት ፡ እየተንጠለጠለ ፡ ወጣና ፡ ገሚሶቹን ፡ በጦር፡ እየወጋ ፤ ገሚሶቹን ፡ በጠመንዠ ፡ እየተኰሰ ፡ ገደላቸው ። ፈላሾቹም ፡ በገዠግንነት ፡ ተዋግተው ፡ መሸነፋቸውን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፤ አንዳንዶቹ ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ገደል ፡ እየገቡ ፡ አለቁ ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ አዝማች ፡ ጕሼን ፡ ከብዙ ፡ ሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ አልማረክም ፡ ሲል ፡ በፈቃዱ ፡ ገደል ፡ ተወርውሮ ፡ ሬሳውታች ፡ በለን ፡ እተባለው ። እንጉሡ ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ ሡፈር ፡ ወድቆ ተገኘ ። በለንም ፡ የጕሼንን ፡ ራስ ፡ አስቆርጦ ፡ ስለ ፡ ደስታ ፡ ለንጉሡ ፡ ላከላቸው ፡ ጌዴዎን ፡ ግን ፡ አመለጠ ፡ ይባላል ።

ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀድሞ ፡ እነኢያሱ ፡ እነሳኦል ፡ በሞዓባውያንና ፡ በአማሌቃውያን ፡ ላይ ፡ በዘመቱ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ ትልቁንም ፡ ትሹንም ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ከብቱንም ፡ ጨርሱ ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ ነፍስ ፡ አታስቀሩ ፡ ብሎ ፡ በነቢይ ፡ በሳሙኤል ፡ አፍ ፡ አዞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ እንደዚሁ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስማቸው ፡ የተጠራው ፡ አባ ፡ ነዋይ ፡ የሚባሉት ፡ መነኵሴ ፡ በዚህ ፡ ጦርነትና ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ፈላሾች ፡ ወንድም ፡ ሴትም ፡ ትልቅም ፡ ትንሽም ፡ የሚጠባም ፡ ልጅ ፡ ከብቱንም ፡ ሁሉ ፡ ሳትገድሉ ፡ እንዳትተዉ ፡ ብለው ፡ ገዝተዋል ፡ እየተባለ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አለቀ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መነኵሴው ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ በግዝት ፡ ቢያዙ ፡ ቀድም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሳኦል ፡ ሳይፈጽም ፡ እንደ ፡ ቀረ ፡ እንደዚሁም ፡ ወታደሮቹ ፡ በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ ምርኮኛ ፡ ፈጽመው ፡ አላጠፉም ፡ ነበርና ፤ ከማራኪዎቹ ፡ አንዱ ፡ ወታደር ፡ የማረካትን ፡ የፈላሻ ፡ ሴት ፡ በእጁ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ በገደሉ ፡ አፋፍ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሲያልፍ ፡ ሴትዮዋ ፡ ሶምሶን ፡ ነፍስየ ፡ ትሙት ፡ ምስለ ፡ ኢሎፍላውያን ፡ «ነፍሴ ፡ ከኢሎፍላውያን ፡ ጋራ ፡ ትውጣ» ፡ እንዳለ ፡ እርሷም ፡ ነፍሴ ፡ አብራ ፡ ትውጣ ፡ ብላ ፡ ወደታች ፡ ጕትታው ፡ ከወታደሩ ፡ ጋራ ፡ ገደል ፡ ገብተው ፡ ሞቱ ፡ ይባላል ። ከሴትም ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ያለች ፡ ደፋር ፡ መገኘቷ ፡ ያስደንቃል ፤ የፈላሾቹ ፡ ጦርነት ፡ በዚህ ፡ ተፈጸመ ።

፨ ፨ ፨

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ የፈላሾችን ፡ ሽፍትነት ፡ ደምስሰው ፡ ተመልሰው ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከረፉ ፡ በኋላ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሄደውበት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ እናሪያ ፡ ወደሚባለው ፡ አገር ፡ ፪ኛ ፡ ለመሄድ ፡ ዝጅግት ፡ ተደረገና ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ፤ ከጐንደርም ፡ በጐጃም ፡ በኩል ፡ አልፈው ፡ በወለጋና ፡ በሊሙ ፡ በጅማ ፡ በከምባታ ፡ እየተበታተኑ ፡ ባንዳንድ ፡ ስፍራ ፡ የሸፈተውንና ፡ አገር ፡ የሚዘርፈውን ፡ ወስላታ ፡ ወታደር ፡ እየላኩ ፡ ከቀጡ ፡ በኋላ ፡ እናሪያ ፡ ገቡ ፡

ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ባለፈው ፡ ጕዟቸው ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ የተቀበላቸው ፡ ሴቤንሂ ፡ የሚባለው ፡ ባላባት ፡ ሞቶ ፡ ልጁ ፡ ባንደኛ ፡ ባላ

ባትንቱን ፡ ይዞ ፡ ነበርና ፡ እርሱም ፡ እንዳበቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካሉት ፡ ሹማምቶች ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሠንጋና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ ተገናኛቸው ። ንጉሡም ፡ በሉበት ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩና ፡ ባላገሩ ፡ በፍቅር ፡ ይተዳደር ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በዘረፋም ፡ በምንም ፡ አልተቀያየሙም ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ፈቃደኞች ፡ መሆናቸውን ፡ ተመልክተው ፡ ባገሩ ፡ ንጉሡን ፡ ተከትለው ፡ ሄደው ፡ የነበሩት ፡ ቀሳውስት ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ለባንደኞና ፡ ለሹማምንቱ ፡ ቢሰብኩላቸው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ተቀበሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ለባንደኞ ፤ የቀሩትም ፡ መኳንንት ፡ ለቀሩት ፡ ባላባቶች ፡ የክርስትና ፡ አባት ፡ ሆነው ፡ ክርስትና ፡ አነሡዋቸውና ፡ ሁሉም ፡ ተጠምቀው ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሆኑ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነ ። ባላባቱም ፡ ባንደኞ ፡ ስሙ ፡ ተለውጦ ፡ በሚቼ ፡ በንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ የክርስትና ፡ ስሙ ፡ ዘማርያም ፡ ተባለ ፤ የወርቅ ፡ መስቀልም ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸው ፡ ባንገቱ ፡ አሠሩለት ።

እንደዚሁም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ሊያስታርቁ ፡ የነበሩት ፡ እቴ ፡ ወለቴ ፡ የሚባሉት ፡ የንጉሡ ፡ አክስት ፡ ለባንደኞ ፡ ሚስት ፡ የክርስትና ፡ እናት ፡ ሆነው ፡ አስጠመቋት ። የቀረውንም ፡ ሕዝብ ፡ ለማጥመቅ ፡ ቄሶቹ ፡ አልበቃ ፡ ስላሉት ፡ ሕዝቡ ፡ ራሱ ፡ እወንዝ ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ተጠመቀ ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልም ፡ በዚሁ ፡ ሰሞን ፡ ትልቅ ፡ ግብር ፡ አድርገው ፡ ለባላባቶቹ ፡ እግብር ፡ ላይ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሽልማት ፡ ሲሰጡ ፡ ሰነበቱ ። ያመት ፡ ግብርም ፡ ሌላው ፡ አገር ፡ ከሚገብረው ፡ ገሚስ ፡ እንዲገብሩ ፡ አደረጉላቸው ። እንደዚሁም ፡ የቦሶ ፡ ባላባት ፡ ክርስትና ፡ ተቀብሎ ፡ ንጉሡ ፡ አነሡትና ፡ ስሙም ፡ በተነሣበት ፡ ቀን ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተባለ ፡ ከዚህ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ብዙ ፡ ቀሳውስት ፡ ትተው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዲሠራላቸው ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተው ፡ ወደ ፡ በጌምድር ፡ ተመለሱ ። በኋላም ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠራላቸው ።

፨ ፨ ፨

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ በደባሩአና ፡ በሐማሴን ፡ ወልደ ፡ ኤሱም ፡ የሚባለው ፡ የባሕር ፡ ነጋሽነትን ፡ ማዕርግ ፡ ከቱርኮች ፡ ተቀብሎ ፡ የንጉሡን ፡ ሹማምንቶች ፡ አውኮ ፡ ነበር ። እርሱንም ፡ በትግሬ ፡ ከንጉሡ ፡ የተሾመው ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ዳህራቆት ፡ የተባለው ፡ ለመውጋት ፡ ያባረረው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወልደ ፡ ኤሱም ፡ በዚያው ፡ በኤርትራ ፡ ካሉት ፡ ቱርኮች ፡ ጋራ ፡ ተስማምቶ ፡ አስቸገረ ። እንዲያውም ፡ ከቱርኮቹ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ከንጉሡ ፡ ሹማምንቶች ፡ ጋራ ፡ ተዋግቶ ፡ አሸንፎ ፡ ነበርና ፤ ንጉሡ ፡ ከእናሪያ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ መልክት ፡ ከትግሬ ፡ ደረሳቸው ። «ቱርኮች ፡ ከምሽጋ

ቸው ፡ ከአርኪቆ ፡ (ከደሆኖ) ፡ ወጥተው ፡ ደባሩአን ፡ ያዙ ። ከዚያም ፡ አልፊው ፡ ካዝማች ፡ ዳህራቄት ፤ ከሐማሴን ፡ ከንቲባ ፤ ከአቃጸን ፡ ሠራዊ ፡ ጋራ ፡ ጦርነት፡ አድርገው ፡ ቱርኮች ፡ አሸነፉ ፡ በጦርነቱም ፡ መኳንንትና ፡ ወታደር ፡ አለቀ» ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ከተት ፡ ሠራዊት ፡ ብለው ፡ የጨዋ ፤ የቊርባን ፤ የበለሚል ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰበሰብ፤ ሳይሰበሰብ ፡ የቀረ ፡ ቤቱና ፡ ንብረቱ ፡ ይወረሳል ፡ ሲሉ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ። በዐዋጁ ፡ መሠረት ፡ ሠራዊቱ ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሽሬ ፡ ሄዱ ። ለግንባር ፡ ቀደሙም ፡ ጦር ፡ የበላይ ፡ አዛዥ ፡ የአኵስሙን ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ቶማስን ፡ አደረጓቸው ፤ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ወሰኖ ፡ መሐመድ ፡ (የክርስትና ፡ ስሙ ፡ ወልደ ፡ ክርስቶስ) ፡ የሚባለው ፡ በውስጡ ፡ የሚታዘዘውን ፡ የጋላ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ አብሮ ፡ እንዲዘምት ፡ አደረጉ ። ቱርኮችም ፡ እስከ ፡ መረብ ፡ ድረስ ፡ መጥተው፡ ነበርና ፤ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፡ የማይችሉ ፡ ሆነው ፡ በቀድሞው ፡ ጦርነት ፡ የማረኩትን ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ሲመለሱ ፡ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ የሚባለው ፡ ወጣት፡ ከጥቂቶች ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ በጫካ ፡ ደፍጦ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጨረሰባቸው ፤ የማረኩትንም ፡ አስመለሳቸው ። ንጉሡም ፡ በዚሁ ፡ ሥራው ፡ ደስ ፡ ስለ ፡ ተሰኙ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ብለው ፡ ሾሙት ። በራስ ፡ ላይ ፡ የሚደረግም ፡ ወርቅ ፡ (ራስ ፡ ወርቅ?)፡ ከሽልማት ፡ ጋራ ፡ ላኩለት ።

፨ ፨ ፨

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግልም ፡ ቱርኮች ፡ ከኤርትራ ፡ ግዛት ፡ ካልጠፉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰላም ፡ አለማግኘቷን ፡ ተረድተው ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ በሺ፡ሕ፡ ፭፻፹፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሄደው ፡ ተዋጉዋቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከወዲህ ፡ ንጉሡ ፡ እየብሱ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ከወዲያ ፡ ቱርኮቹ ፡ እባሕሩ ፡ ላይ ፡ እመርከብ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ በሩቅ ፡ እየተያዩ ፡ ይታኰሱ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በየብስም ፡ የነበሩትን ፡ ቱርኮች ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ከማረኳቸው ፡ በኋላ ፡ እጅና ፡ እግራቸውን ፡ ቈረጧቸው ። አዛዦቻቸውም ፡ ቄስሎ፡ ነበር ።ነገር ፡ ግን ፡ አልተማረከም ።

ንጉሡም ፡ አስቀድመው ፡ እንደ ፡ መደቡት ፡ አሳባቸው ፡ ቱርኮችን ፡ በፍጹም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ለማጥፋት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቱርኮቹ ፡ ከወዲህ ፡ ሲሸነፉ ፡ በአርኪቆ ፡ ምሽግ ፡ እየገቡ ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ፤ ከዚያም ፡ ሲሸነፉ ፡ በመርከብና ፡ በጀልባ ፡ እየሸሹ ፡ ከአርኪቆ ፡ ባሻገር ፡ ወዳለው ፡ ዳህላቅ ፡ ወደሚባለው ፡ ደሴት ፡ እየገቡ ፡ አስቸገሩ ።

የኢትዮጵያም ፡ ወታደር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጠረፉ ፡ ሆኖ ፡ እንዳይጠባበቅ ፡ አገሩ ፡ እህል ፡ የማያበቅል ፡ በረሐ ፡ በመሆኑ ፤ ከለምለሙ ፡ አገር ፡ ሥንቅ ፡ እንዳይመጣለት ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ የማመላለሺያ ፡ ብልኀት ፡ ስላልነበረ ፡ የታሰበው፡ እፍጻሜ ፡ ለመድረስ ፡ አልቻለም ። እንኳን ፡ እዚያው ፡ እጠረፍ ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ፡ ለመቀመጥ ፡ በዚሁ ፡ ሰሞን ፡ እንኳን ፡ ወታደሩ ፡ ሥንቁ ፡ አልቆበት ፡ ከጠረፉ ፡

ሲመለስ ፡ በጣም ፡ ተርቦ ፡ ነበርና ፤ የባላገሩን ፡ እህልና ፡ ከብት ፡ እየዘረፈ ፤
ይበላ ፡ ዠመር ። ባላገሩም ፡ ተሰብስቦ ፡ ለንጉሡ ፡ ቢያመለክት ፡ ንጉሡም ፡ ወታ
ደሩ ፡ የሰነበተበትን ፡ ችግር ፡ ገልጾው ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ነውና ፡ ችላ ፡
በሉት ፡ ያውስ ፡ ቢሆን ፡ ጠላቶቻችሁ ፡ ቱርኮች ፡ ከሚዘርፏችሁ ፡ ወንድሞቻችሁ ፡
ቢዘርፏችሁ ፡ አይሻልምን ፡ አሏቸው ፤ እነሱም ፡ ይኸንን ፡ ንግግር ፡ ከንጉሡ ፡
በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ ተገንዝበው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ተመለሱ ፡ ይባላል ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ቱርኮችን ፡ ከጠረፍ ፡ ካባረሩ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡
ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ይስሐቅ ፡ የከዳውና ፡ ከቱርኮች ፡ ወገን ፡ የባሕር ፡ ነጋሽነትን ፡
ማዕርግ ፡ ያገኘው ፡ ይኸው ፡ ወልደ ፡ (ወደ) ፡ ኤሱም ፡ መዠመሪያ ፡ አልሸፈትሁ
ምና ፡ ታርቄ ፡ እንድገባ ፡ ምሕረት ፡ ያድርጉልኝ ፡ ብሎ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ገጸ ፡
በረከት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሠራዊቱም ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ለከብቱም ፡ ሣርና ፡ እህል ፡
ልኮ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ሲመቸው ፡ አዘንግቶ ፡ ከሰፈሩ ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ፡
ማምለጡንም ፡ ንጉሡ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተናደዱ ። አላይ ፡ ስሙ ፡ የተጠራው ፡
ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ ነበረና ፤ እኔ ፡ አባርሬ ፡
እወጋዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ጭፍራ ፡ አስከትሎ ፡ ወልደ ፡ ኤሱምን ፡ ለማባረር ፡ ሄደ ፡
የሐማሴን ፡ ገዥ ፡ ከንቲባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስም ፡ አብሮ ፡ ከዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡
ተጨምሮ ፡ ሄደ ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ ሲያባርር ፡ ወልደ ፡ ኤሱም ፡
ሲበር ፡ በመጨረሻ ፡ አባራሪው ፡ እንደ ፡ ደረሰበት ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወልደ ፡
ኤሱም ፡ ሽሽቱን ፡ ትቶ ፡ ጋሻና ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ከዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡
ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ተደባደቡ ፡ በመጨረሻም ፡ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ ወልደ ፡ ኤሱ
ምን ፡ አሸንፎ ፡ ገደለው ፤ ከገደለውም ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ቆረጠው ። የዚህንም ፡
ደስታ ፡ ለንጉሡ ፡ መልክተኛና ፡ ደብዳቤ ፡ አስቀድሞ ፡ በኋላም ፡ ራሱ ፡ የተ
ቆረጠውን ፡ ጭንቅላት ፡ አሲዞ ፡ በወታደሩ ፡ ታጅቦ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሄደ ።
በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ነጋሪትና ፡ መለከት ፡ እያስነፉ ፡ በክብር ፡ ተቀበሉት ።
ንጉሡም ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ ዕቁበ ፡ ሚካኤል ፡ በሥጋ ፡ ባልወለደውም ፡ የመን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጄ ፡ ነውና ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ (ባሕር ፡ ነጋሽ) ፡ መባሉ ፡
ቀርቶ ፡ (ወልደ ፡ ንጉሥ) ፡ በሉት ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ፤ የወርቅ ፡ ሽልማትም ፡
(ኒሻንን) ፡ በአንገቱ ፡ አጠለቁለት ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ መላው ፡ ሐማሴንና ፡
ጠረፉ ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እጅ ፡ ሆነ ። ቢሆንም ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡
እስከ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ምስፍንና ፡ ድረስ ፡ የምጥዋ ፡ ጠረፍ ፡ ነገሥታቱ ፡ ሲበረቱ ፡
በነገሥታቱ ፡ እጅ ፡ የነገሥታቱ ፡ ኀይል ፡ ሲቀነስ ፡ በቱርኮች ፡ እጅ ፡ እየገባ ፡ ቈየ ።

ምናልባት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ የሚመራው ፡ መንግሥት ፡
ከዚህ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ መርከብ ፡ በማጣት ፡ እንኳን ፡ ባሕሩን ፡ ተሻግሮ ፡ ከዳህላቅ ፡
ደሴት ፡ ቱርኮችን ፡ ለማባረር ፡ ባይችል ፡ ደባሩአና ፡ ምጥዋ ፡ አርኪቆም ፡ ላይ ፡ ነዋሪ ፡
ሠራዊት ፡ አስቀምጦ ፡ የባሕሩን ፡ ዳር ፡ ዳር ፤ በጥብቅ ፡ ቢያስጠብቅ ፡ ኑሮ ፡ ቱርኮች ፡
በደሴቱ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በመቀመጥ ፡ ጥቅም ፡ አያገኙም ፡ ነበርና ፡ በናጹም ፡ ምጥ

ዋን ፡ መልሰው ፡ ለመያዝ ፡ መቸገራቸው ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ እነ ሱና ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ግብጾች ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኢጣሊያ ፡ መግባት ፡ ድረስ ፡ መቈየት ፡ እንዲሁም ፡ ኢጣሊያ ፡ በእንግሊዝ ፡ ረዳትነት ፡ ከቱርኮችና ፡ ከግብጾች ፡ ወስዶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውጋት ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን፡ በንድ ፡ ወገን ፡ ይህ ፡ በየጊዜው ፡ የምንመለከተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀሰቀሰው ፡ ውስጣዊ ፡ ጦርነት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ቀጥለው ፡ የነገሡት ፡ እነያዕቆብ ፡ እነዘድንግል ፡ ከሥርፀ ፡ ድንግል ፡ ደካማ ፡ ሆነው ፡ መገኘታቸው ፡ በሌላው፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ዓለምን ፡ ያስቸገረውን ፡ የቱርክን ፡ መንግሥት ፡ የዚያን ፡ ጊዜውን፡ ኀይል ፡ አጥብቆ ፡ መቃወም ፡ ስለሚያዳግት ፡ በምጥዋና ፡ በአርኪቆም ፡ ነዋሪ ፡ ወታደር ፡ ለማስቀመጥ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ የዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኑሮና፡ የምግቡም ፡ ነገር ፡ ስለሚያስቸግር ፡ እላይ ፡ የተመኘነው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ለዚያ፡ ጊዜ ፡ ማስቸገሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፴፩ ።

### ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ በዘመናቸው ፡ ስለ ፡ ሠሩትና ፡ ስለ ፡ ዕረፍታቸው ።

ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ፴፩ ፡ ዓመት ፡ በሚሆነው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምጥዋና ፡ ወደ ፡ ደባሩአ ፡ ጠረፍ ፡ ሄደው ፡ ከቱርኮች ፡ እየተዋጉ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጠረፍ ፡ ግዛት ፡ ለማስፋፋት ፤ ሁለት ፡ ጊዜም፡ ወደ ፡ እናሪያ ፡ ተጉዘው ፡ በግራኝ ፡ ጊዜ ፡ የተከፋፈለው ፡ አገር ፡ ከመንግሥቱ ፡ እንዲተባበር ፡ በዚህም ፡ አገርና ፡ በዙሪያው ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲዘረጋ ፡ በመጣር ፡ የቀረውም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ተባብሮ ፡ እንዲተዳደር ፡ በጦርነትም ፡ በዘዴም ፡ ከላስቶችም ፡ ከፈላሾችም ፡ ከጋፋቶችም ፡ ከጋሎችም ፡ ከሐረርጌ ፡ ወላስሞችም ፡ ጋራ ፡ ያደረጉትን ፡ ትግል ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ተመልክተናል ። ይልቁንም ፡ የቱርክን ፡ ግዛት ፡ በጊዜያቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ ማጥፋታቸው ፡ በቀላል ፡ የሚገመት ፡ አይደለም ።

በዘመናቸውም ፡ ከቀደሞ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትና ፡ መዝሙረ ፡ ክርስቶስ ፤ መጽሐፈ ፡ ጠቢባን ፤ የዮሐንስ ፡ መደብር ? ፤ የኒቅያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መጽሐፍ ፡ በግዕዝ ፡ ተጻፈ ። በዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ጊዜ ፡ የተዠመረውም ፡ የድጓ ፡ ምልክት ፡ በርሳቸው ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ፡ ይባላል ። ኢትዮጵያም ፡ ኀይለኛ ፡ መንግሥት ፡ እንድትሆን ፡ ሕዝቡም ፡ በእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ እንዲሠለጥን ፡ የጠመንዣና ፡ የመድፍ ፡ የብረታ ፡ ብረት ፡ ሥራ ፡ የሚያስተምርልኝ ፡ ይላኩልኝ ፡ ብለው ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ውድቀት ፡ በኋላ ፡ ለተነሣው ፡ ለኤስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ ለፊልጶስ ፪ኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ልከው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አሳባቸውን ፡ ሳይፈጽሙት ፡ ሞት ፡ ቀደማቸው ። የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ «ተዋጊም ፡ የዲፕሎማቲክም ፡ ሰው ፡ ነው» ፡ እያሉ ፡ ጽፈውላቸዋል ።

ያገራችንም ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በበኩሉ ፡ በአምላኩ እንጂ ፡ በኀይሉና ፡ በዕውቀቱ ፡ የማይመካ ፡ ምግባርና ፡ ሃይማኖትን ፡ አዘውታሪ ፡ ጻድቅ ፡ ሲያደርጋቸው ፡ ደግሞ ፡ በጕብዝና ፡ ረገድ ፡ ጀግንነታቸውን ፡ ድፍረታቸውን ፡ እያጋነነ ፡ ይጽፍላቸዋል ። ቢሆንም ፡ ዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ እንደ ፡ ሹመት ፡ አባቶቻቸው ፡ እንደነ ፡ ዐፄ ፡ ካሌብ ፤ እንደነ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ በጦርነትም ፡ በዘዴም ፡ በበጎ ፡ ተግባርም ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ በሰው ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ የሚታየው ፡ ጉድለትና ፡ ኀጢአት ፡ በርሳቸውም ፡ ላይ ፡ በፍጹም ፡ አይታይም ፡ ብሎ ፡ በደፈናው ፡ ሥጋ ፡ የለበሰውን ፡ ሰው ፡ ማመስገንና ፡ ማድነቅ ፡ የፍጡርን ፡ ባሕርይ ፡ በፍጹም ፡ እንዳለማወቅ ፡ ይቈጠራል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ፴፬ ፡ ዓመት ኢትዮጵያን ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ ከእናሪያ ፡ መልስ ፡ በዳሞት ፡ የሸፈቱትን ፡ ጋሎች ፡ ሲያበርሩ ፡ ከዘጌ ፡ ባሕር ፡ (እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ ከግቤ ፡ ወንዝ) ፡ መነኰሳት አይብሉ ፡ ያስፈራዎታል ፡ ብለው ፡ የመከሯቸውን ፡ ዓሣ ፡ ስለ ፡ በሉ ፡ በዚሁ ፡ የተቅማጥ ፡ በሽታ ፡ አድሮባቸው ፡ እንሰስሊት ፡ ከሚባለው ፡ የውሃ ፡ ዳር ፡ ታመሙ ፤ ሕመማቸውም ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ሸት ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ወሰዷቸውና ፡ በዚያው ፡ ሳሉ ፡ ሕመማቸው ፡ በረታና ፡ በተወለዱ ፡ በ፵፯ ፡ ዓመታቸው ፡ ከሺሕ ፡ ፭፻ ፡ ፶፭ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ፭፻፹፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገዝተው ፡ ሞቱ ። በሞቱም ፡ ጊዜ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ራማ ፡ ደሴት ፡ ወስደው ፡ በኀዘንና ፡ በለቅሶ ፡ ቀበሯቸው ። እርሳቸውም ፡ ከባለቤታቸው ፡ ከእቴጌ ፡ ማርያም ፡ ሥና ፡ ዓመት ፡ ሚካኤል ፤ ቀሱሳዊት ፡ ወለተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚባሉ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሯቸው ፤ ከሌሎች ፡ ቊባቶቻቸው ፡ ደግሞ ፡ ሚቼ ፡ ዘማርያምን ፤ ያዕቆብን ፡ ወልደዋል ።

የዐፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ታሪክ ፡ በብራና ፡ በወረቀት ፤ በማርኛ ፤ በግዕዝ ፡ ሞላ ፡ ከጐደል ፡ እነወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ ሌሎችም ፡ የጻፉት ፡ በጐንደር ፡ በሌላውም ፡ አውራጃ ፡ በየአድባራቱና ፡ በየገዳማቱ ፡ የተቀመጠውን ፡ እነአርኖ ፡ ዳባዲ ፡ እነማሬዉስ ፡ ሳይነአኖ ፡ እነፒ ፡ ፓኤዝ ፡ በፍራንክ ፡ ፎር ፡ (ጀርመን) ፡ በኦክስፎርድ ፡ (እንግሊዝ) ፡ አገር ፡ አስቀምጠውታል ፤ ከዚያም ፡ ግዕዙን ፡ ራሱን ፡ ያሳተሙ ፡ ወይም ፡ በቋንቋቸው ፡ እያስፋፉ ፡ የጻፉ ፡ አሉ ። ከዚሁ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ከየክፍሉ ፡ አጠራቅመው ፡ ከቀጥተኛው ፡ ከወልደ ፡ ሃይማኖት ፡ ከብራናው ፡ ጽሑፍ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የሚባሉት ፡ የኢጣሊያ ፡ ሊቅ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተርጕመው ፡ Hls-Toria Regis Sarsa Dengel (Malak Segab) በሚል ፡ አርእስት ፡ ከኢኖሲዮ ፡ ጉይዲ የጋላ ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ በማተሚያ ፡ አሳትመው አውጥተውታል ።